# አርምሞ

መጽሐፈ ዘ ዝምታ
ጽሞና ወ ተፈኹር


...ውስጣዊ ጉዞ



6ተኛ
ዕትም

ዶ/ር ኤልያስ ገብሩ አዕምሮ

፳፻፲፬ ዓ.ም አዲስ አበባ፦ ኢትዮጵያ




*join us on telegram*
*@ETHIO_PDF_BOOKS*

# ...እርምጃ

## ውስጣዊው ጉዞ...



|ጥናታዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ፣ መንፈሳዊ፣ ጥበባዊ ረጅም የፍቅር ልቦለድ|

ከዶ/ር ኤልያስ ገብሩ አእምሮ

2014 ዓ.ም

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።
ዶ/ር ኤልያስ ገብሩ አዕምሮ፤
Elation© 2021/ All Rights Reserved!

የመጀመሪያ ዕትም: መስከረም 2014 ዓ.ም
ሁለተኛ ዕትም: መስከረም 2014 ዓ.ም
ሦስተኛ ዕትም: ጥቅምት 2014 ዓ.ም
አራተኛ ዕትም: ታህሳስ 2014 ዓ.ም
አምስተኛ ዕትም: ጥር 2014 ዓ.ም
ስድስተኛ ዕትም: የካቲት 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ፤

**አሳታሚና አከፋፋይ**

አብርሆት ለኢትዮጵያ አሳታሚ
እ-ጦማር ("ኢሜይል"):- danieltefe2000@gmail.com
አድራሻ:- አ.አ፣ ፓኖሮማ ሆቴል ጎን
ስ.ቁ:- ፱፷፮-፮-፯-፰ / 0966-06-07-08

በዚህም ሆነ በቀደሙት:-ኤቶዮጵ፣ አንድ ሀገር/ቢያ ቶኮ፣ ኮሜንትና Pursuit of Unity in Time of Separation መጽሐፎች ላይ አስተያየትና ጥያቄ ካላችሁ|

**የደራሲው አድራሻ**

- 0913714275
- Elationunifire@gmail.com
- Elias Gebru Aimero
- Elation Unifire
- ፖስታ- (ኤልያስ ገብሩ አዕምሮ - 24741
- አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ)

"አፍቅራ ለአርምሞ ፈድፋደ እምአጽግቦቶሙ ለርሑባነ ዓለም፤ ወመይጦቶሙ ለብዙኃን እምነ አሕዛብ፤"

"የተራቡ ዓለማዊ ሰዎችን ከማጥገብና ከአሕዛብ ወገን ብዙዎቹን ከመመለስ ይልቅ አርምሞን በእጅጉ ውደዳት።"

***(መጽሐፈ መነኮሳት ቀዳማይ)***

"...የዝምታን ድምጽ ሰማሁኝ"

***(መጽሐፈ ኢዮብ 4፤ 16)***

". . .ዝም ያለ ሰው ይድናል።"

***(ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ)***

***(ቲርሚዚ 2501)***

"በዓለም ላይ ካሉ ሙዚቃዎች ሁሉ ጥዑም የሆነው ዝምታ ነው። ... ዝምታም በመልሶች የተሞላ እንጂ ባዶ... ኦና አይደለም።"

***(ጓተማ ቡድሐ)***

"የዝምታ፣ የብቸኝነትና የጨለማ ጉዳዮች የጨቅላነት ፍርሃቶቻችን ቅሪቶችን አዝለዋል። ብዙሃኑ የሰው ልጅ አሁንም ከመሰል ፍርሃቶቹ ነጻ አልወጣም።"

***(ሲግመንድ ፍሮይድ)***

ተመን የማይገኝለት ትልቁ ስጦታ ›››› መጽሐፍ

ከ______________________________

ለ______________________________

**መታሰቢያነቱ | በህይወታችን ውስጥ ለገጠሙን፣ በዝምታ ብዙ ላስተማሩን ሰዎች እና....**

**ለኤልያስ መልካ ይሁን፤**

# ምስጋና...

በትዕቢት ስንኖር ምህረቱ ገዝፎ በዝምታ በሚያልፈን፤ ስንዋሽ እንኳን ታግሶ እስትንፋሳችንን በሚያስቀጥለው፤ ስናጠፋ፣ ተጸጽተን ወደ እሱ እንድንመለስ ደጆቹን ከፍቶ፤ ሁሌ በጉጉት በሚጠብቀን... ታጋሽ፣ የፍቅር አምላክ ስም እቀድሳለሁ...

⌘

የመጽሐፉ ዝግጅት ላይ በአንድም በሌላ መልኩ ተሳትፎ ያደረጋችሁ ዶ/ር ብስራት ፍቅሬ፣ ዶ/ር ኤልያስ ተስፋዬ፣ ዶ/ር መ/ቢ ሮዳስ ታደሰ፣ ስምረት መኮነን፣ እሸቱ ብሩ (አትናቲዎስ)፣ ጉቺ ሽመልስ፣ ዶ/ር ገሊላ ዳንኤል፣ ዶ/ር ኪራ፣ ዳንኤል ተፈራ፣ ኢማኑኤል፣ ሰሊ፣ እንቁዮጳ፣ ሙሌ አሥራት(የሽፋን ገጽ አርቃቂ) ሌሎችም ከልቤ እልፍኝ በፈለቀ የጥሞና ዥረት ውስጥ ምስጋናዬ ወደ ነፍሳችሁ-ማህደር ይድረስልኝ፤

⌘

# መልዕክት ለውድ አንባቢያን

ስለ ዝምታና ስክነት ለመጻፍ የማይመከርበት ጊዜ ላይ ተገኘን፤ ምላስ ፈላጭ ቆራጭ የሆነችበት... የድምጾች ጊዜ፡ እልፍ ክፉ አንደበቶች በሚላውሱበት ዘመን ላይ፤ ብቸኝነትና ዝግታ እንደ ድክመት በሚቆጠርበት ጋርዮሽ ባህል ውስጥ ከተምን። ግና ዝምታን ይዘን አላንቀላፋንም። ተለዋዋጩ ጊዜ ወለድ እርግብግቢት ከዘላለማዊው እርጋታ አይበልጥምና ስለ ዝምታ፣ ብቸኝነት፣ ወሸባ፣ ስክነት፣ ጥሞና፣ ተመስጦ | ስለ አርምሞ ልንጽፍ ብዕራችንን መዘዝን፤ ዝምታ በተዘነጋበት የወከባ፣ የይድረስ ይድረስ፣ የቶሎ በል ቶሎ በይ፣ ቱማታ ዓለም ውስጥ ሆነን ወደ ውስጣታችን ተጓዝን፤ ጥልቁን ምሥጢር ጎትተን አውጥተን በልበለድ ሰሌዳ ላይ - አዘናጥፈን አነጠፍነው...

ዝምታ... ምንድነው? ተመስጦስ? አርምሞስ?... ሌላውን ከማወቅ፣ ከመጥላትም ሆነ ከመውደድ በፊት ራስን ማወቅ! - እልፉን ማንነት ማንቃት? ... እየጠበቡ ወደ ስፋት መጓዝ!

እነሆ ይህ መጽሐፍ ጥበብን ለሚሹ፣ የዘመናችን የጥላቻና ጸብ ውጥንቅጥ፣ የፉክክር ድሪቶ ለታከታቸው፣ ሰላማዊውን ውስጣዊ የራስ እውነት ለሚናፍቁ፤ በድምጾች ብዛት፣ በወረኞች መዓት ሐቁ ለተጋረደባቸው የዘመኔ አነፍናፊዎች፤ የሚሰክኑ ተመሳጮች... አርኪ መና ይሆን ዘንድ ተዘጋጀ። በጽሞና ይነበብ፣ ይመስኳ።

አብርሞት የሚለኩስ ንባብና ዝምታ እንደሚሆን እምነቴ ነው፤⌘

**ደራሲው**

# ማውጫ

**ምዕራፍ አንድ** ....................................................1
ነፍስ አለ-ማወቅ
**ምዕራፍ ሁለት** ....................................................16
እውን ነፃ ነን?
**ምዕራፍ ሦስት**....................................................36
ዝምታ
**ምዕራፍ አራት** ....................................................49
ጉዞ ወደ ኤረር ተራራ
**ምዕራፍ አምስት - 1** ....................................................71
የድሀ ፍቅር
**ምዕራፍ አምስት - 2**....................................................87
ታእማኒ ክህደት
**ምዕራፍ ስድስት** .................................................... 103
ፈረንጇ ባላገር
**ምዕራፍ ሰባት** .................................................... 120
ሱባኤ ወ ተፈኩር
**ምዕራፍ ስምንት** .................................................... 138
ዮጋ: ዮድ: ዋልያ
**ምዕራፍ ዘጠኝ**.................................................... 161
ውስጣዊው ጉዞ
**ምዕራፍ አሥር** .................................................... 185
አርምሞ
**ምዕራፍ አስራ አንድ** .................................................... 213
ያልተገለጠው ግዙፍ
**ምዕራፍ አስራ ሁለት** .................................................... 239
መርዕድ
**ዋቢ መጽሐፍት**.................................................... 250

# ምዕራፍ አንድ

# ነፍስ አለ-ማወቅ

Ω

## ሰኞ ምሽት - ግንቦት 2007 ዓ.ም

ከኋላው ፡ በቅርብ ርቀት… የማረሚያ-ቤት ጠባቂዎች ኮቴ ይሰማዋል። ፍጥን ብሎ የእሥር-ቤት ልብሱን እጅጌ በኃይል ተረተረ፤ በእራፊውም የቆሰለ ግራ ባቱን በችኮላ ሸብ አደረገው። ደሙ ከቁስሉ እንደ እዥ ይንዠረራል። ያቺን፡ የወጋቸውን አንዲት ሚስማር ወቀሳት ፡ መጥፎ ናት። ያን የሚያኽል አጥር ዘሎ ያቺ አንዲት ሚስማር እንዴት አገኘችው? ሹል ብረት እቅዱን ልታኮላሽበት? - አምርሮ ረገማት!

አነፍናፊ ውሻዎች በክፉ አፍንጫቸው ከባቱ የተንጠባጠበ ደሙን፣ ላቦቱንና ‹አድሬናሊኑን[1]› እያሸተቱ እየተከተሉት ነው። በማንኛውም ሰከንድ ሊደርሱበት ይችላሉ። …ጊዜ ሳይፈጅ አፈፍ ብሎ ተነስቶ ሽሽቱን ቀጠለ። ጫካውን እያሳበረ፣ በማያውቀው መንገድ ተሳበ። ቁስሉ በጽኑ እየጠረቆሰው ቢሆንም ህመሙን ለማዳመጥ ግን ፋታ አላገኘም። ከኋላው የሚከተሉት ጠባቂዎች የእጅ ባትሪ በዛፎች መሃል ተሽሎክልኮ ከሚያደርሰው ብርሃንና ከሰባራ ሰሃን መሳይዋ ጨረቃ ነጸብራቅ በስተቀር ምንም ምልክትም አልነበረውም። የደመ ነፍስ ሩጫ ላይ ነበር። /የነሲብ ሽምጠጣ ፡ የጨፍን ጉዞ … ወዴት? … የረጅም ጊዜ እቅዱን ለማሳካት ከዳር በደረሰበት አስራ አንደኛዋ ሰዓት፡ ልፋቱ ሊከሽፍም ከጫፍ ደርሷል።

⌘ ⌘ ⌘

---

1 የውሻ አፍንጫ እጅግ ኃያል የማሽተት ችሎታ ስላለው ሰውነታችን ውስጥ ያለው የአድሬናሊን ሆርሞን መጠን ሲጨምር ማሽተት ይችላሉ። ስንፈራና ስንደነግጥ ያውቃሉ። ውሻ ስትፈራ ያውቃል የሚባለው እውነት ነው።

በማግስቱ-ፋና ኤፍኤም ራዲዮ የዕለቱ የጥዋት ዜና እንዲህ ብሎ ዘገበ!

"ከጥቂት ሰዓታት በፊት ሦስት እስረኞች ከቃሊቲ እሥር ቤት አምልጠዋል። አንዱ ብዙም ሳይርቅ በጠባቂዎች ጥይት ተመቷል። ካመለጡት የአንደኛው ማንነት ገና እየተጣራ ሲሆን አንደኛው ግን ለይኩን የተባለ የአስራ አምስት ዓመታት ጽኑ እሥረኛ እንደነበር ታውቋል። የማረሚያ ቤቱ የፖሊስ መሪ ያመለጡትን እስረኞች እግር በእግር እያሳደዷቸው እንደሆነ በተለይ ለፋና ገልጸዋል!"

⌘ ⌘ ⌘

## ____2020 እ.ኢ.አ/ ኮይሻ

መርዕድ ፡ ያ ያሳደገው ዶክተር የለገሰው የነፍስ ምክር ሁሌም ትዝ ይለዋል፡- "ልጅ መርዕድ፤ መናገር ተስኖኛል ብለኸ ታዝናለኸን? ለምን ውቡን የዝምታ ጥበብ አትቆርስም?...እንደ እንቁ የከበሩ፣ እንደ ወርቅ የነጠሩ ዘላለማዊ ዝማሬዎችን አታዳምጥም? ከማይረባ ቃል ውብ ዝምታ እጅጉን ይሻላል። በምስጣት[2] ውስጥ ያማረ ውስጣዊ የዜማ ኸርረትም በውጫዊ ጩኸት አይደፈርስም።

ስማኝማ!...ዝምታክ ፈጣኑ እርጋታ ነው። ዝምታ ዝ..ግ ነው፡ ካለትዕግስት የማይከፈት ምሥጢር፤ ዝምታ ዝ..ት ነው፡ አውቃለሁ የማይል ትሁት፡ ዝምታ ወርቅ ነው፡ ከልብ ተቆፍሮ የሚገኝ ውድ ሐብት፤ ዝንቱ ገንዘብ ነውና፤ አንተም በውዱ ዝምታ ውስጥ ተናገር።

ይህንንም ደግሞ እወቅ - ዝምታ ዝናን የማይሻ ነፍስ አለምላሚ ዝናብ ነው። አስተውል ፡ የቃል ተሲያቶች በልብህ የዝምታ ሰማይ ላይ በቀስታ፡ እያበሩ ያልፋሉ። በቁጥር ሲወሰኑ ያምራሉ፤ ከበዙ ግን ተንጠባረው ዓይንን ያንጠባርራሉ፤ ትርጉም ያጣሉ፡ አጉል የበራ ውበታቸው ይደበዝዛል።"... መርዕድ ለብቻው ፈገግ አለ።

ዛሬም ዝምታ አካባቢውን ሞልቶታል። የወፎቹ ፉጨትና የንፋስ ሽውታ ጬኸትን አልፈጠረም። የበሶቢላ፣ ና ና እና አሪቲ ብናኞች በንፋሱ ተሳፍረው፡እየተንሳፈፉ ሥርንን ያውዳሉ። ማነው አርቆ አሳቢ የተከላቸው? ሲል አሰበ፤ ባያውቀውም አመሰገነው። {እንደዚህ አይነት ቦታዎች አሉኮ!

2 ነገሩ በአእምሮ ተሰራጭቶ በመውጣት በመውረድ በዚያ ነገር አእምሮ ሲሰቀል፤

- ለዓይን ማራኪ፣ መንፈስን የሚያድሱ፣ አጥንት አለምልመው፡ ልብን የሚያሰክኑ... ይሄም እንዲያ ያለ ሰላም የሚሰጥ ቦታ ነበር። መሰል መናፈሻና ፓርኮች የሀገር ሳንባ፡ የከተሞች ውስጥ የሰላም ደብሮች ናቸውና በብዛት ሲኖሩ ደስስስ ይላል። እነዚሁ ስፍራዎች ሲበዙ ህዝብም ከውጥንቅጡ ገለል ብሎ፣ ከመልከ ብዙ መንጋው ተገንጥሎ፡ መናፈሻና መተንፈሻ ያገኛል... እያለ በሐሳብ ከራሱ ጋር ብዙ ተወያየ።)

ዛሬም መርዕድ ትንፍስ፣ እርፍ ብሏል። የሚሰማው ሰላም ከምንጊዜውም የላቀ ነው።|እሷም ዋነኛ ሰላሙ ናት፤ በታፋው ላይ ጋደም ብላ ፡ ተንጋላ፤ በስስት ዓይን የምታየው። የፀሐይቷን ወጨፎ በእርግብግቢቷ እየከላች የምትወደው፡ ጠልሰሟን የምትመሰጥበት፤ ለነፍሷ የምትጠራው ጥርኝ ናት።

እሱ/መርዕድ - ጥቁር ነው፤ እሷ/ቬራ - የቀይና የነጭ ድልህ ናት። በክፉ ቀኑ ያገኛት ፡ የጎን አጥንቱ፤ የወንዙ ልጅ ባትሆንም ውኃ አጣጩ ሆና የተገኘች ኢትዮ-ራሺያዊት፡ ክልስ ናት። ቃላት ሳያወጣ፣ ቃላት ሳታወጣ ተረዳድተዋል። ታዲያ ማናት ብላችሁ ብትጠይቁት በጎልቆ መሳፍርት ሲወራ የሰማሁትን፣ ሲተወን ያየሁን ፍቅር በገሃድ ያገኙሁባት እሷ ናት ይላችኋል። የውስጡን ጩኸት ለመመለስ ሲባዝን ከመልሱ ጋር ሌላ ስጦታው አድርጎ የላይኛው ነው የሰጠው ፤ አምላክ የልቡን አይቶ ሸልሞታል፤ ተመስገን እንጂ ፡ ከቶ ሌላ ምን ይላል?

ንፋሱ ሸው ምልስ፣ ቀለስ ደነስ እያለ ቆዳቸውን ሲያድስ ይታወቀዋል። ስንቱ የማይታደስ አሮጌ ታድሷል? ስንቱ የማይድን የሚመስል ደዌ ድኗል? ስንቱ የማይነጻ የሚመስል ጉድፍ ጸድቷል? ስንቱ የማይሠረይ የሚመስል ሃጢያት ተሠርዮል... "አይሆንም፤" አይልም፤ |እሱ፣ እናቱና አባቶቹ ብዙ አይተዋልና።

ዛሬ ለቬራ ታሪኩን በሰፊው ሊያጫውታት ተቀጣጥረው ነው ከዚህ ውብ ስፍራ የተገናኙት። ሲቀነጭብና ሲቆነጥር የህይወቱን ትርክቶች አካፍሏት ያውቃል። የእሱና የሦስቱ አባቶቹ አንቲካ[3] ሁሌም እንደሚያስደንቃት ትነግረዋለች። ያሳለፈው ህይወትና የተማረው ልዩ ጥበብ አግራሞትን ይፈጥርባታል። ምኑንም ሳያንቀሳቅስ ከሷ ጋር መግባባት መቻሉም ተኣምር ይሆንባታል። ብቻ የመርዕድ ነገር ቬራን ከነፍሷ ምሰሶ ዘልቆ ያር'ዳታል።

---

3 ታሪክ

ሐሳቦቿ ላይ አሁንም እነዚህን ግርምትና ጥያቄዎች እየሰማ ነበር።

ዛሬም ካለ ድምጽ ታሪኩን ይተርክላት ገባ። አንቴናዎቿን ጠልፎታልና| አውታሩ ሆናለችና - ይግባባሉ ⌘

የመርዕድ መነሻዎች እናትና አባቶቹ ናቸው። ኤልሳ የምትባል አንድ እናትና ሦስት አባቶች አሳድገውታል። የመጀመሪያው ለይኩን፣ ሁለተኛው አበጋዝ፣ ሦስተኛው ዶ/ር ሶፎኒያስ ይባላሉ። እንግባበት ካልን ሐተታው ብዙ ነው። እነሆ እሱም ታሪኩን ከእናቱ ጀምሮ ቀሪዎቹንም አከታትሎ ለሼራ ያጫውታት ጀመረ። ወግ ወጉን ይዞ፡ ትረካውን ለጉድ ዘለቀበት...

የመርዕድ እናት... የሺህ ሰው ግምት ያልነበረች፤ አንዲት ዘንካታ ወጣት... ኤልሳ፤

⌘⌘⌘

**አዲስ አበባ : 1995 ዓ.ም**

ክረምት ነው፤ ደመናና ዝናብ ብቻ... ይበርዳል፤ አመዳይ አለ። ጤዛው ልብ ያጦዛል፣ ቅዝቃዜው ይጠዘጥዛል : ብቸኝነት ይከብዳል። ዙሪያ ገባው ጨለምለም ያለ ነው። ... ኤልሳ በኮረዳነቷ ወቅት እንደ ቢራቢሮ እያጨተች በራለች። ማንጸባረቂያ ወጣትነቷንም አጋምሳለች፤ የምድርን አበቦች የምትቀስምበት፤ እሾኹቿን የምትጨብጥበት ለጋ እድሜዋን አልፋ በጠባሳዎቿ ቆዳዋን በመጠኑ አጠንክራለች። አሁን ሁሉን ነገር ለማየት ጉጉት ብላለች፣ ልክ እንደ ጉጉት አንገቷን 360 ዲግሪ እያዞረች ዙሪያዋን መመርመር ይዛለች : ወስናለች/ ኤልሳ፤

አዎን ወስናለች| በልጅነቷ የመሰረተችው ትዳር እያቅለሸለሻት ሰንብቷል። ልጅም በልጅነት ወልዳለች። በልጇ ከመደሰት ይልቅ ትናደድበታለች። በዚህ የውበት አክሊሌ ተሸቀርቅሬ እየወጣሁ እድሌን እንዳልሞክር አስሮኛል ብላ ስለምታስብ...ከልቧ ወዳው አታውቅም። ሁሌም ልጇ ከሷ የተሻለ ህይወት እየኖረ እንዳልሆነ ስታስብ ያብሰከስካት ነበር። ፈላጊ ግን በትወጣም ቤቷ ድረስ መጥቷል። ሆኖም ጩክና ነፃ እስክትወጣ ትንሽ ቆይታለች። የኔ በምትላት ጓደኛዋም ተከድታለች፤ እነሆ ሁሉን ነገር የምትቀይርበትና በቀሏን የምታጣጥምበት ትልቅ የፍርድ ቤት ቀጠሮ ዛሬ አላት። በሆዷ በቀልን እንዳረገዘች ከመስታወቱ ፊት ቆማ በሐሳብ በይነ-መረብ ትደውር ያዘች።

*ሁሌም ልጅነቷን በምልሰት ስታየው አትደሰትበትም፤*

ተወልዳ ያደገችው ጨው በረንዳ ፡ የፍቅር መንደር ነው። ፍቅር ግን ምንድነው? ... *ፍቅር በር አለመዝጋት ነው። ፍቅር እኔን ከእኛ ውስጥ የማግኘት አራድነት ነው። ፍቅር ከሙሉ ምቾት መሰዋእትነትን ማስቀደም፡ ሁልጊዜም ይቅር ማለት ነው ይሉታል። ፍቅር ከባድ ሐብት ነው፤ በየቦታው ስለሰማነው ዋጋው የማይወርድ፣ በእልፍ ቢዳረስም የማይረክስ ጸጋ! {እኛስ ማን ሆነን ነው ግን ፍቅርን የምንተረጉመው?}* ... ብቻ ኤልሳ በጨው በረንዳ ፡ ፍቅር መሐል ተወልዳለች፤ ህዝቡ በጠበቀ የአብሮነት ሰንሰለት ተሳስሮ ከልቡ ከሚረዳዳባቸው ሰፈሮች አንዱ ነው።።።

የአዲስ አበባ ሰው ጦርነቱን፣ በሽታውን፣ ድህነቱን ልክ እንደ አንድ ቤተሰብ ሆኖ አሳልፏል። የባልና የልጆቿን ችግርና ጉድ ከዓዳዋ ሽሽጋ ቀን እንደምታሳልፍ ምስኪን እናት ጥንካሬ የሚገዝፍ፣ የሆነ የማይታይ ማህብረሰባዊ የህብር መጋረጃ ነበረ። ያ ጥምረት ባይኖር ኖሮ ስቃዩ፣ ሐዘኑ፣ መራብ መቸገሩ ካለፈው የባሰ ይሆን ነበር። ለምሳሌ ያኔ በክፉ ጊዜ አንድ እንጀራ ለሰባት ተበልቷል። እንጀራውን አንድ ሰው ለብቻው በልቶት ቢሆን ኖሮ ግን ቀሪዎቹ ስድስቱ ይበልጥ በተራቡ ነበር።

*|ምላም ጎደለ፡ በዛም አነሰ፡ የሆነ የመተዛዘን መንፈስ ነበረ።*

እናም ኤልሳ በብዙ እርከን በተሳሰረ ማኅብረሰብ መካከል ነው በ1971 ዓ.ም የተወለደችው፤ አሁን 24 ዓመት ሆኗታል። ለግላጊት ወጣት ሆናለች።

ባለችበት ሁኔታ ውስጧ የማይረካ ወጣት ሴት! ዙሪያ ገባዋ የማይጥማት ጉብል። ዝም ብላ ስታስበው ማህብረሰቧ የገነባው የአብሮነት ሥርዓት አለማወቁንና ማጣቱን ለማሳመር የተጠቀመው መደበቂያ የሚመስላት ነገር አለ። ለዚህም ምክንያት አላት፤ የሷ እናትና አባት ከባላባቱ ወገን አልነበሩም። ታዲያ ወታደራዊው መንግስት ሲመጣ ጎን ማሳረፊያ የክራይ ቤታቸውን በስማቸው እንዲዞር አደረገላቸው። ደርግን እንደ ግል አዳኛቸው ቆጥረው ያመሰግኑት ነበር፤ የመጀመሪያ ልጃቸው ሲገደል ግን ፡ ኮሌጅ በጣጥሶ በሰፈር አድባሩ ተመርቆ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የገባው ጎበዙ ልጃቸውን በቀይ ሽብር ሲነጠቁ ግን ፡ ያመሰገኑትን መንግስት መልሰው ይረግሙት ገቡ። የነሱ እርግማን ነው መሰል ደርግ ዓመት ከመንፈቅ በኋላ ወደቀ። *{እርግማንና ምርቃት አይናቅም። የተቆጣ ወጣትም አይናቅም።}*

ኤልሳ ለቤቱ ሁለተኛ ልጅ ናት። ያኔ በለጋነቷ ወንድሟ ሲሞት እናትና

በሁለቱ ትላልቅ ባልዲዎች መሙላት ይጠበቅባታል። ይህን ካላደረገች ግን እናቷ ሰሞኑን ይከስራሉ። የግንበኛ ባላቸው ገቢ መቀነስን ተከትሎ መሸጥ የጀመሩት ድንች በሚጥሚጣ በመጠኑም ቢሆን እየደጎማቸው ይገኛል፤ ውኃ ካልተቀዳ ግን ለትልቁ ሰታቴ ማጠቢያ ፣ ለድንቹም መቀቀያ ውኃ የለም ማለት ነው። ኪሳራ ነው!

እቦኖው ጋር ስትደርስ የተወሰኑ ጀሪካንና ባልዲዎች ተደርድረው አየች። ሰሞኑን ውኃ ይሄዳል የሚለው ዜና በመንደሩ ተዳርሶ ኖሯል። በኖውን የሚቆጣጠሩት ኃይለኛዋ ሴትዮ፤ እትዬ ፋጡማ የህዝቡን ጭንቀት አይተው ነው መሰል ሰዓት እላፊ እየሠሩ ነው። ለመቅዳት ወረፋቸውን የሚጠባበቁ ሴቶች ደግሞ ድምጻቸው ሰማይ እስኪነካ ጮኽ ብለው ያወካሉ።

"ያ ልጇ ሳ ምንድነው የሚሠራው?"

"የትኛው?" ... "እንድዬ ልጃቸውን ነዋ?"

"አዎ! ማን ነበር ስሙ?" ... "እ...ዎ... ለ...ለይኩን፤"

"እሂሂ... ምኑን ሆነላቸው እቴ! የድሐ ልጅ ስሙ ሐብታሙ ምናምን ሲሆን ነው የሚያምረው..."

"ባክሽ አንቺ ደሞ፣ እንደዛ ቢሆንማ የሁላችንም ወንድ ልጆች ስም ሐብታሙ በሆነ ነበራ!" አሉ አንድ እናት፤ ሁሉም ሴቶች በአንድ ድምጽ ረዘም ያለ ሳቅ አስረቀረቁ፤

"የታባቱ እንዲህ እየሳቅን ወረፋውን ማሳጠር ነው እናንተዬ!"

"የኑሮን ነው የበኖውን?" ... "አይ አንቺ! ኪኪ .. ኪኪ ..ለማንኛውም ፈተናውን ወድቆ አልቀረም። በቅርቡ የራሱ ጋራዥ ከፈተኮ... አልሰማችሁም?" አለች ወሬውን የጀመረችው ሴት፤

"እልልል... እንኳን እመቤቴ ረዳችው፤ በጣም ምስኪን ልጅ ነው በናትሽ!"

"አዎ ወላሂ፡ እሱ ልጅ የዩንበርስቲ መግቢያ ውጤት አልመጣለትም ሲሉኝ አሳዝኖኝ ነበር፤ ጎበዝ... ሰው አክባሪ ነው።" አሉ እትዬ ፋጡማ፤

"እዎ ... እንድዬ ጥሎ አልጣለውም፤ በጋራዡ ከበረታ ያልፍለታል ...

የጋሽ አያሌው ልጅ ወንዴ እንኳን እንዴት እንደተቀየረ አላየሽውም?"

"በስማም! እሱማ ተድበልብሎ የእርጉዝ ፍየል ሆድ መስሏል ... በጣም ተስማምቶታል።" አሉ የቅድሟ ሴትዮ፤ ወፍሯል ማለት ተስማምቶታል ማለት እንደሆነ ሁሉም ተግባብተው ወሬያቸውን ቀጠሉ፤

"ለይኩን ግን ትዳር የመመስረቻ እድሜው ላይ የደረሰ ይመስለኛል፤ ደህና ሚሽት ፈልገው ቢድሩት አይሻልም?" አሉ አንዲት አሮጊት፤

"ኧረ እሱ እቴ! ሴት የሚባል ነገር እንደ ጦር ነው የሚፈራው አሉ።"... በመላ ምት የተሰነዘረ አስተያየት ነበር።

"ፈርቶ አይቀር መቼስ፤ አሁን ሣንቲሟ ስትመጣለት አንዷ ተጠግታ የያዘውን ዓይነ-ጥላ ትገፍለት የለ?"

"አይ አንቺዬዋ... ደህናዋ ትግጠመው እንጂ ሌላ ምን ይባላል ..." አሉና በኖ አስቀጂዋ እትዬ ፋጡማ ሐሳቡን ገታ አደረጉት፤ ከዚያ በኋላ ሌሎች ብዙ ወሬዎች ተግተለተሉ። ቀስ በቀስ ሁሉም ሴቶች ባልዲያቸውን ሞልተው ይዘው ከሄዱ በኋላ በቦታው አንዲት ባልዲ ብቻ ቀረች። እትዬ ፋጡማ አንገታቸውን መዘው "ይሄ ሰማያዊ ባልዲ የማን ነው?" ሲሉ ጠየቁ፡ ... መልስ አላገኙም።

"ኧረ ተረኛ ቀጂ ማነው? ... መሽቷል ዘግቼ ልሄድ ነው!"

"የ... የኔ ነው!" አለች፤ ከወሬያቸው ተነስታ በሐሳብ የነጎደችው ኤልሳ ወደ ራሷ እየተመለሰች፤

"አንቺ ልጅ ምን ነክቶሻል በአላህ?... ከቀልብሽ ሁኚ እንጂ! ... በይ... ቶሎ አስተካክለሽ ደቅኚው፤" ሲሏት ኤልሳ በታዘዘችው መሰረት ባልዲዋን ደቀነች፤ ውኃው እስኪሞላ ድረስ ስለ ለይኩን እያሰበች ጠበቀች። እሷና እኩዮቿ ብቻ የሚያውቁትን ታሪካቸውን እያብሰለሰለች ቧንቧ ውስጥ እንደሚጋልበው ውኃ ወጥታ ወረደች፤

ውኃው ሲሞላ ጠብቃ ሣንቲሟን እንደከፈለች አስቀጂዋ ሴትዮ፡ እትዬ ፋጡማ ጊዜ ሳያጠፉ በኖውን ቆላለፉት። ኤልሳ እመለሳለሁ ብላ ብትለምናቸውም አልራሩላትም። መሽቶብኛል ብለው ወጡ። የደረሳትን የውኃ ኮታ ተሸክማ ወደ ቤቷ ተመለሰች። በየመንገዱ መዳፏን ሲያማት ባልዲዋን እያሳረፈች፣ ቀኝና ግራ እጇን እያፈራረቀች በትግል ነበር ከቤቷ የደረሰችው ፡ ቤት ግን ጥሩ ነገር አልጠበቃትም።

"ምነው? ከዓባይ ወንዝ ነው እንዴ ቀድተሽ የመጣሽው? አደርሽበት እኮ!" አሏት እናቷ ወ/ሮ መንበረ፡ ገና ቤት ከመግባቷ፤

"ወረፋ በዝቶ ነው እማ!" . . . መለሰች፤

"ለማንኛውም ወሬውን ተይና... ቶሎ ውኃውን በትልቁ ባልዲ ገልብጠሽ፡ ተመልሰሽ ሌላ ቅጂ" ... በየቃላቱ እያመናጨቁ አዘዟት፤

"በኖው ተዘግቷል፤"

"ምን ማለት ነው?..አሁን ቀድተሽ መጥተሽ ተዘግቷል የምትይኝ?"

"እኔ የመጨረሻ ወረፋ ላይ ነበርኩኝ፤ እንደቀዳሁኝ፡ እትዬ ፋጡማ ዘግተው ሄዱ፤"

"ኤዲያ! ድሮም የሆንሽ እድለ ቢስ ነገር ነሽ! ... ምናለ ባታረፍጂ ኖሮ!..." ... ወ/ሮ መንበረ በማይሰሙ ቃላት ተነጫነጩ፤

ኤልሳ ካለ ልምዷ እጇን እያወናጨፈች... "እማ ደግሞ! አንዳንዴ ታበዢዋለሽ!" ብላ ስትመልስና አባቷ ጋሽ ቦጋለ በሩን በርግደው ሲገቡ አንድ ሆነ፤ በበቂ ደረጃ ሞቅ ብሏቸዋል፤

"ገ..ና... ገና ከበር ጭቅጭቃችሁ ነው የተሰማኝ፤ አይ የዚህ ቤት ጣጣ?!" እያሉ በገድጋዴ ገቡና ስፖንጅና ጥጥ ከሌለው የእንጨት ሶፋ ላይ ተለጥጠው፡ ለአመሉ ያህል ተመቻቹ፤

በዚያ ላይ "ይህቺ ልጅህን ብትመክራት ይሻላል፤ እግሯ አያርፍ ትዞራለች፣ አልታዘዝም እያለች ነው!" አሉ ወ/ሮ መንበረ ድንች መቀቀያ ድስትና እፊያውን ኤልሳ ባመጣችው ውኃ እያለቀለቁ፤

"ዋ! አንቺ ልጅ!... ጎረመስኩኝ ብለሽ እኛ ላይ ለመጨማለቅ እንዳታስቢ፤ ሀእ... እንዳንቺ አልደላንም... ይልቅ እስኪ የሚኒስትሪ ውጤትሽን አሳዪኝ?... ዛሬ ሀእ... ጋሽ ለማ ልጁ 99 አመጣ ብሎ አረቄ-ቤት ጉራውን ሲነዛብን ነው ያመሸው!" አሉ ጋሽ ቦጋለ፤ ኤልሳ ደንግጣ እዚያው በቆመችበት ደንዝዛ ቀረች።

"ምን ይገትርሻል?... ውጤትሽን አሳዪን እንጂ?" እናቷ ጥያቄው ላይ ግብጦ አረቄ ጨመሩበት፤

"እ... አልተሰጠንም!" መለሰች ኤልሳ በደመ-ነፍስ፤ ወ/ሮ መንበረ ወዲያውኑ ነበር ልጃቸው እየዋሸች እንደሆነ የገባቸው። ፈጠን ብለው

ኤልሳ ወንበሩ ላይ ያስቀመጠችውን ደብተር እንዳነሱ የሚኒስትሪ ካርዷ ከደብተሯ መሐል ሾርተት ብሎ ወደቀ፤ የኤልሳ እጢም አብሮ ዱብ አለ። ወ/ሮ መንበረ ካርዱን አንስተው ለአባቷ አስረከቡ፤ ባልተቤታቸው እንጂ እርሳቸው ማንበብ አይችሉም። ጋሽ በጋለ ካርዱን ተቀብለው የልጃቸው ውጤት ላይ ለጉድ አፈጠጡበት።

"እንደፈራሁት ወድቃለች አይደል? ... እናሳ? ባትወድቅ ኖሮማ ምን ውጤቷን ያስደብቃት ነበር?" አሉ እናት፤... ባለቤታቸው ካርዱ ላይ ያለውን "አልተዘዋወረችም" የሚለውን ጽሑፍ እስኪያነቡ ትንሽ ጊዜ ፈጅቶባቸው ነበር። በስተመጨረሻም አቶ በጋለ "ለካ ልፋቴ ለከንቱ ነበር!" አሉና በንዴት የልጃቸውን የሚኒስትሪ ካርድ እቤቱ መሐል ካለው ከርካሳ ጠረጴዛ ላይ ወረወሩት!

"ውይ! ውይ! ውይ! ያልኩትም አልቀረ... " አሉ ወ/ሮ መንበረ መርዶ እንደተነገረው ሰው ድምጻቸውን እየቃኙ፡ "ድሮም እኔ ልጄ አንድ ብቻ ነበር፤ እሱንም እሳት በላብኝ... ወይኔ ልጄ! ወይኔ...! ብቸኛው የማህጸኔ ፍሬ... ተስፋ ምትኬ!" እያሉ እንዳዲስ ሙሾ ማውረድ ያዙ። |ኤልሳ ሽምቅቅ ብላ ቆማ ትንዘፈዘፋለች፤ በጣም ክፍት ብሏታል፤ እንባዎቿ በመንታ በመንታ ጉንጮቿ ላይ ተንከባለው ወርደው ከወለሉ ላይ ፈራረጡ። ... ታዲያ የቱንም ያህል በእንባ ቢጋረዱ እንኳን የኤልሳ ዓይኖች የአባቷ ቀበቶ ሲፈታ ለማየት ፈጣን ናቸው፤ በቂ የመገረፍ ልምድ አላት። ሮጣ ልትወጣ ስትል ዘለው ቀኝ ክንዷን አፈፍ አደረጉት። የአውሮፓ ባሪያ-ነጋዴ አረመኔዎችን ጭካኔ በሚያስታውስ መልኩ ገረፏት። ሰውነቷ ላይ የሚድኑ ሰንበሮች አእምሮዋ ላይ ደግሞ በቀላሉ የማይድኑ የትዝታ ቁስሎች፡ በህሊናዋ ውቅር ላይ ተቀርፀው ቀሩ።

ቅጣታቸውን ሲጨርሱ፤ ለወትሮ ምን ቢሰክሩ እንኳን እራት ሳይበሉ የማያድሩት አባቷ አንገታቸውን እንደደፋ ገብተው ተጠቅልለው ተኙ። በቅጡ እንኳን እሷን ለማዳን ያልሞከሩት እናቷም ቢሆኑ አሁንም እሷን የሚያሟሽሽ፡ የሞተው ታላቅ ወንድሟን የሚያወድስ፡ ሙሾ ቢጤ እያሉ ወደ ጓዳ ገቡ።

ምሬትና ህመም| እንደማይታፈሱ የእንባ ዘለላዎቿ እሷም ወለሉ ላይ ዘፍ ብላ ቀረች፤ ጠብ ሳይል ካልቀደሙት በቀር ከመሬት የፈሰሰ እንባና ደም አይታበስም። የኤልሳ አባሽ ያጣ የውስጥም የውጭም ለቅሶ አልቆም አለ፤ ነፍሷ ልትተነፍሰው በማትችለው ቂም ሲወጠር ይታወቃታል፤

ሐዘኔታ የለም፤ እንኳንስ አጋፔ[5] ስቶርጅም2 የለም፤ ተስፋ የለም፣ ብር የለም፤ ሰላም የለም ፡ ድፍት ብላ፣ ማቅ ለብሳ ቀረች።

ከዚያን ጊዜ በኋላ ኤልሳ ፈጽሞውን አልተጠገነችም። ድሮም የማትወደውን ድህነት ብቻ ሳይሆን ሰውንም ጭምር ጠላች። "ተስፋና ንዋይ ከሌለህ የ… የምትለውም ሳይቀር ይጠላኻል!" ብላ ገና በለጋ እድሜዋ ደመደመች።

|ዛሬ ላይ ሆና የዚያች ቀን ህመሟ ትዝ ሲላት ትውስታው በራሱ አንገሸገሻት። ትዝታዋን የምታራግፍ ይመስል ጸጉሯን መንሸር መንሸር አድርጋ፤ ልጇን አፈፍ አድርጋ አቅፋ ከግቢው ወጣች። በር ላይ ሲጠብቃት የነበረው ሰው የመኪናውን በር ከፍቶ አስገባት። መኪናዋ እየተጣደፈች ወደ ፍርድ ቤት አቅጣጫ ከነፈች።

⌘ ⌘ ⌘

ያኔ ግን| ኤልሳ ሚኒስትሪ ከወደቀችበት እለት ማግስት፤ አንድ ጸጉሩን ባጆ የተቆረጠ፣ ሰማያዊ ካኪ ጃኬት የለበሰ ልጅ መልእክት ተልኮ ከነወ/ሮ መንበረ በር ላይ ቆሞ ነበር። ጉንጫም ፊቱ ላይ ጉጉት ይነበብበትም ነበር። እየተቅበዘበዘ... ቃጭል ድምጹን አጥርቶ ተጣራ፤

"እማማ!... ትኩስ ድንች አለ?"

ከማጀት ውስጥ ተስፋ የቆረጡ የሚመስሉ እናት ፡ እንደ ድንች ሰተቴያቸው የቀዘቀዘ መልስ ሰጡት፡ "የ..ለ..ም።"

"እ... እሺ ... ኤልሳስ አለች?"

"አቤት" ... የወጣት ሴት ድምጽ ተሰማ።

⌘⌘⌘

## ጥቅምት - 2007 ዓ.ም/ ኣማኑኤል የሥነ-አእምሮ ሆስፒታል፤

"ከተማው በሙሉ በረብሻ ተሞልቷል። ሁሉም ነገር ይጮኻል። ማረፊያ በታ ነው ያጣሁት ዶክተር!" አለች ሜሮን ፡ በድብልቅልቅ ስሜቶች ተጠርቃለች፤ ማስታወሻ ደብተሯን ጭምቅ አድርጋ ይዛለች፤ የሆነ የሚወስድባት ሰው ያለ ይመስላል።

---

5 ግሪኮች ፍቅርን ለመግለጽ ብዙ ቃላትን አበጅተዋል። ለምሳሌ አጋፔ ማለት ምላሽን የማይፈልግ ፍጹም ውዴታን ሲገልጥ፤ 2 ስቶርጅ ደግሞ ከዚያኛው ወገን የሚገኝን ውዴታና ጥቅም ተመርኩዞ የሚለገስ ፍቅር ነው፡

ዶ/ር ሶፎኒያስ የሜሮን ፊት ላይ በኑሮ ተስፋ መቁረጥና ድካም ይታየዋል። ነፍስን አመንምኖ በሞት ጥላ የሚጋርድ አይነት ድባቴና ጭንቀት፤ ይልቁንም የማኅብረሰቡ ሁኔታዎች የሜሮንን የአእምሮ ህመም እያባባሱት እንደሆነ ያውቃል። ህመሟ ከመሻሻል ይልቅ እያገረሸ ነው የመጣው። ይህቺ ብዙ ጊዜ የተሰበረች ነፍስ ሰላምን ማግኘት አልቻለችም።

"እስኪ ምን ምን አይነት ነገር ነው የሚረብሽሽ... ንገሪኝ?"

"ዶክተር... ሁሉም ነገርኮ ይጮኻል፤ መንገድ ስወጣ የመኪናው ጥሩንባ ይጮኻል፤ የትራፊኩ ፊሽካ ይጮኻል፤ የመንገድ ዳር ሚዛኑ ይጮኻል፤ ታክሲ ውስጥ ሰዉ ይጮኻል፣ ሞባይሉ ይጮኻል፣ በየሙዚቃ ቤቱና ሆቴል ደጃፍ ላይ ያለው ሞንታርቦ ይጮኻል... ከዚህ ሁሉ ሸሽቼ ቤት ስገባ ራዲዮና ቲቪው ይጮኻል፣ ቪዲዮ መር ስፒከራችን ይጮኻል፣ ፍሪጁ ይጮኻል፣ ስልኬ ይጠራል፣ ማታ ላይ የመንደሩ ጭፈራ ቤቶች ካለቅጥ የሚከፍቱት ሙዚቃ ግድግዳ በስቶ ይጮኻል... እንቅልፍ ይነሳል! የእነሱስ የለየለት ነው... ግን ከምንም በላይ የሚገርመኝና የሚረብሸኝ ምን እንደሆነ ታውቃለህ ዶክተር?"

"አንቺው ንገሪኝ እስኪ?"

"ሌላ ጊዜ ጸጥታና ሰላምን ለማግኘት የምሄድባት፣ ያሳደገችኝ ቤተ-ክርስቲያን እንኳን በድምጾች እየተሞላች ነው። መስጊዱም፣ ቸርቹም እንዲሁ በድምጽ-ማጉያዎች ታጅለዋል። ከዓለማዊው ሁካታ መሸሻችን የነበሩት እነዚያ የሃይማኖት ግቢዎች እንኳን ጸጥታቸውን እያጡት ነው። ፈጣሪ በጣም የሚጮኸውን የድምጽ-ማጉያ ልመና ይሰማል የተባለ ይመስል ሞንታርቦ ካለቅጥ ይለቀቃል፤ ቤተ-እምነቶቻችን በ‹ስፒከር› ኃይል የእኔ እበልጥ ፉክክር የያዙም ይመስላሉ። እኔ ደግሞ ይህን ሁሉ ሳስብ የበለጠ ጭንቅ ይለኛል!"... ሜሮን ፊቷን ቅጭም አደረገችው ... "ቆይ ግን ዶክተር? ድምጽ-ማጉያ ሳይገኝ በፊት የነበረው ፈጣሪ አሁንም አለ አይደል? ወትሮስ ፀሎት በአርምሞ አልነበረም ወይ ደንቡ? ያኔ የሰማን አምላክ አሁን ሌላውን እስክንረብሽ ድረስ ካልጮኽን አይሰማንም ወይ? ... እኮ የት ብሄድ ነው እረፍት ማግኘት የምችለው? የውስጥ ህመሜ የሆነው እሱን መርሳት የሚቻለኝ?... እንደነገርኩህ እንቅልፍ ለቀናት በዓይኔ ዞሮ አያውቅም።"...ጭንቀቷ ነፍስ ዘርቶ ከዶ/ር ሶፎኒያስ ፊት ተገተረ፤

"እምም... እርግጥ ነው፤ ከባድ ሁኔታ ውስጥ እንዳለሽ ይገባኛል።" አላት፣ መነጽሩን አስተካክሎ አፍንጫው ላይ እየሰካ፤

"እ... ጭንቀትሽን እረዳለሁ፤ ባይገርምሽ የድምጽ ብክለት ከአየርና ውኃ ብክለት ባልተናነሰ የዓለማችን ራስ ምታት ሆኗል። ጥናቶች እንዳረጋገጡት የድምጽ ብክለት ለደም ግፊት፣ ለደም መርጋት፣ ለኩላሊት ህመም፣ ለእንቅልፍ ማጣት በሽታ፣ ለጆሮ ህመም ብሎም መስማት እስከመሳን ሊያደርስ ይችላል።... ችግሮቹ በከፍተኛ ድምጾች ብቻ ሳይሆን በመካከለኛ ግን በጣም ተደጋጋሚ በሆኑ ድምጾችም ሊከሰቱ እንደሚችሉ ነው በቅርቡ የወጡ ጥናቶቹ የሚያሳዩት። ከምንም በላይ ደግሞ ልክ እንዳልሽው የአእምሮን ሰላም በብዙ መልኩ ያውካሉ፤ ብዙዎቹን የአእምሮ ህመሞችም የድምጽ መብዛት ያባብሳቸዋል[6]። እናም የምትይኝን ነገር እረዳሻለሁ ለማለት ነው።"

"ዶክተር አንድ ነገር ግን አልተረዳኸኝም!" አለች ሜሮን እየተቁነጠነጠች፤

"ምን?"

*"የሚረብሸኝኮ የከተማው ድምጽ ብቻ አይደለም። በጆሮ የማይሰሙ ጩኸቶችም ይረብሹኛል። ለምሳሌ: የሚጮኹ ጽሑፎች አንብበኽ ታውቃለህ ዶክተር? የሚጮሁ ትውስታዎችስ አስጨንቀውኽ ያውቃሉ?"*

"እንደዛ እንኳን አላውቅም፤ በደንብ አብራሪልኝ እስኪ?" አለ ዶ/ር ሶፎኒያስ አዲስ መነቃቃት እየታየበት፤

"ለምሳሌ ኢንተርኔት ስከፍት የሚጮሁ ጽሑፎችና መልእክቶች፣ የሚጮሁ ምስልና ‹ቪዲዮዎች› አያለሁ፤ ከስራቸውም የሚጮሁ ኮሜንቶችና ስድቦችን አነባለሁ። በቃ ይረብሹኛል... ሐሳቤን ያጮሁብኛል፤ እና ደሞ..." አለችና ሜሮን ለመናገር ቃተተች... "...እሱንና ልጄን ሳስባቸው ደግሞ ትዝታዎቼ እሪ እያሉ ይበጠብጡኛል! ውስጤ በናፍቆትና በእጦት ይደባያል።" ... አሁን ደግሞ በይበልጥ የተረበሸች መሰለች። ዶ/ር ሶፎኒያስ ልብ ብሎት የማያውቀውን ነገር በጣም በለፋባት ታማሚው ላይ እያየ መሆኑ ገርሞታል። የሚጮኹ ጽሑፎችና ምስሎች አሉ? ወይስ የታማሚዋ አእምሮ ያቀነባበረው የበሽታው ምልክት ነው? ሌሎች አዳዲስ፣ ተጓዳኝ ህመሞችንም መጠርጠር ጀምሯል። በጥያቄ እያሰላሰለ ሳለ ሜሮን ድንገት ከሐሳቡ አነቃችው።

"አሁን ምን እንደምፈልግ ታውቃለኽ ዶክተር?"

---

6 Mental illnesses sensitive to voice include Depression, Anxiety, Schizophrenia. Plus other brain disorders lik Delirium, Epilepsy & typical one, Tetanus infection.

"እሺ፤"

"ዝምታ ብቻ ... የውስጥም የውጪም ዝምታ!"

ዶክተር ሶፎኒያስ ድንገት መብረቅ የመታው ያህል ተሰማው። ዛሬ ታማሚው መድኃኒትና ምክርን ሳይሆን ዝምታን ነው የፈለገችው። የውስጥም የውጭም ዝምታ፤ እነሆ ዝም ብሎ ቀረ። ለብዙ ጊዜ ያከማትን ታማሚ እንዳዲስ አስተዋላት። እርግጥም ዝምታን እጅጉን እንደምትፈልግ የውስጥና የውጭ ድምጾች ያራኮቱት ገጿ ይናገራል፤ የእንቅልፍ ኪኒን ሊሰጣት ያልቻለውን እረፍት ያጣ ገጿ ገርጥቷል። አበክራ መድሐኒቴ ዝምታ ነው እያለች ነው።

*ዝምታ እንደ ክኒን እንክብል አይታዘዝ፣ በመርፌ አይወጋ፣ ከየት ያገኝላት? ከወዴትስ ያምጣላት?*

## ለመሆኑ የዝምታ መገኛ የት ይሆን?

* ✡ *

# ምዕራፍ ሁለት

# እውን ነፃ ነን?

# Δ

## ግንቦት/ 2007 ዓ.ም

ለይኩን ሽሽቱን ቀጥሏል። አብረውት ከእሥር ቤቱ ያመለጡት ሁለቱ ታራሚዎች የት እንደደረሱ ምንም አያውቅም። የሚያሳድዱት ጥበቃዎች በየሰከንዱ እየቀረቡት ሲመጡ ይታወቀዋል። ያ ቁስሉ ግን እንደ ልቡ እንዳይሮጥ አግዶታል፤ እነርሱ ደግሞ እንዴት አመለጠን በሚል የእልህ ስሜት ግፊት እየገሰገሱ እየተጠጉት ይገኛሉ። የጊዜ ጉዳይ እንጂ እንደሚደርሱበት አልተጠራጠሩም። እሱም እንዳይዙትና ዳግም ወደዚያ አፋኝ እሥር ቤት እንዳይመልሱት የመጨረሻ አቅሙን ተጠቅሞ እየሸሸ ነው።

ድንገት ከእግሩ ጀርባ የሆነ ነገር ከበደው። ዞር ቢል አንድ ከዘቦቹ እጅ ያመለጠ ጆፌ ውሻ እግሩ ሥር ደርሶ ኖሯል። ምናልባትም በማይክሮ ሰከንዶች ልዩነት የውሻው ክራንቻ፣ ቋንጃውን ሳተው! ለይኩን ደንግጦ በደመ-ነፍስ ተመነተፈ። ቀጥሎ ግን ምን እንዳደናቀፈው እርግጠኛ አልነበረም፤ የቀኝ እግሩ ጣቶች ከነገሩ ጋር ሲላተሙና ሚዛኑን ሲስት ግን ይታወቀዋል። ወደ ታች ተምዘገዘገ ፡ ሦስት ሜትር ገደማ ቁመት ካለው ገደል ላይ ቁልቁል ተደፋ። ወደ ጉድባ[7]ው ዥው ብሎ ወደቀ፤ ቀጥ ካለው ገደል ቀጥሎ የተቀበለው ደግሞ ሌላ ተደፋት ነበር፤ በተፈጠፈጠበት ፍዞታዊ ኃይል ወደ ታች ተንደባለለ።

---

7 በዘመናት ጎርፍ የሸረሸረው ጉድጓድ፤

ታዲያ እየወደቀ ባለባት ቅጽበት ውስጥ ሊሞት እንደሚችል አሰበ። ድንገት ሞት መጣ ፡ ጸጥታ መጣ። {ህይወትኮ ተንከባላ ከአፈሩ ላይ በዝምታ ዘፍ ትላለች። ከዚያ ዝምታ ብቻ ይሰፍናል። የውሻው ጬኸት ይቆማል፤ የኑሮ ፈተናው ጸጥ ይላል፣ የውስጥህ እሪታ ይዋጣል፤ ሞት በግዴታ የሚጣልብን ዝምታ ነው።

አጅሬ ሞት ድንገት መውደቅ ነው፤ አንሸራቶህ ከመሬት እንደመደፋት፤ ከፋቱ ደግሞ መቼ እንደሚመጣም አይታወቅም፤ ለመጮኽ ጊዜ አይሰጥም፡ አንዠላጦኽ ከወለሉ ዱብ ፡ ዧ… እንክትክት እንደማለት፤ ቃላት የማያድኑበት ነጥብ.፡፡ ድንገት ይይዛል ፡ በአፈር አፍኖ ጸጥ ያደርጋል፡፡ ለዚህም ይመስል የመቃብር ስፍራ ዝምታ ይደብታል፤ ይከብዳል ፡ የሞት ካባ ዝምታ አይደለምን? ማለት እድሜ ልኩን ያወራ ሰው ዝም ብሎ ሲ.ቀር ለሚያየው ‹ሩህ› ፍርሃት ውርር አያደርግም?

ወትሮም ‹ዝም እንደ መቃብር› ይባል የለ? የሞት ጸጥ ያለ ድባብ ያስፈራል። ምናልባትም ህያዋን ሳለን የምንሸሸው ዝምታ በግዴታ ሲይዘን ዱብእዳ ስለሚሆንብን ይሆናል። ህያዋን ሳሉ ለብቻቸው፡ በዝምታ የሚመረምሩ ግን ብጹዓን ናቸው።}

ለይኩን እየወደቀ ይሄንን ሁሉ፣ መዓት ነገር አሰበ፤ ሐሳብ ግን ከመሬት ስበት ምን ያህል ይፈጥናል? እነሆ ለሱ ዛሬ ሐሳብ ፈጠነች፤ በዚያች በመውደቅ ቅጽበት ውስጥ የዘላለም የሞት ዝምታ በሐልዮቱ ውልብ ብሎበት አለፈ።

ከተዳፋቱ ግርጌ ላይ ደርሶ ጀርባው ጠፍ መሬት ሲነካ ፡ እንደተንጋለለ ሰውነቱን ደባበሰ፤ "አልሞትኩም?" አለ በለሆሳስ፤ የተሰበረ አጥንት የለም፤ ያቺ የረገማት ሚስማር የወጋችው ባቱ በስተቀር ሌላ ህመም አልተሰማውም። "አዎን አልሞትኩም!" ተዓምር ነው እንጂ ማን ከገደል ወድቆ ይተርፋል? ሀሌሉያ! ገለታ ይገባው! አዎን ተዓምር ነው። ቀና ብሎ አሳዳጆቹን ቢፈልጋቸው፡ የተናካሹን ውሻ የአንገት ቀበቶ የያዘ ጥበቃ ወደ ታች ባትሪውን አብርቶ ሲያማትር አየው። ውሻውም ለጉድ ይጬኻል።

ለይኩን የሞት ሞቱን እየተንፏቀቀ ከአንድ ቋጥኝ ጀርባ ተደበቀ፤ ህመሙን ዋጥ አድርጎ፡ አፍኖ ይዟል። ድምጽ ማሰማት ከባድ ዋጋ ያስከፍላል። አሁን ላይ ትንሽ ድምጽ ሞት ማለት ልትሆን ትችላለችና ፀጥ ረጭ ብሎ ጠበቀ። ተከታትሎም ብዙ የእጅ ባትሪዎቻቸውን ያበሩ፤ ጠበንጃ የታጠቁ የጥበቃ ሠራተኞች ከዳገቱ አፋፍ ላይ ሆነው አካባቢውን ሲያስሱ አጮልቆ አያቸው። ትንፋሹን ውጦ አደፈጠ፤

ለደቂቃዎች ካፈላለጉት በኋላ "ይሄንን ገደልማ ካላበደ በቀር አይዘልም!" ተባብለው፤ በስተግራቸው በኩል እየተግተለተሉ ሄዱ። ለይኩን የቻለውን ያክል ትንፋሽ ወሰደና እንደ ጅብ አጎንብሶ ጉዞውን ቀጠለ። ጥሻና ቁጥቋጦዎችን እያሳበረ ጥቂት እንደሄደ ድንገት እግሮቹ ረጠቡበት ፡ አጎንብሶ ቢዳብስ ፡ እስከ ቁርጭምጭሚቱ ድረስ የከብቶች አዛባ ውስጥ ተደፍቋል። ከቅርብ ርቀት ደግሞ የላሞችና የበሬዎች ድምጽ ይሰማው ጀመር ፡ ወደ ከብቶች በረት እንደተቃረበ ተረዳ። የከብት በረት አለ ማለት ገበሬ አለ ማለት ነው። ገበሬ አለ ማለት ሊያጋልጠው የሚችል ሰው አለ ማለት ነው። ደግሞም ገበሬ እንኳን በቲቪና በተንቀሳቃሽ ስልክ ዘመን ድሮም ካለ ራዲዮና ስልክ መረጃ እንደሚደርሰው ፡ መሬት ለመሬት የተዘረጋ ልዩ የመረጃ መረብ፣ ውስጥ ለውስጥ የተነጠፈ የመገናኛ መስመር እንዳለው ያውቃል። የእህል ገበያ ስንት ዋለ? እንትን መንደር ሽቅብ ቁልቁል አድርጎ የሚገድል፣ ትንፋሽን የሚሰልብ ወረርሽኝ ገባ፣ እንትን አገር ጦርነት ተነሳ፣ የአንበጣ መንጋ መጣ፣ ከብት የሚፈነግል ደዌ ገባ፣ ከማረሚያ ቤት አደገኛ እስረኞች አመለጡ ... ገበሬ መረጃ አለው። ዛሬ ጥዋት አንዷ ያቀበለው ወሬ ማታ ላይ ከሀገር ጥግ እስከ ጥግ ተሰምቶ ያድራል። እናም ለይኩን ፈራ ፡ አሳልፈው ቢሰጡትስ? ግን ደግሞ ከዚህ በላይ የመሸሸ አቅም የለውም ፡ ተልፈስፍሷል። የሮጠበት ድካምና የደም መፍሰስ ላይ የቁስሉ ህመም ተደምሮ አሽመድምዶታል። በዚያ ላይ ለጉድ ርቦታል ፡ የውኃ ጥምም እያንገበገበው ነው።

ባጭሩ እጣ ፋንታው እኚህ ገበሬ እጅ ላይ ወድቋል። ወይ ይጠግኑታል ወይም ይሰብሩታል። በዝግታ ወደ ቤታቸው ተጠጋ፤

⌘ ⌘ ⌘

ለዶ/ር ሶፎኒያስ ሌሎችን የማዳመጥ ዝምታ እንጀራው ነው። የእሱ ዋነኛ ጥበብ ዝም ብሎ ታማሚዎቹን መስማትና መረዳት ነው። ህመም ወለድ ችግራቸውን፣ ስኬታቸውን፣ ደስታቸውን፣ ብሶታቸውን፣ ተስፋቸውን፣ ሽንፈታቸውን፣ ሲያኾጎደጉዱበት የማዳመጥ ሆደ-ሰፊ፣ ልበ-ቅቡል ስብእና መገንባት ችሏል። ብዙ ዓመታትን በሀገር ውስጥና በውጭ-ሀገር የቀሰመው ትምህርቱ እዚህ አድርሶታል። ‹ሳይኮ-አናሊስት› ነው።

ሲያዩት የደራሲ ፊት አለው። የደራሲ ፊት ግን ምን ይመስላል? የባህሪ አህጉራት፣ ብዙ ገጸ-ባህሪያት የተሳሉበት ሉል ይመስላል ፡ ከሽለቆ እስከ

ተራራ የተዘረጋ መልክዓ-ምድርን ይመስላል፤ ማለት... ብዙ ብዙ ተረካ ተረኮችን ያካተተ ነው።

*ዶ/ር ሶፎኒያስ ደራሲ ይመስላል ፡ መነጽር ደግሞ አይለየውም፤ ጸጉሩ ላይ ተልባ የሚያኽሉ ሽበቶች ጥቁር ሰማይ ላይ እንደተበተኑ ከዋክብት ጣል ጣል ብለው ይታያሉ። መዘነጥና ልታይ ማለት አይወድም | ቀለል ያለ ሰው ነው። ቀለል ያለ ሰው ባይሆን ታማሚዎቹ ነጻ ሆነው የሆድ የሆዳቸውን ሊያወያዩት ይሳናቸው ነበር። እናም ሥራው ይሆናል እንደዚህ ያደረገው።*

ባለ ብዙ መስመርና ማዕዘናት ሽሚዞችን ያዘወትራል። ከሁሉም ጋር ተግባቢ ነው። መስማት ላይ ቢወደስም ቅሉ ንግግር ላይ ግን ይታማል። የመሰለውን ነገር ፊት ለፊት ፍርጥርጥ የሚያደርግ አይነት ሰው ነው፤ አንዳንዴም በማህብረሰቡ ዘንድ ነውር የሚባሉ አይነት ቃላቶችን ሳይቀር ይጠቀማል። ስለዚህ በተቻለው መጠን ጸጥ ለማለት ይሞክራል ፡ ሌሎችን ላለማስቀየም። ግን ደግሞ እውነትና በደልን እያየ በዝምታ ማድበስበስ አይችልም። ከታፈነ የሚፈነዳ ይመስለዋል። ወይ ካላወራ፣ ወይም የሌሎቹን ብሶት ካልሰማ ግን የውስጡን ጬኸት መታገስ አይችልም። ከራሱ ጋር በዝምታ መደማመጥ አይሆንለትም። የሆነ የሚሰማው ደህንነት ማጣት አለ።

*የሥራ ባልደረቦቹን፣ በተለይም ከፍተኛ ቦታ ላይ ያሉ አለቆቹን በንግግሩ ቅር አሰኝቷል። በታማሚዎቹ ጉዳይ ግን አይደራደርም። እንዲያውም አለቆቹ የሚመስሉት ታካሚዎቹ ናቸው። ልክ የማከሚያ ክፍሉን ከፍተው ሲገቡ ፊቱ በፈገግታ ይሞላል። ሌላ ጊዜ የመሰለውን ካለ ለከት ከመናገር ለመቆጠብ የሚቸገረውና ሰውን የሚያስቀይመው ሶፎኒያስ፤ ታማሚዎቹ ቢዘልፉት አጸፋ የማይመልሰው ‹ሳይኮ-አናሊስቱ› ዶ/ር ሶፎኒያስ ይሆናል። በጣም ስለሚያስብላቸው አብሯቸው ታሞ አብሯቸው ይድናል። ከልቡ ስለሚያክምም ብዙዎችን ከነፍስ አመንማኝ፣ ከባድ የአእምሮ ህመማቸው እንዲያገግሙ ረድቷል። ይሄን ማንነቱን የሚከታተላቸው ታማሚዎችና ቤተሰቦቻቸው ይወዱለታል ፡ ከሰዉ በላይ ደግሞ እሱ ራሱ አጥብቆ ይወደዋል። እንዲሁ ታማሚዎቹን በማከሙ ብቻ የሚሰማው ልዩ ሰላም አለ። ያ ሰላም ግን ሁሌም ቢኖረው ይመኛል። ልክ ከታካሚዎቹ በተለየበት ቅጽበት ግን ሌላኛው መልኩ ይገለጣል።*

ፈጥኖ ይናገራል ፡ ሰው ያስቀይማል ፡ ወዲያው ወደ ራሱ ይመለሳል። በቶሎ ይጸጸታል ፡ ራሱን ይወቅሳል ፡ ደግሞ ሌላውን ያስቀይማል። ይሄን

አዙሪት እንዴት እንደሚያቆመው ሲጨነቅ ኖሯል። በተከታታይ ቀናት ከዚህች ታማሚ ጋር ሲያወራ ግን አንድ የተገነዘበው ነገር አለ። ሁላችንም ሰውን ስንረዳ ራሳችንንም እንረዳለን እንዲሉ ዶክተር ሶፎኒያስም በሜሮን ውስጥ ራሱን አየ... ከልጅነት እስከ እውቀት ዝም ያለ ጠለሉን የሚያደፈርሱ የውጭም የውስጥም ጩኸቶች ብዙ መሆናቸውን ተረዳ። ታማሚዎችን በጸጥታ ማዳመጥ ብቻውን በቂ እንዳልሆነም አወቀ። ቅድሚያ ለራስ ዝምታን አበጥሮ ማወቅና ለሌሎችም ማስተማር፡ መለገስ መቻል እንዳለበት አሰበ። የዝምታን ህክምና መታጠቅ ነፍሱ ከጀለች። የሰው ልጅ የአስተዳደጉና የባህሪው ባሪያ እንደሆነም በተማረው ትምህርት ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ግላዊ ለውጥን ወጠናት። ለዚህ ዋነኛው መነሻው ሜሮን ትሁን እንጂ የራሱንም ህይወት ዞሮ ሲያይ የተለየ ነገር አላገኘም።

*የእሱ አብዛኛው ህይወት በረብሻ፣ በውጥረትና ሩጫ የተሞላ ነበር። ለወላጆቹ ስድስተኛ ልጅ ነው፤ ከሱ በኋላም ሁለት ልጆች ተወልደዋል። ቤታቸው ከሞላ ጎደል ጫጫታ የማይለየው ነበር። እናትና አባቱም በከፍተኛ ድምጽ ካላወሩ የማይግባቡ ነበሩ። አሁን ላይ ሲያስበው የልጆቻቸው መብዛት እነሱንም ቀይሯቸው ሊሆን ይችላል ሲል ይገምታል። የእነሱ ድምጽ ከልጆቻቸው ጫጫታ በልጦ እንዲሰማ መጮኸ ነበረባቸው ፡ ከጊዜ ብዛት ለመዱትና ልጆቻቸው ባይኖሩም ሳይጮኹ ማውራት አልሆን አላቸው። እናም ቤታቸው በድምጾች ጋጋታ የተሞላ ነበር። ለእሱም ተናጋሪ መሆን እነርሱን ይወቅሰል። በደምሳሳው ሰው ሲበዛ ድምጽ ይበዛል ሲልም ያምናል።*

የትምህርት ቤት ህይወቱም እንደ አብዛኛው የኢትዮጵያ ልጆች በቡረቃ የተሞላ ነበር። ጨዋታው፣ ፀቡ፣ ጭፈራው፣ የልጅነት መዝሙሩ፣ የጓደኞች እሰጣ ገባ፣ ሁሉም በረብሻ የታጀበ ነበር። ሶፎኒያስ ከ25 ዓመታት በላይ በትምህርት ዓለም ቆይቷል። የዝምታ ክፍለ ጊዜ የሚባል ነገር ግን አንድም ቀን አጋጥሞት አያውቅም። በሥራው ዓለም ውስጥ ሳለም ቢሆን ብዙ የሚናገሩ፣ ራሳቸውን የማይቆጣጠሩ፣ ሲያሻቸው የሚጮኹና የሚሳደቡ ታማሚዎች ጋር ነው ውሎው። የሚኖርባት ከተማ፤ የሁሉም መዳረሻዋ ሸገርም ብትሆን ወከባ እንደሚበዛባት ሳይታለም የተፈታ ነው። ባጠቃላይ እድሜውን ያሳለፈው በድምጾች ጉም ተከቦ ነው ማለት ይቻላል። የጸጥታን ፍሬ አላጣጣመም። ውጫዊውን ሁካታ መደምሰስ የሚችል ውስጣው የዝምታ ብርጌድም አልገነባም። አዎን! የሌሎችን ችግር ዝም ብሎ ከመስማቱና መፍትሔ ከመስጠቱ በፊት የዝምታን ምሥጢር በራሱ፡ ለራሱ መርምሮ ማወቅ አለበት። |እነሆ ለመወሰን ጊዜ አልፈጀም።

⌘ ⌘ ⌘

በማግስቱ ለአማኑኤል የሥነ-አእምሮ ህክምና ክፍል የሰው ሐብት አስተዳደር ቢሮ አንድ ደብዳቤ ደረሰ ፡ *"ዶክተር ሶፎኒያስ የተጠራቀመ እረፍቱን ወስዶ ከሥራ ገበታው ርቋል"* የሚል ቢሆንም፡ *እንደዚህ ረጅም ጊዜ ይቆያል ብሎ የገመተ ግን ማንም አልነበረም።*

⌘ ⌘ ⌘

**1988 ዓ.ም**

ሚኒስትሪ የወደቀች እለት ኤልሳ ቅስሟ እንደተሰበረ፡ የሌሊቱን አጋማሽ በምሬት ጥርሷን ነክሳ አነጋች። እንደምንም ብላ ከዚህ ቤተሰብ ራሷን ማራቅ እንዳለባትም አመነች።

*"ድህነታቸው ሳያንስ ጭቅጭቃቸው መከራ። ሆ...ሆ! ቆይ እስኪ ምን አድርጊ ነው የሚሉኝ?"* አለች በለሆሳስ ፡ አባቷ አቶ በጋለም እንዳይሰሟት እየተጠነቀቀች፤ "እኔ ወንድሜን መሆን አልችል! እኔ፡ እኔ ነኝ እሱ ደግሞ እሱ ነው።" ውስጧ ሰላም በሚነሳ ቅናት ሲሞላ ይታወቃታል። በወንድሟ፣ ለዚያውም በሞተው ወንድሟ ነው የቀናችው ፡ ፈልጋ ግን አይደለም። ገና ከልጅነት ወላጆቿ ስለሱ ጉብዝናና ስለሷ ስንፍና እያወሩ ሲያሸማቅቋት አድጋለች፤ በእሱ ላይ *"ምርጥ ልጅ"* የሚል ሞገሥ ጥለው በሷ ላይ ውኃ የመቅዳት ኃላፊነት ጭነዋል።

በዚህ የተነሳ ገና ድሮ ከለጋነቷ ጀምሮ፣ እስትንፋሱ ሳትለየው በፊትም የቅናት ካቲካላ ያሰክራት ነበር። አዎ አሁን የመጣ እንግዳ ስሜት አይደለም። በተለይ በዚያች የተረገመች ሌሊት ግን ብቻዋን ስትብሰለሰል አድራለች። የማይነጋ ሌሊት የለም ቢባልም ይሄኛው ግን እጅግ ሲበዛ ረዝሞባታል!

በዚህ አስጠሊታ ምሽት ሌላ በሐሳቧ የሚዋልል ነገርም ነበር። ስለ ለይኩን ፡ ትናንት በኖ ውኃ ለመቅዳት በተሰለፈችበት ወቅት ስሙ ተነስቶ ሲወራ ነበር። ስለ እሷና እሱ ከሰፈሯ ሰው የተሰወረ፤ በትምህርት ቤቷ ብቻ የቀረ መለስተኛ ታሪክ አለ።⌘

ኮረዳዋ ኤልሳ ከወራት በፊት ነበር አንድ ደብዳቤ የደረሳት። ልቅም ባለ የእጅ ጽሑፍ የተረቀቀ፤ የፊደላት ቅርጾች ተሞናሙነው የተከተቡበት የፍቅር ደብዳቤ ነበር። አንድ ዓይናፋር የሚባል የላይ ሰፈር ወጣት ነው

የጻፈላት። በሷ ምርኮ ታሞ ከወደቀበት እስከ ጠናበት ያለውን የውዴታ ውጣ ውረድ፡ በሚያውቃቸው የፍቅር ጥቅሶች አጅቦ እያላወሰ፣ እሱም በስሜት ዶፍ እየተላወሰ፣ በምን ዓይነት አሳር በዚያች ወረቀት ላይ እንዳሰፈረላት...ማን ባስረዳት?

ታዲያ ወረቀቱን ደብተሯ መሀል ተወሽቆ ነበር ያገኘችው ፡ ግር እያላትም አነበበችው። ማታ ማታ በአቶ በጋለ ኮሽኳሽታም ራዲዮ የምትሰማው የፍቅር ታሪክም መሰላት። ባጭሩ ባንቺ ፍቅር ልቤን ተነደፍኩኝ የሚል ተማጽኖ በቃላት ተሽሞንሙኖ ነበር የቀረበላት። እንዳገኘችው ደብዳቤውን ይዛ እየበረረች ወደነሜሮን ግቢ አመራች። በሩን ስትቆረቁር ያጋጣሚ ነገር ሆኖ ሜሮን ራሷ ከፈተችላት።

"ምንድነው ይሄ ሁሉ ፈገግታ?" አለች ሜሮን ከቅጥሩ በር ትከሻዋን እያሳረፈች፤

ኤልሳ ወሬዋን ሌላ ሰው እንዳይቀልብባት ይበልጡኑ ወደ ሜሮን ቀረበችና በአፍላ እድሜ ለዛ ... "የ... የፍቅር ደብዳቤ ተጻፈልኝኮ!" ስትል በጆሮዋ አንሾካሾከችላት።

"ምን?"

"ለይኩን የፍቅር ደብዳቤ ጻፈልኝ፤"

"የ...የኛ ትምህርት ቤት ሰቃዩ ለይኩን ነው?" አለች ሜሮን፤ ድምጿ ድንጋጤና መገረሟን ያሳብቅባታል።

"እረ በፈጠረሽ! ተይ ድምጽሽን ዝቅ አድርጊ ፡ ከቤት እንዳይሰሙሽ!" አለች ኤልሳ ፡ ወሬው እንዳይዳረስ በጣም ፈርታለች፤

ሜሮን እጅግ የናረ ደብዳቤውን የማንበብ ፍላጎት ስላደረባት ወደ ክፍሏ እንድትገባ አቻኮለቻት። ተያይዘው ወደ ውስጥ ዘለቁ። የነ ሜሮን ቤተሰብ ከነ ኤልሳ ቤተሰብ የተራራቀ የሀብት ደረጃ ነው ያለው። በሰፈሩ የመጀመሪያው ባለቀለም ቴሌቭዥን የገባው እነ ሜሪ ቤት ነው። የግንብ ጆጎል፣ ቆንጆ የጡብ ሰቀላ ቤትና አንድ መኪና አላቸው። በሰፈሩ መለኪያ የናጠጡ ሀብታም የሚባሉ አይነት መሆናቸው ነው። {በዱባይ ባለ ሐብቶች መለኪያ ደግሞ ያው... ሁሉም ነገር አንጻራዊ አይደል?}

ሁለቱ ኩብሎች ወደ ሜሮን ክፍል ገብተው በሩን ጠረቀሙ። "እና ለይኩን የምር የፍቅር ደብዳቤ ጻፈልኝ ነው ምትይኝ?" አለች ሜሮን፡ ኤልሳ ሽብልላ ከያዘችው ደብዳቤ ላይ ዓይኗን በጉጉት እያንከራተተች።

"አዎ! አይገርምሽም ድፍረቱ ፡ ደግሞኮ ባንቺ ምክንያት ማጥናት አልቻልኩም..ገለመሌ እያለ ያላዝንብኛል።"- ኤልሳ በለበጣ ሳቀች።

"አንቺ አትቀልጂ ! ልጁኮ ሰቃይ ነው። ትምህርት ቤቱ ራሱ ብዙ ጊዜ ሸልሞታል።"

"እንዴ? ታዲያ እኔ ምን አገባኝ?" ... "እሺ አሁን ደብዳቤውን ስጪኝ በናትሽ ላንብበው..." ኤልሳ ደብዳቤውን አቀበለቻት፤

ሜሮን የተሸበለለውን ወረቀት ዘርግታ ፊቷ ላይ ብዙ ስሜቶችን እያፈራረቀች አንበለበለችው።

*ይህቺ ሜሮን የተባለች ልጅ ከኤልሳ በ2 ዓመት ታንሳለች፤ ገና 16 ዓመቷ ነው፤ ግን በሳል ነች፤ እንደ 26 ዓመት ወይዘሪት ነው አስተሳሰቧ። ለዚህም ትምህርት ቤት ውስጥ ‹ትንሿ ሴትዮ› የሚል ተቀጽላ ስም ወጥቶላታል፤ መጽሐፍ ማንበብ ለጉድ ትወዳለች፤በአቅሚቲ አንዳንድ ጽሑፎችንም ትሞነጫጭራለች፤ በትምህርቷም ከአንድ እስከ አሥርኛ ደረጃ የምትወጣ አይነት ተማሪ ነች። ከሰው ጋር ግን ብዙ አትቀራረብም። ከኤልሳ በስተቀር የኔ የምትላት ጓደኛም የላትም።*

ምንም እንኳን የተወሰኑ የፍቅር ልቦለዶችን አንብባ ብታውቅም እውነተኛ ልብ የወለደውን የፍቅር ደብዳቤ ስታነብ ግን ለሷም ገና የመጀመሪያዋ ነበር። የጸሐፊውን ስሜት ወዲያው መረዳት ግን አልከበዳትም። የለይኩንን አደብና ምግባረ መልካምነት ስለምታውቅ የመልዕክቱን እውነተኛነትም አልተጠራጠረችም። አንብባ እንደጨረሰች ኤልሳን ቀና ብላ አየቻት - "አንቺ የምርም ልጁ ሳይንበረከክ አልቀረም፤" አለቻት፤ ስልል ባለ ድምጽ፤

"ባክሽ ሁሉም እንደዛ ነው የሚሉት! እሱ ቃላቶችን አሳምሮ በደብዳቤ መልክ ስለጻፈው እንጂ መንገድ ላይ አስቁመው የሚጨቀጭቁኝ ወንዶች ራሱ እንደዚህ ነው የሚያደነቁሩኝ..."

"ወይ ጉድሽ ፡ በቃ መልከኛ ሆነሽ ተሰቃየሽ አይደል?" አለች ሜሮን በስሱ እየሳቀች።

ኤልሳ ኩራት ቢጤ እየኮረኮራት… "ሜሪዬ ደግሞ… ቆይ እኔ ቆንጆ ነኝ እንዴ?" አለችና ፡ እምር ብላ ተነስታ የሜሮን ክፍል ካለው ቋሚ መስታወት ፊት ለፊት ተሰየመች፤

"እንዴ ምን ጥያቄ አለውና!" አለች ሜሮን ከኋላዋ እያየቻት፤ "ብለሽ ነው?" አለችና ኤልሳ ራሷን በመስታወቱ ውስጥ ማስተዋል ጀመረች፡፡ ጠይም፣ ቅምቅም ከንፈሯን ወደ ጉንጮቿ አሸሽታ ጥርሷን ፍልቅቅ ስታደርግ ፡ ሳቅ ስትል ገዳይ የምትባል አይነት፤ ቁመናዋ እንደ ሰንፔር[8] ልቦችን የሚያሸፍትላት እንስት መስታወቱን ነፍስ ዘራችበት፡፡ … "እውነትም ለካ ቆንጆ ነኝ!" አለች ኤልሳ ለራሷ፤

"እኔ ግን የዚህ ልጅ ነገር አሳስቦኛል! … የእውነት ያፈቀረሽ ይመስለኛል፤ ባንቺ ምክንያት ማጥናት አቃተኝ እያለሽኮ ነው! … ቆይ ቢወድቅስ?" አለች ሜሮን፤

"ታዲያ ምን አድርጊ ነው የምትይኝ?" …በራሷ መልክ እየታበየች የነበረችው ኤልሳ፡ ዘራ ሜሮንን በጥያቄ ተመለከተቻት፡፡

"ፍቅር ይታወቃል በእግር! ይባል የለ? ብታናግሪውና ብትረጂው መልካም ይመስለኛል፡፡"

"ያምሻል እንዴ? ፡ ሲጀመር ምኑም ደስ አይለኝም፤ ልብሱን እንኳን አይተሻል? ‹ዩኒፎርሙ› አሮጌ፣ የእረፍት ቀን እንኳን የሆነ አንድ ሸሚዝና ሱፍ ሱሪ አለው… ቀን በቀን እሱን ለብሶኮ ነው የሚወጣው…" አለች ኤልሳ በማናናቅ ለዛ፤

ሜሮን የኤልሳ መልስ አልጣማትም፤ "ምን ማለትሽ ነው ኤልሲ? ይሄንን ካንቺ አልጠብቅም ፡ ለይኩን ስንት ሰው ተስፋ የጣለበት ጎበዝ ተማሪ ነው፤ ጥሩ ልጅ ነው፣ ነገ ቀን ይወጣለታል፡፡ እንደዚህ አይባልም!"… በመጠኑ ተቆጣቻት፤

"የተስፋ እንጀራ ምን ይሠራል? ‹ከነገ ዶሮ የዛሬ እንቁላል ይሻላል› ይል ነበር ወንድሜ ፡ ነፍሱን ይማረውና፤" አለች ኤልሳ - ከሜሮን ጋር መከራከሩ ምንም አልጣማትም… አብራት ብዙም አልቆየች፤ ደብዳቤውን እንኳን ሳትቀበላት ረስታ በችኮላ ወጣች፡፡ ☒

8 ኅብሩ የእሳት ከፋይ የሆነ እንቁ ድንጋይ፤

ኤልሳ ከሄደች በኋላ ሜሮን ደብዳቤውን አጣጥፋ ከኮመዲኖዋ ውስጥ አስገባችና አልጋዋ ላይ በቁሟ ዘፍ አለችበት። ለደቂቃዎች ተንጋላ ብዙ ሐሳቦችን ስታወጣ ስታወርድ ቆየች። ኋላም በረጅሙ ተንፍሳ ከአልጋዋ ተነሳች። በቸልተኝነት ራመድ ብላ ከመስታወቷ ፊት ለፊት ቆመች… “ቆይ እኔስ ቆንጆ አይደለሁም እንዴ?” ብላ ለራሷ አንሾካሾከችና ምስለ-መንትያዋ ላይ አፈጠጠችባት። ቀላ ያለ ጉንጯ፣ ሥርጉድ የሚሉ ከናፍርት፣ ስልክክ ያለ አፍንጫ፣ ‹መርሜይድ[9]› መሳይ ሰውነት ያላት ውቢት ሴት ከመስታወቱ ውስጥ ተመልሳ ሜሮን ላይ አፈጠጠችባት። ሀዘኗ ግን ፊቷ ላይ ይነበባል። መስታወቱ ውስጥ ያለችውን ሜሮን ልብ ብላ ስታያት… “የኔ ምስኪን ጥያቄሽን አልመልስልሽ ነገር ድምጽ የለኝም!” የምትላት መሰላት።

⌘ ⌘ ⌘

ኤልሳ ያን ሰሞን የስለላ ሥራ ስትሠራ ከራርማለች። ለይኩን ማነው? እድል የምትሰጠው አይነት ወንድ ይሆን አይሁን ለማወቅ ጥራለች። በእርግጥ ከዚያ በኋላ ብዙ ነገር ተፈጥሯል፤ መገናኘትና መለያየት ተከስቷል። ትናንት ቦኖ ጋር ስለሱ ሲወራ የሰማችው ነገር ግን ተስፋዋን አድሶታል። በዚህ ስሜት ውስጥ እያለች ነበር፡ አንድ ህጻን ልጅ ከበር ላይ “ኤልሳ አለች?” ብሎ ሲጣራ የሰማችው። ማን ሊጠራት እንደሚችል እሙን ነው። መለሰችለት፤ “አቤት፤”

⌘ ⌘ ⌘

## ✍…ያፍቃሪዋ ማስታወሻ

“ሳልነግረው ከረምኩኝ። አበቦች እየፈኩ ረገፉ፣ ማራኪ የሰማይ ጣዎሶች[10] ላይበሰብሱ ሞቱ፣ የፀሐይ አንዲት ዓይን ተከደነች።

ሳልነግረው አረፈድኩኝ፤ አዎ ፍርሃቴማ ትንሽ በዛ… አሁን የሱ ልብ ወደ ሌላ እንስት ተሰዷል። የመስተፋቅር ክልሉ ተደፍሯል። ምን አይነት ደካማ ወንድ ቢሆን ነው እንዲህ ቶሎ እጅ የሰጠው? እውነትን ቻላ ብሎ በዓይን ወለድ ስሜቱ የተሸነፈው? …ግንኮ…ግንኮ እሱ ምንም አላጠፋም፤ አልፈርድበትም፤ በልቤ የሸሸግኩትን አያውቅ ነገር መልአክ አይደለ። … ብቻ ተስፋ አልቆርጥም፡ ነገ ይዞ የሚመጣውን ማንስ ያውቃል? …

---

9 በብዙ አፈ-ታሪኮች ውስጥ የምትገኝ ግማሽ ሰው ግማሽ ዓሣ የሆነች የባህር ፍጥረት፤

10 ሰማያዊ ራስና አንገት ያለው፤ ዥራቱ እንደ አረንጓዴ ወርቅ የሚያብለጨልጭ የወፍ አይነት፤

ለጊዜው ደስታው ደስታዬ ይሁን። የኔ ብቻ ሁን ብዬ አላስጨንቀውም። እኔው ህመሜን ታቅፌ ስብሰለሰል ልኑርለት… ይሁንለት፤ እሱን፣ ውድዬን ለዘመናት ደስስ ይበለው።

⌘ ⌘ ⌘

ከእሥር ያመለጠው ለይኩን ወዳገኘው ቤት እንደምንም እየተንገዳገደ ደርሶ በሩን አንኳኳ። ባለቤቶቹ ገበሬ መሆናቸውን ገምቷል ፡ ልቡ ነግሮታል … ግን ገበሬም ላይሆኑ ይችላሉ። ልብ ሁሌ የሚናገረው እውነት ነው ወይ? ምናልባት የገበሬ ቀበሌ ማህበሩ የጥበቃ ፖሊስ ቤት ሊሆኑ ይችላል። የተሸረካከተ የእሥር ቤት ልብስ፣ ዘበተሎ ያደረገ፤ በደም የተጨማለቀን ሰው ማንስ ሊያምነው ይችላል? ሌላ አማራጭ ግን የለውም፤ ጠኔ፣ ድካምና ህመም አሸንፈውታል ፡ የሰው ልጅ ‹ጅስም›[11] ከብርታቱ ደካማነቱ ያመዝናል ፡ በተለይ ለደዌና ለርሀብ እጅ ለመስጠት ፈጣን ነው።

በድጋሚ ሊያንኳኳ ሲል በሩ ተከፈተ፤

የእድሜ ሸንተረር ፊታቸውን የዳሸን መልክዓ ምድር ያስመሰለው አረጋዊ ወጡና የእጅ ባትሪያቸውን እሱ ላይ በግ አደረጉት። ለይኩን በክንዱ ዓይኖቹን ከፍላፃው ተከላከለ ፡ ይሄ ሁሉ ብርሃን ምንድነው? / አቅም ቢኖረው ተመልሶ ይሮጥ ነበር።

"የፈጣሪ ያለ! ምን ጉድ ገጥሞኽ ነው ልጄ?" አሉት፤ የድምጻቸው አባታዊ ለዛ፣ በተለይም ልጄ የሚለው ቃላቸው ግን ለይኩንን የሆነ አይነት ሰላም እንዲሰማው አደረገው። {መልካም ንግግር ምን ያኽል ልብን ታረግባለች? ክፉዋስ ምን ያኽል ትሰብራለች?}

"አ…ባ አ..ባቴ ፡ እባ..ክ..ዎትን ይር…ዱኝ…እኔ.." ከዚህ በላይ ከንፈርና ምላሱ አልታዘዝ አሉት፤ ላንቃና ትናጋው ባይተዋር ሆኑበት፤ የገዛ ትንፋሹ ያንቀው ጀመር። ለካ መናገርም አቅቶታል። ወዲያው እግራቸው ሥር ዝርግፍ አለ ፡ መቆምም አልሆነለትም።

አረጋዊው ገበሬ ሸብረክ ብለው ጭንቅላቱ መሬት ሳይነካ አተረፉት፤

…ተሸክመው ወደ ውስጥ ሲያስገቡት በሰለምለምታ አይቷል። ቁስሉን ሲያሹለት፣ ገላውን ሲያጸዳዱለትና ልብሱን ቀደው ሲያወልቁለት፣

11 በአረብኛ ሥጋዊ አካልን የሚገልጥ ቃል፤

ሲያጥቡት፡ ሌላ ልብስ ሲያለብሱት፤ የገበሬ ቃና ያለው ሾርባ ሲያጠጡት፡ እንደ ሰመመን ሆኖ ይታወቀዋል።

በማግስቱ ጥዋት ሙሉ በሙሉ ወደ አቅሉ ሲመለስ፡ ራሱን በጠፍር አልጋ ላይ ተንጋሎ ነበር ያገኘው። በማለዳ ሲነቃ ከማታው የስቃይ ሽሽት ተቃራኒ የሆነ ሰላማዊ መንፈስ አረብቦበታል። ያቺ የተረገመች ሚስማር የወጋችው ቦታ ላይ ከሚሰማው መጠዝጠዝ በስተቀር ደህንነት ተሰምቶታል።

"ደህና አደርክ ልጄ?" የሚል ጥያቄ ከክፍሉ ውስጥ ተሰማ፤ ይሄን ትንግርታዊ ድምጽ ያውቀዋል። እንደ ውኃ ጥም የሚያረካ ድምጽ ነው።

"እግዚአብሔር ይመስገን፤" መለሰ ለይኩን፤ ቀጥሎም ድምጹ ወደ መጣበት አቅጣጫ አንገቱን አዞረ። ለካ አረጋዊው ሰው፣ መልካሙ ገበሬ ከክፍሉ በስተግራ ጥግ በርጩማ ላይ ተቀምጠው እስኪነቃ እየጠበቁት ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ በቅጡ ተመለከታቸው፤ ጥጥ መሳይ ሪዛቸውና ነጭ ጋቢያቸው ላይ የማለዳ ፀሐይ ነጸብራቆች ይደንሳሉ ፡ ያበራሉ ፡ ብቻ መልአክ ቢጤ መስለው ታዩት። ይህኚን ክንፍ አልባ ተራዳኢ ለሱ ብሎ ጌታ ልኳቸው ይሆን ሲልም ጠረጠረ። *{ከብት የሚያረባ፣ ጎጆ ቤት ቀልሶ ገጠር ውስጥ የሚኖር መልአክ ይኖር ይሆን?}*

"አሁን ህመሙ ቀለል ብሎልኻል?"

"አዎን አባቴ፤ ይመስገነው፡ አሁን ደህና እንደሆንኩኝ ይሰማኛል። ትንሽ ቁስሌ ብቻ ነው የሚጠዘጥዘኝ፤" አለ ለይኩን፤

"መልካም ነው፤ ማታ አንተን ፈልገው መጥተው ነበር።" አሉት ወደ መስኮቱ አቅጣጫ እያማተሩ። ለይኩን ልቡ ቀጥ አለች።

"እነማን?"

"ዋሸዋቸው ... መዋሸት ነበረብኝ፤ እሥር ቤት ተመልሶ ለመሄድ የሚያስችል አቅም ላይ አልነበርክም። መንገድ ላይ ትሞትባቸው ነበር። ውስጤ ደግሞ እንድትሞት አልፈቀደልኝም ፡ እናም ዋሸዋቸው። እንዲህ አይነት ሰው አላየንም ብዬ ሸኘኋቸው።" አሉትና በዓይኖቻቸው ገረመሙት።

"አባ..." ለይኩን ኃፍረት ሸብቦት ምንም መመለስ አልቻለም። የአልጋውን ጫፍ እየነካካ አጎንብሶ ቀረ።

"ግን ምን አጥፍተህ ነው ታስረህ የነበርከ? እንዴትስ ከእሥር ቤት ልታመልጥ ቻልክ?" ...አሉት በአጽንኦት።

"ረጅም ታሪክ ነው አባቴ። እም..." ለይኩን ያቅማማ መሰለ፤

"እንግዲህ እውነቱን እንደምትነግረኝና እንደማትዋሸኝ እርግጠኛ ነኝ።" አሉ አረጋዊው፤

"ኧረ በፍጹም አልዋሽዎትም አባቴ ፡ ለእርስዎ እንዴት ብዬ እዋሻለሁ?..." {ውለታቸው ባይኖር እንኳን ግርማ ሞገሳቸው በራሱ ሰውን የሚረመርም አይነት፡ ግድንግድ ድባብ አለው፡ ለመዋሸት የማይመቹ ክቡድ ፍጡር ናቸው።} ...

"ማለት ታሪኩ ረዘም ያለ ስለሆነ ጊዜዎን እንዳልሻማብዎት ብዬ እንጂ!" አላቸው ለይኩን እንደ ማፈር እያለ።

"ምንም ችግር የለም ልጄ ፡ ታሪክ የመስማትና የመናገር እድሜ ላይ ያለሁኝ ባዘቶ ሽማግሌ መሆኔን ልብ አላልክም ልበል? ፡ ግድየለህም ቀጥል፤ እንዲያውም ከልጅነትህ ጀምሮ ያለውን ታሪክህን እንድታወጋኝ ነው ፍላጎቴ..." አሉት እጃቸውን ምርኩዛቸው ላይ፣ አገጫቸውን ደግሞ እጃቸው ላይ ደራርበው እየተመቻቹ።... ለይኩንም ታሪኩን ያጫውታቸው ጀመር፤

⌘ ⌘ ⌘

ለይኩን አንገት ደፊ ልጅ ነበር። ከመድፋቱ የተነሳ ከማጀራቱ ጎበጥ ብሎ የሚራመድ፡ ትምህርት የሚገባው ፡ ቀለሜ የሚባል አይነት ተማሪ። አንደኛ መውጣት ልማዱ ፡ 6ኛ ክፍል 2ኛ ወጥቶ ትምህርት ቤቱ በሙሉ የደነገጠለት፤ ሚኒስትሪ 99 በዚያ ጊዜ ያመጣ ተማሪ ነበር። ባስኳላው ትምህርት ዘልቆ መሐንዲስ የመሆን ህልም ነበረው። በዚህም ሳይረካ ገና በእድሜው ማለዳ ጋራዥ ቤት እየሄደ እጁን ያፍታታ፤ ከትምህርትና ከጥናት ሰዓት ውጪ ባገኘው ክፍተት ሁሉ እየሠራ፤ ካለ አባት ለብቻቸው ደፋ ቀና ብለው ያሳደጉትን እናቱን የሚያግዝ...ህልም ያለው ልጅ ነበር።

| ልጅት ወደ ህይወቱ ስትመጣ ግን ሁሉም ነገር ተቀያየረ!

አስራ ሁለተኛ ክፍል ደረሰ፤ ያቺን ጠይም ልጅ ሲያያት ልቡ ስንጥቅ አለ። አይታው ፈገግ ስትል ምን የሚሉት መግነጢስ? የአንድሮሜዳ ቀስት ወጋው፡ የኮከቦች ግጭት ፡ ልብ በርባሪ በርባሮስ አገኘው። ከዚያ በኋላ

በቃ ባያት ቀጥር ውስጡ ርብሽብሽ፡ ስትጠፋ ድብርብር ፣ ድብት ይለው ዠመር። ዛሬ ነገ ሳይል ማንነቷን አጠያየቀ | ኤልሳ ትባላለች ፣ ከእሱ በ4 ዓመት ታንሳለች ፣ የ8ኛ ክፍል ተማሪ ነች።

ስለ ኤልሳ ብዙ ባወቀ ቁጥር ግን የውስጡ ህመም ባሰ እንጂ አልዳነም። አንገት ደፊው ልጅ አንገቱን ደፍቶ መብሰልሰል አበዛ። እያናግራት ነገር እንኳንስ የነደፈችውን ንብ ይቅርና ወንድ እኩዮቹን እንኳን ለመቅረብ የሚፈራ አይነት ብላቴና ነው። ብቻውን ብዙ ተጎዳ። ትምህርቱ አስጠላው ፣ ጋራዥ ሄዶ መስራት ተወ ፡መሐንዲስ መሆን ተቀዳሚ ህልሙ መሆኑ ቀረ። ማታ በህልሙ ፣ ቀን በቀልብያው ኤልሳ ብቻዋን ነገሰች። ከቤቱ እስከ ትምህርት ቤቱ | ከአርብ እስከ ጁምዓ ኤልሳና ኤልሳ ብቻ።

እንደ ቀልድ የግል ህመሙ ሆና ወራቶች አለፉ። ረዘም ካለው አገጩ ላይ ካለእድሜው ጺም ውርር አደረገው። በጥናት የሞጨሞጩ ትናንሽ ዓይኖቹ በእንቅልፍ እጦት ይበልጥ ጠበቡ። ዩኒቨርሲቲ የመግቢያ ፈተናውን ሊወስድ ጥቂት ወራት ብቻ ቢቀሩትም ነገር ዓለሙን ትቶት ቆየ። እናቱ ወ/ሮ ብዙወርቅ መጨነቅ ጀመሩ፤ “ልጄን ምን ነካው?” አሉ። በጎበዝነቱ የተመቀኙ ሰዎች ምናምን አሠሩበት ይሆን? ሲሉም ጠረጠሩ። የሆነውን ሳይታክቱ መጠየቃቸውን ግን አላቆሙም ነበር።

“ልጄ ምን ሆነኻል?” ይሉታል፡ ዓይኖቹን በእናት ስስት እያዩ፤

“ምንም አልሆንኩም እማ!”

“እንዴት አልሆንኩም ትለኛለኽ? ምግቡን ቀማምሰህ ነው የምትተወው፤ እንደ ድሮው አታወራኝ፡ አታስቀኝ። ምን አስነክተውህ ይሆን የኔ ልጅ?” ከከረጢቱ ሞልቶ አልፎ እንባ በዓይናቸው ተንቆረዘዘ፤

“እንዴ እማ ደሞ ምን ማለትሽ ነው? ... ዋናው ፈተናችን እየደረሰ ስለሆነ ትንሽ ፍርሃት ቢጤ ይዞኝ ነው።”

“እሄሄ ... ይሁና እስኪ! ለወትሮ ምንም ፈተና ቢደርስብህ እኔን ለማጫወት ጊዜ አጥተህ አታውቅም ነበር። እሱ መድሐኒዓለም ይጠብቅህ።” አሉና በነጠላቸው ዓይናቸውን እያደራረቁ ወደ ሥራቸው ተመለሱ። እኚህ እናት ያን ሰሞን ልባቸው ላፍታም አላረፈም።

ለይኩን ትምህርት ቤትም ቢሆን ብዙ ጓደኞች የሉትም። አስተማሪዎቹ ግን በጣም ይወዱታል። አንድ አስተማሪ ከተማሪው ሊፈልግ የሚችለው፤

ከዚያም በላይ ያለው አይነት ተማሪ ነበር። ነገ ደረታቸውን ነፍተው "እኔ ነኝ ያስተማርኩት!" እያሉ ሊጀነኑ የሚችሉበት አይነት ተማሪም ነበር። ነበር ባይሰበር።

ታዲያ አስተማሪዎቹም ቢሆኑ ከጥቂት ወራት አንስቶ በትምህርት ቤት ውስጥ ከሚታወቅበት ባህሪው ለየት ያለ አይነት ለይኩንን መታዘብ ጀምረዋል። በሙሉ ትኩረት ትምህርቱን መከታተል ትቷል። የፈተናው ውጤትም ማሽቆልቆል ይታይበታል።

አንድ ቀን የፊዚክስ አስተማሪያቸው መምህር እስጢፋኖስ ስም እየጠራ የፈተና ውጤታቸውን እየሰጠ ነበር። ካንድ የፈተና ውጤት ላይ ሲደርስ ግን ድንግጥ አለ። ወንበሩን ስቦ ተቀመጠ። ወረቀቱን ከሌሎች ውጤቶች ለየና መልሶቹን እያመሳከረ ድጋሚ አረመው፤ ውጤቱ ግን አልተቀየረም። ተማሪው 45 ከመቶ ብቻ ነው ያመጣው፤ የውጤቱን ባለቤት ስም በድጋሚ አየው ፡ ለይኩን ተስፋሁን። ከተቀመጠበት ተነሳና ወደ ተማሪዎቹ ዞረ።

"ለይኩን ተስፋሁን..." ሲል ተጣራ... ቸብ ፡ ቸብ ፡ ቸብ ፡ ቸብ ክፍሉ በጭብጨባና ፉጨት ተሞላ። መምህሩ ሲጠራው "አጨብጭቡለት፤" አላለም ፡ ተማሪው ግን የሱ ስም ሲጠራ ማጨብጨብ ለምዷል፤ በድግግሞሽ ምክንያት ስሙን ከጭብጨባና ፉጨት ጋር አቆራኝቶታል[12]። መምህር እስጢፋኖስ ምንም ሳይናገር የፈተናውን ወረቀት አጥፎ ለለይኩን አቀበለው፤ የአብዛኞዎቹን ጥያቄዎች መልስ በአቦ ሰጥ የሞላው ለይኩንም፡ ጉዱን ያውቃልና አንገቱን እንደደፋ ተቀበለ።

ክፍለ-ጊዜው አልቆ ተማሪዎች ለእረፍት ሲወጡ መምህር እስጢፋኖስ ለይኩንን ለብቻው ሊያናግረው እንደሚፈልግ ነገሮት ወደ ቢሮ አቀና።

|"ምነው ለይክ? ምን ተፈጥሮ ነው?" ... ገና ከመግባቱ በጥያቄ ነበር የተቀበለው።

"ምንም አልሆንኩም ቲቸር ፡ ለ... ለምን ጠየቁኝ?"

"ለይኩን! እኔኮ ለዓመታት አስተማሬኻለሁ። አንድም ቀን ፈተና

---

12 አንጎላችን እንደ ኮምፒዩተር ፕሮግራምና ‹ፓተርኖ›ችን ያስቀምጣል፡፡ በተደጋጋሚ ያሰብናቸውን ሐሳቦች፡ በተመሳሳይ ጊዜ ከተሰማን ስሜቶችና ካደረግናቸው ድርጊቶች ጋር አቆራኝቶ ይመዘግባል፡፡ ለዚህ ነው በጣም ስሜታዊ የነበርንባቸውን ገጠመኞች በዝርዝር የምናስታውሳቸው፡፡

ስትወድቅ ግን አይቼም ሰምቼም አላውቅም። ባይገርምህ አንተ ‹ኤክስ› የሆንከው ጥያቄ ሳገኝ ጥያቄው ስህተት ሊሆን ይችላል ብዬ ‹ቼክ› ያደረግኩበትን ጊዜ ሁሉ አስታውሳለሁ። ባንዲት ጉዳይ ተወጥሬ ይሄንን ፈተና ሌላ ሰው ነበር ያረመላችሁ። ዛሬ ክፍል ውስጥ ያመጣኸውን ውጤት ሳይ ግን በጣም ነው የደገጥኩት፤ ለዚያም ነው ደግሜ ‹ቼክ› ያደረግኹት፤… ለማመን ነው የከበደኝ …የፈተናው ቀን ግን ሰላም ነበርክ? ፡ ማለት ያመመክ ነገር ነበር?"

"እረ አላመመኝም ቲቸር፤ በጣም ደህና ነበርኩኝ።" አለ ለይኩን የክፍሉ ወለል ላይ እንዳቀረቀረ፤

"እሺ ቤተሰብ ውስጥ ያጋጠመህ ችግር አለ?"

"በፍጹም የለም።"

"ለይኩን ‹ፕሊስ› ምንም ሳትዋሸ ንገረኝ። አንተ እንደ ትምህርት ቤት ተስፋ የጣልንብህ ተማሪያችን ነኽ። እኛን ታስጠራለህ ብለን የምናምንብህ ተማሪ፡ ሀገር አቀፍ ፈተና ጥቂት ወራት ሲቀሩት እንደዚህ አይነት ውጤት ካመጣኽ ለኛም ትልቅ ውድቀት ነው። ስለዚህ ችግርህን ንገረኝና በቻልኩት ሁሉ ልርዳህ።"

"የእውነት አምሰግናለሁ ፡ ግን ባሁኑ በደንብ ስላላጠናሁኝ ነው፤ በቀጣይ አስተካክላለሁ።" አለ ለይኩን አንገቱን እያወዛወዘ፤

"እንግዲያውስ ‹ኤኒ ቲንግ› ሚቸግርህ ነገር ካለ አናግረኝ እሺ!"

"እሺ ቲቸር፡ አመሰግናለሁ።" ብሎ ተነስቶ ወጣ፤ ለይኩን ያን ቀን ቤት ሄዶ ለረጅም ሰዓታት ለብቻው ቁጭ አለ። የሐሳብ መዓቶች በውስጡ ተርመሰመሱ። ሳይነግራት ከዚህ በላይ መቆየት እንደማይችል ገብቶታል። ትምህርቱ፣ እናቱ፣ ህልሙ … ሁሉም አደጋ ላይ ወድቀዋል። ነግሯት ካላራገፈው ይሄ ሸክም እየጣለው ነው። በአካል ደፍሮ ሊነግራት ግን እንጥፍጣፊ አቅም አልነበረውም። በዚህ አጣብቂኝ ውስጥ እያለ ድንገት አንድ ሐሳብ ከአእምሮው ተሰነቀረ ፡ ደብዳቤ።

በርግጥም ያለው ብቸኛ አማራጭ ደብዳቤ መጻፍ ብቻ ነበር። እንደ ውዳሴ ተጠበበት፤ እንደ ማህሌታይ ተክኖበት አንድ ገጽ ደብዳቤ አረቀቀ። ቀጣዩ ፈተና ደግሞ ደብዳቤውን ለሷ ማድረስ ሆነና አንድ ሳምንት ፈጀ። ከከፍተኛ ጥንቃቄና መርበትበት በኋላ ነበር ደብዳቤው ታጥፎ የኤልሳ

ደብተር ውስጥ የተሰተረው።

ያን ሰሞን ጉጉትና ፍርሃት ለይኩን ላይ ተካቡ። አይታው ይሆን? ከደብተሯ ወድቆ ይሆን? ሌላ ተማሪ አግኝቶ አንብቦበት ይሆን? ... ልቡ በፍርሃት ይርድ ያዘ። የነፍሱን ውስዋስ የለደሰበትን ገጽ ሌላ ተማሪ አንብቦበት፡ እየሳቀበት ቢሆንስ? ብሎ ራሱን ይጠይቃል መልሶ ደግሞ ሌላ ሰው አግኝቶት ቢሆን ኖሮ እስካሁን በትምህርት ቤቱ መሳቂያ ሆኜ ነበር ፡ ስለዚህ እሷ ጋር ነው ያለው ብሎ ይጽናናል። እሺ ግን አንብባው ይሆን? የሚለው ጥያቄው ደግሞ ይመጣል። አንብባው ከሆነስ ለምን እስካሁን ዝም አለች? ሌላ ጥያቄ ደግሞ ይተካል። እንደዚህ እያለ ለቀናት ብቻውን ባዘነ።

በሰምንቱ| ለይኩን በብዛት እንደሚያዘወትረው ሁሉ የእረፍት ሰዓቱን ጠብቆ ከኳስ ሜዳው ትይዩ ያለው የሲሚንቶ ሊሾ ደረጃ ላይ ቁጭ ብሎ ነበር። ይሄ የሰርክ ልማዱ ነው ፡ ታስሮ የተለቀቀው ታዳጊ ተማሪ እየተንደረደረ ከክፍሉ ወጥቶ፡ እንደ እንቦሳ ሜዳው ላይ ሲዘልና ሲቦርቅ ማየት ይወዳል። ከመጫወት ይልቅ የሚጫወቱ እኩያና ታናሾቹን ማየት በጣም ያስደስተዋል።

|በሰማያዊ የደንብ-ልብስ የተዋቡ አያሌ የአፍሪካ አንድነት ተማሪዎች፡ እንደ ሰማያዊ ጉንዳን ሜዳው ላይ ሲተሙ፤ ሴቶቹ በቡድን በቡድን አጀብ ብለው ሲያውካኩ፤ ወንዶቹ በመንጋ አንዲትን ኳስ ሲያባሩ፤ የጎሉ መረብ ሁነኛ ቋሚ ስለሌለው *"ጎሉ ገብቷል! አልገባም!"* እያሉ ሲነታረኩ፤ ሻይ የሚጠጡት፣ ፓስቲ የሚገምጡት ፡ የልጅ ሐብታሞቹ ደግሞ ወደ ት/ ቤቱ የሻይ ክበብ ሲያቀኑ ሌሎቹ የልጅ ድሃዎች ለሃጫቸውን እያዝረበረቡ ሲጎመዡ| ሁሉንም ትዕይንት ቁጭ ብሎ መታዘብ ይወዳል። ዛሬም ይህ ውብ ድባብ ቀጥሏል። የልጅ ጥበበኞች ማብቀያ ከሆነው የት/ቤቱ ሚኒ-ሚዲያ ግጥምና አጭር ጭውውትን አስከትሎ የአብርሽ ዘ-ጌት *"ዝም ስል ተረጂኝ"* የሚለው ሙዚቃ ተከፈተ... ♫ *"ተይ ተይ አንቺ ልጅ ተይ... አንቺ ልጅ ተይ...*

*ዝም ስል ተረጂኝ ይቅርብን ንግግር*

*ይደረጋል እንጂ አይወራም ፍቅር፣*

*ውዴ ፍቅሬ ማሬ... ወደድኩሽም ጃጀ*

*ፍቅርን መግለጫው ቃላቱም አረጀ፤*

*... ቃላቶች አለቁ፣ አቅም አነሳቸው*

*ፍቅርን ለመግለጸ ፈሰሰ መቅኔያቸው*

*ተይ ተይ ምን ልበልሽ ምን ልበልሽ ሆዴ?*

*መቼም ሴት ነሽና አትሰንፊም ለዘዴ፤"*

ለይኩን ሙዚቃውን እያጣጣመ ሳለ፡ አንዲት የደንብ-ልብስ ሹራቧን አውልቃ ወገቧ ላይ ሸብ ያደረገች፤ ከላይ ነጭ ሸሚዝ ከሥር ደግሞ ሰማያዊ ጉርድ ቀሚስ የለበሰች ተማሪ ወደሱ አቅጣጫ ስትመጣ አያት። እየቀረበችው በመጣች ቁጥር መልኳን መለየት ጀመረ... *ያውቃታል።* ልጅቱ ቆንጆዬ ናት። ምጥን ያለ ቆንጆ መልክ አላት። በተለይ ዛሬ ከጉርድ ቀሚሷ ሥር የሚታይ፡ ቀይ መንደሪን መሳይ ባቷ ዓይነ ገብ ነበር፤ እግሯ ያምራል። ለጋ ወጣት ናት... ሥሟን ለማስታወስ ሞከረ ፡ ተሳካለት ፡ ሜሮን፤

በቀጥታ እየተራመደች መጥታ ከአጠገቡ ተቀመጠች፤

"ሰላም ለይክ?"

"ደህና ነሽ ሜሮን?"

"አለሁኝ፤" አለችና ጣቶቿን አጠላልፋ ወደ ሜዳው ዞረች። ለጥቃም "ይህቺ አሪፍ ቦታ ነች አይደል?... እዚህ ቁጭ ስትል ብዙ ነገር ይታያል..." አለች ኳስ ሜዳው ላይ የተበተኑትን ተማሪዎች እያማተረች።

"አዎ ይመቻል... እኔ ብዙ ጊዜ ወደዚህ መምጣት አዘወትራለሁ።"

"አውቃለሁ፤" አለች ሜሮን። ሁለቱም ሜዳው ላይ ቡዝዝ ብለው ቀሩ። *አኩዮቻቸው ይፈነጥዛሉ ፡ ሳቅና ደስታ እንደ ንግስ ቀን ቄጤማ ተነስንሷል፣ ፍቅር እንደ አደይ ተበትኗል። ባያልፍ የሚያሰኝ የልጅነት ውበት ሞልቶ ተርፏል።* ሜሮን በረጅሙ ተነፈሰች *"ለማንኛውም ዛሬ ስለ ኤልሳ ላናገርኽ ነው የመጣሁት።"* ስትለው የለይኩን ደረት አስራ ሁለት ቦታ ስንጥቅ አለ። መተንፈስ ሥራ ሆነበት ፡ አየር አልወጣ አልገባ ብሎ ስንቅር! *{ትንሹ ሣንባም ለካ ትልቅ ፋብሪካ ነው። ጭስ አልባ ኢንዱስትሪ ☺}*

"ስ... ስለ ኤልሳ ምን?"

"አዎን ኤልሳን ስለማፍቀርህ ላወራህ ነው የመጣሁት፤ ደብዳቤህን አንብቤዋለሁ።"

ደነገጠ፤ "ወ... ወድቆ አግኝተሽው ነው?" አላት ፡ ለይኩን ተነስቶ ለመሄድም አስቦ ነበር።

"አይ... እንደዛ አይደለም፤ ራሷ ነች አምጥታ ያስነበበችኝ፤" አለች ሜሮን ፡ በመጠኑ ተረጋጋ፤ "የእውነትም ግን ታፈቅራታለኸ?"

"...አዎን፤" አንገቱ እንደደፋ መለሰና መሬቱ ላይ ትርጉም አልባ ቅርጾችን በስንጥር ነገር መሞነጫጨረ ያዘ፤

"እ...ሺ ስለዚህ አንድ ነገር ማድረግ አለብን፤ በጣም እየተጎዳክ እንደሆነ ይሰማኛል።" አለች ሜሮን በጨረፍታ እያየችው፤ ለይኩን መልስ አልሰጠም ፡ ራሱን ክንዱ ውስጥ ቀብሮ ሙንጭርጭር አብስትራክቱን ፡ ለጋ የፍቅር ጠልሰሙን መሳል ቀጠለ ፡ ዝምታው ግን ለሜሮን በቂ መልስ ነበር።

"ለምን ግን በአካል አታናግራትም?"

........................ *"እ... እፈራታለኋ!"*

...ተማሪዎቹ ሜዳው ላይ መቦረቃቸውን ቀጥለዋል። የእረፍት ሰዓታቸው ሊጠናቀቅ 3 ደቂቃ ቀርቶታል። አንድም ማይክሮ ሰከንድ አትባክንም ... እያንዳንዷ ቤሳ ጊዜ ደስታ ይዘገንባታል - *{ያኔ በ‹ሰልፊ›ና በፎቶ የሚባክን ደቂቃ አይገኝም። በየቅጽበቱ መኖርና መደሰት እንጂ መታየት የዚያኔ ብዙም አሳሳቢ አልነበረም።}*

ሜሮንና ለይኩን ሳይነጋገሩ ቀሪዎቹ 3 የእረፍት ደቂቃዎች አለፉ። ወደ ክፍላችሁ ግቡ የሚለው ደውል አቃጨለ። ሜሮን ከተቀመጠችበት ተነሳችና ቀሚሷን አረገፈች። ትንሽ አሰብ አደረገች - ተቀጥላም አጎንብሳ ለይኩንን ቁልቁል እያየችው፤

"...በኋላ ሰባት ሰዓት፡ እዚሁ ቦታ ከኔ ጋር ተገናኝተን ስለ መፍትሔው እናወራለን።" ብላው መልሱንም ሳትጠብቅ ሄደች።

⌘ ⌘ ⌘

...ታዲያ ምሳ ሰዓት ሲለቀቁ 7 ሰዓት ሳይሆን ቀድሟት በቦታው የተገኘው ለይኩን ነበር። በእውኑ ሜሮን የተባለች ልጅ ደግነት ገርሞታል። ከሰሞኑ ስቃዩ ላይ ትንሽዬ ሻማ ያበራች የመጀመሪያዋ ሰው ሆናበታለች። ዛሬ ቀጥራው ግን አረፈደች፤ እዚያው ደረጃው ላይ እየጠበቃት 7 ሰዓት ሞላ ፡ 5 ደቂቃ አለፈ። 7 ሰዓት ከሩብ ሲሆን ግን አትመጣም በቃ ብሎ ተስፋ ቆረጠ። ቤት ሄዶ ምሳ መብላት እንዳለበት ወሰነናም ከተቀመጠበት ተነሳ። ደብተሩን አስተካክሎ ለመሄድ እየተዘጋጀ ሳለ ሜሮንን ከሩቁ አያት ፡ እነሆ ካጠገቧ ደግሞ ሌላ ሴት አብራት ነበረች።

ሜሮን ብቻዋን አልመጣችም።

* * *

## ምዕራፍ ሦስት

# ዝምታ

ከኤረር ተራራ[13] ግርጌ ከሚገኙ ሥውር ዋሻዎች የተሰየሙ አንድ አባት በዚህ ትውልድ አኪያሄድ ተክዘው፡ መፍትሔውን እየወጠኑ፡ መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ አራትን ከፍ ባለ ድምጽ ያነበንባሉ…

"2፤ እናንተ የሰው ልጆች፡ እስከመቼ ድረስ ልባችሁን ታከብዳላችሁ?

3፤ እግዚአብሔር በጻድቁ እንደተገለጠ እወቁ፤

እግዚአብሔር ወደእርሱ በተጣራሁ ጊዜ ይሰማኛል።

4፤ ተገሰጹ፤ ኃጢያትንም አታድርጉ፤ በመኝታችሁ ሳላችሁ በልባችሁ አስቡ፤

ዝም በሉ።"

⌘ ⌘ ⌘

ዶ/ር ሶፎኒያስ የዝምታን መገኛ ፈልጎ፤ የሥራ እረፍት ወስዶ ከወጣ በኋላ አየሁት የሚል ሰው አልተገኘም።

እሱ እቴ፡ ዝምታን ለመለማመድ ብሎ ቦታ ለማግኘት አልደከመም ፡ ቤቱ ገባ ፡ በሩን ቆለፈ - አበቃ - ራሱን አገለለ፤ ተወሸበ። ጥዋት ቤት ለማሰናዳትና ምግብ ለማብሰል ከምትመጣው ተመላላሽ የቤት ሠራተኛው በስተቀር ማንም ሊረብሸው እንደማይችል ገምቷል። ዝምታን የማግኘት ጉዞ በግሉ ለመወጣትም ወስኗል። የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናት ትንሽ ከብደውት ነበር። እስከ ሦስተኛው ቀን ድረስ ቁጭ ከማለትና ከመተኛት በቀር ሌላ

13 በድርሳነ-ዑራኤል መሠረት የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ሥፍራ ኤረር ነው።

ያደረገውም ብዙ ነገር አልነበረም።

በሦስተኛው ቀን ግን ከቤቱ ጎን ካለ ግዙፍ የጥድ ዛፍ ሥር ሄዶ ቁጭ አለ ፡ ዓይኑን ጨፈነ። ነጭ ሙሉ ቱታውን ለብሷል፤ ፎጣ አገልድሟል። ዛፉ ሽው.. ሽው.. እያለ ከበላዩ ያለውን አየር ሲያምስ ይታወቀዋል። ዶ/ር ሶፎኒያስ ዳግም ምን ማድረግ እንደፈለገ ራሱን ጠየቀ? ... ራሱም መለሰ ፡ ግቡ ዝምታን መረዳት እንደሆነ አጸመረ። አሁንም ንፋሱ በዙሪያው እንደሚላወሰው ሁሉ በሐሳቡ ይላወስ ገባ።

ቀስ በቀስም ስለ ዝምታ ማስተንተን ዠመረ ... ዝምታ ምንድነው? ሰው ለምን ዝምታን ይፈልጋል? ሁላችንም ዝም ስንል በዝምታችን ውስጥ የቀበርናቸው ምክንያቶች የሉም ወይ?... እርግጥ የዝምታ አንዱ መሰረት ጸጥታ ነው:: ጸጥ ማለት ደግሞ ከባድ ክህሎትን ይሻል:: ጸጥታ ታላቅነት ነው፤ ታላላቅ ኃይላት ጸጥ ያሉ ናቸው:: የመሬት ስበት ጮኸ ያውቃል? ፀሐይስ አንርታ ታውቃለች? ኤሌክትሪክ በኮሬንቲ ውስጥ ሲያልፍ ይሰማል? ዛፍ በቁመት ሲያድግ ድምጽ አለው? የቢሊዮኖች የሳንባ ትራፊ ‹ካርቦን ዳይ ኦክሳይዱን› ወደ እስትንፋስ ግብዓታችን ‹ኦክስጅን› ሲቀይር የማሽኖች ኳኳታ ያሰማልን? – "በፍጹም አያሰማም::" ራሱ ጠይቆ ራሱ መለሰ::

ዝምታ ግዝፈቱ አይታወቅም:: ዝምታ ትንሽ አይደለም፤ ቀና ብሎ ካጥናፍ እስከ አጥናፍ የተዘረጋውን ጠፈር ላስተዋለ ሰው፤ ዓይኑ የተመለከተውን ጠለል ሰማይ፡ ጆሮው ግን አይሰማውም:: ህዋው ጸጥ ያለ ነው:: ከፀሐይ ሚሊዮኖች እጥፍ የሚበልጡ ኮከቦች ፡ የሚገለባበጡ የእሳት ጅራቶች፣ ‹ሱፐር ኖቫዎች›[14]፣ ግዙፉን ሁሉ አስማጭ እንጦሮጦሶች ጸጥ ብለው ከሰማዩ ላይ ተበትነዋል:: መላዕክት ክንፋቸው እስኪሳበቅ ሲወጡና ሲወርዱ፣ ዝንት ሲሰግዱና ሲያጎነብሱ ኮሽታ አይፈጥሩም:: ምድራችን 1700 ኪ.ሜ በሰዓት ዛቢያዋ ላይ እንደ እንዝርት እየሾረች፤ በምህዋሯ ላይ በመግነጢሳዊ ፍጥነት ፀሐይን እየዞረች ፡ ድምጿን ግን አንሰማውም:: ከባቢ አየር፣ ውቅያኖሶችና መሬቱ አብረው ይጦዛሉ፤ አይወድቁም ፡ አይጮኹም:: የእግዚአብሔር ጥበብ፣ የራሙ-ኤል ተዓምር ፡ የአል-ራህማ ሥራ ፡አጃኢብ ነው:: በአግራሞትና መደመም ፈገግ አለ::

14 እጅግ፡ እጅግ ግዙፍ የሆኑ፡ ኃይለኛ የኮከብ ፍንዳታዎች ምክንያት የሚፈጠሩ የጠፈር አካላት ሲሆኑ፤ ጋላክሲያችንን የማጥፋት አቅም እያላቸው ጠፈር ላይ ድምጽ ባለመጓዙ ብቻ አንዳች ኮሽታ ሲፈጥሩ አይሰሙም። ህዋው ድምጽን በሚውጡ እና ከፍተቶች የተሞላ ነው፡

ግና ዝምታ ትልቅ ብቻም አይደለም። በጥቃቅን ረቂቅ መስተጋብሮችም ውስጥ የዝምታ ምሥጢር ተቀብሯል። ሚሊዮንና ሚሊዮኖች የሰውነታችን ህዋሳት እልፍ ቦታ ይካፈላሉ ፡ ይራባሉ ፡ ይላሳካሉ ፡ ይዋጋሉ ፡ ይገድላሉ ፡ ይሞታሉም። አያማርሩም ፡ አያቃትቱም ፡ አይነጫነጩም ፡ በዝምታ ይመላለሳሉ። የፀሐይ ጨረር ስንት ኃይሉን እንዳዘለ ፡ በዚያ ፍጥነት ገስግሶ ምግብ፣ ብርሃንና ሙቀት ሲያደርሰን ድምጹን ግን አንሰማውም። . . .ሶፎኒያስ በግርምት አንገቱን አወዛወዘ። {በዝምታ ማስተንተን የህይወትን ጣፋጭ መቅኔ እንደመምጠጥ ነውና።}

አዎን ተፈጥሮ ነገሮችን በጸጥታ ማከናወኑን ተክናበታለች። አትክልቱ፣ ፍራፍሬው፣ ሰብል ጥራጥሬው እየጮኸ የሚያድግ ቢሆን ገበሬ ሰላም ባጣ፤ መናፈሻችን ውስጥ ያሉት አበቦች ቢከራከሩ እንኳንስ ሊያዝናኑን ከሩቁ በሸሸናቸው ነበር። የዝናብ ድምጽ እንቅልፍ የሚያመጣ ልዝብ ለዛ ባይኖረው፤ እንደ አውሮፕላኖቻችን የሚያስገመግም ቢሆን ክረምታችን ምን ሊመስል ይችል ነበር? ወጀብና መብረቅን የሚያውቅ ሁሉ መልሱን ይረዳዋል። በ... ድጋሚ እንደሞኝ ብቻውን ፈገግ አለ ፡ ዶ/ር ሶፎኒያስ።

“ግን እኛ የሰው ልጆችስ?” አለና በስላቅ ቀጠለ... “እኛማ ጸጥታን የምንፈራ ፍጡሮች ነን! ምርቶቻችን በሙሉ ድምጽ እንዲያሰሙ ታስበው የሚፈበረኩ ይመስላሉ። መኪናዎቻችን ያጓራሉ፣ ባቡሮቻችን ያሽከትፋሉ፣ ጥሩንባቸውን ያንቧርቃሉ። ወዲህ ደሞ ኤሌክትሮኒክሶቻችን ይቀውጡታል፣ ስልኮቻችን ይጠራሉ፣ ደውሎቻችን ያቃጭላሉ፣ ፋብሪካዎቻችን ያስገመግማሉ፣ ማሽኖቻችን ያፏጫሉ፣ የፊሉ ዘይቶቻችን ይንጫጫሉ። ከእጃችን ውጤቶች ባልተናነሰ እኛም ድምጾችን እንፈጥራለን። ገና ወደዚህች ምድር ስንመጣ “እሪሪ...” ብለን ፍጥረትን እንበጠብጣለን። ስናድግም ብዙ እናወራለን፣ በየገበያው፣ በየአደባባዩ፣ በየሚዲያው፣ በየፓርላማው እንጨቃጨቃለን ፡ እንደማመጥም። እናፏጫለን፣ እንጮኻለን፣ እናለቅሳለን፣ እናሽካካለን ፡ በእጆቻችን እናጨበጭባለን፤ በኮቴዎቻችን እንረግጣለን። {የሰው ልጆች በሙሉ ከገጿ ላይ ቢነሱላት ምድር ጸጥ ያለች ወይዘሮ ትመስል ነበር። ንጽህናና ሰላሟን ያገኘች ፡ ባለ ክብ ፊት ወይዘሮ ለም፡ለም - ዐ ፡ ለም።☺}

እኛ ማን አለብኞቹ ግን ካለመታከት ጸጥታዋን እናደፈርሳለን ፡ ዝምታን ስለምንፈራው በድምጽ ውስጥ እንደበቃለን። ጸጥታ ከኋላው ብዙ ጥያቄዎችን ይዞብን ስለሚመጣ እንሸሸዋለን። ብቸኝነትን ሸሸት

በረብሻ ውስጥ፣ በጨኸትና ሆይ ሆይታ ውስጥ ራሳችንን እንሸሽጋለን። የኦባሬያችን ምሥጢር ብዙ ቢሆንም ለመግለጥ ግን አንደፍርም።

...ድንገት የዶክተር ሶፎኒያስ የግቢ በር በኃይል ተንኳኳ። ጥሞናው ተመነተፈበት ፡ ንፋስ እንደነካው ጉም ተነነ።

ጓ ጓ ጓ ... መንኳኳቱ ቀጠለ። የከባቢው ጸጥታ ደፈረሰ። ተነስቶ በሩን ከፈተው። ሠራተኛው ነበረች።

ተናደደ ፡ ከሥራዋ ሊያባርራትም አስቦ ነበር፤ እሷ ከሌለች ልብሱን ራሱ ማጠብ እንዳለበት ሲያስብ ግን ከወዲሁ ደከመው።

"ግቢ..." አላት፡ ለአመሉ ያህል፤

⌘ ⌘ ⌘

ሜሮን፡ ኤልሳን ለይኩንን እሺ እንድትለው ስትለምናት ጅንን ብላባት ነበር። አሁንም ይዛት እሱ ጋር ስትመጣ ቁንን ፡ ቂብ ቂብ፣ ቅልስልስ እያለች አስቸገረቻት። መወደዷን ቀድማ ስለወቀች በድጋሚ በኩራት ኩፍስ ማለቷ አልቀረም። ሜሮን ግን ከመጎተት ባልተናነሰ ሁኔታ እየሳበች ነበር ከለይኩን አጠገብ ያደረሰቻት። አጅሬ ለይኩን ደግሞ አፉ እንደተለጎመ ፈዞ ቆሟል። ... "በቃ አውሩ፤" አለችና ሜሮን ለይኩንን በሽረፍታ አይታው፡ ትታቸው ሄደች። ሁለቱ ብቻ ቀሩ። ብላቴና ለይኩን ብርክ ያዘው፡

"ደ... ደህና ነሽ ኤልሳ?" ... የሞት ሞቱን ሰላምታ ሰጣት።

ባጭሩ "ደህና፤" ብላ መለሰች ፡ ረጅም ጸጥታ ተተካ። የልጅነት ነገር! ያልተጠና ተውኔት ፡ ንጹህ ስሜት ብቻ ሲሆን የሙርሚረት ነፍስን ማቃተት ዝምታ ይወርሰዋል ፡ቃላት አይፈጠሩም፤ አርፍተ ነገሮች አይመሰረቱም። መተያየት ፡ የልቦች ምት፡ ሰውነት ውርርር...ሃፍረት፡ ዝምታ ፡ ከዘመናት በኋላ መግባባት።

ቀስ ብላ እጁን በእጇ ያዘችው። ነዘረው ፡ ለይኩን በዚህች ሴት ሐሴት ሊያደርግ አሐዱ አለ።

... |ከብዙ የሜሮን ውትወታ በኋላ ነበር ኤልሳ የለይኩንን የፍቅር ጥያቄ ለመቀበል ፍቃደኛ የሆነችው። ከምንም በላይ ለሱ የፍቅር ጥያቄ እድል እንድትሰጠው ያደረጋት ነገር ቀጣይ ዓመት ዩኒቨርሲቲ መግባቱ የማያጠራጥር ሰቃይ ተማሪ መሆኑ ነው። ተስፋ ያለው ልጅ ነው።

ምናልባት ለሷም ተስፋ ሊሆናት ይችላል፤ ከምትጠላው ድህነት አውጥቶ ሊያሳልፍላት ይችል ይሆናል። አዎ፣ በዚህች ትንሽ የልጅነት ተስፋዋ ተሞልታ ነበር አብራው ለመሆን የወሰነች።

⌘ ⌘ ⌘

## ...ያፍቃሪዋ ማስታወሻ፤

*ምን ያለ ደስታ ነው? ምንስ አይነት ህመም ነው? አባት ሴት ልጁን ሲድር እንዲህ ያለ ስሜት ይሰማው ይሆን? ዓለም ዘላለማዊ ብትሆን ደስተኛውም ሐዘንተኛውም ያለበትን መገኘት ይሰለቻል ይባላል! ያፈቀሩት ጋር አብረው ያሉ ግን ያን ህያውነትን ቢሸለሙት እድለኛ ይመስሉኛል:: ፍቅርኮ አይሰለችም::*

*ጥንዶች ዘላለማዊ አብሮነትን ይመኛሉ:: እውነተኛ አፍቃሪዎች ደግሞ የሚወዱትን ቢያሳጣቸው እንኳ የዚያን ሰው ደስታ ቢያዩ ይመርጣሉ:: ውይ! ውይ! ውይ! ህመሙ ግን አይጣል ነው! ያቆረቁዛል:: ወዶ ማጣት መድኃኒት ያልተገኘለት የብዙዎች በሽታኮ ነው:: ለአንዳንድ እድለኞች ደግሞ ጊዜ ብቻ ነው ፈውሱ::... አሁን ከሞተች የዘላለም ህይወት ወዳለበት መንግስተ-ሰማይ ነው የምትገባው ቢባል እናቱ እንድትሞት የሚፈቅድ ሰው ይኖር ይሆን? ባይፈቅድስ ራስ ወዳድ ያስብለው ይሆን? ...የኔም ነገር እንዲያ ነው:: ግራ ያጋባል!*

⌘ ⌘ ⌘

ከሳምንት በኋላ በፍቅር የጦፉ የ12ኛ ክፍል ወንድ ተማሪና የ8ኛ ክፍል ሴት ተማሪት በት/ቤቱ የእረፍት ሰዓት እጃቸውን አጠላልፈው ሲንጎማለሉ ታዩ። ተማሪው ጉድ አለ።

*"በቃ ጠበሳት ማለት ነው?"*

*"ምን ጠበሳት... ጠበሰቻው እንጂ!"*

*"እኔ ግን ለይኩን ሴት የሚያውቅ አይመስለኝም ነበርኮ!"*

*"ይሄኔ እሷ ነች ያሰመጠቻው፤ ቀለሜ ስለሆነ!"*

*"ከስምንተኛ ክፍል ተማሪ ጋር ግን አይደብረውም እንዴ?"*

*"ስምንተኛ ክፍል ትሁን እንጂ ኤልሳ እኮ ትልቅ ልጅ ናት::"*

*"ምነው አሁንስ ልታይ ልታይ ማለት አበዙሳ?!"*

ብዙ ተወራ ፡ ያን ሰሞን እስኪበቃቸው ተቦጨቁ። ወሬና ሐሜቱ ደራ። የክፍሉ ተማሪዎች ለይኩንን በቆረጥ እያዩ፡ እየተንሾካሾኩ መሳሳቅ አበዙ። ለይኩን ግን ልብሳቸውን አውልቀው ቢዘሉ፣ በድምጽ-ማጉያ ስሙን እያሽሟጠጡ ቢዘፍኑ፣ እንዳርጋው በዳሰ በአናታቸው ቆመው ቢጨፍሩ እንኳን ደንታ አልነበረውም። ጭልጥ ብሎ በፍቅር ዓለም ሰምጧል። ..ክፍል ሆኖ እሷን ያስባል፣ ቤቱ ገብቶ እሷን እያስታወሰ በትዝታ ሐሴት ያደርጋል። ከየት እንደመጣ ያላወቁት ደስታ ልጃቸውን ሲያጥለቀልቀው ያዩት እናቱ፡ ያን ሰሞን ቤታቸውን በተደጋጋሚ ጠበል አስረጭተዋል። በሌላ በኩል ከዚያ ቁዘማ ልጃቸውን ስላወጣላቸው ፈጣሪያቸውን አመስግነዋል።*ግራ ገብቷቸዋል።*

ለይኩን ዩኒቨርሲቲ ለመግባት የሚጠብቀው የመጨረሻ ፈተናው ከአንድ ወር በታች ነበር የቀረው። ባለፉት ወራት በኤልሳ ፍቅር ሲብሰለሰል ምንም ስላላጠና አሁን በችኮላ ማዳረስ እንዳለበት ያውቃል። ከክፍል ወጥቶ ወደ ቤተ-መጽሐፍት ለመሄድ ራመድ ራመድ እንዳለ ግን፤

"ለይክ?" ... የሚወደው ድምጽ ከኋላ ይጠራዋል። ዞር ሲል ኤልሳን ያያታል። ቆሌው ይደንሳል።

"ወደ ቤት አትሸኘኝም?" ቅልስልስ ስትል ልቡ ልስልስ ይልበታል ፡ ይሽነፋል. . . *እኮ የምናባቱ ጥናት ነው?*

...እጅ ለእጅ ተጠላልፈው ከትምህርት ቤት ይወጣሉ። ሰማያዊ ደንብ ልብስ በለበሱ ብዙ ተማሪዎች ታጅበው። የፈለገ ቢመጣ ግን እጃቸው አይላቀቅም። እየሮጡ መጥተው መሐላቸው ሊያልፉ የሚፈልጉ ተባራሪ፣ ውር ውር ባይ ተማሪዎች ቢቀርቧቸው እንኳን እንደ ኤሌክትሪክ ንፍቀ-ክበብ ባለ የማይታይ ኃይል ተገፍተው አቅጣጫ ይቀይራሉ። *{ፍቅር ወለድ ድንበር እንበለው ይሆን?}*

ከእለታት በአንዱ፡ ከት/ቤት ወደ ቤት ሲመለሱ "ፕሪም ልግዛልሽ ኤልሲ?" አለ ለይኩን፤ ጥዋት ስሙኒ ከኪሱ ሸሽጎ አኑሮ ነበር - እንገቷን በአዎንታ ነቀነቀችለት። ከትምህርት ቤታቸው አለፍ ብሎ ፕሪም የሚሸጡ ሽማግሌ አሉ። ለይኩንና ኤልሳ እጃቸው እንደተጠላለፈ ተጠጓቸው።

"ስንት ስንት ነው ፕሪም?" ለይኩን አቀርቅሮ ጠየቃቸው፤

"የ10 ሣንቲም አምስት ነው።" - ሀይወት እንደዚህ ቀለል ያለች ነበረች።

"እሺ የ20 ሣንቲም ስጡኝ አባት"............"ለኔ ደግሞ የ10 ሣንቲም ስጡኝ፤" አለች ከጠገባቸው የቆመች አንዲት ሌላ ተማሪ፤ ዞረው ቢያዩ ሜሮን ነበረች። ሁለቱም ፊት ላይ ፈገግታ ሞላ።

"ሜሪ ከኋላችን ነበርሽ እንዴ?"

"አዎ ብጠራችሁኮ መስሚያም የላችሁም።" አለቻቸው ፡ ሳቁ።

ከፕሪሙ ግዢ በኋላ ወደ ቤት ጉዞው ለሦስት ቀጠለ። ለይኩን ፕሪሙን ከፌስታሉ እያወጣ፣ እየላጠ ለኤልሳ ያጎርሳታል። የተላጠውን ፕሪም እንደምትወድ ያውቃል። እሱና ሜሮን ግን ፕሪሙን ልብሳቸው ላይ ጠረግ ጠረግ እያደረጉ፡ ከነልጣጩ ነበር የሚበሉት። ብዙም ሳይቆይ፣ እየጣፈጣቸው፣ አለቀ - ፕሪሙ።

የባጥ የቆጡን እያወሩ፣ ለሦስት እየሳቁ ወደ ሰፈራቸው መታጠፊያ ጋር ሲደርሱ ሜሮን ድንገት ቆመች። በስተግራ ወደ ውስጥ የሚያስገባ ቀጭን መሿለኪያ በኩልም መሰስ ብላ ገባች። ካንድ የቆርቆሮ አጥር አጠገብ ስትደርስ በእጅ ምልክት ኤልሳና ለይኩንን ጠራቻቸው። ይህቺ ልጅ ምንድነው የምትሠራው? እያሉ ተከትለዋት ገቡ። ሜሮን ወደ ኤልሳ ጠጋ ብላ "እዘይኝ!" ስትል አንሾካሾከችላት። ኤልሳ ደብተሯን ለለይኩን አስይዛ ጎንበስ አለችላት። አሁን ምን ለማድረግ እንደፈለገች ገብቷቸዋል። ከግቢው አጥር አልፈው የወጡ የኮሽም ፍሬዎች ይታዮቸዋል።

ሜሮን ፈጠን ብላ የኤልሳ ጀርባ ላይ ተፈናጠጠች። እየተንጠራራች የተወሰኑ ፍሬዎች ቆርጣ ለለይኩን ወረወረችለት። ትንሽ ከፍ ብሎ ግን ይበልጥ የሚያስጎመዡ ኮሽሞች፤ የሰማይ ጠሮዎች ይታያሉ። ሜሮን እነሱን ለማውረድ በጣም ስትንጠራራ ድንገት ከኤልሳ ጀርባ ላይ ሸርተት ብላ ወደቀች። ለይኩን በምን ፍጥነት እጁ ላይ የነበሩ ነገሮችን ከመሬት አራግፎ ሜሮንን እንደቀለባት አያውቅም። ብቻ ገላዋ መሬት ሳይነካ ክንዶቹ ላይ ዘፍ አለች። ምንም ሳያወሩ ለቅጽበት በዝምታ ተያዩ። **{ዘላለም የምትመስል ዝምታ ናት ይህቺ፤}**

"ወይኔ ሜሪ!... ተረፍሽ?" አለች ኤልሳ ድንግጥ እንዳለች፤

"ደህና ነኝ ኤልሲ ፡ በስመአብ ...ሊይክ ባይኖርማ ..." አለች ሜሮን፤ ከክንዱ ወርዳ ልብሷን እያስተካከለች። ለይኩን ጎንበስ ብሎ መሬት ላይ

የተበተኑ የኤልሳ ደብተሮችን ሲሰበስብ፤ ሜሮን ደግሞ የኮሽም ፍሬዎቹን ለቀመች። ኤልሳ ቆማ እየሳቀች ታያቸው ነበር። በዚህች ደቂቃ የግቢው በር ተከፈተ ፡ የኮሽሙ ባለቤት እያጉረመረሙ በበሩ ወጡ። ሦስቱም እግሬ አውጪኝ ብለው ፈረጠጡ፤

የተወሰነ ርቀት ሮጠው ሰውዬው እንዳልተከተሏቸው ካረጋገጡ በኋላ ፍጥነት ቀነሱ። እያለከለኩ፣ በገጠመኛቸው እየሳቁ፣ እየተጫወቱ መንገዳቸውን ቀጠሉ። ከተረጋጉ በኋላ ለይኩን የኮሽም ፍሬዎቹን አከፋፈላቸው። ኤልሳ ተቀብላው ገመጠች... *"ወይኔ እንዴት ይጎመዝዛል በማርያም፤ እም፡ጣ!..."* ፊቷን በኃይል ጭምድድ አደረገችው ፡ "ውይ በናትቻሁ ይቅርብኝ።" ብላ ኮሽሙን ለለይኩን መለሰችለት፤

"ቀረብሻ፤" የወረት ሳቅ ሳቁባት ፡ *"ወረቱ ኩርሽም እንደ ኮሽም እሽም፤"* እንዲል ባለ ቅኔው ሙሉጌታ፡ ጉምዛዜውን አጣጣሙት። *{ለመሆኑ ጣፋጭነት ስኳር ስኳር ማለት ብቻ ነው ያለው ማነው? ጨው ወጥን አያጣፍጥም? ሎሚ ሰላጣን አያጣፍጥም? ፍቅር ህይወትን አያጣፍጥም? የሚወዷት ልጅ ድምጽ አይጣፍጥም?}*

ግን ግን ህይወት ሲጣፍጥ ያዘናጋል። ያን ሰሞንም ለይኩን ማጥናት እንዳለበት ቢያውቅም የረባ ንባብ ሳያደርግ ሳምንታቱ ነጎዱ። በፍቅር ዓለም ነሁልሎ ትኩረቱን ጥናቱ ላይ ማድረግ አቃተው። ሠርገኛ መጣ... ሆነና ቀኑ በቀረበ ቁጥር ውጥረት ውስጥ ገባ። የብሔራዊ ፈተና ሦስት ቀናት ሲቀሩትማ ፍርሃቱ ሊደፋው ደረሰ። ቆይ ቢወድቅስ? የዚያ ሁሉ ዓመት ልፋቱ ውኃ ቢበላውስ? በስድስት ወራት ውስጥ የቀደመ የትምህርት ጉብዝናው ተፍረክርኳል። እንኳን አዲስ እውቀት ሊጨምር የሚያውቀውም በከፊል ጠፍቶበታል። *{እውቀትም ካልከላለሱት ባዳ ነውስ። }*

እነሆ ዛሬ ሦስት ቀን ቀርቶታል ፡ በሦስት ቀን ምን መፍጠር ይችላል? ሐሳቡ ሲበረታበት ወደ ኤልሳ ለመሄድ ወሰነ። ያካባቢው ሰው በሙሉ ባንድ ድምጽ እንጀራቸውን ከሚያደንቅላቸው እትዬ ጎርፌ በር ላይ ሲደርስ ደበቅ ብሎ ቆመና ትንሽዬ ልጅ ፍለጋ ማማተር ያዘ።

በቅርብ ርቀት አንድ ባጃ የተቆረጠ፣ ክርኑ ጋር የተቦረተፈ፡ ሰማያዊ ካኪ ጃኬት የለበሰ ልጅ ብይ ሲያንከባልል አየው።

"አቡሽ! አቡሽ! ... ና አንዴ?"

"እ... እኔን ነው?"

"አዎ ና!" ልጁ ከብይ ጨዋታው መጠራራቱ ደስ ያላለው ይመስላል፡ ተነስቶ ራመድ.. ቆም.. ሮጥ.. ራመድ እያለ ለይኩን ጋር ደረሰ።

"አንዴ ኤልሳን ጥራልኝ እስኪ?... ጎበዝ ልጅ!"

"ማናት ኤልሳ?"

"እዚያኛው ቤት ያለችውን ልጅ..." አለ ለይኩን በጠቋሚ ጣቱ ወደነ ኤልሳ ቤት እያመለከተው።

"እ! ድንች የሚሸጥበት ቤት ያለችውን፡ የእማማ መንበረን ልጅ ነው እንዴ?"

"አዎ" ፡ ከማለቱ ልጁ ፈር ብሎ በሩ ደጃፍ ላይ ደርሷል። ከፍታ በኋላ እየበረረ ተመለሰ።

"እ ... ጠርቻታለሁ ... መጣሁኝ ብላለች"

"ጎበዝ ልጅ!"

"እና ድንች አትገዛልኝም?"

"ብር አልያዝኩም አቡሼ"..... "እና ... እህ...ዝም ብሎ ያስለፋኛል እንዴ? እም... እህ..." ልጁ ለራሱ ብቻ በሚሰማ ድምጽ እያጉረመረመ፡ ወደ ብይ ክብለላው ተመለሰ።

ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላ ኤልሳ ከቤቷ ወጣች። ለይኩን ወከክ አለ። እሷ በበኩሏ እንደፈራች በሚያሳብቅ መልኩ በነጠላ ተሸፋፍና፣ ዙሪያ ገባዋን እየገላመጠች ነበር እሱ ጋር የደረሰችው። በመሐከላቸው ክፍተትን ትታ ፡ ፈንጠር ብላ ቆመች።

"ለይክ ግን እንዲህ ቤቴ አካባቢ መምጣትኽን አቁም አላልኩህም ነበር? ቤተሰቦቼ ቢያዩኝኮ ይገሉኛል።" አለችው፡ አፍና አፍንጫዋን በነጠላ እየከለለች፤

"ናፍቀሽኝኮ ነው፤ በዚያ ላይ በጣም ፈርቻለሁ በናትሽ!"

"ምንድነው ያስፈራኽ?"

"ፈተናውን ነዋ ኤልሲ!"

"ለምን ዝም ብለኽ ነገሮችን ታካብዳለህ? አንተኮ ጎበዝ ተማሪ ነህ። ዘና ብለህ ነው የምታልፈው!" አለች ኤልሳ፣ የመተማመን ገጽታ እያሳየችው።

ለይኩን ምንም ሳይናገር ለራሱ ሚዛን አኖረ። የማለፍ ነገር ግን አላጋድልልህ አለው። ኤልሳ እሱ ላይ ያላት መተማመን ቢያስደስተውም ቶሎ ከሱ ለመለየት መፈለጓን ግን አልወደደላትም።

"እሺ ትንሽ አትሸኚኝም?"

"አይ ለይክ! ልግባ በናትህ" አለችው በተማጽኖ ድምጽ፤

ባይዋጥለትም እሺ ብሏት ተሰነባበቱ። እንዲህ በወጉ እንኳን ሳያያት መሄዱ ግን አስከፍቶታል። በሐዘን ፊቱን አዙሮ ወደ ቤቱ በመመለስ ላይ ሳለ "ለይክ?" የሚል የሴት ጥሪ ሰማ፤ ዞር ብሎ ቢያጣራ ሜሮንን አያት። እሷም ከቤቷ መስኮት አሻግራ አይታው ኖሯል የጠራችው። ፈጠን ብላ ከግቢዋ ወጣችና ተጠምጥማ አቀፈችው።

"እንዴ ምነው ለይክዬ... ፊትህ ደስ አይልም?"

"ዝም ብሎ ነው ሜሪዬ፤ ትንሽ የፈተናው ነገር እያሳሰበኝ ነው።" ... ሜሮን ፈገግታዋ ወዲያውኑ ወደ ጭንቀት ሲለወጥ አስተዋለ።

"አይዞኽ... እግዚአብሔር ያለው ነው የሚሆነው።"

"አዎ ልክ ነሽ።" አለ ለይኩን። ብዙ እያጫወተችና እያበረታታችው ረጅም መንገድ ሸኝታው ተመለሰች።

|ታዲያ በመጨረሻም እግዚአብሔር ያለው ሆነ፤ ሳያጠና የከረመው ለይኩን ፈተናውን ወደቀ።

⌘ ⌘ ⌘

"እስካሁን ጥሩ አድርገኽ ታሪክህን አውግተኸኛል።" አሉ ደጉ አረጋዊ ገበሬ፡ የለይኩንን ፊት በሐዘኔታ እያዩ። "አስተዳደግኽን ማወቄ መነሻኽን ይነግረኛል። የሰው ልጅ ምን ክፉ ነገር ቢፈጽም መነሻው መልካም ከሆነ ወደ ጥሩነቱ ለመመለስ ይቀለዋል። ሁሉም ሰው የልጅነቱ ውጤት ነው ይባል የለ ልጄ?"

"አዎን አባቴ ልክ ብለዋል።" አለ ለይኩን።

"እርግጥም ታሪክህ የሚገርም ነው። ኤልሳ ካልካት ልጅ ጋር መጨረሻችሁ ምን እንደሚሆን ለማወቅ ጓጉቻለሁ። በተለይ በተለይ ግን ሜሮን ያልካት ልጅ አስተዋይነት ደግሞ ማለፊያ ነው።" ... ቀና ሳይሉ በከዘራቸው ወለሉን እየተመተሙ ቆዩ።

"በል አሁን ተነስና ምሳ እንብላ፤ ትንሽ እረፍት አድርገን በኋላ ቡና እየጠጣን ደግሞ ጨዋታውን ትቀጥልልኛለኽ" አሉና ከመቀመጫቸው ተነሱ። "ማነሽ አንቺ ልጅ... ምሳ አቅርቢልን እስኪ?"

"እሺ አባ" ብላ አንዲት ታዳጊ ልጅ ከጓዳ ወጣች፤ ለይኩን ልጅቷን ሲያይ ድንግጥ አለ። ይሄንን መልክ በሚገባ ያውቀዋል። ታዲያ ለይኩን ልጅቱን አተኩሮ ማየቱን ያስተዋሉት አረጋዊ ገበሬም...

"እንዴት ያለች የተባረከች ልጅ መሰለችኽ፤ የልጅ ልጄ ናት። እናቷ ትንሽ ራሷን አመም ስላደረጋት አዲስ አበባ ህክምና ላይ ነች።"

"ምን አጋጥሟት ይሆን እናቷ?" አለ ለይኩን።

"የእናንተ የልጆች ነገር፤ ያው ስትፋቀሩም፣ ስትጣሉም ልክ የላችሁም፣ ስታጡም፣ ስታገኙም አትችሉበትም። የሷን ታሪክ ደግሞ ወደኋላ አወጋሃለሁ።" አሉ በቅኔ እየገረመሙት፤ "አሳዛኝ ነው፤ ... እንግዲህ እግዚአብሔር ያለው ነው የሚሆነው" አለና ለይኩን፤ እንደምንም ከመደቡ ተነሳ፤ ...

"ትክክል ብለሃል፤ እሱ ካለው ውጪ ምንስ ሊሆን?!"

⌘ ⌘ ⌘

ከዶ/ር ሶፎኒያስ ሳሎን ውስጥ ገና በማለዳው አንድ ነጎድጓዳዊ ድምጽ የግጥም ስንኝን ይደረድራል።

*"...ውኃ እንደ ጉታ ሲተም ፡ በድን ሽለቆ ሲናገር*

*በሰማይ ፈረስ ተጭኖ ፡ ካጽናፍ አጽናፍ ሲንደረደር*

*ሲያጉተመትም ሲያስገመግም ፡ በዓይነ ህሊና ለመመስከር፤*

*ሳንጨነቅ ሳንገድር÷*

*ለማንም ምንም ሳናዋይ ፡ ሳንናገር ሳንጋገር*

*ከዓይንሽ ፡ ከልብሽ ከልቤ ፡ አዋሽ ማዶ አብረን እንብረር፤*

*...አዋሽ ማዶ አብረን እንውረድ*

*አጉል ነው ብለን ሳንፈርድ፡ ድንቅም ነው ብለን ሳንወድ*

*ዝም ብለን አብረን ብንወርድ*

*ከሰው መንጋ ተለይተን ፡ ከጠረኑ ተነጥለን ፡*

*ከጉምጉምታው ተነጥለን ፡ ከኳኳታው እንከለል*

*ከሳንቃው፣ ከድምጹ ሸሽተን ፡ በእፎይታ ጥላ እንጠለል፤*

*በቆይታ ... በጸጥታ ...*

*ዝም ብለን አብረን ዝም እንበል::" ✍ ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድኅን፤*

ዶ/ር ሶፎኒያስ በሩን ከፍቶ ወጣና ከጥዷ ዛፍ ሥር ቁጭ አለ።

*የመጀመሪያው የሐሳብ ብልጭታ ‹ዝምታ ቅኔ ነው› የሚል ነበር:: ዝምታ ግጥም አለው ፡ ምት አለው ፡ ልዩ ዜማ አለው:: ዝምታ ቶሎ የማይፈታ ምሥጢር ፤ የማይጠገብ ድርሰት ነው:: ችግሩ ግን የህይወትን ምሥጢሯን የሚያነብ፤ ጸጥታዋን የሚያዳምጥ ጠፋ:: ያለውም የሌለውም ችግርን ብቻ ያወራል:: "ያለኝ ይበቃኛል::" ብሎ ዝም የሚል፣ የሚያመሰግን በምድሩ ታጣ:: ሁሉም ለማድመጥ ሳይሆን መልስ ለመስጠት እየተዘጋጀ ለወሬ ተራውን ይጠብቃል፣ ሌላው አውርቶ ሳይጨርስ ጣልቃ ይገባል:: የተሳካለትም ያልተሳካለትም ለጉድ ያማርራል:: መወቃቀስ፣ መከራከር፣ መጨቃጨቅ፣ መሰዳደብ፣ መወነጃጀልና መጣላላት ነግሠዋል:: የውስጡን ጩኸትና ፍርሃት መሸከም ያቃተው ሁሉ እየተነሳ ህዝቡ ውስጥ ለጉድ ጭንቀት፣ ፍርሃት ይረጫል::*

*እዎ! አብዛኛው ሰው የመዋከብ እሥር ቤት ውስጥ ይገኛል:: ስንቱ ሰው አሁን ባለበት ሁኔታ ደስተኛ ነው? ማንነቱን የሚወድስ ምን ያህሉ ነው? ስንቶች ለመለወጥ ሞክረው ስንቴ ከብዷቸው ትተዋል? ...እነሆ በህይወት መንገድ ላይ ሰዎች ሁለት ጎራ አላቸው፤ እጃቸውን ዘርግተው የተማረኩም አሉ፡እጃቸውን ጨብጠው እየታገሉ ያሉም አሉ:: ዶ/ር ሶፎኒያስ ከሁለተኞቹ ለመሆን ወስኗል:: ውስጣዊ ጸጥታን፣ ሰላምን ለማግኘት ቆርጧል:: በዚህ የውሳኔ ቅጽበት የግቢው በር ተቆረቆረ:: ጥሞናው ተረበሸ:: በዘመኑ ሰው መሐል ሆኖ ዝምታን መመኘት ቀቢጸ*

ተስፈኝነት መሰለው። ተነስቶ በሩን ሲከፍት ወዳጁ ዶ/ር ኪሩቤል ከበር ላይ ቆሞ ነበር፣ በደስታ አቀፈው።

የድሮ ጓደኛ ወርቅ ነው ይላሉ። ያው ዛሬም ቤቱ ድረስ ፈልጎት የመጣው ያኔ ገና በለጋ እድሜ ህክምና ትምህርት ክፍል ሳሉ የተዋወቀው ጓደኛው ነው። ጀርመን አገር ሔዶ በዘረመል ጥናት ሁለተኛ ዲግሪውን ጨርሶ ከመጣ 8 ወር ሆኖታል። ወደ ውስጥ እንዲገባ ጋበዘውና ሻይ አቀረበለት። ሻያቸውን እየተጎነጩ ተጨዋወቱ። እነሆ ዶ/ር ሶፎኒያስ እያደረገ ስላለው ዝምታን የማግኘት ጥረት መጀመሪያ ያጫወተው ሰው ዶ/ር ኪሩቤል ሆነ።

"ሰው ግን ለምን ዝምታን እንደሚፈራ... በሥራና መዝናኛዎች ራሱን ‹ኦኮፓይድ› እንደሚያደርግ ታውቃለኽ?" ጠየቀ ኪሩቤል የጓደኛውን የውስጣዊ ጉዞ እቅድ ሲያዳምጥ ከቆየ በኋላ... "እንደኔ እንደኔ ያለፈና የአሁኑን እውነት ለመቀበል የሚያዳግተው የ"ፐርሰናል ኢንሴኩሪቲ" መቋቋም ስለማይችል ይመስለኛል፤" ቢለው ሶፎኒያስ ስላነሳው ሐሳብ እውነታነት ራሱን በማነቃነቅ ተስማማ። ስለዚህም፣ ስለሌሎችም ጉዳዮች ብዙ አወጉ፤ በዚህ ጭውውታቸው መሐል ግን ጓደኛው አንድ ድንቅ ሐሳብ አቀረበለት። ከከተማ ወጣ ማለትን፤

"እንዲያውም ጀርመን የማውቃቸው ወዳጆቼ በቅርቡ ‹ሀይኪንግ› ብለው አንድ ከአዲስ አባ በቅርብ የሚገኝ ተራራ ወጥተው ነበር። እጅግ ደስ የሚል፣ ሰላማዊ ስፍራ ነው ብለውኛል።" አለው ዶ/ር ኪሩቤል፤ ከሻዩ እየተጎነጨለት፤

"የቦታውን ስም አታስታውሰውም?" አለ ዶ/ር ሶፎኒያስ በጉጉት፤

"እምም... ‹ኦው-የስ›" አለ ዶ/ር ኪሩቤል የተራራውን ስም እያስታወሰ...
**"ኤ..ረር!"**

* ✡ *

# ምዕራፍ አራት

# ጉዞ ወደ ኤረር ተራራ

**ከኤረር ተራራ ግርጌ ከሚገኙ ስውር ዋሻዎች የተሰየሙ አንድ አባት መዝሙረ ዳዊትን እያነበነቡ ምዕራፍ አርባ ሦስት ላይ ደርሰዋል፣ በተለይ ቁጥር ሦስትን በሞገደኛ ድምጽ አነበቡት፤ "ብርሃንህንና እውነትህን ላክ÷ እነርሱ ይምሩኝ÷ወደ ቅድስናው ተራራና ወደ ማደሪያህ ይውሰዱኝ።"**

⌘ ⌘ ⌘

ዶ/ር ሶፎኒያስ ወደ ኤረር ተራራ ለመሄድ ሲወስን ጊዜ አልፈጀበትም። ሌላው መንገዱን ቀላል የሚያደርግላት ነገር ደብረ-ዘይት አክስቱ መኖራቸው ነበር። ይህም እስከ ደብረ-ዘይት ጓዝ ሳያበዛ ሄዶ፣ አክስቱ ጋር አርፎ፡ ከዚያ ደግሞ ወደ ኤረር ተራራ ለመጓዝ ነገሮችን ያቀልለታል ማለት ነው። የዚያኑ ቀን ማታ የሚያስፈልጉትን ልብሶችና እቃዎች አስተካክሎ ከሻንጣው ከተተ። ጺሙን ላጨ፣ ጥፍሮቹን ቆረጠ፤ ራሱን ለጉዞ እያዘገጃጀ አመሸና ሲደክመው ወደ መኝታ ሄደ። ... በማግስቱ በሌሊት መኪናውን አስነስቶ ወደ ደብረ-ዘይት ጉዞውን ጀመረ። ፃ

የመኪናው ጎማ መንከባለሉን ቀጥሏል። በአቃቂ አቅጣጫ ከአዲስ አበባ ወጥቶ ለጥ ያለውን መንገድ ተያያዘው። የጋቢናውን መስታወት ዝቅ አድርጎ፣ በግራ ክንዱ መስኮቱን ደገፍ ብሎ ነበር የሚያሽከረክረው። አየሩ ደግሞ ማለፊያ ነው። በረድ ያለ ሰላማዊ አየር። መኪናውን ወደ ደብረ-ዘይት መስመር እያስከነፈ እሱም በሐሳብ መጋለቡን ያዘ።

ታዲያ እየነዳ በፈለገ-ሐሳብ ሲነጉድ የመንገድ ጉዞና የነፍስ ጥሪ ጉዞ በብዙ መልኩ ተመሳሰሉበት። ምክንያቱም ሁለቱም ጉዞዎች የሚያነሳሳቸው አንድ ጥያቄ፣ የሚያሳኩትም አንድ ዓላማ አላቸው። ሁለቱም ዝግጅትን ይሻሉ፣ ሁለቱም ጉልበትና ጊዜን ይፈልጋሉ።

ከምንም በላይ ግን መንገዱን ጨርሰው የደረሱም፣ የውስጣቸውን ጥያቄ የመለሱም እፎይ ብለው ከድካማቸው ያርፋሉ።

አውቀንም ይሁን ሳናውቅ ሁላችንም ጉዞ ላይ ነን። የህይወት ጉዞዋ፣ ውጣ ውረዷ ግን ቀላል አይደለም። ስንቱ ጉዞው ተሰናክሎበት ከመንገድ ዳር ቆሟል። የኑሮ ጎማው ተንፍሶበት ከአውላላው የሐሳብ ሜዳ ላይ የቀረውን ቤቱ ይቁጠረው። መድረሻና ዓላማ የለሽ ኑሮ ተንሰራፍቷል፤ የያንዳንዱ ጓዳ ብዙ አስለቅሰው ትንሽ የሚያስቁ ታሪኮችን አዝሏል። ስንገነባ ሲፈርስ፣ ደግመን እስኪፈርስ ስንገነባ ህይወት ይቀጥላል። ፍርስራሽና ሰቀላ ታሪካችን ነው። {ጂኒውም መልዓኩም ጽፈው የሚያስቀሩት ክታብ አለን።}

በምድር ብዙ የገነባ ብዙ የተሳካለት ሊመስለው ይችላል። ዳሩ ግን ትልልቅ ግንቦችም እንደ ባቢሎን ይወድቃሉ። እናም ዘላቂውን ግንብ መገንባት የቻሉ ብቻ ህያው ይሆናሉ። ታዲያ በግንባታው ውስጥ ዋናው ጥያቄ ፡ "ረጅሙን ግንብ ስትገነባ እውነተኛው ማንነትህን አዝለከዋል ወይስ ጥለከዋል?" የሚለው ነው። ብሎኬት ላይ ብሎኬትን ስትደርብ ህሊናኽን አፍርስከዋል ወይ? በእድገትህ ላይ እውነት፣ እምነት፣ ፍቅር፣ ህብረትህን ጥለህ ከላይ ከደረስክ በተራ ስኬትህ ቆጥ ውስጥ ውሸት፣ ክህደት፣ ፍርሃትና ያልተፈለገ ብቸኝነት ይጠብቁኻል።

ስለዚህ ማንነትህን ሳትጥል ተራራውን መውጣትህን ቀጥል። ከቆምክ ግን ትበሰብሳለህ። ውኃ አቅላሚ እንደወረረው፣ እንደጠረና ኩሬ ትደነብሻለኽ። ስለዚህ ጉዞኽን ቀጥል። ስትጓዝ ደሞ ወደ ፊት፣ አቅጣጫ አስምረኽ ይሁን። ብቻ ህይወትህን የትም የማይደርስ የድግግሞሽ ጉዞ እንዳታደርገው። ከቻልክ ቀድመህ ነቅተህ ለሌሎችም የሚሆን መንገድ ቀልስ። ካልቻልክ ሌሎች ጥሩ ተጓዦች የሄዱበትን መንገድ አክብረኽ ተጓዝ። እንደ ኤሊ በዝግታም ቢሆን አዝግም እንጂ እዚያው እንዳትቸነከር።" ...ይህንን ካሰላሰለ በኋላ ዶ/ር ሶፎኒያስ አንዷት አደራን ራሱ ላይ ጣለ። "እኔ ሆይ ፡ አደራህን አልጌ እንዳፈላበት ኩሬ እንዳትሆን።" ብሎም ራሱን አስጠነቀቀ።

ይህን ምክር እየደጋገመ ሳለ ድንገት ከመንገዱ በስተግራ አንድ እጃቸውን የሚያውለበልቡ አባትን ተመለከተ። "ሸኙኝ" የሚል ምልክት እያሳዩት ነበር። ዶ/ር ሶፎኒያስ መኪናውን "ላቁም አላቁም?" የሚል ውዝግብ ውስጥ ገባ። በነዚያ የሰከንድ ሀባዎች ውስጥ ራሱን ከህሊና ዳኛ ፊት አቆመ። በቀኝ ትከሻው ያለው መልአኩ ጠበቃ እንዲህ አለው "አረጋዊ

ናቸው፣ አያትህ ወይ አባትህ ሊሆኑ የሚችሉ ሽማግሌ ናቸው! ደክሟቸው ወይ አሟቸው ሊሆን ይችላል ፡ እኮ እንዴት ጨክነህ ታልፋቸዋለህ? አሁኑኑ አቁምላቸው።" በሌላ በኩል በግራ ትከሻው ያለው ቀበኛ አቃቢ ደግሞ በተቃራኒው ቆሞ ሞገተው። "ከመፈጠራቸው ለማታውቃቸው፡ አንድ ባዕድ ሰው መኪናህን ልታቆም ባልሆነ!? ስለእርሳቸው ምን አገባኽ? ቆይ ሰውዬው ሌባ ቢሆኑስ? ጥሩ ጠረን የሌላቸው፣ ወንበርህን የሚያቆሽሹ ድሪቶ መንገደኛ ቢሆኑስ? አርፈህ ንዳና ቶሎ አክስትህ ጋር ድረስ።" እያለ ሞገተው። ከከባድ ክርክር በኋላ የህሊና ዳኛው ውጤቱን አሳወቀ። የቀኝ ክንፉ ፡ የእርሳቸው ጠበቃ አሸነፈ። መኪናውን አቆመላቸው።

ልብሳቸውን ሰብሰብ አድርገው፡ ፈንጠር ብለው ገቡ። በወጉ ከተቀመጡ በኋላ "አመሰግናለሁ ልጄ፣ ...ተባረክልኝ።" አሉት፤

"ምንም አይደል አባቴ፤" ብሎ መለሰላቸው፤ ከዚህ በኋላ ግን ምንም አላወሩም። ሶፎኒያስ ትከሻ የሚከብዱ ሰው ሆኑበት። የማይናገር የማይጋገር ጸጥታቸው ያስፈራል። የተወሰነ ርቀት እንደተጓዙ ከአስፓልቱ ጎን የተጠራቀመ ሰፊ ኩሬ ጋር ሲደርሱ፤

ድንገት "አየኻቸው?" አሉት።

"ምኖቹን?"

"አልጌዎቹን"... በጣታቸው ጠቆሙት፤

"አዎን"

"የዓለምን ዘጠና በመቶ ኦክስጅን የሚያመርቱት አልጌዎች እንደሆኑ ታውቃለኽ? ... የህይወት ደጀኖቹ ዛፎች ደግሞ ቀሪውን አሥር በመቶ ያመርታሉ!" አሉት።

"በጣም ይገርማል አላውቅም ነበር።" አለ ዶ/ር ሶፎኒያስ፣ ቅድም ከራሱ ጋር ሲያደርገው የነበረውን ውይይት እያስታወሰ ራሱን ታዘበ፤ ለካ ወንዝ ብቻ ሳይሆን ኩሬ መሆንም ምሥጢር አለው። ከኩሬ የጀመረ በሐይቅ ቀጥሎ፣ በባህር ሰልሶ፡ ውቅያኖስ ይሆናል። ... እርሳቸው ግን ሌላ ነገር አላወሩም። አሁንም ከባድ ዝምታቸው መኪናውን ሞላው።

በጨረፍታ አይቷቸው በግርምት ፈገግ አለ። ምን አይነት እንቆቅልሽ ነው የጫንኹት? ...

ኋላ ላይ ... "ያንን የነጻነት ዋጋ የሚገለጥበት ስፍራስ አየኸው?" አሉና ድንገቴ ጥያቄ አቀረቡለት። በመሐከለኛ መስታወት ሲያስተውል ቃሊቲ ማረሚያ ቤት አካባቢ እንደደረሱ ተረዳ።

"በቃ እዚያች ጋር ታወርደኛለኽ ልጄ፤" አሉት።

መኪናውን ሲያቆምላቸው ፡ ከእድሜያቸው በማይጠበቅ ፍጥነት ቀልጠፍ ብለው ወረዱ። ታዲያ ከመኪናው ብዙም ሳይርቁ ዞረው ተመለከቱት. . . አስተያየታቸው ጠሊቅ ነበር። "እግዚአብሔር ይጥስልኝ። አመሰግናለሁ።" አሉት በትህትና፤

"ምንም አይደለም አባቴ ፡ ሰላም ሁኑ፤"

"አንተም ሰላም ሁን፤ እንደሱ ፍቃድ በቅርቡ እንገናኛለን።" ብለውት፡ እየተቻኮሉ ወደ ማረሚያ ቤቱ አቅጣጫ አመሩ። ዶክተር ሶፎኒያስ ‹በድጋሚ እንገናኛለን› በማለታቸው እየተገረመ የነዳጅ መስጫውን ረገጠው። ብዙ ነገሮች እያውጠነጠነ መንገዱን ለጉድ ፈጨው[15]።

⌘ ⌘ ⌘

ለለይኩን መሸሸጊያ የሰጡት አረጋዊው ገበሬ ጸሎት አድርሰው ገበታ ቀረቡ። ተመግበው ሲጨርሱ አመስግነው ገበታው ተነሳ። ኋላም አረጋዊው ሰው ትንሽ ከብቶቹን አየት አድርጊያቸው ልምጣ ብለው ወጡ።

ለይኩን በደጉ አረጋዊ በጎነት እየተገረመ ወደ ጠፈር አልጋው ተመለሰ። እግሩ አሁንም በመጠኑ እየጠዘጠዘው ነው።

ከውስጥ የልጅ ልጃቸው የበሉበትን ቦታ እያጸዳዳች ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ ልብ ብሎ አያት ፡ ከዚያች ሳይረዳት የተረዳችው ልጅ ጋር ያላት መመሳሰል እጅግ አስደነቀው።

"ስምሽ ማነው?" አላት፤

"ማርታ፤" መለሰች ልጅቱ፤ አጎንብሳ ቤቱን እየጠረገች ነበር።

"ጎበዝ ልጅ ነሽ ማርቲ... ትምህርት ትማሪያለሽ?"

---

15 ሹፌሮች በአጋጣሚ ራሳችሁን በሐሳብ ነጉዳችሁ ካገኛችሁት መኪናውን አቁሞ በረጅሙ ተንፍሶ ሐሳብን ካስተነፈሱ በኋላ ድጋሚ ማሽከርከር ይመከራል። ትኩረት ማጣት የአደጋዎች ዋነኛ ምክንያት ነው።

"አዎ የከሰዓት ፈረቃ ነኝ።" የልጅቷ ዓይን-አፋርነት በያንዳንዱ ቃላቶቿ ውስጥ ይታያል።

"ስንተኛ ክፍል ነሽ?"

"አምስተኛ"

"ጎበዝ ተማሪ ነሻ፤"

"ምንም አልል... እሞክራለሁ ጋሽዬ" ፈገግ አለች።

ለይኩን ትንሽ አሰብ ካደረገ በኋላ ሌላ ጥያቄ አስከተለ "እናት አባትሽ የት ናቸው?"

ልጅቱ አሁን ገና ከባድ ጥያቄ እንደጠየቃት በሚያሳብቅ መልኩ ለመመለስ አቅማማች። "አባቴን አላውቀውም ግን እናቴ አሚት አዲስ አበባ እየታከመች ነው።" አለች፤

"የእናትሽ ስሟ ማነው...?"

... "ልጆቼ ጨዋታ ጀመራችሁ እንዴ?..." አሉ አረጋዊው ገበሬ ድንገት በሩን ከፍተው እየገቡ።

"አዎ አባቴ" ለይኩን ያክብሮት መልስ ሰጠ።

"መልካም ነው።" አሉና አረጋዊው ገበሬ ጋቢያቸውን ጣል አድርገው ከበርጩማው ተቀመጡ።

"ልጄ ማርታ... የትምህርት ሰዓት እንዳይረፍድብሽ፤"

"እሺ አባ" አለች ልጅት ማርታ። ብዙም ሳትቆይ ደብተሯን ይዛ እየተቻኮለች ወጣች።... "አሁን እንዴት ነህ ታዲያ እግርህን?" አሉ፤ እሷ ከወጣች በኋላ፤ ሙሉ ትኩረታቸውን ለለይኩን እየሰጡ።

"ትንሽ ይጠዘጥዘኛል እንጂ ደህና ነኝ አባቴ"

"አዎ ማታ ሳጥብህ አይቼዋለሁ፤ ሚስማሩ አጥንት ድረስ ዘልቆ ገብቷል። ሐኪም ቤት ብትታይ መልካም ነበር ነገር ግን ተፈላጊ እስረኛ ስለሆንክ ሊለዩህና ሊይዙክ ይችላሉ። ስለዚህ እዚሁ ሆነኽ ፈጣሪ እንዲሽርህ መለመን ነው የሚሻለው፤"

"ያሉትን በሙሉ እቀበላለሁ አባቴ፤" ብሎ መስማማቱን ገለጸላቸው፤

"እንግዲያውስ ልጄ፤ ታሪክህን ካቆምክበት ቀጥለኽ አጫውተኝ። እንዴት እንደታሰርክም ለማወቅ እፈልጋለሁ።" አሉት ከመቀመጫቸው ላይ እየተመቻቹ፤ ለይኩን "እሺ አባቴ..." አለና ትረካውን ቀጠለ ...

⌘ ⌘ ⌘

ለይኩን ያኔ ፈተናውን ሲወድቅ ብዙ እሱነቱ ተቆራርጦ ወደቀ። ባዶነት ወደፊቱን የከበበው መሰለው። በዚያ ልጅነት የወጠናት ተስፋው ሰለለች። ያ ሁሉ ጥናቱና ልፋቱ ውኃ ተቸለሰበት። ውጤቱን ተቀብሎ እናቱ ጋር ነበር የተመለሰው። ቀና ብሎ ሊያያቸው ግን አቅም አልነበረውም።

|እንዳጎነበሰ ገብቶ ከፊታቸው ቆመ።

"ምን ሆነኻል ልጄ? እላዬ ላይ ቆመኽ እንደ ዛር ከበድከኝ እኮ፤" አሉት አጎንብሰው ጉድጉድ ከሚሉበት ቀና ብለው እያዩት።

"ወ...ወደቅኩኝ እናቴ!" ለይኩን አንገቱን እንደደፋ መለሰ፤ እጁ ላይ ያለውን ካርድም ወደሳቸው አዙሮ አሳያቸው። እናቱ መልስ አልሰጡትም። ፊታቸው ላይ ምንም አይነት ስሜት አልተነበበም። ቀሚሳቸውን ሰብሰብ አድርገው ብድግ አሉ። ሁለቱም እጆቻቸውን ጸሎት እንደሚያደርስ ሰው ዘረጉ። *ልጃቸውን ለማሳደግ ሲሉ እጃቸው ቢቆሽሽ ሌላውን ላለመንካት እንደ እርግብ ክንፍ እጆቻቸውን አዘቅዝቀው የሚቆሙ እናቶች አሉ። ሁሉን ችግር ሆድ ይፍጀው እያሉ ዝም ያሉ፤ የኑሮ ቃጠሎና ቅዝቃዜ ያልበገራቸው ስንት ደርባባ እናቶች አሉ?*

ለይኩን ፈዞ እንደቆመ እናቱ ቃልም ሳይተነፍሱ መጥተው አቀፉት። ውስጣቸው ሽጉጥ አለ። ምንም ቢመጣ የማይሰበር አይነት ሰላም ተሰማው። ከእቅፋቸው ሲገባ የሆነ የእረፍት ስሜት ውስጡን ሞላው። እናትኮ አለችው። ቃላትም ሳታወጣ ፡ ዝም ብላ ቁስሉን ማከም የሚቻላት | ከዚያም ቃላቶቿ ተተኩ፤

"አይዞህ የኔ ልጅ ፡ እሱ እግዚአብሔር ያውቃል።"

አዎን እሱ ያውቃል ፡ የለይኩንን መጨረሻ የሚያውቀው የፈጠረው ብቻ ነው። ከሱ በቀር ማንም አያውቅም። ለይኩን ቁስሉ በእናቱ ፍቅር ማስታገሻ ተነስንሶበት ያንን ሌሊት በከፊልም ቢሆን ተኝቶ ማደር ቻለ።

በማግስቱ ጥዋት ፊቱን በውኃ አብሶ፡ ቁርሱን ቀማምሶ ሲወጣ አንድ እቅድ ነበረው፤ ኤልሳን ማግኘት። ሰፈሯ ደርሶ የጎርፌ እንጀራ ቤት ጋር ቆመ። ያን በጆ የተቆረጠ ባለ ካኪ ጃኬት ልጅ አሁንም ብይ ሲያንከባልል አገኘው። ባለፈው ትቶት ከሄደ በኋላ ንቅንቅ ያለ አይመስልም። እዚሁ ከብዮቹ ጋር ሲንከባለል ይሆናል ውሎ ያደረው። ልጁ ሲጠራው እንዳልሰማ ሆኖ ዝም አለው። ባለፈው ልኮት ሲያበቃ ድንች በሚጥሚጣ አልገዛም ብሎታል፤ ድጋሚ የሚሸወደው እሱ ልጅ እንጂ ጅል አይደለም።

"ና አቡሽ ድንች እገዛልኻለሁ፤" አለው ለይኩን፤ ልጁ ጊዜና ቦታን ፉርሽ ባደረገ ፍጥነት ለይኩን ጋር ደረሰ። ሳንቲሙን ተቀብሎ፡ ኤልሳን የመጥራት ግዳጅ ተረክቦ ወደነ ኤልሳ ቤት ከነፈ። ካፍታ ቆይታ በኋላ ድንቹን እየገመጠ ወደ ለይኩን መጣ።

"ጠራሃት?"

"ወ…ወይኔ ረሳሁት!" ፡ አለና ድጋሚ ፈር ብሎ ሄደ። ሲመለስ ከኋላው ኤልሳ ተከትላው ወጣች። በተለመደው አኳኋኗ ሰው እንዳያያት እየፈራች ነበር የመጣችው። ነተብ ያለ ቱታና ነጠላ ጫማ ተጫምታለች። ያኔ እሷም ሚኒስትሪ ፈተናዋን ጨርሳ እረፍት ላይ ነበረች።

"ወዬ ለይክ? ምነው በጥዋት መጣኽ? ... ደሞ እዚህ አትምጣ ብዬክ አልነበር?!" አለችው፡ ዙሪያ ገባውን አየ'ት አየት እያደረገች።

"ድብር ብሎኛል ኤልሲ፤"

"ምነው?"

"እም… ማትሪክ ፈተናኮ ወደቅኩኝ"

ኤልሳ ለይኩን የሚላትን ወደ መሬት አውርዳ ለመተርጎም ትንሽ ጊዜ ፈጀባት… "ወደቅኩኝ ማለት? ... አልገባኝም… እና ዩኒቨርሲቲ አትገባም ማለት ነው?" ፊቷ ተለዋወጠ።

"አዎ… እንደዛ ማለት ነው ኤልስ፤" አለ ለይኩን በጫማው ምናምንቴ ነገር ከመሬት እያንከባለለ። የኤልሳ ፊት ላይ ተስፋ ቢስነት ሲያጠላ አስተውሏል።

"እና አንተ ዩኒቨርሲቲ ገብተህ ብር ካላገኘኽ ወደፊት እንዴት ነው አብረን መኖር የምንችለው?" ... ከብዙ መፋጠጥ በኋላ የቀረበለት ጥያቄ

ነበር።

"አይዞሽ...ብዙም አንቸገርም ፡ ያገኘሁት ማንኛውም ሥራ በሙሉ እሠራለሁ፤ ጋራዥ፣ እንጨት፣ ጉልበት ሥራ፤ ማንኛውንም ሥራ..." አለ ለይኩን፤ ሐሳቡን እንድትቀበለው በሚማጸን ለዛ፤

"ከባድ ነው!" ... ኤልሳ፤ ውስጧ በብዙ አይነት ስሜቶች ሲሞላ ይታወቃታል። ለይኩንን ስትወዳጀው ትልቁ ገፊ ኃይሏ ተስፋ ነበር፡ ጠንካራ ልጅ ነው፤ ለራሱም ደህና ደረጃ ደርሶ እኔንም ያሳልፍልኛል የሚል ተስፋ፤ ያ እቅድ ዛሬ አመድ ለበሰ። አሁን ምን እንደምታደርግ መወሰን አለባት። ከምትጠላው የቤተሰቦቿ የድህነት ህይወት ወጥታ ሌላ ድሃ ቤተሰብ መመስረቱን ስታስበው ግን ከወዲሁ አንገሸገሻት።

"ልግባ በቃ ለይኩ!" አለችው ቀዝቀዝ ባለ ድምጽ፤ በቅጽበት ውስጥ የዳሰሰችውን የሐሳብ ናዳ ግን አልነገረችውም።

"ይሻላል?" አለ ለይኩን፤ መመለሷ ደስ አላለውም። ሳያገኛት ነው ያጣት። ምንም ሳትለው ትታው ወደ ቤቷ ገባች። ከመቆም ባልተናነሰ እያዘገመ ወደ ቤቱ ተመለሰ።

ያን ሰሞን እየተመላለሰ ኤልሳን ለማግኘት ጥረት አድርጓል። ያ ባጀ የሚቆረጥ፡ ድንች ወዳዱን ልጅ፡ አንዳንዴ በጉቦ፡ አንዳንዴም በልመና ወደ ቤቷ ይልከው ነበር። ነገር ግን "የለችምና ሥራ ይዛለች"ን የመሳሰሉ ምላሾች ይዞ ብቻውን ይመለሳል። ቀስ በቀስ ተስፋ መቁረጥ ጀመረ። ልታየው እንዳልፈለገች እየገባው መጣ። ሲያመጣው አንዴ ነው እንዲል ያገሬ ሰው ከሁለት ያጣ ሆነ። ይሄን መራራ እውነት የተረዳ እለት ቤቱ ገብቶ እንደ ህጻን ልጅ አለቀሰ። ለቀናት ማንንም አላወራም፣ ምግብ አላሰኘውም፣ ሰው አልፈለገም ፡ በቃ ለብቻው ተከዘ።

*(አንዳንድ ብሶቶቻችን ብቸኝነትን የግድ ይሻሉ። ሰው ሲያዋራን እንኳ የሚያስጠላን ጊዜ አለ። ለብቻችን፣ በዝምታ መተከዝ እንሻለን፣ ድምጽ በሌለው ህምታና እንባችን በኩል ሐዘናችን እስኪወጣልን ድረስ እንቆረፍዳለን። ወደ ውጭና ወደ ውስጥ አልቅሰን የሚቀልልን ጊዜ አለ።) ለይኩንም ብቻውን ተከዘ፣ ከዓይኖቹ ብዙ እንባዎች ተመረቱ።*[16]

16 *የታዳጊነት ህይወታችን አንዱና ትልቁ አሻራ የት/ቤት ህይወታችን ነው፡፡ ከቤተሰብ ውጪ ሌላ ዓለም የማያውቅ ብላቴና በት/ቤት ከጉራማይሌ የሰው አይነቶች ጋር ይቀላቀላል፡፡ በተለይ የአስራዎቹ መጀመሪያ ላይ ያሉት ኢድሜዎች በሥነ-ልቦና ባለሞያዎች ዘንድ የማንነት ፈር መለያ፣ በራስ መተማመንን መመሥረቻ ብሎም የነገን ተስፋ

ሁኔታውን ከእናቱ ግን መደበቅ አልሆነለትም። እናት የልጇን ስሜት ማወቂያ አንቴና አላት እንዲሉ ህመሙን አወቁበት፤ ከሱ እኩል ተጎዱ። ፈተና መውደቁ የልጃ̈ን ቅስም ሰበረው ብለው አብረውት ተከዙ። ልጄ ሳይበላ እኔ አልበላም ብለው ተራቡ። ናላቸውን እያዞረ የሚጥላቸው፣ ያልታከሙት ህመም እየባሰባቸው መጣ።

ለይኩን ይሄን ሲያይ ልቡ ተነካ። ለእናቱ ሲል መበርታት እንዳለበት ገባው። ቢያንስ እናቱ ሲያዩት የውሸት ፈገግታን ማስመሰል ተካነበት። ለእርሳቸው ሲል እህል መቀማመስ ጀመረ።

ከዚያ ሰሞን ፈታኝ ቀናት በአንዱ ታዲያ ቁጭ ብሎ ስለሆነው ነገር ብዙ አሰበ። እሺ ፈተናውን መውደቁስ በኤልሳ ተዘናግቶ ስላላጠና ነው። ኤልሳን ያጣው ግን ለምንድነው? እንደዚያ የሚጣፍጥ የፍቅር ጠብታ አቅምሰው አሁን ለምን ጥርቅም አድርጋ ዘጋችው? መልሱን ለማግኘት ብዙ ኳተነ። በተለይ የዘጋችው ፈተናውን ከወደቀባት ቀን ጀምሮ መሆኑ አሳዝኖታል፤ ለምን ግን ያን አደረገች? ሲል ራሱን በተደጋጋሚ ጠይቋል። "ስለምትጠላኝ አይሆንም! ትወደኛለችኮ!... " የተሻለ ህይወት መምራት እንደምትፈልግ ደጋግማ የነገረችው ትዝ አለው። አዎን የዘጋችኝ ተናዳብኝ ነው ብሎ በደምሳሰው ለማመን ተገደደ። የወደፊት "ኑሯችንን የተሻለ የማድረጊያ እድሌን ስላበላሸሁ አኩርፋኝ ነው።" አለና፤ ይሄ በእርግጥም መሰረት ያለው ምክንያት እንደሆነ ራሱን አሳመነ። ቀጥሎ ያውጠነጠነው ወደፊታቸውን እንዴት ማስተካከል ይችላል የሚለው ነጥብ ላይ ነበር። ሳይደግስ አይጣላምና በትምህርቱ ቢወድቅም በደህና ጊዜ ጋራዥ እየሄደ ያዳበረው የብረታ ብረት ሙያ እንዳለው ያውቃል። አንዱ በር ሲዘጋ ሌላው ይከፈታል የሚባል ይህም አይደል?

በማግስቱ፡ በጥዋት ተነስቶ ተክለኃይማኖት አካባቢ ወደ ሚገኘው፣ እጁን ወዳፍታታበት ጋራዥ ነበር ያቀናው። የሚያውቁትን አሠሪዎች አገኘና ድጋሚ በኮንትራት ተቀጠረ። ለይኩን ወጥሮ ሥራውን መስራት ጀመረ። እንደሱ እምነት ጠንክሮ ከሠራ ብር ያገኛል። ብር ካገኘ ደግሞ ኤልሳ ወደሱ ትመለሳለች። በቃ አለቀ፤ ዓለም ሰመረች ማለት አይደል?

---

የመቅረጫ ወይም ዝቅተኝነት ስሜት የመሸበቢያ ወሳኙ እድሜ ነው:: በግሌ በተለይ በማኅበረሰባችን ትውልድን የመቅረጽ ሂደት ትልቁ ክፍተት ያለው በእዚህ የእድሜ ክልል ይመስለኛል:: ልጅ ራሱን እንዲያገኝ፣ መክሊቱን አከብሮ እንዲያዳብርና የሥራ ባህሉን እንዲያሳድግ ከማድረግ ይልቅ "ልጅ ያቦካው... ቀስ ብለህ እደግ... አርፈህ ተማር!" የሚሉ ማስፈራሪያና ስኬትን በትምህርትና በንግድ ብቻ ማግኘት የሚቻል እንዲመስል ተደርጎ የተቀረጸ ባህል አለ:: ሁሉም የሰው ልጅ ግን ከት/ቱ ውጤትም ሆነ ኪሱ ካለው ብር እጅግ የላቀ ጥልቅ መሰጠትና የየራሱ ልዩ ማንነት፣ ዋጋና ውበት አለው::

*ህይወት ግን እንዲህ ቀላል አልነበረችም! እቅዱ ግብተኛነት እንዳጠቃው ለመረዳት አስራ አምስት ቀን ብቻ ነበር የፈጀበት።*

ለይኩን በነዚያ ቀናት ውስጥ በሥራው ታተረ። ብረት ሲቆርጥና ሲበይድ መዋል ያዘ። ከሌሎቹ የጋራዡ ሠራተኞች በላይ ግራይንደሩን እየያዘ የሚቆራረጡ ብረቶች ላይ በረታባቸው። ብዙ ቀን ዲስኩ ብረቱን ሲሰነጥቅ የሚፈጥረው ፍንጥርጣሪ ዓይኑ ውስጥ እየገባ አሰቃይቶታል። እናም ጋራዥ ውሎ ማታ ወደ ቤት ሲመጣ በጀርባው ተንጋሎ ይተኛል፤ ከዚያም ዓይኑን ብልቅጥ አድርጎ ይከፍታል። ማግኔት ዓይኑ ላይ አድርጎ የብረት ቅንጣቶችን ለማውጣት ይታገላል። እናቱ በበኩላቸው በሳሙና ፈቱን እሸት እያደረጉ ሊያጥቡት ይሞክራሉ። ዳግም በማግስቱ ጥዋት ዓይኑ ደም እንደለበሰ ወደ ሥራው ይሄዳል።

ሆኖም እንዲህ ባይኑ ደም ተፍቶ ለሠራው ሥራ የምትከፈለው ብር እዚህ ግቢ የማትባል አይደለችም። እሷም ትንሽ ነች ፤መውጫዋም ብዙ ነው። የሱ ቢጤ ሠርቶ አደሮች ደሞዝ ከእጅ ወደ አፍ ለመኖር ቢሆን እንጂ ህይወትን የሚቀይር አልነበረም። *(ዓለም አንዳንዴ ለአውርቶ አደሮች ታደላለች።)*

ለይኩን የጋራዡ ባለቤቶች፣ አሠሪዎቹ ከደንበኞቻቸው የሚቀበሉትን ብር ሲያይ ሁሌም ቅናት ያድርበት ነበር። ለዚያ ላብን ለሚያንጠፈጥፍ፣ ዓይንን ለሚያሞጨሙጭ፣ የብየዳው ፍላጻ ብሌንን ለሚወጋ፣ የግራይንደሩ ፍንጣሪ ሰውነትን ለሚጠረቁስ ሥራ፡ ተቀጣሪው የሚያገኘት ክፍያ ስላቅ መስላ ታየችው። ለራሱ ብዙ ካመዛዘነ በኋላ ተቀጥሮ መሥራት እንደማያዋጣው ወሰነ። በሥራው የተሟላ ህይወት መኖር ካለበት እንዳሠሪዎቹ ያለ ቀርሺ[17] ማግኘት እንዳለበት አመነ። ያኔ አንድ ሐሳብ ብልጭ አለለት፤ ለምን የራሴን ጋራዥ አልከፍትም?

በበነጋታው ወደ ሥራ ገብቶ ብዙም ሳይቆይ ነበር ሐሳቡን ለሥራ ባልደረቦቹ ያጋራቸው። ባንድ ድምጽ ከት ብለው ሳቁበት፤

*"አንቺ አባቴ በቃ ለይቶልሻል ፡ ያኔ ፈተናዋን ከወደቅሽ በኋላ ወሰደ እያደረገሽ ነው።"* አለ ከመካከላቸው በቀልደኛነቱ የሚታወቀው ልጅ፤

"ጋራዥ መክፈት ቀላል ነገር መሰለህ እንዴ ጀለሴ? መበየጃ ማሽን ብቻውን ስንት ብር እንደሚሸጥ ታውቃለኽ?"

---

17 ብር፡ አፋን-ኦሮሞ

"አላውቅም።" አለ ለይኩን፤

"እኔም አላውቅም ባክህ!" አለ ጠያቂው እየሳቀ፤

"እስከ አሥር ሺህ ብር ይገኛል፤" አለ ከመሐከላቸው በእድሜም፡ በልምድም በለጥ የሚለው ጎልማሳ፤

*ይህ ሰው ኮስታራ ስለሆነ ማንም አይቀርበውም። ጅብሪል ይባላል። ብቸኝነትን የሚመርጥ፣ ዝምተኛ ሰው ነው። እድሜው አርባዎቹን እየተሻገረ ቢሆንም አላገባም፡ አልወለደም። ይሄን የገለልተኛነት ኑሮ ይወደዋል። በሥራ ቦታም ብዙ አይጫወትም። ነገር ግን በሥራው እሱን የሚያክል ባለሙያ ጋራዦችን አስሶ ማግኘት አታካች ነው። በሚሠራቸው የግቢ በሮችና መስኮቶች ላይ ይጠበብባቸዋል ማለት ይቻላል። በጊዜው በሸገር ከተማ እጅግ የተዋቡ የብረት በሮችና መስኮቶች ካዩ ምናልባትም የሱ እጆች ያረፈባቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ከልቡ ነው የሚሠራው...*

"አው ውድ ነው፤ በቃ አንድ አሥር ሺህ ዓመት ብር ካጠራቀምሽ ትገዢያለሽ፤" አለና ቀልደኛው ልጅ የለይኩን ቅስም ላይ አላገጠ፤

"እንዴ ደሞ መበየጃ ማሽን ብቻውን አይበቃምኮ፤ ግራይንደር፣ ድሪል፣ ከተር... ኧረ ስንት ነገር ያስፈልጋል?!" አለ ሌላኛው በያጅ፤

"እና ለማጠቃለል ያኽል ለይክሻ... ይሄንን የማይጨበጥ ህልምህን ብናደንቅም... በጀት የለንም።" አለ ቀልደኛው። "ይልቅ ያን የሆቴል ቤት በር ቶሎ ፑንታ አድርግና ጨራርስለት፤ ከሰዓት እመጣለሁ ብሏል።" አለና የወሬያቸው መግቻ ሆነ።

ጥዋቱን ብረት ከብረት ሲጋጭ፣ እሳትና ሊድ ሲነድ፣ ብረት በኤሌክትሮድ ሲለበድ አረፈደ። የድምጽ መዓት፣ የጥዝዝ... ቅንጣቶች፣ ገጭ : ጓ... ኳኳታዎች፡ የጋራዥ መለያዎች ናቸው። *{ከጉልበት ሥራው ባሻገር ይሄንን ሁካታ ችሎ፣ እጆችን አሻክሮ ላገር እድገት አሻራ ማኖር ካላስከበረ ምን ሊያስከብር ነው?}*

ሰባት ሰዓት ሲሆን ሁሉም ሠራተኞች ለምሳ እረፍት ወጡ።

...የነተበ ሰማያዊ የሥራ ልብሳቸውን ዚፕ ከፍተው፡ እጅጌውን ወገባቸው ላይ እያሰሩ ምሳ ለመመገብ ሄዱ። ከጋራዣቸው አጠገብ የምትገኝ ትንሽ ምግብ ቤት አለች። ጥዋት ጥሩ ፉል፣ ለምሳ ደግሞ ‹የተቀመመች በያይነት› ታቀርባለች። የብዙ ሠርቶ አደሮች አለኝታ የሆኑት የምግብ ቤቷ ባለቤት

ራሳቸው ወ/ሮ የተቀመመች የሚል ስም ወጥቶላቸዋል።

ለወትሮ ምሳውን ለብቻው መብላት የሚያዘወትረው ጅብሪል ዛሬ ከለይኩን አጠገብ መጥቶ ተቀመጠ። የተቀመመች በያይነታቸውን አዘው እየጠበቁ ሳለ ለይኩንን ያዋራው ገባ፤

"እነርሱን አትስማቸው፤ ከበረታህ የማይቻል ነገር የለም፤ ሰዉ ስላጣጣለኽ ተስፋ አትቁረጥ።" አለው ወደ ለይኩን ዞሮ፤

ለይኩን ምክሩን ተቀብያለሁ በሚል አንገቱን አነቃነቀ። የሥራ ባልደረቦቹ በጣም ቅስሙን ሰብረውት ነበር።

"የእውነትም ግን የራስህ ጋራዥ ለመክፈት እቅድ አለህ?" ሲል ጠየቀው፤ ጅብሪል ቀልድ አያወራም፣ ቀልድ ቢያወራ ራሱ ቁም ነገር የሚመስልበት አይነት ሰው ነው።

"አዎን" መለሰ ለይኩን፤

"ልክ ነህ፤ ተቀጥረኽ እየሠራህ ኑሮህን መለወጥ አዳጋች ነው። እኔም ለረጅም ጊዜ ሳስበው የነበረ ነገር ነው።" አለና ጅብሪል በጨረፍታ አይቶት ቀጠለ፤ "ኢንሻላህ... ጥሩ፣ ለጋራዥ የሚሆን ቦታ አግኝቻለሁ በሠራሁባቸው ዓመታት ደግሞ ብዙ ደንበኞችንም አፍርቻለሁ።"

"ታዲያ ምንድነው የቀረው?" አለ ለይኩን፤ በአዲስ ተስፋና ጉጉት፤

"ማሽኖች ነው የቀሩኝ፤ ቢያንስ መበየጃ ማሽኑንና ግራይንደ ያስፈልገናል።"

"እና ሁለቱን ካገኘን ጋራዥ መክፈት እንችላለን እያልከኝ ነው? ስን ብር ያስፈልገናል ትላለህ በድምሩ?"

"አንድ ሃያ ሺህ ብር ካገኘን መክፈት እንችላለን። እስካሁን አሥር ብር ገደማ አጠራቅሚያለሁ።" አለ ጅብሪል። ይሄንን ምስጢሩን ለሰ ሲያካፍል የመጀመሪያ ጊዜው ነበር። "አንተም የእውነት ፍላጎቱ ካለ ቤተሰብ ወይም ዘመድ ቀሪውን ብር የሚያበድርህ ቢገኝ በሽርክና መክ እንችላለን።"

"እውነት?" ለይኩን በችኮላ ጠየቀ፤ ከተስፋው ጥንካሬ ብዛት እንደሌለው ራሱ ረስቶታል።

"በሚገባ፤ እኔ ዋና በያጅ ሆኜ ከባዶቹን ሥራዎች እሠራለሁ፤ አንተ እንደ ረዳትም፥ እንደ በያጅም ሆነ ታግዘኛለኸ። አንድ ሰው ጨምረን ከቀጠርን በቂ ነው።" አለ ጅብሪል። ከልቡ እንደሆነ ፊቱ ብቻ ምስክር ነው። ሲጀመር ንግግሩ ከዝምታው ካልተሻለ የማያወራ አይነት ሰው ነው። ዋዛና ቧልት አይወድም።

ምሳቸውን በልተው፤ ሂሳብ ከፍለው ሲወጡ ለይኩን ፊት ላይ የሆነ አይነት አዲስ ተስፋ ይነበብ ነበር። ከሰዓቱን በሙሉ ብር ማግኛ መንገዶችን ሲያወጣና ሲያወርድ ዋለ። አስራ አንድ ሠዓት ደርሶ ወደ ቤት መሄጃያቸው ሲቃረብ ወደ ጅብሪል ጠጋ ብሎ አንድ ጥያቄ ጠየቀው።

"ለምን ግን እኔን መረጥከኝ?"... ጅብሪል ሳያየው ነበር ጥያቄውን የመለሰለት... *"ምን መሰለኽ| ቢዝነስ ለመሥራት የማይሆን ሰው ሦስት ባህሪያት አሉት፤ እነርሱም ውሸት፣ ስንፍናና ሱስ ናቸው። እስካሁን ሦስቱንም አንተ ላይ አላየሁብክም።"*

⌘ ⌘ ⌘

ዶ/ር ሶፎኒያስ የውኃዎች መገኛዋ ቢሾፍቱ፣ የፍቅር ቅባት ማደሪያዋ ደብረ-ዘይት፣ የኢሬቻ ገለታ ማቅረቢያዋ ቢሾፍቱ፣ የምህረት ኪዳን፤ የሐብተወልድ አድባር ያለባት ውብ ከተማ ሲደርስ የለበሰው ጃፖኒ ብቻ ነበር። ከአዲስ አበባ ሲወጣ የነበረው ነፋሻማ አየር ቀስ በቀስ በሚወብቅ ሙቀት ተቀየረ። እናም ፀሐይ ቃልም ሳታወጣ ኮትና ሸሚዙን አስወልቃ በጃፖኒ አስቀረችው። ደብረ ዘይት እንደደረሰ መኪናውን እየዘወረ ወደ እጥቤ ሰፈር ገባ። እዚህ ግድም የሐብታም ቤቶች ግቢ በኮሽም ሌላው ደሞ በሰንሰል ታጥሮ ማየት የተለመደ ነው። ተፈጥሮ ያበጀቻቸው የኤሌክትሪክ አጥር ምትኮች ይመስላሉ።

ከመጣ ትንሽ ስለቆየ የአክስቱ ቤት እንዳይጠፋበት ፈርቶ ነበር። ነገር ግን ዥርግግ ብሎ የበቀለው የኮሽም ዛፍ ያኔ እንደነበረው ከነፍካቱ ነበር የጠበቀው። ‹ክላክሱ›ን ሲያጮህ ዘበኛው የግቢውን በር ከፈቱለት። መኪናውን ቦታ ካስያዘ በኋላ ሻንጣውን አንግቦ ወደ ውስጥ ገባ።

አክስቱ ኢሴቴ የስም እንጂ የእድሜ አክስቱ አይደለችም። በትንሽ ዓመታት ነው የምትበልጠው፤ ፊቷ በፈገግታ እንደተሞላ መጥታ ግጥም አድርጋ ሳመችው። አያቷ ጋር ስላደገች በኦሮምኛ ቋንቋ ነው አፏን የፈታችው። አማርኛ ስታወራ ደስ የሚል ለዛና ኩልትፊያ አላት።... "ያቺ

ቲኒሽ ሊጅ አሁን ትልቅ ሰውዬው ፡ ዶክተሩ ሆነ!" አለች ከእግር እስከ ራ በስስት እያየችው።

"አይ አክስቴ! እንዴት ነሽ ግን አንቺ?" ሶፎኒያስ በደስታ ተሞል መለሰና ከሶፋው ላይ ተቀመጠ፤

"ኪዳነ ምህረት ቲመስገን፤ እኛ ደና ነው፤" አለችና አጠገቡ ተቀመጠች እድሜዋ ገና ይሁን እንጂ ሰውነቷ በጣም ወፍራም ስለሆነ ትልቅ ወይዘ ያስመስላታል። ዶክተር ሶፎኒያስ ስላያት በጣም ደስ ብሎታል። ለካ ናፍቃዋለች። (አንዳንድ ሰው እንደናፈቀን የምናውቀው ስናገኘው ነው። እቃውን የተዘጋጀለት ክፍል አኑሮ፣ ገላውን ተጣጥቦ ሲመለስ፤

"ሚሳ ይቅረባ ሶፍዬ ... ?" ብላው ብድግ አለች።

"አንቺ የሠራሽው ጣፋጭ ነገር ከሆነ ብቻ ነው የምበላው፤" እየቀለደ መለሰላት። "ራኮን ሂንጂሩ ፡ ቤቱ ያፈራው አለ!" ብላ እየሳቀች ወደ ማብሰያ ክፍል ገባች። ከአፍታ በኋላ ፈገግታና መብል ይዛ ተመለሰች። የቢሸፍቱ ሐይቅ ያፈራው፤ የተጠበሰ ዓሣ ከአንጮቴ[18] ጋር ነበር ያዘጋጀችለት። ሶፎኒያስ ያኔ ለጋ ወጣት እያለ ሲመጣ ዓሣ ጥብስ በጣም ይወድ ነበር፤ ያንን ስለምታውቅ እንደሚመጣ ሲነግራት በማለዳ ሄዳ ነበር ዓሣውን ገዝታ፤ ከአንጮቴ ጋር አዘጋጅታ የጠበቀችው። ምግቡን አቅርባለት አምቦ ውኃ ልትገዛለት ወጣች።

ሶፎኒያስ በልቡ አክስቱን እየመረቀ ምግቡን በሙሉ ትኩረት አጣጣመው። ከረጅም ጊዜ በኋላ ነበር እንዲህ ምግብን አጣጥሞ የተመገበው። ይህን ሲያስተውል አንድ ጥናት ትዝ አለው ፡ በረብሻ የተበላ ምግብ አይጣፍጥም የሚል። (ጥሩ ምግብ ዝግጅት ራሱን የቻለ ጥበብ ነውና በጥሞና ማጣጣም ያሻል፤)

ከስንዝር ቆይታ በኋላ አክስቱ አምቦ ውኃውን ይዛ ገባች። "ቢላ እንጂ ሶፎዬ፣ ላኒተ ብዬ ነው የሠራሁ!" አለች።

"አውቂያለሁ አክስቴ፤ በጣም ይጣፍጣል!" አለ ሶፎኒያስ፤ ...አምቦ ውኃውን ከፍታለት ካጠገቡ ተቀመጠች። ምግቡን ሲጨርስ አክስቱ ድጋሚ ብድግ ብላ ቡና ልታፈላ ሽር ጉድ ማለት ጀመረች። እሱም ሰውነቱን እያሳሳበ አፍታታ፣ የመንገዱን ድካም አቃለለ። መሰናዶውን

18 አንጮቴ ከተባለ ተክል፣ አይብና ቅቤ ተደርጎ የሚሠራ የኦሮሞ ብሔረሰብ ባህላዊ ምግብ፤

ጨርሳ ቡናቸውን እየተጎነጩ ብዙ ተጨዋወቱ፤ ወደ ኤረር ተራራ መሄድ እንዳሰበና መንገድ የሚያሳየው አጋር እንደሚያስፈልገው ነገራት፤ እሷም እንደምታገናኘው ነግራው ስለ ሥራው፣ ስለ ቤተሰብ፣ ስለ ልጅነቱ እያወጉ ሲሳሳቁ መሸና ወደ ተዘጋጀለት መኝታው አቀና።

በማግስቱ የሚያግዘው ሰው ለማግኘት ብዙ አልተቸገሩም፤ ገመቺስ የተባለ ሰውነተ ደንዳና የቢሸፍቱ ወጣት መንገዱን ሊያሳየው ተስማማ። አክስቱን ተሳናብቶ ሲወጣ የፀሐይ ሙቀቷ ገና ምድርን አላጋለም ነበር። በሰቼቶ ወደ ቢሸፍቱ ሰሜናዊ አቅጣጫ ተጓዙ። ከዚያም ጋሪ ተሳፈሩ። ገመቺስ በጉዘው ወቅት ስለ ቢሸፍቱ የልጅነት ትውስታዎቻቸው እያጫወተው ነበር። ዶክተር ሶፎኒያስ ከሰማው ተነስቶ ከተማዋ የብዙ ባህል፣ ቋንቋና ኃይማኖቶች ቋት እንደሆነች የሚያውቀው እውነታነት አረጋግጧል።

እሮብ ገበያን አለፍ እንዳሉ ከመንገዱ ባሻገር የሚታይ አንድ አርበ ሰፊ ዋርካ ከዶክተር ሶፎኒያስ ዓይን ገባ። ዛፉ የሆነ የሚማርክ ግርማ አለው። *{ዛፉኮ ዝምታ ውስጥ ነው፣ ንቅንቅ አይልም፡ ግን ያየውን ሁሉ ቀልብ ይገዛል። ለዘመናት በተመስጦ ውስጥ ያለ ጠቢብን ይመስላል።}*

እንዴት እንዲህ ቀጥ ብሎ የቆመ ነገር የተንቀሳቃሹን ልብ ማሸፈት ይቻለዋል? ብሎ ተመራመረ። ጥያቄውን ሳይመልስ ግን ዓይኑ ከሌላ ነገር ላይ አረፈበት። ልብ ብሎ ለማየት ሞከረ። አልተሳሳተም እራሳቸው ናቸው። ያኔኮ ድጋሚ እንገናኛለን ሲሉት አላመናቸውም ነበር።

"እዚህ ...እዚህ ጋር አውርደኝ!" አለው ድንገት ወደ ባለጋሪው ዞሮ፤

"ምነው ጌታዬ መዳረሻችንኮ ገና ነው።"

"ኖ! እዚህ ነው መውረድ የምፈልገው።" አለና ቁርጠኛ ውሳኔውን አሳወቀ። ጋሪውን አቁሞለት፣ ሲወርድና ገና መሬቱን ሲረግጥ እዚህ ቦታ ላይ እንደሚቆይ ውስጡ ነገረው። *{አንዳንድ ቦታዎች የኛ የነፍስ ጥሪያችን መዳረሻዎች እንደሆኑ የሚገባን ነገር አለ። ይህም ግን ለተጠሩት ብቻ ነው።}*

ለገመቺስ የሻይ ብር ሰጥቶት ተሰናበተው። አብሬህ ልምጣ ብሎ ቢለምነውም ብቸኝነትን ስለፈለገ አልፈቀደለትም። እስከ መቼ ሊቆይ እንደሚችል ስላላወቀ ተመልሶ የሚመጣበትን ቀን ራሱ አልነገረውም ነበር። እሱን በችኮላ ሸኝቶ ወደ ዛፉ ሲዞር ያኝን አባት በድጋሚ አያቸው።

ግዙፉ ዛፍ ሥር ዓይናቸውን ጨፍነው ተቀምጠዋል። ልክ እንደ ዛፉ እርሳቸውም ስክን፣ ቀጥ፣ ዝም ብለዋል። የዛፉን አይነት ሞገስ ከቧቸዋል... ሞልቷቸዋል።

ዶክተር ሶፎኒያስ ቀስ እያለ ወደርሳቸው ተጠጋ። ዓይናቸው ቢከደንም የሚያዩት ስለመሰለው ፍርሃት ቢጤ ወረረው። ለግማሽ ሰዓት ያኽል ድምጹን አጥፍቶ ቢጠብቃቸውም ከተመስጧቸው አልነቁም ነበር። በመጨረሻ ትዕግስቱ ተሟጠጠና ጉሮሮውን አጥርቶ ሰላምታ አቀረበላቸው፤

"አባቴ እንደምን ዋሉ?" ፡ ቃላቶቹ ባካባቢው የነበረውን ጥልቅ ጸጥታ አደፈረሱት። ጸጥ ባለ ስፍራ አንድም ፊደል ረብሻ ናት። ቃላቶቹ ከዛፉ ሥር ያሉት አባት ጋርም ደርሰዋል። ዓይናቸውን በዝግታ ከፈቱ። እድሜ ጠገብ የነፍስ ብልጭታ ባይናቸው በኩል አፈትልኮ ወጣ። ዶክተር ሶፎኒያስን ሲያዩ ፊታቸው በራ።

"እንኳን በደህና መጣህ ልጄ፤" አሉት ለዘብ ባለ ቃና፤

"ይቅርታ ረበሽኩዎት መሰለኝ፤" አለ ሶፎኒያስ እየተናነሰ፤

"የለም... በጭራሽ!"

"እንዲያው ዝም ብዬ እስኪጨርሱ መጠበቅ ነበረብኝ መሰለኝ!" አለ ሶፎኒያስ፤

"ምንም ችግር የለውም... እስኪ አረፍ በል መጀመሪያ..." አሉትና ካጠገቡ ያለ የድንጋይ ቋጥኝ ጠቆሙት። አመስግኖ ተቀመጠ። ላፍታ ያህል ሳያወሩ ቆዩ ፡ እስኪናገሩ እየጠበቀ ገጽታቸውን በውሉ አስተዋለ... ነጭ ጋቢና ደመናማ ጺማቸው ካንድ ጥጥ የተሰሩ ድርና ማግ ይመስላሉ። ፊታቸው የጥሩ ገበሬ እርሻን ያስንቃል ፡ ተራሮችና ሸለቆዎች ፡ የህይወት ስኬቶችና ውድቀቶች አሉበት። {ጠቢብ የሆነ ሽማግሌ ሲያገኙ ከልጅነቱ ጀምሮ ጠቢብ ሆኖ ያደገ የሚመስላቸው ብዙ ሰዎች አሉ:: አበው እንደሚሉት ግን ‹እድሜ ትምህርት ቤት ነው፤› | የትምህርት ቤቱ አይነት ግን በጣም ይለያያል::}

በመሐል ..."ወዴት እየተጓዝክ ነው?" ፡ ሲሉት ካሳቡ ነቃ፤

"እም... ወደ ኤረር ተራራ ነበር የምሄደው፣ እርሶን ሳይ ነው የወረድኩት።"

"መልካም ነው፤ እዚያስ ምን ልታረግ ይሆን አካሄድህ?" ብለው ሌላ ጥያቄ አስከተሉና ባይናቸው ገረመሙት፤

መልሱ ከገመተው በላይ ቀለል ብሎ ካፉ ወጣ፤ "እኔ ዝምታን ፍለጋ ነው ከአዲስ አበባ የመጣሁት አባ።"

"ማለፊያ ነው፤ ግን አንድ ነገር ልጠይቅኽ... ሰው አዞኽ ነው ወይስ ራስኽ ፈልገህ ነው እዚህ የመጣኽው?"

"ኧረ በፍጹም ፡ በራሴ ፍላጎት ነው የመጣሁት።"

"እንደዛ ከሆነ ጥሩ።" አሉና አንድ ነገር እንደሚያይ ሰው ከሩቅ አድማስ ላይ አተኩረው ቆዩ፤ ቀጥለውም "ይኸውልኽ... ይሄንን ጥያቄ የጠየኹህ በምክንያት ነው። ዝምታን... ራሳችን ፈልገነው ካገኘነው ጥበብ ነው፤ በሰው ተገደን ዝም ካልን ደግሞ የቁም እሥር ነው። አብዛኛው ሰው ዝም የሚለው በራሱ ምርጫ ሳይሆን ያለበትን ማኅብረሰብ ወግ፣ የሥራ ቦታ ደንብ፣ አያውቅም መባልን ወይም ሰውን ፈርቶ ነው። በተለይ ይህ የቱማታ ዛር የወረረው ትውልድ ከእውነተኛው የዝምታና የጥሞና ፍሬ በእጅጉ የራቀ ነው። እንዳልኩህ ዝም ሲል እንኳን የሚናገረው ነገር ስለሌለው አልያም ተሳስቶ አያውቅም ላለመባል ነው። በእውነት አንተን መሰል ጥበብ ፈላጊ ሰው በዚህ ጊዜ ማግኘት ግን መታደል ነው፤ ለዚያም ነው ምክንያትህን የጠየኩህ፤ ...አትርሳ አንድን ነገር የምናደርግበት ምክንያት ውጤታችንን ቀድሞ እንደ ራዕይ ያሳያል፤ ነገን ዛሬ ይወጥናል።"

ዶ/ር ሶፎኒያስ ይሄንን ሲነግሩት ምን እያሉት እንደሆነ በከፊል ገብቶታል። ግን ይበልጥ እንዲያብራሩለት ስለፈለገ "ለምሳሌ በትምህርት ቤት ልጆችን ዝም እንዲሉ ስናስፈራራ አስረናቸዋል ማለት ይቻላል?" ብሎ በምሳሌ ጠየቃቸው፤

"ምን መሰለኽ?... እኛ ልጆቻችንን ዝም በሉ እያልን በጩኸት እያስበረገግን ነው ቤት ውስጥ የምናሳድጋቸው፤ ትምህርት ቤት የምንቆጣቸው:: እንዴት ዝም ማለት እንደሚችሉ ግን አናስተምራቸውም:: ዝምታ ግዴታ እንጂ ምርጫቸው እንዲሆን አንቀርጻቸውም:: ሰው ያልተማረውን ከየት ያመጣል? ልጆች ከኛ ያዩትንና የተማሩትን ነው የሚያንጸባርቁት፤ እኛ ያልተለማመድነውን ጥሞናና ጸጥታ ከየት ሊለምዱት ይችላሉ? ዝምታን ሳይሆን መዋከብን በሳምንት ሰባት ቀን ኖረን እያስተማርናቸው በዝምታ ማሳላሰል የሚችል ትውልድ መፍጠር

የሚያለን ይመስልሃል?" ... አሉና በጥያቄ ተመለከቱት፤

"የምንችል አይመስለኝም። እርግጥም ልክ ብለዋል... ግን እኛስ ካለ ድምጽ፣ ካለ ቃላት እንዴት መኖር እንችላለን?"

"ካለ ቃላትም፣ ካለ ጸጥታም መኖር ሙሉ አይደለም። ጸጥታን እንደ ጠላት ቆጥረን ብንሸሸው እንኳን ወደድንም ጠላንም የህይወታችንን አብዛኛውን ክፍል ጸጥ ማለት ግዴታ ሆኖብናል። እንቅልፍ በአማካይ የሕይወታችንን አንድ ሶስተኛ የሚወስድ የጸጥታ ዝምታችን ነው ፤ ህልም ከምናልምባቸው፣ ቅዠት ከምንቃዠባቸው ቅጽበቶች ውጪ ተኝተን እስክንነቃ ጸጥ እንዳልን እንቆያለን። ብቻችንን በምንሆንባቸው አብዛኛዎቹ የቀን ሰዓታት ባንፈልግም ጸጥ እንላለን። የቃላት አጠቃቀማችንን እንኳን ካለ ጸጥታ ክፍተቶች ትርጉም የላቸውም። እናም ተፈጥሮ በራሷ ጸጥታን ትጫወትበታለች። ዋናው ነገር ግን ጸጥታን ሳንፈራ መለማመድና ፍሬውን እናስተውል ወደ ዝምታና እርምጃ መደረብ መቻል ነው። ለዚህም ነብያት ከተራራ፣ መነኮሳት ከበረሃ፣ ቀሳውስት ከሀገር ብቻቸውን ተቀምጠዋል፤"

"ይገርማል... በግሌ ድምጽን ተፈጥሮ ብዙም እንደማትወድ እኔም ባለፈው ሳስብ ነበር። ግን ቃላትም አስፈላጊ ናቸው ብዬ አምናለሁ።"

"ትክክል ነኽ ግን ጸጥታና ዝምታ ይለያያሉ። ጸጥ ማለት የግዴታ፣ ዝም ማለት ደግሞ የምርጫ ጉዳይ ነው። ዝምታን መረዳት ቃላትንም ለመረዳት ይጠቅማል። ጥሩ ሙዚቀኛ ለመሆን ጥሩ ጉሮሮ ብቻ ሳይሆን ጥሩ ጆሮም ያሻል። አይመስልህም?"

"በሚገባ አስማማለሁ፤ ግን ዝምታን በከተማ ውስጥ ሆኖ ማግኘት በጣም ከባድ ነገር ነው የሆነብኝ። ለዚህም ነው ወደዚህ ለመምጣት የወሰንኩት..." አለ ሶፎኒያስ፤

"ጥሩ አደረግክ... ይህ ለብቻ መገለል የሰባኪያን ሁሉ መነሻ ተግባር ነው፤ እንግዲያውስ በል ና ተከተለኝ፤" ብለው ብድግ አሉ፤

"ወዴት ልንሄድ ነው?" አለ ሶፎኒያስ ተከትሏቸው እየተነሳ፤

"እንደ ወደ ኤረር ተራራ አይደል የምትሄደው?"

"አዎን"

"በል ተከተለኝ እንግዲያውስ..."

ዶ/ር ሶፎኒያስ አንዴ ብቻ መንገድ ላይ ያያቸውን አባት ተከትሎ ወደ ማያውቀው መንገድ ጉዞ ጀመረ። እየሄዱ ሳለ ከኋላ በቅጡ ተመለከታቸው፤ ብርቱ ሽማግሌ ናቸው። ቡላማ ቀሚሳቸውን ሰብሰብ አድርገው በእጃቸው ይዘው ነበር የሚነጉዱት። ቅልጥፍናቸው በጣም አስደመመው። ጥሻዎችን እያሳበሩ ከአድባር ጊዮርጊስ ባሻገር፣ ከጉዲዋ ተራ እስከ ሚጊራ ባለ ወልድ ቤተ ክርስቲያን፤ ማዞሪያ ታጥፎ በስተሰሜን አቅጣጫ ወደ ሆራ የሚወስደውን መንገድ ይዘው ዘለቁ። ይህ መንገድ በጋሪ ግልቢያ ግማሽ ሰዓት ገደማ ይፈጃል። ብዙ ከፊትና ከኋላ ሆነው ከተጓዙ በኋላ ለይኩን፤ ውስጡ የሚመላለሱትን ጥያቄዎች ጠየቃቸው። ..."እርሶ ግን ማን ኖት? ባለፈው እንዴት አውቀው ነው ድጋሚ እንገናኛለን ያሉኝ? ለምንስ ሊረዱኝ ፈለጉ?"

ምንም መልስ ሳይሰጡት በጨረፍታ አየት አደረጉትና "ለሁሉም እውቀት የመገለጫ ጊዜ አለው።" ብለውት ጉዟቸውን ቀጠሉ። የተወሰነ አድካሚ መንገድ ከተጓዙ በኋላ አንድ የተንጣለለ ሐይቅ ጋር ደረሱ።

"እዚሁ ትንሽ እንረፍና፤ አዳራችንን የካህኑ መልኬጼዴቅ ህቡዕ ደብር እናደርጋለን። ረድኤታቸውን ተቀብለን ነገ እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ ወደ ኤረር ተራራ እንጓዛለን።" ብለውት፤ የሐይቁን ትዕይንት በግላጭ የሚያሳይ ቦታ መርጠው አረፍ አሉ፤

"ደብረ-ዘይት ውስጥ ስንት ሐይቆች እንዳሉ ታውቃለህ ዶክተር?" አሉት ተቀምጠው ትንሽ ትንፋሻቸውን መለስ ካደረጉ በኋላ፤

"አላውቅም።" አላቸው በውስጡ ዶክተር መሆኔን መቼ ይሆን የነገርኳቸው እያለ እየተወዛገበ።

"…ያሉት ሰባት ሐይቆች ናቸው። ሰባቱም ውስጥ ለውስጥ ይገናኛሉ። እንዲሁ ሁሉ ሰባት ቅዱሳን ተራሮችና ህቡዕ ዋሻዎችም አሉ። ታዲያ ሰባት የሆኑት በምክንያት ነው።… ይሄ ከፊታችን ተንጣሎ የምታየውና ብዙሃኑ ሰው የማያውቀው ሐይቅ ሆራ አንጋፋይ ይባላል። ይህም በኦሮምኛ ሆራይ ማለት ሐይቅ ሲሆን አንጋፋይ ደግሞ አንጋፋ ወይም ታላቅ የሚለውን ይገልጻል። ከሰባቱ ሐይቆች አንጋፋው ይህ ስለሆነ ነው። እንዲህ የተባለው በፊት ከሌሎቹ ሰለበለጠ ግን እንዳይመስልህ።" አሉና ሐይቁ ላይ አተኩረው ቀሩ።…

"ታዲያ ለምን ይሆን ታላቁ የተባለው?" …ሶፎኒያስ ጠየቀ፤

የሚቻለን ይመስልኻል?" ... አሉና በጥያቄ ተመለከቱት፤

"የምንችል አይመስለኝም። እርግጥም ልክ ብለዋል... ግን እኛስ ካለ ድምጽ፣ ካለ ቃላት እንዴት መኖር እንችላለን?"

"ካለ ቃላትም፣ ካለ ጸጥታም መኖር ሙሉ አይደለም:: ጸጥታን እንደ ጠላት ቅፍለት ብንሸሸው እንኳን ወደድንም ጠላንም የህይወታችንን አብዛኛውን ክፍል ጸጥ ማለት ግዴታ ሆኖብናል:: እንቅልፍ በአማካይ የእድሜያችንን አንድ ሶስተኛ የሚወስድ የጸጥታ ገበታችን ነው ፡ ህልም ከምናልምባቸው፣ ቅዠት ከምንቃዥባቸው ቅጽበቶች ውጪ ተኝተን እስክንነቃ ጸጥ እንዳልን እንቆያለን:: ብቻችንን በምንሆንባቸው አብዛኛዎች የቀን ሰዓታት ባንፈልግም ጸጥ እንባለን:: የቃላት አጠቃቀማችንን እንኳን ካለ ጸጥታ ክፍተቶች ትርጉም የላቸውም። እናም ተፈጥሮ በራሷ ጸጥታን ትጭንብናለች:: ዋናው ነገር ግን ጸጥታን ሳንገደድ መለማመድና ፍሬውን አነኩተን ወደ ዝምታና አርምሞ መድረስ መቻል ነው:: ለዚህም ነብያት ከተራራ፣ መናኞች ከበረኻ፣ ቀዛፊዎች ከባህር ብቻቸውን ተቀምጠዋል፤"

"ይገርማል... በግሌ ድምጽን ተፈጥሮ ብዙም እንደማትወድ እኔም ባለፈው ሳስብ ነበር። ግን ቃላትም አስፈላጊ ናቸው ብዬ አምናለሁ።"

"ትክክል ነኽ ግን ጸጥታና ዝምታ ይለያያሉ። ጸጥ ማለት የግዴታ፣ ዝም ማለት ደግሞ የምርጫ ጉዳይ ነው። ዝምታን መረዳት ቃላትንም ለመረዳት ይጠቅማል። ጥሩ ሙዚቀኛ ለመሆን ጥሩ ጉሮሮ ብቻ ሳይሆን ጥሩ ጆሮም ያሻል። አይመስልህም?"

"በሚገባ እስማማለሁ፤ ግን ዝምታን በከተማ ውስጥ ሆኖ ማግኘት በጣም ከባድ ነገር ነው የሆነብኝ። ለዚህም ነው ወደዚህ ለመምጣት የወሰንኩት..." አለ ሶፎኒያስ፤

"ጥሩ አድርገኻል... ይህ ለብቻ መገለል የጠቢባን ሁሉ መነሻ ተግባር ነው፤ እንግዲያውስ በል ና ተከተለኝ፤" ብለው ብድግ አሉ፤

"ወዴት ልንሄድ ነው?" አለ ሶፎኒያስ ተከትሏቸው እየተነሳ፤

"እንዴ ወደ ኤረር ተራራ አይደል የምትሄደው?"

"አዎን"

"በል ተከተለኛ እንግዲያውስ..."

ዶ/ር ሶፎኒያስ እንዴ ብቻ መንገድ ላይ ያያቸውን አባት ተከትሎ ወደ ማያውቀው መንገድ ጉዞ ጀመረ። እየሄዱ ሳለ ከኋላ በቅጡ ተመለከታቸው፤ ብርቱ ሽማግሌ ናቸው። ቡላማ ቀሚሳቸውን ሰብሰብ አድርገው በእጃቸው ይዘው ነበር የሚነጉዱት። ቅልጥፍናቸው በጣም አስደመመው። ጥሻዎችን እያሳበሩ ከአድባር ጊዮርጊስ ባሻገር፣ ከጉዲኖ ተራ እስከ ሚጊራ ባለ ወልድ ቤተ ክርስቲያን፤ ማዞሪያ ታጥፎ በስተሰሜን አቅጣጫ ወደ ሆራ የሚወስደውን መንገድ ይዘው ዘለቁ። ይህ መንገድ በጋሪ ግልቢያ ግማሽ ሰዓት ገደማ ይፈጃል። ብዙ ከፊትና ከኋላ ሆነው ከተጓዙ በኋላ ለይኩን፤ ውስጡ የሚመላለሱትን ጥያቄዎች ጠየቃቸው። ..."እርሶ ግን ማን ኖት? ባለፈው እንዴት አውቀው ነው ድጋሚ እንገናኛለን ያሉኝ? ለምንስ ሊረዱኝ ፈለጉ?"

ምንም መልስ ሳይሰጡት በጨረፍታ አየት አደረጉትና "ለሁሉም እውቀት የመገለጫ ጊዜ አለው።" ብለውት ጉዟቸውን ቀጠሉ። የተወሰነ አድካሚ መንገድ ከተጓዙ በኋላ አንድ የተንጣለለ ሐይቅ ጋር ደረሱ።

"እዚሁ ትንሽ እንረፍና፤ አዳራችንን የካህኑ መልኬጸዴቅ ህቡዕ ደብር እናደርጋለን። ረድኤታቸውን ተቀብለን ነገ እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ ወደ ኤረር ተራራ እንጓዛለን።" ብለውት፤ የሐይቁን ትዕይንት በግላጭ የሚያሳይ ቦታ መርጠው አረፍ አሉ፤

"ደብረ-ዘይት ውስጥ ስንት ሐይቆች እንዳሉ ታውቃለህ ዶክተር?" አሉት ተቀምጠው ትንሽ ትንፋሻቸውን መለስ ካደረጉ በኋላ፤

"አላውቅም።" አላቸው በውስጡ ዶክተር መሆኔን መቼ ይሆን የነገርኳቸው እያለ እየተወዘገበ።

"...ያሉት ሰባት ሐይቆች ናቸው:: ሰባቱም ውስጥ ለውስጥ ይገናኛሉ:: እንዲሁ ሁሉ ሰባት ቅዱስ ተራሮችና ህቡዕ ዋሻዎችም አሉ:: ታዲያ ሰባት የሆኑት በምክንያት ነው::... ይሄ ከፊታችን ተንጣሎ የምታየውና ብዙሃኑ ሰው የማያውቀው ሐይቅ ሆራ አንጋፎታ ይባላል:: ይህም በኦሮምኛ ሆሪያ ማለት ሐይቅ ሲሆን አንጋፎታ ደግሞ አንጋፋ ወይም ታላቅ የሚለውን ይገልጻል:: ከሰባቱ ሐይቆች አንጋፋው ይህ ስለሆነ ነው:: እንዲህ የተባለው በስፋት ከሌሎቹ ስለበለጠ ግን እንዳይመስልኽ::" አሉና ሐይቁ ላይ አተኩረው ቀሩ።...

"ታዲያ ለምን ይሆን ታላቁ የተባለው?" ...ሶፎኒያስ ጠየቀ፤

"ሚስጥሩ ብዙ ነው ልጄ! ግን ሆ-ራህ የሚለው ቃል በጥንቱ ቋንቋችን ሐብትና ስልጣንን ጠቋሚ ነው። ውኃና ሐብት የተጣመሩ ነገሮች መሆናቸውንም አትርሳ። በቅድሚያ ቃሉ ሁለት ፊደላትን አቅፏል፤ "ሆ እና "ራ"። በጥንቱ የኩሼቲክ ሱባዊ ቋንቋ ትርጓሜ መሰረት ደግሞ "ሆኣ' ፡ ንቃትን መፍጠር፣ ሆ ፡ ብሎ ድምቀት እንደማምጣት ፡ ሆ ፡ ብሉ ጨለማውን እንደመግፈፍ ፡ ሆ ያህ … ሆ ዬህ ብሎ ያህዌን ይዞ ለአዲስ ብስ-ራ-ት እንደመነሳት ያለ ኃይል ሲሆን ፡ "ህዝቤ ሆ፡ይ" ተብሎ ሲጠራ ሆ! ብሎ ለድል እንደመውጣት ያለ ትርጉምም አለው።

"ራህ" ማለት ደግሞ ባለማወቅ ላይ እውቀትን የሚያበ-ራህ፣ በኃጢያት ጽልመት ውስጥ ብርሃንን እንደሚፈነጥቅ ጮ-ራህ፣ ብ-ራህ … የውስጥ ብርሃንን ማውጣት ያለ አበረታች የእግዚአብሔርን ኃይል ፡ ግእዙ ፈጣሪን ራህ፡ሙ፡ኤል እንዲለው ሁሉ፣ አሴፍ ላም ራህ በሚሉ ሚስጥራዊ ኪታቦች፣ በብ፡ራህ፡ና ላይ እንሚገለጽ የእውቀት ጸዳል ይወክላል።" አሉና ወደ ዶክተር ሶፎኒያስን ዞረው ሁኔታውን አነበቡት፤ ከገጽታውም ምንም እንዳልገባው ተረዱ። ገለጻቸውን ቀለል ማድረግ እንዳለባቸውም ገባቸው፤

"ሁሉም ነገር ቀስ እያለ ይገባኻል ልጄ … አትጨነቅ" አሉትና። በረጅሙ ትንፋሽ ወስደው ቀጠሉ፤ "ይሄንን ጉዳይ ለሌላ ጊዜ እናሳደረውና ዋና ወደ መጣህበት የዝምታ ጉዳይ ልመለስ። እም… ቅድም ከጠየከኝ ጥያቄ ስጀምርልህ ከሁሉም በፊት ዝምታ ማለት ጸጥ ማለት ብቻ እንዳልሆነ ማወቅ ይኖርብኻል። ዝምታን ማስተዋል፣ ጥሞና፣ እምነትና ብቸኝነት ያጅቡታል ፡ ያጸድቁታልም። እነዚህ አራቱን ልብ ብለህ ያዝ ፡ የዝምታ መሰረታውያን ናቸውና። እነዚህን ሲያገኝ ታዲያ የዝምታ ዘር ይጎመራል ፡ ፍሬው ደግሞ እርምሞ ነው።"

ይሄኛው ርዕስ በጉጉት ጸጉሩን ቀጥ ያደረገበት ሶፎኒያስ "እባክዎትን ያበራሩልኝ?" ሲል ተማጸናቸው። …

"እሺ ብዙም አታስብ፤ አራቱንም ተራ በተራ አብራራልኻለሁ። ለዛሬ ግን ስለ ማስተዋል በመጠኑ ላሳውቅኽ እሻለሁ። ፍቃደኛ ነኽን?"

"በሚገባ፤ ምክርዎትን መስማት እፈልጋለሁ ፡ ግን ቢያንስ ስሞትን ባውቅ ደስ ይለኝ ነበር።" አለ ሶፎኒያስ እያንገራገረ፤

"እሱ ቀስ ብሎ ይደርሳል ልጄ፤ አሁን ወደ ማስተዋል ትንታኔ እንመለስ፤ ልብ በል … "አውቃለሁኝ" የሚል ሰው ዝም ማለት አይሆንለትም።

ዝምታ አለማወቅን ማወቅ ይሻል። ለሁሉም ጥያቄ መልስ አለኝ ብሎ የሚታበይ ሰው ዝም ማለት እንዴት ይቻለዋል? አዎ እንዳልከው ውጫዊ ድምጾች ይረብሹናል። ግን ቅድሚያ እኛ ነን እኛን የምንረብሸው። ማስተዋል ስለሌለን ወደ ዝምታ የማንገዘው። ማንኛውም ውጫዊ ድምጾች የሚረብሹን እኛ ከፈቀደንላቸው ብቻ ነው። እናም እንዳትሳሳት፡ ቴክኖሎጂ መጥፎ አይደለም። የኛ አጠቃቀምና አለማወቅ ነው መጥፎ። እውቀት ስልህ ደግሞ ወደ ሌላ እውቀቶች አታማትር። አሁንም የእውቀት ምንጭ ከላይ ነው። ምንጩን ከቀዱ በኋላ ግን የሚያደፈርሱ ከታች አሉ። እኚያም ዝም ያላሉ፣ የተረበሸ ስብእናና ልቦና የገነቡ ከንቱ የሰው ልጆች ናቸው፣" አሉና ረገጥ አድርገው ቀጠሉ… "ልጄ ዝምታ የቃላት አለመኖር አይደለም። ቃላት አስፈላጊም ብቻ ሳይሆኑ ውበትም ናቸው። የፍጠረት ሁሉ ጅማሮ ቃል እንደሆነ አትርሳ። ግን ቃልም ከዝምታ ነው የወጣው። ደመና በሌለው ጨለማ ቀና ብለህ ሰማዩን ብታይ ብዙ የሚያበሩ ኮከቦችን ታያለኽ። እነሱ ብርሃን ናቸው፣ የሰማዩ ትርጉም ናቸው፣ ውበት ናቸው። ግን አንድ ነገር ልብ ካልክ ልጠይቅኽ፤ ኮከቦቹ የተበተኑበት ጠፈር ባዶ ቦታ ስፋት፣ ወርድና ቁመት ከኮከቦቹ አይበልጥም? ኦናው ከመከሰቱ አይገዝፍም? ያልተገለጠው ከተገለጠው አይልቅም?"

ዶክተር ሶፎኒያስ ንግግራቸውን ቃል በቃል እያስተነተነ ነበር የሚሰማቸው። ዝም ብለው ቢጠብቁትም ጥያቄም መልስም እንደሌለው ባይኑ አሳበቀላቸው። "እናም ዝምታ ጠፈር ነው። ቃላት ደግሞ እንደ ከዋክብት ናቸው። ሰማዩ ሰፊ ነው። ከዋክብት ሲኖሩ የሰማዩን ሰማይነት ይመሰክራሉ። ጨለማውና ብርሃኑን ይለያሉ። ግን ካለመስካሪ በአርምሞ የሚኖር ደግሞ ከዙፋኑ አለ።

እነሆ ቃላት እንደ ጨው ናቸው። ህይወትን የሚያስቀጥል ጥፍጥናን ያድሉናል። የገበታ ወጣችን ጣዕም እንዲኖረው ጨው መነስነስ ያሻናል፤ ጨው ከሞጀርንበት ግን አያስበላንም ፡ ወጡ ይደፋል።

ቃላት እንደ መድሀኒት እንክብሎች ናቸው። አስፈላጊ ቢሆኑም በጊዜና በመጠን የሚወሰኑ፤ ከልኩ ካለፉ ግን ጉዳትና ሞት የሚያስከትሉ። ለዚህም ከቀጭን ቃላት ይልቅ ወፍራሙን ዝምታ ማዘውተር የጠቢባን መንገድ ነው።" አሉና ምክራቸውን ለጊዜው አበቁ፤

"አባቴ፡ እውነት ለመናገር የሚነግሩኝ ነገር እጅግ አስተማሪ ሆኖ ነው ያገኘሁት። ለኔ መልስ እንዲሰጡ ፈጣሪ የላከዎት በረከቴ እየመሰለኝ ነው።

ከልብ አመሰግናለሁ።"

"አትቸኩል ልጅ ሶፎኒያስ! ለማመስገኑ ትደርስበታለህ... መንገዳችን ገና አልተነካም። ይልቁንም ያልገባህ ነገር ካለ ደግሞ ዋሻው ጋር ስንደርስ ትጠይቀኛለኽ።" አሉትና ፈንጠር ብለው ብድግ አሉ፤ እንዲህ በየመሐሉ የሚያይባቸው ድንገቴ ብርታት እድሜያቸውን እንዲጠራጠር ያደርገዋል።

ከቦታው ሳይርቁ ዶክተር ሶፎኒያስ የሆራ አንጎፍታን ሐይቅ ለመጨረሻ ጊዜ በስንብት ዓይን ተመለከተው፤ ስክን ብሎ የተዘረጋው ሰላሙ አስቀናው። ሌላ ጥያቄ የሆነበት ነገር ቢኖር ይሄን የመሰለ የሐይቅ ዳርቻ *እንዴት ‹ሪዞርትና ሆቴሎች› አልተገነቡበትም? እንዴት ጥሩ መንገድ አልተሠራለትም? ከዋና ከተማዎች በቅርብ ርቀት የሚገኝ አሞቺ ስፍራ እንዴት ተረሳ?* የሚል ነበር። የልቡን ያወቁ ይመስል ሽማግሌው ... "ከዚህ ስፍራ ሳንርቅ አንድ ነገር ልነግርህ እፈልጋለሁ። ያንን ግዙፍ ዛፍ አየኸው?" አሉት ትንሽ እንደተራመዱ፤... "አዎን"

"ያካባቢው ሰዎች በየተወሰኑ ቀናት ሽምግልና ይቀመጡበታል፤ አለፍ ብሎ ያለው ሜዳ ደግሞ የሰሜን፣ የሸዋ ዐማራና የቢሾፍቱ ኦሮሞ ማኅበረሰብ ቋንቋ ሳይገድበው ይገናኛል ፡ ይገበያያል ፡ ይተጫጫል፤ ከብቶችን ከዚህ ሐይቅ በዓመት አንዴ ማጠጣት ከብዙ ክፉ ነገር ይጠብቃቸዋል የሚል እምነት ስላለ፡ ከዓመት አንዴ ከቅርብም ከሩቅም መጥተው ከብቶቻቸውን ውኃ የሚያጠጡ ኢትዮጵያውያን አርብቶ አደሮችም እልፍ ናቸው። እናም እንዳሰብከው ባለሐብቱና ባለስልጣናቱ ዓይን ውስጥ ያልገባው በምክንያት ሊሆን ይችላል።" አሉትና ሳቅ ብለው አይተውት መንገዳቸውን ቀጠሉ።

ዶ/ር ሶፎኒያስ ያሰበውን እንዴት እንዳወቁ ግራ ተጋባ፤ ራሱንም መጠራጠር ጀመረ። ሌሎች ሰዎች ሐሳቤን እየሰሙብኝ ነው ብሎ ማመን ደግሞ የአእምሮ ህመም ምልክት እንደሆነ ያውቃል።

ምን እየሆንኩኝ ነው?

እኚህ እንግዳ ሰው ምን እያደረጉኝ ነው?

...ብዙ ጥያቄዎች ቢፈራረቁበትም እየተከተላቸው ነበር።

* ✡ *

# ምዕራፍ አምስት - 1

## የድሀ ፍቅር

እነ ሜሮን ግቢ ካለ አንድ ክፍል የአስቴር አወቀ ዘፈን ከቴፕ አልፎ፣ ለ‹ቴምፓኒ›[19] ዘልቆ፣ ከ‹ቴምፖራል›[20] ተተርጎሞ፡ ልብ ላይ ይፈሳል…

*"♪ በሰባራ ፎሌ ውኃ አይጠለቅም*

*እኔ እወድኻለሁ ያንተን ግን አላውቅም!*

…

*ለመድክ ወይ ፍቅሬ አንተ አንጀቴ ሆይ?*

*ፍቅር ከኔ ሌላ ተስማማህ ወይ?*

*…ፍቅርህን ለኔ ትተህ ስትሄድ ወደ ሌላ*

*ትንሽ ተሰቃየሁ እህልም ሳልበላ …*

*በጣም ተሰቃየሁ እህልም ሳልበላ"*

"አንቺ ሜሮን ይሄንን ሙዚቃሽን ድምጽ ቀንሰሽ አትሰሚም?" አሉ የሜሮን እናት - ወ/ሮ እልፍነሽ ወደ ክፍሏ በር ተጠግተው፤

ሜሮን… "እሺ እማ፤" አለችና የቴፑን ድምጽ መቆጣጠሪያ ወደ ግራ አዞረችው።

"ይልቅ ነይና ሥራ አግዢኝ፤ የአያትሽ መምጫ ደርሷል።"

"ወይኔ… አባባ ሊመጡ ነው እንዴ?" አለች ሜሮን ትካዜዋ ባንዴ እየለቀቃት። ካልጋዋ ፍንጥር ብላ ተነሳታ ከክፍሏ ወጣች።

---

19 የድምጾች ተቀባይ የጆሮ ክፍል፣ ታምቡር፤

20 የድምጾች ተርጓሚ የአንጎል ክፍል፤

"የምርሽን ነው እማ?... አባባ ሊመጡ ነው?"

"እዩልኝ እንግዲህ የደስታ መዓት!" አሉ ወ/ሮ እልፍነሽ፤ ጥርሶቻቸውን ገሽለጥ አድርገው እየሳቁ፤

"ያው አባባ አባባ እንዳልሽ! ሊመጡልሽ ነው እንግዲህ፤"

ሜሮን ትካዜዋ ለጊዜውም ቢሆን በኖ ጠፋ። ሁሉን ነገር ረስታ እናቷን ሥራ ማገዝ ጀመረች።

አያቷ አባ በላይን በጣም ትወዳቸዋለች። አንዳንዴ ከእናት ከአባቷ በላይ ትቀርባቸዋለች። በልጅነቷ የተወሰኑ ዓመታትን እርሳቸው ዘንድ አድጋለች፤ የልቧን የሚያውቁላት፣ በነጻነት ጭንቀቷን የምታወያያቸው፡ አያቷ ናቸው።

አያቷ በጎልማሳ እድሜያቸው አዲስ አበባ ከተማ ነበር የሚኖሩት። 20 ዓመት አብረው ከቆዩት ሚሽታቸው ጋር ጥሩ የሚባል ኑሮ ነበራቸው፤ ከአማካዩ የአዲስ አበባ ኗሪ ህይወት ከፍ ያለ ዘመናዊ አኗኗር ነበራቸው፤ ያ አባ በላይ ... ቡላማ ኮትና ሱሪ ያዘወትሩ ነበር። በመጠኑ ተጎፍሮ ችምችም ያለው ጸጉራቸው ሞላ ካለው ፊታቸውና ሰፊ ደረታቸው ጋር ታክሎ በሄዱበት ሁሉ ልዩ ግርማ ሞገስ ያላብሳቸው ነበር።

አርበ ሰፊ ባለቤታቸው የሜሮንን እናት እልፍነሽን ጨምሮ አምስት ልጆች ወልዳላቸዋለች። አንዱ በጥይት፣ ሁለቱ በህመም ሞቱ፤ ሌላው ደግሞ ውጭ አገር በስደት ሄዶ ኑሮውን እዚያው መሠረተ። እልፍነሽ ብቻ ብረት መዝጊያ የሚባል ባል አግብታ እዚሁ ቤተሰብ መመሥረት ቻለች። ታዲያ ልጆቻቸውን ማጣቱን አባ በላይና ሚሽታቸው ተደጋግፈው አልፈውት ነበር። ባለቤታቸው ሲሞቱ ግን አባ በላይ ሐዘኑን መቋቋም አልቻሉም፤ ብዙ ትዝታቸውን ሸክፎ የያዘ ቤት ውስጥ ብቻቸውን መኖር እንደ ቋጥኝ ከበዳቸው።

በአርባ አመታቸው የኖሩበትን ቤት ሸጠው፤ ከሰፈሩ ብቻ ሳይሆን ከከተማውም ጭምር ወጡና... ዱከምን አለፍ ብሎ የሚገኝ መሬት ገዝተው ገቡ። ብቸኝነት ውስጥ ሰተት ብለው ተከተቱ። ልጃቸው እልፍነሽ ከስንት አንዴ እየሄደች ትጠይቃቸዋለች። ከልጃቸው ውጪ ግን ሌላ ሰው ሳያዩ ወራት ይቆጠሩ ነበር።

ይህ ከሆነ ከአስራ ሰባት ወራት በኋላ እልፍነሽ ሜሮንን ወለደች፤ አራስነት ጊዜዋን አገባዳ ጠና ስትልና አቅም ስታገኝ የልጅ ልጃቸውን ይዛ ልትጠይቃቸው ሄደች። ታዲያ አባ በላይ ትንሽዬዋን ሜሮን ሲያዩ የአባትነት

ቆሌያቸው ዳግም ገዘፈ። አስተከዟቸው የነበረው አንቲካ ደብዝዞ ውስጣቸው በአዲስ ተስፋ ተሞላ። ሦስት ልጆቻቸውንና የሚወዷት ሚሽታቸውን በሞት የተነጠቁት አባ በላይ የመጀመሪያ የልጅ ልጃቸው የሆነችው ሜሮንን ሲያዩ እንደገና በረቱ፤...ሚጢጢ እጇን በሰፊ መዳፋቸው ላይ ስታላወስ የደስታ እክርማ ልባቸውን ዳበሰው፤ ሳሱላት።

ያን ሰሞን ትንሿ ሜሮንና አባባ በላይ ምርጥ ጓደኛ ወጣቸው። የሚነጣጥላቸው ጠፋ። ምኑንም በወጉ ሳየውቁት፡ ውዴታቸው ሳይሟጠጥ የነእልፍነሽ ወደ አዲስ አበባ መመለሻ ቀናቸው ደረሰ። ... *{የደስታ ወቅቶች እንዲሁ አጭር ናቸው። ብዙዎቻችን ለዓመታት ምድር ላይ እንገኛለን፤ በህይወት የምንኖርባቸው ዘላለማዊ እፉኝት ጊዜያት ግን ወራትም አይሞሉም። ሌላው ባዶ ቁጥር ነው።}* ለአባ በላይ የሆነውም ይሄው ነው .. ያቺ አንድ እፍኝ የደስታ ጊዜ እንደ ብርሃን ከንፋ አለፈች። እልፍነሽ ሜሮንን ይዛ ወደ ሸገር ስትመለስ ታላቅ ሐዘን ቤታቸው ውስጥ ተፈጠረ። ዳግም የድብርት ዝተት ሸፈናቸው።

ያ የሸሹት ብቸኝነት ዳግም ዝበባቸው። መናፈቅ ቢፀናባቸው ተነስተው አዲስ አበባ እየመጡ የልጅ ልጃቸውን እስከመጎብኘት ደረሱ። ነገር ግን የሞቱት ሚሽታቸውና ልጆቻቸው ትዝታ ስለከበዳቸው አዲስ አበባ ብዙም ሳይቆዩ ነበር የሚመለሱት። ለሜሮን ያላቸውን ፍቅር ስለተረዳች አንዳንዴ እልፍነሽም ልጇን ይዛ ትሄድ ነበር። አንዳንዴም ሜሮንን እርሳቸው ዘንድ ላንድ ሁለት ወር ትተዋትና ድጋሚ ሄዳ ይዛት ትመለስ ነበር ። ...ሜሮን አምስት ዓመት ሞልቷት ትምህርት ቤት ስትገባ ግን ነገሮች ተቀየሩ። ወደሳቸው መሄድ አልቻለችም። ዳግም ብቸቸኝነት የሁልጊዜ ደባላቸው ሆነ። ብቸኝነትን ሽሽት አማራጮችን ፈለጉ።

ታዲያ ያን ሰሞን አንዳንድ ገዳማት እየሄዱ ሰንበትበት እያሉ ይመለሱ ነበር። የሆነ ቀን ግን ለማንም ሳይናገሩ ድንገት ወጥተው ለሁለት ዓመታት ጠፉ። ደብዛቸው አልተገኘም። ልጃቸው ወ/ሮ እልፍነሽ የቻለችውን ያህል አፈላለገቻቸው፤ ነገር ግን ሊገኙ አልቻሉም። የመኖሪያ አካባቢያቸውን ሰዎች አጠያየቀች፣ ለፖሊስ አመለከተች፣ በሚዲያ አስነገረች... ልፋቷ ሁሉ ፍሬ አልባ ነበር።

...|ይህ የሆነው ሜሮን ገና የአምስት ዐመት ፋንድሻ እያለች ነው። ለረጅም ጊዜ በልጅ አንደበቷ "አባባ የት ጠፉ?" እያለች መጠየቋን ግን አላቋረጠችም ነበር። ... ለጥያቄዋ መልስ ሳታገኝ፡ እርሳቸውም ሳይገኙ ዓመታት ነጎዱ።

⌘ ⌘ ⌘

እንዲህም ሆነ፤

...ሜሮን የአስራ አራተኛ ዓመት ልደቷን ባከበረች በሳምንቱ አንድ እንግዳ ሰው ጨው በረንዳ ሰፈር መጡ። በዝግታ እየተራመዱ ወደ ሰፈሩ ሲዘልቁ ብዙ ሰው ዓይን ውስጥ ገብተዋል። የሚያውቃቸው ግን ማንም ሰው አልተገኘም ነበር። ገጽታቸው ለየት ያለ ነው፤ ሽበት የወረረው ጸጉራቸው ከትከሻቸው ላይ ተነስንሷል። ዘረገግ ጺማቸው የደረታቸውን እኩሌታ አልፎ ተንጠልጥሏል። አናቱ የተቆለመመ መቋሚያ ተመርኩዘዋል፣ ረጅም ቡላማ ቀሚስ ለብሰዋል። ሲራመዱ እንደ ግመል በዝግታ ነው። በያንዳንዱ እርምጃቸው መሐል ቆም የማለት አዝማሚያ ይታይባቸዋል። ይለያሉ! የአባ-ቦራ መስጊድን አልፈው ሽቅብ ዘለቁ።

ማንንም ሳያናግሩ፣ ዙሪያቸውን እየገረመሙ ወደነ ሜሮን ቤት በቀስታ አቀኑ። በር ላይ ሴ-ማክሴ ስትጫወት የነበረችው ሜሮን ሰውዬውን ስትመለከት ድንግጥ ብላ ቆመች። ... "ሜሮን ልጄ፤" አሏት ፊታቸው በፈገግታ እንደተሞላ፤ ሜሮን የልጅነት ትዝታ ማህደሯን አገላብጣ የምትወደውን መልክና ድምጽ አስታወሰችው። "አባ... አባባ" አለችና ሮጣ እግራቸው ሥር ተጠመጠመች። የሙጥኝ ይዛቸውም ወደ ውስጥ ገባች፡ ወ/ሮ እልፍነሽ እንባዋ እየፈሰሰ አቅፋ ሳመቻቸው።

ሁሉም ሰፈርተኛ "እንኳን ደስ አላችሁ!" ሊል ወደነሱ ጎረፈ ፡ ቤታቸው በደስታ ተሞላ። ከዚያች ቀን በኋላ አባ በላይ ከስንት አንዴ እየመጡ ልጅና የልጅ ልጃቸውን ይጎበኙ ነበር። ከየት እንደሚመጡና ወዴት እንደሚመለሱ የሚያውቅ ግን ማንም አልነበረም፤ ሆኖም ጠፍተው ከተመለሱ በኋላ ግን ባህሪያቸው ከድሮ ለየት ብሏል። የቀድሞ ሐዘን፣ ጭንቀትና ፍርሃት አይታይባቸውም። ብዙ ከማውራት ይልቅ ዝምታን የሚያበዙ ሰውም ሆነዋል። ከሜሮን ጋር ሲሆን ግን እንደልባቸው ይጫዋወታሉ፤ ከሷ ጋር በታሪክ አይጠጋገቡም። እሷም ብትሆን ብዙ ምስጢሮቿን ታጋራቸዋለች፡ የእምቡጥ ወጣትነቷን ጥያቄና ጭንቀቶች፡ በነጻነት የምታወያያቸው ለርሳቸው ነበር።

⌘ ⌘ ⌘

ቤቱ ተሰነዳድቶ፣ ምግቡ ተዘገጃጅቶ እንዳበቃ የነሜሮን ግቢ በስሱ ተንኳኳ። ሜሮን እየበረረች ሄዳ በሩን ከፈተች። አባባ በላይ በሩ ላይ ቆመዋል፤ ተጠመጠመችባቸው፤ በርከክ ብለው አቀፏት። ናፍቆታቸውን

በመተቃቀፍ ካስታገሱ በኋላ ተያይዘው ወደ ቤት ገቡ።

ምሳ ተበልቶ ቡና ከተጠጣ በኋላ ወ/ሮ እልፍነሽ ለቅሶ ደረስ ብዬ ልምጣ ብለው ወጡ። አባ በላይና የሚወዷት የልጅ ልጃቸው ሜሮን ብቻቸውን ቀሩ።

"ሜሮን ልጄ?" አሏት፤ በሁለት ትውልድ አባታዊ ፍቅር እያዩት፤

"አቤት አባባ፤"

"አሁን ብቻችንን ስለሆንን ምን እንደዚህ እያስጨነቀሽ እንደሆነ እንድትነግሪኝ እፈልጋለሁ።"

ሜሮን በጭንቀት ውስጥ እንዳለች ማንም እንዳያውቅ በተቻላት ሁሉ ሞክራለች። ሐሳቧን ዋጥ አድርጋ በውሸት ፈገግታ አብዛኛውን ሰው ደህና እንደሆነች አሳምናለች። አያቷን ግን መሸወድ አልቻለችም።

"ደህና ነኝ አባባ ... ትንሽ የሆነች ነገር እያሳሰበችኝ ስለሆነ እንጂ ብዙም አልተጨነቅኹም።"

"ያቺ ትንሽ የምታሳስብሽ ነገርስ ምንትሆን?" አሏትና በመርማሪ ፈገግታ ገረመሟት።

"አባባ፤ ማርያምን ከባድ ነገር አይደለም... አታስብ።" አለች ሀፍረት ቢጤ እየተነበበባት።

እርሳቸው ግን ቀበል አድርገው : "ልጁ ግን ስሙ ማነው?" ሲሉ አፋጠጧት። ያልጠበቀችውን ጥያቄ ስለጠየቋት ደነገጠች።

"የቱ ልጅ?"

"የምትወጂው ልጅ።" ...

⌘ ⌘ ⌘

የዚያን ቀን ማለዳ...

ለይኩን ጅብሪል ጋራዥ እንከፍታለን ስላለው የተስፋ ጮራ ሰበሰበ። ይሄንን የዘሬ አለላ፣ የነገ ገበታ ይዞ ወደ ቤቱ መግባት አላስቻለውም። ወደነ ኤልሳ ሰፈር አቀና። ዛሬ እድል ወይም ኤልሳ ፊቷን አዙራለት ካገኛት ስለአዲስ እቅዱ ያጫውታታል። ተስፋውን ተጋርታው ወደሱ ትመለስም

ይሆናል...ማን ያውቃል?

ጎርፌ እንጀራ ቤት ሲደርስ ባለ ባጆ ቁርጡን ልጅ ከሩቁ አየው፡ አጋጣሚውን ላስተዋለ ትንሹ ልጅና ለይኩን ተቀጣጥረው የሚገናኙ ነበር የሚመስሉት። ፈላ[21]ውን መልእክተኛ በሄደ ቁጥር ያገኘዋል... ዛሬም ለይኩንን ሲያይ ወከክ አለና ጨዋታውን ጣጥሎ መጣ።

"እንዴት ነኽ አቡሽ?"

"ደህና ነኝ፤ ምነው ግን ጠፋክ እእ... ኤልሳ ጋር ተጣላችሁ እንዴ?" አለ ትንሹ ልጅ እንደማፈር እያለ፤ ያልጠበቀው ጥያቄ ስለነበር ለይኩንም ፈገግ አለ።

"አልተጣላንም አቡሼ፤ ባይሆን ዛሬም ሂድና ጥራልኝ እስኪ፤ በዚያውም ድንችህን ግዛ..." አለና ሳንቲም ወረወረለት ፡ አቡሽ እንደ በረኛ ተወርውሮ ቀለባት፤ ፈቱ በራ፤ (ደስታ መነሻው ከትርጉም እንጂ ከብዛት አይደለም።) በብርሃን ፍጥነት ነው እነ ኤልሳ በር የደረሰው። መልእክቱን አድርሶ፣ ድንቹን እየገመጠ ተመለሰ፤... "እምኛምኛም ...ኛም ... እምም_ የለችም..." አለው ፡ ድንቹን ለጉድ እያጣጣመ።

ለይኩን ኤልሳ ቤት ባለመኖሯ በጣም ከፋው። መቼ ይሆን አለች የሚባለው? መቼ ይሆን የናፈቀውን ፊቷን የሚያየው? በሳቋ ዜማ የሚሽመለመለው? የሆነ የሐዘን ስሜት ልቡን ክፉኛ አወከው፤ (በቀን ጭልም፣ በጤና ህምም፣ በሰላም አገር ክፍት ያደርጋል ፡ ሰው ሲናፍቅ፡ አንጀት ስፍስፍ፣ ጉልበት ድክም፣ ልብ ጭንቅ ይላል - ያ የሚወዱት ሰው ሲናፍቅ። ከባድ ነው!)

ብላቴናው ለይኩን ሐዘኑን ዋጥ አድርጎ ወደ ቤቱ ለመሄድ እርምጃ እንደጀመረ "ለይክ?" የሚል የሴት ድምጽ ከኋላ ጠራው። ኤልሳ መጣችልኝ ብሎ ልቡ ወከክ እንዳለ ዞሮ ቢመለከት ሜሮንን አያት። እየሮጠች መጥታ ተጠመጠመችበት።

"ሜሪዬ እንዴት ነሽ?"

"ደህና ነኝ ለይክ፣ በስማም ካየሁኽ ስንት ጊዜ?"

"ትምህርት ከተዘጋ በኋላ አልተገናኘንም አይደል?"

21 በአራዳ ቋንቋ ትንሽ ልጅ!

"እዎዋ! በጣም ቆየንኮ?"

"ህይወት እንዲህ ናት እንግዲህ... አንቺ ግን ደህና ነሽ? የውነት ይሄ እረፍት ተስማምቶሻል"

"ሃ ሃ ብለህ ነው? ..." አለችና ሜሮን ፈገግታዋን ከረጅም ትንፋሽ ጋር ሸኝታው ቀጠለች። "ይልቅ አንተ እንዴት ነህ? ደሞ ኤልሳ እንደተጣላችሁ ነግራኝ ነበር? ምን ሆናችሁ ነው?"

"ያው መጣላት እንኳን ማለት ይከብዳል ግን በመሐላችን ትንሽ ክፍተት ተፈጥሯል። ብዙም አንገናኝም። " አለ ለይኩን ከኤልሳ ጋር የተጣሉበት ጊዜ በትክክል ለማስታወስ እየተቸገረ - ለነገሩ መጣላታቸውንም በቅጡ አላመነበትም። ..."ለምንድነው ክፍተት የተፈጠረው አጫውተኝ እስኪ..." አለች ሜሮን፤

"ኧረ ሜሪ... ብዙ አስቆምሻለሁ፣ ይቅርብሽ" ብሎ ሊቋጨው ቢሞክርም ሜሮን ግን ቶሎ ልትለየው ፍቃደኛ አትመስልም።

"እንዲያውም ና እየሸኘሁ...‹ወክ› እያደረግን ትነግረኛለኽ፤" አለችና የቀኝ እጁን ክንድ ጥብቅ አድርጋ ይዛ መራመድ ጀመረች። በእርምጃዎቻቸው ‹ሪትም› ውስጥ ለይኩን ከኤልሳ ጋር ስለተፈጠረው ነገር ነገራት። ኤልሳ ለምን እንደራቀችው የሱን መላምት አስቀምጦ አወራት። ለጥቆም በሽርክና ጋራዥ ሊከፍት እንዳሰበና ብር እያፈላለገ እንደሆነ አጫወታት።

"ግን አሥር ሺህ ብሩን ከየት ለማግኘት አሰብክ?" አለች ሜሮን ልክ ለይኩን ንግርቱን ሲጨርስላት፤

"እ... እኔንጃ" ... ለይኩን ከነበረበት የምናባዊ ሐሴት ከፍታ የወረደው በዚህች ቅጽበት ነው ማለት ይቻላል። ከጅብሪል ጋር ያወሩት ነገር አዲስ ቀቢጸ ተስፋን ሰጥቶት፤ ብሩን ማግኘት እንደማይችል አስረስቶት ነበር። ላጠራቅም ቢል እንኳን ብዙ ወራትን ይፈጅበታል፤ ብር ሊያበድረው የሚችል ሰውም የለም። :ሜሮን የለይኩን ፊት ቅይርይር ሲል አስተዋለች። መሐል መንገድ ላይ ቀጥ ብሎ ቆመ፤ ከሜሮን ጋር መሆኑን ራሱ ረስቶታል። አንገቱን ደፋ፤ ፊቱ ላይ ተስፋው ሲደበዝዝ አሳበቀ። (ወንድ ልጅ አይጣ የሚባለው እውነትኮ ነው። ግን ግን ሴት ልጅስ ትጣ?) ... ሜሮን ውስጧ ርብሽብሽ አለባት። የለይኩን ነገር አይሆንላትም።

ተደነጋግሮ ... በቅጡ እንኳን ሳይሰናበታት ሄደ። ከኋላው ቆማ ከዓይኗ

እስኪርቅ ድረስ ፈዛ አየችው ፡ በልቧ ሸኘችው። ቤቷ ገብታም ስለሱ ብ
ነበር ያሰበችው። ጭንቀቱ ጭንቀቷ ነው። ትካዜና ሐሳብ ሲበዛባት እን
ልማድ አላት... የአስቴር አወቀን ለስላሳ ዘፈኖች ማዳመጥ። ካሴቷ
አጠንጥና ቴፕ ውስጥ ሰነገችው። ለዛ ያለው ዜማ መንቆርቆር ጀመረ
......*"በሰባራ ፎሌ ውኃ አይጠለቅም..."*

⌘ ⌘ ⌘

## ✍...ያፍቃሪዋ ማስታወሻ

ዛሬ ደስ ብሎኛል፡ ከፍቶኛልም:: ያ ልጅ፡ የልቤ ኩብል፡ ትንሽ
ቢሆን ከውሸት የፍቅር ዓለም እየወጣ ይመስላል:: በሌላ በኩል ደግ
ተጨንቋል። የሚወዱት ሰው ሲጨነቅ ማየት ምን ያህል ይረብሻል?
የሚወዱት በኑሮ መዳፍ ጥፊ ሲመታ ከማየት በላይ የሚያምስ ም
ቁስል አለ? ቆይ ምን ልሁንለት? ምንስ ሳድርግለት? ሳየው ያነደደው
የኑሮ መጥፎ ትንባሆ አመድ ማራገፊያ ብሆን እላለሁ፤ ገንጫው መሆ
ያምረኛል:: ማለት እሱን ከሚጨንቀው የፈለገ በላ እኔን ያግኘኝ፤ የሰማ
ቁራዎች ዓይኔን ይቧጡት፣ ውዴን ከሚከፋው ውስጥ እግሬን እሾ
ይውጋው:: የሱን ሐዘን ካልተካፈልኩት መገኘቴ ትርጉሙስ ምንድነው?
ድህነቱን እንዲያሸንፍ ካልረዳሁት ምንስ ልረባ?... ምንም!

⌘ ⌘ ⌘

*ካንድ ሣምንት በኋላ...*

ለይኩን ሣምንቱን ያሳለፈው በትካዜ ተውጦ ነበር። ጅብሪል
የጠየቀውን ብር ማግኘት ሰማይ ዘሎ እንደመንካት ራቀው። የዘ
ተክል በበረሃ እንደተከበበ ሁሉ ያሰባቸው እቅዶችም በድህነት ታጠሩ፡
ተስፋውንም ኤልሳንም ማጣቱ እያብከነከነው ከረመ። የሳምንቱ ቀዳማይ
ሰንበት ፡ ቅዳሜ ደረሰ። ያን እለት ካድካሚ የሥራ ውሎው እያዘገመ ወ
ቤቱ ሲመለስ እናቱ ፊታቸው እንደ ደማቅ ጨረቃ እያበራ ነበር የጠበቁት
... *"እማ ምን ተገኝቶ ነው እንዲህ ደስታ ፊትሽን የሞላው?"* ... ወ/ሮ
ብዙወርቅ ምንም ሳይመልሱ አንድ የተጠቀለለ ፖስታ ሰጡት። ለይኩን
ግራ እንደተጋባ ፖስታውን ተቀበላቸውና ከፈተው። ውስጡን ሲመለከት
ዓይኖቹ ብልጥጥ ብለው ተከፈቱ፣ አገጩ ወደ ታች ተደፋ ... ያየውን ነገ
ማመን አልቻለም። እጆቹ እየተንቀጠቀጡ ፖስታ ውስጥ ያለውን ብ
አወጣና ቆጠረው ፡ አሥር ሺህ የኢትዮጵያ ብር! ...የፖስታው ጀርባ አዞ

ሲያነበው አንድ ጽሑፍ አገኘ።

**"ለይኩዬ አንተ ህልምህን እንድታሳካ ከልቤ እመኝልኻለሁ፤ ይህቺ ገንዘብ ያሰብከውን ለማስፈጸም እንደምትጠቅምኽ ተስፋ አደርጋለሁ::"** ይላል፤ ስምም አድራሻም የለውም። ለይኩን ይበልጥ ግራ እየተጋባ እናቱን አያቸው። ከደስታው ይልቅ አግራሞቱ ግዝፈት ነስቶበታል። "ማ... ማነው ግን የሰጠሽ ፖስታውን?"

"አንድ ካኪ የለበሰ ትንሽዬ ልጅ ነው አምጥቶ የሰጠኝ።"

"ምንም አላለሽም? አንቺስ ማን ነው የሰጠኽ ብለሽ አልጠየቅሽውም?"

"ይሄን ያህል ሰነፍማ አታድርገኝ ልጄ፤ በደንብ ነው እንጂ የጠየኩት።"

"ምን አለሽ?".... "ልጁማ ‹አንዲት በነጠላ ፊቷን የሸፈነች ልጅ ናት እዚያኛው ቤት ላሉት እናት ይሄን ፖስታ አድርስ ያለችኝ› ብሎ ነው የነገረኝ፤ ከቤት ወጥቼ ዙሪያ ገባውን ባማትር ግን ልጅቱን ላገኛት አልቻልኩም። ... እኔማ" አሉ እናቱ ደስታቸውን ከፊታቸው ለመደበቅ ቢታገሉም ፈንቅሎ እየወጣባቸው። "እኔማ ቢቸግረኝ እመቤቴ ልመናዬን ሰምታ ለልጄ ደርሳለት ይሆን ስል ጠረጠርኹኝኮ..." አሉ፤ የየዋህ እናት ገጽታ ሞልቷቸዋል፤

"አይ እማ... እኔ ግን እመቤቴን ወዳጅ የሆነች አንዲት ባለ ደግ ልብ የፀደቀችብን ይመስለኛል!" አለ ለይኩን በደስታ ተገፍተው ውጮ ያደሩ ጥርሶቹን እንደምንም ወደቦታቸው ለመመለስ እየታገለ፤ የነገ ጋራዡ የሆነውን ብር አጥብቆ እንደያዘ፤ የዚህችን ምሥጢራዊ ሴት ማንነት ለማወቅ ሐሳቡን እያመሳሰለ። በደስታ ተገትሮ ቀረ... ⌘

...ከሦስት ቀን በፊት የእልፍነሽ ባል ብር ተዘረፍኩኝ ብሎ አገር ምድሩን ሲያምሰው ነበር። ማን እንደወሰደበት ግን አልታወቀም። ⌘

ዶ/ር ሶፎኒያስ የማያውቃቸውን አባት ተከትሎ ወደ ተራራው አቀና። በእርምጃዎቹ ዳና እንዴት እንዳመናቸው እያውጠነጠነ ነበር። {*አንዳንድ ሰውን እድሜ ልክ አውቀውት እንኳን ለማመን ይቸገራሉ። አንዳንድ ሰውን ደግሞ በሰከንዶች ውስጥ ልቦት ያምነዋል። የእምነትና የፍቅር አጥናፋት በጊዜና በቦታ አጥራት አይወሰኑም። የልብ መናበብና የነፍስ ቋንቋ አንዲት ቅጽበት ብቻ ይበቃቸዋል ፡ ፍቅርን ስታውቀው በነጥብ ውስጥ ዘላለምን*

ታገኝበታለህ... ከስንት አንዴ ቢሆንም ሰውን ታምናለኽ። ሶፎኒያስ አንዳንድ ሰው ለመተማመን ቀድመን እንጠናና ሲል ይሰማል። እናም ይጠይቃል የሰው ልጅ ግን ተጠንቶ ያልቃል ወይ? የሰው ልጅ በውስጡ ምን እንደሚያስብ ከማወቅኮ በቢሊዮን ኪሎ ሜትሮች ርቀት የሚገኝ ኮኮብን አጥንቶ መረዳት ይቀላል። የሰው ልጅ ህቡዕ ነው፤ ቅዱስ ስትለው እጥፊ፣ አጥፊ ስትለው ቅዱስ የሚሆን እንቆቅልሽ። ያም ሆነ ይህ ለሰው ልጅ ባለባት ቅጽበት የነፍስና ህሊናን ምክር ከመስማት በላይ አስፈላጊ ነገር የለም። የነፍስህን እድል ፈንታ፣ የእጣ ፈለግ ሲከተሉ ግን አእምሮን እንዳማከረ መሰየም አስፈላጊ ነው።}

ዶ/ር ሶፎኒያስ በዚህ ሐሳብ ውስጥ እያለ ሽማግሌው ሰው ድንገት ተናግረው ወደ እውነታው መለሱት| "ደርሰናል ልጄ፤"

"የት?" አለ ሶፎኒያስ ዙሪያውን ግራ በመጋባት እያስተዋለ፤ ድንጋያማ አለትና በዋንዛ ዛፍ የተከበበ ቦታ ላይ ነበር የቆሙት። ፈገግ ብለው አዩትና በስተግራ በኩል እጥፍ ብለው፡ ከጥሻው ውስጥ መሰስ ብለው ገቡ፡ ተከተላቸው። ትናንሽና ትላልቅ ድንጋዮች ተደራርበው የሠሩት፡ ሠወር ያለ የአለት ጎጆ ቤት ነው። ከጎጆ ቤት ይልቅ ግን ዋሻ ይመስላል። አጎንብሰው ዘለቁ። እሱም ተከትሏቸው ገባ። አራት ሰው ብቻ አግድም ሊያስተኛ የሚችል ስፋት ያለው ጠባብ ክፍል ተቀበላቸው።

"ቁጭ በል ልጄ፤" አሉትና የተነጠፈ ጅባ ጠቆሙት፤ ጫማውን አወላልቆ ተቀመጠ። እርሳቸውም ቀስ ብለው ወጡና በብረት ሳህን ላይ እንጀራ ዘርግተው፤ ምሥር አፍስሰው አመጡለት። ዶ/ር ሶፎኒያስ ዓይኖቹን ተጠራጠረ። እኮ ከዚህ ዋሻ እንጀራ በወጥ ከየት መጣ?

"ይህቺን እየቀማመስክ ጠብቀኝ፤ ጸሎት አድርሼ እመለሳለሁ።" አሉና ወጡ። በእውኑ የሚማርክ እርጋታ የተላበሱ ሰው ናቸው።

ዶ/ር ሶፎኒያስ ጥጉን ይዞ እንደተቀመጠ የባጥ የቆጡን እያወጣ ሲያወርድ ቆየ። እርሳቸውም ያሉትን ፈጣጥመው ሲመለሱ አንድ ሰዓትም አልፈጀባቸውም።

እንደገቡ "ጠፋሁብህ አይደል?" አሉና ከፊትለፊቱ ተመቻችተው ቁጭ አሉ።

"ኧረ ምንም ችግር የለውም፤"

"እሺ ልጄ፡ ጨዋታችንን እንቀጥል አይደል? ባይገርምህ ይሄ ቦታ በድርሳነ ዑራኤላችን ላይ የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስፍራ ተብሎ የሚጠራ ነው። ወደ ፊት ደግሞ በጤንነት ልቦች አድሮ፣ በልጆቻችን ልፋት መልከ-ጼዴቅ ደብር ይሆናል። ይህም የሚፈጸም ራእይ ነው... ለመሆኑ ግን መልከ ጼዴቅን ታውቀዋለኽ ዶክተር?"

"አላውቀውም አባቴ..."

"መልከ-ጼዴቅ ማለት በዘፍጥረት ምዕራፍ አስራ አራት እንደተጠቀሰው አብራምን ሰማይና ምድርን በፈጠረ ኤል ስም የባረከ፤አብራምም አክብሮ አስራትን ያስገባለት የነበር ሰው ነው፤ እነ ያዕቆብ ከመወለዳቸው በፊት የሳሌም ንጉስ ተብሎ ኢየሩ-ሳሌም፣ አየሩ-ሰላም ብሎ በኢስራ-ኤል የነገሠ ንጉሥ፤ በመንፈሳዊ ሰላም አጥኖ በክህነት ያስተዳደረ ካህን ነበረ። በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ መቶ አሥር መሰረት ደግሞ ይህ ክህነቱ እንደ ክርስቶስ ክህነት ዘላለማዊ እንደሆነ ተተንብዮልናል። ወደፊትም ልጆቻችን ደብር ቆርቁረው፤ ጽላት አስቀርጸው ምስጋናና ሰላምን እዚሁ ዳግም ያፈሱበታል።" አሉና በተስፋ ዓይን ነገን አሻግረው ተመለከቱ። የሚያወሩት ነገር ብዙም ያልገባው ዶ/ር ሶፎኒያስ በደፈናው በመስማማት አንገቱን ነቀነቀ፤

"ለምንድነው ይሄን ለኔ የሚነግሩኝ? የሚል ጥያቄ አድሮብህ ይሆናል። ነገር ግን ቅድም ወዳነሳነው ሐሳብ ልመለስልህ ነው። አሁን ከማስተዋል ወደ ጽሞና እናልፋለን። የዝምታና የስክነት ፍሬው ፍጹም ሰላም ነውና። ጽሞና ደግሞ ጥዑም እርጋታ ይሰጣል። ይሄም በነ መልከ-ጼዴቅ ተመስጦ ወ ሱባኤ ውስጥ ተገልጿል። ውዱ ዝምታ የመልከ መልካም ነፍስ ቀንዲልም ነው። ... ደግሞም እወቅ! የዝምታና የጽሞና ዋናው ምንጩ ከውስጥ ነው። በእያንዳንዳችን ውስጥ ውቅያኖስ አለ።" አሉና ቀሚሳቸውን ሰብስበው ከተቀመጡበት ብድግ አሉ።

*ፀሐይ የሽርሽር ጊዜዋን ጨርሳ ወደ ምዕራባዊ ጋጣዋ ጎበጥ ብላ እየገባች ነበር። ድክምክም ብላ ከዚያ ማዶ የምትኖር የጨረጨሰች አሮጊት ትመስላለች። የነሶፎኒያስ ቀሻም ጨለምለም ማለት ጀምሯል። አባ ኩራዙን ለማብራት ነበር አነሳሳቸው። ኩራዙ ላይ ጋዝ በጥንቃቄ እየሞሉ ንግግራቸውን ቀጠሉ፤ "አዎ- እኛ ሰዎች ውስጣዊ ውቅያኖስ አለን። ያንዳንዶች ውቂያኖስ የረጋ ሰፊፍ ነው፣ የሌሎቻችን ደግሞ የሚናወጥ ማዕበል ይበዛበታል። የውስጡን ውቅያኖስ ከማዕበል የከለከለ ሰው ማለት ያኖስ ባህሪውን የወቃ፤ ኃይለኛ ማንነቱን መግራት የቻለ ነው። ሰው*

*በጽሞና ከነቃ የልቦናውን ባህር በሚያምር ባህሪው የመዋጀት እምቅ አቅም አለው:: ለዚህም ውስጣቸው የሰከነ ሰዎች ዝምታ መለያቸው ነው:: ውስጣቸው የተረበሸ ሰዎች ደግሞ ውጫቸውንም በረብሻ ይሞላሉ::*
አሉና በቀስታ ተመልሰው ከመደባቸው ቁጭ አሉ።

በሙሉ ልብ ሲከታተላቸው የነበረው ሶፎኒያስ የሚያገኘው እውቀት እንዲሁ እየጣመው እንዲቀጥል ሳያቻኩላቸው ጠበቃቸው። እሳቸው ግን በዝምታቸው ለግማሽ ሰዓት ያህል ቆዩ። ሁለቱም ከቤቱ መሐል ላይ ሆና በምትንጨለጨለው ኩራዝ ላይ እንዳተኮሩ ጊዜው አለፈ። ... ዶ/ር ሶፎኒያስ እንደ ምንም ብሎ ጸጥታውን የሚሰብሩ ቃላትን ሰነዘረ፤ "አባቴ... ትልቅ ትምህርት ነው እያገኘሁ ያለሁት፤ ግን ችግሩ ባለፈው እንዳልክዎት የኛ ብቻ ጥፋትም አይመስለኝም። ዙሪያችን ላይ ያሉ ድምጾች ያውኩናል። ዓለም በሙሉ ትጮኻለችኮ። በተለይ የዚህ ዘመን ምርቶቻችን ድምጽን ለጉድ ይፈጥራሉ። አባታችን...እንዴትስ ታዲያ ዝም እንበል?"

እርሳቸው ግን ሌላ ረዘም ያለ ዝምታቸውን ጋበዙት ፡ ጠበቃቸው። "ንገሩኝ አባ?..." ... ደግሞ ጠየቀ፤ መልስ የለም፤

⌘ ⌘ ⌘

ኤልሳ ለይኩን ጋራዥ መክፈቱን ከሰማች ከሁለት ሣምንት በኋላ ወደ ቤቱ ሄደች። ደርሳም ከውጭ ቆማ አስጠራችው፤ ከቤቱ ሲወጣ በሩ ላይ ቆማ አያት፤ ፊቱ በደስታ ወከክ አለ። ሁሉን ነገር ረሳው፤ ተቃቀፉ።

⌘

*ከሦስት ወር በኋላ የለይኩን ተስፋሁንና የኤልሳ ቦጋለ የሠርግ ቀን ሆነ። ተጋቡ! ... መለስተኛ ድግስ ተሰናዳ። ወ/ሮ ብዙወርቅ "እልልል..." ብለው ልጃቸውን ዳሩ። ዝምተኛው ጅብሪል ጭፈራውን ሲያስነካው ዋለ። የኤልሳ እናት ወ/ሮ መንበሩና ወ/ሮ ብዙወርቅ በእስክስታ ትከሻቸውን ተፈታተሹ። ሳቅ፣ ደስታ፣ ከበርቻቻ... ህይወት አንዳንዴ እንደዚህ ቀለል ያለች ቀጥተኛ መስመር __ ትመስላለች። በብዙ እጥፋቶች ካደከመችን በኋላ ልፋታችንን የሚያስረሳ ጽዋ ታቀብለናለች። ችግሩ ዓለማዊ ጽዋዎች ሁሉ ማለቃቸው፣ ዳግም ሙሉኝ ማለታቸው ነው::*[22]

ያን እለት ለይኩን የብዙ ጊዜ ህልሙ ስለተሳካ በደስታ ሰክሮ ነበር።

---

የሐንስ ወንጌል 2፤1-11

ያ ደስታ ለዘላለም ቢዘልቅ ብሎ እየተመኘ ሐሴት ሲያደርግ ዋለ። እናቱ ወ/ሮ ብዙወርቅ ፊትም ላይ ደስታ ሲደንስ ነበር። ጥርሳቸው ከልካይ አጣ። ፍልቅልቅል... ልቅቅ...አሉ።

ሠርጉ ያው ያን ያህል ትልቅ ወጪ የወጣበት የሚባል አይነት ሠርግ አልነበረም፤ ብዙም ሰው አልተጠራም ግን ሁሉም ደስተኛ ሆኖ ነበር የዋለው። ሁሉም የእውነት ሲደሰት ውሎ እየሳቀ ወደ ቤቱ ገብቷል። አንዲት ልጅ ብቻ የውሸት ጥርሷን ስታሳይ ውላለች። ሠርጉ አብቅቶ ቤት እንደገባች ደሞ ራሷን ደብቃ ተንሰቅስቃ አልቅሳለች። ትራሷ በእንባዋ ርሷል።

⌘

## ✍... ያፍቃሪዋ ማስታወሻ

### "አገባኮ!"

የነለይኩን ጋራዥ ክሱት እንዲሆን ከለይኩን በላይ ጅብሪል ዋጋ ከፍሏል። እርግጥ ሁለቱም ብዙ ቢለፉበትም ውጤቱ ደግሞ ለሁለቱም በጣም አርኪ ነበር። ምንም ቢሆን እንደራስ የሚሆን የለምና በታውን አመቻችተው፤ እቃዎችን አሟልተው ሥራ ሲጀምሩ የስኬትና የነጻነት ስሜት ሞልቷቸዋል። ጋራዡም ፈጣን ሊባል በሚችል መልኩ ደንበኞችን ማፍራት ችሏል። በተለይም የጅብሪልን ሙያ የሚያደንቁ የድሮ ደንበኞቹ በራሱ ጋራዥ መክፈቱን ሲሰሙ ሥራቸውን ወደነሱ ይዘው መምጣት ጀመሩ። ገቢያቸው ደራ።

ለይኩን እናቱን ከምንጊዜውም በተሻለ ሁኔታ መንከባከብ ቻለ። አሳከማት፤ እስካሁን ያመኛል ብቻ ትለው የነበረው በሽታ ስሙ ታውቆ መድሃኒት እንድትጀምር ተደረገ። ያከማት ሐኪም ጭንቀትና ውጥረትን እንድታስወግድ መከራት። እሷም እሰየው ልጄ ደርሶልኛል ብላ፣ ፈጣሪዋን አመስግና በህይወቷ ለመጀመሪያ ጊዜ ለራሷ ጊዜ ሰጠች። ጥሩ መመገብ፣ በቂ እረፍት ማድረግ፣ ለህመሟ ኪኒን መዋጥ ጀመረች።

ያኔ ነበር ኤልሳ ተመልሳ ወደ ለይኩን ህይወት የመጣችው። ትታው ስለሄደች ብዙ ተጎድቶ፣ ብዙም ተቀይሟት ነበር። ከቤቱ ደጃፍ ቆማ፡ አስጠርታው ሲወጣ፡ ከደጃፉም ቆማ ሲያያት ግን፤ ሁሉንም ህመሙን እርግፍ አድርጎ ተወው። ስስ ልቡ ወዲያው ወደሷ ሸፍቶ አረፈው። ብዙ ነገር ነግራ አሳምናው ቤቱ ገባ። በተለይ ማታ ላይ ቁጭ ብሎ ብዙ ካሰበበት

በኋላ ግን ጥርጣሬ ቢጤ ገብቶት ነበር። ጋራዥ በከፈተ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ወደሱ ተመልሳ መምጣቷ ደስ አልልህ አለው።

*ብቻውን ብዙ እያወጣ እያወረደ ከቆየ በኋላ መወሰን ሳይችል ግራ በመገባት ውስጥ ተዋጠ። የሚያማክረው ሰው በሐሳቡ ፈለገ። ... እናቱን በእንደዚህ አይነት ነገር ለማውራት ያፍራቻዋል። ሠርጉ ቀን እስኪቆረጥ ድረስ ስለ ኤልሳ ማንነትና ስለ ግንኙነታቸው ነግሯቸው አያውቅም። ጅብሪልንም ለማወያየት አስቦ ነበር ግን የሥራ ውጥረት ላይ ሌላ ሐሳብ መደረብ አልፈለገም። ቢሆንም ጭንቀቱን መገላገል ግን ፈልጓል። ወዲያው አንዲት ሰው ትዝ አለችው ፡ እሷም ሜሮን ናት! እርግጥም የሁለቱን ግንኙነትና ጸብ ከሷ በላይ የሚያወቅ ሰው በምድር የለም።*

በማግስቱ ወደ ሜሮን ቤት አቀናና አገኛት።

"ከኤልሳ ጋር ተመልሰን አንድ ላይ ልንሆን ነው።" አላት ፡ ከሰላምታቸው ለጥቆ፤

"አሂ... ብር ማግኘትህን ስታውቅ መጣች?" ለራሷ አጉተመተመች ሜሮን፤ ዜናው ቢከብዳት ወደ መሬት አቀረቀረች። ምስኪን እሷነቷን በምሬት መውቀስ ጀመረች። ፍርሃቷን ረገመችው።

"ምን አለሽኝ ሜሪ?"

"ምንም..."

"እና ምን ትመክሪኛለሽ?" ... ሜሮን ባጎነበሰችበት ትንሽ ስታስብ ቆየችና ቀና ብላ ለይኩንን አየችው።

"ለይክ?"

"አቤት ሜሪ"

"ሚስትህ ምን አይነት ሴት እንድትሆን ነው የምትፈልገው?"

"የምወዳት ... ሳያት ደስ የምትለኝ..."

"ከምትወዳት ግን የምትወድህ አትሻልህም?"

"እ... እኔ እንደዛ አስቤ አላውቅም። ለምን ጠየቅሽኝ ግን?"

"አይ ... ተወው በቃ... ዝም ብዬ ነው። ግን ውስጥህ ዛሬም እሷን ከመረጠ አግባት።" አለችና ቀናም ብላ ሳታየው በፍጥነት ተመልሳ ገባች። ችኮላዋ ያስገረመው ለይኩን ቢጠራትም ባልሰማ ገብታ በሯን ዘጋች።

⌘

ሜሮን ክፍሏ እንደገባች ማስታወሻ ደብተሯን ነበር ያወጣችው። አንዳች እንኳን ቃላት ግን መጻፍ አልቻለችም።

⌘ ⌘ ⌘

|ለይኩን ኤልሳን ካገባ በኋላ እዚያው ጨው በረንዳ ውስጥ የራሱን ቤት ተከራይቶ ከናቱ ቤት ወጣ። ከኤልሳ ጋር አብሮ መኖሩ በጣም ደስተኛ አድርጎታል። ሥራም በጥሩ ሁኔታ እየሄደ ነው። የሆነ ሰሞን አንድ በቅርቡ የተከፈለበትን የግቢ በር ትዕዛዝ እየሠራ ነበር። ጅብሪል ማጠፊያውን በይዶ እንደጨረሰ ከጥቃቅን የብረት ቅንጣቶችና ከብርሃኑ እንዲከልለው ያደረገውን ትልቅ የፀሐይ መነጽር አውለቆ እየወለወለ ወደ ለይኩን ዞረ።

"እና አዲስ ትዳር እንዴት እንዴት እያደረገህ ነው ወዳጄ?"

"እግዚአብሔር ይመስገን ጥሩ ነው፤ አንድ ያልነገርኩህ ነገር አለ ጅብሪል..." አለ ለይኩን ፊቱ ላይ ለየት ያለች ብርሃን እየታየች።

"ኧረ? አንተኮ ብዙ ነገር አትነግረኝም።" ጅብሪል ቀበል አደረገውና መድረኩን ለቀቀለት።

ለይኩን በሁለት ቃላት ትልቁን ደስታውን አበሰረው፤ "ኤልሳ አርግዛለች።" "ማሻላህ! እንኳን ደስ ያለህ ለይክ፣ የልጅ አባት ልትሆንልን ነዋ!" ጅብሪል በደስታ ተሞልቶ የለይኩንን ትከሻ ቸብ ቸብ አደረገው።

..."ምን ይደረግ ብለህ ነው? ... እድሜ ላንተ! ቤተሰብ ለመመሥረት የሚያስችል አቅም አግኝቼ፡ ከሚስቴ ጋር መኖር ከጀመርን ሰነባበትን። ከዚህ በኋላ ምንም የሚያግደን ነገር እንደሌለ አሳመንኳት። እሷም እሺ ብላኝ ያው ዓይኔን በዓይኔ ልታሳየኝ ቀን እየቆጠርን ነው እልኻለሁ።"

"በጣም ደስ ይላል! እሷንም በሰላም ለመገላገል ያብቃት። የመጀመሪያ ልጅ መውለድ፤ ለዚያውም በለጋ እድሜ መውለድ ትንሽ ሊያስፈራ ስለሚችል በደንብ ተንከባከባት፤ አይዞሽ በላት፤"

"እሺ ወዳጄ ምክርኽን ተቀብያለሁ።... ግን ኤልሲዬ ከምታስበው በላይ ጠንካራ ሴት ናት። ነገሮችን ለማድረግ ጥሩ የራስ መታማመን አላት።" አለ ለይኩን በሙሉ ልብ፤

⌘ ⌘ ⌘

ኤልሳ ለይኩንን ማግባት ከብዙ ምክንያቶች አንጻር የተሻለ አማራጭ ሆኖ ነበር ያገኘችው። በተለይም ቤት ውስጥ ቀን ከማታ ከሚጠብቃት ንዝንዝ ራሷን ለማትረፍ ብቸኛ መንገድ ሆኖ ነበር የታያት። የእናቷ ወ/ሮ መንበረ ‹ሞራል› የሚነኩ ነቆራዎችና ያባቷ እሷን ከቁብም ያለመቁጠር ኑሮ በርግጥም አንገሽግሿት ነበር። በሌላ በኩል ለይኩን በሽርክና የከፈተው አዲስ ጋራዥ በሚያገኘው ገቢ ካደገችበት ድህነት እጅግ የተሻለ ኑሮን ሊያኖራት እንደሚችል አውቃለች። ለይኩን ደግሞ በጣም ስለሚወዳት፡ እንደማያስከፋት አምናለች። ... ነገር ግን ልጅ ለመውለድ ያቀረበላት ሐሳብ ላይ ደስተኛ አልሆነችም። ምክንያት ግን አልነበራትም። ልጅ ለሚባለው ኃላፊነት ፍቃደኛ ባትሆንም ዳሩ ጥንቃቄው ላይ ግን እስከዚህም ነበረች፡ የወር አበባዋ 3 ወር ሲያልፈው ነበር እንዳረገዘችም ያወቀችው። እንዲ ሆኗል በሚል አክርማና በለይኩን ያላሰለሱ የማሳመኛ ንግግሮች ተከባ ነው ለመውለድ የወሰነችው።

ቀኗም ደርሶ ወንድ ልጅ በሰላም ተገላገለች። ታዲያ ያን እለት ከየት መጣ የማይባል፤ ሰዉን በፍርሃት ያራደ የመሬት መንቀጥቀጥ ተከሰተ፡ የጨው በረንዳ ህዝብ ጉድ አለ። ኤልሳን በአራስ ቤቷ ለመጠየቅ የመጡ ሰዎች ሁሉ ይሄ ልጅ ጉደኛ ልጅ ነው! በተወለደበት ቀን መሬቱን አራደውኮ እያሉ የቡና ወሬዎችን አሟሟቁበት። አንድ በሰፈሩ የታፈሩና የተከበሩ አባት ድምጻቸውን ሞርደው እንዲህ አሉ።

*"ይሄ ልጅ ሲወለድ አይተን የማናውቀውን የመሬት መራድ ያስከተለ ህጻን ነውና ስሙ መርዕድ ነው መሆን ያለበት።"* ለይኩን ከእጁ ሥር በፍጹም ሰላም የተንጋለለውን ልጁን በስስት እያየ ስሙን ደገመው፤

*"መር...ዕድ" ... ወደደው! ... አፀደቀው!*

✶ ✶ ✶

# ምዕራፍ አምስት - 2

# ታእማኒ ክህደት

*ከጫው በረንዳ እንብርት ላይ ወደ 700 ካሬ የሚሆን የታጠረ መሬት አለ። ማን እንደገዛው? ማን እንዳሰጠረው? የሚታወቅ ነገር የለም። የህጻናት መጫወቻ የነበረ ሜዳ ግን በቆርቆሮ ከታጥረ ከራረመ። ከወራት በኋላ እዚሁ መሬት ላይ አንድ ከሰፈሩ የኑሮ ደረጃ እጅግ የተለየ፣ የናጠጠ ቪላ ቤት መገንባት ጀመረ። ⌘*

ለይኩንና ኤልሳ የተከራዩት ቤት ከዚህ ቪላ ቤት አጠገብ ያለ የሰቀላ ቤት ነው። ሁሌ ጥዋት ጥዋት ህጻኑን መርዕድ ፀሐይ ልታሞቅ የምትወጣው ኤልሳ የቪላውን ለውጥና የቀን ተቀን መዋብ ታይ ነበር። ወራትን ከፈጀ ወጪና አድካሚ ሥራ በኋላ ቪላው ተገንብቶ አለቀ። ⌘

አንድ ዕለት በማለዳ ኤልሳ በዘውትር ልማዷ መሠረት ህጻኑ መርዕድን አቅፋ ቁጭ ብላ ሳለች፤ የምታምር ዴክስ መኪና እየተንጎማለለች መጥታ ካዲሱ ቪላ ቤት አጠገብ ቆመች። የመኪናው በር ተከፈተና ዝንጥ ያለ ጎልማሣ ወረደ። በሩን ቆልፎ ቁልፉን እያሽከረከረ ዞር ሲል ከኤልሳ ጋር ዓይን ለዓይን ተገጣጠሙ። ትንሽ እንደማመንታት ካለ በኋላ እየሳቀ ወደሷ መጣ፤

"ዋው የሚያምር ልጅ ነው ያለሽ፤" አላት መርዕድን ቁልቁል እየተመለከተ።

"አመሰግናለሁ፤" አለች ኤልሳ እየተሽኮረመመች፤

"ካንቺ ወጥቶ ነው።" አለ እየሳቀ፤

"ነው ብለኽ ነው?"

"እንዴ ምን ጥያቄ አለው? ... ምን ይወጣልሻልና?"

ኤልሳ እንደማፈር ብላ ወደ መሬት አቀረቀረች።

"እንተዋወቅ?" አለ ባለ መኪናው ሰው፤

"እሺ..."

"አበጋዝ እባላለሁ"

"ኤልሳ"

"ያንቺ ነው የልጅሽ"

"እረ የኔ ነው፤"... ሳቀች፤

"የልጅሽስ?"

"መርዕድ ይባላል፤"

"ቆንጅዬ ልጅ ነው የእውነት፤ ...እም... " አለና አበጋዝ መልስም ሳይጠብቅ ንግግሩን ቀጠለ... "የዚህ ቤት ባለቤት ነኝ። ባይገርምሽ ‹ፊኒሺንጉ› ከተጠናቀቀ ራሱ ሳምንታት ተቆጠሩ። ...ከዛሬ ነገ እገባበታለሁ እያለኹኝ እስከዛሬ ቆየሁ። እንግዲህ ከዚህ በኋላ ጎረቤትሽ ነኝ ማለት ነው።" አለና ጥርስ በጥርስ ሆኖ ተመለከታት፤

"አው በጣም ደስ ይላል፤ እንኳን በሰላም ወደ ሰፈራችን መጣህ!" አለች ኤልሳ፡ የአበጋዝን ቤት እንዳዲስ እየገረመመች።

"እንኳን ደህና ቆያችሁኝ፤" ብሎ ትንሽ ተገትሮ እናትና ልጅን ሲያማትር ከቆየ በኋላ ተሰናብቷት ወደ ግቢው ገባ።

...ያን ሰሞን ሲወጣ ሲገባ አበጋዝና ኤልሳ በሩቁ ሰላምታ ይለዋወጡ ነበር። የሆነ ቀን ግን በድጋሚ መጥቶ ካጠገቧ ቁጢጥ አለና ህጻኑ መርዕድን እያጫወተ ያወራት ገባ።

"... ግን ለምንድነው እንዲህ በለጋ እድሜሽ ወደ ትዳርና ልጅ የፈጠንሽው?" ሲል ያላሰበችውን ጥያቄ ጠየቃት፤

"እ... እንዴት ልትጠይቀኝ ቻልክ?" አለች መልሳ በጥያቄ ዓይን ቀና ብላ እያየችው፤

"ሳይሽ በጣም ለጋ እድሜ ላይ ነው ያለሽው፤ ቁንጅናሽም እንደ ማለዳ ፀሐይ ያበራል፤"

"ብለኸ ነው?" ...አፈር አለች፤

|አበጋዝ ኤልሳን ባየበት ቅጽበት በውበቷ ተለክፏል። በጥዋቱ የፀሐይ ጸዳል፣ ከደጃፏ ቁጭ ብላ ሲያያት ያቺን ውብ ቀዘባ በምኞት አቅፏታል - ያውም ከነልጇ።

ከዚያ ቀን ጀምሮ ሰበብ አስባብ እየፈለገ እየመጣ ብዙ ነገር ያጫውታት ገባ። ለይኩን ሥራ ስለሚውል አብዛኛውን ጊዜ ብቻዋን ሆና ነበር የሚያገኛት። ቀስ በቀስ እየተግባቡ መጡ። አንዳንዴማ መርዕድንም ሳትይዝ ከአበጋዝ ጋር ለማውራት ብቻ የመምጫ ሰዓቱን እየጠበቀች ውጭ ላይ ቁጭ ብላ ትጠብቀው ጀመር።

"ኤልሲ ግን... መቼ ነው ከዚህ በርጩማሽ ተነስተሽ፡ በሥርዓት ወደ ከተማ ወስጄ ምሳ የምጋብዝሽ?"

"አንድ ቀን፤" አለችና ጡቷን የሚጠባውን ህጻን ልጇን ጉንጬ ጠረግ አደረገችለት። ምን እየተደረገ፣ ምን እየተወራ እንደሆነ ምንም እውቀቱ የሌለው ህጻን መርዕድ በደስታ ተውጦ ፈጣሪ ቀምሞ ያዘጋጀለትን| ምግብም፣ ውኃም፣ መድሃኒትም የሆነውን ወተት ይመጠምጣል። *{አንዳንድ ህመም የሚፈጥሩ የመለያየትና ክህደት ጅማሬዎችን አለመስማት ሳይሻል ይቀራል? ማለት በህይወቴ ባልሰማሁት፣ ባላየሁት ኖሮ የሚሉት ብዙ አስከፊ ነገር አለኮ።}*

ህጻኑ መርዕድ የማይሰማው ጨዋታቸውን ቀጥሉ።

"እሺ ቢያንስ ቤቴን እንዳስጎበኝሽ ፍቀጂልኝ?" አለ አበጋዝ በሚማጸን ለዛ፤

"አቤ ደሞ? ተዋ... ሰው ቢያየኝ ምን ይለኛል?"

"አንቺ ደሞ ሁሌ ሰው ሰው እንዳልሽ ልትሞቺ ነው እንዴ?" አለና ሳቀባት "ይልቅ ባለፈውም ስለምንሽ ሌላ ቀን ታሳየኛለኸ ብለሽኝ ነበር። ዛሬ ግን አንላቀቅም..." አለና አቋሙን የማይቀይር መሆኑን ቆፍጠን ብሎ ነገራት፤

"እሺ አሁን አንተ ግባ... መርዕድን አስተኝቼ ቀስ ብዬ እመጣለሁ፤ የግቢውን በር ክፍት አድርገህ ተወው..." አለችው፤

... |ካንድ ሰዓት በኋላ የአበጋዝ ቪላ ቤት በር በቀስታ ተንኳኳ፤

⌘ ⌘ ⌘

ለይኩን ካድካሚ የሥራ ውሎ ወደ ቤቱ ሲመለስ የሚጠብቀው አቀባበል ቀን በቀን እየደበዘዘ እንደሆነ ታዝቧል። ኤልሳ ከወትሮ ለየት ያለ የቸልተኝነት ባህሪ እያሳየችው ነው። በተለይ ሰሞኑን የሥራ ባልደረባው ጅብሪል መታመም ተከትሎ ጭንቀት አድሮበታል፤ የሥራው ውጥረትም በዝቶበታል፡ እሷ ግን ምንተዳዬ ያለችው ትመስላለች።

...ጉዳዩ እንዲህ ነው፤ ከሳምንት በፊት ነበር በሥራ መሐል እያለ ጅብሪል ራሴን አመመኝ ብሎ ተዝለፍልፎ የወደቀው፤ ለይኩንና አንድ ተቀጣሪ ወጣት አፋፍሰው ወደ ሆስፒታል ወሰዱት። ብዙ ጊዜ ጥዋት ጥዋት... በተለይ ቡና ካልጠጣሁ ራሴን ክፉኛ ያመኛል፤ ይል የነበረው ጅብሪል ሰውነቱን ለማዘዝ እስኪከብደው ድረሶ፡ ራሱን ስቶ ሲወድቅ የመጀመሪያው ነበር። ሙሉ ምርመራ ማድረግ እንዳለበት ተነገረው፡ እናም በዚህ ውሳኔ መሰረት ባደረገው የጭንቅላት ‹ሲቲ ስካን› ምርመራ ነበር አንጎሉ ውስጥ እያደገ ያለ መለስተኛ እጢ እንዳለ ያወቀው፡ ዶክተሮቹ እጢው ትልቅ የሚባል መጠን ላይ እንዳልደረሰ ነግረውታል፡ ግን ውጭ ሃገር ሄዶ በቀዶ ጥገና እስካላስወጣው ድረስ እያደገ መጥቶ ለህይወቱ እንደሚያሰጋውም አስረድተውታል። ካገር ወጥቶ ለመታከም የሚያስፈልገውን ብር ሲነግሩት ደግሞ ወሽመጡ ቁርጥ አለ። ስንት ዓመት ብረቶችን የገጣጠመ ብርቱ ክንዱ ዛለበት። አዲስ ጋራዥ ከፍቶ ተስፋው ማበብ በጀመረበት ወቅት ትልቅ ዱብዳ ወደቀበት። ነገን ለማየት መጓጓቱ በፍርሃት ሲቀየር ጊዜ አልፈጀበትም።

ችግሩን አይፈቴ ያደረገበት ዋናው ጉዳይ ውጭ ሄዶ ለመታከም የሚያስፈልገው ብር መብዛት ነበር። አማራጭ ሲያጣም ተስፋ ቆረጠ፡ የመጣው ይምጣ ብሎ ኑሮውን ቀጠለ። ያጋጠመውን ነገር የሰሙ ወዳጆቹ ግን በያቅጣጫው ሊረዱት መሯሯጥ ጀመሩ፤ ከእነርሱ አንዱ ለይኩን ነበር።

መጀመሪያ ሰሞን ለይኩን የሥራቸውን ገቢ በሙሉ ለጅብሪል ህክምና ለማጠራቀም ሞከረ። የሚስቱና የልጁ ነገር ግን ከሁለት በኩል ውጥረት ፈጠረበት። ቤት ሲገባ በድህነት የተከፋ የሚስቱ ኤልሳን ፊት ማየት፣ ብሶቷን መስማት ሌላ ራስ ምታት ሆነበት።

"ላታኖረኝ ነገር ለምን አገባኸኝ?" የሚል ሊመልሰው የማይችል አዲስ ጥያቄ አንገበገበው።

"ኤልሲ... ይሄ ይመጣል ብዬ መች አሰብኩኝና? ደሞ ጅብሪል ለጋራዡ መቋቋም ምን ያህል እንደለፋ ነግሬሻለሁ አይደል?"

"እኔ ስለዛ ምን አገባኝ?" ኤልሳ ፊቷ ልውጥውጥ ይላል፤

"ስታገባኝ አስተዳድርሻለሁ ብለኸ ነው! ያም ሳያንስህ ቆይ እንጠብቅ እያልኩህ፡ ቸኩለኸ ይሄ ኑሮ ላይ ልጅ ጨመርክበት።"

"አንዴ ጅብሪል ውጪ ሄዶ፡ ታክሞ፡ ከዳነኮ ሁሉም ነገር ይስተካ..."

"ኤጭ! ምን አስሬ ጅብሪል ጅብሪል ትለኛለህ? እኔ ያገባሁት አንተን እንጂ እሱን አይደለም... ይገባኻል? ..በቤታችን ዘይት ካለቀ ሁለት ሳምንት አለፈ፤ የቤት ክራይም ያንን ወር ሳንከፍል ቀጣዩ እየመጣ ነው። ምንድነው የምታስበው?!" በቁጣ ጠየቀችው፤

"እሺ በቃ አትቆጪ ውዴ... " ብሎ እጇን ያዝ ሊያደርጋት ሲሞክር ምንጭቅ አድርጋው ወጣች። ቢጠራትም ሳትመልስለት ሄደች፤

እሷ ሄዳ... ለይኩን ለብቻው ብዙ ተጨነቀ። እንደሁሌው ዛሬም የኤልሳ መከፋት ውስጡን አላወሰው። ምን ማድረግ እንዳለበት ከራሱ ተሟገተና ወሰነ። ቀጣዩን ሁለት ሳምንታት ለጅብሪል ህክምና የሚቆጥበውን ብር አቆመና የቤት ክራዩን ከፈለ፣ አንዳንድ አስቤዛ እንድትገዛም ለኤልሳ ብር ሰጣት።

እሷ... ሚስቱ፣ የልጁ እናት፣ ኤልሳ ግን በጥቅሉ ደስተኛ አትመስልም።

⌘ ⌘ ⌘

ኤልሳ ከልጅነቷ ጀምሮ የምትጠላው ህይወት ውስጥ ራሷን ደግማ በማግኘቷ ቁጭት ወሯታል፣ ድብርት ወርሷታል። ለይኩን ሥራ ሲውል እሷ ብቻዋን ቤቷ ቁጭ ብላ ነገር ስትበላ መዋሉን ተያይዛዋለች። አሁን አሁን ግን አንድ አጫዋች አግኝታለች ፡ እሱም ጎረቤቷ አበጋዝ ነበር።

አንዴ ቤቱን ለማየት ከገባች በኋላ ቤተኛው ሆናለች ማለት ይቻላል። በእርግጥ የአበጋዝ ቤት ኤልሳ ከልጅነቷ ጀምሮ ልትኖርበት ስትመኘው የነበረውን ቤት ይመስላል። የቤት እቃው የተሟላ፣ የሚያማምሩ ሰፋፊ ክፍሎች ያሉት፣ የአትክልት ሥፍራውና ሰገነቱ የሚማርክ ትልቅ ቪላ ነው። የኔ በሆነ ብላ ቋመጣለች።

|...ባንዱ ያዘቦት ቀን ህጻን መርዕድን አስተኝታ እንደ ልማዷ አበጋዝ ቤት ዘለቀች። አርፍዶ ከእንቅልፉ የተነሳው አበጋዝ ቁርስ እያበሳሰለ ነበር፡ ጥቁር ቱታ ለብሷል፤ ፀጉሩ ጨብረር ብሏል።

"አብጌ እንደምን አደርክ?" አለች ኤልሳ፡ በሩን ገርበብ አድርጋ እየገባች፤

"ኦ ኤልሲ... ነይ በናትሽ... እንዲያውም ባይገርምሽ ቁርስ ከማን ጋር እበላለሁ ብዬ እያሰብኩኝ ነበር። እንኳንም መጣሽልኝ!" አለና ፍንጭት ጥርሶቹን ፈልቅቆ አስነበኛት።

ኤልሳ እየተግደረደረች ወደ ውስጥ ዘለቀች።

"ለካ የምግብ ባለሞያም ኖረኻል፤"

"እንዴ! ገና ምኑን አየሽና?... በሁሉም ነገር ባለሞያ ነኝ!" አለና በውስጡ ወይራ ጠቀሳት፤ እንደማፈር አለች።

ያበሳሰለውን እንቁላል በቱና አብረው በልተው ሲያበቁ እንፋሎቱ የሚተን ሻይ ይዘው ከሶፋው ተቀመጡ።

"ኤልሲ?" አላት፡ ሙሉ ሰውነቱን ወደሷ እያዞረ፤

"ወዬ"

"በጣም ቆንጆኮ ነሽ፤"

"አውቃለሁ።" ... እንደ መሽኮርመም እያለች ሳቀች፤

"ጉረኛ..." ብሎ እሱም ሳቅ አለና የሻይ ብርጭቆውን ከጠረጴዛው አስቀምጦ፡ ከቅድሙ ይበልጥ ተጠግቷት ተቀመጠ።

"ይልቅ ስሚኝ... "

"ምን ልስማህ?"

"ማለት በቃ...ወድጄሻለሁ"

"አላምንህም..." ከመልሷ በተቃራኒ ፊቷ ላይ የሚነበበው ግን የአመኔታ ገጽ ነበር። ... "ግን... ልጅ አለኝኮ አቤ..."

"ለምን አሥር ልጅ አይኖርሽም!... ‹ኬር› አላደርግም፤ የምሬን ነው!

እኔ ወድጄሻለሁ ማሬ!" አለና ወደ ገላዋ ጥብቅ ብሎ ክንዶቹን ትከሻዋ ላይ ጣል አደረገ።... "አቤ..." ብላ ሳታወራ ቀጣይ ቃላቶቿን የሱ ከንፈር አገዳቸው። ከንፈሮቿን ገመጣቸው። ትንፋሽ አልሰጣትም ... "እ... እረፍ..." የይስሙላ፣ ልል ትግል ታገለች። ለአመሉ ያህል ተግተረተረች። እሱም የዋዛ ስላልሆነ ከንፈሮቹም፣ እጆቹም ሥራ አልፈቱም ነበር። ጣቶቹን ወደ ደረቷ ሰደደ። የሹራቧን ቁልፎች ሲከፍት ጊዜ አልፈጀበትም። በቀስታ ከሶፋው ላይ አጋደማት። ጡትና ዳሌዋን እየቃኘ በሌላ ልሳን ያናዝዛት ገባ። / ቃላቶች በዝምታ፣ በሲቃና ቁና ቁና ትንፋሾች ተተኩ።

አበጋዝ ሲሠራራት ኤልሳ ከእጇ የነበረው የሻይ ብርጭቆ አምልጧት ከወለሉ ላይ ወደቀ። ታማኝነቷም በዚያች ቅጽበት ከአፈር ተዋሃደ። አንሶላ ተጋፈፉ ለማለት የአንሶላው መኖር የግድ ይሆን? ... የሷ ሹራብና የሱ ጥቁር ቱታ ግን ከወለሉ ተገኝተዋል። ሁሉም ነገር ተፈጣጥሟል። ከዚያች ቀን በኋላ የኤልሳና አበጋዝ ግንኙነትም ሌላ ምዕራፍ ይዟል።

⌘ ⌘ ⌘

ዶክተር ሶፎኒያስ ከጥበብ ማዕድ እየበላ ርሃቡን ማስታገስ ጀምሯል። ነገሮች ይበልጥ ግልጥ እንዲሆኑለት ደግሞ ደጋግሞ መጠየቁን አላቆመም። በድጋሚ "አባ፡ በደንብ እንዲያስረዱኝ የምፈልገው ውጫዊ ድምጾች ለጉድ ከበውን ሳለ እንዴት ውስጣችንን ዝም ማሰኘት እንደምንችል ነው?" አላቸው፤

እርሳቸውም ረጅም ዝምታቸውን ሰብረው በእርጋታ ቃለ-ህይወት ምክራቸውን መለገስ ቀጠሉ... "ልጄ ሶፎኒያስ፤ ዙሪያ ገባው እንደሚጮኽና እንደሚረብሽኮ ይገባኛል:: ዝምታ ግን ምንጩ ከውጫዊ ይልቅ ውስጣዊ እንደሆነ በቅጡ መገንዘብ አለብኽ:: ልጄ ሆይ! ደግሜ እልኻለሁ፤ ዝምታ ከውጭህ ጸጥ ማለት በላይ በዋናነት የውስጥህ መስከን ነው::

አድምጠኝ... እነሆ ዝምታ ዋናው መነልቁን የሚጥለው ውስጣዊው ውቅያኖስህ ውስጥ ነው:: እሱንም እንደነገርኩህ ማስተዋል፣ ጥሞና፣ ብቸኝነትና እምነት ያጸድቁታል:: ለመሆኑ አብዝቶ "አውቃለሁ" የሚል ሰው ዝም ማለት ይሆንለታል ወይ? ዝምታኮ ከምንም በላይ አለማወቅን ማወቅ ይሻል:: ታዲያ ለሁሉም ጥያቄ መልስ አለኝ ብሎ የሚኮራ ሰው ዝም ማለት እንዴት ይቻለዋል?... እስኪ ንገረኝ?" - ሶፎኒያስ ዝም ብሎ ቀረ፤

"አየኽ... ብዙዎቻችን ዝምታን የማንለማመደውና የማናዘወትረው ዝምታ አስፈሪ እውነታ ስለሆነ ነው:: ዝም ስትል ውስጥህ ያለው የገዛ ግለ-አውሬኽ ጋር ትፋጠጣለኽ:: እናም አውሬው እዚያው ባለበት ታስሮ ይቆይ ዘንድ ዝምታን ትሸሸዋለህ:: ራስህን በተለያዩ ነገሮች ውጥር አድርገኽ ትጠፍራለህ፤ በመዝናናትና በፍሬ ቢስ ወሬ ውስጥ ጊዜህን ትፈጃለህ፤ እድሜህን ትዘልሳለህ:: መራሩን እንክብል ላለመዋጥ ፈርተህ ከረሜላ እየላስኽ ከደዌህ ጋር ተጣብቀህ ትኖራለኽ::" አሉና በወጉ ቢለካ ትውልድን በሙሉ በሚገረምም ኩስትሪያ ተመለከቱት፤ ይህቺ ኩስትሪያ ውስጥ ከሞቀ እንቅልፋችሁ ንቁ የሚል ቀዝቃዛ ውኃ ታቁሯል:: ቅጥልጥል ያለ አየር ካስወጡ በኋላ ጥርትርት ያለ ንጹህ አየር አስገቡ... ቀስ በቀስ ፊታቸው ላይ የሚነበበው ትዝብት እየደበዘዘ መጣ:: እነሆ ቀጠሉ... "ልጄ ስማኝማ፣ዝምታ ፈጣኑ እርጋታ ነው:: ዝምታ ዝ...ግ ነው : ካለትዕግስት የማይከፈት ምሥጢር፤ ዝምታ ዝቅ ነው : አውቃለሁ የማይል ትሁት : ዝምታ ወርቅ ነው : ከልብ ተቆፍሮ የሚገኝ ውድ ሐብት ነው::

እስኪ መልስልኝ? የአበበ ቢቂላን ዝምታ አስተውለኻል? ላቡ ጠብ ሲል በምስለ-መስኮት አይተኻል? አቀርቅሮ መሬቱን እያየ ሲሳብ አስታወስከው? ...አጣጣሉ የሚያምር፡ ጨኸት አልባ፣ ባለ ባዶ እግር፣ ባለ ኮስታራ ቅንድብ፣ ቆፍጣናውን ኢትዮጵያዊ ተመልክተኻል ወይ? ዝምታ ምን እንደሆነ አሁንም አልገባህም?

ዝምታማ ልጄ፡ ዝናን የማይሻ ነፍስ አለምላሚ ዝናብ ነው:: አስተውል : የቃል ተሲያቶች በልብህ የዝምታ ሰማይ ላይ በቀስታ፡ እያበሩ ያልፉሉ:: በቁጥር ሲወሰኑ ያምራሉ፤ ከበዙ ግን ትርጉም ያጣሉ : ውበታቸው ይደበዝዛል:: አንተና እነርሱ በየፊናችሁ ትደርቃላችሁ::

እናም ይህንን ውድ ጥበብ ለመላበስ ታጥቀህ ከተነሣህ ዘንዳ የሚጠበቁብኽን ሂደቶች መወጣት መቻል አለብህ:: ፍሊጋው ዋጋ ሊያስከፍልህ ይችላል:: በተለይ የጊዜ ዋጋን ይጠይቃል::"

"እሺ የሚሉኝን በሙሉ ለማድረግ ዝግጁ ነኝ አባቴ! ... ማድረግ ያለብኝን ነገር ብቻ ይንገሩኝ::" አላቸው ዶ/ር ሶፎኒያስ የማወቅ ጭራውን እያቁነጠነጠ... "እመነኝ፡ የልብህን መነሳሳት እጅግ አደንቃለሁ:: እውነተኛ ዝምታን ለማወቅ ግን መጀመሪያ ውስጣዊውን የነፍስ ዝምታህን ጠልቀህ ማግኘት ይኖርብኻል:: አንድን እውቀት ጠንቅቆ ለማወቅ ለብቻ ሆኖ ማንበብና መመርመር እንደሚያሻው ሁሉ ዝምታም የብቸኝነት፡ ጽሞናና

እርምጃን ይፈልጋል። ታዲያ አንድን ነገር ጠንቅቆ ያወቀ ሰው በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ሆኖ እውቀቱን መግለጽ ይቻለዋል፤ እንዲሁ ሁሉ የዝምታን ክህሎት ያዳበረ ሰው በረብሻ ውስጥም በዝምታ ሊኖር ይቻለዋል። ይህ ዓይነት ሰው መርከቡ በማዕበል መሐል ብትሆንም በእርጋታ ነገሮችን እንደሚከውን መርከበኛ ካፒቴን ይመሰላል። ውስጣዊ ውቅያኖሱ የሰከነ ነው።" ብለው ምክራቸውን ገታ አደረጉና ሶፎኒያስን በአትኩሮት እያዩ…

"በብቸኝነት ውስጥ ረጅም ጊዜ ለማሳለፍና ጥበብን ለመቅሰም ዝግጁ ነኝ ብለህ ታስባለኽ?" ሲሉ በአጽንኦት ጠየቁት።

ዶ/ር ሶፎኒያስ ትንሽ አሰብ ካደረገ በኋላ በእርግጠኝነት መንፈስ ዝግጁነቱን ገለጻላቸው።

"ልብ በል፣ ብቸኝነት ደግሞ የጠንካሮች፣ ጥሞናም የብልሆች ትምህርት ቤት ናቸው። አንተም በእርግጠኝነት ፍርሃቱን… ርሀቡን… እንቅልፍ ማጣቱን… በሙሉ ለማስተናገድ ትዕግስቱና ፅናቱ አለኝ ብለኽ ታምናለኽ?"

ዶ/ር ሶፎኒያስ ድጋሚ በአዎንታ ጭንቅላቱን ከፍ ዝቅ አደረገ። ከዚህ በኋላ ተጨማሪ ጥያቄ አልጠየቁትም።

ምሽቱ በጨለማ ታጅቧል። ከዋሻው ጥግና ጥግ የተለኮሱት ሻማና ኩራዝ ጭልጭል ይላሉ። የሻማ ማስቀመጫው ላይ የተንዠረገገው ሰም ላስተዋለው በድንገት ወደ በረዶነት የተቀየረ ፏፏቴ ይመስላል። ደንገዝገዝ ካለው ሰማይ ሥር ካለች አንዲት ዋሻ ውስጥ አንድ አባትና አንድ ዶክተር ተቀምጠው እያወጉ ነው። እያወጉ ይሁን እንጂ በወጉስ አይተዋወቁም።

*{… በወጉ መተዋወቅ ማለት ግን ምን ማለት ነው? ለዓመታት ያመኑት ሲከዳ፣ ለወራት ያወቁት ሲሰዋ አላየንም? የሁለት ሰው ነፍስና ልቦች ሲናበቡ ጊዜና ቦታ አይገድባቸውም።}* እኚህ አባትና ወጣት ሐኪምም መተዋወቅን ቋንቋ አድርገው፤ ከሰው መንጋ ተገንጥለው፡ ለእርምጃ ከትመዋል። ዛሬ…. ወጣትዬው የአባት ምክር እየሰማ፣ የህይወትን ጠሊቅ ትምህርት እየተማረ፡ ምሽቱን አጋምሷል።

ሶፎኒያስ ምሽቱ ሲገፋ እንደ ነገሩ እራት ቀማምሶ ከአቁፋዳው ላይ አረፍ አለ። እንቅልፍ ግን በቅጡ አልወሰደውም። ሲገላበጥ፣ ሲጠፋ-ሲበራ፡ ቆይቶ ከሌሊቱ አሥር ሰዓት ከእንቅልፉ ነቃ። ጭልጭል በምትለው ደካማ የሻማ ብርሃን ዙሪያውን ቢያማትር በትንሿ ክፍል ውስጥ ብቻውን

ነበር። ብዙም አልተገረመም፣ ሽማግሌው ሰው ለጸሎት ወጥተው ይሆናል ሲል ራሱን አሳመነ።

እርሳቸው ግን በማግስቱም አልተመለሱም፣ በቀጣዩም ቀን ሳይመጡ አደሩ፤ ሦስት፣ አራት፣ አምስት እያሉ ቀናቶች ነጎዱ… ሆኖም ተመልሰው አልመጡም። ዶ/ር ሶፎኒያስ በትክክል ብቻውን ቀረ። ይሄኔ ፍርሃት ወረረው፤ የመኖር፣ ያለመኖር፣ የመውደቅ፣ የመዋረድ፣ የመናቅ፣ የመረሳት ፍርሃቶች በልቡ ውስጥ ሥራቸውን ሰደዱ። በተለይ ግን የብቸኝነትን ፍርሃት አልቻለውም… {ብቸኝነት ደግሞ… ብዙዎች ገና ሲያስቡት የሚፈሩት፣ ጥቂቶች ብቻ ደፍረው ሊወጡት የሚሞክሩት ዳሽን ተራራ ነው። ከተራራው ጫፍ ለደረሰ ሰው ግን ‹ሰላም ለክሙ› የሚሉ ፍሰሀዎች ግን ለጉድ አሉ። አንዳንዴ ደግሞ ብቸኝነት እልም ካለ በረሃ ውስጥ የሚገኝ ምድረ-ገነትን የማግኘት ጉዞን ይመስላል። አብዛኛዎቹ ተጓዦች የበረሃው ቃጠሎና ውኃ ጥም አሸንፏቸው እጅ ይሰጣሉ። ግን የጸኑት በረኸኞቹ መነኮሳት እንዲህ ይላሉ፤

*"በረሃ የገባነው ራሳችንን ለመቅጠት ሳይሆን ራሳችንን ለማግኘት ነው።"}*

⌘ ⌘ ⌘

የለይኩን የሥራ ባልደረባና አዲሱ የልብ ጓደኛው ጅብሪል ቀስ በቀስ ለደዌው እጅ ሰጠ። ከሥራ ገበታው ከቀረ ሳምንት አለፈው። የተዋጣለት ገንዘብ ውጪ ሄዶ ለመታከም ከሚያስፈልገው ብር አንጻር እዚህ ግባ የማይባል ነበር።

ከጅብሪል መታመም በኋላ የጋራዡ ገቢያቸውም እጅጉን አሽቆልቁሏል።

|ከእለታት በአንዱ ቀን ለይኩን የቀኑን ሥራ እንደጨረሰ ጋራዡን ቆላልፎ ወደ ጅብሪል ቤት አቀና።

የጅብሪል ቤት ሲደርስ በሩ ገርበብ ተደርጎ ተከፍቶ ስለነበር ዘው ብሎ ገባ። ከተሰናዳ በርካታ ቀናትን ያስቆጠረው የጅብሪል ቤት ትርምስምሱ ወጥቷል፡ መለስተኛ ክርፋት አየሩን አምኮታል።

ለይኩን ዓይኑን ከቤቱ ጨለማ ጋር አለማምዶ፡ ከአልጋው አጠገብ ካለው ወንበር ላይ ተቀመጠ።

"እንዴት ነህ ጅብሪሎ?" አለው ለይኩን የጓደኛውን ዓይን በጭንቀት

እያየ።

"አል.. ሐምዱ… ሊላሀ፤ ለ… ለይክ … ደሀ… ደህና ነኝ አታ…ስብ" … እያቃሰተ መለሰለት፤ ጅብሪል ግን ደህና አልነበረም። ጥንካሬው ከድቶታል፣ ተስፋው ተሟጧል፤ የሰውነቱ በሽታ መከላከያ ኃይል ውጫዊ ወራሪ ደዌ ቢመጣ ለመዋጋት ዝግጁ ነበር፤ ከራሱ አፈንግጠው ወጥተው ነቀርሳ የሆኑበትን የገዛ ዜጎቹን ግን ምን ያድርጋቸው? ከልክ በላይ የሚራቡ የካንሰር ህዋሶች ውስጣዊውን ሰላም በጠበጡበት። {እንዲሁ ሁሉ ከሚሊየን የውጭ ጠላት ይልቅ አንድ ወገኑን የከዳ ባንዳ ለሃገር ከባድ ሳንካ ይሆናል።}

ለይኩን የጅብሪልን እጅ መስጠት ለመረዳት ጊዜ አልፈጀበትም። ውስጡ እርብሽብሽ አለበት፤ እንደምንም ብሎ ራሱን አረጋጋ… "አይዞክ ወንድሜ… ደህና ትሆናለኽ፡"… ለማጽናናት ሞከረ፤

"አሄሄ…! አሁ..ንስ በቅ..ቶኛል ለይ..ኩኔ… አላህ እስት…ንፋሴን ሊወ… ወ..ስዳት ቀር… ቧል።" ጅብሪል እያቃተተ መለሰለት፤

"ተው ጅብሪሎ እንደዛ አይ…ባል…" ብሎ አረፍተ ነገሩ ተቋረጠ ፡ ጉሮሮው ደረቀበት። ጓደኛውን ሊያጣው ነው። የኗሪ ትልቁ ድክመቱ በሞት መገታቱ ነውና ይህን የማቆም አቅም የለውም፤ ነገር ግን ማዘን ይችላል። በሐዘን ጥላ ውስጥ ሆኖ የሚወደው ጓደኛውን አስተዋለው።

ጅብሪል አላገባም፣ አልወለደም፣ አንድ ቀን ሳይደላው ከብረት ጋር ሲታገል ነው የኖረው፣ የኔ የሚለው ወዳጅ የለውም፤ እንዲሁ አንገቱን ደፍቶ ኖሮ አንገቱን ደፍቶ ሊያልፍ ነው። ሰው ከሞት እንደማይቀር ቢያውቅም ያንዳንድ ሰው አሟሟት ከሌሎች የበለጠ ያሳዝናል ሲል አሰበ። እና ጅብሪል አሁን መሞት አለበት? ተኖረና ተሞተ የሚሉት ይሄን ይሆን?

ለይኩን የጅብሪልን ጨለምለም ያለ ቤት ባይኑ እያሰሰ በሐሳቡ ሜዳ ላይ መጋለብ ቀጠለ። እኮ በብቸኝነት ኖሮ በብቸኝነት የሞተ ሰው ታሪክ አሳዛኝ አይሆንም? ግን ለመሞት ትክክለኛ ጊዜስ ይኖረው ይሆን? ሰዎች ትምህርት ጨርሰው፣ ሠርተው፣ ነግደው፣ ሐብት አፍርተው፣ አግብተው፣ ወልደው … "ወግ ማዕረግ" ካዩ በኋላ ሲሞቱ ነው በጊዜያቸው ሞቱ የሚባሉት? ለመሆኑ አሁን በቃኝ ልሙት የሚል የአዳም ዘር ይገኝ ይሆን? "እድሜ በገፋ ቁጥር ህይወት የበለጠ ጣፋጭ ትሆናለች።" የሚሉም አሉ። የሆነ ሆነ ሞትስ ከሞት አይለይም ወይ? አንድ- ለፍቶ ተምሮ፡ ተመርቆ፡

የአንድ ወር ደምወዝ እንኳን ሳይበላ በመኪና አደጋ የሞተ ወጣት/ ሙስና ሲበላ፣ ታዳጊ ልጃገረዶችን ሲያማግጥ ኖሮ ከሞተ አዛውንት የበለጠ ያሳዝን ይሆን? የዓለምን ትርጉም በወጉ ሳታውቅ በተወለደች በአንድ ዓመቷ የሞተች ህጻን ልጅ ሞት፤ ጠንቋይ ቤት ተመላልሳ አንገቷን በወርቅ መዓት ካጥለቀለቀች አሮጊት ሞት ይበልጥ አንገት ያስደፋ ይሆን? ... እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ከሞት በኋላ ያለውን ፍርድ ቤት መጎብኘት ሊጠበቅብን ይችላል፤ አልያም ሞቶ፣ ሁሉን አይቶ የተመለሰ ሰው ማግኘት ቢቻል ምንኛ መልካም ነበር?... ለይኩን በሐሳብ ዘፈቀ፤ የጅብሪል ነገር አንጀቱን በልቶታል። የጅብሪል አይነት ብቻቸውን ኖረው ብቻቸውን ያለፉ፣ ያላገቡ፣ ያልወለዱ፣ የሥራ አሻራቸው በስማቸው የማይጠራ፣ ከሞቱ በኋላ አስታዋሽ የሌላቸው ስንት ሰዎች ይኖሩ ይሆን? / ግን ግን ከሞቱ በኋላ መታወስስ ለእነርሱ ትርጉም ይኖረው ይሆን?..." ድንገት የጣር ድምጽ ጨለማውን ቤት ሞላው። ለይኩን ከሐሳቡ ነቃና ፈጠን ብሎ የጅብሪልን መዳፎች አጥብቆ ያዛቸው።

"በቃ... ይ... ሄ... ነ...ው...?" ጅብሪል የመጨረሻ ቃላቶቹን መናዘዝ ጀምሯል። "ላ...ኢላህ.. ኢል... አላ..." ለይኩን የጓደኛውን እጅ ይበልጥ ጭምቅ አድርጎ ያዘ። ጅብሪል ረጅም ትንፋሽ ወሰደና ጸጥ አለ። ዓይኖቹ ግልብጥ ብለው ጣሪያው ላይ አተኩረው ቀሩ። ጅብሪል አረፈ... ከብረትና እሳት ጋር መታገሉን አቁሞ እፎይ አለ።... የለይኩን ዓይኖች በበኩላቸው በእንባ ረጠቡ። ቀስ ብሎ ሽቅብ የተንጋለሉ የጅብሪልን ዓይኖች በመዳፉ ከደናቸው። እንባውን ጠራርጎ ቆመና የተጋደመውን፡ የጓደኛውን በድን አካል ተመለከተው። ወደ ጆሮው ጠጋ ብሎ ሦስት ቃላት ተነፈሰ። ... "እኔ አልረሳህም ወንድሜ!"

⌘ ⌘ ⌘

በማግስቱ የጅብሪል የቀብር ሥነ-ሥርዓት ጥቂት ወዳጆቹ በተገኙበት ተፈፀመ። ለይኩን ለረጅም ጊዜ አብሮት ኖሮ በቅርብ ጊዜ ውስጥ የእውነት ያወቀውን ጓደኛውን የፈጣሪ ፍቃድ ነው ብሎ ለአፈር አስረከበ።

*{አንዳንድ ሰው በዝምታ ውስጥ ኖሮ በዝምታ ውስጥ ያልፋል። የራሱ ወዳጅ ራሱ ብቻ ሆኖ፤ አንድም ቀን የሆዱን መበሰልሰል ገልጦ ለሰው ሳያወራ፡ የዚህችን ዓለም ድልድይ የሚሻገር ብዙ አልፎ ሂያጅ አለ። እናም/ አንዳንድ ዝምተኝነት ይህችን አጭር እድሜ ወዳጅ አልባ የሚያደርግ ግርዶሽ ይመስላል።}*

ለይኩን ያንን ሰሞን ጋራዡን ሳይከፍት ሰነበተ። ዘግይቶም ቢከፍት ሥራው ግን እንደወትሮ ሊሆንለት አልቻለም። ደንበኞቻቸው በዋናነት ጅብሪልን ፈልገው ነበርና የሚመጡት ገቢው እጅጉን ቀነሰ። ከትርፍም በሻገር መሠረታዊ ወጪዎችን መሸፈን አልቻለም። ደምወዝ መክፈል ስላቃተውም ቀጥሮ ያሠራው የነበረውን ረዳት ልጅ ለማሰናበት ተገደደ። ለሁለት ወራት ያክል የጋራዡን ክራይ ሳይከፍል ቆየ። ይሄኔ ነበር የግቢው ባለቤት እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ ወደ ጋራዡ የመጣው ፤ ... "እኔ የምልህ ለይኩን...?" አለ እንደ ቦንዳ የተወጠረ ቦርጩን እያሻሸ፤ "እኔ የምልህ ለይኩን? ...ያ ወዳጅህ... የሥራ ባልደረባህ ማለፉን ከግምት ውስጥ አስገብቼ ዝም ብልኽ፤ ጭራሽ የራስህ ቤት መሰለህ እንዴ? ኪ .. ኪ..ኪ" ...ጥያቄውን የፌዝ ሣቅ አከለበት፤

"ኧረ እንደዛ አይደለምኮ ጋሼ! . . . ትንሽ ሥራ ቀዝቀዝ ስላለ ነውኮ ዝም ያልኩት..." .... "እሱ ያንተ ችግር ሊሆን ይችላል! ... እኔ የምፈልገው ገንዘቤን ብቻ ነው። እናም በዚህ ሣስት ቀን የተጠራቀመብህን ብር መክፈል ካልቻልክ ቤቴን በአስቸኳይ ለቀኽ እንድትወጣ እፈልጋለሁ!"

ለይኩን ድንጋጤ ጉሮሮውን ሸንቅሮ ያዘበት። ቃላቶች የቋጥኝ ያህል ከበዱት ... "ሣ...ሣስት ቀ..ቀን ጋሼ? ት... ንሽ ትንሽ አላጠረም? ብሩኮ ት..ንሽ ስለ... ስለሚበዛ..."

"አይ እንግዲህ አትንገፍገፍብኝ ... የምትከፍል ከሆነ ክፈል! ካልሆነ ለቀህ ውጣ! ይሄ የበጎ አድራጎት ድርጅት አይደለም።" ብሎ ተመናቅሮ ሄደ| የቤት ባለቤት ነኝ ባይ አከራዩ፤

ለይኩን እጆቹን ጭንቅላቱ ላይ ጭኖ ከመሬቱ ላይ ቁጢጥ አለ። ዳግም ተስፋው ላይ የጽልመት ጎርፍ ተቸለሰበት። ያንን ብር ከየትም ማምጣት እንደማይችል ያውቃል። ያፈሩትን ትንሽ ጥሪትም ለጅብሪል ህክምናና ሌሎች የቤት ወጪዎች አውሎ ባዶ እጁን ቀርቷል። አንገቱን እግሮቹ መሐል እንደቀበረ ለረጅም ደቂቃዎች ሲያወጣና ሲያወርድ ቆየ። ሰዓቱ ወደ አመሻሽ ግድም ነበር። እዚያው ቁጩ ባለበት ፀሐይ ጋቢዋን አጣፍታ ወደ ማደሪያ ጎሬዋ ማዘቅዘቀ ጀመረች። በደመ-ነፍስ ከተኮራመተበት ተነሳና ጋራዡን ዘጋግቶ ወደ ቤቱ አቀና። ሌላ ጊዜ አምሽቶ ሁለት ሶስት ሰዓት ነበር ቤት የሚመለሰው። ዛሬ ግን ቆይቶ የመሥራት ተነሳሽነት አጣ። ቅስሙ ዳሽቆበታል።

ለይኩን ወደ ቤት የሚያደርሰውን መንገድ በዝግታ አዘገመበት። ሸዋ ዳቦ ቤት ጋር ሲደርስ የነበረውን ብቸኛ 5 ብር አውጥቶ ፋርኖ ዳቦ ገዛ። ቤት ሲገባ የሆነ ነገር ከያዘ ሚስቱም ልጁም ደስ እንደሚላቸው ያውቃል። ህጻኑ መርዕድ ባልበረታው ጥርሱ ዳቦውን ሲታገል በሐሳቡ ድቅን አለበትና ለብቻው ፈገግ አለ። የተረገሙ የሚመስሉ ቀናትን ቢያሳልፍም ማታ በልጁ የጨዋታና የሳቅ በረከት መንፈሱ በመጠኑም ቢሆን ይታደሳል። ጭንቀቱ በስሱ ይራገፋል። ዛሬም ገና የልጁን ነገር ሲያስብ መሪር፡ ጋሬጣ ያጠላበት ቀኑ ላይ ትንሽ ጣፋጭ ደስታ ጠብ ሲል ታወቀው። ፊቱ ላይ ምናምንቴ ፈገግታ እየታየ ፡ እጆቹን ቤሳቢስቲ የሌላቸው ኪሶቹ ውስጥ ወትፎ/ ጎዳናዎችን አቋረጠ።

ቤት ሲደርስ የህጻን ልጁ የመርዕድ ለቅሶ ነበር ከሩቁ የተቀበለው። በችኮላ ሲጠጋ የቤታቸው በር ካለወትሮ ገርበብ ብሎ ተከፍቶ ነበር የጠበቀው። ፈጠን ብሎ ገባና ልጁን አንስቶ እያባበለ ወደ ውጭ ወጣ። መርዕድ አባቱን ሲያገኝ ጩኸቱን ትቶ መሳቅ ጀመረ። ለይኩን በበኩሉ መርዕድ እንዲህ እያለቀሰ ኤልሳ ለምን ቻላ አለችው? እንዴት ብቻውን ጥላው ትወጣለች? የሚሉ ጥያቄዎችን እያብሰለሰለ ከበሩ ደጃፍ ላይ እንደቆመ ከጎረቤታቸው ቪላ ቤት ላይ ካለው ሰገነት አንድ ወንድና ሴት ተቃቅፈው ሲሳሳሙ ተመለከተ። በከፊል እርቃናቸውን ነበሩ። ግራ ገባው ፡ ዓይኑ ያየውን ልቡ እየካደ ወደ እነርሱ በፍጥነት ገሰገሰ። በቅጡ እንኳን ያልተዘጋውን የግቢ በር በርግዶ ሲገባ ሰገነቱ ላይ የነበሩት ወንድና ሴት ቁልቁል ተመለከቱት፤ ተፋጠው ቀሩ። ሁለቱም ፊት ላይ ድንጋጤ ነገሠ፤ በተለይ ሴቲቱ ክው ብላ ቀረች። ለይኩን መርዕድን እንዳቀፈ ወደ ሰዎቹ ተጠጋ።

*"ኤልሳ?! . . . እኮ የኔዋ ኤልሳ ከሌላ ወንድ ጋር?"* ... አየር አጠረው፣ የሆነ ክፉ ስሜት ደረቱን ሰቅዞ ያዘው። *የሚያምኑት ሲከዳ ያማል። የኔ ነው ያሉት ሲሰረቅ ያንገበግባል። ግን ለመሆኑ ሰው የኔ ነው ይባላል ወይ? ጀ*

ከአበጋዝ ጋር የሥርቆሽ ዓለሟን እየቀጨች የነበረችው ኤልሳ ባሏ እጅ ከፍንጅ ሲይዛት መሬት ተሰንጥቃ ብትውጣት ተመኘች፤ ከሚፈጠረው ጸብና የትዳር ቀውስ በላይ ያሳሰባት ደግሞ ሰፈሩ ውስጥ ወሬው መነዛቱ ነበር። አንድም ቃል ሳትተነፍስ ገላጣ ሃፍረቷን በእራፊ ጨርቅ ለመሸፈን እየሞከረች ተገትራ ቀረች። አበጋዝ በበኩሉ ከሁለቱ በጣም ባነሰ ደረጃ ነበር ድንጋጤ ያረበበበት። እንዲያውም በቸልተኝነት መንፈስ ነበር የተገተረው። ገና በቅጡ ያልበረደው የፍትወት ስሜትም በደንብ አልጠፋለትም። የሞቀ

ደሙ እስኪበርድ ቅጽበቶችን ሽቷል። ኋላ ተረጋግቶ ዙሪያውን ሲያስተውል ግን ጉዳዩ አደገኛ ሊሆን እንደሚችል ተረዳ። እናም የሞት ሞቱን ቃላትን አወጣ፤ "ወንድሜ ለይኩን... ተረጋጋ... ጉዳዩ እንደምታስበው አይደ..."

"ዝም በል!" ለይኩን አንባረቀ፤ "አንተ እኔን ተረጋጋ ልትለኝም፡ ልትመክረኝም አትችልም!" ዓይኑ ደም ለብሷል፤ ጥርሶቹ ይንቀጫቀጫሉ፤ እየተንቀጠቀጠ ቀጠለ... "በገንዘብህ ተመክተህ የፈለግከውን የድሃ ትዳር ማፍረስ ችሎታ ይመስልሃል? ትሰማኛለኸ? እኔ ብር ባይኖረኝም ክብር አለኝ እሺ!" የእልህ እንባ ጠለሎች የለይኩንን ዓይኖች ሲሞሉት ጊዜ አልፈጀባቸውም። "እንዳንተ አይነት ለሰው ክብር የሌለው ቅሌታም! እኔን ተረጋጋ ሊለኝ አይችልም!"

"አይ እንግዲህ! በገዛ ቤቴ መጥተህ ባዶ አፍህን እንድትከፍትብኝ አልፈቅድልህም። ድሃ የድሃ ልጅ!" አበጋዝም የተቆጣ መሰለ።

"አንተ ልክስክስ...የውሻ ልጅ!" ብሎ ለይኩን በሽምጠጣ ወደ አበጋዝ ተንደረደረ። ህጻኑን መርዕድ ከወዴት እንዳኖረው ለጊዜው ትዝ አይለውም። በመጣበት መግነጢሳዊ ፍጥነት ጡጫውን አበጋዝ ላይ አሳረፈው። ለይኩን እንደ አውሬ ተወርውሮ ስለመታው አበጋዝ ራሱን ለመከላከልም ሆነ አጸፋ ለመመለስ ጊዜ አላገኘም። ከወለሉ ተነጠፈ። ለይኩን ግን ይህም ሳይበቃው ላዩ ላይ ተከምሮ የቦክስ መዓት ያቀምሰው ገባ። ንዴቱን በመጠኑ እያስተነፈሰ ሳለ የእሪታ ለቅሶ ወደ ቀልቡ መለሰው። ቀና ቢል ኤልሳ ልጇን መርዕድን አቅፋ በጩኸት ቤቱን ስታደበየው ተመለከታት። ወዲያው ዓይኑን እቅፏ ውስጥ ወዳለው ጨቅላ ላከ። ከግንባሩ ግድም ደም እየፈሰሰው እንደሆነ አስተዋለ።

ለይኩን ወደ አበጋዝ ሲምዘገዘግ ልጁን ከቤቱ መሐል ካለው መስታወት ላይ ጥሎት ኖሯል። ተነስቶ ወደ ኤልሳ ተጠጋ... እውነትም ልጁ እየደማ ነው ፡ በድንጋጤ ላይ ድንጋጤ ተደራርቦበት፡ ቀልቡን መሰብሰብ አቅቶት፡ ተገትሮ ቀረ። በዚህች ቅጽበት አበጋዝ ከኋላው ደርሶ ምን በሚያኽል አጠና አናቱን በረቀሰው። ሰማይ ምድሩ ድብልቅልቅ አለበት ፡ አጥወለወለው ፡ ሚዛኑን አጥቶ ከመሬቱ ዘፍ አለ። ራሱን ሳተ።

|ኤልሳና አበጋዝ ትንሹን መርዕድ ይዘው ወደ ሆስፒታል ከነፉ።

⌘ ⌘ ⌘

አበጋዝ ብዙ ብር አውጥቶ ሀጻኑን መርዕድ አሳከመው። ብዙም ለህይወት የሚያሰጋ ችግር ሳይገጥመው ነበር የዳነው።

⌘ ⌘ ⌘

ከ15 ቀን በኋላ የኤልሳና ለይኩን ትዳር በይፋ ፈረሰ። መርዕድን ይዛ ኤልሳ አበጋዝ ጋር ተጠቃለለች።

⌘ ⌘ ⌘

ጉዳትና ሐዘን የደቆሰው ለይኩን ግን ከእና ቤቱ ገብቶ በሩን ዘጋ። ሚስት፣ ልጅና ሥራውን በአጭር ጊዜ ውስጥ ተነጠቀ።

ሲያመጣው አንዴ ነው እንዲሉ ተስፋ ከመቁረጥ ውጪ ምንም መጽናኛ አልነበረውም።

# ምዕራፍ ስድስት

# ፈረንጇ ባላገር

ራሺያዊቷ ክልስ ቬራ የመርዕድ ቤተሰቦችን ታሪክ ካለማቋረጥ ስታደምጥ ቆየች። መርዕድም በተለይ የወላጅ አባቱ፡ የለይኩንን ታሪክ በብዛት ሲያጫውታት ካረፈደ በኋላ ትረካውን ገታ አደረገና እረፍት ወሰደ። አባቱ ያሳለፈውን የመከራ ህይወት ሲያስብ ፊቱን ቅጭም አደረገ። ነፍስ አውቆ በአካል ፈተናውን ያላየው ቢሆንም ህመሙ የሱም ህመም ነበር። ምናልባትም በዘረ፡መል በኩል ልጅና አባት የሚጋሩት የመገናኛ መረብ ይኖር ይሆናል። |አልያም መንፈሳቸው በአንድ እርግብግቢት ይናበብ ይሆናል። የተሰማውን ጭንቀት በረጅም ትንፋሽ አስወገደና ትኩረቱን ወደ ቬራ አደረገ። ወዲያውም ልቡ እርግት አለች።

አሁንም ዝምታ አካባቢውን ሞልቶታል። የወፎቹ ፉጨትና የንፋስ ሽውታ ጩኸትን አልፈጠረም። የበሶቢላ፣ አሪቲ፣ ናና ብናኞች ከንፋሱ እየተንሳፈፉ ደርሰው አፍንጫን ያውዳሉ። ማነው አርቆ አሳቢ የተከላቸው? ባያውቀውም አመሰገነው።

እንደዚህ አይነት ቦታዎች አሉ ፤ ለዓይን ማራኪ፣ መንፈስን የሚያድሱ፣ አጥንት አለምልመው፡ ልብን የሚያሰክኑ . . . መናፈሻና ፓርኮች የከተሞች ውስጥ የሰላም ደብሮች ናቸውና በብዛት ሊኖሩ ያሻል። ...*በዚሁ እርጋታ ውስጥ እያለ ቬራን አስተዋላት። ስለሱና ቤተሰቦቹ ታሪክ ብቻ እየተጨነቀች የሷን የህይወት ጉዞዋን ግን ሁኔ ብላ አውግታው አታውቅም። የጥያቄውን አቅጣጫ ወደሷ አዞሮ ሞገዱን ሰደደ። በትውስታ ማህደሯ ውስጥ ደምቀው የተከተቡትን የቬራ ሰነዶች እያገላበጠ ማንበብ ጀመረ። አልከለከለችውም። የአሁኗ የመርዕድ ውኃ አጣጬ ቬራ ማናት? ክልሷ ባላገር!*

⌘ ⌘ ⌘

*ከዓመታት በፊት...*

አንድ ከአዲስ አበባ ተነስቶ ወደ ደብረ-ዘይት የሚያቀና ‹ዶልፊን› መኪና በሰዎች ታጭቆ ይከንፋል። ተሳፋሪው ካለመበት ለመድረስ ልቡ እንደቆመ የጎማውን እሽክርክሪት ይተምናል። አብዛኛው የመኪና መስኮት አለመከፈቱ ላይ የወሩ ፀሐያማነት ተጨምሮ መኪናዋን መለስተኛ ‹ስቲም› አድርጓታል። ውቅያኖስ ውስጥ ኖሮ ውኃ እንዳጣ ዓሣ፡ ተጓዡም ንጹህ አየር ተርቧል።

ታዲያ ከአብዛኛው ጥቁር፣ ጠይምና የቀይ-ዳማ ተሳፋሪ ለየት ብላ የምትታይ አንዲት ነጭ ወጣት ከአራተኛው ረድፍ፡ በስተቀኝ፡ ጥግ ላይ ተቀምጣለች። ድንገት ከወንበሯ እምር ብላ ተነሳችና ሻንጣዋን እንዳንጠለጠለች አጎንብሳ ወደ ሹፌሩ አቀናች። ቀጣይ ከአፏ የወጣው ምን የመሰለ... ቅልጥፍ ያለ አማርኛ ከ'ፈረንጇ' ወጣት ሴት የሚፈልቅ አይመስልም ነበር።

*"እባክህን ወንድሜ አንዴ መኪናውን ልታቆምልኝ ትችላለኽ?"* አለች።

ለግላጋው ሹፌር በአግራሞት እያያት በአዎንታ ጭንቅላቱን ነቀነቀ። ከአፍታ በኋላ መኪናዋን አንድ ጥግ አስይዞ አቆመላት። ብዙሃኑ ሽንቷን ልትሸና አልያም መንገዱ ሆዷን ረብሿት ወደላይ እያላት ነው ብሎ ነበር የገመተው። ልጅት ግን ከመኪናው እንደወረደች ፈጠን ብላ ወደ መኪናው ጣሪያ የሚያስወጣውን መሰላል ተቆናጠጠች። በሚገርም ቅልጥፍናም ወደ መኪናው እቃ መጫኛ፡ ፖርቶ መጋላ ወጣችና ተመቻችታ ተቀመጠች።

ወደ ሹፌሩ መስኮት አዘቅዝቃ እያየች "አመሰግናለሁ... በቃ መሄድ እንችላለን፤" አለችው፤

ሹፌሩም፣ ተሳፋሪዎቹም ግራ ተጋቡ። ሹፌሩ በጋቢናው መስኮት አንገቱን ብቅ አድርጎ . . ."እርግጠኛ ነሽ ልንዳ... ማለቴ እዚያ ላይ ነው የምትቀመጪው... *ብትወድቂስ?"* ሲል ጠየቃት፤

"አዎ አታስብ ወንድሜ... ከዚህ የባሱ ጉዞዎችንም አድርጌ አውቃለሁ፤ ንፋስና ጸጥታ ስላለው እዚህ የበለጠ ይመቸኛል።" አለችውና መንገዱን እንዲቀጥል በምልክት ነገረችው፤ ሹፌሩ "የሰው ሰው ጭኜ ወድቃ እንደ ነገር እንዳትሆንብኝ!" እያለ፤ ፍርሃቱን በሆዱ እንዳዘለ፤ "ይመችሽ" አለና፤ የመኪናዋን ሞተር ቀሰቀሰው። ጉዞ ቀጠለ።

ቬራ፤ በንፋሱ ወጨፎ ወርቃማ ጸጉሯ ወዲህ ወዲያ እየተዘበራረቀ፤ የዓይን ሽፋሽፍቶቿ ለጉድ እየተርገበገቡ ... ከነበረችበት የሚወብቅ ሙቀት ወጥታ ነፋሻማ ዓየሯን እየማገች፡ ወደ ጥልቅ ጥሞና፣ ‹ሜዲቴሽን› ውስጥ እየቀዘፈች፤ መንገዱንም ልብ ሳትለው ቢሾፍቱ/ ደብረ-ዘይት ከተማ ገባች።

ይህቺ ነጭ ወጣት ላገሩ እንግዳ፣ ለህዝቡ ባዳ ብትሆንም በሙሉ የራስ መተማመን ነበር ከመኪናው ወርዳ ከተማውን የረገጠችው። እንደወረደችም ስልኳን አወጣች፤ ቀድማ በካርታው ላይ ምልክት ወዳደረገችበት ቤት አቀናች። በዚያ ቁመቷ ላይ ትልቅ ከስክስ ተጫምታ፣ ከጭንቅላቷ አንስቶ እስከ ዳሌዋ ድረስ የተወጠረው ሻንጣዋን አንግባ፤ ሽከተፍ... ሽከተፍ... እያለች ስትራመድ የከተማው ኑዋሪዎች እይታ ውስጥ መግባቷ አልቀረም ነበር።

ከግማሽ ሰዓት በላይ ተጉዛ ከአንድ በጣሊያን ጊዜ እንደተሠራ ከሚያሳብቅ ግንብ ቤት ጋር ስትደርስ ቀጥ አለች። ካርታው ላይ ምልክት ያደረገችበት ‹የላቲቲዩድና ሎንግቲዩድ ኮርዲኔሽን›[23] ጋር እንደደረሰች ስልኳ ቀይ ምልክት አሳያት። ወደ ግንቡ ቤት ተጠጋች። ደጋግማ ብታንኳኳም መልስ አላገኘችም። ገርበብ ያለውን በር ከፍታ... ሰተት ብላ ገባች።

"ሰላም ለዚህ ቤት..." እያለች ወደ ውስጥ ዘለቀች።

አንድ ድክምክም ያሉ ሽማግሌ ድምጿን ሰምተው ወደሷ ሲመጡ አየቻቸው... በጥርጣሬ መንፈስ "አባባ ተምትሜ?" ብላ ጠየቀቻቸው፤ ስማቸው በማያውቋት እንስት መጠራቱ ግራ ያጋባቸው አባት "አቤት ልጄ..." እያሉ ወደሷ ተጠጉ፤

"እስካሁን ድረስ እዚህ ሊኖሩ እንደሚችሉ አባቴ ነግሮኝ ነበር።" አለች በመጠኑ ፈገግ እያለች፤

"ይገርማል!... የአባትሽን ሥም ልትነግሪኝ ትችያለሽ ልጄ?" አሉ ሽማግሌው ሰው ፊታቸው ላይ አዲስ የጥርጣሬ ድባብ እያደራ፤

"ዲምትሪብ፤"

ሽማግሌው ድንግጥ አሉ። ከብዙ ዓመታት በፊት የሰሙትን ሥም ነው

23 ምድርን አግድምና የቁም የሚያቋርጡ ምናባዊ መስመሮችን ተመርኩዞ የሚገለጥ የቦታ መጠቆሚያ፤

ደግመው የሰሙት። ጆሯቸውን እየተጠራጠሩ፤ ማረጋገጫ ጠየቋት፤

"እኮ የኒኮላይ ሊዮንቴቭ አሺኖቭ[24]ን ወንድ ልጅ ዲምትሪቭን ነው የምትይኝ?"

"በትክክል... አባቴን አልረሳከውም ማለት ነው።"

"እንዴት እረሳዋለሁ ልጄ? ... ገና ጨቅላ ሳለ ጀምሮኮ ነው ያሳደግኩት። እንዴት እረሳዋለሁ ብለሽ ነው? ባልወልደውም ልጄ ነበርኮ፤ እኔም ሁለተኛ አባቱ።" አሉና ለአፍታ ትዝታ ወልፈት አደረጋቸው ... "ውይ ውይ በሞትኩት... ገና ከመንገድ ከመግባትሽ በጥያቄ ወተወትኩሽ አይደል? .. አሂ የኔ ነገር..." ብለው የያዘችውን ሻንጣ ተቀብለው ወደ ውስጥ ገቡ። ቬራም ተከትላቸው ወደ ውስጥ ገባች። ማረፊያ ፎቴውን ረገፍ ረገፍ አድርገው እንድትቀመጥ ጋበዟትና ወደ መታጠቢያ ቤቱ ገቡ።

ቬራ ለዓመታት እንዳይፈርስ ‹ጆዲድ›[25] ሆኖ የተሠራው እድሜ ጠገብ ቤት ጋር ተፋጠጠች፤ የዋንዛ እንጨት መስኮቶቹ ስድስት ቦታ እኩል ተከፍለው፡ መስታወቶች ተሰንጎባቸዋል፤ በሚጠማዘዝ እጀታ ይዘጋሉ፤ ይከፈታሉ። ጣሪያው ራቅ ተደርጎ መሠራቱ አያቷ ቤቱን ለሆቴልነት አስበው እንዳስገነቡት ያሳብቃል። ወለሉም በረጃጅም፣ ጠፍጣፋ ጣውላዎች የተለበደ ሲሆን የሽማግሌውን ጠንቃቃ የቤት አያያዝ በሚመሰክር ሁናቴ፡ ሰምና ናፍጣ ተወልውሎ ያብረቀርቃል። የቤቱን ይዘታ እያስተዋለች ትንሽ እንደቆየች ሽማግሌው ፎጣና የገላ ሳሙና ይዘው ተመለሱ።

"ሙቅ ሻወር ተዘጋጅቷል ልጄ..." ብለውም አቅጣጫውን ጠቆሟት። እሷ የጉዞ ድካሟን ለብ ባለ ውኃ እስክትለቀልቅ ድረስ ‹ፔልመኒ› የተሰኘውን በራሺያውያን ዘንድ የሚወደድ ምግብ ለመሥራት ጉድ ጉድ አሉ። ፓስታና የተጠበሰ ሥጋው እንጂ ሌሎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በበቂ ባያገኙም እንደ አቅሚቲ አበሳስለው ጠበቋት።

ቬራ ከገላ መታጠብ መልስ የቀረበላትን ገበታ ስታጣጥም ለመጀመሪያ ጊዜ ሽማግሌው ሰውም አረፍ ብለው ተቀመጡ።

"ፔልሞኒው ክሬም ባይኖረውም ከመንገድ ስለመጣሽ ለጊዜውም

---

24 ይህ ሰው የእውነትም በታሪክ የነበረ ራሺያዊ የጦር አዛዥ፣ ጸሐፊና ተጓዥ ሲሆን፤ ኢትዮጵያን ለጉድ የሚወድ፣ ለዓመታት እዚህ የኖረ ከመሆኑም ባሻገር አጤ ምኒሊክ ጋር የቅርብ ወዳጅ ነበር።በአድዋ ጦርነት ወቅት በርካታ የመሣሪያዎችን ከራሺያ ከማምጣት አልፎ በጦር አማካሪነትም ያገዘን ባለውለታችን ነው፤

2 በእረብኛ በጣም ጠንካራ፤

ቢሆን ርሀብሽን ያስታግስልሻል... በደንብ ብዪ..."

"አባባ አይጨነቁ፤ በጣም ነው የሚጣፍጠው!" አለችና ፈገግ ብላ ምግቡን እንደወደዱችው አረጋገጠችላቸው፤

ሦስት አራቴ ከጎረሰች በኋላ ጥያቄ አስከተለች። "እና እዚህ ብቻዎትን ነው የሚኖሩት?"

"አዎ ከሞላ ጎደል፤ በተለይ እድሜዬ እየገፋ ሲመጣ ብቻዬን ምግብ ቤቱን ለማስቀጠል ታከተኝ። ምሰና እራቱን ትቼ ጥዋት ጥዋት ብቻ ቁርስ እዘጋጅም ነበር። ብዙም ባይሆን ደንበኞችም ነበሩኝ። ያም ስላልተሳካና በሥሬ ትሠራ የነበረችው የምግብ ባለሙያ ጥላ በመሄዷ፡ ሙሉ ለሙሉ ለመዝጋት ከተገደድኩኝ አምስት ዓመት ከመንፈቅ ሊሆነኝ ነው። ከዚያ በኋላ የነበሩትን ጊዚያት እንግዲህ ብቻዬን ነው የማሳልፈው። ለነገሩ... አባትሽ ተመልሶ ወደ ራሺያ ካቀና በኋላ ሁሉም ነገር ቀስ በቀስ ተቀይሯል።" ... ትካዜ ፊታቸው ላይ ሲያጠላ ታዘበች።

"ያው የአያታሽም አደራ ስለነበረብኝ ቤቱን በተቻለኝ መጠን እየጠበቅኩኝ፤ መንግስት በተቀየረ ቁጥር ካርታ እያሳደስኩኝ፣ ከቁርስ ተመጋቢዎች በማገኘው ገቢ ግብር እየከፈልኩኝ እስካሁን ዘልቂያለሁ። እውነት ለመናገር ተቀማጩም አልቆ፣ ሁሉም ነገር ድክም እያደረገኝ ባለበት ወቅት ነው የመጣሽው..." አሉና ለደቂቃ ታህል ዝምታቸው ተተካ።

"ከባድ የብቸኝነት ጊዜ እንዳሳለፉ ይሰማኛል።" አለችና ዝምታቸውን ተጋራች... መብል ጨርሳ እንደተቀመጡ... "እስኪ ከአያቴ ጋር እንዴት እንደተገናኛችሁ አጫውቱኝ? ከልጅነት ጀምሮ አባቴ ሲነግረኝ ደስ ይለኝ ነበር።" አለቻቸው።

"ካልሽማ ታሪኩ ወዲህ ነው... የኔ አባት ዓድዋ ዘማች ነበር። ጣልያንን ወጥ በወጥ አድርገው ከሸኙት አርበኛ፡ ጀግኖች መካከል አንዱ ነበር። ታዲያ ልጅ ሆኜ ከሚነግረኝ ነገሮች መካከል አንዱ ራሺያውያንን ምን ያክል እንደሚወድ ነው። ራሺያውያን ሁሌም ከኢትዮጵያውያን ጎን እንደነበሩና በዓድዋ ጦርነት ጊዜ እንኳን ኢትዮጵያውያን አርበኞች የታጠቁት አብዛኛው መሣሪያ ከራሺያ የመጣ እንደሆነ ይነግሩኝ ነበር። አባቴ ስለሚወዳቸው እኔም ለነሱ ጥሩ አመለካከት ነበረኝ። ታዲያ ገና ነፍስ አውቄ ባልጨረስኩበት የእድሜዬ ማለዳ ነበር ጣሊያን ድጋሚ መጥቶ የወረረን። ሳንዘጋጅበት ከተፍ ባለብን የማይጨው ጦርነት ላይም ጀብደኛው አባቴ ለእናት ሃገሩ ተሰዋ።

ታዲያ ይህ ወረራ ማብቂያ አካበቢ ነበር ያንቺን አያት ኒኮላስ አሺዮንብን ያየኋቸው። ወደ ግራና ቀኝ የሾለ የከንፈር ጺማቸው፣ ነጭ ሪዛቸው፣ ችምችም ያለው ቅንድባቸውና ክብ ቆባቸው መቼም አይረሳኝም። ያኔ ከእኛ መንደር መጥተው ይህንን ሆቴል ሲያስገነቡ ማህብረሰቡ ግራ ተጋብቶ ነበር። መልእክት ለማድረስ መጥተው በኢትዮጵያዊቷ ሚስታቸው ፍቅር ወድቀው ነው እዚሁ የቀሩት ተብሎም ይወራባቸው ነበር። ብቻ ለተላላኪነትና ለሆቴሉም አንዳንድ ሥራዎች እንድሠራና በምትኩም ቁርስ ምሳ እራት እንደሚችሉኝ ሲነግሩኝ የልጅ ልቤ ፈነደቀ። ቀድሞዉንም ለራሺያውያን ጥሩ ነገር ስለነበረኝ ደስታዬ እጥፍ ድርብ ነበር።" አሉና ከትዝታቸው ማህደር የመዘዟትን ፈገግታ ለግሰዋት ጨዋታቸውን ቀጠሉ።

"እናም ከዚያ የልጅነት እድሜዬ ጀምሮ እርሳቸው ወደ ራሺያ እስኪመለሱ ድረስ ታማኝ አገልጋያቸው ነበርኩኝ። ከኢትዮጵያዊ ሚስታቸው፣ ከመቅደስ ወንድ ልጅ ሲያገኙ አብረን ተደስተናል። ከብዙ ክርክር በኋላ ነበር ዲሚትሪቭ የሚለው ስሙ የጸደቀው። አያትሽ እሱን ወልዳ ስታበቃ ባጋጠማት የማህጸን ህመም ምክንያት ነበር ድጋሚ መውለድ እንደማትችል የተነገራት። በዜናው ብታዝንም ባባትሽ ግን ትጽናና ነበር። ይሄው ጦሰኛ ህመም ለሞት እስኪዳርጋት ድረስም እንደ ዓይኗ ብሌን ትንከባከበው ነበር። እናቱ ስትሞት አባትሽ ዲሚትሪቪ ገና አስራዎቹ መጀመሪያ ላይ የሚገኝ ለግላጋ ታዳጊ ነበረ።" አሉና ረጅም ትንፋሽ ወስደው በሐዘኔታ ለዛ ቀጠሉ፤ "እናም እሷን ሲያጡ አባትሽም አያትሽም በጣም አዘኑ። ለዚህም ይመስለኛል ሙት ዓመቷም ሳይታሰብ አባትና ልጅ ተያይዘው ወደ ራሺያ የተጓዙ። ከአምስት ዓመታት በኋላ ሲመለሱ ጎረምሳው አባትሽ እዚያ ፍቅር ይዘት ኖሮ አንዲት ራሺያዊት ወጣት ይዞ ነበር የተመለሰው፤"

"እናቴን ማለትዎ ነው?"... ፈገግ አለች ቬራ፤

"አዎ ቆንጆዬዋ እናትሽ ነበረች፡ የቤታችን አዲስ እንግዳ ሆና የመጣችው። ታዲያ አያትሽ ሚስታቸውን ያገኙበትና ብዙ የፍቅር ህይወት ያሳለፉበትን ቦታ ጥለው መሄድ ባይሆንላቸው ነበር ተመልሰው የመጡት። አባትሽና አዲሱ ፍቅረኛው እናትሽ ግን ብዙም ደስተኛ አልነበሩም። አባትሽ ወላጅ አባቱን ብቻውን ጥሎ መመለስ ስለከበደው ነበር የመጣው፤ እናትሽ ግን በጭራሽ እዚህ መኖርን አልወደደችውም ነበር። እንመለስ እያለች አባትሽን ብትወተውተውም እሱ ለአባቱ ሲል ሁለት ዓመት ገደማ እዚሁ ቆየ። ያኔ ነበር ታዲያ ታላቅ ወንድምሽ የተረገዘው። የእናትሽ ሆድ እየገፋ

ሲመጣ በደንብ ትዝ ይለኛል። እናም የመውለጃ ጊዜዋ ሲቃረብ እናትሽ ወደ አገሯ ተመልሳ መውለድ እንደምትፈልግ ቁርጥ ያለ ውሳኔዋን ለአባትሽ አሳወቀችው። በሣምንታት ጊዜ ውስጥ ተጠቃለው ወደ ራሺያ ሄዱ፤ በቃ... ከዚያች ቀን በኋላ እኔና አያትሽ ብቻ ቀረን። ለዓመታታ አብረን ኖርን። እርሳቸው የሚሠሯቸው የራሺያ ምግቦች በኛ ሰው ዘንድ ተወዳጆች ስለነበሩ ቤታችን በሰዎች የተሞላ ነበር። እርሳቸው ከሞቱ በኋላ ግን ሁሉም ነገር ደበዘዘ። ቀኑ ጨለመብኝ። ብቻ ተይኝ ልጄ ያንን የብቸኝነት ጊዜ እንዴት እንደምነግርሽ አላውቅም።" ቀስ በቀስ ፊታቸው በትካዜ ሲወረር ታዘበች።

"የለመዱት ሰው ጋር መለያየት እጅግ አስቸጋሪ ፈተና እንደሆነ አልጠራጠርም። ያን ሁሉ ጊዜ በብቸኝነት መኖሮም ከባድ እንደነበረ እገምታለሁ።"

"አልተሳሳትሽም... ብቸኝነት ከባድ ነው ልጄ፤ ብቸኝነትን መቋቋም የሚችሉት ደግሞ ጥቂቶች ብቻ ናቸው። ብቻሽን ስትሆኚ ጊዜ ምርኩዝ ይዞ የሚያዘግም የኔ ቢጤ አረጋዊ ይሆንብሻል። ድሮ የማታ'ያቸውን ጥቃቅን ነገሮች ልብ ማለት ትጀምሪያለሽ። እንዳሉ እንኳን አሌ ብለሻቸው የማታውቂያቸው ሐሳቦችሽ ሰላማዊ ሰልፍ ይወጡብሻል። አንዳንዴም ያምጹብሻል።" አሉና የመታከት ብልጭታ በጋሽ ተምትሜ ገጽታ ላይ ሽው ብሎ አለፈ።

"የሚነግሩኝ ነገር በሙሉ ትልቅ እውነትን ያዘለ ነው። እንደዚህ አይነት ጊዜ በማሳለፍዎ አዝናለሁ።"

"ኧረ ምን በወጣሽ ልጄ፤ ብቸኝነትም ቢሆንኮ ሙሉ በሙሉ መጥፎ አልነበረም። በዚህ ረጅም እድሜዬ አስተውያቸው የማላውቃቸውን ነገሮች እንድረዳና ዓይኔን ገልጬ እንዳይ አድርጎኛል። በዚያ ላይ አባ በላይ የሚባሉ ቀና ሰው እየመጡ ያጽናኑኝ፣ ይመክሩኝና ለተወሰኑ ቀናት ቆይተው ይሄዱ ነበር። እርሳቸው ባይኖሩ ሁኔታዎች ይበልጥ ይከብዱኝ ነበር።" ... በረጅሙ ተነፈሱና ብድግ ብለው ቬራ የተመገበችበትን ሰሀን አነሱ። "ልክ ብለዋል፤ ሰው ብቻውን ሲሆን ተፈጥሮን በአዲስ ዓይን መመልከት ይጀምራል፤ የህይወቱን መርሆዎች እንዳዲስ ፈትሾ ራሱን በተሻሉ መርሆዎች ይቃኛል። ባይገርሞት እኔም ይህንን ሆቴል መልሶ ከማቋቋም ባሻገር ብቸኝነትና የራስ ጊዜም ፈልጌ ነው አንድም መምጣቴ..."

"ጥሩ አድርገሻል ልጄ፣ አባ በላይም ብዙ ጊዜ "ሰው ከረብሻ ርቆ ራሱን ካልተመለከተ ትርጉምና ሰላም ያለው ህይወት መምራት አይቻለውም።" እያሉ ብቸኝነቴን እንዳልጠላው ይመክሩኝ ነበር።" አሉና አንድ አዲስ ነገር እንዳስታወሰ ሰው ፈገግ ብለው ቬራን ተመለከቷት። "ባይገርምሽ አንድ ነገር ትዝ አለኝ፤"

"ምን ትዝ አልዎት?" አለች ቬራ፤

"እኚሁ አባት በቅርቡ መጥተው አንዲት የሩቅ፣ ጸጉረ ልውጥ ሰው እኔ ጋር እንደምትመጣ ነግረውኝ ነበር።"

...| ቬራና ጋሽ ተምትሜ በአግራሞት ተያዩ።

⌘ ⌘ ⌘

*...የብቸኝነት ቆፈን፤*

*ዳዊት መለሰ ይዘፍናል...*

*♫ "እስኪ በይ ፍረጂኝ ፣ ቅጣቴ አልበዛም ወይ?*

*አንቺንም ኑሮንም፣ ማጣት ቀላል ነው ወይ?"*

ጉዳትና ሐዘን የደቆሰው ለይኩን ከእና ቤቱ ገብቶ በሩን ዘግቷል፡ ሙዚቃ ከፈቷል። ሚስት፣ ልጅና ሥራውን በጥቂት ወራት ውስጥ ተነጥቋልና ቢተክዝ በምን ይጽና?

*♫ "እኔ ያላንቺ መሽ ነጋ ምንተዳዬ?*

*አንቺ ጎለሽ ከጓዳዬ፣*

*የኔ... ልቤም ቤቴም ዝግ ነው በሩ*

*ፍቅሬ ፡ አንቺ ነግሰሽ በመንበሩ፣*

*ኧረ፡ ኧረ እጦቴን ተመልከቺ ፣ እስረኛሽን ልቤን ፍቺ፤"*

ደግሞኮ፡ ከሷም ብሶ ትስቃለች። ድምጿን ከፍ አድርጋ ትስቃለች/ ኤልሳ የምትባል ፍጡር ታሰቃየዋለች።

የሳቋ ድምጽ ደግሞ እሱ ጋር አስጠሊታ የገደል ማሚቱ አለው። አንዴ የሰማው ሳቋ ለቀናት ያጠነጥንበታል። ከመሄዷ በላይ ርቃ አለመሔዷ ሌላ ፈተና ሆኖበታል። አንዳንዴ ሁለቱንም ጆሮዎቹን በእጆቹ ጥብቅ አድርጎ

ይይዝና ድምጿን ላለመስማት ይጥራል። ያ ሳቋ፣ የጣዕረ ተስፋ ማቃተት የሚመስል ቅንጡ መፍነክነኳ ግን አይቀረፍም። እያፌዘች ጆሮው ውስጥ የተቀመጠች ንውስ፣ ቤሳ ኤልሳ ያለች ይመስለዋል። ጎትቶ ሊያወጣት ጣቱን ሲሰድ ሸሽታ ወደ አንጎሉ ትዘልቃለች። እዚያም ገብታ አታርፍ፡ በትዝታ ደማ ሥርኖቹን ትቆፍራቸዋለች። ያኔ ራስ ምታት ያመዋል። በጣም ያመዋል። እንደምንም ተነስቶ የረሳችውን ነጠላ እንደ እራፊ ጭንቅላቱ ላይ ያስራል። ትንሽ ህመሙ በረድ ይልለታል።

ወዲያው ደግሞ ህጻኑ መርዕድ ሲያለቅስ ይሰማዋል። "ወይኔ ልጄ! ምን ሆኖ ይሆን የሚያለቅሰው?" ውስጡ ድጋሚ ርብሽብሽ ይልበታል። እህህ...አሄሄ... ይታመማል፤ ይሄኛው ህመም ደግሞ ከወደ ሆዱ ግድም ነው የሚሰማው። እልፍ ጥያቄዎች ከትናጋው ጀርባ እየተነኑ ወደ አእምሮው ይጎርፉበታል። የድሮ ሚስቱ ልጁን አልተንከባከበችው ይሆን? ልጁን ማባባል የማይችል አባት ምን ይባላል? ባልኖርኮ ነው የሚሻለኝ! እያለ ይተክዛል፡ የሷን ትዝታ እንዳዘለ ይቆዝማል። ባዶ ነው። ኦና ቤት። ብቸኝነት ውስጡን አመነመነው። በምንስ ሊጽናና ይቻለዋል?

የፈረደባቸው እናቱ ፡ ወ/ሮ ብዙወርቅ ከሚጥል በሽታቸው ጋር እየተናነቁ መጥተው ሊያጽናኑት ሞክረዋል። በእድሜና በኑሮ አቅማቸው ስለደከመ ብዙ ሊረዱት ግን አልቻሉም።

የልጃቸው ነገር ከቀን ወደ ቀን አሳሳቢ እየሆነ መምጣቱን እያዩ ቁጭ ማለቱ ግን አልሆነላቸውም። ጭንቀታቸው ቢበዛ አንድ ቀን ህመምና ክብራቸውን ዋጥ አድርገው የኤልሳ ቤተሰቦች ጋር ሄዱ። ደርሰው ሲያንኳኩም ወ/ሮ መንበረ በሩን ከፍተው ቆሙ። ይግቡም አላሏቸው። ከአንገት በላይ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ "ምን ፈልገው መጡ?" የሚል፤ በውስጡ "አንፈልጎትም ሂዱ!" የሚል አንድምታ ያለው ጥያቄ አስከተሉባቸው። የለይኩን እናት፡ ወ/ሮ ብዙወርቅ እልህና ህመማቸውን ዋጥ አድርገው...

*"አንድ ነገር ቢጨንቀኝ ነው መምጣቴ"* አሉና የነጠላቸውን ዘርፍ እያሻሹ፣ መሬት መሬቱን እያዩ ቀጠሉ። *"የልጄ የለይኩን ነገር በጣም እያሳሰበኝ ነው። የእርስዎ ልጅ ኤልሳን በጣም ነበር የሚወዳት። ከእሷ ጋር ከተለያዩ በኋላ ሰው አልሆነም። እንዲያው ልጅዎትን ቢመክሯትና ቢታረቁ አይሻልም?..."*

"እሂሂ..." አሉ ወ/ሮ መንበረ በፌዝ ሳቅ፣ "በውሸት እሉባልት የጨዋዋ ልጄን ስም ካጠፋና የገዛ ህጻን ልጄን አደጋ ላይ ከጣለ በኋላ... እኮ ምን ብላ ነው አብራው የምትኖረው? በሉ አሁን እንደአመጣጦ ይሂዱ፣ የማይሆን ነገር አይጠይቁኝ!" አሉና በሩን እንደመዝጋት ቢጤ ቃጣቸው፤

"በአማላጇቱ ይዤሻለሁ!"... ወ/ሮ ብዙወርቅ ሁለመናቸው ልውጥውጥ አለ፤ ክብራቸውን ጥለው ቧገቱ ..."አንድዬ ልጄ ራሱን ጥሎ የአእምሮ ህመምተኛ መስሏል... ብቻዬን ተሰቃየሁ..." ከንግግራቸው መባቻ በፊት እንባቸው ቀደመ።

"ኧረ በፈጠረሽ አታልቅሺብኝ ሴትዮ... እዚያው በጸበልሽ፣ ሲጀመርም እኛ አይደለም ያጋባናቸው፤ እኛም አላፋታናቸውም። ቀድሞውንም ያንቺ ልጅ ለልጄ አይመጥናትም። ቆይ እስኪ ይንገሩኝ?!... ከዚያ መናጢ ልጅዎ ጋር ስታክክ እንድትኖር ነበር እንዴ የፈለጉት? ... ኡኡቴ¡" - አንቱታው ቀረ፤

"እንዴት እንደዚህ ትያለሽ?... አብረን በልተን ጠጥተን፣ አብረን ጨፍረን አይደል እንዴ የዳርናቸው? ... ከቶውንስ ድሃ መሆን ኃጢያት ነው እንዴ? አክብሬ በመጠየቄ እንዲህ እንድታዋርጂኝማ አልፈቅድልሽም!" ... የወ/ሮ ብዙወርቅ ስሜት ከሐዘን ወደ ቁጣ ሲለወጥ አየር ምድሩ ታዝቧል። ..."እዎ! ምን ትሆኚ እስኪ?... ምርጧ ልጄ አሁን ማጀቱ ሞላ ያለ፣ የተሞናደለ ህይወት ጀምራለች። እንኳን ለራሷ ለኔም ተርፋለች። አሁን በህግ አምላክ ይዤሻለሁ! ይሄን የማይመስል ሐሳብሽን ይዘሽ፡ በመጣሽበት ሂጂልኝ፤" አሉና ወ/ሮ መንበረ በሩን በኀይል ፊታቸው ላይ ደረገሙት። ወ/ሮ ብዙወርቅ በንዴትና እልህ እየተብከነከኑ፡ በሩ ላይ እንደተገተሩ ለደቂቃዎች ቆዩ። ቁጭታቸውን እንደምንም ዋጥ አድርገው፣ በነጠላቸው ፊታቸውን እየጠራረጉ ወደ ቤታቸው መመለስ የግድ ሆነባቸው።

⌘ ⌘ ⌘

የጨው በረንዳ ሰፈርተኞች አንዲት ሴትዮ አውላላ መንገድ ላይ ድንገት አጥወልውሎ ሲጥላቸው ተመለከቱ። ሁሉም ሮጦ ሄዶ ከበባቸው። ከሰፈሩ ውስጥ የሚጥል በሽታ ያለባቸው ማን እንደሆኑ ሁሉም ያውቃል። ገሚሱ ሚሪንዳ፣ ገሚሱ ክብሪት ለማምጣት ተሯሯጠ። አብዛኛው ከንፈሩን መጠጠ፡ ቢጠቅምም ባይጠቅምም ያ መተሳሰብ በቦታው ነበረ።

|ከሰዉ መሐል ግን አንዲት ወጣት ሴት ስትበር መጥታ ከጎናቸው

ተቀመጠች። ጭንቅላታቸውን ዳሌዋ ላይ አድርጋ፤ አረፋቸውን እየጠረገች፣ በጥንቃቄ ስትንከባከባቸው ሁሉም አይተዋታል።

... |እኚያ ሴትዮ የወደቁት ከነ ሜሮን ቤት ፊት ለፊት ነበር።

⌘ ⌘ ⌘

ለይኩን ነገር ዓለሙን ችላ ብሎ ከቤቱ ተጋድሟል። የእናቱን ለልመና መሄድና መንገድ ላይ መውደቅ አልሰማም። ሲያመጣው አንዴ ነው የሚሉት አካች፣ ሥጋ ለብሶ ወዳጁ ከሆነ ግን ከራርሟል። ደብሮታል፣ ከፍቶታል፣ ሐዘን ወርሶታል። ተስፋ ቢስነት አንሶላ፣ በኑሮ ትርጉም ማጣት ደግሞ ትራሱ ሆኗል። የህይወት ሽንቁሮችን፣ ትናንሽ የሚዋጉ ወስፌዎች እንደ ጨቤ ሲገዝፉ፣ እነሱን ለማዶልዶም ሲኳትኑ መኖር ከባድ ሸክም ነው። *{ባልታከመ ድባቴ ውስጥ ያሉ ሰዎች በጥዋት ተነስቶ ወደ ሥራ መግባት፣ ከሰው መቀላቀል እንደ ቋጥኝ ይከብዳቸዋል። ሰው የመሆን ኑባሬ ምኑም አይጥማቸውም።}*

*{የእጦት ብሶት ደግሞ በሦስት እሳት ነዶ አመድ ይሆናል - በለቅሶ፣ በጊዜና በመተንፈስ። እንባ የተቃጠለውን የውስጥ እሳተ-ጎሞራ ይዞ የሚወጣ ግንፋሌ ነው። ጊዜ በመርሳት ጥበብ የኑሮን ቁስሎች ወደ ህመም አልባ ጠባሳነት የሚቀይር ኃይል ነው። መተንፈስ ደግሞ ሁለት ግብር አለው። አንዱ ወደ ውስጥ መተንፈስ፣ ከራስ ጋር መነጋገር ሲሆን ሁለተኛው ወደ ውጭ መተንፈስ ... መጮኽ፣ ከሰው ማውራት ወይም መዝፈን ሊሆን ይችላል፡ ተንፍሰውና ይውጣልኽ እንደሚባለው። መተንፈሻ፣ ጭስ ማውጫ ያለው ሸንት ቤት ብዙም አይሸትም እንዲሉ። ታዲያ ምርጡ መተንፈሻ መንገድ ኪነ-ጥበብ ነው ይባላል። ህመምን በግጥም፣ በቲያትር፣ ሙዚቃና ጽሑፎች መተንፈስ። በመሰል ፈታኝ ቀናት ከማይርቁህ ነገሮች አንዱም ዜማ ነው።}*... ለይኩን አሮጌዋን ቴፕ አወጣና የዳዊት መለሰ ምስል ያለበትን ካሴት መታ መታ አድርጎ ሰነገው። *"ፍረጂኝ!"* የተሰኘው ሙዚቃው ቅድም ከቆመበት ቀጠለ። ለይኩን ከንፈሮቹን እያርገበገበ በልቡ አብሮ ያዜም ጀመር... *"እስኪ በይ ፍረጂኝ ቅጣቴ አልበዛም ወይ?*

*እንቺንም ኑሮንም ማጣት ቀላል ነው ወይ?"*

በእጦት የተቃጠለ፣ በናፍቆት ለተከዘ ነፍስያው፣ ገላጭ ግጥሙ፣ አጥንት ገዝጋዥ ዜማው፣ ሰርስሮት ገባ። ዘፈኑ የልቡን ፍም እሳት የሚያቀጣጥል ማራገቢያ ሆነለት።

{{ሙዚቃ መሐረብ ከማቀበል ውጪ ያለውን ሁሉንም የአላቃሽ ሥራ ይሠራል። ነገር ግን ሙዚቃ አይነት አለው አንዳንዱ ከጆሮ ላይ ተንጫጭቶ፣ ነጥሮ ይመለሳል፤ አንዳንዱ ደግሞ ዘልቆ ገብቶ ልብን ያረሰርሳል።}

ዳዊት ቀጥሏል...

*"ይከፋኛል ሳስታውሰው*

*መሆንሽን የሌላ ሰው፤"*

... ይገርማል፣ የኔ ያልነበረች እንቡጥ አበባ፣ አካሌን ሸክላ አድርጌላት፣ በፍቅሯ ሞቼላት፡ ሥጋዬ ላይ ከተከልኳት በኋላ፣ ፍሬም ካፈራችልኝ በኋላ፡ ከነፍሬዋ፡ አንድ አልፎ ሂያጅ መንገደኛ ቀጥፎ ወሰዳት። ለነገሩ እሷን አይደለም እኔን ነው ቀጥፎኝ የሄደው፣ ይሄንን ሸክላ እኔነቴን ፈርክሶ የጣለው። መናኛ ፍራሹ ላይ ተጣጥፎ ኩርምት አለ/ያ ፍራሽ አፍ ቢኖረው አብሮት ተንሰቅስቆ ባለቀሰ ነበር።

እናም ...በዚያች ቤት የሐዘን ጉባኤ ተሰይሟል።

ዳዊት ቀጥሏል፤

*"እኔ ያላንቺ መሸ ነጋ ምንተዳዬ?*

*አንቺ ጎድለሽ ከጓዳዬ፤"*

አዎን ቢኖር ባይኖር ህይወቱ ትርጉሙ ምንድነው? ምድር ላይ የሚራመድ በድን ገላ ምን ይረባል? ሞት አይሻልም? ከዚህ ከፍተኛ የድብርት ስቃይ ሞት ግልግል ማለት - ምንኛ እረፍት ነው? ... ጆሮይ ብሎ ለዘላለሙ መተንፈስ...

ቀና ቢል የጣሪያ ድጋፍ የሆነ ጣውላ ተመለከተ። አንድ መጥፎ ሐሳብ መጣለት፤ ብድግ ብሎ ከተኛበት ተነሳ። ጠንከር ያለ ገመድ ፍለጋ በየሥርቻው አማተረ። ከልብስ ማስጫነት ተርፎ የተጣለ ጥልፍልፍ ገመድ ከዓይኑ ገባ። ብድግ አደረገውና ሸምቀቆ ሰራበት። አንዱን ጫፍ ከጣውላው ላይ አሰረው። ... ውስጡ በሙግት ተሞልቷል። ላድርገው አላድርገው? አዎ! መሞትና መኖር በአንዲት የውሳኔ ገመድ ላይ የሚንጠለጠሉበት ጊዜ ሊመጣ ይችላል።... ማን ምን ያውቃል?

ዳዊት ቀጥሏል

*ይህ ይመጣል ብዬ አላውቅም፣*

*የቅጣት ቀን ጭንቁ አያልቅም።"*

በፍጹም... ይሄ ይመጣል ብሎ አስቦ አያውቅም። *{በምድር ሲኖሩ ስለ ነገ እርግጠኛ ከመሆን በላይ ታላቅ ስህተት የለም።}* ለይኩንም ይህንን *እውነታ በከባዱ መንገድ ተምሯል።* እየተርበተበተ አንገቱ ላይ ሸምቀቆ አጠለቀ። በርጩማው ላይ ቆመና ስለኤልሳ ለመጨረሻ ጊዜ አሰበ።

*{ሰው ለካ ራሱን ወደ ቀጣይ ዓለም ሲያሸጋግር አብሮ በውስጡ ይዞት የሚሄደው የሌላ ሰው ሽራፊም አለ።}*

ዓይኑን እንባ ከአፍ እስከገደፉ ሞላው። ሁለመናዋ በጣም ናፍቆታል። ያኔ የሳማት ከንፈሩ የሷን ከንፈር ቢራብ፣ የወሸቃት ጉያው በብርድ ቢቀሰፍ፣ አንሶላው የሷን ጠረን ለጉድ በየሸንቁሩ ወትፎ አየር ቢያሳጥረው፡ "አይዞህ" የምትለው የልቡ ነርስ የለችም። ሊሞት ከጫፍ ላይ ቢገኝም ፈውሱ ግን ጥላው ሄዳለች። የስንብት እንባ ከዓይኖቹ እያወረደ የቆመበትን በርጩማ፤ ከመሬት ጋር የቀረውን ብቸኛ ጥምረት ሊጥል ሲል... በሩ ተንኳኳ። ባልሰማ ችላ ሊለው ቢሞክርም ድጋሚ ደመቅ ተደርጎ ተንኳኳ። በልቡ "ብለው ብለው ሞቼ እረፍቴን እንዳላገኝ ሊከለክሉኝ ነው እንዴ?" እያለ፣ እየተነጫነጨ ገመዱን ፈታ። ከተንጠላጠለበት ወርዶም በሩን ከፈተ።

|ሜሮን እናቱን ደግፋ ከደጅ ቆማለች።

⌘ ⌘ ⌘

*ብቸኝነት ጋር ትንቅንቅ! ...ጥዝጥዝ!*

... ቀን ቀንን ሲተካ ዶክተር ሶፎኒያስ ከባድ ሁኔታ ውስጥ እየገባ መጣ። የእኚያ አባት ዋሻ ውስጥ ያገኛቸውን ጥራጥሬዎች ቆረጣጠመ፤ እያገነፈለ በላ... ስንቁ ለጥቂት ቀናት ቢዘልቅም የተቀመጠው ምግብ ለመሟጠጥ ግን ብዙ ጊዜ አልፈጀበትም ነበር። ሆዱ ውስጥ የነበረው አልቆ ሰውነቱ ከሆዱ ውጭ ያለውን አካላዊ ስብ መመገብ ጀምሯል። እየከሳ ነበር።

ትልቁ ርሐብ የሆነበት ግን የጆሮ ርሐብ ነው። ብቻውን በሆነ በቀናት ውስጥ ወሬ ለጉድ ጠማው፣ ንግግር የመስማት ጠኔ ያዘው። ቀን ወጣ ብሎ ቢያይ የማይነቃነቁ የሚመስሉ ተራሮችና ግራ ቀኝ የሚሉ ዛፎች ብቻ ይቀበሉታል። *ህይወት ቀጥ-ለጥ-ጸጥ-ረጥ-ያለች* መሰለች። ለማረፍም መድከም እንደሚያስፈልግ እስኪገባው ድረስ ማታ ማታም

እንቅልፍ በዓይኑ አልዞር አለ። ኋላ ላይማ ሌሊት ሌሊት የሚሰማቸውን የእንስሳት ድምጾች ትርጉም እስከመስጠት ደረሰ። እስከ ዛሬ ሰምቷቸው የማያውቃቸውን ድምጾችን መስማት ጀመረ። በመወሸቡ የፍጥረትን ቱባ ድምፀቶች አዳመጠ። ... በእርግጥም በህይወቱ ውስጥ አጋጥሞት የማያውቅ የራስ ጊዜን እያሳለፈ ነበር። ነገር ግን የብቸኝነት ድብታና ፍርሃቱ ላይ ዘርፈ ብዙ ርኃቦቹ ተጨምረው ፈተና ሆነውበታል።[26]

ሁሉም ሰው ጉልበቱ የሚሰበርባት አንዷት ነጥብ አለች ሲባል ይሰማ ነበር። ይህቺ የመቋቋም ለከቱ አልፎ ቅንጥስ የሚልባት ነጥብ ነች። ሶፎኒያስም እዚህች ነጥቡ ላይ እንደደረሰ አልተጠራጠረም። ብቸኝነትና ጸጥታው መቀበል ከሚችለው በላይ ሆነውበታል። እርግጥም ፈተናውን መቋቋም አልቻለም። ...እርሳቸው በጠፉ በሣምንቱ ጓዙን ጠቅልሎ ወደ ሞቀ ቤቱ ለመመለስ ወሰነ።

በማለዳ ተነስቶ፣ ባዶ ሆዱን አክኮ፣ ፀሐይቱን በጨንባሳ ዓይኖቹ ታግሎ ፊቱን ታጠበ። ቦርሣውን ሸክፎ፣ ከዋሻው ወጥቶ፡ ራመድ ራመድ አለና ዞር ብሎ ተመለከተ። ለቅጽበት የሳምንት ቤቱን በስንብት ዓይን ገረፍ ካደረጋት በኋላ የደከመ ጉልበቱን እየጎተተ ወደ መጣበት አቅጣጫ መመለስ ጀመረ።

ይህ የመመለስ ውሳኔው ግን ከቶውንም ሊጸና አልቻለም። ከተወሰኑ እርምጃዎቹ በኋላ ከራሱ ጋር ከባድ ክርክር ውስጥ ገባ። ይህንን ሁሉ ርቀት አቋርጦ የመጣበትን ጥያቄ ሳይመልስ፣ ሚስጥሩን ሳይገልጥ መመለስ ሞት መስሎ ታየው። ምን አልባትም ይሄ ከዚህ በኋላ ደግሜ ላገኘው የማልችለው አጋጣሚ ነው ሲልም አሰበ። ሁሉን ነገር ችዬ የዝምታን ጣዝማ እቀስማለሁ ያላቸው አባት ታወሱት። ከየት እንደመጡ? ታሪካቸውን ባያውቀውም ከአንደበታቸው የሚወጣው የህይወት ቃል፣- የዝምታ ሐተታ በሙሉ ማርኮታል። ብቸኝነትን እንደሚወጣው አምነው ነው ይሄንን ኃላፊነት ሰጥተውት የሄዱት። ይህንና ሌላም እልፍ ነገሮችን አውጠንጥኖ አርባ ምናምን እርምጃዎችን ከሄደ በኋላ ጉዞውን ገታ። ብዙ አመነታ፣ በውዝግብ መሀል ከራሱ ጋር ተሟገተ፤ በስተመጨረሻም ቢያንስ አንድ ቀን ልጨምርና ነገ እመለሳለሁ ብሎ ደመደመ። አዲስ

26 ለብቻ መሆን በእርግጥም ፈታኝ ነገር ነው። የአሜሪካ ሳይኮሎጂስቶች አማካሪ የሆኑበት አንድ 'Alone' ወይም ለብቻ የተሰኘ፣ ግማሽ ሚሊዮን ዶላር የሚያሸልም የቲቪ ውድድር ነበረ። በውድድሩ መሰረት ብዙ ተወዳዳሪዎች ለብቻቸው ከቤት ውስጥ እንዲዘጋባቸው ይደረግና ብቸኝነቱን ተቋቁሞ ረጅም ጊዜ የቆየ አሸናፊ ይሆናል። የሚገርመው ለመወዳደር ከሚገባው አብዛኛው ሰው በቀናት ውስጥ የሥነ-ልቡና ቀውስ እያጋጠመው ለአስቸኳይ የህክምና እርዳታ ነበር የሚወጣው፤ የአሸናፊዎቹ መለያ ደግሞ ሜዲቴሽን በዋናነት ተቀምጧል፤

የሚከሰት ነገር ካለ ልይ ብሎ ወስኖ፤ በዚያው በደከመ ጉልበቱ እየተጎተተ ወደዚያች ማረፊያው ተመለሰ። ይዞ የወጣውን በርሳ መልሶ አስቀመጠና ወደ ደጃፍ ወጣ። ዙሪያውን ቢያስተውል በቅርብ ርቀት የሚገኝ ግዙፍ፣ ቅርንጫፈ ዠርጋጋ ዛፍ እይታው ውስጥ ገባ። በዚያች ቅጽበት ያኒ አባት ከዛፍ ሥር ቁጭ ብለው በተመስጦ ሲዘፍቁ ትዝ አሉት። የታጠፈ አንጀቱን፣ የተንጠፈጠፈ ኃይሉን ይዞ ወደ ዛፊቱ አቀና። እግሮቹን አፈራርቆ ከዛፏ ሥር ተቀመጠ- በቀስታም ዓይኖቹን ከደነ።

ዓይነቹን በከደነበት ቅጽበት የሐሳብ፣ ትውስታና ስሜቶች መዓት በአእምሮው ውስጥ ሲፈሱ ታወቀው። ጭንቅ አለው፤ ርቦታል፡ ደክሞታል... ግን እንደምንም ወደ ዝምታ ሐሳቦች ለመግባት እየታገለ ጥቂት ደቂቃዎች እንዳለፉ ከየት እንደመጣ ያላወቀው የሐሳብና የድምጽ ሰረገላ ወደ አእምሮው ጓዳ ከተፍ ይል ጀመር። በሙያው ዘርፍ ለእንደዚህ አይነት እንግዳ የሆኑ ድምጸ-ሐልዮቶች ‹ሀሉሲኔሽን›[27] ተብለው እንደሚጠሩ ያውቃል። በሌሎች የገሀድ ዓለም የሌሉ ነገር ግን በሰውዬው አእምሮ ውስጥ ተዋቅረው ‹እውነት› የሆኑ ድምጸ-ሐሳቦች ናቸው። እናም አሁን ወደ አእምሮ እየመጡ ያሉ ድምጾች ከድካምና ርሀብ ጋር ተያይዘው የተከሰቱ ‹ሀሉሲኔሽኖች› ሊሆኑ ይችላሉ ብሎ ሰጋ፤ ወዲያውም ራሱን መጠራጠር ጀመረ።

"ወይኔ ሶፎኒያስ፡ ዝምታን ፈልጌ መጥቼ እዚሁ ልቀር ነው? ሰው ላክም መጥቼ ራሴው ታምሜ ልመለስ ይሆን?" እያለ በጭንቀት ቆዘመ። ነገር ግን ወዲያውኑ አንድ ሌላ ድምጽ ወደ አእምሮው መፍሰስ ጀመረ...

"እነሆ ሶፎኒያስ ይሄ ያንተ ድምጽ አይደለም። እየቃዠክ፣ እየቀባዠርክ ወይም እየቀዠብክ አይደለም። ይሄ በተመስጦ ውስጥ ስለበረታህ፣ ዝምታን በመሻት በትዕግስት ስለዳከርክ ወዳንተ የደረሰ የምናበ-መረብ መልዕክት ነው። በዘመናችሁ ‹ኢንተርኔት› ብላችሁ እንደምትጠሩት ያለ የማይታይ ከቦታ የዘለለ ግንኙነት ነው። ግንኙነታችን ግን በስልክ ሳይሆን በአዕምሮና ነፍስ መስተጋብር በኩል በሚፈጠር አጥናፍ ተሻጋሪ መስመር ነው።"

"እሺ ግን... አንተ ማነህ?" ... ጠየቀ ለይኩን፤

"አንተስ ማነህ?" ... መለሰ ድምጹ፤

27 ለታማሚው ብቻ የሚሰሙ፣ የታወቀ ውጫዊ መነሻ የሌላቸው ድምጾች፣ ንግግሮች ወይም ትዕዛዞች፤

"እኔማ..." ዝምታ ተተካ፤ "...እኔ ግን ማን ነኝ?" የማይመለስ ጥያ
ሆነበት፣ ሳያስበው ውይይቱ ውስጥ ዘው ብሎ ተዋሀደ።

ግን ከጅምሩ በዝምታ ውስጥ ማውራት ይቻላል እንዴ? ሲል ራሱ
ጠየቀና በረጅሙ ከነፋሻማው አየር ማገለት። ወዲያው የሚወደ
የኤፍሬም ስዩም ግጥም በድምጽ፡ ምናቡ ውስጥ በተዘረጋ የብርሃ
መድረክ ላይ ተቀንጭቦ ሲቀርብ ታዳሚ ሆኖ አዳመጠ...

*"...በዝምታ ብረት ፡ ታስረን የምንሰማት፣*

*የትም የሚጀመር ፡ የማንም ሰው እውነት*

*ይሄን ሲል ነው ሲባል ምንም አለማለት፣*

*የንፋስ ታላቅ መብት!..."*

ሶፎኒያስ ዓይኑን ክድን እንዳደረገ ተመስጦ ቀረ። ድምጹም በምና
ሞገድ መምጣቱን አላቆመም። ነጻው ንፋስ አሁንም እያፏጨ ይንከላወሰ

"አንተ ወጣት ሰው፣ ከዛፍ ሥር ቁጭ ያልክ አጥር አልባ አካል
ሰማያትን የምትመጥቅ ነፍስ ሆይ - እነሆ ከሰዎች መራቅኽ፣ ብቻህ
መቀመጥኽ፣ ለጥሞና ዓይንኽን መክደንህ መልካም ሆነልኽ:: አሁ
ትኩረትህን የከበበህ አየር ላይ አድርግ::[28] ነፋሻው አየር በአፍንጫህ ፍስ
እያለ ወርዶ ለህዋሳቶችህ ነፍስን ሲዘራ ልብ በል:: ቀስ ብለህ በአፍንጫ
አየር እየማግክ ሣንባህ አቅሙ እስከፈቀደ ድረስ በህይወት አየር ሙላው
ይሄን የህይወት አየር በውስጥህ እንዳዘልክ ለተወሰኑ ሰከንዶች ዝም በል
...ይህቺ ዝምታ በመውጣትና በመግባት፣ በመወለድና በመሞት መካከ
ያለች ቅጽበትን ትወክላለች:: ውስጥህ የገባው አየር አስወጣኝ የሚለ
ጥያቄ ሲበረታ በዝግታ በአፍህ በኩል ተንፍሰው:: ይሁንን ልምም
በተከታታይ ለሰባት ጊዜ ፈጽመው:: ትኩረትህን አተነፋፈስህ ላ
ስታደርግ አእምሮህ ከጊዜያዊ ጭንቆቹ ተነጥሎ ወደ እልፉ መገኛትህ
አሁናዊ ዓላማህ ላይ እንድትሰለጥን ይረዳኻል:: ይሄን ድምጽም ወ
አንተ ለማድረስ ለኛ ቀላል ይሆንልናል ማለት ነው:: ...ታዲያ ይህ
ልምምድ ለማድረግ ስትሞክር በየጊዜው ወደ ጭንቅላትህ የሚመ
ማናቸውም አይነት ሐሳቦች ሊኖሩ ስለሚችሉ በፍጹም አትግፋቸው

28 አንባቢው ለአፍታ ንባቡን አቁሞ፡ ለአንድ ወይ ሁለት ደቂቃ ይሄንን የመተንፈስ ልምምድ ጽሑፉ
እንዳለው ተመሳሳይ መልኩ እንዲተገብር እመክራለሁ::

ሐሳቦችህን አንተ ለመምራትም አትሞክር... ራሳቸው እንደ ችረት እየፈሰሱ ይለፉ:: በየመሐሉ የሚመጡ፡ እንደ በረዶ የቀዘቀዙ የሐሳብ ግግሮች ሲያጋጥሙህ ደግሞ አንተን ከፈጠረ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በነጻ ንጹህ አየር እየለገሰ እስትንፋስህን በሚያስቀጥለው ፈጣሪህ ላይ ተንጠላጠል:: ከፍ ... ሰፋ በልና| የመዳኛውን ገመድ አጥብቀህ ይዘኽ - የእሳቤ መሰናክሎችህን እለፍ::" አሉት፤

ሶፎኒያስ የሚመጣለትን ምናባዊ ትዕዛዝ እየተከተለ ሳለ ድምጹ ለደቂቃዎች ጥፍት ብሎ ቀረ። ወዲያው እነዚህ የሐሣብ ጋጋታዎች ከአእምሮው ሰሌዳው ላይ እየተከታተሉ ሲያልፉ ታዘበ። ቀስ በቀስ ግን የሐሳብ ማዕበሎቹ እየረጉ ሄዱና የተንጣለለ የመገኘት ባህር በውስጡ ተፈጠረ። ወደ እርጋታው ዓለም ኡፈ...ይ ብሎ... ዝፍ...ቅ... ስም...ጥ ሲል በውል አልታወቀውም ነበር።

ቀጥሎ ያ ምናበ-ድምጽ "አሁን ትኩረትህን ዝምታ ላይ አድርግ::" አለው። "ልክ ከጨፈንካቸው ዓይኖችህ መሐል፣ ከአፍንጫህ ራስጌ ላይ ያስቀመጥከው ያኸል በመጣህበት ዓላማ፣ በዝምታህ ላይ አተኩር። ይሄም ላንተ መልካም መንገድ ነው።

እነሆ በተከታታይ ወዳንተ የምንልከውን ትምህርት አብሰልስል:: ...እርግጥ እናውቃለን... በዝምታህ ውስጥ የምትጋፈጠው አንተነትህ ብዙ ከባድ ሸክሞች ሊኖሩበት ይችላሉ:: እሙን! ውስጣዊው ጉዞ ከየትኛውም ጉዞ የበለጠ ይፈትናል:: እናም በየተራ እየመጣን አንተነትህ ጋር እንድትደርስ፣ ከታቹ ስሜትና እጦት እስከላይኛው ህሊናና ሙላት ድረስ አብረንህ እንጓዛለን:: ግን አስታውስ! እኛ መንገድ ጠቋሚ ብቻ ነን - ተጓዡ አንተ ነህ!" ዶ/ር ሶፎኒያስ ቃልም ሳይተነፍስ መስማማቱን ለአናጋሪዎቹ፣ በጽሞና| ከምናቡ ሙክራብ ለሚፎለፎሉት ድምጾች አሳውቋል። ግን መጀመሪያ እነርሱስ እነማን ናቸው?

ለመሆኑ... እሱ፣ እኔ፣ አንተስ ማን ነን? እኮ... እኛ ምንድነን?

* ✵ *

# ምዕራፍ ሰባት

# ሱባኤ ወ ተፈኩር

♀

ሜሮን ወ/ሮ ብዙወርቅን እንደ ደገፈች ወደ ውስጥ ዘለቀች። ለይኩን ግራ እንደተጋባ ሁለቱንም ተራ በተራ አያቸው። የእናቱ ልብስ በአቧራ ተደልሶ፣ እጆቻቸው ተላልጠው ሲመለከት መንገድ ላይ እንደ ወደቁ ገባው። ወ/ሮ መንበረ ጋር ሄደው ቧግተው፣ ተንቀው መመለሳቸውን ግን አልነገሩትም። ፈጠን ብሎ ከትከሻቸው ደገፍ አደረገና ከሜሮን እቅፍ ተረከባቸው። በጥንቃቄም ከፍራሹ ላይ አስተኛቸው። መንገዱን በሙሉ እሳቸውን ደግፋ የመጣችው ሜሮንም ቅድም ለይኩን ከተፈናጠጠበት በርጩሜ ላይ አረፍ አለች። ብዙም ሳይቆዩ ወ/ሮ ብዙወርቅ ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወሰዳቸው።

"አመሰግናለሁ እሺ ሜሪ..." አለ ለይኩን ወደ ቀልቡ ሲመለስ፤

"ኧረ ምንም ችግር የለውም፣ ዋናው እርሳቸው ደህና መሆናቸው ነው።ይልቅ መድኃኒት የላቸውም እንዴ?" "

"አዎ ካለቀባቸው ትንሽ ቆይቷል።" አለ ለይኩን አንገቱን እንደደፋ። መድኃኒቱ ያልተገዛበትን ምክንያት ሜሮን የለይኩንን ፊት በማየት ብቻ ተረድታለች። ያም ብቻ ሳይሆን ክፍሉ ከገባች በኋላ የለይኩንን ሐዘን ያጠቆረው ፊት፣ ማጣት ያጎሳቆለው ገጽታ አስተውላ ክፉኛ ስሜቷ ተነክቷል። የውሸት ጥርሱን እያሳየ ሊስቅላት ቢሞክርም ዓይኖቹን ስታይ ግን ስቃዩን መረዳት ችላለች። *(የሰውን ትክክለኛ ስሜት ለማወቅ ጥርሱን ሳይሆን ዓይኑን ሰርስሮ ማየት ያሻል።)*

... "የመድኃኒት ማዘዣው አለክ?"

"አዎ፤" ብሎ ለይኩን አንድ ቢጫ ወረቀት ለሜሮን አቀበላት። |ምንም ሳትለው ስትከንፍ ሄደችና በአጭር ጊዜ ውስጥ መድኃኒቱን ገዝታ

ተመለሰች።

"ለይክ... ይኼው ኪኒኑን አምጥቼላችኋለሁ፤" ብላ አቀበለችው፤ ከእንቅልፋቸው ሲነቁ እንዲውጡ አደራም አለችው።

"በጎነትን ከፋይ አንዱ በጎ አምላክ ብቻ ነው ትላለች እናቴ፣ እና እሱ ይክፈልሽ፤" አለ ለይኩን በይሉኝታ ተሸብቦ አንገቱን እንደደፋ፤

"ውይ ለይክ ምን አደረግኩላቸው ብለህ ነው?" አለችና ለይኩንን በስስት ተመለከተችው። የውስጧ እሳተ ጎሞራ እንዳይፈነዳ ታግላ ልታበርደው ብትሞክርም ከአቅሟ በላይ እየሆነ ነበር።

ጣቶቿን እያፋተገች፣ ቶሎ ቶሎ እየተነፈሰች "ለይክ?" አለችው በለሆሳስ...

"አቤት ሜሪ" ወደ መሬት እንዳቀረቀረ እንደ ነገሩ መለሰላት፤

"እየኝ እስኪ?" ... *በመከራ ቀና አለ። ዓይን ለዓይን ተጋጩ። በእንባ የተሞሉት ዓይኖቿ የለይኩንን ነፍስ አርገፈገፉት። ለይኩን ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ ሜሮንን አይቷት ያውቃል| ዛሬ ሲያያት ግን እስካሁን የእውነት እንዳላያት ገባው።*

*ዓይን ሳይሆን ልብ ነው ተመልካች እንዲሉ ገና ዛሬ አስተዋላት። ይህቺ ውብ ነፍስ ግን ማናት? እንደ እህት ዓለሙ በችግሩ ጊዜ ሁሉ ብቅ የምትለው ይህቺ ወዳጁ ማናት? ለይኩን ከየት እንደመጣ ያላወቀው ሰላማዊ ማዕበል፣ አዲስ የውዴታ ጎርፍ ውስጡን ሲሞላው ታወቀው። ሜሮን ምንም ሳትናገር፡ ሳትጋገር ቁጭ እንዳለች እንባዋ ዱብ ሲል አስተዋለ። ብድግ ብሎ አቀፋት። መቆሸሹ፣ መጎሳቆሉ ቁብም ሳይሰጣት ጥምጥም አለችበት። ማልቀሷ ግን ባሰ እንጂ አልቀነሰም።*

*ስቅ፣ ንፍርቅ እያለች እውስጡ ተወሸቀች።* ... "ለይክ?"

"ወዬ ሜሪ፣ አታልቅሺ እንጂ... ምን ሆነሻል?"

"እ... እኔኮ ከልቤ አ...**አፈ..ቅርኻለሁ!"**

ከዚህ የሜሪ ኑዛዜ በኋላ ዘለግ ያለ፣ እፎይ የሚል ትርጓሜ ያዘለ ዝምታ ነበር የተተካው። *{ከልብ ተጨንቀው ያወጧት አንዲት እውነተኛ ቃል ብቻዋን መጽሐፍ ናት።}*

⌘ ⌘ ⌘

"ይህቺ ሜሮን ያልካትን ልጅ ከጅምሩም ቀልቤ ወዷት ነበር።" አሉ ደጉ አረጋዊ ገበሬ፤ ለይኩንን ለየት ባለች፣ ምስጢራዊ የደስታ ድባብ እየተመለከቱ፤ ለይኩንም አስተኒያዊ ስሜታቸው ቢጋባበት ፊቱ ላይ ጢኖ ጮራ ፈነጠቀ።

ትንሽዬዋ ልጅ ማርታ፡ በቡሃቃ ውኃ ይዛ ወደ ውስጥ ዘለቀች። ምሳ እንዲበሉ እጃቸውን ልታስታጥባቸው ነበር መምጣቷ። ለይኩን ህጻኗን ባያት ቁጥር ድንግጥ እያለ ነርቮቹ ንዝር የሚሉት ነገር አልቀረም።

"ወይ ጉድ… መልካቸው ቁርጥ አንድኮ ነው።" አለ ለራሱ፤

⌘ ⌘ ⌘

*(ቬራ ቃልም ሳትተነፍስ ለመርዕድ ታሪኳን መተረክ ቀጥላለች።)*

ቬራ ደብረ-ዘይት ገብታ ከከተመች በኋላ ‹ሜዲቴት› ከማድረግና ተፈጥሮን ከነጸጥታዋ እያጣጣመች ከመዝናናት ባሻገር የአያቷን ሆቴል በጥቂት ጊዚያት ውስጥ አድሳ ለሥራ አብቅታለች። የአባቷ ዲሜትሪቭ ወዳጅ የነበሩት ሽማግሌው አገልጋይም ከጎኗ ሆነው በቻሉት መንገድ ሁሉ አግዘዋታል።

በሌላ በኩል ሲወራ ብትሰማውም በአካል ግን ኖራበት የማታውቀውን የኢትዮጵያ ባህል ለመልመድ ብዙ ጊዜ አልፈጀባትም ነበር። በተለይ አባቷ ያስለመዳትን አማርኛ ቋንቋ አቀላጥፋ መናገሯ ነገሮችን በእጅጉ አቅልሎላታል። ሆቴሉን ከፍታ ጣፋጭ ምግቦችን ማቅረብ ከጀመረች በኋላ ደግሞ ይበልጥ ከህዝቡ ጋር መቀራረብ ቻለች። በሥሯም አስራ ሁለት ገደማ ሠራተኞችን ቀጥራ ማሠራት ጀመረች።

የኢትዮጵያውያንን አኗኗር በብዙ መልኩ ወዳዋለች። ዘርዝሪ ብትባል የህዝቡ እንግዳ ተቀባይነት፣ ማህብረሰባዊ ቁርኝት፣ መረዳዳት፣ ሰው አክባሪነት፣ ታማኝነት፣ ገራገርነት፣ ፈጣሪን መፍራት፣ ተፈጥሯዊ አኗኗር፣ ሌላ ዓለም በፍጹም የሌለ ልዩ ልዩ ባህል፣ ታሪክ፣ ቋንቋ፣ ዘፈን፣ ጭፈራና አለባበስ፣ አመጋገብ፣ የበዓላት ድምቀት ወዘተ… ብላ አንድ በአንድ መግለጽ ትችላለች።

በዚያው ልክ ኢትዮጵያውያኑን የታዘበችባቸው ሐቆችም ነበሩ። አንዱና ዋነኛው ይህንን የመሰለ አየርና አፈር ታቅፈው በድህነት መኖራቸው ሲሆን

ከዘመኑ ስልጣኔ እጅግ ኋላ በቀረ ደረጃ ላይ ሆነውም ነበር ያገኘቻቸው። በተለይ ደግሞ ከሠራተኞቿ ያልወደደቻቸው ባህሪያትም ነበሩ። ታግሳ የቻለቻቸው ክፍተቶች መካከል ከሥራ መሸሽ፣ በወሬ ጊዜ ማጥፋት፣ የጊዜን ዋጋ አለመረዳት፣ ኃላፊነትን ለመውሰድ መለገም መሰል አሉታዊ ነገሮችን እስተውላለች። አንዳንድ ሥራዎችን ላለመሥራት በኩራት የመኮፈስ አባዜም ብዙ ጊዜ ገጥሟት ያውቃል። አንድ ጊዜ ከጽዳት ሠራተኞች ጋር ያሳለፈችው ገጠመኝ ግን እሷም ሠራተኞቿም የሚረሱት አይደለም።

*ነገሩ እንዲህ ነው...*

ቬራ የሆቴሉን ሽንት ቤት የሚያፀዳ ማሽን ከራሺያ ድረስ ገዝታ ታስመጣለች። የጽዳት ሠራተኞችም አጠቃቀሙን ተለማምደው በማሽኑ ያጸዱ ነበር። የሆነ ቀን ታዲያ አንዷ የጽዳት ሠራተኛ ማሽኑ ቆሸሸ ብላ ውኃ እየቸለሰች ሙልጭ አድርጋ ታጥበዋለች። ማሽኑም ጸጥ ይላል። ያጋጣሚ ነገር ሆኖ ሽንት ቤቱም ብዙም ሳይቆይ በቆሻሻ ድፍን አለ። ሠራተኞቹ አንድ ሁለት ቀን በእንጨት ምናምን ጎርጉረው የተደፈነውን ቱቦ ለመክፈት ቢሞክሩም አልሆን አላቸው። ታዲያ ነገሩንም ለቬራና ለሽማግሌው ተምትሜ ሳያሳውቁ ችላ ብለውት ለቀናት ቆዩ። ቀን ቀንን በተካ ቁጥር ሽንት ቤቱ ከአፍ እስከ ገደፉ ሞልቶ ፈሰሰ። መሙላት ብቻም አይደለ መጥፎ ጠረኑ ክፉኛ ተጠቃሚዎችን ሲረብሽ ስሞታው እነ ቬራ ጋር ደረሰ።

ይህንን የሰማች እለት ቬራ በፍጥነት የጽዳት ሠራተኞቹን ሰብስባ ወደ ተደፈነው ሽንት ቤት ወሰደቻቸው። ለምን ሞልቶ እንደፈሰሰ ስትጠይቃቸው ማሽኑ መበላሸቱን፣ የሆነ ነገር ቱቦ ውስጥ ተሰንቅሮ ቀዳዳውን እንደደፈነውና በእንጨት ቢጎረጉሩትም ሊከፈት እንዳልቻለ በደቦ ነገሯት።

ቬራ በነገሯት ክስተት ውስጧ በትዝብት ተሞላ። ታዲያ ቀጠሮም ሳትሰጥ ጽዳቶቹ የሚያደርጉትን ወፍራም የቆሻሻ ጓንት ከአንዷ ሠራተኛ ተቀበለች። በእራፊ ጨርቅ አፍንጫዋን ሸፍና ጓንቱን አጠለቀችና ቀጥ ብላ እንኳን ለመግባት በዓይን ለማየት ወደ ሚቀፈው ሽንት ቤት ገባች። ሁሉም የጽዳት ሠራተኞች ከውጭ ቆመው የሚሆነውን ነገር በአግራሞት ይከታተላሉ።

ቬራ ግን ካለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ሽንት ቤቱ ውስጥ ጎንበስ አለችና እጇን በቀዳዳው በኩል ወደ ውስጥ ሰደደችው። ሁሉም በድንጋጤ እርስ

በርስ ተያዩ። የነሱ ትዝብት ምንም ደንታ ሳይሰጣት እጇን ከወዲያ ወዲህ እያማሰለች ቱቦውን የደፈነውን ቁርጥራጭ ፌስታልና የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ ሞዴስ እየጎተተች አወጣች። ከዚያም የጽዳት ሠራተኞቹን በርከት ያለ ውኃ እንዲያመጡላት አዘዘች። ውኃውን በላይ በላዩ እየቸለሰች ስትለቅበት ሙሉ አይነ ምድርና ቆሻሻ ተጠራርጎ ወደ ጉድጓዱ ገባ። ሽንት ቤቱም በደቂቃዎች ውስጥ ንጹህና ለመጠቀም አመቺ ሆነ። ቬራ ጓንቶቿን በጥንቃቄ አውልቃ ጣለችና እጆቿን በሳሙና ታጠበች። ቀጥላም ንጹህ እጆቿን አድርቃ፣ መዳፍና አይበሉባዋን እያገላበጠች ለተደረደሩት ሠራተኞቿ አሳየቻቸው። አንድ ጥያቄም አስከትላ አቀረበች...

"ተቆረጡ ወይ? ... በመሥራቴ እጆቼ ተቆረጡ ወይ?"

መልስ ለመስጠት ድፍረቱ ያለው አንድም ሠራተኛ አልነበረም። አብዛኞቹ በሃፍረት አንገታቸውን ደፉ።

ሁሉም የሆቴሉ ሠራተኞች ግን የዚያችን ቀን ትምህርት እስኪሞቱ ድረስ የሚረሷት አልነበረችም።

ከእነሱም አልፎ አገር መንደሩ ሁሉ የሆነውን በሙሉ ሰማ። ያገሬው ሰው አወራ | ያቺ ከዛፍ ሥር፣ ከኮረብታ ላይ እየተቀመጠች ዓይኗን የምትጨፍነው ክልስ ሴት ጉደኛ ነች ተባለ። ጉደኛ ክልስ ባላገር፤

⌘ ⌘ ⌘

ዶ/ር ሶፎኒያስ በምናቡ የሰማው ድምጽ ከጠፋም በኋላ እዚያው በተቀመጠበት ለአንድ ቀን ገደማ ቆየ። ያ ሞርሟሪ ርሐቡ፣ የውስጥ ውጥረቱ፣ የሰው ዘር መናፈቁ ሁሉ ቀስ በቀስ እየተነኑ ወደ የት እንደገቡ ሳይታወቀው ጠፉ። ብቻ በቃላት ሊገለጽ የማይችል የጽሞና ዓለም ውስጥ እየዋኘ፣ እየበረረ፣ እየተንዶለዶለ ነበር። ድንገት አንድ በእድሜ የገፉ አረጋዊ ወደሱ የናላ አውታር ሲመጡ በዓይነ-ህሊናው ተመለከተ። በአካል ይሁን በምናብ የመጡት እርግጠኛ መሆን ግን አልቻለም። የሆነ የህልም ዓለም ውስጥ ያለ መሰለው፣ መልካቸውንም በውሉ ለይቶ ማየት አልቻለም ነበር።

ነጭ የመነናጸፊያ ቀሚስና ስፍር ቁጥር የሌላቸው ዶቃዎች ያሉት መቁጠሪያቸው ግን ቁልጭ ብሎ ይታየዋል። ሰውዬው ደርሰው በእርጋታ ከጎኑ ተቀመጡና ለሰባት ደቂቃ ታህል ዝም ብለው ቆዩ። ከሰባት ደቂቃዎች በኋላ ግን ወደ ዶክተር ሶፎኒያስም ሳይዞሩ፣ ከንፈራቸውን ሳያንቀሳቀሱ

መልዕክታቸውን ማድረስ ጀመሩ። (ትላልቅ ኃይል ያዘሉ መረጃዎች በቃላት አይተላለፉም!)

"ልጅ ሶፎኒያስ አሁን ሽጋውን መንገድ ይዘኸዋል፤ እነሆ የጽሙና ምሥጢር በጥልቀት ይገለጥልህ ዘንዳ ቀጣዮቹ ሳብእ ቀናት፡ ሱባኤ ይዘህ፡ አዲስ ሰብእ የምትሆንባቸው ይሆናሉ።" ቢሉት ሶፎኒያስ ይበልጥ ግራ ተጋባ፤

"ብዙም በሐሳብህ ባቡር አትወሰድ። ብዙም ቸል አትበል፣ ብዙም አትጨነቅ፤ ... ብዙም አታሳሳው፣ ብዙም አታጥብቀው። ከራስህ ጋር መነጋገር፣ ቁጭት ፀፀቶችህን መናዘዝ ዓላማው ልብስ በእንደድ እንደሚጸዳው አንተም ውስጥህን በቅን መሰጠት ውስጥ ማንጻት ነው።" አሉና በዝምታ መቁጠሪያቸውን እያግተለተሉ ለደቂቃዎች ቆዩ።

"ይኸውልኽ ልጅ ሶፎኒያስ፣ ሱባኤ ያዝ ስልህ ሌላ ትርጉም እንዳትሰጠው... ሐቁን ስማና አሰማ፤ ሱባኤ ቀጥተኛ ትርጉሙ ሰባት ማለት ነው። ቅዱስ እግዚአብሔር ሥራውን በስድስተኛው ቀን ፈጸመ፤ እነሆ በሰባተኛው ቀንም በአርምሞ ከዙፋኑ ተሰየመ። በአመስኳ ውስጥ ሆኖ የፈጠረው ሁሉ መልካም እንደሆነ እውቅና ሰጠ። እናም የሥራው ሁሉ ትርጉም እየተገለጠ ያለው በሰባተኛው የዓመታት እኩሌታ ቀን ውስጥ ነው ማለት ነው። የዚህ አካል መሆን ደግሞ የሰው ልጅ በጎ ፍቃድን ይሻል።

እንደዚሁ ሁሉ የሰው ልጅም የዘላለም ህይወትን ትርጉም፣ የዘላቂ ሰላምን ምንነት፣ የተፈጠረባቸውን ሚስጥራዊ አውታራት እንዲረዳ በዝምታ ቅብቅቡን ማስተንተን መቻል አለበት። በህይወት መንገድ ላይ መስመር ስቶ ከራቀው/ ከዘነጋው ንጹህ ማንነቱ ጋር ይታረቅ ዘንድ፣ ከገዛ ራሱ የአስተሳሰብ እሥር ቤት ነፃ መውጣትም እንዲችል፡ የሰው ልጅ ራሱን ማግለል፣ በተአቅቦ ከምግብ፣ ከመጠጥና ንግግር መራቅ፣ በጥሞናም መቀመጥ ያሻዋል። ከዚህ መሰል የአርምሞ ሥርዓቶች አንዱ ሱባኤ ይባላል።" አሉና በዝግታ ወደ ሶፎኒያስ ዞሩ፤... "ስለሆነም በሚቀጥሉት ሰባት ቀናት በሱባኤህ ውስጥ በሰባት ክፍሎች፣ በሰባት ደረጃዎች/ከታች ወደ ላይ፣ በሰባት እርከኖች/ከትንሽ ወደ ትልቅ፣ በሰባት ዋሻዎች/ከጠባብ እስከ ሰፊ ውስጣዊ ከተማዎችህ/ በጥበብ በተደለደሉ ውስጣዊ ‹ክሪስታሎችህ› ማለፍ ይጠበቅብኻል።" ቢሉት ዶ/ር ሶፎኒያስ ሳያመነታ ትዕዛዛቸውን መቀበሉን በአዎንታዊ ስበቃ አሳወቀ። ለጥቆም በምናቡ የሚመላለሰውን ጥያቄ አቀረበላቸው። "ሁሉም ቁጥር ያው ቁጥር ነው፤ ታዲያ ሰባት መሆኑ ለምን አስፈለገ?"

"ጥሩ ጥያቄ ጠይቀኸል ልጅ ሶፎኒያስ፣ ሰባት ቁጥር የሆነው በሰው ምርጫ ሳይሆን በተፈጥሯዊና መንፈሳዊ ምክንያቶች ነው:: ከሰባት ቁጥር ጀርባ ያለው ጥበብ የምሥጢር ቁልፍን አዝሏል:: ከሥነ-ፍጥረት ካየን ሰባት አህጉራት፣ ሰባት የአፈር አይነቶች፣ ሰባት ውቅያኖሶች፣ ሰባት የሳምንት ቀናቶች፣ ሰባት እልፍ አእላፍ ዓመታት/ ሚሊኒየሞች፣ ሰባ በመቶ ውኃ የሆነ ሰው፣ ህዋስ[29]ና ዓለም፣ ሰባት ቀለማት ያሉት ቀስተ ደመና እያልን ብዙ ብዙ ሰባታዊ ሥነ-ፍጥረቶችን መዘርዘር እንችላለን።

ግን በዚህም ሳናበቃ ከተፈጥሮ አልፎ በመንፈሳዊውም ዓለምም በቂ ማስረጃዎች አሉን:: ለመጀመር ያኸል የክርስታናውን መስመር ብንመለከት ዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ ስምንት ቁጥር አንድ ላይ፡

"ሰባተኛውንም ማኀተም በፈታ ጊዜ እኩል ሰዓት የሚያህል ዝምታ በሰማይ ሆነ::" ብሎ ሰባት ቁጥር ከአርምሞ ጋር ያለውን ጥልቅ ምሥጢር ይጠቁመናል:: ሰባቱ ሊቃነ መላእክት፣ ሰባተኛዋ ቀን ሰንበት መሆን፣ ሰባቱ ጸዋማት፣ ሰባቱ ሚስጥራተ ቤተ-ክርስቲያን መሰል የሰባት ውክልናዎች የሆኑት በአጋጣሚ እንዳይመስልህ::

በመጽሐፈ ኢያሱ በምዕራፍ ስድስት ቁጥር አስራ አምስት ላይ ኢያሪኮን ለሰባት ጊዜ ዙሯት ከዚያም በሰባተኛው ቀን ሰባት ጊዜ ዙሯት ይላል:: በዘፍጥረት ምዕራፍ ስምንት ቁጥር ስድስት እንደተከተበው ደግሞ ኖህ ርግብ እየላከ ጠፍ መሬት መኖሩን ያጣራው በየሰባት ቀን ቆይታ ነበር:: ቅዱስ ዳዊትም በመዝሙር መቶ አስራ ስምንት ቁጥር መቶ ስድሳ አራት ላይ "ስለ ጽድቅህ ፍርድ በቀን ሰባት ጊዜ አመሰግንሃለሁ" ብሎ ምስጋናውን በሰባት ክፋፍሎ ያስቀምጣል::" አሉና አንድ ነገር እንደሚያስታውስ ሰው ዝም ብለው ቆዩ፤ ኋላም በዚያ የረጋ ልሳናቸው ሶፎኒያስን ማስተማራቸውን ቀጠሉ- "ልጄ፤ ሁሉም ነገር ምክንያት አለው:: በዚህች ምድር አጋጣሚ የሚባል ነገር የለም:: የድርሰቱ ምሥጢር ረቂቅ ቢሆንም ሁሉም ክስተት የትልሙ አካል ነው:: ለምሳሌ ሊቀ-ዜማ ቅዱስ ያሬድ ትሏ በሰባተኛዋ ሙከራዋ ስታልፍ፣ ሲሳካለት ማየቱና በዋናነት ሰባት የዝማሬ ምልክቶችን መቅረጹ የትልቅ ጸጋ ማሳያ እንጂ የአጋጣሚ ጉዳይ እንዳይመስልህ:: ለምን በአምስተኛው ወይም በስምንተኛው ሙከራ አላለፈችም? ብለህ መጠየቅ አለብህ:: ጠይቅ፣ መርምር፣ ታገስ ... ቆንጆ፣ አርኪ ምላሽን ታገኛለህ::" አሉና የደስታ

---
29 Cell

ሞገድ ለሶፎኒያስ ላኩለት፣ አንቴናዎቹን ሰድሮ ተቀበለ:: የሆነ ስሜት ውርር አደረገው:: እርሳቸው ቀጠሉ ... "ስለ ዝምታም ክርስትና አበክሮ ያስተምራል:: መጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ አስር ቁጥር አስራ ዘጠኝ ይህን ይላል:: "በቃል ብዛት ውስጥ ኃጢአት ሳይኖር አይቀርም፤ ከንፈሩን የሚገታ ግን አስተዋይ ነው::"

ይልቁንም የወሬ ትብታብ ያሳመመውን ትውልድ በመጽሐፈ ኢዮብ ምዕራፍ አስራ ሦስት፣ ቁጥር አምስት ላይ ሲወቅስ / "ምነው ዝም ብላችሁ ብትኖሩ! ይህ ጥበብ በሆነላችሁ ነበር::" ብሎ ያስቀምጣል::

በተለይ በተለይ ከነቢብ[30] ኃጢያት የነጻችው፡ በእሾኽ ተከባ የጸደቀችው፣ የሱፍ አበባዋ ቅድስት ድንግል ማርያም የትህትናና ዝምታ ተምሳሌት ናት:: በአጠቃላይ ህገ-ኃይማኖቱም ቅድስናን ከአርምሞ ጋር በጽኑ ያቆራኛል:: በብቸኝነት መገለል ደግሞ ለጻድቃን መለያ ነው::"[31] አሉት... ሶፎኒያስ እነዚህን ማስረጃዎች ሲያቀርቡለት ይበልጥ ወደ ውስጡ ዘልቆ ለመንዝ ብርታት አገኘ:: እውነትም አስገራሚ መንገድን ወደ ውስጡ እየሳበረ ነበር:: ዓይኑን እንደጨፈነ ያሳሰበውን ቀጣይ ጥያቄ ወደ ክቡዱ ሽማግሌ ሰደደ፤

"ስለዚህ አንድ ሰው የዚህ ጥበብ ተጠቃሚ ለመሆን ክርስቲያን መሆን አለበት ማለት ነው?"፤

እርሳቸውም መልሳቸውን በዝምታዎቻቸው እየሸነሸኑ ይለግሱት ቀጠሉ፤

"በፍጹም! ግብሩ እንዲያ አይደለም ፣ ጥሞና ማንኛውም ሰው ሊጠቀምበት የሚችል ጸጋ ነው:: የሰባት ቁጥር ልዩ ኃይል ደግሞ በሁሉም ኃይማኖቶችና ባህሎች ውስጥ ይገኛል:: ምክንያቱም እውነተኛ ጥበብና የበሰጸገ ህሊና/ የትኛውም አጥርና ድንበር ስለማይገድበው ነው::

ለምሳሌ በእስልምና ምልከታ አርምሞን ካየነው ከሶላትና ‹ተፈኩር› ጋር አብረን ልናብራራው እንችላለን:: የሶላት ሥነ-ሥርዓት በሙሉ በጽሞና መካሄድ ያለበት የአርምሞ መገለጫ ነው:: በተለይ ‹ተሸሁድ›

30 አንደበታዊ፡ አነብናቢ፤

31 ከእነዚህ መካከል ጣዝማና አንበጣ እየበላ ከበረኻ የከረመው መጥምቁ ዮሐንስ፣ ነቢዩ ዳንኤል የባቢሎንን ንጉሥ ህልም ለመፍታት ለብቻው ሱባኤ ገብቷል፣ አቡነ ተክለ ኃይማኖት የዱር ቅጠል እየበሉ ከዳሞት ተራራ ለብቻቸው ተቀምጠዋል፤

የተሰኘው በሶላት ውስጥ የመቀመጥ አካል የጽሞና ቅርፅ ጋር በእጅጉ ይመሳሰላል::

በሌላ በኩል ተፈኩር ማለት ከጥልቅ የጥሞናና የማሰብ ሂደት ጋር የተያያዘ የማስተንተን፣ የማገናዘብና የማውጠንጠን ተግባር ነው:: ይህም በቅዱስ ቁርዓን ሱራህ አል-ኢምራን ቁጥር መቶ ዘጠና አንድ እንደሰፈረው፤ "(እነርሱም) እነዚያ ቆመው፣ ተቀምጠውም፣ በጎኖቻቸው ተጋድመውም አላህን የሚያወሱ፡ በሰማያትና በምድር አፈጣጠርም የሚያስተነትኑ፡- «ጌታችን ሆይ! ይኸን በከንቱ አልፈጠርከውም፤ ጥራት ይገባህ፤ ከእሳትም ቅጣት ጠብቀን» የሚሉ ናቸው::" ብሎ ይጠቅሰዋል::

ልክ እንደ ክርስትናው እስልምናውም የድንግል ማርያምን የአርምሞ ምሳሌነት በምዕራፍ አስራ ዘጠኝ ቁጥር ሃያ ስድስት ሲጠቁም "ብይም፣ ጠጭም፣ ተደሰችም:: እኔ ለአልረሕማን ዝምታን ተስያለሁ፤ ዛሬም ሰውን በፍጹም አላነጋግርም» በይ::" ብሎ ይገልጠዋል:: በተጨማሪም ዝምታና ብቸኝነትን በተመለከተ የተጻፉ በርካታ ሐዲሶች አሉ:: ከመካከላቸው "ዝም ያለ ሰው ይድናል::" እና "በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ መልካም ይናገር አልያም ዝም ይበል::" የሚሉትን መጥቀስ እንችላለን::

ብቸኛ ሆኖ ከሰዎች መገለልን ስንመለከት በእስልምናው ‹ኢቲካፍ› ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ይህም ከሱባኤ ጋር የሚመሳሰል ከቤተሰብና ከድሎት ተነጥሎ በብቸኝነት፣ ራስን ወደ ፈጣሪ ለማቃረብ ጊዜ ተወስዶ የሚደረግ ልምምድ ነው:: በተለይ በረመዳን የጾም ወር የበለጠ ይዘወተራል:: ነቢዩ መሐመድ[32] የመጀመሪያውን ራዕይ ከመቀበላቸው በፊት በብቸኝነት ሂራ ተራራ ውስጥ ለወር ገደማ የመቆየታቸው ጉዳይም ተዘግቦ ያለ ነው:: ሌሎች ከአርምሞ ጋር አብረው የሚሄዱ ኢስላማዊ ጉዳዮች መካከል ተስቢህ፣ ዚክርና የእንጉርጉሮ መንዙማንም መጥቀስ እንችላለን::

ሰባት ቁጥርና እስልምናን ካነሳን ደግሞ ሌሎች አስገራሚ እውነታዎችን እናገኛለን:: በኢስላማዊ አስተምህሮ መሰረት ሰባት ሰማያትና ሰባት ምድራት በሰባት ወቅቶች ውስጥ ተፈጥረዋል፤ እንዲሁም ሰባት ዋነኛ ኃጢያቶች ከመኖራቸው ባሻገር የገነትና የገሐነም ቁጥሮች ሰባት ሰባት ናቸው፣ የገሀነም በሮችም ሰባት ናቸው:: በቅዱስ ቁርዓን ውስጥ ከአንድ ቁጥር ቀጥሎ በጣም በተደጋጋሚ የተጠቀሰው ቁጥር ሰባት ሲሆን

32 (ሰ.ዐ.ወ)

የመከፈቻው ምዕራፍ የሚሰኘውና በሁሉም ሰላት ላይ የሚቀራው ሱረቱል ፋቲሃም ሰባት አንቀጾች አሉት።

አንድ ሙስሊም ስሙ በተወለደ በሰባተኛው ቀን ይወጣለታል፤ ሐጅና ኡምራ ሲያደረግ ካዕባን ሰባት ጊዜ ይዞራል፤ ወደ ሰይጣን አዘቅት ሰባት ጠጠሮችን ይወረውራል። ከሰፋ መረዋህ ሰባት ጊዜ ይመላለሳል፣ {ይህም አጋር ህጻን ልጇ እስማኤልን እንደ ያዘች ውኃ ፍለጋ ከሰፋ መረዋህ ሰባት ጊዜ ከተመላለሰች በኋላ አምላክ የዘምዘም ጠበል እንዳፈለቀላት ማሳያ ነው።} በቅዱስ ቁርዓን በአያ አስራ ሦስት አንቀጽ አርባ ስድስት ላይ በተገለጠው መሰረት ደግሞ ነቢይ ዮሴፍ ወይም የሱፍ የንጉሡን ህልም እንዲፈታ ተጠይቆ ነበር። ህልሙም ሰባት ወፍራም ላሞች በሰባት ከሲታ ላሞች ሲዋጡ፡ ከዚያም ሰባት የእሸት መስኮችን የሚገልጥ ነበር። የጥጋብና የርሀብ ዓመታቶች መፈራረቅንም አመላካች እንደሆነ ገልጦ ሚስጥሩን ፈቶታል። እናም 7 ቁጥር በእስልምና ውስጥም ሚስጥራዊ ነች ብለን መደምደም እንችላለን።"

"ይገርማል!" አለ ዶ/ር ሶፎኒያስ፤ የዝምታ፣ የአርምሞና የሰባት ቁጥር ጉዳዮች ይሄን ያህል በሃይማኖቶች ውስጥ ትኩረት ያገኙ መሆናቸው እርግጥም አስገራሚ ሆኖ ነበር ያገኘው። ነገር ግን ከሃይማኖት ውጪ በሰው ልጆች ቀደምትም ሆነ ዘመነኛ ባህል ውስጥ ያለው ቦታ፤ ብሎም ከሁለቱ ሃይማኖቶች ውጪ ያለው ምልከታስ ምን ይመስል ይሆን?" እያለ ማውጠንጠን ያዘ፤ ይህም የውስጡ ጥያቄ ከእሱ አልፎ ለእርሳቸው መድረሱ አልቀረም ነበርና መልሱን ይመግቡት ጀመር።

"እርግጥ ነው አርምሞና ሰባት ቁጥር በሃይማኖቶች ውስጥ ሚስጥራዊ ትርጉማቸው በይበልጥ ጎልቶ ይታያል። ነገር ግን አርምሞ ወይም ሜዲቴሽን ወደር የለሽ ጥቅሞች እንዳሉት በሳይንሳዊ መንገዶችም ተረጋግጧል። ከእነዚህ ግኝቶች መካከል አርምሞ ወይም ‹ሜዲቴሽን› ለጤና ያለው መጠነ ሰፊ ጥቅም ይጠቀሳል። የአካላችንን የደም ዝውውር ማስተካከል፣ የአተነፋፈስ ሥርዓትን ማሻሻል፣ የስኳር መጠን ምጣኔ፣ የውፍረት መቆጣጣር፣ የምግብ መፈጨት ሂደትን ማስተናበር ወዘተ ጥቅሞች እንዳሉት በበርካታ ጥናቶች ተረጋግጧል።

በተለይ ለእርጉዝ ሴቶች፣ ለታዳጊ ወጣቶች፣ ጦርነትን መሰል ከባድ አደጋ ውስጥ ላለፉ ንጹሃን ዜጎችና ተጎጂ ወታደሮች፡ እንዲሁም በኑሮ ውጥረት ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች እጅግ በጣም ጠቃሚ እንደሆነ ተደርሶበታል።

ጥናቶች መሠረት አርምሞ ወይም ሜዲቴሽን ከእርግዝና ጋር ተያይዘው የሚመጡ የደም ግፊትና ስኳር መሰል ህመሞችን በጣም በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል:: ከአእምሮ ጤና አንጻር ካየነው ደግሞ ጥቅሙ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም:: ለከፍተኛ ድብርት፣ ለጭንቀት፣ ለእንቅልፍ ችግር፣ ለአመጋገብ ችግር፣ በራስ የመተማመን ችግር፣ አደጋን ተከትሎ ለሚመጣ የሥነ-ልቦና ቀውስና ሌሎችም እክሎች እጅግ ጠቃሚ መሆኑ በተግባር ተረጋግጧል:: ባይገርምህ ከግለሰብ ደረጃም ብቻ ሳይሆን አርምሞ ለብዙ ህዝቦች እንደ ሀገርና እንደ ዓለም ችግሮችን መፍቻ መንገድ እንደሆነ ተረጋግጧል:: ብዙ ሰዎች ተሰባስበው በአርምሞ እንዲመሰጡ በተደረገባቸው አካባቢዎች የወንጀልና ሥርዓት አልበኝነት ክስተቶች ከሃያ እስከ ሠላሳ በመቶ ቀንሰዋል::[33] እናም በርካታ ሀገራት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተውት በከፍተኛ ደረጃ እየሠሩበት ይገኛሉ:: እኔ ከነገርኩህ እጅግ በበለጠ ሁኔታ አርምሞ ላይ የተሰሩ በርካታ ዘመንኛ ጥናቶች ዘርፈ ብዙ ጥቅሙን አጽድቀዋል:: እኛ ኢትዮጵያውያን ግን እንደ ጥበቡ መነሻነታችን ሳይሆን በቅጡ እየተቀምንበት አይደለም::" አሉና በቁጭት ቢጤ ተብሰለሰሉ:: በረጅሙ ትንፋሽ ወሰዱናም ተረጋግተው ቀጠሉ...

"ለማንኛውም ወደ ሰባት ቁጥር ተመልሰን ዓለማቀፋዊ ማስረጃዎችን ብንመለከት ቁጥሩ በብዙ የዓለማችን ሃገራት ባህል ውስጥም እንደ እድለኛ ቁጥር እንደሚታይ እንረዳለን:: ለምሳሌ በእብራውያን ዘንድ ሰባት ፍጹም ቁጥር ነው ተብሎ ይታመናል:: ታዲያ እነዚህን ምስጢሮች በተቻላቸው መጠን ያጠኑና ያወቁ የውጭ ድርጅቶች ቀላል የሚባሉ አይደሉም:: ብዙ ካምፓኒዎችም ራሳቸውንና ስያሜያቸውን የእድል ምልክት ተደርጎ ከሚቆጠረው 7 ቁጥር ጋር አቆራኝተዋል:: <ቦይንግ 777፣ 7 አፕ፣ 7-11፣ ነምበር 7 በርገር...> ወዘተ መጥቀስ ይቻላል:: ከ5፣6 ቁጥርም ሆነ ከ8 ቁጥር ልቆ በኳስ ተጫዋቾች ዘንድም ይከበራል::

የዓለም አቀፍ ዘመናዊ የሙዚቃ ኖታዎች ቁጥርም ሰባት ነው:: እንዲህ እንዲህ እያልን ብዙ ዘመነኛ ማሳያዎችን ማንሳት እንችላለን::[34] ሌላው ቀርቶ ወረቀት እንኳን በሰው አቅም ከሰባት ጊዜ በላይ አይታጠፍም::[35]"

---

33 መሐሪሺ ዩኒቨርሲቲ በ2006 እአአ አሜሪካ ውስጥ 1800 ገደማ ሰዎች በአንድ ላይ ለሰላምና ፍቅር ሜዲቴት እንዲያደርጉ በመሰብሰብ ከተማዎች ላይ በሠራው ሰፊ ጥናት በዚያች ቅጽበት በሀገሪቱ የነበሩ ወንጀሎች በ30 በመቶ እንደቀነሱ አረጋግጧል። በሊባኖስ ጦርነት ጊዜ መሰል ጥናት ያደረጉ የእስራኤል ተመራማሪዎች ቀድመው social therapy ጠቀሜታ ከተናገሩት መሐል ይጠቀሳሉ።

34 RMP=-70 mv;

35 እርስዎም ይሞክሩት!

አሉና እንደ ማለዳ ጀንበር ፈገጉለት::

"ይሄን ሁሉ እንዴት ልብ ብዬው አላውቅም? ይገርማል!" አለ ሶፎኒያስ፤

"አዎ ግብሩ ብዙ ነው:: የኛ የቁጥሩ ሊቃውንት በዚህም ሳያበቁ በየአንዳንዱ የሰው ልጅ ውስጥ የሰባት እርከን አደረጃጀት እንደሚገኝ ያትታሉ:: ምስጥሩንም ከነቁልፉ ዕፊው አውርሰውናል:: ቁልፉን ሽተህ መጥተኻልና አንድ በአንድ በሰፊው አብራራልኻለሁ::

የአርምሞና የተመስጦ ነገሮች በባህላችን ውስጥ አንዳንዶች በማወቅ ሌሎች ደግሞ ባለማወቅ ሲተገብሩት ኖረዋል:: ከቀላሉ ብጀምርልህ የኢትዮጵያ እናቶች ምግብ ሲያዘጋጁ ልብ ብለህ ብትመለከታቸው በምግብ ዝግጅቱ ላይ በትኩረት ሙሉ ለሙሉ መሰጠታቸውን ታስተውላለኽ፣ ምግቡን የሚያጣፍጠው ምግቡ የተዘጋጀበት ግብዓት ብቻ ሳይሆን የእናቶቻችን ሽርፍራፊ የመንፈስ ቅመም መሆኑንም ትረዳለህ:: {ምግብ ብቻ ሳይሆን ህይወትን ነው ከልባቸው እየኖሩ የሚያበስሉት::}

የዝምታን ታላቅነት ደግሞ ከአባባልና ምሳሌያዊ አነጋገራችን ጀምሮ እስከ ሙዚቃዎቻችን ድረስ ተካቶ እናገኘዋለን:: ለምሳሌ "ዝምታ ወርቅ ነው::" ብለው አባቶቻችን የዝምታን ዋጋ በአጭር አረፍተ ነገር ከፍ አድርገው አውርሰውናል፤ ወርቅ ዝቅ ብሎ ከአፈር ውስጥ እንደሚገኝ ሁሉ ዝምታም ከትሁት ልቦና ትነሳለች::

ራቅ ብሎ መገለልና ከሰው ተነጥሎ መመሰጥን በተመለከተ በየሃይማኖቶቻችን የኦርቶዶክስ ተዋህዶ መነኮሳትና ባህታዊዎች፣ የእስልምና ቃዲ፣ ሙራድና ወልዮች፣ የፕሮቴስታንት ጾም ጸሎት ቆይታ አድራጊ አገልጋዮች.. የመሳሰሉትን ማንሳት እንችላለን:: በባህሎቻችን ውስጥም እንደ ገዳ መንፈሳዊ አባት "ቃሉዎች[36]" ያሉ ከማህብረሰቡ ተገልለው በዋርካው ኦዳ ሥር በጽሞና ይቆያሉ:: ሃድያዎች የእርቅ መፍቻ የመጨረሻ አማራጫቸው ጉዳዩን ከሰው ተገልለው፡ በአርምሞ ወደ ሚቀመጡ ‹ሂራጋኖዎች› መውሰድ ነው፤ ‹ሂርጋኖ ቤይ መሌ›... ሂራጋኖ ጋር ሂዱ ብለውም ዳኞች ያዛሉ:: የጉራጌውን፡ በጥሞና የተቀመጠ፡ አንገት ደፊ የጀካ ዛፍ ጥሞናስ እንዴት ይረሳል? እንዲህ እንዲህ እያልን በርካታ ሀገር በቀል ባህሎችን ለጥሞና ማሳያነት ማንሳት እንችላለን::

36 አንዳንድ ኤሺያዎች አሁንም ጥቁር ሰውን "ካሉ" እያሉ ይጠራሉ::

/እንደ ጥምና ሁሉ የሰባትነት ምሥጢር ደግሞ በኛ ቀደምት፡ ጥንታዊ ስልጣኔ ውስጥም ትልቅ ቦታ የነበረው ነው። ሰባተኛው የአዳም ትውልድ ከሆነው ከቅዱስ ሄኖክ አብራክ የፈለቅነው የኢትዮጵያ ልጆች በእርግጥም ከቁጥሩ ጋር ቁርኝታችን ለየት ያለ ነው። ፊደሎቻችንን እንኳን በሰባት ቁጥር ከሀ እስከ ሆ ይደረደራሉ። አንዳንድ ጎሳዎቻችን እስካሁንም በሰባት ቤት ህብረትነታቸው ይጠራሉ። ለማሳያ ሰባት ቤት ጉራጌና ሰባት ቤት አገውን ማንሳት ይቻላል። ተጋሩዎችም በሰባት ቤት ይጠሩ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያትታሉ። አሁን ያሉ የባህል አወቃቀሮችንም ብናስተውል ለምሳሌ ሸካዎች ሰባት እርከን ሥርዓቶች አሏቸው፣ ደራሼ ማኅብረሰብ ሰባት ንዑስ አካላት አሉት፣ ከአምስቱ ዋነኛ የገዳ ሥርዓቶች አንዱም በሰባት እርከን የተደራጀ ነው። ባለ 777 የከንባታ ደረጃ፣ የሀምበርቾ አናት ላይ የተገነባው በአጋጣሚ እንዳይመስልህ![37]

እኛ ገና ከጥንቱም በነበረን ግዙፍ ግዛት ወቅት ያስተዳደርናቸው እንደ አሴናቱ ግብጽና የህንደኬዎቹ ህንድ ውስጥም እነዚህን የአርምሞና የሰባት ቁጥር ሚስጥራት እናገኛቸዋለን። የጥንታዊ የግብጽና ሱዳን ልዑሎች አሁን ‹ሜዲቴሽን› እና ‹ዮጋ› በሚባሉት አቋቋሞችና አቀማመጦች ላይ ሆነው የተቀረጹ ሃውልቶቻቸው፡ ፒራሚዶች ውስጥ ተቀርጸው ይገኛሉ። የአርምሞ መገለጫ የሆነው መቁጠሪያም እጃቸው ላይ ተንጠልጥሎ ይታያል። አሁን ላይ በተገኙ የሱባ መዛግብት መሰረት ያሁኒቷን ግብጽ የገዙ ጥንታዊ የኩሽ ነገስታት ነበሩ። በጣም የሚገርመው እነዚህ ጥንታውያን ልክ እንደ ክርስትናና እስልምና የመንግሥተ-ሰማይ መንገዶች ሰባት ናቸው ብለው ያምኑ ነበር። የሰባቱ ሰማያት ላሞችና ሰባት የምድር ስውር ዓለሞችም አሉ ብለው ይቀበሉ ነበር። ሰባት ዋና ዋና ኃጢያቶች መኖራቸውን ከማመናቸው ባሻገር በአርምሞ ውስጥ ሰባት የሱል ክብ ውስጣዊ ‹ፕላኔቶች› በኩል ማለፍ እንዳለብንም በኃይማኖት ድርሳኖቻቸው ላይ ከትበው አስቀርተዋል። ከአቅጣጫ አንጻር ግራ፣ ቀኝ፣ ፊት፣ ኋላ፣ ላይና ታች ብለው ስድስቱን ይቆጥሩና ሰባተኛው ማዕከላዊነት ነው ይላሉ።

ወደ ምስራቁ የዓለም ክፍል ሄደን ህንድን ብንመለከት ምናልባትም በአርምሞ ወይም ሜዲቴሽን ረገድ ለዓለም ምሳሌ የሚሆኑ ጉሩዎችንና ዮጊዎችን[38] ያበረከተች ሀገር ሆና እናገኛታለን። አርምሞን ዋነኛው የአምልኮ አካል አድርገው የሚያስተምሩት የሂንዱዝምና ቡዲዝም

37 ቀዳማው ኃይለ ስላሴም ሰባ ደረጃን ሲያስገነቡ ይሄንን ጥበብ አስበው ይሆን?

38 የሂንዱዝም እምነት መነኮሳትና የአርምሞ መምህራን፤

ሃይማኖቶች ከምሥራቅ አልፈው ለብዙ ምዕራባውያን ራስን የማወቅን መንገድ አስተምረዋል:: ለምሳሌ ከቅዱሳን መጽሐፍቶቻቸው አንዱ በሆነው ባሃጋቫድ ጊታ ምዕራፍ አስራ ሰባት ቁጥር ስድስት ላይ.. "ዝምታ፣ እፎይታ፣ መተናነስ፣ ወደ ውስጥ መሳብ፣ ራስን መቆጣጠር እና ብጹእነት የአንድ ሰው እውነተኛ የአእምሮ ምሦሦዎች ናቸው::" ብሎ አስቀምጦታል:: ‹ቄና ኡፓሻንዲ› በተሰኘው መጽሐፋቸው ውስጥ ብ-ራህማ ወደ ተሰኘው የምህረት አምላክ ለመቃረብ ልክ እንደ ግዑዝ እቃ ሳይናገሩ ሳይጋገሩ መመሰጥ እንደሚያስፈልግ ይጠቅሳሉ::[39] ክሪሽናና ራማ-ሃይ[40] የተባሉ ጥንታዊ ጥቋቁር የኩሽ ቅዱሳንና ንጉሶች ያስተማሯቸውን የጽሞና መንገድ በሚገባ በመጠበቅ አሁን ላለው የዓለም ትውልድ አውርሰዋል ማለት ይቻላል:: እናም ጥልቅ አርምሞ ውስጥ ያሉ መነኮሳትን ህንድ፣ ቻይና፣ ታይላንድ /ቲቤትና ሂማሊያ ተራራዎች ውስጥ ማግኘት የተለመደ ነው::

{ስሪ ስሪ ራቪ ሻንከር፣ ዳሊ ለማ፣ ሳድ ጉሩን የመሳሰሉ በዓለም አቀፍ ደረጃ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ተከታዮች ያሏቸውን የአርምሞ ተማሪና መምህራንን መጥቀስ ይቻላል::}

ለጥቆም ሰባት ቁጥርን ከሂንዱዝም ኃይማኖት አንጻር ካየነው አሁንም አስገራሚ እውነታዎችን እናገኛለን:: በሳንስክሪታቸው[41] መሰረት ሰባት ቁጥርን ሰፓታ ብለው የሚጠሩት ሲሆን የሙዚቃ ኖታቸውም ሰባት ነው፤ ሰባቱን ዋና ዋና ቅዱሳኖቻቸውን፣ ወይም ‹ሳፓታ ሪሺዎችን› በሰባት የጠፈር ከዋክብት ይመስላሉ፤ ጋብቻ ሲፈጽሙ ሰባት ጊዜ እሳትን ይዞራሉ፣ ቃል ኪዳን በሰባት ይጸናል ብለው ይስማማሉ፤ የሰው ልጅ ከሞተ በኋላ በሰባት አይነት መልኩ ዳግም ይገለጣል ብለውም ያምናሉ::

"ከምንም በላይ አንተ እንድታተኩርበት የምፈልገው ደግሞ የሰው ልጅ ሰባት ቻክራዎች እንዳሉት ያስቀመጡትን ጥበብ ነው::" አሉና ሽማግሌው ሰው ጠንከር ያለ አንድ ሰበዝ ኃይል ወደ ሶፎኒያስ ላኩ፤ ነቃ ብሎ ያዳምጣቸው ጀመር:: ... "ሰባቱ ቻክራሶች ማለት የሰው ልጅ የተዋቀረባቸው ሰባት የኃይል፣ ባህሪና ግብር እርከኖች ናቸው:: ሀሳቡ በደንብ እንዲገባህ ቻክራስ የሚለውን ቸክ-ራስ ብለህ አስታውሰው፣ ይህም የራስ - ችካል ወይም ሰባት ደረጃዎች ያሉት የማይነቃነቅ የውስጥ

39 kena upashandi(1.9).[6]

40 ሁለቱም ጥቁር ነበሩ::

41 ከጥንት መግባቢያዎች መካከል አንዱ፤

*ምሶሶ አድርገህ አስበው:: ችካሉ ከአከርካሪና ከህብለ-ሰረሰር ጋር የተያያዘ ነው:: በተጨማሪም ከ‹ፔናይል› ጀምረን ‹ታላመስ›፣ ‹ፒቲዩታሪ›፣ ‹ሃይፖታላመስ›፣ ‹ታይሮይድ›፣ ‹አድሬናል› እስከ ‹ጎናድስ› ብንቆጥር ሰባቱን ዋና ዋና የሰው ልጅ ሆርሞን አመንጪ እጢዎች መደርደር እንችላለን::*

*በሥነ-ልቦናው ዓለምም እንደምታውቀው ህጻን ልጅ በተለይ እስከ ሰባት ዓመቱ ባለው ጊዜ ውስጥ ስብእናው በዋናነት እንደሚገነባ ይጠቀማል::*[42] *በአብይ ዘርፍም ሰባት የሰው ልጅ አይነቶች እና ሰባት የስሜት ደረጃዎች እንዳሉ የዘርፉ ምሁራን ይስማማሉ:: እናም ሰባት ቁጥር ከሰው ልጅ አፈጣጠርና የንቃተ ህሊና መንገድ ጋር እጅጉን የተቆራኘ ነው:: ለዚህም ይመስላል ቀደምት አባቶቻችን ሰው ን ሲጠሩ ሰብእ እያሉ ከ ሳብእ ወይም ሰባት ቁጥር ጋር በሚመሳሰል ስም የሚጠሩት:: አሁንም ሰብእ የሚለው ቃል በግእዝኛ፣ በትግረኛ፣ በጉራግኛ፣ ስልጥኛ ወዘተ… ውስጥ ሰው የሚለውን ትርጓሜ ይዞ ታገኘዋለህ:: አሁንም አማርኛ ውስጥ ህብረተ-ሰብ፣ ማህብረ-ሰብ፣ ግለ-ሰብ፤ ብሔረ -ሰብ እያልን እንደ ቅጥያ እየተቀምነው እንገኛለን:: በኦሮምኛ ደግሞ ሰብ ማለት አንድ ቦታ ላይ የሚኖር የሰዎች ስብስብ ወይም ብሔር ተብሎ ይተረጎማል::*

*እናም ይሄንን ሁሉ አገናዝበህ፣ የሰው ልጅ በሰባት ግልጽና ህቡዕ እርከኖች ላይ እንደተፈጠረ ማወቅ አለብህ:: እርምሞ ለማድረግ ስታቅድም በሰባቱ ውስጣዊ እርከኖች ማለፍን ዋነኛው ግብህ ብታደርግ ስኬታማ ትሆናለህ:: ይህም ከአንደኛው የቆሰለ ዝግ ስሜት ወደ ሰባተኛው የበለፀገ ክፍት ህሊና፣ ሰውን ከመጥላት ጠላትን እስከ መውደድ፣ ከታች ተገንጣይነት እስከ ሰባተኛው ማዕከላዊነት፣ ከስሜት ህዋሳት እስከ መዋሃድ ፀጋ፣ ከቁጥራዊ የስሌት ስሜት እስከ ንቁ የፍቅር ሀሴት፣ ከእኔነት እስከ ሁለንተናዊነት ድረስ ማደግ፣ ከእንቁልጢ እስከ ፒቱታሪና ፔናይል፤ ከደመ ነፍስ እስከ ቅዱስ መንፈስ መነጠቅ ድረስ ያደርሳል:: ዘላለማዊነትንም ያጎናጽፍኻል!*

*እንግዲህ ለማጠቃለል ያኽል፡ ይሄ እስካሁን የነገርኩህ በሙሉ ያስፈለገው የሰባት እርከን ጉዞኽን ከመጀመርህ በፊት ውስጥህ እንዲያምንበት ነው::*

---

42 Hypnotic period ሊባል የሚችል የህጻንነት መሠረት መጣያ ጊዜ የመጀመሪያዎቹ አመታት ናቸው። በዚህ ጊዜ ህጻን በተለይም እናቱን ከጎኑ ባያጣት ፈሪ፣ ግራ የሚጋባ አልያም በራሱ የማይተማመን፣ ቁጡ፣ የተረበሸ ልጅ ከማሳደግ ትዳጋላችሁ። ይህን የተረዱ እንደ ዴኒማርክ ያሉ ሃገራት ሴት ልጅ ስትወልድ እስከ ሦስት ዓመት ድረስ የሚደርስ የሥራ እረፍት ከመሥጠት አልፎ ደሞዟ እንዲከፈላት ያደርጋሉ። ዴኒማርክ ወንጀል ከማነሱ የተነሳ እሥር ቤት የሚዘጋባት አንዷ ሀገር ናት።

አሁንም ጥበቡ እኛ ከራሳችን የፈጠርነው ፍልስፍና ሳይሆን ቅዱሱ አምላካችን በ፯/7 ቁጥር ላይ የገለጠው ጥንታዊ ኃይል እንደሆነ እንድትረዳ ነው:: "በዙፋኑና በአራቱ እንስሶች መካከልም በሽማግሌዎችም መካከል እንደ ታረደ በግ ቆሞ አየሁኝ፥ ሰባትም ቀንዶችና ሰባት አይኖች ነበሩት፤ እነርሱም ወደ ምድር የተላኩ ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው::" (ዮሐንስ ራእይ፤ 5:6) ተብሎ እንደተጻፈው «7» ቁጥር የፍጥረት ህግና ሚስጥራት ያዘለ ድብቅ ትንግርት አለው:: ለዚህም ቅድም እንዳልኩህ እጅግ ግዙፍ የሆኑ ሰባት ሰማያትን፣ ሰባት ዓለማትን በሰባት ወቅቶች (ቀኖች) ስብኃት ለአብ በመፍጠሩ ምሥጢር 7ተኛው ቀን ‹‹ሰንበት›› መከበሩ ማሳያ ነው:: እግዚአብሔር በራሱ ምሳሌ መሰረት በሰባተኛው ሳብዕ ፊደል መዋቅር አዋህዶ የተፈጠረውን የሰው ልጅም ያመለክታል::" አሉና አንድ ጥቅል ፈተው ምናቡ ፊት ለፊት ዘረጉት:: ሊቃውንት አባቶቻችን ለትውልድ ያወረሱት፣ በአርምሞ የገለጡት የሰው ልጅን እግረ-ህሊና የሚያበረቱ፣ ንቃተ-ናላውን የሚያንጹ ሰባቱ የአርምሞ እርከኖች ናቸው:: ዶ/ር ሶፎኒያስ ምስሉንና ከጎኑ ያሉትን ጽሑፎች ጊዜ ወስዶ አጠናቸው::

ይህም ምስለ ሰው/ቶ ከላይ ካለው ራስ ፣ 7ባተኛው ፍቅር ወለድ፣ ከፈጣሪያችን የመገናኛ በር የሆነው ንቁ ህሊናችን ጀምሮ ወደ ታች ሲሰፋ፣

6ኛው የማይለዋወጥ ፅኑ ሃሳብ ያዘለ የማንነታችን መለያ፡ እውን የሆነው መንፈሳዊ ሰላማዊ ብርሃን፣

5ኛው በአስተዋይነት ሰፊ ራእይ ማየት መቻልና በነፃፍቃድ በእጅ የሚሠራ ሥነ-ምግባር፣

4ኛው ተመስጦን ተጠቅመን በማሰላሰል የምናልመውን የምንሆንበት ግባችን፤

3ኛው በማስታወስና በጥናት አእምሯችንን ተጠቅመን የምናገኘው ማዕረግና መልክ፤

2ኛው ሰውኛ ስማችን ተጠቅመን በአንደበተ ርቱዕ ንግግር፣ ዜማና ቋንቋ መክሊታችን (ምላስ) እስከ ከርስ (ሆድ)

የሥረኛው 1ኛ ደረጃ ላይ ያለው ስሜትና ጥርጣሬ ወለድ የጭንቅላት ቅዠት የሚተርከው ተረት ተረታችን ድረስ ያሉትን የሰውነታችንን መሰረቶች የሚገልፅ ነው:: {ከብልቶቸ ፣ ከእግር ሥር ወደ ምድር የሚጣል ሥጋዊ

ፍላጎትና ተረፈ ምርት ድረስ ያለው፤ ከአውሬ በዘረ-መል የምንጋራቸው ተፈጥሮዎች ናቸው።}

ሶፎኒያስ አንብቦ እንደ ጨረሰ ሲያውቁ ሸማግሌው ሰው የመዝጊያ ጥቅሳቸውን አስከተሉ።

"ልጅ ሶፎኒያስ ዝምታን ከሰበኩ ጠቢባን አንዱ የሆነው ባሃውላህ በአንድ ጽሑፉ ምን ይላል መሰለህ፤

"*ትቢያ ከለበሰው ጎጆ ወርዶ ወደ ምድረ-ገነት የሚጓዘው መንገደኛ የሚያልፍባቸው ምዕራፎች ሰባት ናቸው። አንዳንዶቹ ‹‹ሰባት ሸለቆዎች›› ሲሏቸው አንዳንዶቹ ደግሞ ‹‹ሰባት ከተሞች›› ይሏቸዋል። መንገደኛው ከእርሱነቱ ተላቆ እነዚያን ምዕራፎች እስካልተሻገረ ድረስ ወደ ቅርበትና ውህደት ውቂያኖስ ከቶ ሊደርስ አይችልም፤ ወደር የማይገኝለትን መንፈሳዊ ወይን ጠጅም አይቀምስም።"* ...ብሎ አስቀምጦታል። እናም በቀጣዮቹ ሰባት ቀናት እነዚህ ሸለቆዎች አብረን እናልፋለን፤ ተራሮቹን አብረን እንሻገራለን ማለት ነው። እነሆ ባለ ሰባት መዳረሻው ውስጣዊው ጉዞኽ ዛሬ ይጀምራል... በርታ!" ብለውት ከተቀመጡበት ስፍረታዊ ይዞታ ለቀው፡ በዓይን ጥቅሻ ከቦታው ተሰወሩ።

{ምስጢሩ ብዙ ነው። የምንገልጸው ወርጠን ነው።}

# ምዕራፍ ስምንት

## የጋ፡ የድ፡ ዋልያ

ሜሮን በፍቅር ውስጧ ሲማስን የኖረችለትን ልጅ - ለይኩንን ስታቅፍ ውስጧ በሐሴት ተምነሸነሸ። ያልተከረከመ ጸጉሩ፣ ያልተቆረጠ ጥፍሩ፣ የማያውድ ጠረኑ ደንታም ሳይሰጣት ጥብቅ አድርጋ ዐቀፈችው - ዐቀፋት ላያቸው ሰው የሚላቀቁ፣ የሚለያዩ አይመስሉም ነበር። አንድ አካል አንድ አምሳል ሆኑ። በገረጣው ደረቱ ላይ ሆና እንዴት እንዲህ ሊመቻት እንደቻለ አንድዬ ብቻ ነው የሚየውቀው። {የፍቅር ፍላሚንጎዎች እንዴት የጥንድ ዳንስን እንደተማሩ? እንዴትስ አብረው ውኃ ላይ መሮጥ እንደቻሉ? እሱ ብቻ ነው የሚያውቀው።}

ሜሮን በለይኩን ደረት ላይ ልክ እናቱ ላይ እንደተመቻቸ ጨቅላ ህጻን ልጥፍ ብላ ሐሴት አደረገች። እዚህ ደረጃ ላይ የሚደርስ ደስታ እንዳለ ያወቀችው ራሱ ዛሬ ነው። ፍቅር ግን ምን አይነት ትንግርት ነው? ስትል ከራሷ ጋር ተጠያየቀች። እዚያው በሰመመን እንደተንጋለለች ስለ ፍቅር ማሰብ ጀመረች።

በፍቅር ውስጥ እንዲህ ሰምጬ እዋኛለሁ ብላ በፍጹም አስባ አታውቅም። ስትሰምጥ ግን ብዙ ነገሮች ድሮ ከምታልመው በላይ ሆነው ነው ያገኘቻቸው። ይህቺ አይነት ደስተኛና ሰላማዊት ሜሮን መኖሯን ራሱ አታውቅም ነበር። {ለካስ እውነተኛ ፍቅርን ስታገኝ አጋርህን ሳይሆን ራስህን ነው የምታገኝ። ተደብቆብህ የኖረውን ብፁእ ማንነት ነው በፍቅር ጠምደህ፣ ጎትተኽ የምታወጣው። እውነተኛ አፍቃሪ ሐዘንህን በደስታ፣ ድካምህን በብርታት የሚቀይር የአንተ አካልና ምሳሌ ነው። እኛ በፍቅር አምሳያ ተቀርጸን እንደተፈጠርነው አብሮነታችንም ፍቅር ይወልዳል። ህይወት ያለው ልጅ፡ ፍሬም ያፈራል።}

ሰው የእናት ፍቅር፣ የሃገር ፍቅር፣ የጓደኛ ፍቅር እያለ ሲከፍል ሰምታለች። ፍቅር ግን አንድ እንጂ ብዙ አይነት ክፍል እንዳለው መቀበል ከብዷታል። ምክንያቱም ፍቅር ውክልናው ይለይ እንጂ መነሻው አንድ ሲሆን - እሱም ፈጣሪ ነው። ፍቅር እግዚአብሔር ነው። ወዱድ ነው። እናም በእናትና ልጅ መካከል ይህ ኃያል - ፍቅር ይገለጣል፣ በጓደኛ መካከል ይህ ኃያል - ፍቅር ይገለጣል፣ በወንድና በሴት መካከል ይህ ኃይል - ፍቅር ይገለጣል፣ በሀገርና በዜጋዋ መካከል... ይህ የፍቅር ንጹህ ኃይል ብቅ ጥልቅ እያለ ልብን ያሞቃል።

{ፍቅርና መገለጫዎቹ ልክ በሶኬት በኩል እንደሚመጣ ኤሌክትሪክና አሌክትሮኒክሶች ያለ ተምሳሌትነት አላቸው። ከመብራት ኃይል አመንጪ ግድቦች አንድ የኤሌክትሪክ ኃይል ይበተናል። ይኼው ኃይል በረጃጅም ስልክ እንጨቶች በኩል አልፎ በየቤቱ ይገባል። በሶኬቶቻችን በኩልም ወደ መሳሪያዎቻችን ይፈሳል። ሶኬቱ ላይ ፍሪጅ ከሰካንበት ኃይሉ ቅዝቃዜ ሆኖ ይገለጣል፣ ስቶቭ ከሳክንበት ኃይሉ ሙቀት ሆኖ ይገለጣል፣ ቴሌቪዥን ከሳከንበት ምስልና ድምጽ ሆኖ ይገለጣል፣ ስልካችንን ከሰካንበት ባትሪውን ይሞላልናል። እንዲሁ እያለ አንድ አይነት የኤሌክትሪክ ፍሰት፣ ቮልቴጅና ከረንት የተለያየ መልክ ይዞ ይገለጣል።

ፍቅርም እንዲሁ ነው፤ ኃይሉና ምንጩ አንድ ፈጣሪ ቢሆንም በብዙ መልኩ ይገለጣል። ይህ ኃይል ግን ንጹህ፣ ምቾቱን የማያስቀድም፣ ከራሱ በላይ የሌሎችን ደስታ የሚያስበልጥ፣ ጠቢብና አዛኝ የሆነ ፍጹም መንፈስ ነው። ለዚህም ነው ፍቅር የሚለው ቃል ከመዋደድ፣ ከመላመድ፣ ከመማረክ፣ ከመከጃጀልና አብሮ ከመኖርም በላይ የገዘፈ፣ የረቀቀ ነው የሚባለው። ሌላው ቀርቶ በመለያየት ውስጥ እንኳን ፍቅር ሊኖር ይችላል።}

ይህ ተጻፈ እንጂ ብዙ ሐሳቦች በአእምሮዋ እየመጡ አልፈዋል። ሜሮን በዚህ ሃሳብ ሰረገላ ስትጋልብ ቆይታ እንቅልፍ ሸለብ አደረጋት። ይኼ ዘማም እንቅልፍ ባያልቅ ምንኛ ደስ ባላት!

⌘ ⌘ ⌘

"እና ከዚህች ሜሮን ካልካት መልካም ልጅ ጋር የነበራችሁ ነገር በምን ተጠናቀቀ?" አሉ ደጉ አረጋዊው፤ ከለይኩን አጠገብ በጥንቃቄ እየተቀመጡ። ለይኩን እኚህ ደግ አርሶና አርብቶ አደር ዘንድ ከተሸሸገ አምስት ቀናት አለፉት። በቂ እረፍትና ምግብ በማግኘቱ ትንሽ ነፍሱ መለስ ቢልም ቁስሉ

ግን ይበልጥ እያመረቀዘና እያበጠ መጥቷል። እንደ ልቡ ለመንቀሳቀስም ስላገደው ሰፊውን ጊዜ ከአልጋው ተኝቶ ነበር የሚያሳልፈው።

ግን ብዙም አልደበረውም። ያቺ ትንሽዬ ልጅ እየመጣች ታጫውተዋለች። እርሳቸውም በየመሐሉ እንዲህ እየመጡ ታሪኩን ይተርክላቸዋል። እናም ዛሬም ሰዓታቸውን ጠብቀው መጥተው ከጎኑ ተቀመጡ። ከሜሮን ጋር ቀጥሎ ያለውን ታሪክ እንዲነግራቸውም ጠየቁት። ለይኩንም ከህመሙ ጋር እየታገለ የመጨረሻዎቹን የእድሜ ክፍሎች አጫወታቸው።

*ከሜሮን ጋር ያሳለፋቸውን እነዚያን ፍጹም ንጹህ፣ ሰላማዊና በፍቅር የተሞሉ ሳምንታት ሲያወራላቸው ከህመሙ ሙሉ ለሙሉ የተፈወሰ ይመስል ፊቱ ፍክት ብሎ ነበር። ቀስ በቀስ ግን ፊቱ እየዳመነ ሄዶ መናገር የማይችል ደረጃ ደረሰ። ሽማግሌው ሰው እንደልቡ መናገር እንደተሳነው ስለተረዱ ታግሰው ይጠብቁት ገቡ።*

⌘ ⌘ ⌘

*ኤረር ተራራ ግርጌ ሥር፣*

ዶ/ር ሶፎኒያስ የሰባት ቀን የቤት ሥራውን በተቀበለ በመጀመሪያው ቀን ምሽት ላይ አንድ ጅብ እያደባ እሱ ወዳለበት ዋሻ ቀረበ። ይሄው የተራበ ጅብ እያነፈነፈ ወደ ተቀመጠበት ተጠጋ። ዓይኑን ጨፍኖ በተመስጦ ውስጥ የሚዋልለው ሶፎኒያስ የተጋረጠበትን አደጋ ሳይረዳ በምናብ መንደልደሉን ቀጥሏል። ቀድሞም ከርሡ ያልጠረቃው ጅብ የሰው ሥጋና ደም ሲሸተው ይበልጥ ርሐቡ አገረሸበት። ለሀጩን እያዝረበረበ ሰተት ብሎ ገባ። ስንቱን ምስኪን የዘነጠለበትን ጥርሶቹን አሹሎ ወደ ሶፎኒያስ ሲመዘዝ ትንፋሹ ገረፈውና ሶፎኒያስ ዓይኖቹን ገለጠ።

ከፊቱ በለኮሰው ኩራዝ ነበልባል፡ በጨረቃይቱ የብርሃን ነፀብራቅ ታግዞ ከፊቱ የተሰየመውን አስፈሪ አውሬ ተመለከተ። የሾለ ጥርስ፣ የሚያለከልክ ምላስ፣ የፈጠጡ ዓይኖች - የሞትን ጨረር የሚረጩ ሥጋ በል ፍላፃዎች። ለማመን ቢከብደውም አስፈሪውን ትርጓሜ ግን አእምሮው ነገረው - "ሶፎኒያስ በጅብ ልትበላ ከጫፍ ደርሰሃል" አለው። ጊዜ የለውም በድንጋጤ ፍንጥር ብሎ ተነሳ። ጅቡም ምንም ጊዜ ሳያባክን ሮጥ ብሎ ተጠጋው። ሶፎኒያስ እየሸሸ ወደ አንድ ጥግ ላይ ተለጠፈ። ማምለጫ በሌለው ሁኔታ አጣብቂኝ ውስጥ ነበር ያለው። በማያውቀው መንደር፣ ረዳት በሌለበት፣ በጨለማ ድባብ ውስጥ በጅብ ተበልቶ ሊሞት እንደሆነ ሲያስበው ነፍሱ

ተጨነቀች።

አያ ጅቦ ሶፎኒያስ ላይ ሊከመር ዘለለ። በቅጽበት ከየት እንደመጣች ያላወቃት ዋልያ በድንገት ከሶፎኒያስ ፊት ቆመች። ሰፍ ብሎ የመጣው ጅብ አንገት ውስጥ የዋልያዋ ቆልማማ ቀንድ ሲሰነግ ከዓይን ይፈጥን ነበር። ጅቡ ከአንገቱ ደም እየተንዠረረ ትንሽ ተንገዳገደና ከመሬት ተዘረረ። ሶፎኒያስ እየሆነ ያለው ነገር በሙሉ ቅዠት እየመሰለው አንዴ ዋልያዋን አንዴ የሞተውን ጅብ ሲያይ ቆየ።

ሶፎኒያስ ጅቡ የፈጠረበት ፍርሃት ሲቀልለት የሰሜን ተራራዋ ዋልያ በዚህ ሰዓት እንዴት እዚህ ተገኘች ብሎ ተወዛገበ። ወደ ቀልቡ ተመልሶ ሳይጨርስ አሥር ገደማ የሚሆኑ ጅቦች ያሉበት የጅብ መንጋ እሱ ወዳለበት እየገሰገሱ ሲመጡ ተመለከተ። ቅድም የመከተችለት ዋልያም ወደ እሱ ተጠግታ መንጋውን የፈራች መሰለች። ያኔ ነበር አንድ ቀይ የ‹ማርሻል አርት ጋውን› የለበሰ ሰው ከዋሻው መግቢያ ላይ የተከሰተው። ከየት እንደመጣ ማንም መናገር አይችልም። ብቻ ሁለት እግሮቹን ግራና ቀኝ አራርቆ ከፍቶ፣ በግራ እጁ ረጅም በትር ይዞ፤ ቀኝ እጁን ደግሞ እንደ ሻሞላ ሞርዶ ከዋሻው መግቢያ ላይ ቆሞ አየው። ጅቦቹም አቅጣጫቸውን ቀይረው ወደ ሰውዬው ገሰገሱ። ልክ ከአጠገቡ እንደደረሱ ሰውዬው ሽቅብ ዘሎ፡ ወደ ላይ ተንሳፈፈና በያዘው በትር ተመርኩዞ፡ አስማታዊ በሚመስል ሚዛን ቀጥ ብሎ ቆመ። ከዚያም በመግነጢሳዊ ፍጥነት የጅቦቹን ጭንቅላቶች እየረገጠ፡ ከአንዱ ወደ አንዱ መስፈንጠር ያዘ። ወደኋላ ተከርብቶ ከመሬት ቆመና በልዩ ጥበብ እንደ እንዝርት እየሾረ ጅቦቹን በክርንና ተረከዙ ነራረታቸው። ፍጥነትና ኃይሉን ላየ በሰው አካል የተገለጠ አንበሳ ይመስል ነበር። ለዓይን የፈጠነው ሰው ጅቦቹን ዶግ አመድ ለማድረግ ጊዜ አልፈጀበትም ነበር። ያላሰቡት ዱብዳ የገጠማቸው ጅቦችም እያነከሱም፣ እየዳሁም፣ እየሮጡም ከአካባቢው በፍጥነት ሸሹ።

ሰውዬው ትግሉን ሲፈጣጥም መዳፎቹን አገጣጥሞ ራሱን አረጋጋና በረጅሙ ተነፈሰ። ወደ ሶፎኒያስ ዞሮም በአንክሮ ከተመለከተው በኋላ ሙሉ ቀይ ልብሱን እያስተካከለ ወደ እሱ መጣ። ከአገጩ ላይ ቁልቁል የተንጠለጠለውን ረጅም ሪዝ እየደባበሰ፣ ከአጠገቡ በርከክ ብሎ - ለመስገድ የተዘጋጀ አማኝ መስሎ ተቀመጠ።

"ወንድም ሶፎኒያስ?" አለው፣ ቆፍጠን ባለ ድምጽ።

“አቤት፤” መለሰ ሶፎኒያስ፡ ሙሉ በሙሉ ፍርሃቱ ባይለቀውም ከቅድሙ ግን አሁን ተረጋግቷል።

“አሁን ያደረግኩትን ሁሉ እያየክ ነበርን?”

“አዎን አለቃዬ - በጣም የሚያስደንቅ ነገር ነው ያየሁት። ማለት እንጃ እንደዚህ አይነት እንቅስቃሴዎችን ያየሁት ምናልባትም በቻይና የካራቴ ፊልሞች ላይ ነው።” አለ ሶፎኒያስ መገረሙን በፊቱም ገጽ ላይ እያንጸባረቀ።

“እንደዚያ ሊሆን ይችላል፤ ሙሉ በሙሉም ባይሆን ይህ ጥበብ ካራቴ ወይም ማርሻል አርትስ የሚሉት መጠሪያዎች ይገልጡታል። እንዳየኸው ጠቃሚ ክህሎትም ነው።”

“እኔን ግን የገረመኝ?... ማለቴ እርስዎ በዚህ ቦታ እየኖሩ ይህንን መሰል ጥበብ እንዴት ልትካኑ ቻሉ?” ሲል ጠየቀ።

“እባክህን አንተ በለኝ - ለመሆኑ በመጀመሪያ እዚህ ኗሪ መሆኔን በምን እርግጠኛ ሆንክ? አሁን ያለንበት፣ የተቀመጥንበት፣ የምናወራበት ንቅፈ-መገለጥስ እውነተኛ ወይስ ምናባዊ ለመሆኑ ምን ማረጋገጫ አለህ?”

ሶፎኒያስ ዘለግ ያለ የዝምታ ቆይታ ከወሰደ በኋላ “እኔንጃ፤” አለ።

“ብዙም በጥያቄ አትባዝን... በየትኛውም እውነታ ወይም ‹ሪያሊቲ› ውስጥ ብንገኝ ዋናው ነገር ማወቅ ያለብንን ማወቃችን፣ መሆን ያለብንን መሆናችን ነው። ...የሆነ ሆኖ ይሄ ‹ማርሻል-አርት› ወይም ካራቴ የተሰኘ ጥበብ አንተ እንደምትለው ከኛ የራቀ ወይም የፊልም ጥበብ አይደለም። በፊት ኖረንበት ለሌሎችም አውርሰነው እኛ ግን የረሳነው ጥበብ ነው። እንግዲህ ሰባቱን የአርምሞ ደረጃዎች ለመውጣት ወስነክ እስከተነሳህ ድረስ ይሄንን የመጀመሪያ እርከን በወጉ ላስረዳህ” አሉና ራሳቸውን አመቻቹ። ...“**ይህ የመጀመሪያው ደረጃ ይባል እንጂ እጅግ ብዙ ኪኖችን[43] ያዘለ እርከን ነው:: ሌሎቹ ስድስት እርከኖችም ከዚህ እርከን ጋር ተቆራኝተው የሚገለጡ ናቸው:: ይሄንን እርከን ልክ እንደለበስኩት ቀይ ቀሚስ በእሳታዊ ስሜትና ደሙ-ነፍስ ልትወክለው ትችላለህ:: በታችኛው ህብለ-ሰረሰር የሚመሰል፤ ከአራስነት ጀምሮ ከአባለ-ህዋስ[44] የሚመነጭ**

43 ኪን ማለት ብልሃት ወይም ፍልስፍና፤

44 Gonads

ወንዴ-ሆርሞን[45] መር፣ ስድ ንዴትና ግሬተ-ፍትወት[46] ይመስላል። ይህንንም በወጉ መርገጥና ማጎልመስም ሌሎቹን ደረጃዎች ለመቆናጠጥ እንደ መሠረት ያግዛል። …እንግዲህ እንደምታውቀው የኛ ነፍስ ሥጋና አካል በተሰኘ ውስን መገለጥ፣ የመገኘት ብልቃጥ በኩል ነው መሬት ላይ ንቡርነቱ የሚረጋገጠው። በዚህ የሥጋ መገለጥ በብዙ መልኩ መከወኑን እንደ እንሥሣ ካሉ ከሌሎች ፍጥረታት ጋር የምንጋራቸው ነገሮች ቢኖሩንም ሰው ለመሆን በተቸረን ፀጋ መሠረት ይሄንን እርከን ከሌሎች ፍጥረቶች በተሻለ መልኩ ተክነንበት ወደ ላይኛው ደረጃ መግዘፍ እንችላለን። እዚህኛው እርከን ላይ ያሉት አብዛኛዎቹ ነገሮች ከሥጋና ሥሜት፣ ለመኖር ካለ ፍላጎትና ሞትን ከመፍራት ጋር የተሳሰሩ ናቸው።" … "እነዚህ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ማወቅ ይቻል ይሆን?" ብሎ ጠየቀ ሶፎኒያስ፤

"አዎን … መብላት፣ መጠጣት፣ መሰረይ፣ መራባት፣ ልጅ ማሳደግ፣ መልበስ፣ አምሮ መታየት፣ መኖሪያ ስፍራ ማበጀት፣ ጠንካራ መሆን፣ ራስን ከጠላት መከላከል፣ ጤንነትን መጠበቅ፣ የትዳር አጋር ማግኘት፣ በመንጋ መታቀፍ፣ የመኖሪያ ክልልን ማስከበር የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል። እንግዲህ አንተም ማስተዋል እንደምትችለው ሁሉንም ከላይ የጠቀስኩልህን ነገሮች እንስሳትም ማድረግ ይችላሉ። ነገር ግን ሰው ለመሆን እነዚህን ነገሮች የምታደርግበትን ከፍ ያለ ጥበብ መላበስ አለብህ።

ከላይ የጠቀስኩልህን ሁሉንም መሠረታዊ የሥጋ ፍላጎቶች ለማሟላት ግን የሰው ልጅ የተሻለ መንገዶችን ይጠቀማል። አመጋገባችን፣ አለባበሳችን፣ ትዳር አመሰራረታችን፣ ቤት አገነባባችን በአጠቃላይ አኗኗራችን በእውቀት፣ በማስተዋልና በእቅድ የተሞላ መሆን አለበት።

ለምሳሌ ቅጥ ባጣ አመጋገቡ፣ ከመጠን ባለፈ አልኮልና ሲጋራ አወሳሰዱ የአካል ክፍሎቹን ክፉኛ የጎዳ ሰው ወደ ቀጣዮቹ የሰውነት እርከኖች ከፍ ለማለት ጉዞውን በእጅጉ ያከብደዋል። ለዚህም ይመስላል የጥንታዊ የኢትዮጵያ ወይም የአፍሪካውያን ስልጣኔዎች ለአካል ብቃት እንቅስቃሴ፣ ለሚበሉትና ለሚጠጡት ነገር ከፍተኛ ትኩረት ያደርጉ የነበረው። እንግዲህ ቅድም ያየከውና ያስገረመህ፡ ከእነዚህ ጥበቦች አንዱ ነው - ልብ ብለህ አድምጠኝ ወዳጄ፤ ይህ የሥጋ ልህቀትና የጦርነት ጥበብ ‹ካህ-ራህ-ቴ› ነበር የሚሰኘው፤ በጥንታዊው ኬሜት

45 Testasterone

46 Anger & Sexual Drive

ቋንቋ ካህ ማለት "የአካልና መንፈስን ልዕለ-ኃይል" የሚገልጥ ካህ-ምላክ የተገለጠ ጥበብ ሲሆን "ራህ" ማለት ደግሞ የበ-ራህ- የነቃ-የጠ-ራህ መሆንን የሚያመለክት ነው። የመጨረሻዋ ቃል "ቴ" ደግሞ "እጅና እግር" መጠቀምን ይገልፃል። ለዚህም ይመስላል አሁንም በአማርኛው "እጀ-ቴ"፣ "ማጀቴ" መያዣን፣ በኦሮምኛው "ኢጀ-ቴ"-እርግጫን የሚገልጹ ቃላት ሆነው ይገኛሉ። ይህም ካራቴ የሚለው ቃል በጥንታዊ ሳባውያን ቋንቋ መሠረት በእጅና እግር የሚከወን የአካልና ነፍስ ኃይል ማነቃቂያ አልያም ማብሪያ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።"

"እውነት ከሆነ በእርግጥም የሚገርም መረጃ ነው። ግን ካራቴ ምናምን ከአፍሪካውያንም በፊት ቻይናውያን ይተገብሩት እንደነበር ነው እስከዛሬ የማውቀው፡ ማለቴ እኛን ራሱ እነሱ ናቸውኮ እየመጡ ያስተማሩን።" አለ ሶፎኒያስ፤

"እውነት ለመናገር ጥበቡ ከየትም መጣ ከየትም ዋናው ነገር መተግበሩ እንደሆነ መርሳት የለብህም። ነገር ግን በተለይ አሁን ያለው የኛ ማኅበረሰብ ካራቴን ጨምሮ እንደ ዮጋና ሜዲቴሽን ያሉ ጥበቦችን እንደ ባእድ ነገር የማየት፡ የተሳሳተ አስተሳሰብ ስላለው ሥረ መሠረቱን ማሳወቁ ጠቃሚ ይመስለኛል።

መቼም የኋላው ከሌለ የለም የፊቱ አይደል ብሂሉ። እንግዲህ የካራቴንም ሆነ የዮጋ የውሹንም ሆነ ምስራቃዊው ሚዲቴሽን ምንጭ ከመመርመራችን በፊት ስለ ቻይና ቀደምት ስልጣኔ መሥራች ጥቁሮች መነጋገር ያለብን ይመስለኛል። የቻይናን ስልጣኔ የመሠረቱት የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ጥቁሮች እንደነበሩ በቻይና ታሪክ ውስጥ በሚገባ ተመዝግቦ የሚገኝ እውነታ ነው። እነዚህ ቀደምት ጥቁሮች ሊ-ሚንግ[47] ትርጉሙም ጥቁር ራስ ያላቸው ሰዎች[48] ተብለው ይጠራሉ። ከዚህ በተጨማሪ የቻይናውያን ከጎግ ማንጎግ ለመጠበቅ የተገነባው ታላቁ የቻይና ግንብ በጥቁሩ ንጉሥና ነብይ አቀርንቲሁ[49] ወይም ዙል-ቀርነያን[50] እንደተገነባ ብዙ ማስረጃዎች አሉ። ይሄ የአሁኒቷ ቻያናን የመሰረታት ዚንግ-ቂን የኖረበት ዘመን፤ መጽሐፈ ያሻር ኢትዮጵያዊው እስያኤል ምድር ላይ ከኖረበት ዘመን ተመሳሳይ ነው። የቻያና መጠሪያ ስም መነሻ ራሱ ብናይ ‹ቺን› ከሚለው የመጣ ሲሆን ይህም የተገኘው ‹ቂን› ከሚለው

47 (Li-Ming)
48 (Black Headed people)
49 መጽሐፈ-አቀርንቲሁ በተሰኘ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ መጽሐፍ ብሎም
50 በኢብኑ አቡ ጧሊብና ኢብኑ አባስ ኪታቦች ጥቁር መሆኑ ተመዝግቧል

የዚንግ-ቂን ስም እንደሆነ ያነገራል::[51] እዚህ ላይ <<ዡል-ቀርነያን›› ከሚለው ስም ከቻያናው ሥርወ-መንግስት መስራች <<ዚንግ-ቂንን›› ጋር ተመሳሳይ ነው:: ቀርነይን ማለት በራሱ በግእዝና በትግርኛ ቀንድ ማለት ነው:: ይህም በሁለት የምድርና ሰማያዊ ጥበብ ቀንዶች ተቀርጾ ከሚገኘው ጥቁር ሃውልት ጋር በእጅጉ የሚመሳሰሉ ናቸው:: ከዚህም በተጨማሪ የዡ[52]ና ዢያ[53] እና ሻንግ[54] ሥርወ መንግስት መስራቾችም እነዚሁ ገራሚ ጥቁር ኢትዮጵያዊና የአሁኖቹ አፍሪካውያን ናቸው::

እነዚህ ጥቁሮች በሞንጎል ወረራ ተውጠውና አህጉሪቱን ለቀው ቢወጡም አሁንም በደቡብ ምሥራቅ ኤዥያ ባሉ የፓሲፊክ ደሴቶች[55] እና ከህንድ በስተደቡብ ባሉ ‹ኖርዝ ሲሲሌ› ደሴት ውስጥ እየኖሩ ይገኛሉ::" አለና ማስተሩ እግሮቹን ይበልጥ አነባብሮ ተመቻቸ:: በረጅሙ ትንፋሽ ወስዶም በዝግታ አስወጣ:: ሶፎኒያስም የንግግሩን ሀዲድ እንዳይስት በማሰብ በዝምታ ታግሶ ጠበቀው::

*{ባለዝናውና ከ4900 ዓመት በፊት የኖረው ጥቁሩ Fu-Hsi (Shang ሥርወ መንግስት) Nakhi ተብሎ ይጠራል:: Na (Black) Khi (man) ለቻይናውያን ከ I-Chang (book of change)፣ በተጨማሪም የአፍሪካውያን ጥበብ የሆነውን ማርሻል አርት እንዳስተማራቸው ይነገራል:: yoga,meditation ,ku-ta (defender of pharoah) በኃላ Kuntao በሚል የተቀየረ የማርሻል አርት ጥበብንም ከአፍሪካውያን (ጥንታዊ ኢትዮጵያውያን) ቀስመዋል::}*

"ምን መሰለኽ? የኛው ትውልድ እውነታውን ይርሳው እንጂ ግሪኮች ሳይቀሩ የዚህን ስፓርት ባለቤት ጠቅሰዋል። ሄሮድተስ እንዳለው ራምሲስ ሁለተኛ ጥቁር ግብፅንና ኢትዮጵያን ከማስተዳደሩ በፊት እንደዚህ አይነት ጥበቦች እንዳሉት ይጠቅሳል።

*{John Grombach "The Saga of the Fist" በተባለው መጽሐፉ እውነታውን በግርድፉ ገልጾታል:: ጃፓኖችም የመጀመርያዎቹ "Samurai" ጥቁሮች ነበሩ ይላል:: "A Samurai, to be brave, must have a little Black blood" ሚሉት አባባላቸው ምናልባት ለምስክርነት ሳይረዳን*

51 ኪን
52 (Zhou)
53 (Xia)
54 (Shang)
55 misnomer Nigritos" (small black man)

አይቀርም::} በተጨማሪ ምሳሌ ኦሎምፒክን ብንመለከት መጀመሪያ ግሪኮች እንደፈለሰፉት ያለ እፍረት ይሰበካል፤ እውነቱ ግን ጥንት ኢትዮጵያውያን፣ አፍሪካውያን እንደ መዝናኛ ውድድር ይገለገሉበት እንደነበር መዛግብት ብሎም የማይታበዩት ጥንታዊ የፒራሚድ፣ የግድግዳ ላይ ስዕሎችና ጽሁፎች ይነግሩናል:: እርግጥም የመጀመሪያዎቹ የ‹ሻወሊን› አለቆች ጥቁር አፍሪካውያን ነበሩ::

ይህ ምናልባት ለብዙዎች ላይዋጥ የሚችል ሃቅ ይሆናል:: ይህም እንዳልከው ሲነገርው የቆየው እንደ ቻይና፣ ጃፓንና ኮሪያ ያሉ የሩቅም ምሥራቅ ሃገራት የጥበቡ ፈጣሪዎች እንደሆኑ ስለሆነ ነው:: እውነታው ግን ከዚህ የራቀና ወደ ጥንታዊ "የማርሻል አርት የትውልድ ሥፍራ" አፍሪካ የሚወስደን ነው:: በጥንታዊ የጥቁር ግብጽ ንጉሥ መቃብር ላይ ተዋጊዎቹ የትግል ስልቶችን፣ አቋቋሞችን መያዝ፣ መወርወር ፣ መምታት ፣ መዝለል፣ መሰንዘር፣ መራገጥ፣ የቡጢ ምት እና የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርጉ በሥዕላዊ መግለጫ ላይ ተቀርጾ ይታያል::

*{በአሁኗ ግብፅ ቤኒ ሐሰን የጥንቷ ራምሰስ እና ካሜቲክ አስተዳዳሪዎች መቃብሮች ላይም ከ500 በላይ ጥንድ ተፋላሚዎችና ተዋጊዎች በመሳሪያ፣ ሻምላና ዱላ ሲጠቀሙ የሚታየው ሥዕላዊ መግለጫ ጥንታዊው የማርሻል አርት ጥበብ ገለፃ ሆኖ ተመዝግቧል::}*

አፍሪካውያን ከእንስሳት ፍልሚያ ትግል እንቅስቃሴ በመቅዳት[56] ሽንፈት አልባ ስልትን በመፍጠርም የመጀመሪያዎች ናቸው:: ከእነዚህም ውስጥ ጦጣ፣ ነብር፣ እባብና ዋልያ ይጠቀሳሉ::

*{ከሮማውያን፣ ከኤዥያውያን፣ከማርሻል አርት በፊት ግን ጥንታዊ አፍሪካውያን እራስን የመከላከል ጥበብን "Montu" ይሉት ነበር:: ይህንንም የሚመስል በዳንስ መሰል እንቅስቃሴ የታጀበ፡ አሁንም በደቡባዊ ኢትዮጵያ የሱሪ ጎሳ አባላት ዱላ በመጠቀም የተካኑ እንደሆኑ ይታወቃል:: ጥበብ ጥንታዊ መሆኑን የ "Vice ሪፖርተር" በአንድ ወቅት ዘግቧል:: የፈረስ ጉግሥና ጦር ውርወራም በባህላችን የሚገኙ መሰል ጥበቦች ናቸው::}*

ኤዥያውያን ያንን ትምህርት ተቀብለውና አራቅቀው አሁን ለደረሰበት ደረጃ ማብቃታቸውን እያመሰገንን ዓለም በአድሎአዊነት የደበቀውን ሌላኛውን የጥቁር የቅድመ አያቶቻችንን አስተዋጽኦም ግን እንናገራለን:: ይህም እውቀትና ጥበብ በቅድሚያ እኛ ልናምንበት ስለ ሚገባ ነው::

---

56 'Animal styles & principles in shaolin kung fu

ይህንን ስናምንም እንደ ቴኳንዶ፣ ካራቴ፣ ውሹ መሰል ጥበቦችን እንደ ባዕድ ማየት እናቆማለን። በስፋት ከተገበርነውም እንደ ሀገር በተለያዩ አልባሌ ነገሮች፣ የመጠጥና መሰል ሱሶች፣ የፊልምና ኳስ ሱስ ወዘተ የተጠለፈውን ወጣት ጤናውን የሚጠብቅ፣ በአደጋ ጊዜ ሃገሩን ለመጠበቅ ለውትድርና ዝግጁ፤በእለት ተእለት ሥራውም ላይ ንቁና ፈጣን የሆነ ብሎም በሥነ-ምግባር የታነጸ ብቁ ትውልድን ለመፍጠር ያግዛል።

*{አሁንም ቢሆን በኢትዮጵያችን ዙሪያ የሚገኙ መሰል የስፖርት ማሰልጠኛዎች ብዙ ወጣቶችን እየቀረጹ ይገኛሉና ሊበረታቱ ይገባል። እንደነ ማስተር አብዲ ያሉ ኢትዮጵያውያን የማርሻል አርት ጠበብቶች በዓለም አቀፍ መድረክ ኢትዮጵያን እያስጠሩ ጥበቡ ከደማችን ጋር የተዋሀደ እስኪመስል አኩርተውናል። ወደፊትም የሚገባው ትኩረትና ድጋፍ ተሰጥቷቸው በተለይ በታዳጊው ላይ ሰፊ ሥራ እንዲሠሩ ማድረግ ያስፈልጋል። በየቀበሌው መሰል ልምምዶች እንዲኖር ማድረግ ያሻል። ከዚያም አልፎ ኢትዮጵያዊ የሆነ መሰል ጥበብን መፈልሰፍና ማቀናጀት ቢቻል መልካም ነው።}*

... እንግዲህ ይህንን ሁሉ የምነግርኽ ሶፎኒያስ የአካል ጤናና ንቁነት የመጀመሪያው እርከን መሠረት ስለሆነ ብቻ አይደለም።

ይልቁንም በሰውነትህ እንቅስቃሴዎችህና የውሹ ትርኢቶች ውስጥ ዝምታ ራሱን ይገልጣል። ብዙ ጊዜ እንቅስቃሴ ላይ ያለን ሰው ብታስተውለው ጸጥ ያለ ነው። ጎል ሊያገባ ሲል የሚያወራ ኳስ ተጫዋች፣ በቡጢ ተጋጣሚውን ሊነርት ሲል የሚናገር ቦክሰኛ አልያም ለማሸነፍ መቶ ሜትር ርቀት ቀርቶት እየከነፈ ሳለ የሚለፈልፍ ሯጭ ማግኘት ከባድ ነው። የስፖርትና ውዝዋዜን መሰል ጥበቦች አንዱ መገለጫ ዝምታ ነው። እዚህ ግድም ቃላት በሰውነት እንቅስቃሴዎች ይተካሉ።

*በመጨረሻም የምጨምርልኽ ነገር አመጋገብህ ላይ ጥንቃቄ እንታደርግ ነው:: ከምትበላው ምግብ ሰውነትኽ ይበረታል፣ ይገነባል:: ታዲያ ቤተ-መቅደሱን በእንቧይ ካብ የሚገነባ ሰው ቂል አይደለም ወይ? እንዲሁ ሁሉ አንተም አመጋገብህን ምረጥ፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ አዛዕርትን አብዛ፣ በቻልከው መጠን ጹም፤ አፍ ሲጾም ልብንም ከተንኮል ለማራቅ ጥሩ ነው::*

እና በጤነኛ አካል ላይ ተመስጦ ሲጨመርበት ህይወትን ትኖራታለህ ሳይሆን ትሆናታለኽ:: አንተ ራሱ በእጆችህ መላወስ፣ በእግሮችህ መራመድ፣ በሳንባህ መተንፈስ ውስጥ የምትገለጥ ህይወት፣ ዮድ[57]ን ታስደስታለህ:: ንቁ፣ ብቁ፣ ጠንካራና ብርቱ ትሆናለኽ::" አለና በአትኩሮት ከተመለከተው በኋላ ከወዲያኛው ገደል ላይ የቆመችው ዋልያ ትታይኽለች?" ሲል ጠየቀው፤ ሶፎኒያስም ወደጠቆመው አቅጣጫ ዞር ብሎ ዋልያዋን ካያት በኋላ በግርምት "አዎን፤ አየር ላይ ነው እንዴ የቆመችው?" ብሎ መልሶ ጠየቀው፤ ዋልያዋ ሸቅብ ካሾጠጠው አለት ላይ ተቆናጣ ሳይት የእውነትም በተኣምር አየር ላይ የቆመች ትመስል ነበር::

"አየር ላይ አይደለም የቆመችው ወዳጄ፣ ግን ይህቺ ንቁና ደፋር ዋልያ በራስ መተማመኗ እጅግ የጠነከረ ስለሆነ ፈጣሪ የሰጣትን መክሊት ተጠቅማ ከገደልና ተራሮች ወገብ ሳትወድቅ ትራመዳለች:: ዋልያዎች መንፈሳዊ የጽናት ህይወትን የሚወክሉ የብርታት ዋልታዎች ናቸው::[58] ከልባቸውም ኢትዮጵያዊ ብርቅዬ እንስሳት ናቸው:: ባይገርምኽ ብዙ ጊዜ በአውሮፓ ሃገራት ሊያራቧቸው ሞክረው አቅቷቸዋል::" አለና በኩራት ዋልያዋን አያት፤ ከዚያም ያጣጠፋቸውን እግሮቹን አፍታታ:: በዝግታም ተነስቶ ከፊቱ ቆመ:: ሪዙን እየዳበሰ ደግሞ ቁልቁል ሶፎኒያስን አስተዋለው:: "እንግዲህ የመጀመሪያውን እርከን እውቀት በመጠኑም ቢሆን ካስገነዘብኩህ ዘንዳ አሁን በምናብህ የትውስታ ምህዳር ውስጥ በርካታ መሰል ጥበቦችን እንድጭንልህ ፍቀድልኝ፤" ሲል ጠየቀው፤

ሶፎኒያስም እኔ ምን ገዶኝ በሚል የስምምነት ዓይነ-ልቦና አስተዋለው። ሰውዬውም በእጁ ይዞት በነበረው በትር ግራና ቀኝ ትከሻዎቹን መታ መታ አደረገው። ቀጥሎም ዓይንን የሚያንጠባርር እፍጋታዊ ብርሃን ሲለቅበት ራሱን ስቶ ተዘረረ።

|ዶ/ር ሶፎኒያስ ወደ ነፍሱ ሲመለስ ድሮ የማያውቃቸውን ብዙ የአካል ብቃትና ራስን የመከላከል ጥበቦች ያውቅ ነበር።

⌘ ⌘ ⌘

ኤልሳ ከፍ ካለው ኑሮዋ፣ ከላይኛው መስኮቷ ቆማ ከድሮ የዝቅታ ጎጆዋ ውስጥ ሁለት ወጣቶች ተቃቅፈው ሲወጡ አየች። ዓይኖቿን

57 በመዝሙረ ዳዊት የተጠቀሰ ስመ አምላክ፤

58 ብዙ ቅዱሳንም በአርምሞ ውስጥ ሳሉ በዋልያዎች ታጅበዋል፤

አላመነቻቸውም። አተኩራ ብታጣራ እውነትም ራሳቸው ናቸው። ልቧ ዝቅ አለባት። ለይኩን እኮ ነው ሜሮንን አቅፎ የወጣው| ኤልሳ እንደሆነ ነገር አደረጋት! ተቁነጠነጠች፣ ተብከነከነች፣ ተብሰለሰለች፣ ተንጨረጨረች - እንደምንም ግድግዳ እየተደገፈች ወደ አልጋዋ አቀናችና ከግርጌው ቁጭ አለች። ስላየችው፣ እየሆነ ስላለው ‹ካርማ›[59] በሃሳብ ሙግት ገጠመች።

ሜሮንንኮ ትወዳታለች። ማለት ትወዳት ነበር። በዚህ ብርሃን ብዙም ባለጎበኘው ህይወቷ ውስጥ ጓደኛዋ፣ ብርቅዬ ፋኖሷ ነበረች። በማይረዳት የቅርብ ሩቅ ቤተሰብ ውስጥ ስታድግ ያጣችውን ፍቅር በመጠኑም ቢሆን ከእሷ አግኝታለች። የሆዷን የምትነግራት ምስጢረኛዋም ነች። ዛሬ ግን ታደርጋለች ብላ ያልጠበቀችውን ነገር ስታደርግ አገኘቻት። በተዓምር ይሆናል ብላ ያልጠበቀችው ሆነ። የሰው ልጅ የጣለውንም ቢሆን ሲያነሱበት አይወድም የሚሉት ብሂል ዛሬ ገባት።

ኤልሳ በግልፅ፤ የነገ ምኞቴን ሊሰጠኝ አይችልም ብላ ነው ለይኩንን የራቀችው። ከምትጠላው ድህነት የመውጫ ትኬቷ አበጋዝ እንደሆነ አምናለች። ዛሬ ለይኩንን ከሜሮን ጋር ስታየው ግን የሆነ የማታውቀው የቅናት ስሜት ደምስሮቿን ተቆጣጠራቸው።ለወንድሟ ከነበራት ቅናት ቀጥሎ ይሄን ያኽል ስትቀና ሁለተኛዋ ነው። ለይኩንን ብትጥለውም የሷ ቅሪተ ነፍሶችም እሱ ጋር ቀርተዋል[60]። አብራ የጣለቻቸው ትዝታዎችና ባለቤትነቶች አሉ። በዚያ ላይ የልጇ አባት ነው። የፈለገ ብትርቀው የማትፍቀው እውነታ አለው። መርዕድ የአበጋዝ ልጅ እንደሆነ እየነገርች ልታሳድገው ብትወስንም፤ ይሄ ግን እውነቱን እንዳያውቀው በቂ ማስተማመኛ አይደለም። በዚህ ተቀራርቦ በሚኖር ማኅብረሰብ ውስጥ የወሬ ሽንቁሮች እጅግ ብዙ ናቸው። ነገር ግን የአቅሟን ትሞክር ዘንድ ወስና ነበር ቁጭ ያለችው። ዛሬ ግን ሌላ ጉድ መጣ። የቀድሞ ባሏ ለይኩንና የቅርብ ጓደኛዋ ሜሮን አብረው ተጣመሩ።

ያን ቀን ኤልሳ ከመስኮት ወዳ አልጋዋ እንዲሁ ስትመላለስ ዋለች። ሥራ ውሎ፣ አመሻሹ ላይ ወደ ቤት የተመለሰው አበጋዝ የኤልሳ ባህሪ ከወትሮ ለየት ብሎ ነበር የጠበቀው። እራት ለመብላት የመመገቢያ ጠረጴዛው ላይ ከተቀመጡ ጀምሮ አንድም ቃል አልተነፈሰችም። ምንም ሳይላት ራሱ

---

59 በሂንዱ ኃይማኖት ያለ አስተምህሮ ሲሆን ማንኛውም የሠራከው ጥሩም ይሁን መጥፎ ነገር ተመልሶ፡ በሆነ መንገድ አንተኑ እንደሚያገኝህ የሚጠቁም ቃል ነው፤ ሁሉም ሰው የዘራውን ያጭዳል እንደማለት፤

60 በህይወታችን ውስጥ አብረን ገመናችንን ገልጠን ከምናሳልፋቸው ሰዎች ጋር ሥጋዊ ብቻ ሳይሆን የሐሳብ፣ የነፍስና የመንፈስ ውህደት እናካሂዳለን፡፡ ስንለያይም የሚቃወሱት እነዚህ ሁሉ የማንነት አካላቶቻችን ናቸው፡፡

እንጀራ ቆርጦ ወስዶ፡ ከሰሀኑ ዘረጋ። ከቀይ ጎድጓዳ ሳህኖች አልጫና ቀይ ወጥ አንድ፡ አንድ ጭልፋ አደረገችለት። በዝምታ በልተው እስኪጨርሱ የሚሰማው ድምጽ በወለል ምንጣፉ ላይ እየዳኸ የሚጫወተው የልጅ መርዕድ፤ ሳቅና ትርጉም አልባ ቃላቶች ጉምጉምታ ነበር።.."ምነው ዛሬ? ደህና አይደለሽም እንዴ ኤልሲ?"

"ኧረ ደህና ነኝ።"

"ግን ደህና አትመስይም ውዴ..."

"አንተ ሰውዬ! ደህና ነኝ አልኩህ አይደል? ለምን አትተወኝም?"

ብላ ገበታውን ጥላ ወደ መኝታ ክፍሏ ሄደች።

አበጋዝ ይበልጥ ደነገጠ። ቃልም ሳይተነፍስ ወደ ሶፋው አመራና እግሮቹን አፍታቶ ተንጋለለ። ለምን እየተነጫነጨች እንዳለች ግራ እየገባው ስለ ኤልሳ ማሰብ ጀመረ።

የአበጋዝን ቁመናና የኑሮ ደረጃ ያየ ሰው ለምን አግብታ ከወለደች ሴት ጋር አብሮ ለመሆን መረጠ ብሎ ቢጠይቅ ምክንያታዊ ነው። ጉዳዩ ወዲህ ነው፤ አበጋዝ ሲወለድ የባህል አዋላጇ እንደማንኛውም ህጻን ልጅ ሙሉ ሰውነት እንዳለው አይታ ለእናቱ አሳቀፈቻት። ከዘጠኝ ወር ቤቱ ሥጋና ደም ከተካፈለ፣ በህያው እስትንፋስ ንፋስ ስቦ ካለቀሰ በኋላ እንደ ማንኛውም ህጻን አድጓል። እናትና አባቱ ለጉድ ይወዱት፤ እሱም በጣም ይወዳቸው ነበር።

በጉብዝናው እድሜ ተፍጨርጭሮ ወደ ሐብት ጎዳና ማምራት ሲጀምርም ዋናው ህልሙ እነርሱን መጦር ነበር። ባንዲት ጎዶሎ ቀን ግን ሁለቱንም በመኪና አደጋ አጣቸው።[61] ሰማይ ምድሩ ጨለመበት። ከብዙ የድባቴ ወራት በኋላ ነበር ወደ ራሱ የተመለሰው። እነዚያውን ውድ ወላጆቹን መልሶ ማምጣት እንደማይችል በከባድ እንግልት ተረዳ። ከብዙ መብሰልሰል በኋላም ከአንድ ውሳኔ ላይ ደረሰ፤ የራሱን ቆንጆ ቤተሰብ መሥርቶ ወላጆቹ ለሱ ያሳዩትን ፍቅርና እንክብካቤ ለልጆቹ መድገምን ግቡ አደረገ።

61 ትኩረትና ትዕግስት በማጣት የቅጽበት ስህተት ተመን አልባው የሰው ነፍስ ይቀጠፋል፡፡ ዮጋና ተመስጦ ትኩረትን ለመሰብሰብና ታጋሽነትን ለማጎልበት በጣም ያግዛል፤ ሜዲቴት ማድረግ ለሾፌሮች በእጅጉ ይመከራሉ፡፡

[illegible] በፈረስ ይቀላል።)

[illegible] ሁለት [illegible] ቢሞክርም ልጅ [illegible] በስተመጨረሻም [illegible] ወደ ሥራው ዞረ። ብርቱ [illegible] ትኩረት አደረገ። የሥራ [illegible] ግን የሌለህ ነገር ያምርሃል፤ [illegible] እንድዬ ብቻ ነው።) ልጅ [illegible] እድሜውን ቆጠረ። ብዙ [illegible] አልሆነም። ልጅ ያላቸው ጓደኞቹ [illegible] አይሰጡትም፤ "አንተኮ ተምረሃል፣ [illegible] ምን ያስጨንቅሃል?" ይሉታል። በተቃራኒው [illegible] "የህጻን ልጅ የአንገት ሥር ሽታ ነፍስን ያድሳል" [illegible] በሁለቱም ዋልታዎች ግን የእሱ አቋም አንድ ነው። ልጅ ይፈልጋል።

ሞክሮ ሞክሮ አልሳካ ቢለው በራሱም በኑሮውም ተስፋ መቁረጥ ጀመረ። ይህ ደግሞ ቀስ በቀስ ጨካኝ ሰው እያደረገው ነ[illegible] ላይ፣ በሌሎች ላይ፣ በሃገር ተስፋ ላይ መጨከን አበዛ። "ለማ[illegible] የምሠራው? ለማንስ ስል ነው የምለፋው?" ለሚሉት ጥያቄዎ[illegible]

እንጀራ ቆርጦ ወስዶ፡ ከሰሀኑ ዘረጋ። ከቀይ ጎድጓዳ ሳህኖች አልጭና ቀይ ወጥ አንድ፡ አንድ ጭልፋ አደረገችለት። በዝምታ በልተው እስኪጨርሱ የሚሰማው ድምጽ በወለል ምንጣፉ ላይ እየዳኸ የሚጫወተው የልጅ መርዕድ፤ ሳቅና ትርጉም አልባ ቃላቶች ጉምጉምታ ነበር።..“ምነው ዛሬ? ደህና አይደለሽም እንዴ ኤልሲ?”

“ኧረ ደህና ነኝ።”

“ግን ደህና አትመስይም ውዴ...”

“አንተ ሰውዬ! ደህና ነኝ አልኩህ አይደል? ለምን አትተወኝም?”

ብላ ገበታውን ጥላ ወደ መኝታ ክፍሏ ሄደች።

አበጋዝ ይበልጥ ደነገጠ። ቃልም ሳይተነፍስ ወደ ሰፋው አመራና እግሮቹን አፍታቶ ተንጋለለ። ለምን እየተነጫነጨች እንዳለች ግራ እየገባው ስለ ኤልሳ ማሰብ ጀመረ።

የአበጋዝን ቁመናና የኑሮ ደረጃ ያየ ሰው ለምን አግብታ ከወለደች ሴት ጋር አብሮ ለመሆን መረጠ ብሎ ቢጠይቅ ምክንያታዊ ነው። ጉዳዩ ወዲህ ነው፤ አበጋዝ ሲወለድ የባህል አዋላጇ እንደማንኛውም ህጻን ልጅ ሙሉ ሰውነት እንዳለው አይታ ለእናቱ አሳቀፈቻት። ከዘጠኝ ወር ቤቱ ሥጋና ደም ከተካፈለ፣ በህያው እስትንፋስ ንፋስ ስቦ ካለቀሰ በኋላ እንደ ማንኛውም ህጻን አድጓል። እናትና አባቱ ለጉድ ይወዱት፤ እሱም በጣም ይወዳቸው ነበር።

በጉብዝናው እድሜ ተፍጨርጭሮ ወደ ሐብት ጎዳና ማምራት ሲጀምርም ዋናው ህልሙ እነርሱን መጦር ነበር። ባንዲት ጎዶሎ ቀን ግን ሁለቱንም በመኪና አደጋ አጣቸው።[61] ሰማይ ምድሩ ጨለመበት። ከብዙ የድባቴ ወራት በኋላ ነበር ወደ ራሱ የተመለሰው። እነዚያውን ውድ ወላጆቹን መልሶ ማምጣት እንደማይችል በከባድ እንግልት ተረዳ። ከብዙ መብሰልሰል በኋላም ከአንድ ውሳኔ ላይ ደረሰ፤ የራሱን ቆንጆ ቤተሰብ መሥርቶ ወላጆቹ ለሱ ያሳዩትን ፍቅርና እንክብካቤ ለልጆቹ መድገምን ግቡ አደረገ።

61 ትኩረትና ትዕግስት በማጣት የቅጽበት ስህተት ተመን አልባው የሰው ነፍስ ይቀጠፋል:: ዮጋና ተመስጦ ትኩረትን ለመሰብሰብና ታጋሽነትን ለማጎልበት በጣም ያግዛል፤ ሜዲቴት ማድረግ ለሹፌሮች በእጅጉ ይመከራሉ::

ብዙም ሳይከርም አንዷ ዓይንና ልቡ ያረፈባትን ኮረዳ አግብቶ ተጠቃለለ። ፍቅርና ደስታ ዳግም ወደ ህይወቱ ተመልሰው ነበር። ነገር ግን ቀስ በቀስ ነገሮች መቀያየር፡ ጭቅጭቆችም መበራከት ጀመሩ። የጥላቻው ምንጭም አንድና አንድ ነበር። ወደ ተባረከው የትዳር ህይወታቸው ልጅ ሊመጣ አልቻለም። ቢሉ ቢሞክሩ፣ ቢታገሱ፣ ቢያማርሩ፣ ቢሳሉ፣ ቢገዘቱ ልጅ የሚባል ነገር አልሆን አለ። ለችግሩ መፍትሔ ቢያጡለት በስተመጨረሻ በዘመናዊው ህክምና ምርመራ አካሄዱ። ውጤቱም ከልጅ ማፍራት አለመቻል ባለፈ ትዳራቸውን የሚያፈርስ ሆነ። አበጋዝ የወንድ የዘር ፍሬው ልጅን ማፍራት የማይችል ልፍስፍስ እንደሆነ ተነገረው። የመጀመሪያ ሚስቱ ታዲያ ለተወሰነ ጊዜ ስትግደረደር ከቆየች በኋላ ለልጅ ወግ ካላበቃኸኝ ካንተ ጋር ምን እሠራለሁ ብላ ጥላው ሄደች። ለነገሩ የእለት ተእለት ጭቅጭቆቹም ትዳራቸውን የአሉታዊ ስሜቶች መፈንጫ አድርገውት ነበር። {አንዳንዴ ሰርክ ከማይፈቱ የጭቅጭቅና የትዳር ንትርኮች፣ ተብሎ ተለምኖ የማይሆን ከሆነ መለያየት የተሻለ መፍትሔ ነው፤ በተለይ በመሐል ልጅ ከሌለ የሁለቱም የግል ህይወት በመጣላት እርግብግቦሽ መቀመቅ ከሚገባ የጋራ ተቋማቸው ቢፈርስ ይቀላል።}

አበጋዝ ከሷ በኋላ በጋብቻ ሁለት ሚስቶችን፣ ከጋብቻ ውጪ ሁለት ሴቶችን አሳምኖ ቤተሰብ የመመስረት እቅዱን ሊያሳካ ቢሞክርም ልጅ መውለድ ባለመቻሉ የእምቧይ ካብ እየሆነ ፈራርሶበታል። በስተመጨረሻም ቤተሰብ የመመስረቱን ጉዳይ ተስፋ ቆርጦበት ወደ ሥራው ዞረ። ብርቱ የልጅ ፍላጎቱን ለማስቀየስ ሐብት ወደ ማካበቱ ትኩረት አደረገ። የሥራ እድገቶችም አግኝቶ ነበር። {ሰው ስትሆን ግን የሌለህ ነገር ያምርሃል፤ ያለህ ነገር ደግሞ ይሰለችኻል። ዝንት የማይሰለች አንድዬ ብቻ ነው።} ልጅ እንደጉድ ያማረው አበጋዝም ምኞቱን እንዳዘለ እድሜውን ቆጠረ። ብዙ አማራጮችን ቢሞክርም የሚሳካ ነገር አልሆነም። ልጅ ያላቸው ጓደኞቹ የሱ ልጅ ፍለጋ መባዘን ትርጉም አይሰጣቸውም፤ "አንተኮ ተምረሃል፣ በዚያ ላይ ገንዘብ አለህ። ምን ያስጨንቅኻል?" ይሉታል። በተቃራኒው አንዳንድ እናቶች ደግሞ "የህጻን ልጅ የአንገት ሥር ሽታ ነፍስን ያድሳል" እያሉ| ችግሩን ሳያውቁ ያጓጉታል። በሁለቱም ዋልታዎች ግን የእሱ አቋም አንድ ነው። ልጅ ይፈልጋል።

ሞክሮ ሞክሮ አልሳካ ቢለው በራሱም በኑሮውም ተስፋ መቁረጥ ጀመረ። ይህ ደግሞ ቀስ በቀስ ጨካኝ ሰው እያደረገው ነበር። በራሱ ላይ፣ በሌሎች ላይ፣ በሃገር ተስፋ ላይ መጨከን አበዛ። "ለማን ስል ነው የምሠራው? ለማንስ ስል ነው የምለፋው?" ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ

ስላጣ ለነገ ብሎ የሚሠራና የሚኖር ሰው መሆን አልቻለም። {ልጅና ህሊና ከሌለህ ከራስ በላይ ንፋስ ለማለት ቅርብ ትሆናለኽ። ሀገር ኖረች አልኖረች፣ ከሰረች፣ ወደቀች፣ ቆረቆዘች ያንተ ጥቅም እስካልተነካ ድረስ ደንታም አይሰጥህም።}

አበጋዝም እንዲሁ በልቼ፣ ጠጥቼ፣ ተዝናንቼ፣ በምቾት ኖሬ በምቾት ልለፍ እንጂ ምን አገባኝ? የሚል አይነት ሰው ሆነ። በትምህርቱና ልፋቱ የተቆጣጠረውን ስልጣን እንደልቡ መዘወር ጀመረ፣ የመንግሥት ብር መዘበረ፣ ሙስናውን አደራው፣ በጉቦ ብር ኪሱን አሳበጠ። ቤት ሠራ፣ መኪና ገዛ፣ የባንክ ደብተሩን ቋት አጨቀ።

አዲስ የሠራው ቤት ውስጥ በገባ በሣምንቱ ግን ኤልሳን ከልጇ ጋር ተቀምጣ አያት። ለዘመናት ተለይቷቸው ኖሮ ዛሬ ያገኛቸው ሚስትና ልጁ መሰሉት። እየሮጠ ሄዶ ሊያቅፋቸውም ዳድቶት ነበር።⌘

አበጋዝ አንድ ላይ ሊያጠቃልላቸው የቋመጠላቸው፣ ሚስትና ልጁ እንዲሆኑ የወጠነላቸው፡ እናትና ህጻን ለማጥመድ ተነሳ። እንደልክፍት ቢሆንበት ሙሉ ኃይልና ገንዘቡን መድቦ ተንቀሳቀሰ። በመጨረሻም ተሳካለትና አገኛቸው፤ ወደ ቤቱም አስገባቸው። ወደ ቤቱ ለመግባታቸው የእነርሱ ምክንያት ምንም ይሁን ምን እሱ ግን ደስተኛ ነው። የፈለገውን አግኝቷልና ምንተዳው? |ይህቺ ተመኝቶ ያገኛት ሴት ያው ዛሬ ደግሞ ከጎኑ አኩርፋ ተኝታለች። ባህሪዋ ከወትሮ ተቀያይሮበታል። ከሥራ ሲመለስ ጭራሽ የማያውቃት ሌላ ሰው ሆና ጠብቃዋለች። ...አበጋዝ ልብሱን ቀያይሮ ከአልጋው እንደተከተተ ኤልሳ በበኩሏ ከአልጋው ላይ ተነስታ ምንቅር ምንቅር እያለች ተረማመደች። ከቁም መስታወቱ ስትደርስ እጆቿን አጣምራ ቆመች።

"ዛሬ ምን ሆነሻል ግን?"

"ያልሆንኩትን ብትጠይቀኝ አይሻልም?"

"ምን ተፈጥሮ ነው?" አበጋዝ ግራ ተጋባ፤

"አንተማ ምን አለብኽ እቴ? ዘና ብለህ ተኛ! ... በየቀኑ እየመጣ የሚበጠብጠው እኔኑ ነው..."

"ማነው እሱ?"

"ለይኩን"

"እሱ ሰውዬ ደግሞ ምን አድርጊ ነው የሚልሽ?!" ...ከተኛበት ብድግ ብሎ ቁጢጥ አለ።... "ዛሬ ጭራሽ ቤቴ ድረስ መጥቶ በሩን ሲደበድብ ነበር።" አለችና ኤልሳ ፈቷን ቅጭም አድርጋ ወደ አበጋዝ ዞረች፤ መጨፍገጓ በምላሷ የምትናገረው ውሸት በዓይኖቿ በኩል አምልጦ እንዳይወጣ ስትታገል መሆኑ ነው። አበጋዝ ወዲያው በንዴት ጦፈ... ዘሎ ከአልጋው ወረደና ወደ በሩ አመራ... ኤልሳ በፍጥነት እጁን ለቀም አደረገችው። ዞሮ ሲመለከታት ከቅድሙ በተቃራኒው የተረጋጋ ስሜት ውስጥ መሆኗ ግራ አጋባው።

*"ተው አቤ፣ አሁን በዚህ ንዴት እሱ ጋር ሄደህ የምትፀፀትበትን ነገር እንድታረግ አልፈቅድልህም!"*

*"ከዚህ በላይ እንዴት እስኪደፍረኝ ድረስ ልጠብቀው ነው?!" አለ አበጋዝ ነፃ እጁን እያወናጨፈ... "ይሄ ተንከሲስ ሰውዬ እስካለ ድረስ ሰላማችንን እየረበሸ መቀጠሉ አይቀርም!"*

"እሱን እኔም ቀድሜ አስቤበታለሁ፤" አለችና እጁን ለቃው ወደ ቁም መስታወቱ ተመለሰች... "ይሄንን ክብር የሌለው መናጢ እንዴት እንደምንሠራለት እኔ ነኝ የማውቀው!... ብቻ አንተ ይሄን ንዴትህን ተውና ለነደፍኩት እቅድ እንድታግዘኝ ብቻ ነው የምፈልገው!"

አበጋዝ በንዴት እየተንጎራደደ መለሰላት... "በምንም አይነት መንገድ ላግዝሽ ዝግጁ ነኝ... ምንድነው ያቀድሽው?"

⌘ ⌘ ⌘

### *... ያፍቃሪዋ ማስታወሻ*

*አገኘሁትኮ! ታግሼ በተራዬ ... ገነቴን የኔ አደረኩት! ውስጡ ዘልቄ በአትክልት ቦታው ተምነሸነሸኩኝ:: ውብ ጽጌረዳ ቀስሜ እየዘለልኹኝ በረቅኹበት:: የደስታን ምንነት፣ የሀሴትን ጽዋ ተጎነጨሁት፤ በፍቅሩ ሰክሬም ሀ ብዬ ሴት ሆንኩኝ:: ውድዬን አቅፌው ተኛሁ፣ ስሜው ነቃሁ፣ ህብረ-ከዋክብት የሚቀኑበትን ብርሃን በህይወቴ ሳሉን በርቶ አየሁ - ሞቅም አለኝ::*

*እነሆ ሰርክ የማልጠግበውን የሰማይ መናም ቀመስኩኝ:: ደስም አለኝ:: ማርና ሃለዋ እንዲጣፍጡ ሁሉ ኑሯችን ጣፈጠ:: ቢራቢሮና አደይ እንዲያምሩ ሁሉ አማርን:: ያልበረታውን ገመናውን ባልበረታው*

*ገመናዬ ጎበኘሁት:: አብረንም የዘላለም የሚመስል ፊንጢዚያ ውስጥ እርቃናችንን ጠለቅን:: አብረንም እፎይ አልን:: አንድ ሆንን:: ማንም ላይለየን ተጣመርን - ተጣበቅን::*

⌘ ⌘ ⌘

በአንድ ዝንጥ ባለ፣ በዘመናዊ እቃዎች ቂቅ ምንቂቅ ባለ የቅንጦት ቪላ ሳሎን ውስጥ ሁለት ጎልማሶች እየተጨዋወቱ ነው። ፎቴ ወንበር ላይ ፈልሰስ ብለው ተቀምጠዋል። ከመሐከላቸው ካለው ቄንጠኛ ክብ ጠረጴዛ ላይ ጠንከር ያለ መልእክት ያለው፣ ውድ የስኮች ውስኪ ተሰይሟል። በስተግራ በኩል የተቀመጠውና የቤቱ ባለቤት የሆነው ደንደን ያለው ሰውዬ ጌታቸው ይባላል። ባለው የባለስልጣን ዝምድና በጥቂት ዓመታት ውስጥ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የመሀል ዳኛ መሆን የቻለ የህግ ምሩቅ ነው። በስተቀኝ በኩል የተቀመጠውና በእድሜ አነስ የሚለው ሰውዬ አበጋዝ ነበር።

"እኔና አንተ ስንትና ስንት ሥራዎችን እንደሠራን እንግዲህ የማይታበይ ሀቅ ነው።"

"ቂ ቂ ቂ ቂ... ሥራ አልከው ጃል?"

"እና ምን ልለው ፈልገህ ነበር?... አንተ ደግሞ? በዚህች የጉድ ሃገር እየተፈጸሙ ስንት የማይወሩ ነገሮች እንዳሉ ላንተ ልንገርህ ደሞ... ሃሃሃ" አለና አበጋዝም በሳቅ አጀበው።

"ይሁና አለ አያቴ"

"እሺ ታዲያ በነገርኩህ ነገር ተስማማኽ?"

"አዎ! ያን ያህል የሚያስጨንቅህ ሰው ከሆነ መፍትሔ እናበጅለታለን። የነገርከኝ እቅድም ነገሮችን ቀላል የሚያደርግ ይመስለኛል። ነገር ግን..." አለና ዳኛው ጌታቸው ውስኪ ጠርሙሱን ከፍቶ ብርጭቆውን ከአፍ እስከገደፉ ሞላ።

"ነገር ግን ምን ...?" ጠየቀ አበጋዝ፤

"እንዲያው... ያው ብሯ ትንሽ አነሰች... ባይሆን አንድ መቶ ሺህ ጣል አድርግባት።" አለና ከሰፋው ተመቻችቶ የጎሪጥ አየው።

"እምም… እሺ ካልክ ይሁን… ብቻ ጉዳዩ በምሥጢር ያዘውና ያስፈልጋሉ የምትላቸውን ሰዎች ብቻ አካተህ በአግባቡ ይፈጸም።"

"አይ ወዳጄ አበጋዝ… እያወቅከኝ!? እንኳን ይህቺንና ስንቱን ጉዳይ ፈጣጥመን የለ እንዴ… ቂ ቂ ቂ ቂ… ይልቅ ና… ለጤናችንና ለአዲሱ ቤተሰብህ… ና በናትህ…ቺር…ስ!"

…ገጭ።

⌘ ⌘ ⌘

ይህ በሆነ በሳምንቱ የሲቪል ልብስ የለበሱ ሁለት መርማሪ ፖሊሶች ለይኩን የተከራየውን ቤት በር በኃይል ደበደቡ። ሀገር አማን ብለው ተኝተው የነበሩት ሜሮንና ለይኩን በድንጋጤ ብድግ አሉ፤

*"ምንድነው ጉዱ ለይክዬ?" አለች ከደረቱ ላይ ልጥፍ ብላ፣ ሀሳቧን ጥላ፣ ጭንቀቷን ገድላ … ተኝታ የነበረችው ሜሮን። በቅጡ አልነቃችም ነበር።*

"እኔንጃ ሜሪ፤" አለና ለይኩን ልብሱን በፍጥነት ለባብሶ ወደ በሩ አቀና። በሩን ሲከፍት አንደኛው ፖሊስ ቃልም ሳይተነፍስ እጁን ጠምልሎ ያዘውና በካቴና አሰረው። እየሆነ ያለው ነገር ግራ ያጋባው ለይኩን "እናንተ ማን ናችሁ? ለምንድነው የምታስሩኝ?" እያለ ደጋግሞ ቢጠይቅም፡ "ፖሊሶች ነን!" ከሚል አጭር መልስ በቀር ምንም ማብራሪያ አላገኘም። በድንጋጤ ደንዝዛ ከመኝታዋ የነበረችው ሜሮን ምንም መናገርም መንቀሳቀስም አልቻለችም። እየሆነ ያለውን ነገር ትርጉም ከመረዳቷ በፊት ሁለቱ ሰዎች ለይኩንን አሥረው ወሰዱት። ሁሉም ነገር የሆነው በድንገትና በፍጥነት ነበር። ሜሮን ወደ ራሷ የተመለሰችውም የፖሊሶች ‹ቶዮታ ፒካፕ› ለይኩንን እንደጫኑት ከአካባቢው ከራቀች በኋላ ነበር።

⌘ ⌘ ⌘

ዶ/ር ሶፎኒያስ በምናብ ዓለም ውስጥ ይነሆልል ይዟል። ያ የቴኳንዶ ማስተር ከፈጠረበት አስገራሚ ኃይልና ንቃተ-አካል ነሽጦ ወደ ቀጣዩ ሽለቆ፡ በሽምጠጣ ተጓዘ። በሁለተኛው ቀን፤ ወደ ሁለተኛው ዋሻ እየተቃረበ ሲደርስ ልብን የሚሰልብ ልዩ ዜማ ወደ ጆሮው ይንቆረቆር ጀመር። ቀስ እያለ ወደ ዋሻው ተጠጋ። አንድ ብርቱካናማ ቀሚስ የለበሱ፣ ፀጉራቸው የተንዠረገገ አባት ከዋሻው ውስጥ ቁጭ ብለው በገና ይደረድራሉ። እርሳቸው ከአፋቸው አንድም ቃል አይወጣም። ዜማዎቹ ግን የነፍስን

ጽዋ እንደሚሞሉ ፏፏቴዎች ይንዠቀዠቃሉ። እንደ ቅልስልስ የዝናብ ጠብታዎች እየወረዱ ከልብ ውቅያኖስ ውስጥ ይገማሸራሉ። ምስጋና፣ ሐሴትና ፍሰሀ የሚባሉ መልእክቶችን አዝለዋል። ሶፎኒያስ ቀልቡን ሰብሰብ አድርጎ ከሽማግሌው አጠገብ ተቀመጠ። ዘለግ ላሉ ደቂቃዎች ድምጹን አጥፍቶ በዜማቸው ውስጥ በሰመመን ተመሰጠ፤ የተፈጥሮን ጥንስስ ዜማ በዜማዎቹ ውስጥ አጣጣመ፤ ልብን በሚሰውሩ ህቡዕ ንዝረቶች ምህዋር ውስጥ ተንሳፈፈ።

|በየትኛው ደቂቃ እንደሆነ ባያውቅም አንድ ልስልስ ያለ ምክር፣ ቅኔ ወ ዝክር ወደ ምናቡ መፍሰስ ጀመረ - ለኔ ብሎ ተረከበ።

"...እንዲህም ይሆናል ልጅ ሶፎኒያስ፡ ሁለተኛው እርከን ጋር ስትደርስ ዝምታን በወጉ ትቀዳጃታለህ። ይሄ የኪን ሸለቆ በውስጡ የቃል፣ የአንደበት፣ የቅኔ፣ የስም፣ የዜማ፣ የመልክ፣ የግጥም፣ የማእረግ ስብስብ መድብልን፣ ርቱዕ ነቢብነትን አካቶ ታገኘዋለህ። በውስጥህ እንዳለ የጠፈር ነጋሪት፣ የህዋ መለከት ታዳምጠዋለኸ። ... ስለ ዝምታ ምሥጢር ብለህም አይደል ጉዞኽን የጀመርከው? እንግዲያውስ ይህ እርከን ወሳኙ ምዕራፍህ ነው።" አሉት... ጠበቅ አድርገው።

"እሺ እቀበላለሁ፣ ከራሴም አዋህዳለሁ።" የሚል ሞገድ ከሶፎኒያስ ሐልዮት ተለቀቀ፤

*"እንግዲያውስ ልብ በል! ወደ ምድራዊ ኑሮኽ የመጣኸው በአጋጣሚ አይደለም። ህይወት የተሰጠኸ ለፈተናም ለፍርቱናም ነው። እለት ተእለት የሚገጥሙኸ፡ የኑሮ መሰናክሎችህም የቃልና የተግባር መፍትሔ ይሻሉ።*

*ታዲያ በዚህ ሂደት ውስጥ አንጎል በላይኛው ህብለ-ሰረሰር ሲወከል፤ የሁለተኛው እርከን ቆንጽላ የሆኑት ደግሞ ኩላሊትና ከበላዩም ያለው ‹አድሬናል›[62] ዕጢ ናቸው። በጭንቀትና ፈተናዎች ጋር ተያይዞ የሚመነጭ ‹ኮርቲሶል›[63] የሚባል ሆርሞንም ዋነኛው መልእክተኛቸው ነው። ከአደጋ ለማምለጥ አልያም አደጋን ለመጋፈጥ ታስቦ የሚመነጭ[64] ሲሆን በተጨማሪ ፍርሃቶች፣ ጭቅጭቆችና ትናንሽ ጸቦች፣ ንዴትና ብስጭቶች እንዲሁም ሌሎች የስሜት ዋልታዎችን ይፈጥራል። ይሄን የቅርብ ክፍለ ዘመናት የህክምናው ዓለም ግኝት የቀደሙ የጥበብ*

62 ከኩላሊቶቻችን በላይ ባለ ስብ ተሸፍኖ የሚገኝ ዕጢ፤

63 በአደጋ፣ በጭንቀትና በፍርሃት ጊዜ ከአድሬናል ዕጢ የሚመነጭ ሆርሞን

64 Fight, Flight or Freeze response;

አባቶች ያውቁት ነበር። ለምሳሌ ሊቀ-ትጉኃን ንጉሥ ዳዊት "የኃጥአን ክፉት ይጥፋ፥ ጻድቁን ግን አቅና፤ እግዚአብሔር ልቡናንና ኩላሊትን ይመረምራል።"[65] ይልና፤ በሌላ ቅዱስ ቃሉ ደግሞ ኩላሊቶቹን ተጽእኖ ፈጣሪ አካላት እንደሆኑ ሲጠቅስ "የመከረኝን እግዚአብሔርን እባርካለሁ፤ ደግሞም በሌሊት ኩላሊቶቼ ይገሥጹኛል።"[66] ይላል። ጠቢቡ ሰሎሞን በበኩሉ በመጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ ሃያ ሦስት እንደሰፈረው "15፤ ልጄ ሆይ፥ ልብህ ጠቢብ ቢሆን ልቤ ደግሞ ደስ ይለዋል፤ 16፤ ከንፈሮችህም በቅን ቢናገሩ ኩላሊቶቼ ደስ ይላቸዋል።" ብሎ ይመክራል።

ጥበብ ከዚህ ግድም አለ፤ እነሆ የጠቢባን አስተምህሮ ሥረ-መሠረቱ አንድ ነው። መልእክቱም በዝርው ከመናገር ይልቅ የጥበብን ቅዱስ ቃል መስማት፣ ከመናደድ ይልቅ መታገስ፣ ከመቸኮል ይልቅ ማስተዋል ዋጋ እንዳለው የሚያሳይ ነው። ከዛሬ ቀቢፀ ፌሽታና ተበርቻቻ ይልቅ የነገን ጠሊቅ ደስታ አስቦ መታገስ ታላቅ ጥበብ ነው።[67] የነፍስ እርካታ ለዛሬ ብለን ሳናቻኩል ለነገ ያሳደርነው፣ ያበሰልነው የህይወት ስንቅ ነው። በጽናት ዛሬ የተለፋበት የነገ ስኬትም እንዲሁ ውብና ያማረ ነው። ስሜታችንን ተቆጣጥረን ከተመሰጦና እውቀት በኋላ የምናወጣት ቃል ከችኮላ ስህተትና ፀፀት ታድናለች። ይህቺም እውነተኛ፣ ትሁት፣ ፍትሐዊ፣ ቀጥተኛና ትርጉም ያለው ለዘብተኛ ንግግር ውስጥ የምትገለጥ ቃል ነች።

ላስተዋይ ሰው ዝምታ የኑሮ ቀንዲል ነው። ዝምታ ማለት ግን ድምጽ አልባነት ብቻ አይደለም። ከጥንስሱም ድምጽ አልባነት በፍጥረታት ዓለም በምሉዕነት አይገኝም። ፍጹም ጸጥታ የሚባል ነገር በዚህች ህዋ ውስጥ የለም። ፍጥረት የራሷ ዜማ አላት። የተከፈተ ጆሮ ያለው ሁሉ የፍጥረትን ሙዚቃ ያዳምጣል። ለምሳሌ ፀጥ ያልኹኝ ነኝ ያለ ማንም ሰው እንዳንተ ከከተማው ተገልሎ ለብቻው ቢቀመጥም ዙሪያው ላይ ያለ የንፋስ ሽውታ፣ የአፈሩ ኮሽኮሽታ፣ የውኃው ጨዋታ፣ የአውሬ ጩኸት፣ የወፎች ዝማሬን መሰል ድምጾችን መስማቱ አይቀርም። ጆሮውን በእጁ፣ ሀሳቡን በአንጎሉ ደፍኖ በተመስጦ ዓለም ቢያደባ እንኳን ሳንባው ዓየር ሲያስገባና ሲያስወጣ ይሰማዋል፣ ልቡ ሲመታ ይታወቀዋል፤ እነዚህን እንደምንም ረስቶ ከፍ ያለ የጸጥታ ደረጃ ላይ ቢወጣም ጆሮው ውስጥ

65 መዝሙረ ዳዊት

66 መዝሙረ ዳዊት 16:7

67 Delayed Pleasure

*ያሉ የደም ቧንቧዎች ሲሞሉና ሲጎሉ ይሰሙታል:: ሰውዬው የሚሰማው ምንም ድምጽ የለም ብንል እንኳን የሰው ልጅ ጆሮ መስማት የሚችለው የድምጽ እርግብግቢት መጠን ውስን መሆኑን መርሳት የለብህም::*[68] *እናም እውነተኛ ጸጥታ ከፍጥረታት ዘንድ ሊኖር አይችልም:: ለዚህም መሰል ኢዮብ "የዝምታን ድምጽ ሰማሁ" ያለው:: እነሆ በፍጥረት ቀመር ውስጥ ዝምታ ያልነው ጸጥ ማለት እንዳልሆነ ሊገልጽ ይህንን ብሏል::*

*እናም በነፍስና መንፈስ ምጥቀት ውስጥ ካልሆነ እውነተኛ ዝምታን ማጣጣም አዳገች ይሆናል:: በሥጋዊ አካላችንና ምላሳችን አለማውራት ብቻውን ዝምታን አይወክሉም:: ይህንን እውነት በሚገባ ልብ ትል ዘንድ ደግሜም እልኻለሁ፡ ዝምታ ጸጥ ማለት ብቻ አይደለም:: ከዚያ ይልቅ በረብሻ ውስጥ ያለ የከተማ መናኝ የመሆን ጥበብንም አዝሏል::"*

"በእውኑ እየገባኝ ነው። ግን ዝምታ በፍጥረት ውስጥ የለም ያሉኝ በሌላ መልኩስ ሊብራራልኝ ይችላል?" ጠየቀ ሶፎኒያስ።

*"ምን መሰለኽ? ልጅ ሶፎኒያስ! ዝምታ ጸጥታ አይደለም ስልህ በሰበብ ነው:: ምክንያቱም እውነተኛ ጸጥታ ከፍጥረታት መገኘት በፊት፡ ከፈጣሪ ዘንድ ብቻ የነበረ ነው:: ያ ፍጹም ጸጥታና መዐልት፤ ሁሉም ከሁሉም ጋር አንድ ሆኖ የነበረበት፡ የምልዐት ስክነት ___ በአንዲት ቃል ከተዋጀ፣ ኹን ብሎ ከኾነ፣ ዜሮ የነበረው ሞገድ በአዎንታና አሉታ መካከል ተርገብግቦ፤ ህዋ አክናፋቷን ዘርግታ ከተርገፈገፈች በኋላ እውነተኛ ጸጥታ የሚባል ነገር ተፈጽሟል - ፍጹም ሰላምም በጠፈር ውስጥ ተጠፍሯል::" አሉና ባለ ብርቱካናማ ቀሚስ የዜማ መልዕክተኛ ገለጻቸውን ለአፍታ ገታ አደረጉ::*

"እሺ ሁሉንም እውቀት ከልቤ ተቀብያለሁ፣" አለ ሶፎኒያስ... "የዝምታ *ዜማ ግን ምንድነው?"*

*"ዝምታ ከምንም በላይ ወደ ጥበብ ዘንበል ትላለች:: ዝምታ ዘማም የሆነ ዜማና ግጥም አላት:: ቅኔና ምት አላት::*[69] *ከጆሮ በላይ የሆነ መዝሙር ትዘምራለች፣ የህሊናን ዘፈን ታዜማለች:: ሙዚቃና ውዝዋዜም በውሉ ካየኻቸው ከዚህ እውነታ ጋር የተያያዙ ናቸው::*

---

68 የሰው ልጅ ጆሮ መስማት የሚችለው ፍሪኩዌንሲ ከ20hz – 20000hz ድረስ ብቻ ነው:: ከዚህ ወሰን ውጪ ያሉ የድምጽ እርግብግቢቶችን ከሚያዳምጡ እንስሳት መካከል ዝሆን አንዱ ነው::

69 "በነፍስህ ጎጆ ውስጥ እልፍ ቃላት የማይገልጡት ዜማ አለ::" ሩሚ፤

አንድ ጥሩ የጥበብ ሥራ ለማቅረብ ብዙ የዝምታና የዝግጅት ጊዜ ያስፈልጋል። ዓለማችንን የለወጡ ትላልቅ ግኝቶች የፈለቁት ከብቸኝነትና ከዝምታ ውስጥ ነው። ከዝምታ ውስጥ ፍጥረት በሙሉ ተወልዷልና ዝምታ ውስጥ የፈጠራ ችሎታ ይዳብራል። የማስታወስ ብቃትም ይጨምራል። ተሰጥኦን ለማውጣት ተመስጦ የግድ ያሻል። እንዲሁ ሙዚቃን ከሙዚቃ ምን ይለየዋል ብትል ሙዚቃው ከመውጣቱ በፊት ለምን ያህል ጊዜ በዝምታ ታስቦበታል? ምን ያህል ጊዜስ በዝምታ ተደጋግሞ ተደምጧል የሚለው ነው።[70] እነሆ በእያንዳንዱ ምትና ዜማ መሐል እጅግ በጣም አጭር የጸጥታ እረፍቶች ባይኖሩ አንድም ሙዚቃ በዓለም ላይ ባልተፈጠረ ነበር። ጥሩ ዘፋኞች ጥሩ ጆሮ አላቸው የሚባለው ለዚህስ አይደል?[71] ነገር ግን ጥሬ አድማጭ ለመሆን የጆሮ መኖር ብቻ በቂ አይደለም። ይህንን እውነታ ፈጣሪ በቅኔ ሲነግረን ግዙፉ የዝሆን ጆሮ እኩል እግሩንም የሚሰማ አድርጎ ፈጠረው።" አሉና በፈገግታ አስተዋሉት፤[72]

*{የዝሆን እግሮች በተለይ ከሩቅ የሚመነጩና ትናንሽ እርግብግቦሽ ያላቸውን ድምጾች የሚለዩ ሲሆን ግዙፍ ጆሮዎቻቸውም ድምጾችን ከመሰብሰብ በላይ የውስጣዊ ሙቀት የማስተንፈስና በዝሆኖች መካከል የምልክት መግባቢያ ሆነው እንደሚያገለግሉም የቅርብ ጥናቶች ጠቁመዋል፤ እነዚህ ምን ግዙፍ ቢሆኑም በእርጋታና ዝምተኝነታቸው የሚታወቁ እንስሳት በእድሜ ዘመናቸው እንቅልፍ የሚባል ነገር በዓይናቸው አይዞርም።}*

ሽማግሌው መምህር ቀጠሉ - "ይህንን እወቅ፤ መስማት ያለው ከዝምታ ነው። ውበትም ያለው ከመጮኹ ሳይሆን ከመመሰጡ ነው። እናም ዝምታን ከመሰል ጥበቦች ውስጥ መፈለግ ያላየኻቸውን ቅጽበታዊ የአብርሆት በሮች ይከፍትልኻል። በነዚህ በሮች ውስጥ ከሚመላለሱትም ጋር ትገናኛለህ። ይህንንም የመገናኛ አውታር እንለዋለን። በዚህ እልፍ የዝምታ ቅንጣቶች ውስጥም ሰው ሳይነጋገር ይግባባል።

---

70 ለዚህም በዝምታቸው ውስጥ ለወለዱልን ጥዑም ዜማዎች እንደ ሙሉጌታ አባተ፣ይልማ ገብረዓብ፣አበበ መለሰ፣ኤልያስ መልካን መሰል የትውልድ ፈርጦች ማመስገን ይገባል፤

71 ጥናቶች ጥሩ ሙዚቃዎችን በተደጋጋሚ የሚሰሙና የሚያዘጋጁ ሰዎች አንዳንድ የአእምሮ ክፍሎቻቸው ይበለጥ ያደጉና ፈጣን እንደሚሆኑ አረጋግጠዋል፤

72 "ዝሆኖች ያንን የሚያክል ጆሮ ቢኖራቸውም በተለይ ከሩቅ የሚመጣን የድምጽ ሞገድ ለመለየት እግሮቻቸውን ይጠቀማሉ። ጆሯቸውን እንደ ቬንትሌተርም ይጠቀሙታል።

ሌላው የምመክርህ የሐሳብ ዜማ የሌለው፡ አንደበታዊ ንግግርህን መቆጠብ እንድትለማመድ ነው:: እጅግ አስፈላጊ ካልሆነ አንዳች አትናገር:: ያኔ ብቻ ባዶ በርሜል አብዝቶ ይጮኻል የተባለው ምሳሌ ይገባኻል:: ብሮች ዝም ብለው ለምን ሳንቲሞች እንደሚንኮሻኮሹ ትገነዘባለኽ::

*{ማንም ሰው ለሙከራ ያኽል በየቀን የሚያወራቸው ቃላት በግማሽ ቀንሶ ቀኑን ቢያሳልፍ ልዩነቱን ያየዋል:: የነፍስን እውነተኛ፣ ዘላቂ መቆበድ[73] ይጎናጸፋል::}*

*አንተም ይህን ብታደርግ ከምታስበው በላይ ውስጥህ በሰላም ይሞላል:: አርምሞ ማለትም ሌላ ምንም ሳይሆን በእለት ተእለት ህይወትህ ላይ ውስጣዊው የሰላም ማእበልህን የመቆጣጠር ብቃት ማለት ነው:: ያኔ ውጫዊ ድምጾችና ረብሻዎች የውስጥን የሰከነ ባህር አያደፈርሱትም:: የ‹ሚዲያ› ድግምቶች[74] አያደነዝዙኽም::*

*አንተ! በአርምሞ ሞገድ ውስጥ ስትቀዝፍ ቃላቶችህ ዋጋና ውበት ይኖራቸዋል:: በየቦታው የሚዘሩ ርካሽ ልፈፋዎችም አይሆኑም:: እንደ እንቁ የከበሩ፣ እንደ ወርቅ የነጠሩ፡ ዘላለማዊ ዝማሬዎችን ይመስላሉ እንጂ:: እናም ከማይረባ ቃል ውብ ዝምታ እጅጉን ይሻላል:: ያማረ ውስጣዊ የዜማ ኸረትም በውጫዊ ጩኸት አይደፈርስም::"*

* * *

73 ደስታ፤

74 ድግምት ማለት አንድን ነገር እየደጋገሙ በማሰብ፣ በመጥራት፣ በማድረግ ወደ እውነታ የመቀየር ሂደት ነው:: በተለይ ባለንበት ዘመን እንደ ቲቪና ሞባይል ባሉ አውታራት ህዝብ ይደገምበታል አልያም ሳያውቀው ሂፕኖታይዝ ይደረጋል:: አንድን ውሸት፣ ስህተት የሆነ ተግባርም ሆነ መረን የለቀቀ ባህሪ በተደጋጋሚ ለህዝቡ በማሳየትና በማሰማት ሰው ጉዳዩን ትክክለኛና እውነተኛ እንደሆነ እንዲያምን ይደረጋል:: ለምሳሌ በልብ አንጠልጣይ ፊልም ልቡ የዋጀጀ ሰው በፊልሙ ውስጥ የሚከሰቱ ነገሮችን ሳያስበው ሙሉ በሙሉ ወደ ኋለኛው/አመክንዮ የማይሻው Subconcious አእምሮ ክፍል ያጠራቅማል:: ይሄንን የድግምት መንገድ ከሚጠቀሙት መካከል ትላልቅ ዓለም አቀፍ የዜና ተቋማት የሚጠቀሱ ሲሆን የውሸት ወሬን እንኳን በድግግሞሽ ብዛት እውነት አድርገው መስበኩን ተክነውበታል:: እናም የምናይ፣የምንሰማና የምናምነውን እንምረጥ!

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ውስጣዊው ጉዞ

ቬራ ከአዲሱ ቤቷ፣ ከአዲሲቷ ሀገሯ ጋር በፍቅር ወደቀች። ኢትዮጵያን ለጉድ ወደደቻት። የአየር ሁኔታዋ፣ መልክዓ ምድሯ፣ የተመጠነ የፀሐይ ብርሃኗን እያጣጣመች በየቀኑ በደስታ ብርሃን ትሞላ ይዛለች። {የሰው ልጅ ሲፈጠር እንዲኖር የታቀደው ኢትዮጵያ ውስጥ ይመስላል። ፀሐይ ሳትበዛ ሳታንስ በእኩሌታ ሚዛን፡ ሙቀትና ብርሃኗን የምትለግሳት፣ ቀንና ማታዋ በእኩሌታ የተመጠነ፣ ከላይ በሚያረሰርስ ዝናብ፣ ከታች በተዘረጉ ወንዞች ልምላሜዋ የሚዘወትር፣ ነፋሻማው አየሯ ወላፈንና ቆፈንን በእጅጉ ቀንሶ የተለሳለሰበት፣ መሬቷ የሰጡትን የሚያበቅል፡ ብሎም በእልፍ ማእድናት የታጨቀ። በመሬት መንቀጥቀጥ፣ በጎርፍና አውሎ ንፋስ እንብዛም የማትጎበኝ፣ ቅድስት ምድር ለመሆኗ ከነዋሪዎቿ ይልቅ ባዕዳን ምስክር ናቸው። በዓለም ኢኮኖሚና ፖለቲካ ቁልፍ የሆነ አካባቢ ላይ መቀመጧም የማያስተውሉ ባንዳዎች ያልገባቸው እነርሱ ይገባቸዋል። አንዳንዴም ክፉ ባዕዳን ከጎምጂነት ወደ ወራሪነት እየተቀየሩ/ በየዘመኑ ሊወሯት እያሰፈሰፉ መጥተው ባይሳካላቸውም ለሀጫቸውን እያዝረበረቡ፡ በምኞት መጎምጀታቸውን አላቆሙም። እሷ ግን የምድር ገነትነቷ የሚገባቸው ልጆቿን ብቻ ጥማት የምታረካበት እጹብ ጠበል አላት። ለናቋት መራራ፣ ለተራዷት የምትራራ፤ የፍጥረት-ሐይቅ፣ የጸጋ ሰማይ፣ የታሪክ ሜዳ፣ የእምነት ተራራ ናት።}

ቬራ በተለይ የአያቶቿን ታሪክ ስትሰማ ከራሺያዊነቷ ጎን ለጎን ኢትዮጵያዊነቷም ግዝፍ እያለባት፤ በዚህች ሀገር ፍቅር ተጠልፋ ወድቃ ለአመታት ቆየች። ብዙ ሰውኛና እንቶኔ ቁርኝቶችን ስለዘረጋች ተመልሶ መሄዱ አልሆንልሽ አላት። ኢትዮጵያ ተዋሃደቻት። እርግጥ የቤተሰቧ ናፍቆት አለ። ከዚያ በላይ ደግሞ ሳታገባ፡ ሳትወልድ በሰው ሀገር እድሜዋ

እየገፋ መሆኑን ስታስበው ያሳስባታል። ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ኢትዮጵያን ልትተዋት አልቻለችም። ከሁሉም ከሁሉም ደግሞ ከሆቴላቸው በስተ ቀኝ ጥቂት ርቀት ተጉዛ የምታገኛት፡ ከሰው የተገለለች ኮረብታማ ስፍራን እጅግ ትወዳታለች። ቢያንስ በሳምንት ሁለቴ እየሄደች በጽሞና ትቀመጣለች። አንዳንዴማ በማለዳው ተነስታ፣ ቡልኮዋን ደርባ፣ በሹራብ ኮፍያ አናቷን ሸፍና ወደ ኮረብታው ስታቀና ላያት ልታስቀድስ የምትሄድ አቃቢት እሴቴ ትመስል ነበር።

ሁሌ ከጉብታው እንደደረሰች፡ ቁጢጥ ብላ፡ መልክአ-ምድሩን በደስታ ስሜት ተሞልታ ትቃኛለች። የልቧን ንሥር ወደ ሰማይ ሰዳ ከእያንዳንዷ የምድሪቱ ቅንጣት ውበት ጋር በጥልቀት ትናበባለች። ቀልቧን ሰብሰብ አድርጋ በአተነፋፈሷ ውስጥ በአመስኳ ትወዘወዛለች። ከተፈጥሮ ጋር ትወያያለች፣ ከራሷ ጋር በዝምታ ትነጋገራለች። ራሺያ ሳለች በ‹ኦን ላይን› የተማረችውን የሜዲቴሽን ስልጠና ትተገብራለች። ዝም ላለች ነፍስ ፍጥረት ትታዘዛለች እንዲሉ ለሷ የሚገለጥላት የተፈጥሮ ውበትና ትርጉም ለሌላው አይገባው ይሆናል። እሷ ግን ተማርካለች።

ታዲያ አንድ ቀን እንዲሁ እንደለመደችው የጥሞና ልምምድ ላይ ሳለች ወደ ማታውቀው ጥልቅ የተመስጦ ዓለም ተጓዘች። መጀመሪያ እንደ መፍራት ብላ ነበር። አንድ ከየት እንደመጣ ያላወቀችው የጽሞና ዓለም ነበር የገጠማት። ስለፈራች... ልቧ በኃይል ይመታ ጀመር፤ ትንፋሽ አጠራት፤ ሰውነቷ ጋለባት፤ ከራሷ ሰውነት ተላቃ በአንገሏ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ የምትገማሸር፡ ሚጢጢ ነፍስ የሆነች መሰላት። እንደምንም ውስጧን ሰከን ማድረግ ስትጀምር፡ ከየት እንደመጣ ያላረጋገጠችው ድምጽ በምናቧ ጓዳ አቃጨለ።

ድምጹ ልክ እንደ ፈጣን የስልክ ጥሪ ምልክት በአእምሮዋ ብልጭ ብሎ ጠፋ። የሆነ ሰው በ‹ቴሌፓቲ›፡ ገመድና በይነ መርብ አልባ የአእምሮ ጥሞናዊ ኃይል ሊያናግራት እየሞከረ ነበር። እስካሁን አጋጥሟት የማያውቅ ልምምድ ቢሆንም ስትፈራ ስትቸር የሚላክላት የሐሳብ ሞገድ ለማነፍነፍ ሞከረች - የአቅሏን አንቴናዎች ዘረጋች። ቀስ በቀስ የሞገዶቹ ኃይላት ቅርጽ እየያዙ ወደ ቃላትነት ሲቀየሩ ይታወቃት ጀመር። መልእክቱን ለመተርጎም ሞከረች። እኮ ማነው? ... በመጨረሻም አራት ቃላት እየጎሉ መጡና በምናቧ ሙክራብ ነገሡ። ... "መ ... ር... ዕ... ድ... ።"

⌘ ⌘ ⌘

## ጨው በረንዳ

## የለይኩን ፍርድ ቤት መቅረቢያ ቀን፤

ኤልሳ ዛሬ ላይም ቆማ በልጅነቷ ያሳለፈችው ህመም ትዝ ሲላት ትውስታው በራሱ አንገሸገሻት። ትዝታዋን የምታራግፍ ይመስል ጸጉሯን መንሸር መንሸር አድርጋ፤ ልጇን አፈፍ አድርጋ አቅፋ ከግቢው ወጣች። በር ላይ ሲጠብቃት የነበረው አበጋዝ የመኪናውን በር ሲከፍትላት ገባች። መኪናዋ እየተጣደፈች ወደ ፍርድ ቤት አቅጣጫ ከነፈች።

⌘ ⌘ ⌘

ሜሮን ከሁሉም ሰው ቀድማ ነበር ከፍርድ ቤቱ አዳራሽ የተሰየመችው። ምናልባትም መራመድ አቅቷቸው ከቤት ባይቀሩ ኖሮ የለይኩን እናት ብቻ ሊቀድሟት ይችሉ ነበር። ዛሬ ጥዋት ግን ጥበቃው ብቻ ነው የቀደማት፣ እርሱም ቢሆን እዚያው ስላደረ እንጂ ቀድሟት አይደለም። የትናንቱንም ሌሊት ሳትተኛ እንዲችው እንደፈጠጠች ነበር የነጋባት። የለይኩንን መጨረሻ እያሰበች ስትጨነቅ፡ ስትጠበብ አደረች። ነፍሷ እስኪወጣ የምትወደው ሰው በማታውቀው ምክንያት ለችሎት ቀርቧል። የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ምንም ሊሆን ይችላል። እሷ ግን አንዳች ክፉ ነገር ስለ እሱ መስማት አትፈልግም። ከራሷ በላይ ትጨነቅለታለች። የምትወደው እንዲሁ እንጂ በምክንያቶች አይደለም።

ቀስ በቀስ የፍርድ ቤቱ ወንበሮች ሞሉ። ታዛቢዎች፣ አቃቢ ህጉን ተከትለው አበጋዝና ኤልሳ ገቡ። ሁሉም ሰዎች ቦታ ቦታቸውን ከያዙ በኋላ ዋና ዳኛው በግራ በኩል ካለው በር ገብተው የክብር ቦታቸውን ተቆናጠጡ። የእለቱ ፖሊስ ባደረገው ጥሪ መሠረት አቃቢ ህጉ የክሱን መዝገብ ማነብነብ ጀመረ።

"ተከሣሽ አቶ ለይኩን ተስፋሁን፤ የጋራዥ ሠራተኛ የነበረ ወጣት ሲሆን በዚህ ሥራው ዙሪያም ጅብሪል ነስረላህ የተባለ ሌላ ጎልማሳ ጋር በሻሪካ በመሆን አንድ ጋራዥ ይከፍታሉ። እናም ይህ ጅብሪል ነስረላህ የተባለ ሠራተኛ በጣም በሥራው አንቱ የተባለ ነበርና ጋራዡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍተኛ ገቢን ማስገባት ይጀምራል። ይሄንን የትርፍ መካበት በቅርብ ሆኖ ሲከታተል የነበረው ተከሳሽ አቶ ለይኩን ተስፋሁን የሚያገኙትን ሀብት ለብቻው ለመቀራመት ሲያደባ ይቆያል።" አለና አቃቢ ህጉ ወደ ለይኩን ዞሮ በክፉ ዓይን ረመረመው። ለይኩን በበኩሉ ህልም ይሁን ፈልም ባልገባው ሂደት ውስጥ ሃውልት መስሎ ተገትሯል።

"እናም አንድ ቀን የሁኔታዎችን መመቻቸት ተጠቅሞ የጅብሪልን ምግብ ይመርዛል። የተመረዘ ምግብ የተመገበው ጅብሪልም ቀስ በቀስ ለከፍተኛ የጤና መቃወስ ይዳረጋል። ነገር ግን ተከሳሹ እንዳሰበው ቶሎ ህይወቱ ልታልፍና እንዳቀደውም ሀብቱን ለብቻው መቀራመት አልቻለም። በመጨረሻም በሰኔ 16 1998 ዓም ጥዋት ላይ... እዚያው ጅብሪል ታሞ የተኛበት ቤቱ ድረስ በመሄድ፤ በትራስ አፍኖ ህይወቱ እንዲያልፍ አድርጎታል።" ብሎ አስረግጦ ተናገረ፤

ስሜቱን መቆጣጠር ያቃተው ለይኩን... "እኮ እኔ ጅብሪልን ገደልኹኝ?" ብሎ ተወራጨ፤

"ሥነ-ሥርዓት!" ሲሉ አዘዙ ዳኛው፣ ቤቱ በጸጥታ ተሞላ። "አቃቤ ህግ ቀጥል..."

"አመሰግናለሁ ክቡር ዳኛ፡ እናም አሁን እንደሰማችሁት ተከሣሹ ወንጀሉን መፈጸሙን ቢክድም የህክምና ምርመራ ማሥረጃዎችና የአሻራ ምርመራዎች ወንጀሉን መፈጸሙን ይጠቁማሉ። ከዚህም በተጨማሪ ሦስት የሰው ምሥክሮችም አሉን። ክቡር ፍርድ ቤቱ የሚፈቅድልኝ ከሆነ ሦስቱን ምስክሮች ተራ በተራ ብጠራና ምስክርነታቸውን ቢሰጡን...?"

"ተፈቅዷል!" አሉ ዳኛው በፍጥነት፤

የመጀመሪያው ምስክር ተጠራ። አንድ የጋራዥ ቤቱ ተቀጣሪ ሠራተኛ ነው የተባለ ወጣት መጣ። ለይኩን ይህን ወጣት ከተፈጠረ ጀምሮ አይቶት አያውቅም። ምስክሩም በቦታው ቀርቦ ለይኩንና ጅብሪል በገንዘብ ጉዳይ ከፍተኛ ፀብና መዛዛት ውስጥ ሲገቡ እንደተመለከተ መስክሮ በመጣበት ተመለሰ። ቀጣይ ደግሞ የጅብሪል ጎሮቤት ነኝ ያለች አንዲት ሴት እየተቅለበለበች መጣች። እርሷም በተራዋ ጅብሪል ያረፈ ቀን ለይኩን ቤቱ እንደነበርና ተጠራጥራ ስትገባ በእጁ ትራስ ይዞ ከአልጋው አጠገብ ቆሞ እንዳየችው፤ ዓይኔን ግንባር ያድርገው ብላ መሰከረች።

የሦስተኛዋ ምስክር ስም ሲጠራ ግን ሜሮንም፡ ለይኩንም ክው አሉ። ... ኤልሳ ምንም እንዳልተፈጠረ ሁሉ ጣደፍ ጣደፍ እያለች ገብታ ከምስክርነት መስጫው ጉብታ ላይ ቆመች። በወገቧ ያቀፈችው መርዕድ የሚያፈጥበት ሰው በዛበተ መሰል ጭንቅ ብሎት ከእናቱ ጉያ ውስጥ ውሽቅ ብሏል። ለይኩን የሚሆነው ነገር ግራ ግብት ብሎት አሁንም እንደ እንጨት ደርቆ ቀርቷል፤ ሜሮን በበኩሏ ይሄ ሁሉ ክፋት ቅዠት እንዲሆን

ፈጣሪዋን እየተማፀነች ነበር።

"እሺ ስምሽን ለክቡር ፍርድ ቤቱ ልትነግሪን ትችያለሽ?"

"ኤልሳ ቦጋለ እባላለሁ።"

"ሃይማኖትሽ ምንድነው ወ/ሮ ኤልሳ?"

"ክርስቲያን ነኝ።"

አቃቤ ህጉ ባዘዛት መሠረት ኤልሳ ከፊቷ የነበረው መጽሐፍ-ቅዱስ ላይ እጇን ጭና የምትሰጠው ምስክርነት በሙሉ እውነት እንደሆነ ቃል ገባች።

"እሺ ወ/ሮ ኤልሳ፣ ከተከሳሽ አቶ ለይኩን ጋር የነበርሽን ግንኙነት ማወቅ እንችላለን?"

"የቀድሞ ባለቤቴ ነበር፤ የወንድ ልጄም አባት ነው።" አለች፤ በታው ላይ ከቆመች ጀምሮ አንገቷን ቀና ስታደርግ አልታየችም።

"እሺ ተከሳሹ ጋር አብራችሁ በነበራችሁበት ጊዜያት ስለጅብሪል ያለው ምልከታ ምን አይነት ነበር።"

"ያው በሽርክ ነው አብረው ሥራ የጀመሩት፤ ጥሩም ገቢ እያገኙ ነበር። የኋላ ኋላ ግን ለይኩን በጅብሪል በጣም መቅናት አበዛ። ትርፉን ለብቻው ቢያገኝ ኑሯችንን መለወጥ እንደሚችል ደጋግሞ ይነግረኝ ነበር። ይሄን ሐሳብ ተው ብለውም አልሰማ ብሎኝ ነበር።"

ለይኩን ጆሮዎቹ ተዘግተው ቢፈጠር ተመኘ። አለማመን፣ ሀዘንና ንዴት ተፈራረቁበት። ውስጡ እ ርር... ድብን... ብግን ከማለቱ ብዛት ንዴቱ ገንፍሎ ወጣ፤

"አንቺ ዋሾ!... የወደደሽን ልብ ሰባሪ፣ ያጎረሰሽን እጅ ዘንጥልሽ አቁሳይ!... እኮ እኔ ነኝ ለጅብሪል ክፉ የማስበው?" ... መቀጠል አልቻለም... ተንዘፈዘፈ.. ልቦናው ተረበሸ፣ ህሊናው ተቃወሰ፤ *{እንዴት የሰው ህሊና ይጨልማል? የብርሃንን ፈለግ ትቶ የፍልፈልን ጉድጓዶች ይከተላል? እንዴትስ ከጥቅማ ጥቅም ጎሬ ገብቶ ይወሸቃል? እኮ ወሰን የለሹ ህሊና እንዴት በውሸት ቃላት ይበከላል... እኮ እንዴት?}* ከነፍስያው ተሟገተ፤

"ሥነ-ሥርዓት!" የሚለው የዳኛው ቁጣዊ ትእዛዝ ወደ ቀልቡ መለሰው፤

"ክቡር ዳኛ፡ እኔ አንዳችም ነገር አልዋሸሁም!" አለች ኤልሳ፤ "ዛሬ በዚህች ምላሴ እየዋሸሁ ከሆነ ይሄ ከእቅፌ ያለ ህጻን ልጄ አንደበት ተዘግቶ ይቅር።" ብላ ማለች፣ ወዲያው በእቅፏ ያለው ህጻን መርዕድ እሪ ብሎ አለቀሰ| በግጥጥሞሹ ትንሽ እንደመደናገጥ አለች፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ቀና ብላም ታዳሚውን በድንጋጤ ተመለከተች። ከሁሉ ከሁሉ ግን የሁለት ሰዎች ዓይን ጦር ሆኖ ወጋታ። ከባድ ነበርና በድጋሚ አንገቷን ደፋች።

"ሰውን ባትፈሪ ፈጣሪን ፍሪ!" ለይኩን ቃተተ፤

"ክቡር ፍርድ ቤት፡ ሥነ-ሥርዓት እየተጣሰ ነው!"... አቃቤ-ህጉ ስሞታ አሰማ፤ ዳኛው ቀበል አድርገው ተናገሩ... "አቶ ለይኩን? ከዚህ በኋላ የፍትህ አካሄዱን የምትረብሽ ከሆነ ቅጣት እንደሚከተልኽ እወቅ!" ብለው አስጠነቀቁትና ለአቃቤ-ህጉ ቀጥል የሚል ምልክት ሰጡት። አቃቤ ህጉ ወደ ኤልሳ ተጠግቶ... "እሺ ኤልሳ አንድ የመጨረሻ ጥያቄ ልጠይቅሽ... በሰኔ አስራ ስድስት አስራ ዘጠኝ ዘጠና ስምንት ዓ.ም... ማለትም ጅብሪል ባረፈበት ቀን የተከሰተውን ነገር እስኪ ንገሪን?" ብሎ ጠየቃት፤

"እሺ ... እም... በእለቱ ለይኩን ከወትሮ ቀደም ብሎ ነበር ወደ ቤት የተመለሰው። ለየት ባለ መልኩ በጣም ተጨናንቆ ነበር የመጣው፤ ልብሱን አወላልቆ አዲስ ልብስ ቀየረና ወዲያው ተመልሶ ወጣ... ለምን እንደተቻኮለ ስጠይቀው አንድ መጥፎ ስህተት እንደሠራ ነግሮኝ እየተጣደፈ ሄደ። ሁኔታው በሙሉ ደስ አይልም ነበር። ከቀናት በኋላም ሳያስበው በድንገት ጅብሪልን እንደገደለው እያለቀሰ ተናዘዘልኝ። እሱን ትቼ ከቤቱ ለመውጣትም ዋነኛው ምክንያቴ ይሄ ነበር።" ብላ ጨረሰች፤

"አመሰግናለሁ፤" አለ አቃቤ ህጉ፤

... ኤልሳ ምስክርነቷን ስትጨርስ፡ ልጇን እንዳቀፈች፡ እንደ አመጧጧ ወደ በታዋ ተመለሰች። ታዛቢዎች ክቡር ዳኛው ውሳኔ ለማሳለፍ ቀነ ቀጠሮ ይሰጣሉ ብለው ነበር የጠበቁት። እርሳቸው ግን ቀጠሮም ሳያሻቸው ከደቂቃዎች በኋላ ወደ ውሳኔው ገቡ። "ግራ ቀኙን አይተን፣ የምስክሮችን ቃል ካዳመጥንና ሌሎች ማስረጃዎችን ካጣራን በኋላ ተከሳሽ ለይኩን ተስፋሁንን ነፍስ በማጥፋት ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ አግኝተነዋል። እናም በአስራ አምስት አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ፍርድ ቤቱ ወስኗል። ፋይሉ ወደ መዝገብ ቤት ይላክ።" አሉና በመዶሻቸው ጠረጴዛውን ነረቱት።

ወዲያው ፖሊሶች የለይኩንን ክንዶች አፈፍ አድርገው አነሱት። በኃይል

ጠፍንገው ይዘውት ሲወጡ ሜሮን እየተዳፋች ቀርባ ከፊቱ ተደቀነች። ፊቷ በእንባ ርሷል፣ ዓይኖቿ ከማልቀስ ብዛት ቀልተው፣ ጠበዋል። እንደሆነ ነገር እያደረጋት ነበር ፖሊሶቹን ሰነጣጥቃ የገባችው። ከፊቱ ስትደርስ እየተንሰቀሰቀች ተጠመጠመችበት። እሱም እንባውን መቆጣጠር አልቻለም። የማያልቅ የሚመስል ሀዘን ከመቅጽበት ዙሪያውን ሞላው። ከልቦቻቸው ያኮበኮቡ የመለያየት ቁራዎች ከበላያቸው ተንሳፈፉ። *{ለአመታት እንደሚራራቁ እያወቁ መተቃቀፍ ግን ምን ይመስላል? ማለት የመጨረሻዋ መነካካት፣ የመጨረሻዋ መደባበስ፣ አንዱ በአንዱ ውስጥ ውሽቅ ማለት ዋጋ ተመኑ ምን ያህል ነው? አጃቢውስ እረፍት ወይስ ሞት፣ ጊዜያው እፎይታና የዘመናት እጦት፤ እውነታው ከነፍስ አስኳል ሰርጾ ያማል!}* እነሆ ሜሮን ለጠላት የማይመኙት ህመም እያመማት ለይኩንን አቀፈችው፤ አንገቱን በመለያየት እንባ አርሳ፡ የሜሮናዊ ዘይት በፍቅር ቀባችው። ቀስ ብላ ወደ ጆሮው ተጠጋችናም አንድ ነገር አንሾካሾከችለት... *"ለይክዬ እርጉዝ ነኝ።" ... ዝምታ...ተተካ | እያቻኮሉ ይዘውት ወጡ፤ የእለቱ ተረኛ ዳኛ ስም ጌታቸው ተክሌ ይባል ነበር።*

⌘ ⌘ ⌘

ዶ/ር ሶፎኒያስ በተመስጦ ዓለም ውስጥ ጠልቆ ከገባ ሦስተኛ ቀን ሆኖታል። ባለ ብርቱካናማው ቀሚስ ሽማግሌም ምክራቸውን ቀጥለው ነበር፤ በምክራቸው መካከል ግን ድንገት ዞር ቢል ቀሚሳቸው ወደ ቢጫ ተቀይሮ ጠበቀው። በግራ መጋባት ስሜት አስተዋላቸው።

*እርሳቸውም መልሰው በሰከነ መንፈስ አዩት፤ "...አትደንግጥ፣ ልብስም ከግብር ጋር ይቀየራል። አሁን ያለነው ሦስተኛው እልፍኝ ውስጥ ነው። በአንጎላችን ኮርቴክስና ብሬን ስቴም የሚመሰል ሲሆን፤ ከዕጢዎችም ሙቀት፣ እድገትና ማብላላትን ባስተባበሩት ‹ታይሮይድ›ና ‹ፓራ-ታይሮይድ› እጢዎች የሚወከል እርከን ላይ እንገኛለን።"*

"እኮ እንዴት? ምንም ወደ እልፍኙ መዳረሻ መንገድ ሳንጓዝ?" ጠየቀ ሶፎኒያስ፤

"መንገዳችን የእግር መቼ ሆነና ልጄ፤ ዋሻዎቹ፣ ሸለቆዎቹ፣ ድልድዮቹም ሆኑ እልፍኞቹ በሙሉኮ ውስጥህ ነው ያሉት። የምትጓዘው ርቀት ወደ ውስጥ ለማየት ባለኽ ጥሞናና ማስተዋል ልክ ይወሰናል። የምትሄድበት ፍጥነት ደግሞ ራስህን ለማግኘት ካለኽ ቁርጠኝነት ይለካል። ለማንኛውም አሁን ያደረግነውን ፈጣን ሥፍረተ-ቦታ የመለወጥ ጥበብ መሰወር ወይንም

በተሻለ አጠራር ‹መስፈንጠር› እንለዋለን። ፈረንጆቹ ደግሞ ‹ቴሌፖርት› ይሉታል። ወደ ፊት በደንብ ትለማመደዋለኸ። ለጊዜው ሦስተኛው እርከን ላይ መድረሳችንን ዙሪያኽን ተመልክተህ ተረዳ..." ...ብለው በእጃቸው ክፍሉን እንዲያይ አመላከቱት። ሶፎኒያስ ዙሪያው ቢያማትር በእልፍ አእላፍ መጽሐፎች የተጠቀጠቀ፡ ሰፊ ቢጫ አዳራሽ ውስጥ ራሱን አገኘው። "ዋው! ይሄ ሁሉ መጽሐፍት፣ ቢጫ መደቡ ደግሞ ሲያምር!" አለ አንጋጦ ቤቱን በአግራሞት እያስተዋለ።

*"እነሆ ቢጫ የአብርሆት፣ የእውቀትና ንቃት፡ ፍክ ቀለም ነው:: እውቀት ስንል ግን በምዕራባውያን ተነድፎ በሚቀርብልን ዘመናዊ ትምህርት የሚገኘውን ብቻ እንዳይመስልህ:: እውቀት፣ በዋናነት ህይወትን፣ ምግባርን፣ ጥበብን፣ መንፈሳዊነትን፣ ማንነትን፣ መክሊትን፣ ከምንም በላይ ደግሞ ፈጣሪንና ራስን ማወቅን የሚያስቀድም መሆን አለበት:: ተፈጥሮን በጥልቅ ምርምርና ጥናት ማስተዋል፣ አኗኗርን ማበልጸግና ያልታየን የሚመለከት፣ ከአጥሮች አሻግሮ እያየ የሚያገናዝብ፣ የመፈላሰፍ ሐልዮትን ይሻል:: ለራሱ የእውቀት ድንበር ያበጀ ሰው በዘርፉ ብቻ ተጠቦ አዋቂ ሊባል ይችላል:: አዋቂ ግን አይደለም:: እውነት እውነት እልኻለሁ አለማወቅህ ገደብ የለውም፣ እውቀትህ ግን በእጅጉ ውስን ነው:: እናም አብዝተህ አላውቅም በል::*

*ለማወቅም የሚቀድመውን ነገር አስቀድመኽ እወቅ:: ራስህን ሳታውቅ ወደ ሌላ እውቀት አትቻኮል:: ለሁሉም እውቀት ጊዜና ቦታ አለው:: ለምሳሌ አሁን ግብህ ዝምታ ነውና ስለሱ እንነጋገራለን፤ እንግዲህ በዋናነት ልብ ማለት ያለብህ ነገር ማንም ሰው ከጫጫታው ተገልሎ፣ ከምግብ ርቆ፣ ሌሎች አሳሳች ግብዓቶችን ከራሱ አርቆ፡ በተአቅቦ ከተቀመጠና፤ በመንፈሱ ለመጎልበት ከሞከረ ራስን የማወቅና የመንቃት ቁልፍ ይቀርጻል፤ የህይወትን እውነተኛ ጣዕም ለማግኘት እጅግ ቅርብ ይሆናል:: የሆዱን ጎተራ ፈታኝ ጥሪ ማዘዝና መታገስ ከቻለ፣ የአጥንት አልባ ሥጋይቱን - ምላሱን አለንጋ ማጠፍ ከቻለ ሌሎች ውስጣዊም ውጫዊም ጩኸቶችን ለመቆጣጠር ይረዳዋል:: ራሳቸውን በአካልም በአእምሮም የእውነት አርቀው በብቸኝነት የተመሰጡ ሰዎች ትልቅ ደረጃን በእርግጥም ይጎናጸፋሉ:: ግን ከሁሉም በፊት የእውቀት ቀንዲል ቀድሞ መምጣት አለበት::"* አሉና በዝምታ የዶ/ር ሶፎኒያስን ስሜት ሲያነቡ ቆዩ - አንድ መስመር ላይ አገኙት:: በለስላሳ አንደበት ምክራቸውን ቀጠሉ::

*"ይህንን ስነግርህ... እወቅ፣ አስተውል ስልኽ፡ ታዲያ ሐሳብና ጭንቀት*

ሳበዛብህ ፈልጌ እንዳይመስልኽ:: እንዲያውም ላንተ እውነተኛ ደስታና ሰላምን ስለምመኝ፣ ካንተ አልፎም ብዙሃንን የሚጠቅም አስተምህሮ ታዳርሳለህ ብዬ ስለማምን ነው:: እናም ይሄን የዘውታሪ ደስታ ፍለጋ ጉዞ አድርገህ አስበው:: ከነፍስህ ጋር የሚጉላ ሽርሽር እንደወጣህም ቁጠረው:: ሽርሽሩ ግን እንዳልኩህ ወደ ውስጥ እንጂ ወደ ውጭ የሚኬድበት አይደለም::

የሰው የውስጥ ሀሳቡና ልቡ የጠለቀ ነው::[75] እንዲል ይሄ ጉዞ ጠሊቅ ነው:: የዚህ ህይወት ቀያሪ ጉዞ መንገዱ የተቀየሰው፣ አስፓልቱ የተነጠፈው፣ ሀዲዱ የተዘረጋው ደግመ ወደ ውስጥ ነው:: መዳረሻውም ወደ ጥልቁና ረቂቁ፣ በጥበብ ከፍ ወዳለው ማንነትህ እልፍኝ መዝለቅ ነው::" አሉና ትከሻውን በማግኔታዊ መስተጋብር ቸብ ቸብ አደረጉት:: ሶፎኒያስ ጥልቅ ተመስጦ ውስጥ ቢሆንም እየነገሩት ያለው ነገር ትንሽ ግራ አጋቢ ሆኖበታል:: ድምጹ ብዙም ሳይቆይ ተመልሶ መጣ... "አሁንም ስማኝ ልጄ! በእርግጥ ግራ የሚያጋቡ ሐሳቦች ሁላችንንም ሞልተውናል:: በተለይ ዝም ብለን ማሰላሰል ስንጀምር መወዛገብ፣ ማመንታት፣ ማወላወል፣ መጠራጠር ሊኖሩ ይችላሉ:: እነዚህ የሰው ልጅ መገለጫዎች ናቸው:: ምክንያቱም የማናውቀው ነገር ወሰን የለውም:: እኛም ይሄንን አንክድም:: ነገር ግን እኛ እነዚህን በሙሉ የሚያስተናግድና የሚያስተካክል ውስጣዊ ቤተ-መቅደስና ቤተ-መንግሥት እንድትገነባ ነው የምናግዝህ:: ለውስጣዊው ማንነትህ ከውስጥህ የሚበቅሉ ንጉሥና የንስሀ አባት እንዲኖሩኽም ነው የምንመራህ::

እነሆ ውስጣዊውን አንተነትህን ስታነቃው ውጫዊ ፍላጎቶችህና ተግዳሮቶችህም ከሌላው ጊዜ ለየት ያሉ ይሆናሉ:: የአእምሮኽን ሙሉ አቅም ወደ መጠቀም ትጠጋለኽ:: ለምሳሌ ከተግባር ብጀምር በሰዓትና ቦታ ተዋህደህ ከቦታ ቦታ በአስፈንጥረት መጓዝ፣ ሩቅ ቦታ ካለ ሰው ጋር በሐሳብ ሞገድ መግባባት አልያም ‹ቴሌፓቲ›፣ የሰውነትህን የምግብ መፈጨትና ኃይል ማቃጠል በመቆጣጠር ለረጅም ጊዜ ሳትበላ መቆየት[76]፣ ቁስ አካላትን በእጅህ ሳትነካ ማዘዝና ማንቀሳቀስ ‹ቴሌካይናቲክን› መሰል ልዩ የሚባሉ ኃይሎችን ትካናለህ:: ከዚህ መካከል አሁን ልታደርግ

75 መዝ 64:6

76 ብዙ የሜዲቴሽን ልምድ ባላቸው መነኮሳት ላይ በተሰራ ጥናት ሰውነታቸው ‹Low metabolic state› እንደሚሆንና ካለምግብ ረጅም ጊዜ እንዲቆዩ እንደሚያስችላቸው ጥናቶች አረጋግጠዋል::

የምትችለውን የመንሳፈፍ ችሎታ[77] ይከፈትልሃል::"

"የምን መንሳፈፍ?"

"አሁን የማለማምድህ ከመሬት ከፍ የማለት ጥበብ ነዋ::"

ሶፎኒያስ በሚሉት ነገር ተደንቆ በአግራሞት አያቸው። "ከተቻለማ ብሞክረው ምን ገዶኝ?"

"እንግዲያውስ መልካም... ምልክቶቹኮ እጅግ ቀላል መገለጦች ናቸው። እርግጥ ለሰው ልጆች ከባድ መስሎ ቢታይም፤ በተለይ በሌላ ዓለማት ውስጥ ለሚኖሩ ፍጥረታት/‹ኤሊያንስ›፤ አእምሯቸው የበለጸገ ፡የእውቀት እርከናቸው ከእኛ ከፍ ያሉ ፍጡራን እነዚህን ጥበቦች በሚገባ ተክነው በጠፈር ውስጥ በብርሃን ፍጥነት ለመጓጓዝ ይጠቀሙበታል።"

{በ1952 እ.አ.አ፣ በአሜሪካ - ጂዮርጅ አዳምስኪ የተባለ ሰውና ሌሎች 6 ምስክሮች የሌላ ዓለም ፍጥረታትን መንኮራኮር ከሰማይ ወርዶ ሲያንዣብብና በቅርብ ርቀት ሲያርፍ ያያሉ። ጂዮርጅ አዳምስኪ ከሌሎቹ የዓይን- ምስክሮች ቀድሞ በፍጥነት መኪናውን እያሽከረከረ ከቦታው ይደርሳል። ከማንኮራኩሩ በር ላይ ቆሞ ያየው የሌላ ዓለም ፍጥረት አንድም ቃል ሳይተነፍስ ነበር ያነጋገረው። የኑክሊየር ጦርነት እንዳይከሰትም አስጠንቅቆት ሄዷል።

በ1959 እ.አ.አ በፓፓዉ ጊኒ ፋዘር ዊሊያም ጊል የ‹ዩፎ› አካላት ጋር ፊትለፊት ተገጣጥመዋል። ለሁለት ተከታታይ ቀናት ከሌሎች 38 ሰዎች ጋር ሆነው ዲስክ መሳይ በራሪ አካል በቅርብ ርቀት ከሰማይ ላይ ሲያንዣብብ አይተዋል። በማንኮራኩሩ የሚንቀሳቀሱ የነበሩት ያልታወቁ ሰው መሳይ ፍጥረታት እንደነበሩም እኚህ ቄስና ሰዎቹም መስክረዋል። እንደ ምስክሮቹ ቃል ከሆነ እነዚህ ፍጥረታትም ሆኑ የተራቀቀ ማንኮራኩራቸው አንዳችም ድምጽ አላሰሙም ነበር። እነ ፋዘር ጊል እጃቸውን ሲያውለበልቡላቸው ፍጥረታቱም በተራቸው እጅ መሳይ አካላቸውን እንዳውለበለቡና ከዓይን ጥቅሻ በፈጠነ ሁኔታ ከሰማዩ ላይ እንደተሰወሩ ተናግዋል። በተጨማሪም በ1964 እ.አ.አ በኒው ሜክሲኮ፡ ሎኒ ዘሞራ የተባለ የፖሊስ አባል የሚያበራ በራሪ አካል ከመሬት ተነስቶ ሲንሳፈፈ አጋጥሞት ነበር፤ ፍንዳታና እሳት

77 Levitation

ሊኖር ይችላል ብሎ ሲሸሽ ወድቆ መነጽሩም ቢሰበርም በራሪው አካል ግን እንዳችም የሰው ልጆችን በራሪ መጓዣዣዎች የሚመስል እሳትና ጩኸት ሳይፈጥ በጸጥታ ተንሳፎ ከቦታው ተመንጥቆ ሄዷል። እነዚህን ለማጥናት አሜሪካ ‹ፕሮጀክት ብሉ ቡክ› ብላ በሚሊዮኖች ዶላር አፍሳ ጥናት ብታደርግም ማብራሪያ ሳያገኙ በመቅረታቸው ፕሮጀክቱ ተሰርዟል።}

"በጣም ይገርማል" አለ ሶፎኒያስ፤ "እውነትም ከምናውቀው የማናውቀው እልፍ ማለት ነው።"

"በሚገባ... እነዚህን መሰል ክህሎቶች ከመካን በፊት ግን የሚቀድሙ ክህሎቶች አሉ። ከምንም በፊት የሚቀድመው ታዲያ ከራስህ ጋር ይቅር መባባል ነው። ራሱን ያላወቀና ከራሱ ጋር ያልታረቀ ሰው እውነተኛ ጥበብ አይገለፅለትም። ራሱንም ሆነ ሌላውን ሊረዳና ለሌላው ሊያስብ አይችልም። ከራሱ ያልታረቀ ሰው ፍቅር፣ እምነት፣ ሀገርና ጥበብን ለመረዳት አቅም ያንሰዋል። ታዲያ ከውስጠትህ ጋር ስትታረቅ እንደ መስታወት ጥርት አድርጎ ማንነትህን የሚያሳይ ሥርየት ገብተህ መሆን አለበት። ድክመትና ጥንካሬህንም አንጥረህ ልታይ ይገባል።

"እባክህን ጌታ ስጠኝ መስታወት

የሰው ሥራ ትቼ ራሴን ማይበት፤"

እንዲሉ ሊቃውንት አሁንም ትልቁ ቁልፍ ራስን መመልከት መቻል ነው። ‹ጠላትህንም ወዳጅህንም ለማወቅ ከፈለግኽ ከመስታወት ፊት ቆመህ ራስህን ተመልከት› እንደሚባለው፤ ችግርህም መፍትሔም አንተው ራስኽ እንደሆንክ እወቅ። ስለዚህ ምንም ሳታስቀር ድክመት፣ ግድፈቶችህን ለራስህ ተናዘዝ። ለራስህ ትህርምት ውሰድ፣ ስለ አስተሳሰብክ አስብ! የአውቃለሁ ትዕቢትን አንድርብ አውርድ፤ ይልቁንም በዝምታ ውስጥ ራስህን አሸንፍና ለነፍስህ ጥበብ በር ክፈትላት። {ራስን በሐቅ መነጽር ተመልክቶ ድክመትን ከማወቅ በላይ የእውቀት መክፈቻ ቁልፍ የለምና።}

ታዲያ ይህንንም ታደርግ ዘንድ አብዝተህ ዝም በል፣ ሐሳብህን ስበህ እየመዘዝክ በጽሙና ተንሳፈፍ ፣ ተፈላሰፍ።" አሉና ከአድማስ ባሻገር ያለችውን ፀሐይ በአማትሮ ተመለከቷት።

"እንዲያው ለመሆኑ ከተራራና ከሸለቆ ለፀሐይ ማን ይቀርባታል? ከተራራና ከሸለቆስ የትኛው ይሞቃል? ጥበብም እንዲሁ ከጩኸት ሳይሆን ከዝምታ ትመዘዛለች። ዛፍ ከከሰል እንደሚቀድመው ሁሉ ከሚፋጀው

ነበልባል በፊት ልባዊ መሆን ፊተኛ ነው። ዝቅ ብሎ የበሰለ ጒላ ከተራራው ጫፍ ወጥቶ ራዕይና ሹመት ይቀበላልና። በብርድ የማይበገር ውስጣዊ ግለትን ስለሰነቀ ይህ ለሱ ይገባል። እነሆ ከመተናነስም በላይ አኩሪ ጥበብ የለም።"

"አስገራሚ እውቀት እየቀሰምኩኝ ነው መምህር" አለ ሶፎኒያስ፤ በእርግጥም ውስጡ በሆነ ዘላለማዊ ደስታና ሰላም ሲሞላ እየታወቀው ነበር።

"የምታዳመጥው ከልብህ ስለሆነ ደስተኛ ነኝ። የምትሰማውና የምትረዳውም ላንተ ቀድሞ የተከተበልህን እውቀት ነው። የውልህ ልጀ የሚያወራ ሰው ብዙ ነው፣ ጸጥ ብሎ የሚያዳምጥ ግን ጥቂት ነው። ሁሉም ሰው የሚከፈትለት ያንኳኳው በር ብቻ ነው። ባታንኳኳ፣ ባትጠይቅ እዚህ አትገኝም ነበር። እናም እውቀትን መሻት፣ መጠየቅና መመርመር ወደ ጥበብ ይመሩኻል። እውቀት ደግሞ የህይወት ብርሃን ነው። የሚያውቁና የማያውቁ ዓለምን እኩል አይኖሩባትም፣ እኩልም አይረዱትም። እውቀትን ያጣ ህዝብ ይጠፋል እንዲል ቅዱስ ቃሉ እውቀትን ፍለጋ መልፋት አለብኽ። እውነተኛ እውቀት የሚተፋ ቀለም ከሰማዕታት ደም ይልቅ የከበረ ነውና፤ ራስኽን በየትኛውም የልምዶች አጥር ሳትገድብ እውቀትን አነፍንፋት። እሷም አርነት ታወጣኻለች።

ሌላ አንድ የምጨምርልህ ምክር ደግሞ አለ። ልጅ ሶፎኒያስ … ከምንም በላይ ወደ ዝምታ መገለጥ ትቀርብ ዘንድ ፈጣሪኽን ለማወቅ ጣር። ፈጣሪኽን ባወቅክ ቁጥር ራስህን ታውቃለኽ። በተለይ ደግሞ መንፈሳዊነትህ ላይ እንድትበረታም እመክርኻለሁ። አስተውል መንፈሳዊነትና ኃይማኖተኛነት የተለያዩ እሴቶች ናቸው። ኃይማኖተኝነት ያጥራል፣ ይመስላል፣ ይፈርጃል፣ ይከፍላል፣ ይሰብካል| መንፈሳዊነት ግን ያስተውላል፣ ይተገብራል፣ ይመሰጣል፣ ያቀራርባል፣ ይኖራል። እንዲሁ ሁሉ አርምሞም ይታወቃል እንጂ አይሞከርም፤ ይኖራል እንጂ አይወራም፤ ይዋሃዳል እንጂ አይቀመስም። ነገር ግን ኃይማኖት አንዱ የመንፈሳዊነት መዳረሻ መንገድ እንደሆነ አትርሳ።

እናም › ዝም የማለት መነሻዎች ስታጣራ እውቀትን መሻት፣ ብቸኝነትና መተናነስ እንደሆኑ ታውቃለኽ። መዳረሻውም የሚኖር፣ በማዕበል ውስጥም የማይናወጥ አርምሞ ሆኖ ታገኘዋለኽ።

*ትልቁ እውነታ| የፍጥረት እውቀት ተጠልቶ የማያልቅ ውቅያኖስ መሆኑ ነው፡፡ አንተ ግን በህይወት እስካለኽ ድረስ መጥለቅኽን አታቁም፡፡ ወደ ታች አጎንብሰህ እውቀትን ፍለጋ ዝቅ ባልኽ ቁጥር ነፍስያኽ ከፍ ከፍ ትላለችና፡፡" ብለው ትምህርታቸውን ፈጸሙ፡፡*

*ሶፎኒያስ ጎንበስ ቢል ራሱን ከመሬት ከፍ ብሎ ተንሳፎ ነበር ያገኘው።*

⌘ ⌘ ⌘

## ቃሊቲ እሥር ቤት

አንድ ፊቱ ጥውልግልግ ያለ ወጣት ከአንዱ የእሥር ቤት ጥግ ተቀምጦ ሲጋራውን ያጉተለትላል። የተያያዘው ቅንጡ የመዝናናት አጫጫስ አልነበረም። የእልህ፡ የነፍስ ውጪ ነፍስ ግቢ የሚመስል ትንቅንቅና መጠጣ እንጂ። ለይኩን ከሰውዬው ትይዩ ተቀምጦ በፍርሃትና በግርምት ያየዋል። እሥረኛው ይባስ ብሎ ሲጋራው ነዶና ጨሶ የሚቀረውን የአመድ ተረፈ ምርት ምላሱ ላይ ነበር የሚተረኩሰው። ሲጋራውን በላው እንጂ አጨሰው ለማለት በሚከብድ ስሌት መጦ ሲጨርስ፡ ፍሙንም በምላሱ ትሽሽሽ... አድርጎ አጠፋው። ለኩሶ እስኪገድለው ድረስ በመገረም ሲያየው የነበረው ለይኩን ይበልጥ ደነገጠ።

ለይኩን ለዚህ ማረሚያ ያለው ፍርሃት ቀን በቀን እየናረ መጥቷል። ምን አይነት አስፈሪ ቦታ ነው የገባሁት ብሎ እየጠየቀ በጭንቀት ይበዝናል። እኔን ከማይመስሉ ሰዎች ዘንድ ነው የተገኘሁት! በልጅነት እንኳን አንድ ሰው ጋር ተደባድቤ የማላውቅ ሰው እዚህ ዱርዬዎች መካከል ምን እሠራለሁ? ምንስ ቢያደርጉኝ ምን ሊውጠኝ ነው? ...እኮ ይሄንን ስቃይ እኔ ላይ ያሴሩ ሰዎች ምን አድርጊያቸው ነው? ሌላውስ ይቅር የኔ ብዬ አብሪያት የኖርኳት ሴት እንዴት እንዲህ ልትጨክንብኝ ቻለች? ቆይ ምን አፍ አለኝና ልናገር? ምንስ ልል እችላለሁ?

ለይኩን በሐሳብ ማእበል እየቀዘፈ ሳለ የእሥር ቤቱ ቴዲ አፍሮ በመባል የሚታወቀው እስረኛ ጩኒ ድምጹን ከፍ አድርጎ መዝፈን ጀመረ። የትዝታው ንጉሥ፣ የአንጋፋው መሐሙድ አህመድ ሙዚቃ - በምግብ እጦት ከደከመ የእስረኛ ጉሮሮ ይንቆረቆር ጀመረ።

*♫"ለዋልኩት ውለታ... ይሄ ነው ወይ ውርሴ?*

*ልፋቴ፡ ድካሜ ... ይሄ ነው ወይ ውርሴ?*

*እንግዲህ ምን ልበል ይህ ከሆነ ቅርሴ?*

*አሀ ... ዝምታ ነው መልሴ::*

*ክፉ ደግ አትበል፣ አታውጋ ምላሴ*

*አሀሀሀ... ዝምታ ነው መልሴ::*

*ሾተሉ እስኪነቀል የነገር አንካሴ*

*ዝምታ ነው መልሴ...*

*የእውነት ፀሐይ ወጥታ እስከሚታይ ክሴ*

*ዝምታ ነው መልሴ*

*..........ዝምታ ነው መልሴ"*

እያለ ደጋገመና ጬኒ ወደ ዝምታው ተመለሰ። ከጎኑ የነበረው፡ የግዙፉ ጉዋንጉል ሞቅ ያለ ጭብጨባ ተተካ።

"አ! ዋው! ዋው! ዋው! አንቺ ትዘፍኚው የለ እንዴ በናትሽ!" አለና ጀርባውን ቸብ ቸብ አደረገው። ሁሉም እሥረኞች ትኩረታቸውን ወደ ዘፋኙ ሰደው ነበር።

"ግን ስለዘፈንከው ዘፈን ግጥም ምን ታስባለኽ?" የሚል ጥያቄ ከወዲያ ማዶ ተወረወረ። እስረኞቹ ይሄንን ጥያቄ የጠየቀው ማን እንደሆነ መገመት አላዳገታቸውም። የዚህን ሰው ድምጽ ሁሉም ጠንቅቀው ያውቁታል - ዳዊት ዲባባ ወይም ዳዋን የማያውቅ ሰው ቢኖር አዲስ ገቢው ለይኩን ብቻ ነበር። ዘፋኙ ጬኒ የዳዋን ጥያቄ ለመመለስ በትግል ላንቃውን አላቀቀ።

"ያ... ያው አለ አይደል? ላይፍ ላይ ግፍና ስቃዩ ሲበዛብኽ፣ ብትናገርም ያንተን ብሶት የሚሰማ ሰው ስታጣ፣ ላሽ ስትባል፣ ፍትሕ ሲጓደል፡ ቀን እስኪያልፍ... ያንተም የእውነት ብርሃን እስክትወጣ ድረስ፤ ለነገሮች ምላሽ አይኖርህም፣ ለጥያቄዎችም መልስህ ዝምታ ይሆናል። ይሄም ይመስለኛል ‹ብሮ›፡ የሙዚቃው መልእክት..."

"ባልከው እስማማለሁም፡ አልስማማምም..." አለ ዳዋ - ሁሉም ወደሱ ዞሩ። "የምስማማው አንተ ላይ የተፈፀመን ግፍ የሚሰማህ ላይኖር ይችላል ያልከውን ነው። እመነኝ! ስለ አንተ ስቃይና ጉዳት የሚጨነቅልህ ሰው በዚህ ምድር አታገኝም። ነገር ግን የማልስማማበት ሐሳብህ ደግሞ መልሴ

ዝምታ ነው መሆን ያለበት ያልከውን ነው።" አለና ዳዋ ከተቀመጠበት ብድግ አለ።

የሆነ የሚያስፈራ ውቃቢ አለው። የሚያስገርመው ያን ያህል ግዙፍ ሰው እንኳን አልነበረም። ከቁመቱ አጠር ያለ፣ ተክለ-ሰውነቱም ቀጫጫ የሚሉት አይነት ወጣት ነው። ነገር ግን ለየት ያለ ባህሪውና ሁሌም ከሱ ቀድሞ የሚደርሰው ገናናው ታሪኩ፡ ገዘፍ ያለ፣ አስፈሪ መንፈስ እንዲያረብበት አድርጎታል።

በቀስታ ተነሳና ከጬኒ አጠገብ ሄዶ ተቀመጠ። ጬኒ ውስጡን ፍርሃት ቢጤ እየወረረው በቆሪጥ ያየዋል።

"ምን መሰለሽ ጬኒዬ፣ ማንን ደስ ይበለው ብዬ ነው ዝም የምለው? ይሄ ህዝብኮ ዝም ካልክለት አናትህ ላይ ድስት ጥዶ አንጎልህን እንደ ወጥ ማማሰል ያምረዋል። አዛ ያደርግሃል። የራስህን ፍላጎት ራስህ የምታስፈጽም ሳተና መሆን ነው ያለብህ፤ ማንንም መስማት የለብህም።" አለ ዳዋ፤

ወዲያው ከሁሉም እሥረኞች በእድሜ ገፋ ያሉት ታራሚ ጋሽ በቄ ወደ ውይይቱ ስፍራ ተጠጉ። እኚህ ሰው በሁሉም ታሳሪ ዘንድ የሚከበሩ አባት ናቸው። ብዙዎችን ያግዛሉ፣ ይመግባሉ፣ ያስተምራሉ፣ ይመክራሉ… ብቻ መለስተኛ የእሥር ቤቱ[78] ኩራዝ ናቸው። *{በጨለመ ሥፍራ እንደዚህ የሚያበራ ተስፋ ማግኘት እጅግ አዳጋች ቢሆንም እንደዚህ አይነት ሰዎች ግን በየቦታው እንደ ቅመም ጣል ጣል ተደርገው ይገኛሉ፤}*

"አዎ ግን ዳዋችን፤ የበደሉህን ለመበቀል ድምጽ ሳያሰሙ መሥራትና መለወጥ ይሻላል ባይ ነኝ። ጣፋጩ የበቀል ጽዋ ስኬታማ ሆኖ መገኘት ነው ይባላል። ነገር ግን ብዙ ካወራህና ከፎከርክ እቅድህን ቀድሞ ያወቀ ጠላት ይቀድምኻል። ያሸንፍኻልም። እውነተኛ ጀግና ግን ከድል በፊትም ከድል በኋላም ብዙ አይፎክርም።" አሉት። የውይይቱ ርዕስ ከባድ የፍልስፍና ነጠብ ላይ እየዞረ ስለነበር ሌሎች ታሳሪዎች[79] ወደ ቦታው ጠጋ ጠጋ ብለው ማዳመጥ ጀመረዋል።

አይበገሬው ዳዋ ለጠቅ አድርጎ ቀጠለ "ይቅርታ አድርጉልኝና ጋሽ በቄ

78 በሰፊ ንባብ ራስን ለማዳበር ብሎም የብቸኝነትና የጥሞና ጊዜን ለማሳለፍ ተመራጭ ከሆኑ ቦታዎች አንዱ እሥር ቤት ነው፡፡ በእሥር ላይ ያለ ታራሚ ከየትኛውም ሰው የተሻለ ትርፍ ጊዜና የጥሞና አማራጭ አለው፡፡ ሥጋው ቢታሰርም በነፍስና መንፈሱ ነጻ መሆን ይችላል፤

79 አታውቂያትም

አሁንም ቢሆን በዚህ ሐሳብ አልስማም። ጠላትህ ዝም ካልከው ይበልጥ ይበረታል። ትዕቢቱ ይጨምራል። ስለዚህ በየመሀሉ ጃስ እያልክ ማስደንገጥ አለብህ። ካለመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል ይባል የለ? እንዴ ማንን ፈርቼ ነው ዝም የምለው? እንደፈለግኩኝ እንጂ የምናገረው... የምን መታፈን ነው?... ቲሽ!"

"መታፈን አይደለምኮ ዳዋችን፣ ነጥቡ ዝምታኽ የምርጫ ዝምታ መሆን አለበት ነው። ማንም ሳያስገድድህ፣ ማንንም ሳትፈራ በፍቃድህ ነው ዝም የምትለው..."

|ውይይቱ ጦፎ ብዙ ከተከራከሩ በኋላ ባለመስማማት ተስማምተው ተለያዩ፡ ከበው ሲያዳምጡ የነበሩት መልከ ብዙ እሥረኞችም ተበተኑ። ለይኩን ወደ ሙዚቀኛው እስረኛ ጩኒ ተጠግቶ ስለ ጋሽ በቄና ዳዋ መረጃ ጠየቀ፤

"እንዴ ጀለሴ! እስካሁን ዳዋን አታርፈያት[80]ም እንዴ?" አለ ጩኒ፤

"ኧረ አላውቀውም"

"ዳዋማ ታሪከኛ ልጅኮ ነው!"

"እውነት? እስኪ ቢያንስ አንድ ታሪኩን ንገረኝ..."

"እሺ፣ በግሌ በጣም የሚገርመኝን ጭዌ ልንገርሽ"

"እሺ፤"

"እናልሽ ዳዋ ማለት ሽጉጥ ይዞ ከወርቅ ቤት ገብቶ ሀብልና ቀለበቶችን በሹራቡ ጠቅልሎ እያፈተለከ ከማምለጥ ጀምሮ አሁን የግል-ጠባቂዎችን ቀጥሮ ከፖሊሶች ጋር እስከ መታኮስ የደረሰ ከባድ ሌባ ነው። ከሥሩ ብዙ ላቦሮዎችን[81] ያስተዳድራል። በዚያ ላይ የመጬ[82] ይቀየሳል አይገልጸውም። ዛፓዎች[83] ብዙ ጊዜ ሊይዙት ፍሉካ[84] ቢደርሱበትም፡ እንደ ዓሣ እየተሙለጨለጨ ከእጃቸው ሥር አምልጧቸዋል። ከዚህ በፊት ሁለቴ ከርቸሌ ታስሮ አምልጧል። ብቻ ሀገር ሁሉ የሚያውቀው የሌባ ዝነኛ ነው

---

80

81 የመጨረሻ

82 ሌቦች፤

83 ፖሊስ

84 ፊትለፊት ማየት/ ሁሉም የአራዳ ቋንቋዎች ናቸው፤

ዳዋ። የሚገርመኝ ግን ይሄን ሁሉ ሲያደርግ በእድሜ የገፉት እናቱ ስለ ልጃቸው ሥራ አንዳችም ነገር አለማወቃቸው ነው።"

"የምር ይገርማል!" አለ ለይኩን ትንሽ ተክለ-ሰውነቱ እና የገዘፈ ስሙ ያልተጣጣሙበትን ዳዊት በሩቁ እያየ።

"እና አንድ ስሰማው የደነቀኝን ታሪክ ላጫውትሽ..."

"እሺ"

"እናልህ ማዙካው[85] ይሄንን የተደከለ[86] ብርና ወርቅ ሰርቼ ነው ያመጣሁት ብሎ እያመጣ ይሸልማቸው ነበር። እርሳቸውም ልጄ ለወግ ደርሶ፣ ከራሱ አልፎ ለኔ ተረፈ እያሉ ፈጣሪያቸውን ያመሰግናሉ። ታዲያ አንድ ቀን የጓደኛቸው ልጅ ታገባ ነበርና እንደምንም ሰርጉ ላይ ለመታደም ይወስናሉ። ልጃቸው ከሰጣቸው ሐብሎች መካከልም ትልቅ የሚባለውን መርጠው አጥልቀው ይወጣሉ። ታዲያ ከሰርጉ መንደር ሲደርሱ ይሄንን ጩባ[87] የከለመ[88] የሌላ ሰፈር መንጩ ሰሪ[89] ጀለስ[90] የመጭ ይከየፋል[91]። እናም ትንሽ ተከታትሏቸው ሀብሏቸውን መንጭቋቸው ይሮጥልሃል... ከዛማ በቃ ይሄንን ጩባ ጀሮ ግንዱን ብዬ ‹ላይፌ›ን ላስተካክል ነው ብሎ ይቦርቃል።

በኋላ እንደሱ መንጩ የሚሰሩ ሁለት ጓደኞቹን ያገኛቸዋል። ወርቁን ባያሳያቸውም ከአንዲት አሮጊት የሚገርም ሀብል እንደመነተፈ ነገራቸው። እነርሱም አብረውት በደስታ ዘለሉ። መለስ ብለው ደግሞ ይሄንን የሚያክል ወርቅ እንዴት እንደቀናው ይጠይቁታል። ወርቁ ስለተወሰደባት ሴትዮ ገጽታ ሲነግራቸው ግን ቀስ በቀስ የጓደኞቹ ፊት መለዋወጥ ጀመረ። "ወይኔ አንተ ልጅ በቃ የዳዋን እናት ነው ያስቀየምከው።" ቢሉት ... ባንዴ በላብ ተዘፈቀ፤ "እኮ የዳዋ እናት ማለት... የዳዋ?!" ብሎ ጠይቃቸው።

መልሰው "አዎ፤" ቢሉት ትንሹ ሌባ የትልቁን ሌባ ድምጽ ሲሰማ

---

85 እናት፤
86 የተሰረቀ፤
87 ወርቅ፤
88 ያየ፤
89 ነጣቂ፤
90 ማንኛውንም ሰው የሚወከል ቃል፤
91 ይማልላል፤/ ሁሉም የአራዳ ቋንቋዎች ናቸው፤

ብርክ ያዘው አሉ። ሽኖ[92]ውን ሁላ ሳይለቀው አልቀረም፤" አለና ጬኒ በሳቅ ሞተ፤ "እናልሽ የዳዋን ማዙካ እንዳስቀየመ ሲያርፍ ቤቱም ሳይቀመጥ የሠረቀውን ጬባ ይዞ እየከነፈ ወደ ዳዋ ቤት ሄደ። የእድሉ መክፋት በሩን ሲያንኳኳ የከፈተለት ራሱ ዳዋ ቢሆንስ? ጀለስ በድንጋጤ ዝም ብሎ ሲንተባተብና ሲወዛገብ አየውና...

"ተረጋጋና ንገረኝ፤ ምን ልታዘዝ?" አለው አሉ - የዳዋ ትህትናኮ ከጀርባው የደበቀው ነፍ ቁጣ እንዳለ ያሳብቃል፤ የሆነ ከዶፍ ዝናብ በፊት የምትወጣውን ፀሐይ የሚመስል ትህትና በለው። "ዳዋዬ እኔ አንቺን በጣም ነው የማከበርሽ፣ ማለት አንቺን ሊጎዳ የሚችል ለማድረግ ምንም ሐሳብ የለኝም፤" አለው አሉ፣ በሺም[93] አጎንብሶ፣ ኩርንችች ፀጉሮቹን እያፍተለተለ።

ዳዋም "ሰውዬ ወደ ገደለው ግባልኝ!" ብሎ ተቆጣው፤ ከዚያ

"እ...እሺ ቅድም... ያ... ያንተ ማዘር መሆኗን ሳላውቅ ሀብል ነጥ... ነጥቄ ወስጄባቸው..." ልጁ ለጉድ ተንተባተበ... አስብ እንግዲህ ከአሁን አሁን ቡጢ ወይም የሆነ ነገር ያርፍብኛል እያለ በፍርሀት ተውጦ ነበር። "እ...እና ሐብላቸውን ልመልስ ነው የመጣሁት ዳዋ - ይቅርታ አድርጊልኝ በያ[94]።" አለና ሀብሉን ከኪሱ አውጥቶ ወደሱ ዘረጋለት፤

ሲነግሩኝ የዳዋ ፊት ወዲያውኑ ተቀያየረ አሉ፣ በጣም ተናደደና ምን እንዳለው ታውቃለኽ... "ትሰማኛለህ?!" ብሎ አንባረቀበትና "ሥራህ ለመሆኑ ምንድነው? ... ሌባ ነህ አይደል?" ብሎ ጠየቀው አሉ። ልጁም "እ... አዎ ነ...ኝ ዳዋ... ያ...ው...ያው መንጬ ነው የምሠራው ዳዋ..." ብሎ መለሰለት፤ *(ጬኒ ታሪኩን ሲናገር በቦታው የነበረ ይመስል በእንቅስቃሴም ጭምር ነበር።)*

ዳዋ ታዲያ ምን ቢለው ጥሩ ነው፤ ኮስተር ብሎ... "እንደዛ ከሆነ ታዲያ ለምንድነው የለፋህበትን ሥራ አምጥተኽ የምትሰጠኝ? ሠራተኛ ደምወዙን አሳልፎ ይሰጣል እንዴ?... ቆይ እንዴት አባህ ብትንቀኝ ነው?" አለና ሽጉጡን መዞ ሌላ ታሪክ ውስጥ ሊገባ ተጋበዘ አሉ። በመጨረሻም "በአሥር ሰከንድ ውስጥ ከፊቴ ካልጠፋህ በእጄ ሰበብ ትሆናለኽ!" ሲለው መንጬ የሚሠራው ልጅ ዓይኑን ይዞ ጠፋ አሉ።" ብሎ ኮስማናው ታሳሪ

92 ሽንት፤

93 ይሉኝታ፤

94 በሀገርኛ ወንድሜ ሁሉም የአራዳ ቋንቋዎች ናቸው፤

አፈ-ታሪክ የሚመስለውን የዳዋ ገጠመኝ አጫወተው።

ለይኩን በግርምትና ፍርሃት ድብልቅ ስሜት ዳዋን በጨረፍታ አስተዋለው። "የሌባም ደረጃ አለው ለካ!" አለ ለራሱ።

"እሺ ጋሽ በቄስ ማን ናቸው?"

ጬኒ ምንም ሳይመልስ ስማቸውን ብቻ እየደጋገመ ጋሽ በቄን አሻግሮ ሲያያቸው ቆየ፤ "በነገራችን ላይ ጋሽ በቄ ጥሩ ሥራ የነበራቸው፣ የሁለት ዲግሪ ባለቤት የነበሩ... የተማሩ ምሁር ናቸው። የእርሳቸው ነገርማ እንዲያውም ያሳዝናል።"

"ለ... ለምን ይሆን የሚያሳዝኑት ጬኒ?"

*"በአንድ ወቅት በመንግሥት መሥሪያ ቤት በከፍተኛ ባለስልጣንነት እየሠሩ በነበረበት ወቅት በዙሪያቸው ያሉ ባለስልጣናት አንድ ትልቅ የሙስና ሰንሰለት ይፈጥሩና ጠቀም ያለ ብር ለማግኘት ይስማማሉ። ነገር ግን ሰንሰለቱ ሄዶ ሄዶ የጋሽ በቄ ፊርማ የሚያስፈልግበት ደረጃ ላይ ይቆማል። እናም እኚህን ሀገር ወዳድ ሰው ወደ ሙስናው ሰንሰለት ለመሳብ የተደረጉ ጥረቶች በሙሉ ሳይሳኩ ይቀራሉ።*

ሰውዬው በፍጹም እንዳማይቀበላቸው የተረዱት ባለስልጣናት ታዲያ ሴራ ሸረቡ። በጎን አንድ ዳኛ ጋር ተሻረኩና በጸረ-ሙስና ሥም እሥር-ቤት እንዲወረወሩ አደረጓቸው። ያው እነርሱ በምቾት ይንጎማለላሉ ጋሽ በቄ ግን እዚሁ ከኛ ጋር ታማኝ እሥረኛ ተብለው ቀን ይቆጥራሉ፤" አለና ኮስማናው እስረኛ ትካዜ ቢጤ በገጽታው ታየ። በዚሁ ቅጽበት ጋሽ በቄ በዝግታ እየተራመዱ መጥተው ከለይኩን ጎን ቁጭ አሉ።

*"ስምህ ማን ነበር ወንድሜ?"*

*"ለይኩን"*

*"እሺ ለይኩን/ እንኳን ደህና መጣህ አልልህ ነገር...*
*"አሉና ሳቅ አሉ። ለይኩንም አብሯቸው ፈገግ አለ፤ ቢያስተውላቸው ራሳቸውን እንደጣሉ ወዲያው ተረዳ። ቆሸሽ ያለ ልብስ ለብሰዋል፣ ሳይቆረጥ የከረመው ጥፍራቸው በጭቅቅት ተሞልቷል፣ ለአገጩና ከጉንጫቸው አጎዛ መሳይ ጺማቸው ካለ ሥርዓት አዝግዝጓል።*

በጣም ሲያፈጥባቸው ፍርሃት ቢጤ እንደያዘው ገባቸው... "ለይኩን...

ብዙም አትፍራ፤ ይሄ እንግዲህ የነጻነትን ዋጋ በጸጸት ኮሌጅ ውስጥ የምትማርበት ሥፍራ ነው። ወህኒ፣ ከርቸሌ፣ ዘብጥያ፣ እሥር-ቤት ይበሉት እንጂ ትርጉም አንድ ነው። ሰፊ ጊዜ በትንሽዬ ውስን ቦታ ውስጥ ማለት ነው። ተስፋ የተወናወነችበት... በአካል ተኝተህ አድረህ በሃሳብ ተኝተህ የምትውልበት ስፍራ ነው። ስትታሰር ጊዜ ዝግ ትላለች። በሳቅ በጨዋታ ካላሳለፍክ በቀር አዕምሮህም ሊረበሽ ይችላል። እናም ተጫወት ለማለት ነው ይሄ ሁሉ የለፈለፍኹት፤" ብለው በይበልጥ ወከክ አሉ፤ "እሺ አመሰግናለሁ" መለስ ለይኩን

"እስኪ ስለራሥህ አጫውተኝ" አሉትና ከጎኑ ተቀመጡ። ... ብዙ ብዙ ነገሮችን ተጨዋወቱ። ተወዳጁ።

⌘ ⌘ ⌘

## ✍... ያፍቃሪዋ ማስታወሻ

*እኮ እኔስ ምን ጉድ ነኝ? ምንስ እርግማን ነው እግር በእግር የሚከታተለኝ? እንደሰዉ ለእኔስ ለምን ቀን አይወጣልኝም? የምወደውን ልጅ እንጂ ሌላስ ምን ጠየኩኝ? የመለያየት ቀስቶች ለምን ወደ ምስኪኗ የፍቅር እልፍኜ አብዝተው ያነጣጥራሉ? ምን አጠፋሁኝ? ከዚህች እልፍ ህዋ ውስጥ አንድ ሰውን ብቻ መሻቴ ትልቅ ጥያቄ ነው ወይ? ከሚሊዮን፣ ከቢሊዮን ወንዶች መሀል አንድ ለይኩንን መመኘቴ ለምን ከባድ እዳ ሆነ? እድለ ቢስ ነኝ! አገኘሁት ብዬ ያቀፍኩት እንቁላል ፈርካሽ በዛበት፣ ብፈካ ብዬ የተከልኩት አበባ መንገደኛ ቆራረጠው፣ ልቤን እየወጉ አንጀቴን ሸረካከቱት፣ ምቀኛ ጭራቅ ቀን እየጠበቀ ጎጆዬን አስጨነቃት፣ የፍቅሬን ድንኳን ውታፍ ነቃይ ከበባት፣ ከልቤ እንዳልስቅ ጥርሱን የሚነክስብኝ የጥላቻ መናፍስት ዘመተብኝ... ይህ ምስኪን ጉልበቴ ይሄንን ክቡድ መከራ ሊቋቋም አልቻለም።*

*ሰዎች አስጠልተውኛል። በተለይ ይሄንን ህመሜን ሳይረዱኝ ነገር እየመጡ ሊያጽናኑኝ ሲሞክሩ ይባስ ያበሳጩኛል። የወደቀብኝ ሸክም ለሌላው የማይካፈል የግል ኑሮዬ ብድራት ነው። እንኳንስ ሸክም ሊጋራኝ ይሄንን ህመሜን ሊረዳኝ የሚችል አንዳች እንኳ ሰው በምድር የለም። በእርግጠኝነት የእሱ ወደ ጨለማ ወህኒ መውረድ የእኔ ወደ ተስፋ ቢስ ጽልማሞት መግባት ጋር ይከወናል። እናም እየመጡ ቀለል አድርገሽ እይው ሲሉኝ መከራዬ ይበልጥ እየከበደ ይሄዳል። ቃላቶቻቸው ጭንቀቴን ይበልጥ እየወጠሩ ያከሩታል። በወሬ መሮ እየቦረቦሩ የውስጤን ሰላም*

*ይበጠብጡታል፡፡ ድምጻቸው የአባዶንን ቆርቋሪት ጩኸት እየሆነ ይረብሸኛል፡፡ በቃ አያናግሩኝ፡፡ ምንም አይነት ድምጽ አያሰሙኝ፡፡ በዝምታዬ ውስጥ እሱን እያሰብኩኝ እንድብሰለሰል ይፍቀዱልኝ፡፡ ቢያንስ የግል ድባቴዬን አይንጠቁኝ፡፡ ወደ ውስጤ እንዳለቅስ አይከልክሉኝ፡፡እሱን ካጣሁ ቆሜ መቅረቴን አውቀዋለሁና ይተዉኝ!...ሆዴን እቅፍ አድርጌ፡ ትርፌ ከሆነው ጽንሴ ጋር ልነጋገር፡፡ በፍቅራችን ብልጭ ካለችው የአብሮነት ጊዜዬ ካረገዝኩለት ልጄ ጋር ለብቻችን ይተዉን፡፡ በቃ እኔ የምፈልገው ዝም እንዲሉኝ ብቻ ነው፡፡ በቃ ዝም ይበሉኝ!...*

*{በዓይን የማይታይ የሥነ-ልቦና ቁስል ውስጥ የሚደማ ቀላይ ደም አለ፣ ይህ የሐሳብ ደም ወደ ውስጥ እንደ መርዝ-ፏፏቴ እየፈሰሰ ነፍስን ያመነምናል፣ አንዳንዴ ደግሞ በዓይን ቀዳዳዎች እያመለጠ ይንዣረራል፤ ይህም እውነተኛ እንባ ነው፡፡} ከአፍቃሪዋ ማስታወሻ ላይ በቁጥር የተወሰኑ፣ በኃይላቸው የበረቱ የእንባ ዘለላዎች ተንጠባጠቡ፡፡*

⌘ ⌘ ⌘

በዚያ ሰሞን የወ/ሮ እልፍነሽ ልጅ ሜሮን የአእምሮ ህመምተኛ መሆን የጨው በረንዳ ሰፈር መነጋገሪያ ሆነ።

"የዘንድሮ ልጆችኮ ውላቸውም አይታወቅ!" አሉ እትዬ ፋጡማ የበኖ ውኃ ሊቀዱ የመጡትን ሴቶች በየተራ እያዩ፤

"ይተዉኝ እስኪ እቴ... አሁንማ አደብ ያለውና አደብ የሌለውንም መለየትኮ ከባድ ሆኖብናል።"

"እኮ ያቺ አንገት ደፊ ሜሮን፡ የሥራ ባልደረባውን በጬካኔ ከገደለው ከለይኩን አርግዛለች ነው የምትሉኝ?" አለች አንዲት ቀጭን ሴትዮ፤

"አባቱ ከርቸሌ ያለ ልጅ ቆይ ምንድነው እጣው?"[95] ሌላ ጥያቄ ተከተለ፤

"አንቺ እሱ ያስጨንቅሻል እንዴ? ልጅቱ እኮ እንደሆነ ነገር እያደረጋት ነው። ልክ እንደ ታማሚ አክስቷ ሰው ጠልታለች፣ ራሷን አግልላ ለብቻዋ ነው የምትሆነው... ትምህርቷንም ካቋረጠች ስንት ጊዜ... ብቻ የአእምሮ ህመም ይባላል እንጂ እኔስ ደንበኛ ልክፍት እንዳጠናገራት አልጠራጠርም።"

---

95 *በአሜሪካ በተደረገ ጥናት አብዛኛዎቹ በሪጋንግ ሱስና ጸበኝነት የሚሳተፉ ወጣቶች አባቶቻቸው ከእጠገባቸው ሆነው ያላሳደጓቸው እንደሆኑ ታውቋል፡፡

"ውይይ… የኔ እናት… ስታሳዝን በአማላጂቱ!" አሉ አንድ ጉንጫቸው ሙልት ያሉ እናት፤ "የልጁ አባትስ እንዴት ሆኖ ይሆን?"

"እሱማ ያው በፍርድ ቤት ተፈርዶበት ለአስራ ምናምን አመታት ዘብጥያ ወርዷል፤"

"ያሳዝናል በናትሽ።" … ከንፈራቸውን መጠጡ፤

"እኔ ግን ከምንም በላይ የሚያሳስበኝ አንድ ነገር አለ፤" አሉ እትዬ ፋጡማ፤

"ምንድን ይሆን የሚያሳስቦት?"

"ያኚው የሚያማቸው እናቱ ወ/ሮ ብዙወርቅ ጉዳይ ነዋ የሚያሳስበኝ… በባዶ ቤት ምን እንደሚውጣቸው ብቻ እሱ ጀሊሉ ይወቅ!" አሉና ወደ ሰማይ አንጋጠው፡ መዳፎቻቸውን ለዱዓ ወደ ላይ ሰበቁ።

"እንዲት ልጃቸው ቢያንስ ለእርሳቸው ሲል ከዚህ ክፉ ወንጀል መራቅ ነበረበት!" አሉ ጉንጫሟ ሴትዮ፤

"እኛስ በወጉ መቼ ልጆቻችንን እንመክርና ብለው ነው?"

"አዎ ትክክል ነው፤ ትንሽ አውርተን እንረሳዋለን… ለወሬ የለው ፍሬ አይደል የሚባል… እኛም ልጆቻችንን በወጉ ተከታትለን መቅረጽ አለብን…"

"ከሰሞኑ እስኪ የሆነ መዋጮም ነገር ቢሆን አድርገን ልንጠይቃቸው ይገባል።" አሉ ጉንጫሟ ሴትዮ፤

"ይሄ የተቀደሰ ሐሳብ ነው፤" ሁሉም በአንድ ድምጽ ተስማሙ፤ በሉ ቶሎ ቀዳ ቀዳ አድርጉና ሂዱ፣ ቆልፌ ልወጣ ነው፤" አሉና እትዬ ፋጡማ ጨዋታውን ዘጉት፤

{እንዲሁ ሁሉ የአንድ ሰው አታካች የህይወት ስንክሳር የሌሎች አጭር የወሬ ርዕስ ሆኖ ያልፋል።}

⌘ ⌘ ⌘

ይህ በሆነ በሳምንቱ ወ/ሮ ብዙወርቅ ከቤታቸው ውስጥ ሞተው ተገኙ።

እድር[96] ባይኖራቸውም የሰፈሩ ሰው ተሰባስቦ፣ ተቢቱ[97]ን ለብሶ፣ መጠነኛ ሽኝት አድርጎ አስቀበራቸው። በለቅሶ ላይ ወ/ሮ መንበረን ጨምሮ ሁሉም ሰፈርተኛ ተገኝቷል።

*ወህኒ ቤት የነበረው ልጃቸው ለይኩን ግን ዜናው የደረሰው ከሁለት ሳምንት በኋላ ነበር። የሐዘኑ ነገር ተከድኖ ይብሰል።*

⌘ ⌘ ⌘

ለደጉ ገበሬ ታሪኩን ሲያጫውታቸው የቆየው ለይኩን የእናቱን አሟሟት ሲያስብ እንባው ቀደመው። የኔ ከርታታ እናት አለ በሆዱ። "አንድም ቀን ሳይደላሽ አለፍሽ፤ ቢያንስ የኔን ምርቃት ሳታይ፣ ሰው ሆኜ ሳላግዝሽ... በወጉ የልጅ ልጄን ሳላሳቅፍሽ አረፍሽ እማ..." እያለ ከራሱ ጋር በሀዘን ተብሰለሰለ። ለጉድ የሚፈሰውን እንባውን ያስተዋሉት ደግ ሽማግሌ እጃቸውን ትከሻው ላይ ጣል አድርገው ያጽናኑት ገቡ፤ ..."*ተው ልጄ! ራስህ ላይ ሀዘን አታብዛ... ምትኮ ድልድይ እንጂ መዳረሻ አይደለም። ህግና ደንብ በሌለው ረጅም ሰልፋችን ላይ ሁላችንም በረድፍ ቆመን ተራ እንጠብቃለን። አእምሯችን የሚያቅደው ህይወት ለዚህ የነፍስ መሻገሪያ ሰልፍ ትርጉም የለውም። ሰዓቷ ስትደርስ ከተፍ፣ ነፍስህ በቃ ስትባል ቆይ አንዴ የለም፤ አቤት ብሎ መቀበል ብቻ ነው። እናም የኛ ሀዘን ማብዛት የተፈጥሮን ህግ አይቀይርምና ሀዘን አታብዛ"*

"እሺ አባት!" አለ ለይኩን በለሆሳስ"

"ይልቅ ሰውነትህ በጣም ያቃጥላል፤"

"አዎ አባት ብርታት አይሰማኝም፣ ቁስሌም ክፉኛ እየጠዘጠዘኝ ነው"

"እንግዲያውስ ቁስልህ በባክቴሪያ ‹ኢንፌክትድ› ሳይሆን አልቀረም?" ብለው በጥንቃቄ ልብሱን ከፍ አድርገው ሚስማር የወጋውን ቦታ ተመለከቱት፣ ክፉኛ መርቅዟል፣ ሳያስቡት ፊታቸውን ቅጭም አደረጉት። ለይኩን የገበሬው ፊት ላይ ያየው ስሜት ደስ አላለውም። በሌላ በኩል

---

96 አንዳንድ ትምህርት ቀመስ ሰዎች እድር ምን ያደርጋል እያሉ ቢከራከሩም ኪሎን-ልቦና ሣይንስ አንጻር የሚመከር ነው:: ሰው የኔ የሚለውን፣ የሚወደውን ሰው ሲያጣ እንዲያለቅስና ውስጣዊ ሀዘኑ በእንባው እንዲታለብ ይመከራል:: ወደ ውጭ ካላለቀሰ ወደ ውስጥ እልቅሶ ራሱን ይጎዳል:: ብቻውን ከሚያለቅስም ከሰዎች ጋር ቢሆን በአብሮነትና ድጋፋቸው መጽናናት ያሻል:: ስለዚህ ለቅሶ ለሟች ሳይሆን ለቀሪ ወዳጆቹ ነው ማለት ነው ጠቀሜታው:: ምንም ጠቀሜታ ቢኖረውም ከልኩ በላይ የበዛና የተራዘመ የለቅሶ ሥርዓት ግን ጎጂ ነው::

97 ለለቅሶ ቤት የሚለበስ ጥቁር ነጠላ፤

አንድ ሽማግሌ ገበሬ ‹ኢንፌክትድ› የሚል እንግሊዘኛ መጠቀማቸው ግራ አጋብቶታል።

በደጉ ሽማግሌ ትእዛዝ መሰረት ያቺ የለይኩንን ቀልብ የገዛች ትንሽ ልጅ ለብ ያለ ውኃ በጨው አድርጋ ይዛ ገባች። ይህቺው ብሩክ ልጅ የእግሩን ቁስል እያጠበች ሳለ፤ ህመሙ እየረበሸውም ቢሆን ለይኩን የህይወቱን የመጨረሻ ክፍል ለደጉ ገበሬ ያጫውታቸው ጀመር።

* ✡ *

# ሃያ አራተኛ ምዕራፍ

# አርምሞ

◉

ዶ/ር ሶፎኒያስ ለዝምታ ሲል ተጉዞ በአርምሞ ተሸልሟል። ይኸው አሁንም ሰተት ብሎ አራተኛው ሸለቆ ገብቷል። ውቡ አራተኛው ሸለቆ አረንጓዴ በአረንጓዴ ሆኖ ነበር የጠበቀው፤ ልምላሜ ዙሪያ ገባውን አጥለቅልቆታል። በፍቅር ተተክለው የጸደቁ ችግኞች አካባቢውን ሞልተውታል። የናሺፍ ቄጤማው ተፈጥሯዊ ማዕዛ፡ እስትንፋስ ያለውን ነፍስ ሁሉ ያውዳል። በዚህ ደን ውስጥ ምድረ ገነት መሳይ ሥፍራ ሰማይ ጠቀስ ዛፎች ተሰይመዋል። እጅግ በሚማርክ አስገራሚ ግርማ ሞገሥ ወዝ ወዝ፣ ዘንጠፍ፡ ገንደስ ሲሉ ልብን ያሸፍታሉ።

ሶፎኒያስ በዝግታ ወደ አንዱ ግዙፍ ዋርካ ተጠጋ። በቀረበ ቁጥር ዓይኖቹ ከዛፉ ሥር አንድ ለየት ያለ ቅርጽን መለየት ጀመሩ። ይበልጥ እየተጠጋ ሲመጣ የሰው ቅርጽ እንደሆነ አስተዋለ። ገላቸው ላይ ቅጠሎች የበቀሉባቸው፣ በዛፉ ግንድ ውስጥ የተሰበጠሩ፣ እጆቻቸውና ጣቶቻቸውን እንደ ቅርንጫፎች ያስጨፈረሩ፣ እግሮቻቸው ከዛፎቹ ሥራ-ሥሮች ጋር ተጋምደው ከመሬቱ የተቀበሩ፣ አረንጓዴ ድልሽ ሽማግሌን በቅጡ አስተዋላቸው። እንደዚህ አይነት አስገራሚ ፍጡር በህይወት ዘመኑ በፍጹም አይቶ አያውቅም። እየፈራ፡ እየቸረ ወደ ዛፉ-ሰው ተጠጋ።

"ና!... ቅ..ረ..ብ.. ወደዚህ... አት..ፍ..ራ...!" አሉት፡ ጎርነን ባለ ድምጽ፤

"እሺ" ብሎ ይበልጥ ተጠጋቸው፤

"ቁጭ በል፤" ብለው ከጎናቸው እንዲቀመጥ ጋበዙት፤ ሲፈራ ሲቸር ከዛፉ አጠገብ ተቀመጠ፤

"ፈራህ እንዴ?"

"በመጠኑ፤"

*"ሕንግዲያውስ ለኔ ብለኽ ስማና ቆፍጠን፣ ደፈር በል፤ እንደኔ አይነት ከምታውቃቸው ለየት ያሉ ነገሮችን ባየኽ ቁጥር የምትፈራ ከሆነ ጥሩ ተጓዥ አትሆንም። የአዲስ ነገር ፍርሃትኽን በማነኛውም መንገድ ማሸነፍ መቻል አለብህ። ፍርሃት ማለት በምናብህ ውስጥ የሚሰለጥን/ዞሮም የምናብህ ገዳይ ደዌ ነውና። "እመን እንጂ አትፍራ" እንዲል ቃሉ በእምነት ሥሮችህ ለመጥለቅና ለመዝለቅ ሞክር። እርግጥነው ብዙኃን ሰው እንኳንስ እኔን መሰል ፍጡር አይቶ ጫካ መሄድን ይፈራሉ። ብዙ ጎልማሶች ውስጥ ጫካና ጨለማን የሚፈራ ትንሽዬ ልጅ አለ። ይሄም በአስፈሪ ተረቶች፣ ፊልምና ትርክቶች ተቀርጾ ስለሚያድግ ይሆናል። እርግጥ ጫካ ከሌሎች እንደ በረኻ፣ መስክ፣ ተራራና ውቅያኖስ ካሉ የዝምታ ተምሳሌቶች ይለያል። ምክንያቱም ሌሎቹ ላይ ተሰይመኽ በዓይንህ እስከ አድማስ ጫፍ ታያለኽ። በጫካ ግን ከፉም ደግም ቢመጣ የማየት እድልኽ ጠባብ ነው። የኛ ደን በድምጽና በጸጥታ፣ በዛፍ ጥላና በዛፍ ጠል የተደበቁ እልፍ ሚስጥራትን አዝሏል። አንተ ግን እርምጥ ከሆነ ግብርኽ ፍርሃት ከቶ አያሻኽም። ከደኑ ኑዋሪዎች ጋር ካለ ቃል ትግባባለኽና መጥፎ አያገኝኽም። እናም ፈጽሞ አትፍራ።*

*ደግሞም ይህን በቅጡ እወቅ፣ ፍርሃት ትልቁ የፍቅር ጠላት ነው። ውጫቸውንም ውስጣቸውንም መጋፈጥ የሚፈሩ ሰዎች በወከባና በጩኸት ተደብቀው ፍቅርና እውነትን ሲሸሹ ይኖራሉ። እኛ ዛፎች ግን በእርምጥ ጸንተን ዝናብ ቢዘንብብንም፣ ንፋስ ቢነፍስብንም፣ እሳት ቢነድብንም ከመሠረታችን ሳንርቅ እንቀበላለን።" አሉና ሽማግሌው ዛፍ የቅርፊት ቅንድባቸውን ሽቅብ ሰቅለው፡ ጭራሮ የከበበው ዓይናቸውን በለጠጡት፤*

*"የሆነ ሆኖ ከዚህ አድካሚ ጉዞኽ በኋላ አሁን አራተኛው እርከን ላይ ደርሰኻል። ይህ በእጢዎች አለቃ ‹ፒቲዩታሪ[98]› እጢ፣ የሚዛንና ቀጥ ብሎ የመቆም ኃላፊው የአንጎል ክፍል ‹ሴሬብለም› ይመሰላል። በዚህ ድልድይ ላይ ቆመህም በተመስጦና ማሰላሰል ብዙ ጥያቄዎችን*

---

98 ይህ ስም ‹ፐቲያና ‹ፐትሃ› ከተሰኘው የኩሽ ንጉሥ የተገኘ እንደሆነ አንዳንድ የጥቁር ታሪክ ጸሐፍት መላ ምታቸውን ያስቀምጣሉ፤ ለዚህም የፒዩቲታሪን እጢ የሚያሳይ ከ3000 ዓመታት በፊት በፒራሚድ የተቀረጸን የአእምሮ ስዕል ማስረጃ አድርገው ያቀርባሉ።

ታስተነትን ዘንድ ይገባኻል። ገና ልጫጭም፣ ልዋጭም የሆኑ ወሳኝ የኑሮ ሐሳቦችን እያነሳኽ ትመራመራለኽ። ከአንቀጽ እስከ ፊደላት ድረስ ምስጢሩን ትፈታለህ… የቀደምት ጠቢባን መንገድንም ትከተላለኽ፤ ያኔ ገና… ያኔ… ከጥላችን ሥር ተቀምጠው፤

"ይሄ ዛፍ እንደኔ ምን ይወዘውዛል?

አፉ ባይናገር ሆዱ ነገር ይዟል።" ሲሉ ተቀኝተው ነበር ወልዩ የደርቃ ልጅ"

…አሉና ሽማግሌው ቅርንጫፍ እጆቻቸውን እያሳጉ ተንጠራሩ፤ የተወሰኑ ቅጠሎች ከሰራ አካላታቸው ላይ ረገፉ።

"ምን መሰለኽ?… እኛ ዛፎች ብዙ እናያለን፣ ብዙ እንታዘባለን፣ በግንድ ሆዳችን ብዙ ፈውስም፣ ምስጢርም አቁረን እንይዛለን። ነገር ግን የትኛውንም ምስጢር አውጥተን አናባክንም። እንደ ጠንካራ ወንድ የሆዳችንን በሆዳችን ይዘን ሥራና ኑረታችን እንቀጥላለን… እናም ልጅ ሶፎኒያስ፤ እንደኛ ወንድ ሁን ብዬ ልመክርኽ እፈልጋለሁ። ወንድ ሁን ስልኽ ደግሞ ከሴት ተቃራኒ ስለመሆን/ አልያም ጡንቻዎችህን ስለማደለብ እያወራሁ አይደለም። የሥጋህን ነገር በአንደኛው እርከን ላይ ተምረሃልና እሱን አልደግምልህም። ወንድ ሁን ማለቴ ግን ባጭሩ ራስህን አሸንፍ ለማለት ነው። እንደ መድሐኒዓለም በትህትና ጎንበስ ብሎ እግር ለማጠብ የማይታበይ ወንዳወንድ ብጹዕ ማንነትን ገንባ። ጀግና ማለት ጠላቱን ታግሎ የጣለ ሳይሆን በንዴት ጊዜ ራሱን መቆጣጠር የቻለ ነው እንዲሉ ነቢ. እኔም ወንድ ሁን፤ ቃላቶችኽን ለመቆጠብም ጀግን እልኻለሁ።

እስኪ በህይወትኽ የምታውቃቸውን ሰዎች መለስ ብለኽ አስታውስ። በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት ደህንነት የማይሰማቸው ሰዎች እብሪተኛ ሆነው ታገኛቸዋለኽ። መሰል ሰዎች እውነትን በሀሰት ያጠለሻሉ፣ ከራሳቸው አልፎ የሌሎችን የሰላም ጥልቅ ጉዞ ያኮላሻሉ። የሰላምና የጽድቅን መንገድም አስቸጋሪ ያደርጋሉ። ይህንን አስመልክቶ አንድ ሊቅ በብሒለ አበው ውስጥ እንዲህ ይላሉ፤

"እመ ተናገርኩ ጽድቀ ሰብአ ዛቲ ዓለም ይጸልዑኒ፤

ወከመ ኢይንብብ ሐሰተ ኩነኔ ዚአክ ያፈርሀኒ፤

*እም ኵሉስ አርምሞ ይኄይስ ወይሤኒ፤" ትርጉሙም...*

*"እውነት የሆነ ቃል መናገር እንዳልችል የዚህ ዓለም ሰዎች ጠላት ያደርጉኛል፤*

*ሐሰት ተናግሬ በሰው እንዳልወደድ ያንተ (የፈጣሪ) የእውነት ፍርድህ ፍጹም ያስፈራኛል፤*

*ከዚህ ሁሉ ሥጋት፣ ከዚህ ሁሉ ፍርሃት፤*

*ታላቁ አርምሞ፣ ዝምታ ይሻለኛል::"*

እንደማለት ነው:: እናም አንዳንዴ ዝም ማለት የተሻለ አማራጭ የሚሆንባቸው ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ:: ነገር ግን ፍርሃት ቀጣይነት ያለው ያልሆነና በራስ መተማመን ከማጣት የሚመነጭ መሆን የለበትም:: በራስ መተማመን የሌለውማ ሰው እዩኝ እዩኝ እያለ ይውላል:: ተፈጥሮ ግን ይሄን አታውቅም: ለምሳሌ ብዙ መድሃኒትነት ያላት እንጉዳይ በትንሽ ዛፍነቷ አታፍርም:: እንዲሁ ሁሉ ትልቅ መስሎ ለመታየት የሚሞክረውና ፍርሃት የሚወርሰው የሥነ-ልቦና ደህንነት ስጋት ያለበት ሰው ነው:: ይህንን ፍርሃት ለመደበቅ የሚደረጉ ጥረቶች ደግሞ እብሪት፣ ቁጣ፣ ንቀት፣ ታይታና ማስመሰልን ይወልዳሉ:: እናም ወዳጄ መሸነፍን አትፍራው:: አበክረህ ልብ በል... የማጣት፣ የማነስና የመበለጥ ፍርሃት የአብዛኛው ኃጢያት ሥረ-መሠረቶች ናቸው::

ከታዘብኩ ከምንም ነገር በላይ የሰው ልጅ መቀበል የሚከብደው ሽንፈቱን ነው:: ከስንፍናው በላይ ሰነፍ መስሎ መታየቱ ያሳስበዋል:: ለሌሎች ደካማ መስሎ መታየትን የማይፈሩ ግን እውነተኛ ጠንካራዎች ብቻ ናቸው:: ደካሞች ያሌላቸውን ለመሳየትና በጥቂት ባለቻቸው አልያም በሌላቸው ነገር ራሱ ሲኩራሩ ታያለኽ፤ ሌላው ማወቅ ያለብኽ ነገር ልኩራ ብትል እንኳን ኢምንት መጠንህና እዚህ ግባ የማይባል ኃይልህ ለኩራት እንደማያበቃኽ ነው:: የአንተ አካል ምድር ላይ ልክ ‹ዳይኖሰር› ላይ እንደ ቆመ ቫይረስ ይመሰላል:: እሱንም ሳትረሳ በዚሁ ላይ የህዋ አካላትን ግዝፈት ደግሞ አስብ:: ለምድር ቅርቧ ኮከብ ፀሐይ፡ ከመሬት 1.3 ሚሊዮን እጥፍ ትበልጣለች:: እናም ከፀሐይ በሚሊዮንና ቢሊዮን እጥፍ የሚበልጡ ከዋክብት እንዳሉ አክልበት:: እናም ከዚህ አንጻር ያንተ አካልና ቁሳቁስ ኢምንት ሳይሆን ምንም ነው:: ለብዙሃኑ ግን ይሄ እውነታ አይገለጥም:: ምክንያቱም ለቅማል ከምንዱባን የአንዱ የራስ ቅል ዓለሟ ነው፣ ቀጫጭን ጸጉሮቹም ዋርካዎች ሊመስሏት ይችላሉ:: ማን ያውቃል? አንድ ጢኖ ባክቴሪያ ደግሞ በተራው እዚሁ ቅማል

ላይ አህጉሬ ነው ብሎ ከትሞ ይሆናል:: ሐቁ ግን ለህዋ ማነኛችንም እንዲያው ከቁጥር የማንገባ እፉኝት ነንና፤ እንኩራ! ... እንስገብገብ!... እንመጻደቅ!... እንታበይ!::" ብለው በአፅንኦት አስገነዘቡትና ቀጠሉ፤ "ሌላው ወንድ ሁን የምልህ ልጅ ሶፎኒያስ| ከውጫዊው ገጽታ የበለጠ ውስጣዊ ማንነት ይኑርህ ለማለት ነው:: መልክህ፣ አለባበስህ፣ የምትነዳው መኪና አልያም የምትኖርበት ቤት ያንተን ዋጋ አይተምኑ:: እንኳንስ ቁሳቁስህና ሀብት ንብረትህ ቀርቶ ሥራህ፣ ማእረግና ቤተሰብህ እንኳን ያንተ አይደሉም:: ሌላው ቀርቶ ጤንነትህ፣ የሰውነት ክፍሎችህ... አንተ ራሱኮ ያንተ አይደለህም:: አለኝ የምትለው ነገር በሙሉ ከጊዜ በኋላ ያገኘካቸው፣ ከጊዜ በኋላም የምታጣቸው ናቸው:: ታሪክን ዞር ብለኸ ብታስተውል የሰውን ልጅ አኗኗር በልህቀ የቀየሩ ዲበ ሰዎች| ከውጫዊው ይልቅ ውስጣዊ ማንነታቸው ላይ የሠሩት ናቸው:: ነብያት፣ ሳይንቲስቶች፣ ምሁራን፣ ጠበብት፣ ፈላስፎች፣ ጸሐፍት፣ ተመራማሪ፣ ደጎች፣ ፈጣሪዎች፣ መሪ፣ ሊቃውንት፣ ዜመኞች፣ ትጉሃኖች፣ ፈር ቀዳጅ ባለጠጋዎች፣ ህልም ያላቸው ባለ ራእዮች በሙሉ ከውጫቸው ይልቅ ውስጣቸው ላይ የሠሩት ናቸው:: ራሳቸውን አውቀው፣ ዓላማቸውን አስምረው የሚጓዙ ሰዎች አሁንም ምድር በብዛት ያስፈልጓታል:: ቀደምት የሰው ተምሳሌቶችም አንድ የሚነግሩን የጋራ እውነታ ቢኖር ከውጩ ይልቅ ውስጣችን ያለው አንጡራ ሐብት በብዙ፡ እልፍ አእላፍ እጥፍ እንደሚበልጥ ነው:: *ይህን ስትረዳ እንደ ቡድሀ በወርቅ የተሞላ ቤተ-መንግሥት ትተህ በባዶ እግርኸ ትወጣለህ:: ዘጠኝ መቶ አመት የኖረው አብርሃም ለምን ቤት እንዳልገነባ ይገባኻል:: እንደ ካሌብ በትረ-መንግሥትህን በሰላም አስረክበህ ወደ ገዳም ትመንናለህ:: ብቻህንም ቢሆን ከተፈጥሮ እውነት ጋር ትዛመዳለኸ:: ታዲያ ዋጋ ሊያስከፍልኸ ይችላል:: የህዋ ድንበር አልባነት ቀድሞ እንደገባው የአስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን ሳይንቲስት ከነ ህይወትህ ልትቃጠል*[99] *ሁላ ትችላለህ:: እውነትህ ግን ለዘላለም ያንጸባርቃል::"*... ሶፎኒያስ በምናባዊ የተመስጦ ምህዋር የሚደርሰውን ጥበብ በትኩረት እየተከታተለ ዘልቋል:: ወደው የሰሙት ነገር ከልብ ያርፋልና እያንዳንዷን ጥበብ እየመዘገባት ነው:: ነገ ለሚገጥመው ፈተና፣ ለሚረዳቸው ታማሚዎች፣ ለሚጽፈው መጽሐፍ ብዙ ግብዓቶችን አግኝቷል::

በአንዳች መንፈሳዊ ኃይል ከዛፉ ጋር ተዋህደው በእርምሞ የሚኖሩት

99 በ1600 እ.አ.አ ጂዮርዳኖ ብሩኖ የተባለ ጣሊያናዊ የሒሳብ ሊቅ፣ ጸሐፊ፣ ገጣሚና ፈላስፋ በሮማ ካቶሊክ ቤ/ክ ውሳኔ በእሳት ተቃጥሎ እንዲሞት ተፈርዶበታል:: ይህ ውሳኔ የተፈረደበት በወቅቱ ለብቻው ባደረገው ጥናት የጠፈርን ወሰን አልባነትና የሌሎች ከዋከብትን ከፀሐይ እኩል መሆንና መበለጥ በመናገሩ ነው፤

ሽማግሌ የአራተኛውን እርከን የመጨረሻ አስተምህሮዎቻቸውን አስታትለው አደረሱት።

"እናም የአራተኛው እርከን አረንጓዴ የመሆን ምስጢሩ ሲፈታ የምድርን ዝቅ ብሎ የመለምለም ጥበብ የሚገልጥ ነው። ምድር የወደቀባትን በሙሉ፣ ሳታዳላ፡ ከሥሩ ሆና ትቀበለዋለች። ምን ግዙፍ ብትሆን ከቆዳዋ ላይ የሚርመሰመሱትን ጥቃቅን ፍጡራን ታግሳ ታልፋለች። የሚጥሉላትን ቆሻሻ በዝምታ ተቀብላ አበስብሳ ከገላዋ ጋር ታዋህዳለች። እኛ ዛፎች ደግሞ ይህን ሁሉ ችላ የምታሳድገን ልጆቿ ነን። ትንሹ ፍሬያችን፣ ቀጭኑ ሥራችን፡ ከውስጧ ሲተክል ሳትንቀን ታበቅለናለች። ዘራችንን አበስብሳ፣ አብስልስላ፣ አሰላስላ፡ ወደ ፍሬ ትቀይረዋለች። ከሚከረፋ የእስክሬን ብስባሽ አረንጓዴን ቅጠል የማብቀሉን ጥበብ ተክናበታለች። የሚጠረናውን የሽንት ቤት ተረፈ ምርት ተረክባ፡ የሚያውደውን ውብ ጽጌሬዳ ታፀድቃለች። ይህም የዝምታዋ፣ ትእግስቷና የሞላው መሰጠቷ የሚሠራው የፈጣሪ ተዓምር ነው። ስለዚህ እያንዳንዱ ዛፍና ተክል የምድር ውለታ አለበት። ሰውን ጨምሮ እያንዳንዱ ምድር ላይ የሚኖር ፍጡር ደግሞ የዕጽዋት ውለታ አለበት።

ይህንንም ጠንቅቀኸ ታውቅ ዘንድ ነገርኩህ፤ ሁላችንም የተሳሰርን ክብ እንጂ የተለያየን ነጠብጣቦች አይደለንም። ሁሉም የተፈጥሮ አሠራር የተናበበ ጥልቅ መስተጋብር አለው። የተተከለ ሁሉ እስኪበቅል ትዕግስትና ጽናትን ይሻል። ዘር ከአፈር ሲከተት ይበሰብሳል። የሚበሰብሰው ግን ውብ አበባን ይዞ ለመውጣት፣ ለመፍካት ነው። በትውልድ መተካካት ካየነው ሁላችንም መሬት የምትባል የአንድ ግዙፍ ፍጡር ህዋሳት ነን። ለምሳሌ የዚህ ደን ዛፎች በሙሉ በሥሮቻችን በኩል ሳናወራ እንናበባለን። *{በተለይ አልበርት ፈርናንድ የተባለ የደን ተመራማሪና ሌሎችም የቅርብ አጥኚዎች እንዳረጋገጡት ዛፎች በእንጉዳይና ፈንገስ መረብ የተዘረጋ የአፈር ሥር የግንኙነት መስመር ‹ኔትወርክ› አላቸው። በሥሮቻቸው ይናበባሉ፣ ይረዳዳሉ፣ ማዕድናትን ይጋራሉ ወዘተ... ይህ አንድነታቸውም በአፍር ውስጥ ያለን ድንጋይ እስከማፍረስ የሚደርስ ጥንካሬ ለግሶ የደኖችን ህልውና ያረጋግጣል፤}*

ችኩሉ የሰው ልጅ ግን ይህን ውድ ትእግስት አያውቀውም። ትንሹን እውቀቱን ሆጼላስ ብሎ አዝሎ፡በወሬ እንደ ዮጵ ወርቅ ሊያገዝፈው ይዳዳል፤ ትልቁን የጥበብ ዋርካ ለማናናቅ ትንሽዬ ስንጥር ይዞ ይዘምታል። ተፈጥሮን ለምቾቱ ሲል እጇን እየጠመዘዘ ...ራሱን ይሰብራል። በረደኝ ብሎ ዛፍ ቆርጦ እየሞቀ ግግሮቹን የምድር በረዶዎች ያቀልጣል...

*በጎርፍ ሲጥለቀለቅ፣ በነበልባል ሙቀት ሲቃጠል ይፋጠናል።*

*ይህን ደግሞ መሐመድ ደርቃ እንዲህ ሲሉ ተቀኝተውታል፤*

*"ቆረጡት ያንን ዛፍ እነ ልክ አያውቁ*

*ምን ያፈራ ይሆን ብለው ሳይጠይቁ፤*

*አባይ ጣና ሞልቶ ዳሩን ሲጠርገው*

*ምን ጥልቅ አደረገው ዋና የማያውቀው?"*

አበባና ዛፍ እጅ አይወዱም። እናም አረንጓዴነት ከተስፋና ከታጋሽ ሂደት በኋላ የሚመጣ ሲሆን በተቃራኒው ማፍረስ፣ መቁረጥ፣ ማቃጠል፣ መንቀል ግን በቀይ ቀለሙ ከሚወከለው ዝቅተኛው ስሜታዊ ግልፍታ የሚፈጸም የቅጽበቶች ጉዳይ ነው። ከሙላት እስከ ጉድለት ይደረድራል። ይህን የቀለማት ውክልና የሚያውቁ ኢትዮጵያዊ አባቶች ባንዲራችንን ከላይ ወደታች በአረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ መደብ አኑረው አሳልፈውታል። ቅደም ተከተሉ በምክንያት እንጂ በአጋጣሚ እንዳልሆነ ልታውቅ ይገባል። ይህን የተረዱ የዘመኑ ሥርዓቶችም ቀለሞቹን በቅደም ተከተላቸው ይጠቀሙታል።

*{የትራፊክ መብራት፣ የባትሪ ቻርጅ መለኪያ፣ የአውሮፕላን በረራ የአየር ንብረት መጠቆሚያ፣ የሙቀት መጠቆሚያ ካርታዎችና ሜትሪዮሎጂ ወዘተ መጥቀስ እንችላለን።}*

*ታዲያ ይህንን የመስከንና የመታገስ ጥበብ ስትላበስ ትበስላለኽ። በሰውነት ቆይታህም ከመጠን በላይ በልተህ አትጠረቃም፣ በቁንጣንም አትሰቃይም። ይልቅ በትንሽ ነገር ረጅም ጊዜ የመዝለቅና የመኖር የዛፍ ባህሪን ትላበሳለህ። በጥቂት ምግብ ለቀናት የሚቆዩ ተመሳጮችኮ የውስጣቸውን የምግብ መፈጨትና መቃጠል መቆጣጠርን የቻሉ ናቸው። ይህም ኃይልን አስፈላጊ ለሆኑ ነገሮች ብቻ በመጠቀም ፍጆታን መቀነስንም ያካትታል። በዚህ ጥበብ ምግብ በአፋቸው ሳይዞር ለዘመናት የቆዩ ሰዎች እንዳሉ አፈ-ታሪኮች ይነገራሉ። ለመኖር እንደ ዛፍ ውኃ፣ ፀሐይ፣ ንፋስና አፈር ብቻ በቂያቸው የማድረግ መሰጠት ላይ ለደረሱት ይህ የማይሆንበት ምንም ምክንያት የለም።*

*ምክንያቱም መንፈስህ ገደብ አልባ ነው፤ ሁሌም ቢሆን ከሥጋኽ በላይ ነፍስና መንፈስህ ጠንካራ እንዲሆን ሥራ። ለዚህም የመግቢያ በሩ ልብ ነውና ልቦናኽን ግራው። ያኔ ግሩም የሆነን አክሊል ትጎናጸፋለኽ። ይህ*

እርከን ላይ ስትደርስም ሰላማዊነት፣ ሁለንተናዊነት፣ ትእግስትና ዘላቂነት ይዋሃድኻል። እናም አንድ ሆነኽ ብዙ፣ ትንሽ ሆነኽ ትልቅ ትሆናለህ። ከዛፍ ሥር በጽሞና[100] እንደተቀምጥክ የቀንዲልህ ቅርንጫፎች ከፍ ከፍ፣ ዘለግ ዘለግ ይላሉ!" ብለው ምክራቸውን አገባደዱ። ሶፎኒያስ ጥያቄዎቹ ከጠበቀው በላይ እየተመለሱለት ቀጥሏል። እንዳሉ የማያውቃቸውን ጥበቦች እየተገለጡለት| እንደሚችል ያላስተዋላቸውን ክህሎቶች እየተካነ ዘለቀ። ለሜሮንም ሆነ ለሌሎች ታማሚዎቹ የሚጠቅሙ እውቀቶችንም እየቀሰመ ነው። ያሳለፈውን አስገራሚ ጉዞ ዞር ብሎ ሲመለከት ደግሞ የቀሰመውን ልዩ ትምህርት በመጽሐፍ መልኩ ለብዙኃኑ ማዳረስ እንዳለበት ማሰብ ከጀመረም ከራርሟል። በምን መልኩ መጽሐፉን እንደሚያዘጋጅ እያውጠነጠነ ሳለ የዛፉ-ሰው ድምጽ ደርሶ ቀሰቀሰው።

"እነሆ ወደ ታች ተመልከት!" የሚል ትእዛዝ ነበር የመጣለት፤ ሶፎኒያስ ጎንበስ አለ። ከግዙፉ ዛፍ ሥር አንድ ሰማያዊ ምንጭ ቡልቅ ቡልቅ ሲል በዓይኑ-ልቦናው አስተዋለ። ምንጩም እየጨመረ መጥቶ በአንድ ቀጭን መስመር ተጀርቶ፣ ይንፎለፎል ገባ። ... "ልጅ ሶፎኒያስ! ይህቺን ቸረት ተከትለህ ዝለቅ፣ ወደ እምስተኛው እርከንም ታደርስኻለች፤" አሉና ዛፉ-ሰው ቅርንጫፎቻቸውን ሰብስብ አድርገው ወደ ውስጥ ሰረጎዱ። የስንብት የሚመስል ዝማም ኃይል ለቀቁናም| በቅርፊት ሽፋሽፍት ዓይኖቻቸውን ከደኑ። እንቀላፉ።

⌘ ⌘ ⌘

## ቃሊቲ ማረሚያ ቤት

ጩኒ ከእሥር ቤቱ አንድ ጥግ ቁጭ ብሎ የእንጋፋው ቴዎድሮስ ታደሰን ዘፈን ያንጎራጉራል፡

*"ሽረ እንዲያው ዝምታስ ምን ሊሆን?*

*ልብ እየተረታ - ሆድ እያመነታ፣*

*እንደበትህ ታስሮ በጊዜ አትረታ*

*ጉም ጉሙን ትተኽ ተናገር ለአንድ አፍታ!*

---

100 ከቀደምት ኃይማኖቶች አንዱ የሆነውና አሁን በዓለም ላይ ከሚሊዮን በላይ ተከታይ ያለው የቡዲዝም ኃይማኖት መሥራች ጉተማ ቡድሓ የእውቀት፣ እምነትና እውነት ጥበብ የበራላት ለሰባት ሳምንታት በዲ ኩተለንኙ፣ ቅጠሏ ልብ ቅርጽ ከሆነ ዛፍ ሥር ሳይንቀሳቀስ በአርምሞ ከተቀመጠ በኋላ ነው፤

*ልብም እንደ ባዳ ከከዳት ተማክሮ*
*እውነት በሆድ ይዞ እውነት ተቸግሮ፣*
*የነገን ሳይቋጨው በተስፋ ውሎ አድሮ*
*ድካም ይጫነዋል እድሜ ብዙ ቆጥሮ፤*
*አዬ ጉድ.. አዬ ጉድ.. ይላል የሀገሬ ሰው*
*ትዝብቱ ታምቆ ሆዱን ሲያላውሰው፤*
*ቀኑም ቢጨላልም ሌሊቱም ሲነጋ*
*ሳያልፍ እያለፋም ከሐሰት አትጠጋ፤*
*ያሰብከው ባይሞላም ያልከው ባይሰካ*
*ያለምከው ቢጠፋ...*
*ወዳጅ ፊቱን ቢያዞር በውሎህ ባትረካ*
*አትዘን እንግዲህ ከቶ አትቁረጥ ተስፋ*
*ጊታም አይጣላ ሳይደግስ ሳይዘክር*
*እውነት ከቤት ይዘህ በብድር አትመስክር፤*
*ሆድ ከሀገር አይበልጥም ግን ከሀገር ይሰፋል*
*የወለዱት እንጂ ቃል እንዴት ይጠፋል?"*

የመጨረሻውን ስንኝ ወልኛ አባባል ሲሰማ ለይኩን የኛ ሰው ለቃል የሚሰጠው ዋጋ ከልጆቹ በላይ ነው ሲል አሰበ። መልሶም "የኔ ሚስት ግን በልጇ ምላ በውሸት መሰከረች።" ብሎ እድሉን አማረረ። እኮ ግን ምን ነክቷት ይሆን? በኔስ እሺ በአንድ ልጇ ግን እንዴት ጨከነች? ... ሐሳብ ሐሳብን እየተካ ቀጥሎ ስለ ህጻን ልጁ ስለ መርዕድ ማሰብ ጀመረ። ሌላው ቀርቶ ዓይኑን እንኳን ካየው ብዙ ጊዜያት አልፈዋል። የህጻን ጠረኑ፣ ትንቡክ ትንቡክ የሚል ገላው፣ ዓይኑን ፍጥጥ አድርጎ እያቁለጨለጨ የሚጫወተው ነገር፣ ከምንም ተነስቶ የሚፍለቀለቀው ገጽታው በሙሉ ቀን በቀን ትዝ ይሉታል። ሌላው ቀርቶ ንጭንጭና ለቅሰው ራሱ ናፍቆታል። ትዝታ ደግሞ ልዕለ ኃያል ነገር ነውና ስሜቶች ሁሉ ይገዙለታል። ለይኩንም የልጁ ነገር ትዝ ሲለው ስሜቱ ይረበሻል። ብዙ ሲያውጠነጥን ከቆየ በኋላ እንደ ምንም ወደ ጬኒ ሄዶ ከጎኑ ተቀመጠ።......."ጬኒ?"

"አቤት፤"

"ላስቸግርሽ እስኪ? ... አንድ ዘፈን ዝፈንልኝ?"

"ምን የሚለውን ዘፈን?"

"እብነት አትናፍር ስለ ልጅ የዘፈነውን... እእ... ልርሳህ እስኪ ትዝ አትበለኝ... የሚለውን..."

"አው... ልጅ አለሽ እንዴ አባቱ?"

"መጀመሪያ ዝፈንልኝና እነግርሻለሁ።" አለ ለይኩን አሁንም የትንሽዬ ልጁ የመርዐድ ገጽ በዓይኑ እየዋለለ፤

"እሺ..." አለና ጩኒ ጉሮሮውን ጠራርጎ ጀመረ፤

*"ልርሳክ እስኪ ትዝ አትበለኝ፤*

*ልጁ እባክህ አትናፍቀኝ!*

*የአባት ፍቅር የተለየኝ*

*የአብራክ ክፋይ እንደምነኝ?*

*ትዝታዬም... አንተኮ ነህ*

*ሐብቴም ቅርሴም... ንብረቴ ነህ፤"*

ጩኒ ሆን ብሎ ለይኩንን ለማስደሰት ነበር ‹የእናት ፍቅር› የተለየኝ የሚለውን ስንኝ ‹የአባት ፍቅር› የተለየኝ ብሎ ያዜመው። በመሐል ዞር ብሎ ለይኩንን ቢያስተውለው አንገቱን አንጋጦ፣ በትካዜ የእሥር ቤቱን ጣሪያ ጣሪያ ሲመለከት አየው። ምንም ሳያዋራው ወደ ሙዚቃው ተመለሰ፤

*"አምላክ ካለ ጠንክር በርታ*

*እድሌ ነህ የኔ አለኝታ..."*

በዚህች ቅጽበት የእንባ ዘለላዎች ከለይኩን ጉንጮች እየተንደባለሉ ወርደው ከወለሉ ፈራረጡ። አፋም ከጩኒ ጋር አብሮ አዜመ...

*"... አምላክህን አመስግነው*

*ልጄ ሁሉም አላፊ ነው።"*

ጩኒ በተለይ በእርግጠኝነት የሚያስታውሳቸውን ስንኞች ረገጥ አድርጎ እስከተለና ዘፈኑን ደመደመ።

*"ስስት ህመም መከራዬ*

*ግንጥል ጌጤ አበባዬ፣*

*የምድር ላይ ጸጋ ጭንቄ*

*አንተኮ ነህ ለኔ ወርቄ፤"*

..."ዝፈንልኝ ስትልኮ እንዲህ የምታዝን አልመሰለኝም ነበር።" "ይቅርታ ...አስደበርኩህ መሰለኝ?" አለና ለይኩን ጉንጮቹን ጠራርጎ ወደራሱ ተመለሰ።

"እረ በፍጹም አላስደበርከኝም፣ የአባትነት ስሜት ምን ያህል ውስብስብ እንደሆነ ይገባኛል።" አለና ጩኒ ወደ መለስተኛ ማብራሪያው ገባ... "እናትነት እውነት አባትነት እምነት ቢባልም ቅሉ የእኔን ፋዘር ልፋት ሳስብ፡ የአባትነት ዋጋው ሁሌም ከፍ ብሎ ይታየኛል። ... እምም ለምን መሰለህ? የእናትነትን ዋጋኮ ሁሉም ያውቀዋል። ከእርግዝናው ጀምሮ የሚታይና የሚመሰከር ድካም አላት። የምጥን ተሰባብሮ የመገጠም ያኽል የሚከብድ ህመም ችላ ስትወልድ፣ ነፍስ ያላወቀ ጨቅላዋን መግባ፣ አሙቃ፣ ተንከባክባ ለራሱ እስኪሆን ድረስ ያለው ልፋቷ ሳይታለም የተፈታ| የአደባባይ እውነታ ነው። እናም ይሄን ሁሉ ልፋቷንና ስኬቷን ላየ፡ እናት እንደዚህ ለደከመችበት ፍጡር ፍቅር ባይኖራት በጣም ሊያስገርመው ይችላል። ማለት የእናት ፍቅር የተፈጥሮ ግዴታ ይመስለኛል። ለዚህም በግሌ ጥሩ አባቶችን ሳገኝ ይበልጥ ይገርመኛል። ከተፈጥሮ ህግ በላይ ህሊናና ልባቸው መርቷቸው ነውና ጥሩ አባት የሚሆኑት እጅግ ይደንቀኛል።"

"እምም.. የተወሰነ እውነት አለኽ... ግን ሁሉም እናት ተፈጥሯዊ የእናትነት ፍቅር እንዳለው ያጠቃለልከው ነገር አያስማማኝም፤"

"እንዴት?"

"እሱን እንኳን የልጄን እናት ተግባር ብታይ ነው የሚገለጽልህ!" ... ለይኩን እንቆቅልሽ ሆኖበት የቀረውን ጉዳይ ሲያስብ ነገሩ ሁሉ ገጣሚው - "አንቺን ግራ ይግባሽ ግራ እንዳጋባሽኝ - እንኳን ከሰውና ከራሴ አጣላሽኝ፤" ያለው አይነት እየሆነበት ለሰዎች ማብራራት ይከብደዋል።

"ታዲያ አጫውተኛ?" ጩኒ በጥያቄ ከሐሳቡ አነቃው፤ "አይ እሱ ረጅም ታሪክ ነው ... ይቅርብኽ... ይልቅ አንተ ራሱ ብዙ ጊዜ የምትዘፍናቸው ዘፈኖች ብሶትን ያዘሉ ናቸው። በውስጥህ የሆነ የሚያብሰለስልህ ሐሳብ እንዳለ ይሰማኛል።" አለ ለይኩን፤

"እንዴት እንደዛ ልትል ቻልክ?"

"ነገርኩህኮ እኮ...የምትዘፍናቸው ሙዚቃዎችህ ሁሉ የሚጠቁሙት እንደዚያ ነዋ።"

"ምድር ላይ እየኖረ... ለዚያውም እሥር ቤት ታሽጎ| ማን በሐሳብ መረብ የማይብሰለሰል ሰው አለ ብለህ ነው?"

"እሱማ ትክክል ነህ፣ ሁላችንም ጋር ቁስል አለ። የቁስላችንን ህመም የምንገልጥበት መንገድ ይለያያል እንጂ... አንዳዶቻችን ዝም እንላለን፣ አንዳንዶቻችን እንጮኻለን፣ አንዳንዶች ደግሞ እናዜማለን።"

"ልክ ብለኻል ለይክ"

"እዚህ ከገባሁ ጀምሮ የብዙ እሥረኞችን የተለያዩ ታሪኮች እየሰማሁ ነው።" አለ ለይኩን፤

"አዎ እዚህ እሥር ቤት መልከ ብዙ ታሣሪ አለ። እናቱ ባለማወቅ የሸጠችውን ሻት አልባ እቃ እኔ ነኝ የሸጥኩት ብሎ ለእናቱ ዳፋውን ከሚቀበል ልጅ አንስቶ ቤተሰቡ ታክቶት ‹ተመስገን! እሥር ቤት ገባልን› እስከሚባልለት ቦርኮ[101] ድረስ እዚህ ይገባል።"

"ያንተስ የእሥር ምክንያት ምን ይሆን?"

"የእኔ እንኳን ተወው፣ ፍቅር እዳ ሆኖ ነው የታሰርኩት፤"

"ማለት?"

"ንገረኝ ብለኽ ከገገምክ ልንገርኽ መቼስ... ያኔ ክለቦች እየሠራው ሙዚቃ ምናምን ስሞካክር ተመስጣ ነው መሰል አንዲት የጀኔራል ልጅ ካልጠፋ ሰው እኔን አፈቀረች፤ እኔ ወንድምሽ ደግሞ የምወዳት የምትወደኝ አንዲት የመዋለ ህጻናት መምህርት ፍቅረኛ ነበረችኝ፤"

---

101 ዱርዬ

"ሀእ?"

"እናማ የጄነራል ልጅት ካላገባኽኝ ሞቼ እገኛለሁ አለች። እኔም ፍቅረኛዬን መተው አልችልም አልኳት። ... እንደሆነ ነገር አደረጋት። በብስጭት አባቷ ጋር ሄዳ ደፈረኝ ብላ አቀሳሰረችብኝ[102]። እኔም ሰውዬው ፈልጎ ሳይገድለኝ በፊት ሄጄ እጄን ለፖሊስ ሰጠው። ይኼው ወህኒ ቤቱ ብዬ ተወርውሬ አለሁት።"

"አይዞን ወንድሜ፤" አለ ለይኩን በጬኒ አሳዛኝ ገጠመኝ እየተገረመ፤

"እኔ ግን የምልህ ለይክ?" አለ ጬኒ ትንሽ ሲያስብ ከቆየ በኋላ፤

"አቤት..."

"አንድ ወንድ አንድ ሴት ብቻ ነው ማግባት ያለበት ብሎ የወሰነው ማነው?"

"ምን አይነት ጥያቄ ነው ደሞ ይሄ? አንድ ለአንድማ ቅዱስ ቃሉ ያዘዘን ጥምረት ነው። ለአንድ አዳም አንድ ሄዋን እንጂ ሁለት ሦስት አልተፈጠሩምኮ!" አለና ለይኩን ረገጥ አድርጎ መለሰለት፤

"እሱንማ በሚገባ አውቃለሁ ለይክ፣ ግን ከታሠርኩኝ በኋላ ሁሌም የሚቆጨኝ ነገር ምን እንደሆነ ታውቃለህ?...መምህርቷ ፍቅረኛዬ እንዲህ የሚያስጨንቅህ ከሆነ ያሳሰረችኝን ልጅ አግባትና ተገላገል፣ እኔን እንደሆነ አታጣኝም ትለኝ ነበር። እናም አንዳንዴ ሁለቱንም አግብቼ ቢሆን ኖሮ ለዚህ አስከፊ የእሥር ህይወት አልዳረግም ነበር እያልኹኝ እፀፀታለሁ።"

"ምናልባት፤ ባንተ መንገድ ካየነው የሚያስኬድ ይመስላልል። ማለቴ እንደዚህ ካቅም በላይ የሆነ ችግር ሲኖር የማይፈጸምበት ምክንያት አይታየኝም።" አለ ለይኩን ከአፍታ ማሰላሰል በኋላ፤ "እኔም እንደዛ ነው የማስበው፣ ባይገርምኽ እዚሁ ቁጭ ብዬ ይሄ ሐሳቤ ሲበረታብኝ መጽሐፍ ቅዱስን አሌ ብዬ አጥንቼዋለሁ። እና በቅዱስ ቃሉም ቢሆን ያዕቆብ፣ ዳዊት፣ ሰሎሞንና ኤሳው ከአንድ ሚስት በላይ አግብተዋል። አብርሃም ልጅ ስላጣ ከሣራ ተጨማሪ አጋርን አስጠግቷል። በተለያዩ ጥቅሶችም ላይ ከአንድ በላይ ማግባት እንደተፈቀደ ያሳያል።" አለ ጬኒ፤ ያጣውን ህይወት መልሶ ያገኝ ይመስል በተስፋ ፊቱ እየነጋ፤

---

102 "በተንኮል አሻጥር ሠራችብኝ"

"አንተ ሰውዬ መታሰሬ ሳያንስ እንዳታስቀስፈኝ!"... ለይኩን ሳቅ አለ።

"የምሬንኮ ነው፤ ከአንድ በላይ ማግባት የሚቃወሙት በዋናነት ምዕራባውያን ናቸው። ለሴት መብት ተሟጋቾች ነን እያሉ በአፍ የሚሰብኩት እኒሁ ፈረንጆች ደግሞ ሴት ልጅን በመስታወት ውስጥ እርቃኗን አቁመው፣ እንደ ሸቀጥ አስተምነው የመሸጥ እርክሰት ላይ ደርሰዋል። ሴት ልጅ በወጣትነቷ ዘመን እንደ ሸንኮራ ተመጣ የምትጣልበትን የወሲብ ‹ኢምፓየር› ገንብተዋል። የሁሉም መጠቀሚያ አድርገው ከራሷ ጋር ያጣሏታል። እግር ጥሎህ በመሸታ ቤት ጎራ ብለኽ ብታይ ለክብር ሚስትነትና ለልጅ ማእረግ መብቃት የነበረባቸው ሴቶች በመጠጥና ሲጋራ እየናወዙ ገላቸውን ሲቸበችቡ ታገኛለህ። ሐቁን እንነጋገር ከተባለ በአሥርና መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ሴቶቻችንም በስደት ከሚንገላቱ፤ የአረብ መጫወቻ ከሚሆኑ አግብቶ የሚያስተዳድር ያስፈልጋቸዋል፡ ካለ አባት የሚያድጉ ልጆች ቁጥርም ይቀንሳል። የሚያሳዝነው የእነዚህ ምስኪን ነፍሶች ደንበኛ አብዛኛው ባለትዳር[103] ወንድ መሆኑ ነው። እናም እንደኔ እንደኔ የማስተዳደር አቅም ያላቸው ወንዶች እንደ አያቶቻችን ባህል፤ ከአንድ በላይ እያገቡ ይህንን የተበላሸ ሥርዓት ማስተካከል ያለባቸው ይመስለኛል።"

"ሀሀሀ... አንተ ሰውዬ በጣም ትቀልዳለኽ... እንዳልከው ይሁን ቢባል እንኳን አንድ ችግር አለ። መጀመሪያ ያገባኻት ሚስትህ ሞታ ካልሆነ በቀር ሁለተኛ ሚስት እንደማትፈቅድልህ ማወቅ አለብህ። አብዛኛው የዘመኑ ሴት ጣውንት ከምታመጣበት ጣዖት ብታመልክ ይቀላታል።" አለና ለይኩን ጩኒን በፌዝ ተመለከተው፤

"አዎ ያንማ እኔም አውቃለሁ ግን ቢያንስ ህጉ ሊያግደው አይገባም ባይ ነኝ። እሷ ከፈቀደች..." አለ ጩኒ በደምሳሳው፤

"እሱን እንግዲህ እግዜር ብሎ አንተ ከእሥር ስትፈታ ሁለቱንም አፍቃሪዎችኽን አግብተህ ታሳየን ይሆናል፤" ... ሁለቱም ሳቁ።

"ከእሥር መፈታቱን እንኳን ተወው፣ ባይሆን ወይ ማምለጥ ከቻልን እንጂ...!"

"ከምርህ ነው?" አለ ለይኩን አዲስ መነቃቃት ከፊቱ ላይ እየተነበበ፤

---

103 ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ያገቡ ወንዶች ካላገቡ ወንዶች ባልተናነሰ ደረጃ ለመሳብ ይከፍላሉ፡፡

"የእውነት ብችል ጥሩ ነበር ግን..." ... "አዎ እሱማ ጥሩ ነበር!" አሉና ታማኙ እስረኛ ጋሽ በቄ ወደ ውይይታቸው ተቀላቀሉ...

"አዎ ጥሩ ነበር፤ ግን እነዚህ ሹል እሾኾች የተወናገሩባቸው ረጃጅም ግንቦች እንዴት ሊታለፉ ይችላሉ። በማማዎቻቸው ላይ ተሰይመው እንደ ቆቅ ነቅተው የሚጠብቁ አልሞ ተኳሾችንስ እንዴት ማምለጥ ይቻላል?" አሉና ሁለቱንም በጥያቄ ዓይን ተመለከቷቸው።

"እንኳን ከዚህች ከሌላም ከባድ እሥር ቤት ማምለጥ ቀላል ነው።" አለ ዳዋ ከየት መጣ ሳይባል በወሬያቸው መሀል ዘው ብሎ ጣልቃ እየገባ። "አይ ልጅ ዳዊት ላንተ ሁሉም ነገር ቀላል መስሎ ነው አይደል የሚታይህ?" አሉ ጋሽ በቄ፤

"ላንተ ማለት ምን ማለት ነው? እንዳንተ ለዘመናት ታስሮ እዚሁ ከመበስበስ ስንት እጁን የኔ አማራጭ አይሻልም?" አለና በነገር ሸነቆጣቸው፤

*"ነው ብለኽ ነው? ...እንደኔ፡ እንደኔ ግን የሥጋ እሥር ምንም አይደለም፤ የአእምሮ፣ የህሊናና የስሜት እሥር ነው ከባዱ፤"* አሉና በውስጠ ወይራ አፀፋውን መለሱለት፤ ዳዊት ከመቅጽበት ሲነቃነቅ ውሎ እንደተከፈተ አምቦ ውኃ ገነፈለ። እንደ ግስላ ተምዘግዝጎ ጋሽ በቄን ገፈተራቸው። ተንገዳግደው ከመሬቱ ተዘረጉ። ከላያቸው ተፈናጠጠና በቡጢ ሊነርታቸው ሲዘጋጅ ለይኩን እጁን ቀጬም አደረገው። ዳዊት ቁና ቁና እየተነፈሰ ቀና ብሎ ለይኩንን በንዴት አየው። አሁን ቁጣው ከሽማግሌው ጋሽ በቄ ወደ ለይኩን የተሸጋገረ ይመስላል። እጁን መንጭቆ አስለቀቀውና ከእርሳቸው ላይ ብድግ ብሎ ቆመ። ለይኩን ላይ ሊከመርበት እያደባ ሳለ ከበር የእሥር ቤቱ ጥበቃ ድምጽ ተሰማ፤

*"ለይኩን ተስፋሁን? ... ጎብኚ ስላለኽ ቶሎ ወደ በሩ ና!"*

⌘ ⌘ ⌘

ሶፎኒያስ በአምስተኛው ቀን መባቻ አረንጓዴውን ጥበብ ተሰናብቶ| ጊዜም ሳይፈጅ ጅረቷን እየተከተለ ተንዶለዶለ። በምናብ የውኃ ሀዲድ በሄደ ቁጥር አረንጓዴው መደብ ወደ ሰማያዊ ቀለም እየተቀየረ ነበር። ከአፍታ ጉዞ በኋላ ግን ውኃው ከአንድ ስፍራ ጠርቀምቀም ብሎ ሲያቁር ተመለከተ። አጠገቡ ተጠግቶም ቆመ። ወዲያውም አንዳች አጥንት ያላት ይመስል ጅረቷ ጭር እያለች ወደ ላይ ስታድግ አያት። ቀስ በቀስ፡ ቀጥ ብላ ሽቅብ ረዝማ፡ ዠርጋዳ የሰው ቅርጽ እየያዘች መጣች። ሶፎኒያስ

የሚያየውን ነገር ማመን እየተሳነው በአግራሞት አንጋጦ ቀረ።

ውሀዋ በስተመጨረሻ የአንዲት ተለቅ ያለች ሴት፣ እናት የምትመስል ተክለ-ሰውነት ቅርጽ ይዛ ቆመች። ልዩ ፍጡሯ ዘባ ቀዘባ እያለች ስትወዛወዝ ከሰውነቷ ላይ የውኃ ዘለላዎች ይንጠባጠቡ ነበር። ፀጉሯ የተጎነጎነ፡ የውኃ ፏፏቴ ሲሆን አከላቷ በሙሉ ከሰማያዊ ውኃ የተገነባ ነበር። እንደፈለገች ትልመጠመጠለች። ሙሉ ቅርጸ-ለውጧን ከፈጣጠመች በኋላ ወደ ሶፎኒያስ ቁልቁል አማተረች። ለጥቆም የሚቡለቀለቅ ውኃማ ድምጿ ወደሱ ደረሰ፤

"ልጅ ሶፎኒያስ... እኔ ሞ-ያ እባላለሁ። የውኃ እናት፣ ንግሥት ነኝ። በተለይ የማያ ጥቁር ሥልጣኔዎች ያውቁኛል። የአሁኖቹም የታሪክ ተመራማሪዎች በጥልቀት አጥንተውኛል። የእማዬ ማያ፣ የማያ፣ መመልከቻ ማማ፣ ማይ[104]፣ እማማ፣ እማይ፣ እትያ፣ ኢታዬ፣ እትዬ ብለውኛል - ነገዶችና ሴቶቻቸውን በኔ ስም ባለ-ሞያ ተብለው ተጠርተዋል። ከጥቁር ግብጥ ሞያ ተራራ እስከ ሶማሊ ሞያ-ሌ እናት ተፈጥሮ፣ የውኃ ምንጭ ስባል ለቁጥር አልባ አመታት ዘልቂያለሁ። ስሜ ተዳፍኖ ለዘመናት ቢቆይም ይኸው ዛሬ በእውነተኛው ቀለሜ፡ ሰማያዊ መደብ ተገልጬ የአምስተኛውን እርከን ጥበብ በአጭሩ ላስረዳኽ ፈቅጃለሁ።" አለችና እጹብ ድንቅ የሆነ መለስተኛ ፏፏቴ በፊቱ አንፎለፎለችለት። ልቡ ረሰረሰበት፤ ለአንጎሉ ጥምቀት ራሱን አዘጋጀ።

"...ቅድሚያ የተጠማች ህያው ልቦናህን በሌላ የጥበብ ጽዋ ለማርካት አንድ ረጅም ትንፋሽ ውሰድ!" የሚል ትእዛዝ አስተላለፈችለት። ሶፎኒያስ ሳንባው እስኪለጠጥ አየር ወደ ውስጥ ሳበ። ወዲያውም ከየት እንደ መጣ ያላወቀው የውኃ ማዕበል ከእግሩ ሥር እያሾረ ይዞ ወደ ላይ አጎነው። ምንም ትንፋሽ ማግኘት እስካይችል ድረስ ሙሉ ለሙሉ በውኃ ተዋጠ። ቀጥሎም ሞያ በምናቡ ገዝፋ ተሰየመች። መልእክቷም በናላው አውታር ይደርሰው ጀመር።

"እነሆ አስተውል... ማዕበል ጊዜያዊ ነው ያልፋል፣ የባህር ጠለል ግን ዘላለማዊ ነው፡ ይሰክናል። እንዲሁ ሁሉ ውናፍ፣ ዝተት ወሬ ጊዜያዊ ነው ያልፋል፣ አርምሞ ዘላለማዊ ነው ይዘልቃል። ከአርምሞ የወጣ ቃል ብቻም ሰማይና ምድር እስኪያልፉ አያልፍም። "የሰው አፍ ቃል የጠለቀ

104 እውነም በብዙ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች መሠረት መይ/ማይ ማለት ውኃ ማለት ነው፤

*ውኃ ነው ፥ የጥበብም ምንጭ ፈሳሽ ወንዝ ነው::"*[105] እንዲል ቃሉ ከጠለቀ ውኃ ተነስቶ የሚፈስ ቃል ብቻ የጥበብ ወንዝ መሆን ይቻለዋል:: ከዚያ ውጪ ያለው አልባሌ የቃላት አልቦ ነው:: ለዚህም መሰል፡ አባቶች *ሲገስጹ በዋል ፈሰስ ኗሪ አትሁን ይላሉ:: አፈሳሰህን እንድታስተካክል ይመክራሉ::*

እነዚያ የዚህች ምድር ጌጦች፣ ደጋግ አባቶችም... አብርኖትን ፍለጋ የሚዳዝ ሰው ልክ እንደ ዓሣ አጥማጅ ነው ይሉ ነበር:: አንድ ዓሣ አጥማጅ በተመስጦ ውስጥ፣ ዝም ብሎ በትዕግሥት ይጠብቃል:: በዚያው ልክ ደግሞ ያሰገረውን መንጠቆ አጥብቆ የሚይዝ፣ ደውሏ ስታቃጭልም በንቃት ገመዱን የሚስብ... የሰከነ ውቅያኖስም፣ ኃያል ማዕበልም መሆን እንደሚችል ሰው ይመስሉታል::

ደግሞም እወቅ! አምስተኛው እርከን በ‹ታላመስ›ና ‹ሃይፖታላመስ[106]› የሚወከል ሲሆን፤ እንዲሁ ግብሩ መታገሥ ከመቻል ክህሎት ጀምሮ በአስተዋይነት ሰፊ ራእይ እስከ ማየት ሊደርስ ይችላል:: ይህም መቼ መናገር፣ መቼ ዝም ማለት፤ መቼ መጀመር፣ መቼ ማቆም እንዳለብኽ ስታውቅ የሚገኝ ነው:: ከላይ በተሰጠ ነፃ-ፍቃድ በጊዜውና በቦታው የሚሠራ ሥራን ያፀድቃል::

በዚያው ልክም ከሥራው በላይ ለአሠራር ሥነ-ምግባር ትኩረት ይሰጣል:: ከመፍሰሱ አፈሳሰሱን ያያል:: ከግቡ በላይ ከአካሄዱ ፍሰህን ይለቅማል:: ምክንያቱም ውኃ ጋር ሲደርስ ጊዜ ራሱ ይታጠፋልና ነው:: ከቶውንስ ሳያቋርጥ ለሚተካካው ጋላቢ ውኃ ዛሬና ነገ ምን ልዩነት አላቸው? የሰው ልጅም እንዲህ ባለው የመገኘት ጥበብ ሲሰለጥን፡ ነገን ዛሬ ላይ የማየት የራእይ ጸጋ ይሸለማል:: ትናንት፣ ዛሬና ነገ ቃላት ብቻ ይሆናሉ:: አሁን ማለት በኋላ፣ ቅድም ማለትም አሁን ይሆናሉ::

የአእምሮ ሐሳብ ደግሞ እንደ ፈሳሽ ወንዝ ነው:: ልታቆመው አትችልም:: ፈር ልታሲዘው ግን ትችላለኽ:: ወደ ፍሬያማ መስኖነት ልትቀይሰው ትችላለኽ:: ግዙፍ የዓላማ ወንፊት፣ ታታ[107]፣ የትኩረት ተርባይን አበጅተህ ለዓለም ብርሃን የሚያመነጭ ፋብሪካ ልታደርገው

---

105 (ምሳ፤ 18:4)

106 የአንጎል ክፍሎች ሲሆኑ የልብ ምትና ደም ዝውውርን፣ እስትንፋስን፣ ሙቀትና ግፊት፣ እንቅልፍ፣ ንቃትና እርጋታ፣ ባህሪና ስሜትና የስሜት ህዋሳትን ከበላይ ሆነው የሚቆጣጠሩ አመራሮች ናቸው::

107 መንጎንጎን፡ ማስተላለፍ፤

ሁሳ ትችላለኽ። ግድብና መስኖ የሃገር ኃይላት ሲሆኑ፤ አመስኳና ጽሞና ደግሞ የሰው ልጅ እሳቤ ኃይላት ናቸው። ስለዚህ የአርምሞ አንዱና ትልቁ ጠቀሜታ የሐሳብ ኸረትህን እንድትሰድር፡ ብሎም አቅጣጫ እንድትቆጣጠር ማስቻሉ ነው። አብዛኛው የሰው ልጅ ግን እንደ እፉዬ ገላ በስሜቱ ግልቢያ ይመራል፣ ለደመ ነፍስ የፍላጎት ሐልዮቶች ይገዛል፣ እንደመጣለት ይሄዳል፣ እንደነገሩ ይኖራል፣ በተቀደደለት ቦይ ይፈሳል።

ታዲያ ዝምታ እነዚህን ስሜቶች የመለጎም ትልቅ አቅም አለው። ለዚህ ዝርው ማሳያው የስሜቶች የመጨረሻ ከፍታ ዝምታ መሆኑ ነው። ከመጠን በላይ ያዘነ፣ የደነገጠ፣ የተደሰተ ሰው ከቃላት በላይ የሆነ ስሜት ውስጥ ገባ ይባላል። ከተጠበቀው በላይ ያማረ ነገር ሲታይ … "…ብሎ ዝም ነው" ተብሎ ይሞካሻል። ይሄ የሆነው ዝምታ የገለፃዎች ሁሉ ታዛ ስለሆነም አይደል? እንዲሁ ሁሉ የውኃ እርከኑም በስሜቶች ጡዘት ወቅት ይገለጣል። የውስጣዊው ሐይቅ ሲላወስ እንባ ሆኖ ሊፈስ ይችላል። ይልቁንም ውስጣዊው ሰላሙ የተበጠበጠ፣ የተረበሸና አቅጣጫው ጠፍቶበት በወከባ የተሞላ ሰው በውስጣዊው ሐይቁ ላይ እንደ ‹ቦርቲሶል› ያለ ከባድ ኬሚካል እየደፋ ሰውነቱን ይመርዛል። አዎን በዋናነት አርምሞን ተጠቅሞ ሰው ራሱ ላይ ከጫነው የስሜቶች እሥር አርነት መውጣት ይችላል፤ አብሮት ያደገ ሰንሰለቱንም ይበጠሳል። የመኖር ትርጉም በውስጡ እንደ ቀላይ ይንጣለላል። ወደ ርቱዕነትም ይመጥቃል።

ታዲያ በኃይል ትመጥቅ ዘንድ ጠንካራ ፍላጎትና የጸና ልብ ያሻኻል። ምክንያቱም ይህንን መሰሉን ጉዞ ስትጀምር ኩሬውን ከበው እንደሚጮኹ እንቁራሪቶች ያሉ ነቃፊዎች ሊገዳደሩኽ ይችላሉ። በየመንገድህ መሐልም ብቅ እያሉ ሊፈትኑኽ ይታገሉኻል። እነሆ በርታ ብለኽ አለፋቸው እንጂ ፊፅሞ አትጥላቸው፤ በህይወትህ መምጣታቸው ክፉ እጣፈንታ ሳይሆን ላንተ እውነተኛ ንቃት አስፈላጊ ተግዳሮት በመሆናቸው ነው። ነገር ግን የማንኛቸውንም አሉታዊነት አትስማ፣ ዝም ብለኽ ጉዞኽን ቀጥል።

ይህንንም እልኻለሁ - ራሳቸውን ያላወቁ ሰዎች ሌሎችን ለማሳወቅና ለመምራት ስለሚሞክሩ በምድር ችግሮች እንዲህ ተንሰራፍተው ይገኛሉ። አሁንም ቢሆን ለአንዳንዶች ብዙ ሰው ሆይ ሆይ ስላለላቸው ብቻ በፍጹም አትከተላቸው፤ እነርሱን ለመምሰልም አትኳትን። የሰው ልጆች ስልጣኔ ለዘመናት የወደቀው በግለሰብ ደረጃ ስብእናን ለማበልጸግ ከመሥራት ይልቅ በታዋቂዎች ዋዛ ፈዛዛና በቡድኖች ፉክክር ላይ ስላተኮረ ነው።

ፉክክር ደግሞ የውስጣዊ ሰላም ዋነኛ ጠላት ነው:: ከዚህ ቀደም ሰዎች 'ራስህን ከሌሎች ጋር አታፎካክር" ብለው መክረውኽ ያውቁ ይሆናል:: እኔ ደግሞ እልኻለሁ፤ ከራስህም ጋር ቢሆን አትፎካከር፣ ከትናንትህም ጋር አትወዳደር:: ዛሬኽን በንጽጽር አታባክን:: እያንዳንዱ ሰው ልዩ ልዩ ሆኖ ተፈጥሯልና አንተም በራስህ መንገድ ራስህን አግኘው:: መክሊትህን ክፈተው፣ ኣላማኽን ቅረጸው፣ በእውቀት የተገነባ ራስኽን ሁን:: ከዳር ቆሞ በምቀኝነት እያየ እንካ ሰላምቲያ ለሚልኽ፣ በህጸጽ አንጻ ግራንጻ ለሚያጣጥልህ መልስ ሳትሰጥ፣ ዝም ብለህ ተጓዝ:: ምክንያቱም ለጥላቻ ቅፍለቶች ጆሮ ካዋስካቸው እንቶ ፈንቶ ነገር እያወሩ ያደናግሩሃል:: የድንዛዜ አርቲ ቡርቲ[108] ያነባብሩልኻል:: ስለዚህ ከነሱ አንድ ሁለት ሳትባባል:: ራስህን ለማግኘት ወደ ውስጥኽ ተጓዝና ከነፍስያኽ ጋር ተዋሃድ፡ እነሆም ቅዱሱን የህይወት ስጦታ አስተውለኽ በሰላም ውቅያኖሱ ላይ ተንሳፈፍ:: በልቦናዊነት ህያው ሁን፣ በሁለንተናዊነት ሰፊ ሁን፣ በህልውነት አንተን| ራስህን ሁን:: ሌላው ትርፍ፣ ቀጥሎ የሚመጣ ነገር ነው::" … ለይኩን የሞያ የውኃ ፈፋ ገላውን ብቻ ሳይሆን ነፍሱንም እያረሰረሰው ነበር:: እሷም በጥበብ መዝነቧን ቀጠለች…

"ይህንን ካደረግክ ታዲያ አንተ እውነትን ለመሆን ትጣጥራለኽ… ግን ግን እውነት ምንድነው? ብለኽ ቀጣይነት ባለው መልኩ ጠይቅ እንጂ ከቶውንም እውነት ይሄ ነው ብለኽ እንዳትመልስ:: ለዚህ ጥያቄ መልስን አገኘሁ በቃ ባልክ ቁጥር ከእውነት ትርቃለኽ:: እነሆ በምድር ትላልቆቹን እልቂቶች የፈጠሙ ሰዎች እውነት እኔ ጋር ብቻ ነው ያለቸው ብለው ያመኑት ናቸው:: እውነት ግን የማንም አይደለችም:: ለመሆኑ እውነት በቃል ይወሰናል ወይ? ፈጣሪን ሙሉ በሙሉ አውቀዋለሁ እንደሚሉ ሰዎችስ ሞገደኛ አለ ወይ?

እውነትስ እንዲሁ ብጹእ ነች፤ በውስን ቃላትም አትገለጽም:: ጲላጦስም "እውነት ምንድነው?" ብሎ ኢየሱስ ክርስቶስን በጠየቀ ጊዜ አንድስ እንኳ አልመለሰለትም:: በሚያስደምም ዝምታም ገረመመው:: እውነትም እውነትን የያዙት በቃላት አይንዘባዘቡም:: ለማንም ራሳቸውን ለማስረዳት አይለፉም:: ነባሪ ናቸው:: የጊዜ ጉዳይ እንጂ እውነት አርነት እንደሚያወጣ ጠንቅቀው ያውቁታል::

"እናም ምክሬን ሰምተኽ ከልብኽ አሳድር" አለች ሞያ ከሰውነቷ

108 በሂንዱ ኃይማኖት መሰረትም አርቲ ቡርቲ ማለት ጥቅም የሌለው ወሬና አሉባታ፣ ጫጫታ እንደማለት ነው::

የሚንጠባጠበውን ዘለላ ውኃ እያርገፈገፈች፤ "ይሄን የጠቢብን ቃል የሰማ ቤቱን በአለት ላይ ይሠራል። ዳሩ ዝም ያላለ ሰው ግን ቃልን አይሰማም። እምነት ከመስማት ነው መስማትም ከቃሉ እንዲል ቅዱስ ቃሉ ከልብህ አድማጭ፣ ከነፍስህ አንባቢ ሁን። እውቀት ከእምነት እምነትም ከእውነት ይቀድማሉና። አበጥረኽ ያላወቅከውን አትመን፣ ከልብህ ያላመንከውንም እውነት የሚል ማዕረግ አትስጠው። ትኩረት ሳይኖረው፣ ራሱን አሳልፎ ሳይሰጥ የሰማና ያነበበ ሰው ‹አምኛለሁ› ብሎ ቢለፍፍም አላመነም። ነገ ለሰው የሚያወራውን እያሰበ እውቀትን ፍለጋ የዳከረም፡ ዛሬም ሆነ ነገ ጥበብን አያውቃትም። በውስጥ ጸጥታ ውስጥ ያልዘወተረ ሰው አንብቦም ምንም አይፈይድም። አብዛኛው የሰው ልጅም እንዲሁ በመግባትና መውጣት ውስጥ ሲመላለስ፣ ስለ ራሱ ትቶ ስለሰው እያወራ፣ በመንፈስ እንጂ በሥጋ ሳይጸና ሲውተረተር፣ በመገኘት ብቻ ከርሞ፣ ሳይኖር የሚያሸልብ ብኩን ነው።

አዎን ቃሉ፣ እምነት ከመስማት ነው እንዳለን ሁሉ እኔ ደግሞ እምነት ከማንበብም ጭምር ነው እልኻለሁ። ለመሆኑ በሙሉ ትኩረት መጽሐፍን የሚያነቡ ሰዎች ደራሲውን ከልባቸው እያደመጡት አይደለም ወይ? በቅዱስ መጽሐፍት ውስጥ የተጻፉ ቡራኬዎች የእምነት ዳናዎች አይደሉም ወይ? ...| እናም በመጽሐፍ ንባብ ውስጥም እርምጃ ይገለጣል። በሥነ-ጽሑፍ ጥበብ በኩል ዝምታ በእልፍ እርከን ተጠርቶ ይገኛል፤[109] በጽሑፎች መሀል ባዶ ቦታዎችና ሥርዓተ ነጥቦች ያስፈለጉት፡ ሰዎች እያንዳንዱን ቃላት በቀቢጸ ጽሞና ያገናዝቡ ዘንድ ነው። በፊደላት፣ በቃላት፣ በሐረጎች፣ በአረፍተ ነገሮች፣ በአንቀጽና በምዕራፎች መካከል ክፍት ቦታ አለ፣ ዝምታ አለ። በውል ላስተዋላቸው ከቃላቶቹ በላይ ዝምታዎች ይበልጣሉ!

እነሆ ከመናገር መስማት፣ ከመጻፍ ማንበብ ሳይሻል አይቀርም። ከልባቸው የሚያነቡ ከጸሐፍቱ እኩል ክብር ይገባቸዋል፤ ከልባቸው የሚታደሙ ከአቅራቢ፣ ከያኒው እኩል ክብር ይገባቸዋል፤ ከልባቸው የሚያዳምጡም ከተናጋሪ፣ አዚያሚው እኩል ክብር ይገባቸዋል። እነዚህኞቹ እርግጥም ያነፈነፉትን እውቀት ቀስመዋልና ክብረት ይስጣቸው። እውቀትን በማጣታቸው ምክንያት ጠፍተዋል ከሚባሉት አህዛቦች ጎራም አይመደቡም። አህዛብነትም እውቀት አልባነት እንጂ

109 ከአራተኛው ከፍለ ዘመን በፊት ድምጽ ሳያወጡ ማንበብ በአውሮፓውያን ዘንድ አይታወቅም ነበር። ኢትዮጵያውያን ግን ከአንደኛው ክፍለ ዘመን በፊት መዝሙረ ዳዊትን በዝምታ ይደግሙት፣ ያመሰኩት፣ ይመሰጡበት ነበር።

ከዘርና ነገድ አይመዘዝም:: ምዕመናን ነፍሳቸውን ከፍተው ያስተዋሉት እውቀት ሌሎችን ለማየት፣ ለመፈረጅና ለመፍረድ ሳይሆን ራሳቸውን ለመገምገም ይረዳቸዋል:: ቃሉም ሲነግርኽ የወንድምህን ጉድፍ ከመለየትህ በፊት በራስህ ዓይን ውስጥ ያለውን ምሰሶ አውጣ ብሎ ነው:: ያኔም አጥርተህ ማየት ትችላለህ::[110] አጥርተህ ስታይም እንከኑ የበዛ ፍጡርነህት ታውቃለኽ፣ አንድ ደካማ የሰው ልጅ ብቻ መሆንኽንም ትረዳለህ:: ለመፍረድ አቅም እንደሌለህ ስታውቅ ለዳኛነት አትቸኩልም:: ኃጢያተኛ ያልከው ላይ ድንጋይ ለመወርወር ፍጹም ቅዱስ እጆችም የሉህምና ፍርዱን በሰማይ ላለው ዳኛ ትተዋለኽ::

ይህን ካወቅኽ ዘንዳ ሌላውን ተወውና የአምስተኛው እርከን መቅደስ ወደ ሆነችው ልብህ አተኩር:: አምስተኛው ጉዞ ከአንጎል ወደ ልብ የሚደረግ ነው:: ብርቱዋ ልብ የሰውነት የውኃ አስተዳዳሪ ነች:: ከተወለድኽ ጀምሮ እስክትሞት ድረስ አታርፍም:: ሥራዋን አክብራ፣ የማያቋርጡ የአንጎል ትዕዛዞችን በትህትና ተቀብላ፡ በጽናት ትታትራለች:: የሰውነታችን አንድ ሦስተኛ መጠን የሚይዘውን ደም ታስተናብራለች:: እነሆ የውኃ ቅኔና ጥበብ በዚህ አለ፤ ሰው - ልብ ግዛ፣ ልብ በል፣ ልብ አድርግ፣ ቀ-ልብኽን ሰብስብ ሲባል ሐረጉ ከጀርባው ሰፊ ትርጓሜን አዝሎ እናገኘዋለን፤

ከህይወት ዥረቶች የሚንፏለሉት ደሞች የመኖራችን ዋልታዎች ናቸው:: የዝውውር ሥርዓታቸው ከተዛባም ጤንነታችን ይጓደላል:: ደም ማነስ፣ ደም ብዛት፣ ደም ግፊት፣ ደም መርጋት፣ ደም አለመርጋት፣ ደም ብክለት፣ ደም ካንሰር ወዘተ እያልን ደዌ እንቆጥራለን:: ልብ መምታት ሲያቆምም ሐኪሞች ታማሚን ሞቷል ትላላችሁ፤ እንዲሁ ሁሉ ለመሬት ውኃ አካላት ጠንቅ የሆነው ደዌ የሰው-ልጅ ነው:: ምድርንም አሳምሚታል:: የሰው ልጅ ምድር ላይ ሲኖር ሥነ-ምግባር ከጎደለው በዓለም ጎርፍና ከፍተኛ ሙቀት፣ አደጋና ቸነፈር ይበዛል:: ውኃ፣ አየርና አፈሩን በማን አለብኝነት ከበዘበዘ የራሱን ፍጻሜ ያፋጥናል:: እስኪ ለተምሳሌት አንድ የውቅያኖስ ግፍ ላሳይኽ፡ አለችና ሞያ ሶፎኒያስን ከማዕበል ግልቢያ በፈጠነ ሽምጠጣ፡ ከቀድሞ የ‹ኢትዮጲስ› ከአሁኑ የ‹አትላንቲክ› ውቅያኖስ ጠረፍ ወሰደችው:: እጅግ ግዙፍ የሆኑ መርከቦች አንድ የኳስ ሜዳ የሚያኽል መረብ ጥለው ዓሣ ሲያጠምዱ ተመለከተ:: ይልቁንም ሞያ በሐዘን ሰውነቷን ሲንዘፈዘፍ አስተዋለ::

በቁጭት ተሞልታ እያየችው መናገር ጀመረች፤ "ያኔ አባ በላይ

110 ማቴዎስ ወንጌል 7፤ 3-5

እንዳጫወቱኝ የዓለምን ዘጠና በመቶ ኦክስጅን የሚያመርቱት በትላልቅ ውኃ አካላት ውስጥ የሚገኙ ውኃ አቅላሚ[111] አልጌዎቼ ናቸው፡፡ ይህም እንዲሳካ ከፍጥረት ጀምሮ ባህር ውስጥ ያ ሁሉ ህይወት በዝምታ ይዘወትር ነበር፡፡ የተፈጥሮን የክብሮሽ ሥርዓት አክብሮ ሲደጓጎም ዘልቋል፡፡ እንደ ዓሣ-ነባሪ ያለ ትላልቅ ዓሣ መካከለኛውን፣ መካከለኛዎቹ እንደ ሻርክ ያሉ ዓሣዎች ደግሞ ትናንሹን በሚበቃው ልክ እየበላ፡ የሚጥለው ተረፈ ምርትና ብስባሽ የውኃ አቅላሚዎች የምግብ ምንጭ ሆኖ ያገለግል ነበር፡፡ ነገር ግን የማይጠረቃው የሰው ልጆች ሆድ ዓሣን የሚመገብበት ስግብግብነት ይህቺን ዓለም በቅርብ ዓመታት ውስጥ ለሰው ልጅና ለፍጥረቷ የማትመች ‹ፕላኔት› ሊያደርግ ከጫፍ ደርሷል፡፡ ድሮ ዓሣ አጥማጅ የሚበቃውን ለመያዝ በዝምታ፣ በዘረመትራን[112] ዓሣ እያጠመደ ቀኑን ይውላል፡፡ የዘመኑ ማሽን ግን ውቅያኖሶችን እያራቆተ ይገኛል፡፡ የምድርን ደም እየበዘበዘ ዓለም ደም ማነስ፣ ደም ግፊትና ደም ብክለት አጋጥሟታል፡፡

______{ኔትፍሊክስ የተሰኘው የበይነ-መረብ ተቋም በሠራው ‹ሲስፓይሬሲ›[113] የተሰኘ ኦሪጅናል ጥናታዊ ፊልም መሠረት የምድር ባህሮችና ውቅያኖሶች ላይ 5 ሚሊዮን ዓሣ አጥማጅ ግዙፍ መርከቦች አሉ፡፡ በተለይ ለቱና የሚፈለጉ ዓሣዎችን ካለ ገደብ የሚያፍሱት እነዚህ መርከቦች በዓለም ላይ ይገኙ የነበሩ የዓሣዎችን መጠን ከ80 እስከ 90 ፐርሰንት በላይ ጨፍጭፈዋል፡፡ ለምሳሌ ‹ብሉ ፊን› የሚባለው ለቱና ሰርዲን ተመራጭ ዓሣ 97 በመቶ ቁጥሩ ተመናምኗል፡፡ ክንፋቸውን ቆርጦ ለመብላት ብቻ በዓመት 50 ሚሊዮን ሻርኮች ይገደላሉ፡፡ ሻርኮች የሉም ማለት ደግሞ በሻርኮች ይበሉ የነበሩ ዓሳዎች በጣም ስለሚበዙ ካርቦን ሞኖ ኦክሳይድ አስወጋጅ ፤ኦክስጅን አምራች አልጌዎች ተሟጠው ያልቃሉ ማለት ነው፡፡ ያኔ ምድር ትሞቃለች፣ የዋልታ ‹ፖላር› በረዶዎቿ ይቀልጣሉ፡፡ ዓለም ላይ የምናያቸው ጎርፍ፣ ሙቀት መጨመርና የተፈጥሮ አደጋዎች ከዚህ የሚመነጩ ናቸው፡፡ የሚያሳዝነው እነዚህ መርከቦች ለምግብ የሚሆኑ ዓሣዎችን ለማጥመድ የሚዘረጓቸው እጅግ ሰፊ መረቦች ለመብል ከሚፈለጉት ዓሣዎች በተጨማሪ የማይበሉ ዓሣዎችንም ይዘው ይወጣሉ፤ እነዚህ ዓሣዎችም ካላንዳች ርህራሄ እንዲሞቱ ተፈርዶባቸው ወደ ባህር ተመልሰው ይጣላሉ፡፡ በአንድ

111 Phytoplankton

112 ዓሣ የሚያዝባት መግለቢ፤

113 የNetflix አማራጭ ካላችሁ Seaspiracy ብላችሁ በመፈለግ ሙሉ ዶክመንተሪውን ማየት ትችላላችሁ፤

ሰዓት ከሚጠመዱ 30 ሺህ ዓሣዎች 15 ሺው እንደ ተረፈ ምርት አብረው የሚያዙና አስከሬናቸው ተመልሶ ወደ ውኃው የሚጣሉ ናቸው:: በሌላ በኩል ጃፓኖች አሁንም የምድራችን ህይወት አለኝታ የሆኑ ዓሣ ነባሪዎችን እየገደሉ ይሸጣሉ:: እዚህ ጋር ሌላ ሳይነሳ የማይታለፍ አስደንጋጭ እውነታ ደግሞ ውቅያኖስና ባህሮቻችንን አጭቀው፡ ምድርን እያሳመሙ ካሉ የፕላስቲክ ምርቶች መካከል 43 በመቶ የሚሆኑት ከእነዚህ ዓሣ ጨፍጫፊ መርከቦች የሚጣሉ ተረፈ ምርቶች፣ የፕላስቲክ መረቦችና ገመዶች ናቸው:: አንድ ጥናት እንዳሳየው በየቀኑ ከመርከቦቹ የሚጣሉት እነዚህ የላስቲክ ክምችቶች በቀን ምድርን 500 ጊዜ መዞር የሚችል ርዝማኔ አላቸው:: ሳይንቲስቶች በዚሁ ከቀጠልን ምድር ከግማሽ ክፍለ ዘመን ያነሰ እድሜ እንዳላት እየነገሩን ነው:: ባጭሩ ብር አምላኪ ካምፓኒዎች ዓለምን እየገደሏት ይገኛሉ:: እነሆ ተፈጥሮም እየተቆጣች ከተሞች ሲጥለቀለቁና ደኖች ሲነዱ በዓይኖቻችን እያየን ነው:: ለመሆኑ ከርስና ስሜታችንን ከመግታት ሞትን የምንመርጥ ኧረ እኛስ ምን ጉድ ነን?}

ታዲያ የሚያሳዝነው ይሄን ሁሉ እያዩ ራሱ እንዳላዩ የሚያልፉት ይበዛሉ:: ብዙሃኑ ልቦናቸው ተዘግቷል:: ተቆርቁረው የሚናገሩ ጥቂቶች ቢኖሩም የሚሰማቸው ግን አላገኙም፤ ምክንያቱም የሰው ልጅ ሰው መክሮት ነገሮችን ካደረገ የተሸነፈ የሚመስለው ከንቱ ፍጡር ነው:: ነገሮችን የሚያደርገው ውስጡ ሲገፋው ብቻ ነው:: ጥያቄና የትርጉም ማጣት ፍርሃቱ ሲበረታ ብቻና ብቻ ግን የበለጠ ትርጉም ያለውን ህይወት ያነፈንፋል::

ይህንን ጥያቄውን ለመመለስ ብቻውን መሆን የማይጎረብጠው ሰው ደግሞ ጠንካራ ስብእና ያለው እንደሆነ አትርሳ:: ማንም በጣም ስለጮኸ በጣም አይሰማም:: እናም ከድምጽህ ይልቅ የሚሰማ ማንነት መገንባት ላይ አተኩር:: ልታይ ልታይ፣ ልታወቅ ልታወቅ ያለ ሰው መሬት የሚረግጥ ሥራ መሥራት ላይ እስከዚህም ስኬታማ አይደለም:: ሙያ በልብ ነው እንዲሉ የጠቢባኑ ከልብ የተብላላ ሐሳብና እቅድ ብቻ ያጸድቃል:: ከመልካም ሥራ ሁሉ ትልቁ ደግሞ ተደርጎ ያልተወራ ሥራ ነው:: መልካም አድርገህ ዝም ማለት አማኝነትን ይሻል:: ስለ ሥራህ ከሚሰማ የሰው ጆሮ ቁጥር በላይ ወሰን አልባው የውስጥህ መንፈስ ጋር መግባባት ይበልጣል:: ያኔ የራስህን ዋጋ በሰዎች እይታ ሳይሆን በህሊናህ ሚዛን ትወስናለህ:: ከትርፍና እውቅና በፊት አበርክቶትና ዓላማን ለማስቀደም ታዲያ ለብቻ መብሰል ግን አስፈላጊ ነው:: ወትሮም

ማታ አብረኽ የምተኛው ከህዝብ ጋር ሳይሆን ከህሊናኽ ጋር ነው።

ከብዙዎቹ መንገዶች መሐል ታዲያ እድሜ አንዱ የብስለት መፍቻ ቁልፍ እንደሆነ በርካቶች ይስማማሉ። በዚህ ጉዞኽ የገጠሙኽ የምናብ መምህራንም ሽምገል ያሉ ናቸው።" አለችና የለዛ ዘለላ አሳየችው፤ ለጥቃም... "እኔ ግን በመጨረሻ ይህን እልኻለሁ... ከእድሜህ ሽምግልና በፊት በአስተሳሰብህ ሽምግል። በአስተሳሰብ ስትሽመግል ደግሞ ምራቅህን ብቻ ሳይሆን ቃልህንም ዋጥ ታደርጋለኽ፤ ድርጊትህም ፍጥረትን በሙሉ ያገናዘበ ይሆናል ... ይሄው ነው፤" ...አለችና አስተምህሮዎቿን ፈጸመች... "እነሆ ከእኔ አምስተኛው የውኃ ማማ ጥበብን አጥምደኻል። አምስተኛው ቀን ተገባዶ መሰነባበቻችንም ደርሷል። እነሆ አሁን ጅረቴ ላይ ታንኳህን አስግረህ ወደ ውስጥህ ቅዘፍ፣ ጥለቅ፤ ወደ ስድስተኛው እርከንም ተጓዝ።" አለችና ሞያ በውኃዋ ቀዝቃዛ እንፋሎታዊ ትነት በኩል ወፍራም ጉም ዘርግታ ሶፎኒያስን እያስጋለበች ታከንፈው ጀመር።

⌘ ⌘ ⌘

ለይኩን ማን ሊጠራኝ ይችላል በሚል ጥያቄ ግራ እየተጋባ ወደ ጎብኚው አቀና። ህመሟ ከመጽናቱ በፊት ተመላልሳ የምትጠይቀው ሜሮን ብቻ ነበረች። በተደጋጋሚ ከአጥሩ ባሻገር ቆማ ዓይን ዓይኑን እያየች አንብታለች። የአእምሮ ጭንቀት ድባቴዋ እየናረ፣ የመውለጃ ጊዜዋም ሲቃረብ ግን እሥር-ቤት እየመጡ እሱን ማየት የህመሟ ማባባሻ ስለሆነባት ቀረች። ከዛሬ ነገ ትመጣለች እያለ ለዓመታት ደጅ ደጁን ቢያማትርም እልም ብላ ጠፋች። ምስኪኗ አፍቃሪው ሜሮንና በጽንሷ የያዘችው የአብራኩ ክፋይ መጨረሻቸው ምን እንደሆነ ሳያውቅ ቀናት ተቆጠሩ። ጭንቅ፡ ጥብብ እንዳለው ነፍስ የሚያከስም፣ ደም ሥር ውስጥ ሰርጾ የሚሰቅዝ ናፍቆትና ጥያቄ ተፈራረቁበት።

ቀናት ሳምንታትን፣ ወራት ዓመታትን በተኩ ቁጥር የሜሮን ውድነት ይበልጥ ገባው። ከአጠገቡ እያለች ያልታየው ዋጋዋ ሊያገኛት በማይችልበት ቦታ ውስጥ ሆኖ ተገለጠለት። ከጥንት ከጥዋቱ ጀምሮ ከጎኑ የነበረች አፍቃሪው እንደነበረች የትውስታውን ማህደሮች እያገላበጠ ሲረዳ፡ ሀዘን አቆራፈደው፣ ቁጭት አባዘነው። በእሱ ምክንያት የሆነችውንና ለእሱ ስትል የሆነችለትን ሁሉ ሲያስብ ጸጸት የእግር እሳት ሆኖ ለበለበው። እንዴት ያኔ ልረዳት አልቻልኩም!? እያለ ከራሱ ጋር ተሟገተ።

አንዴ አግኝቷት ፍቅሯን እንደተረዳት፣ እሱም ልቡን ከነጓዙ ለሷ

እንዳስረከባት ነግሯት ቢሞትም አይቆጨውም። አዎ አንዴ ብቻ አግኝቷት፣ አቅፏት፣ ስሟት... እንደሚወዳት ነግሯት ከወጣለት ለመኖር እምብዛም አይጓጓም፤| ስለ እሷ እያሰበ ወደ ጎብኚው ክፍል ሲገባ አንድ ሽማግሌ ሰው ነበር ቆመው የጠበቁት፤ ጠያቂው እሷ ባለመሆኗ እያዘነ ወዳስጠሩት ጎብኚው ተጠጋ። ክፍሉ ጨለምለም ያለ ስለነበር መልካቸውንም በቅጡ ማየት አልቻለም ነበር።

"ሰላም ልጅ ለይኩን?" ብለው በፈገግታ ተቀበሉት።

"ሰላም ጤና ይስጥልኝ?" አለ ለይኩን እንዳላወቃቸው በሚያሳብቅ ማመንታት፤

"እኔ አባ በላይ እባላለሁ። በምን መልኩ እንደማውቅኽ እና ምን እንዳገናኘን ሌላ ጊዜ አወጋኻለሁ። ለዛሬ ግን አንድ አስቸኳይ መልእክትን ላደርስህ ነው አመጣጤ፤" አሉና በጥሞና አስተዋሉት፤ ለይኩን ምኑም ሳይገለጥለት በአጸፋው ተገትሮ ሲያያቸው ቀጠሉ፤

"ከሦስት ቀን በኋላ፡ ልክ በዚህች ሰዓት አንድ የፍንዳታ ድምጽ ትሰማለኽ። ያኔ ካለምንም ማመንታት ከክፍልህ ውጣና በግራ በኩል፣ በምእራብ ወዳለው የኤሌክትሪክ አጥር አቅጣጫ ሩጥ። ከዚህ ሥፍራ መውጫኽ በዚያ ነው።" አሉና መልሱን ሳይጠብቁ ጀርባቸውን ሰጥተውት ሊሄዱ ሲሉ፤

"ቆይ እንጂ? ... እንዴት እንዴት ነው ነገሩ?" አለ ለይኩን፣

ዞር ብለው ተመለከቱት፤

"ማንነትዎን? ምን እንደሚፈልጉ?... ሳላውቅ ምን አይነት ድፍን ያለ ትዕዛዝ ነው የሚነግሩኝ? ለምን ብዬስ ላምኖት እችላለሁ?" ብሎ አስረግጦ ጠየቃቸው፤ እርሳቸውም ትንሽ አሰብ አደረጉና ጥያቄውን በአጭር ጥያቄ መለሱለት፤

"ሜሮንን ታውቃታለኽ?" ... ለይኩን ይሄንን ስም ሲሰማ የሆነ ነገር ውርርር አደረገው፣ ሰውነቱ በሙሉ በአዲስ ሞቃት ኃይል ተሞላ። ከአፍታ ቆይታ በኋላ "እሺ እዘጋጃለሁ፤" አለ በንቁ ስሜት፤ ጎብኚው ሽማግሌ ፈገግ ብለው አስተውለውት ወደ መውጫው በር አመሩ።⌘ ... *ይህ በሆነ በሦስተኛው ቀን፣ ልክ ለይኩን በአንድ ሽማግሌ በተጎበኘበት ሰዓትና ደቂቃ| በቃሊት እሥር ቤት የምሥራቅ አጥር ሥር ከባድ ፍንዳታ ተሰማ። የጥበቃ*

ሠራተኞቹ ፍንዳታው ወደተከሰተበት በታ ተንጋግተው ሄዱ።

⌘ ⌘ ⌘

**ዳጎስ ካሉ ዓመታት በፊት…**

**ምሽት 2 ሰዓት፤ ጨው በረንዳ፤**

ክረምት በጋን "ነይ ግቢ" እያለች የምታሽኮረምምበት የቡሄ ወቅት ነው። በጨው በረንዳ መንደር ህይወት እንደወትሮ ቀጥሏል። ፀሐይ እንደ ኳስ እየተንከባለለች፣ በየቀኑ መውጣት መግባቱ አልታከታትም። ኤልሳ ከማህብረሰቡ እንደተኳረፈች ዓመታት ነጎዱ። አብዛኛው የመንደሩ ኗሪ እውነት ብሎ የያዘውን የህይወት መንገድ እያጠጋገነ ንበራ አልሰለቸውም። ለሷ ግን ይሄ ሁሉ ሂደት ዛሬም አይዋጥላትም።

"አንዳንዴ እዚህ ሰፈር ባልተወለድኩ ኖሮ ብዬ አስባለሁ፤" አለችው አበጋዝን፤ አንድ ምሽት ውስኪያቸውን እየተጎነጩ ከሰገነት ላይ ተቀምጠው ሳለ። ጨው በረንዳ ሰፈር ከፊታቸው ወለል ብሎ ተዘርግቷል። … "ለምን እንደዛ አልሽ?" አለ አበጋዝ አንገቱን ልጥጥ አድርጎ፣ በከፊል ኤልሳን፣ በከፊል ሰፈሩን እያየ፤

"በቃ ኑዋሪውን ሳየው ምንም አይጥመኝም። ለነገ የተሻለ ስኬትና ሐብትን ማየት የማይችል ድኩማን ህዝብ ይመስለኛል።" አለችና በብርጭቆ ያለውን ውስኪ እያሽሞነሞነች ጸጥ አለች። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመጠጥ ፍጆታዋ ጨምሯል።

"እኔም በሐሳብሽ እስማማለሁ፤ … ግን ለምን ይመስልሻል የሰዎች አኗኗር እንዲህ የሆነው?"

"እኔ ምኑን አውቄው አቤ፤" ሳቅ አለች።

አበጋዝ ከተለያዩ የሥነ-ልቦና መጽሐፍት የቃረመውን እውቀት አዋቅሮ ሊያስረዳት መሞከር ጀመረ… "የሚመስለኝን ልንገርሽ… ማንኛውም ማኅብረሰብ የግለሰቦች ጥርቅም ነው። ግለሰብ ደግሞ ያዘለው አስተሳሰብ ከአስተዳደጉ ይመዘዛል። ማንኛውም ጎልማሳ ሰው የህጻንነቱ ልጅ ነው እንዲሉ የሥነ-ልቦና ባለሞያዎቹ ሁላችንም ያደግንበትን እንመስላለን። ትልቅንም ትንሽንም ሰው ልጅነቱ ይወልደዋል። እኔ እውነትና ትክክል ብዬ

የያዝኩት ሐሳብ፣ እምነት፣ ወግ፣ ልምድና ባህል በአብዛኛው ተወልጄ ካደግኩበት አካባቢ ይቀዳል። ለምሳሌ አንቺ እልም ያለ የአማዞን ጫካ ውስጥ ተወልደሽ ቢሆን ኖሮ ራቆትሽን የምትሄጂ ኢ-አማኝ ልትሆኚ ትችይ ነበር። አልያም አንድ የህንድ ገጠራማ መንደር ውስጥ አድገሽ ቢሆን ሌላው ቀርቶ ኃይማኖትሽ ራሱ የተለየ ይሆን ነበር።"

"አንተ ደግሞ... ኧረ በስማም በል! ምንድነው የምታወራው?"... ከት ብላ ሳቀች፤

"የምሬንኮ ነው!... እንዴት መሰለሽ?... አንድ እከሌ ወይም እከሊት የተባለች ሰው የኔ የምትለው አብዛኛው መገለጫዎቿ ከሌላ ሰው ዓይታ፣ ሰምታ፣ ተምራ የቀዳቻቸው ናቸው። በተለይ ደግሞ ቤተሰብሽ አንቺ ላይ ያለው ተጽእኖ ተነግሮ የሚያልቅ እንዳይመስልሽ።"

"የቤተሰብን ነገር እንኳን ተወው፤" ድንገት መሳቋን ታትታ በነገር ተብሰለሰለች፤ ..."ብዙ ደስ የማይሉ ትዝታዎች እንዳሉሽ አውቃለሁ፤" አላትና አበጋዝ አተኩሮ ተመለከታት፤ ወደ ውስጧ የሰመጠ፣ ምስጢሮቿን የሚመረምር መስሎ ስለተሰማት ፊቷን መለሰች።

"ኤልሲ... እኔ ግን በተለይ ወላጆችሽ ላይ የቋጠርሽውን ቂም መተው እንዳለብሽ ይሰማኛል። ብስጭትና ከልክ ያለፈ አጠጣጥሽ ከእነርሱ የወረስሽው ነው የሚመስለኝ..."

"እስኪ ተወኝ እቴ?"

"አልተውሽም! አንቺ ወላጆችሽ ላይ የያዝሽውን ቂም ካልሻርሽኮ አሁን ለልጅሽ ጥሩ እናት አትሆኚም። ምክንያቱም አንቺ ውስጥ እናትሽ አሉ፤ አንዳንዴማ ስለእርሳቸው የምትነግሪኝን ሰምቼ አንቺን ሳይሽ ቁርጥ እርሳቸውን ነሽ። እናም ይህንን የውስጥሽን ፍጭት ካልፈታሽ ምንም ሰላም አታገኚም። ለልጅሽ የምትችይውን ያህል ምርጥ እናት መሆንም አትችይም፤" ብሎ አስረግጦ ነገራት... ያለው ሐቅ ነበርና አንዳችም አልመለሰችለትም። እሱ ግን በሞቅታውም ታግዞ መወትወቱን አላቆመም፤

"ኤልሲሻ ... እናትሽኮ ብዙ ስህተት ሠርተው ሊሆን እንደሚችል ይገባኛል። ግን አንዲት ድሃ ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን አትርሺ፤ እኔ በግሌ ከዚህች ጦሰኛ ሃገር ብላቀቅ ደስታዬ ነው። የኛ ማኅብረሰብኮ እንደሌሎቹ ማኅብረሰቦች ሁሉ ብዙ ጎጂ ልምዶች አሉት። የራሱ በረከትና እርግማኖች

አሉበት። አንዳንዴ ልክ አይደሉም ያልሻቸው ነገሮች ግን በጊዜ ሂደት ትክክል ሆነው ልታገኚያቸው ትችይ ይሆናል። ያ ነው የኔ ነጥብ፤"

"አቤ! ዛሬ ምን አድርጊ ነው የምትለኝ? ... አንተ ቆይ የኔ ችግር መቼ ነው የሚገባኽ?" ... ተነፋረቀች፤

"እሺ በቃ አትቆጪ...ትቼዋለሁ፤ ግን አንድ..." ብሎ ንግግሩን ሳይጨርስ መርዕድ ዓይኖቹን እያሻሸ ከመኝታ ቤቱ ወጣ። ኤልሳ ከወንበሯ እንደተሰየመች አንድዬ ልጇን እንደ ነገሩ አየችው።

|አሁን አሁን አንድ ሐሳብ ኤልሳን እያስጨነቃት መጥቷል። በቅርቡ ልጇ አምስት ዓመት አልፎታል፤ "ማ" እና "ባ" ከሚሉ ቃላት፣ "ሃጢሽ" ከሚለው ማስነጠስና፣ "እኚያያ" ከሚል ለቅሶው በቀር እስከዚህ እድሜው ድረስ ቃላትን መናገር አልቻለም። ኤልሳና አበጋዝ ከዛሬ ነገ መናገር ይለምዳል ብለው ቢጠብቁም ምንም የሚለወጥ ነገር ጠፋ። መርዕድ መናገር ተስኖት ቀረ።

|አውጥታ ባትናገረውም ኤልሳ አንድ የሚጎረብጥ ግምት በውስጧ ዝም ብሎ ይመላለስ ይዟል። የውሸት መሀላዬ ጦስ ለልጄ ተረፈ የሚል ሐሳብ በተደጋጋሚ ይረብሻት ይዟል።

* ✵ *

# ምዕራፍ አስራ አንድ

# ያልተገለጠው ግዙፍ

*‹ሳይኮ-አናሊስቱ› ሶፎኒየስ በጉም ሠረገላ ተንደልዱሎ ወደ ስድስተኛው ከተማ ዘለቀ:: ከፊቱም ስድስተኛው ሃምራዊ የብርሃን ሰበዝ በራ ☀ከሰው ቀጠሮ የእግዜር ቀጠሮ ሆነና ከእለታት በስድስተኛዋ ቀን፤ የነፍስን አብርኖት ሊለኩስ በማለዳ ከከዋክብት ስድሩ ኦሪዮን፤ አርዮብ ጋር ተገናኘ::*

*{የተጻፉት ነገሮች ቅዠት አይደሉም፤በሃይማኖትም ሆነ በመንፈሳዊነት ከፍ ብለው የዘለቁ አባቶች ይህንን ልዩ ጉዞ ተጉዘውታል:: ለምሳሌነትም ቅዱስ አቡነ ሺኖዳ የመንፈስ ነጻነት በተሰኘው ድርሳናቸው የአርምሞ ገጠመኞቻቸውን እንደዚህ ብለው ይተርኩልናል::*

*"እንዲህ በሆነ ጊዜ በጸሎት ክፍሌ ብቻዬን እግሮቼን ዘርግቼ ወደ ላይ አንጋጥጬ ሳለ፤ በዚያች ምሽት አንድ ክስተት ተፈጠረ፤ ይህም እጅግ እንግዳ ነበር:: ራሴን ከመጠን በላይ አጨናንቄ ይሆን? ወይስ ምናብ ዓለም ውስጥ ገብቼ፤ በቅዠት ባህር ውስጥ እየዋኘሁኝ ይሆን? አልያም እግዚአብሔር ራዕይ ገልጦልኝ ይሆንንን? ...ብቻ አላውቅም፤ የማውቀው በፊት የብርሃን መልዓክት ማህበር በክንፋቸው ተሸክመው ወደላይ ሲነጥቁኝ ብቻ ነው:: ከበታቼ ያለችውን ምድር ስመለከት፤ ቀስ በቀስ ክበቧ እየጠበበ፣ እያነሰ ከዓይኔ ተሰወረች:: ዳግመኛ የዓለም ብርሃን እየቀነሰ መጣና ጠፋ፤ ፍጹም ዝምታ ሆነ::"}*

*...እነሆ ሶፎኒያስም የብርሃን ቅጥር ግቢ ውስጥ ሰተት ብሎ ገባ:: ወደዚህ ሥፍራ እንዴት እንደመጣ ያላወቀው ግዙፍ በር፣ ሽቅብ የሾሉ ጦሮች፣ በአልማዝ የተሞረዱ የዮጵ ወርቅ ዘንጎችን አልፎ መሰስ ብሎ ተከተተ:: ‹ቴምፖራል› በተባሉት አንጓል ክፍሎች የተከበቡ፣ ‹ሰብ*

ኮርቲካል› አካላት፡ ‹ባዛል ጋንግሊያ›ና የ‹ሊምቢክ› ተምሳሌት ወደሆነው ቤተ-መቅደስ ሲዘልቅ ብር የማይገዛው የከበረ ድንጋይ፣ የከበረ ጥበብ፣ ሩቢና ክሪስታሎች ተዘርተው አየ። ነፍስን የሚያሽቆጠቁጥ፣ ልብን ስንጥቅ የሚያደርግ ውበት ተቀበለው። የከርቤ፣ ሚስክ፣ ሉባን-ጃና ሉባን-ዘከር[114] እጣኖች ማዕዛ ስርጉን አወዱት። ዙሪያውን ቢያስተውል የእልፍኙ አውታራት፡ በእልፍ ሻማዎች ተሽቆጥቁጠዋል።

ጣሪያውን ጨምሮ በሁሉም አቅጣጫ ያሉ ግድግዳዎች በጠልሰም ስዕል ተሸልመዋል። ቀጥሎ ደግሞ ከመቅደሱ መሐል ስድስት ደረጃዎችን ተወጥቶ የሚደረስ ግዙፍ ዙፋን አለ። እያንዳንዱ ደረጃም ከቀይ እስከ ነጭ በተቀለሙ ጌጣጌጦች እጅግ ያሸበረቀ ነበር። ዙፋኑ ግን ግጥም፣ ድፍን ያለ ጥቁር ነው፤ ከሥሩም ብዙ ልብሳቸው እንደ እሳት የሚያብለጨልጭ ሰዎችን ተመለከተ። ገሚሱ ባለበት ቆሞ እጆቹን ወደ ላይ ዘርግቷል፣ ገሚሱ በተባህታዊ ጥሞና ተቀምጦ ይመሰጣል። ሁለንተናዊው ክዋኔ ከምድራዊ ይልቅ ወደ ሰማያዊነት ያደላ ነበር።

ከሰዎቹ መካከል አንዱ በመደነቅ ቆሞ ሲገረም ወደነበረው ሶፎኒያስ በብርሃን ፍጥነት መጣ። "እንኳንም ደረስክ፣ በንቃተ ህሊና፡ እኛ ጋር ስለተቀላቀልክ በእውኑ ደስ ብሎናል።" አለው በነጎድጓዳዊ ድምጽ፣ ሶፎኒያስ የሚያየው፣ የሚሰማውና የሚያሸተው ብሩክ ውበት ልቡን ሰውሮት በቅጡ መልስ ለመስጠት አቅም አጣ፤ "አሁን ያለኸበት መደነቅና ግርምት ይገባኛል።" አለ ብርሃናማው ንቃተ-ህሊና … "ከሥጋና አእምሮ ጠረፍ ሰርገው ማየት የቻሉ ሰዎች ጥቂት ናቸው። እነርሱም እዚህ ሲደርሱ በመገረም እንዳንተው ደንዝዘው ይቀራሉ። ዓባይን ያላየ እንዲሉ የናንተ ሊቃውንት፤ በምድር በሚገኙ ውበቶች የሚደነቁ ሰዎች ያልተገለጠውን ግዙፍ በጨረፍታ ቢያዩ እስከ ምድር ፍጻሜ ፈዘው ይቀሩ ነበር። ይሄን የመሰለ እርከን ግን ለጥቂቶች ብቻ በአርምሞ የሚገለጥ ነው።[115] ነፍስ እንዲህ እንዳንተ በአብርሆትና በአመክንዮ፣ በትምህርትና በትሕርምት፣ በእውነት፣ በእምነትና በእውቀት ስትታጀብ ጠረኗ እንዲህ ያምራል። ቃናዋ ይማርካል። ህያውነቷ የሚረጋገጠውም ያኔ ነው።

የአብርሂት እንጨት ተለኩሶ የእምነት እጣን ሲንጣጣ፡ የኑሮ ጣጣ በጥሩ ማዕዛ ይሸፈናል። ስድስተኛው ምድጃም መገለጦች ላይ ይጣዳል። ኤሌክትሪክን በብቃት እንደሚያስተላልፍ የወርቅ መስመር አዲስ ብርሃንን

114 ለአርምሞና ምጥቀት የሚያግዝ የእጣን አይነት፤

115 ማቴዎስ ወንጌል፤ 7፡14

ይፈነጥቃል:: ታዲያ አንተም ብርሃን ላይ ቆመኽ፡ ራስህ ለራስህ በግልጽ ተነጋገር፣ ከባድ ምስጢሮችህ ላይ ባትሪ አብራባቸው:: ከእውነተኛው አንተ ጋር ወለል ባለ አደባባይ ተወያይ፤ ራስህን ስልለውና እወቀው፤ ከማንቀላፋቱ ቀስቅሰከው ለህያው አንተነትህ ጋር ወዳጅ ሁን::

ለዚህም የሚያግዙ ብዙ ጥበቦች አሉ፤ ለምሳሌ ይሄ ሁሉ አልማዝ፣ ሩቢስ፣ በሉር፣ ሰንፔር፣ ኢያስጴድ፣ ሰርዲኖን፣ ዮጵ፣ ጳዝዮን፣ ዕብነ-አድማስ... እዚህ የተደረደሩት ለውበት ብቻ እንዳይመስልህ:: የእያንዳንዳቸው ለዘመናት ጉልበት ያጠራቀመ እርግብግብታ፣ ክሪስታላዊ ዝውተራ-ምች| ለመንፈሳዊ እድገት ስለሚያግዙ፣ ትንግርታዊ መዋቅርና ስድራቸው፡ ኤሌክትሮ-መግነጢሳዊ ኃይልን ስለሚረጨም ጭምር ነው:: ነበልባላዊ ብራኸ፡ ሚራኸነትን ለሚለማመደው ነፍሳችን ልምዳቸውን ስለሚያካፍሉት ድንቅ ናቸው:: ለዚህም ቃላት አያሻቸውም[116]:: እነሆ ስድስተኛው ውስጣዊ እልፍኝ የማይለዋወጥ ፅኑ ሃሳብ ያዘለ የማንነታችን መስያ፡ እውን የሆነው መንፈሳዊ፣ ሰላማዊ ብርሃን ያለበት እኛነት ነው::

እናም ይህንን ሐቅ እወቅ፣ ሁሉም ሰው ውስጥ ሊፈነዳ ያደባ ኮከብ አለ:: በጥበብ ነቅተው የበሩ ሰዎችኮ የዓለም ፀሐያት ናቸው፤ ታዲያ ሁሉም ሰው መለኮስን ካወቀበት ያበራል:: ትክክለኛ ፀሐያት ደግሞ ሰው አያቸውም አላያቸውም ያበራሉ:: በማሳወቅና በአርአያነት ሰዎችን ከጥበብ በሲራዊነት ይመልሳሉ:: ታወቁም፣ አልታወቁምም የተሰወሩ ዓይኖችን ያበራሉ:: እመነኝ የእያንዳንዳችን እሳቶች እየነደዱ የሚጫወቱት ሚና አሌ የሚባል አይደለም:: የተፈጠርነውም ካለምክንያት አይደለም:: መሀይምነትም ላይ ሆነ የአውቃለሁ ትዕቢት ላይ የአርምሞን ብርሃን ማብራት አለብን:: ሙቀትና ብርሃን ከኛ ይፈንጥቅ!" አለና መላ ሰውነቱ በደማቅ ቡግቦጋ ፈካ፤

..."ዶ/ር ሶፎኒያስ? እስኪ ልጠይቅኽ? ፀሐይ የተደበቀን ሰሀ ቀዳ ስታበራ አይተኽ ታውቃለህ? አንድ ዓይኗን በጥበብ ስትገልጥ ገጥማኽ ታውቃለች? ፍኖቱን ፍንትው ያደረገ የብርሃን ፋና፤ ጮ-ራህ ሲፈነጥቅ፣ ወገጋን ሲፈካ፣ ጎህ ሲቀድድ፣ ቀኑ ሲበ-ራህ ከነፍስህ ገመና አስተውለኻል? የበጋው ሙቀት የሚወክል፡ ጠቋሚ ቀስትና ግዙፍ ሰይፍ የያዘ የኦሪዮን/ አርዮብ ህብረ-ከዋክብትን አጥንተኻል? የሴህ እሳት ምልክት፣ የጊዛ ፒራሚድና አሙናዊ| የኦሳይረስ፣ ፒታህ፣ ዮ-ቶርና ሴት ☀|ከኦሪዮን

116 ነንቃተ-ህሊናን ከፍ ያደረግ እርግብግብታ፤ ከራሳቸው ወደ ሌላው ሪዞኔት ያደርጋሉ፣ ያስተላልፋሉ፤

ሥነ-ፈለክ የተሰናሰለን ግሩም ግንባታ መርምረኻል? የግርማ ሞገሣማው የዐባይ ወንዝ ወኪል፡ ኮከብ ሲሪየስ፣ እጅግ ግዙፍ እሳታማ ጅራቶች የሚደንሱበትን ጸፍጸፈ ሰማይ ቀና ብለኽ አይተኻል ወይ? እነሆ እኔና አንተ ወደ ጠፈር መጣቂ፣ ተንዶልዷይ መንኮራኩሮች፣ የዚያ ምሽትን አንጊ ወጋገን--- የብርሃን ክሮች ነን!

የነቃነው ጥቂቶችም ብንሆን አቅመ ነቂስ እንጂ ዘሃ አይደለንም:: በ‹ኮዝሞ›ዎች ላይ የምንስፈነጠር ካቴና አልባ፡ ዘላለማዊ፡ ተወርዋሪ ኮከቦች ነን:: የወግ ተራኪው ባለ ቅኔ ደናሽ፡ የኤቶዮጵ ሥጋና ብርሃን ሽራፊ፣ እኛ ነን:: የሰማይ ግማጁ ቢጫ ፍላጻ፡ በነፍስ ምህዋሮች ላይ ዛሬም በኛ በኩል ይፈነጥቃል:: ልክ የአእምሮ መብረቃት፣ እሳታዊ የ‹ኒዩሮ-ትራንስሚተር›[117] አፍታዊው ‹ዶፓሚን›ና ዘላቂው ‹ሴሮቶኒን› አስተኔዎች| የማሰብ ኃይል ሚዛን መለያዎች ሲጎለብቱ እንደ ‹ዩኒቨርስ› ከላ ወሰን ይሰፋሉና::[118] አንጎላችን የተጠላለፈ የጥቃቅን መብራቶች ጠፈር፣ የጥቃቅን መብረቆች ህዋ ነው:: በሐልዮት አውታራችን ውስጥ ‹ኤሌክትሮ-ማግኔቲክ› ፊልድ አለ:: እመነኝ፣ ይህንን በትንሽዬ የራስ ቅላችን ውስጥ የሚካሄደውን ተዓምር ያየ አጃኢብ ማለቱ አይቀርም::[119] እኛ አቅሙን የተረዳን ደግሞ ለሌሎች ተዓምር የሚመስል ሥራን እንሠራለን::

እነሆ የተቀመጥክበት የወርቅ ቅልና የህይወትን ዕንቁ ፋና ያጨቀ ሳጥን ከአንገትህ በላይ ይገኛል:: የሳጥኖቹ አምራችም እጅግ ርህሩህና አዛኝ ባይሆን ኖሮ ይህ ባልተገባን ነበር::" አለና የብርሃን ንዝረቶችን ከአቅሉ ውስጥ አርገበገበ፤ ሶፎኒያስ ግን በቤቱ ውበት መደነቁ አላባራም ነበር::

"ይሄ የምታየው እጹብ ድንቅ ቤተ-መቅደስ ከሰዓታት በፊት አልነበረም:: በዚህ እርከን ላይ ያሉ ግንባታዎችና መዘጋጀቶች ግን ጊዜን የማይፈጁ የእምነት ጉዳዮች ናቸው:: በዓይን ጥቅሻ ፍጥነትም ይከወናሉ:: ይህንን ቤተ መቅደስ ስንገነባም አንድ ተምሳሌት ነበረን:: በመጽሐፈ ነገሥት

---

117 አንጎል ውስጥ መልዕክት የሚያስተላልፉ ንጥረ ነገሮች፣

118 አንጎላችንን ብዙ በተጠቀምነው ቁጥር በኃይልም፣ በመጠንም የመጨመር ተፈጥሮ አለው ፤

119 ጃፓን ፉጂሲ ውስጥ ከሰው ልጅ አንጎል የበለጠ ፈጣንና ትልቅ የማከማቸት አቅም ያላቸው ‹ሱፐር-ኮምፒዩተሮች ኔትወርክ› ለመፍጠር የተቻለ ቢሆንም አንድ ከተማ የሚሞሉ ሰርቨሮችና አስር ሺህ ቤቶችን ማብራት የሚችል ኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቅመዋል:: የሰው ልጅ አንጎል ግን እናናስ በምታክል የራስ ቅል ውስጥ ተወስኖ፣ አንዲት የሻማ አንፖል የሚያበራ የኤሌክትሪክ ኃይል እየተጠቀመ እንዲህ መሥራቱ አፈጣጠሩን በጣም አስገራሚ ያደርገዋል!

ቀዳማዊ ምዕራፍ አስር ቁጥር አስራ ስምንትና ዘጠኝ እንዲህ ይላል፤

"18፤ ንጉሥ ሰሎሞንም ከዝሆን ጥርስ ታላቅ ዙፋን አሠራ፥ በጥሩም ወርቅ ለበጠው:: 19፤ ወደ ዙፋንም የሚያስሄዱ ስድስት እርከኖች ነበሩ፤ በስተ ኋላውም ያለው የዙፋኑ ራስ ክብ ነበረ፤ በዚህና በዚያ በመቀመጫው አጠገብ ሁለት የክንድ መደገፊያዎች ነበሩበት፥ በመደገፊያዎቹም አጠገብ ሁለት አንበሶች ቆመው ነበር::" እንዲሁ ሁሉ እኛም ይህንን መቅደስ ገንብተናል:: የአንበሳን እሳትነት፡ የኪሩቤል ውክልና ከማይነጥፈው የብርሃን ጅረት ጋር ነፍሳቸውን አቆራኝተው እንደሚያበሩ ሲቀ-ትጉኃን የነበረን ማንቀሳቀስ፣ ያልነበረን መትከል የቅጽበት ብቻ ጉዳይ ነው:: "ኖኅት ሰማይ ለራእይ"፡ ኀብረ-ፀሐይ ህንጻ ጥበብ ለመገንባት አይፈተኑም:: መቼም ቢሆን በእምነት ከተጓዝን ይህንንም| ከዚህም በላይ እንድናደርግ ስልጣኑ እንደተሰጠን አትርሳ:: ብቻ በእውቀትና እምነት መንቃት ነው የሚጠበቅብን::

ታዲያ ጥበቡ በአፍ እንደሚወራው ቀላል እንዳይመስልህ:: ኢዮብ እንዳለው ይሄን ጥበብ የኢትዮጵያ ቶጳዝዮን ወርቅ አያክለውም::[120] ከልቡ የፈለጋት ግን ታገኘዋለች:: ታዲያ ቁም ነገሩ መቼ መብራት መቼ መጥፋት እንዳለብን ስናውቅ ነውና ላንተም መልካም ይሆን ዘንድ የእሳታዊ ኃይሎችህን ማብሪያ ማጥፊያ ተቆጣጠር:: የህብረ-ኮከብ ወርቃማ ዘንጎችህን መቼ መያዝና መቼ መተው እንዳለብኽ እወቅ:: አስታውስ፡ ይህ ንጽጽር ተምሳሌትነትና እንቶኔ እንጂ መጠነ-ቁሳዊነት አይደለም:: ይህ ከስሜት ህዋሳት አልቦ ነው:: ምክንያቱም አርምሞን አታደርገውም፣ ትሆነዋለኽ እንጂ:: ተመስጦን አትሞክረውም፤ ትኖረዋለህ እንጂ:: የምትናገራቸውን ቃላት ቀንስ፤ ሸክምህን መተንፈስ፣ መሰናክሎችኽን መበተን ካሰኘህም ወደ ውጭ ሳይሆን ወደ ውስጥህ በፍቃደኝነት ፈንዳ፡ አብራ፡ ተተኮስ◍::

እነሆ ከሰሜን ዋልታ የተንጸባረቀች ደግሞ ሁለተኛ ፀሐይ☀ አለች:: የሰባቱን እርከን ምስጢር ተረድተው፣ የግእዝ ሰባት ቁጥር አጠላልፈው በቀረጹት|[121] የሰው ጥበብ በኛ እርከን ላይ ሆነው በፈለፈሉት| በላሊበላ ውቅር አብያተ ቤተ-ክርስቲያን ትይዩ በሚገኘው ‹ፕሌይደስ› ህብረ

120 (መጽሐፈ ኢዮብ፤ 28:19)

121 ስዋስቲካ ቅርጽ በናዚዎች ከብሩ ከመጉደፉ በፊት በላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት በክብር ተቀርጾል፤ ከዚያ ሺህ ዓመታት በፊት ደግሞ ጥቁሮቹ እነ ከሪሽና በመሠረቱት የሂንዱ ኃይማኖት ቤተ-መቅደሶች ውስጥ በብዛት ተቀርጾ ይገኛል::

ከዋክብት አስገራሚ የካርታ ግልባጭ መስለው ተበትነዋል፣ ሰባቱ ከዋክብት ሳይጠፉ ያበራሉ። እኛም እዚህ እርግብግቢት ውስጥ ከገባን የወርቃማው ንጽራዊ ስድርን ሥርዓት ሳናንድል በሰላማዊ ሽክርክሪት ላይ እንዋባለን።

ታዲያ ውበታችን ለሌሎች በማብራታችን እንጂ በግል ምቾታችን ውስጥ አይደለም። ፀሐይ ለራሷ በሚያንገበግብ ቃጠሎ ውስጥ ሆና የኛን መራብ፣ መጨለምና መብረድ ትከላከላለች። ሻማ ራሱ እየቀለጠ ብርሃኑን ሲለግሥ፣ አንፖል ደግሞ እየበራየ ብርሃኑን ሲለቅስ መች ድምጽ አውጥተው አማረው ያውቃሉ? የሰው ልጆች ግን በጭላንጭል አበርክቷቸው እንደ ተራራ ይኮፈሳሉ። ይህም ከእውቀት አልባነትና ከአርምሞ ከመራቅ ምክንያት ይመነጫል።

እርግጥ እውነት መናገርና የዋህነት የአብርሆት መገለጫ ሊሆን ይችላል። ዋናው አብርሆት ወይም ንቃተ ህሊና ማለት ግን የህጻንነትን የዋህነት ሳይለቁ የጠቢብን እውቀት ማካበት መቻል ነው። ዝቅ ብለህ ካዳመጥኸ ከፍ ያለ ሀልዎታዊ ጥበብን ትቀስማለህ። ለሌሎችም እንደ ታዛ ታብራለኸ።" አለና ፍላጻው ኦሪዮን የሶፎኒያስን ዓይን አበራለት። ሶፎኒያስ በበኩሉ በዚህ አስገራሚ የብርሃን ጉዞ እየሾረ ሳለ በቅርቡ ያዳመጠው የባለ ቅኔ አያ ሙሌ ግጥም ትዝ አለው። እንዲህም ይላል... "ከየማዕዘናቱ እየተመመ የሚናጠዉን የብርሃን ኸረት ተከትዬ የተንጣለለ፣ ወርቃማ የህይወት ዉቂያኖስ ደረስኩ፡ ግን ከድንጋጤ ሳይሆን አይቀርም ከመገረሜ የተነሳ ደፈረስኩ ... ድምፅ በማይሰማበት የፀጥታ ምህዋር ልሳኑ አለተርጓሚ እየተፈታልኝ አቀበለኝ፣ አንዳች ነገር...

ዳግመኛ የማይነገር... ዉብ አገር

ህዋሶቼ በአርምሞ ተመስጠዉ

እያንዳንዷን ክስተት ሲያስተዉሉ

ድንገት ተፈታሁ..."

እነሆ እሳታማው የድምጽ ጎርፍ ወደ ሶፎኒያስ መፍሰሱን ቀጠለ። "እናማ አንድ ማወቅ ያለብኸ ሌላ ነገር በዚህ ዘመን ዓለምን ግራ የሚያጋቡ ታሪካዊ ቅርሶች የተገነቡት በመሰል ምስጢራዊ ጥበብ ነው። የፒራሚድና ላሊበላን እንደነገርንኸ ሁሉ በአክሱምም ይህ ጥበብ ተንጸባርቋል። በአራቱ የፍጥረት መሠረታውያን መሬት፣ እሳት፣ ውኃና ንፋስ የተገለጠ፣ ሰባቱን

እርከን 5 x 7 = 35 እንደመሆኑ የአክሱምም ሃውልት በ35 እርከኖች ተወቅሯል:: እነዚህ ደረጃዎች ከሠላሳ አራቱ የአከርካሪ አጥንቶቻችንና ሀብለ-ሰረሰራችን ውቅሮች ጋር ተመሳሳይ ናቸው:: እነዚም ለመንቃት ያደፈጠውን የ‹ኩንደሊኒ› ☤ ወይም ስርነ-ሰረሰር ⚕ ኃይላችንን ይወክላሉ::

ከታችኛው የጅራትና ፍትወታዊ የስሜት እርከን እስከ ላይኛው የአርምሞ ጵኒኤል[122] ደረጃ የተዘረጋ እሳታዊ ሥርዓት ነው:: የነርቭ-መድብሎች ወይም ‹ፕሌክሰስ› በየእርከኑ ላይ ይገኛሉ:: ዘ ፍጥረት 32፤30 በምሳሌ ስለዚህ ጥበብ ሲገልጥ “ያዕቆብም፦ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ፥ ሰውነቴም ድና ቀረች፡ ሲል የዚያን ቦታ ስም ጵኒኤል ብሎ ጠራው:: {ጵኒኤል የሚለውን ቃል የግእዝ መጽሐፍ ራእየ እግዚአብሔር ይለዋል::} 31፤ ጵኒኤልም ሲያልፍ ፀሐይ ወጣችበት[123] ፥ እርሱም በጭኑ[124] ♂ ምክንያት ያነክስ ነበር::”

እነሆ ወደ ጽድቅ የምትወስደው መንገድ እንደ ሀብለ ሰረሰር ፈሳሽ[125] ቀጭን ናት:: እናም እንደ ምሉዕ ሰው ቀጥ ብለህ የምትቆመው ከጭን ርቀህ ወደ ጭን-ቅላትህ ማብራት ስትጀምር ነው:: ለዚህም ጀርባህን ቀጥ አድርገኽ፣ በፀሐይ ብርሃን ሥር ተቀምጠህ በጥሞና መጓዝ ስትጀምር ይህ ይሆናል:: እነሆ አሁንም ከዚህ ‹ቴምፖራል› የማዘዣ ማዕከል ወደ ሰባተኛው ጵንኤል ተጓዝ:: እኛም እናጅብኻለን:: ይህንንም እናውቃለን - አንድዬ እንደጀመረው እስኪጨርሰው ድረስ ሁሉም ነገር በእርግብግቢት ውስጥ ይቀጥላል:: እኛ ተመሳጮች ግን ለዘላለም በማይናወጠው መሠረት፤ በጀማሪውና በጨራሹ አብሪ ፍላጻ ላይ ራሳችንን አጽንተን በእርግብግቢቱ ላይ እንዘወትራለን:: በዘላለማዊው ክራማ ውስጥ፣ ‹ራ በል አንተ ነፍሴ› እያልን በመንፈሳችን ስንበ-ራህ እንከርማለን::” አለውና በብርሃን ዝናብ አጥቦት በመብረቅ ፍጥነት ተሰናበተው:: ሶፎኒያስ ቀጭኗን የብርሃን ፈለግ ተከትሎ በውስጣዊው በር ከግሩሙ ቤተ-መቅደስ መሐል ወደ ተሰየመው ዙፋን ተጠጋ:: እየቀረበ በመጣ ቁጥር ብርሃናማዋ ፈለግ እየቀጠነች ሄዳ ሙሉ ለሙሉ ጠፋች:: እነሆ ሶፎኒያስ ራሱን ድቅድቅ ባለ ጨለማ ውስጥ አገኘ::

⌘ ⌘ ⌘

122 Pineal
123 Serotonin
124 gonads
125 CSF

ኤልሳና አበጋዝ መርዕድ መናገር የማይችል ልጅ እንደሆነ ለማመን አመታት ፈጀባቸው። የሰፈሩ ሰው ደግሞ የኤልሳ የውሸት ማህላ ለልጇ ተረፈ እያለ ተዘባበተባቸው። በቤታቸው ውስጥም ቢሆን ያን ያህል ሰላም አልነበረም። ጭቅጭቃቸው በዝቷል። የኤልሳ የመጠጥ ሱስ ከቀን ወደ ቀን እየባሰ መጥቷል። የመንግሥት መለወጥን ተከትሎ የአበጋዝ ሥልጣን ተጠያቂነት ውስጥ መግባቱ ደግሞ ነገሮችን አባብሶታል። ብዙም ሳይቆይ በሙስና ክሥ ተመሠረተበት። በስሙ የነበሩ ንብረቶች በሙሉ በፍርድ ቤት ታገዱ። ቤቱና መኪናው ተወረሱ። እሱ ማቆያ ቤት ሲገባ ኤልሳ ልጇን ይዛ እዚያው የፈረደበት የወላጆቿ ቤት ተጠጋች። ቀኑ ጨለመባት። ድሮም ለማበሻቀጥ የማይሰንፉት ወላጆቿ፡ ጭራሽ አባት የሌለው ልጅ ይዛ መምጣቷ ክፉኛ አስቆጣቸው። ለተወሰኑ ጊዜያት እንደ አባቷ በአረቄም፡ በጠጅም ጭንቀቷን ለመርሳት ብትሞክርም ነጋ ጠባ በነገር ሲነዘንዟት፤ መንቋሸሸና መራብ ሲጠናባት ልጇን ይዛ ወጣች።

ብይ አንከባላዩ፣ ባለ ካኪ ጃኬቱን ልጅ ጨምሮ ኤልሳን ከዚያች ቀን በኋላ አየኋት የሚል ሰው ከሰፈሩ አልነበረም።

⌘ ⌘ ⌘

ለይኩን ሽማግሌውን እሥረኛ ባናገረ በማግስቱ አንድ አዲስ እሥረኛ ወደ ቃሊት ማረሚያ ቤት ገባ። ሰውዬው በመነሳቀል ገጽታው ቢጠቋቁርም ለይኩን ግን ፊቱን እንዳየው ነበር የለየው።

በንዴት "አበጋዝ!" ብሎ ጮኸና እንደ ነብር ዘሎ ተከመረበት። የተወሰኑ የቡጢ ናዳዎችን ካዘነበበት በኋላ ሌሎች እሥረኞች ተባብረው፡ ጎትተው ከላዩ አነሱት። ለይኩን ግን የዚህ ሁሉ ዓመታት የእሥር ብሶቱ፡ በትንሹም ቢሆን ሲቀንስለት ታውቆታል። ከዚያ በኋላ ጸብ ለመጫር አልሞከረም። ያን ሌሊት በቅጡ ሳይተኛ ነጋበት።

በማግስቱ፣ ልክ ያ ሽማግሌው ጎብኚ ባሉት ቀንና ሰዓት፤ ትልቅ ፍንዳታ ተከሰተ። ጆሮውን ቀስሮ እየሰማ ሲጠብቅ የነበረው ለይኩን ጩኒን አስከትሎ በስተግራ ወዳለው አጥር አቅጣጫ አመራ።

እሱ ባያየውም ከኋላቸው ዳዊትም ተከትሏቸው ወጥቶ ነበር። ከብረት አጥሩ ሥር እንደደረሰ ኤሌክትሪክ ይኑረው አይኑረው እየተጠራጠረ ጥልፍልፉን ሽቦ ያዘው። ምንም ኃይል አልነበረውም። ለይኩን እፎይ አለና ዘሎ አጥሩ ላይ ተንጠላጠለ፤ ጩኒም ተከተለው። ወደ ላይ ሽቅብ

ወጥተው ከጫፍ ሲደርሱ ከአጥሩ እየተስፈናጠሩ ከግቢው ውጪ አረፉ። በዚህች ቅጽበት ነበር አንዲት ሚስማር የለይኩንን ባት የሸነቆረችው። ለይኩን ቁስሉን ለማየት ጎንበስ ባለበት ቅጽበት ጩኒ ወደ ሌላ አቅጣጫ ሮጠ።

ወዲያው ለይኩን ሩጫውን ለመቀጠል ቀና ሲል ከጀርባው ዳዊትን አየው። አሁን የሚሸሸው ከሁለት ጠላቶቹ ሆነ፤ ያለ የሌለ ኃይሉን ተጠቅሞ፣ ቁና ቁና እየተነፈሰ ተፈተለከ።

⌘ ⌘ ⌘

ጩኒ ድምጹን አጥፍቶ ከእይታ አምልጧል። ዳዊት ግን የተወሰነ ርቀት ከሮጠ በኋላ ዞሮ ዘበኞችን የስድብ ናዳ ያወርድባቸው ገባ።... "እኔ ማለት ዳዋ ነኝ! ማንንም የማልሰማ ሳተና! ... ወንድ የሆነ እስኪ አሁን ይያዘኝ!"

|አንድ ከቃሊቲ እስር ቤት ማማ ላይ የተሰየመ አልሞ ተኳሽ| አፈሙዙን አነጣጥሮ፣ ትንፋሹን ዋጥ አድርጎ፣ በጸጥታ አድብቶ፡ ቃታውን ሳበ። ሰከንድም ሳይቆይ ዳዋ ከመሬት ተነጠፈ። ታዲያ ሬሳውን ተሸክመው ከስገቡት እስረኞች መካከል አንዱ ጋሽ በቄ ነበሩ።

⌘ ⌘ ⌘

እነሆ ለይኩን ለደጉ ገበሬ ታሪኩን በሙሉ አውግቶ ጨረሰ። ሲቋጭም በረጅሙ ተነፈሰና... "ያው... ከዚያ በኋላ እንግዲህ እግሬ አምጥቶ እርሶ እጅ ላይ ጣለኝ፤ እርስዎም ለደግነ... አ... አ... አ..." ለይኩን ወሬውን ሳይጨርስ በመሀል ማቃሰት ጀመረ። ህመሙ ሰውነቱን በሙሉ ሰቅዞ ማውራት፣ መላወስ ከለከለው። እንደምንም ኃይሉን አሰባስቦ አንድ መልእክት ነገራቸው።

መልእክቱም... "አደራ፡ እኔ የሆነ ነገር ብሆን ሜሮንና ልጆቼን አግኝታችሁ እንደምወዳቸው ንገሩልኝ፤" የሚል ነበር።

⌘ ⌘ ⌘

የለይኩን ነገር ያስጨነቃቸው ደጉ ገበሬ ከቤታቸው ወጡና ከአካባቢው አንዳንድ ቅጠሎችን በጣጥሰው ተመለሱ። በጎድጓዳ ሸክላ ሳህን ውስጥ ቅጠሎቹን እያለመሙ በዓይኖቻቸው ደግሞ አስሬ በር በሩን ያማትሩ ነበር።... "ምነው ቆየች? ... አትመጣም እንዴ?" እያሉም በተደጋጋሚ ለብቻቸው ያጉተመትማሉ። የባህላዊ መድሃኒቱን አዘጋጅተው ሲጨርሱ፡

የለይኩን የቆሰለ ባት ላይ ሞጀሉትና በንጹህ ጨርቅ ጥፍንግ አድርገው አሰሩት።

ተንጋሎ እንደተኛ ቢያስተውሉት ልባቸው በሀዘኔታ ተሞላ። የበርካቶች ህይወት እንዲህ እንደ ለይኩን በውጣ ውረድ የታጨቀ ነው። ይህቺ ምድር የፈተናዎች ቋት ናት። ይህንን የምድር ምቾት ነሺነት የተረዱ ግን ጥቂቶች ናቸው። ጊዚያዊ ማታለያዋ ዘላቂ እየመሰላቸው አሁንም ብዙሃን ያምኗታል። በግፍ ሌሎችን እያስለቀሱ በምቾት መኖር የሚመኙ የአእምሮ ሞፎ፣ የህሊና ፋስቶ፣ የልቦና አንጉልፋቶ የሸበባቸው ብዙዎች አሉ። እንደ ለይኩን ያሉት ምስኪኖች ደግሞ ለፍተው ያገኙትን እንኳን በግፍ ይነጠቃሉ። ዓለም ላይ ያሉ ሰዎች በክፋት አለንጋቸው ይዠልጧቸዋል። ብር የሚባል ተራ መገልገያ፡ ከተመን አልባው የሰው ልጅ በላይ እየነገሠ ልባቸው እንክትክት ብሎ ይሠበራል። ብዙሃኑ በምድር ላይ ፍትሕ ሳያገኙ እንዲሁ እንደተበደሉ ለዘላለሙ ያሸልባሉ። በቀጣይ ዓለም ፍርድና ፍትሕ ካሌለ የዓለም ዳኝነት ማግለልና መድሎ፣ ፍርደ-ገምድልነት ቁጥር ስፍር የለውም።

ደጉ ገበሬ እነዚህን መሰል ሐሳቦች እየተፈራረቁባቸው ሳለ ለይኩን ትንሽ አቅም አግኝቶ ወደ ነፍሱ ተመለሰ። ናላውን ሲያውቅ "ወይኔ… የት ነው ያለሁት… ምን ሆኜ ነው?" እያለ ተወዛገበ፤ ጠጋ ብለው እጃቸውን ትከሻው ላይ አኖሩ፤

"አይዞኽ ልጄ፣ ተረጋጋ… አየኸኝ? … እኔው ነኝ…"

"አው ጋሼ! እርስዎ ኖት እንዴ… ራሴን ስቼ ነበር መሰል…" አለ ወደ ሙሉ ንቃቱ የተመለሰው ለይኩን፤

"አዎ… አይዞህ፤ አሁን ለጊዜው ደህና ነህ። ደግሞም የናፈቁህን ሳታገኝ፣ ህልምህ ሳይሰምር… ምንም እንድትሆን አልፈቅድም።" አሉና በአባታዊ ዓይን ተመለከቱት፤

|ከደቂቃዎች በኋላ ትንሽ ነፍሱ በቅጡ መለስ ስትልለት ደጉ ገበሬ አንድ የምነግርህ ቁም ነገር አለ ብለው ከጎኑ ተቀመጡ።

"… ቅድም ስለ ልጅ ልጄ የማርታ እናት ጠይቀኸኝ ነበር አይደል?"

"አዎን…" አለ ለይኩን ባለችው አቅም ንቅት እያለ፤

"እንግዲህ እውነታውን እወቅ፤ የማርታ እናት ስም ሜሮን ነው፤ አባቷ ደግሞ ለይኩን ተስፋሁን ይባላል።" ብለው ሲነግሩት፤ እሱም ሰምቶ ክው

ሲልና የቤታቸው በር ሲንኳኳ አንድ ሆነ።

⌘ ⌘ ⌘

ደጉ ገበሬ፣ አባ በላይ በዝግታ ተነስተው የሚንኳኳውን በር ከፈቱ። ... ሜሮን ማርታን ይዛ ወደ ውስጥ ስትገባ ለይኩን ዓይኑን ማመን አልቻለም። ከአልጋው ከመነሳቱ በፊት ተስፈንጥራ ቀደመችው። እንደተኛ ላዩ ላይ ተከመረችበት። ለአፍታም ቢሆን ህመሙ ጠፋ። የሠራ አካላታቸው ተጣበቀ። አቀፋት... አቀፈችው... ዓይናቸው በደስታ እንባ ራሰ። በተለይ ከንፈሮቻቸው ለጉድ ተጋምደው አልላቀቅ አሉ።

*{የሚዋደዱ ጥንዶች ሲቀራረቡ ከንፈሮቻቸው እንደተቃራኒ ዋልታ/ ማግኔታዊ ስበት ይጓተታሉ። ሲስማት፡ ስትስመው ግን ከከንፈሮች፣ ከቆዳዎች መተሻሸት አልፈው በውስጠኛው የነፍስ ቋንቋ ይግባባሉ። በዝምታ ውስጥ እኔነታቸውን ያዋህዳሉ፤ የዚህችን ምድር ኑሮ ጣፋጭ ጥንቅሽ ይመጣሉ፣ አብረው ህይወትን ይቀጫሉ። ወር በይሉኝታ ካወሩት፡ ለደቂቃ ከልብ የሳሙት ይበልጣል። ዝም ብሎ በደስታ ያስዋኛል። ለዚህም ነው የሁሉም ስሜቶች የመጨረሻ ከፍታ በዝምታ የሚገለጸው፤ እኮ ማንስ ነው በተመሳሳይ ጊዜ የሚወዳትን እየሳመ ማውራትም የሚሆንለት? እንዲሁ ሁሉ ጥልቆቹ ደስታዎች ከዝምታ ማህጸን ይወለዳሉ።}*

*ለይኩንና ሜሮን ብዙ መጠያየቅ የፈለጉት ነገር ቢኖርም፤ አንዳች ቃል ሳይተነፍሱ ለሰዓታት፣ ለዓመታት፣ ለዘመናት ተቃቅፈው ቆዩ። ለዘላለም ቢሆን ራሱ ደስታቸው ወደር አልነበረውም። ቀስ በቀስ ግን የለይኩን ሰውነት እንደ እሣት ይለበልብ ጀመር። ልቧን ፍርሃት ፍርሃት እያለው ቀና ብላ አየችው።*

*"ሰውነትህ ለምንድነው እንዲህ የሚያቃጥለው?"*

*"ተ...ተይው፡ ዝ... ዝም ብሎ ነው፤" ለይኩን የሞት ሞቱን መለሰላት፤*

*ሜሮን ግን ሆዷ ርብሽብሽ አለ። ደስታዋ የሚዘልቅ አልመስልሽ ፡ አልመስልሽ አላት።*

*"ሜ... ሜሪ?"*

*"ወዬ የኔ ጌታ..."*

*"እስኪ ማርታን ወደዚህ ጥሪልኝ? ልያት" "እ... እሺ... ማ... ማርቲ...?"*

"ወዬ እማ"

"ነይ ጠጋ በይ..." ማርታ ፈራ ተባ እያለች ወደ አልጋው ተጠጋች። "ሁሌ አባቴን አሳይኝ እያልሽ ትጠይቂኝ አልነበር? ... ይኸው ዛሬ አባትሽን ተዋወቂው።" ስትላት ማርታም መጥታ አባቷን ለመጀመሪያ ጊዜ አቀፈችው። ለይኩን አዳዲስ የእንባ ዘለላዎች ከዓይኑ ይመረቱ ጀመር። የሴት ልጁን እጆች ያዘና በስቃይ፡ የመጀመሪያም የመጨረሻም ምክሩን መከራት። "ል... ልጄ፣ የአብ...ራሀ...ኬ ክፋይ፣ አንድም ቀን በዓይኔ አይቼሽ ባላውቅም፣ እንደ አባት ወግ ከጎንሽ ሆኜ ባላስከብርሽም፡ ፈጣሪ በሚያውቀው ከልቤ እወድሻለሁ። ልጄ፡ እኔ የማወርስሽ አንዳችም ሐብት የለኝም። ግን ይሄን ምክሬን ከልብሽ አኑሪ፣ እንዳትረሺ.... ከምንም በፊት ለትምህርትሽና ለህይወትሽ እድገት ቅድሚያ ስጪ፤ ደግሞም በፍቅር መሳይ የአፍላ እድሜ/ አማላይ ስሜቶች እንዳትሸወጂ። ይህቺ ምድር እንደ እናትሽ ካሉ ቀና ሴቶች ብቻ ሳይሆን ልባቸው በማይገኝ መሰሪዎችም የተሞላች ነችና በምላሶች ጨዋታ እንዳትሸወጂ! ከምትወጂያቸው ይልቅ ግን የሚወዱሽን ሰዎች አስቀድሚ። አስታውሺ፡ የወደድሽው ሁሉ ይወድሻል ማለት አይደለም። ማንንም ሰው እንድትጠይ አልመክርሽም/ ግን የራሴ ብለሽ የምታቀርቢያቸውንና የምታምኚያቸውን ሰዎች በጥንቃቄ ምረጪ። በምንም ይሁን በማንም ለሚገጥሙሽ ፈተናዎች ደግሞ ፈጽሞ እንዳትሸነፊ.... በርቺልኝ... ጀግና ሁኚልኝ። ... አ...አደራ ለእናትሽ ለሜሮን እና ለእኚህ ጠቢብ አያትሽ ታዘዢላቸው። ገና ያላገኘሽው መርዕድ የሚባል ወንድም እንዳለሽም ማወቅ አለብሽ። እግዜር ያለ ቀን ትገናኛላችሁ። አንቺ ብቻ በርቺ..." ብሎ ቁና ቁና እየተነፈሰ ምክሩን ለገሰትና አንገቱን ወደ ሜሮን አዞረ።

"ሜ... ሜሪ?"

"ወ...ወዬ..." ሜሮን እየተንሰቀሰቀች ማልቀስ ይዛለች፤ በፍቅር ዓይን ዓይኗን እያየ የሆዱን ይተነፍስላት ጀመር...

"ህይወቴ ከሞላ ጎደል እርባና ቢስ የሚባል ነው። ብቸኛ፣ ደካማና እዚህ ግባ የማልባል ከንቱ ሰው ነበርኩኝ። የኖርኩባቸውን ዓመታት ሳስብ ሐዘንና ትግሌ ብቻ ይታዩኛል። በትውስታዬ ውስጥ የገዘፍሽ የህይወቴ ትርጉም፣ የደስታ ነጠብጣቤ አንቺ ነሽ። ትንሽም ቢሆኑ ያሳለፍናቸው የፍቅር ጊዚያት ለኔ ከምንም በላይ ውድ ናቸው። በትዝታዬ ማህደር ሁሌም ደምቀው ኖረዋል። የእውነት አንቺ ልዩ ሴት ነሽ! ዘግይቼም ቢሆን ለኔ ደስታና ስኬት ያደረግሽውን ሁሉ አውቂያለሁ። ፍቅርን ባንቺ አይቻለሁ። ከልቤ

እወድሻለሁ! ... ግ...ግን መወደድም ያንስብሻል። ፈጣሪ እድሜ ሰጥቶኝ፡ ለኔ የሰጠሽኝን ሩብ ,ታህል ፍቅር ብሰጥሽ እድለኛ እሆን ነበር... ግን ለዚያ የምታደል አይመስለኝም... ሰውነቴ በየደቂቃው እየከዳኝ ነው። ብቻ ... እንደምወድሽ እንድታውቂ እፈልጋለሁ፣ ለምንም በላይ ደግሞ... " አለና እንባውን እየዘራ፣ ዓይን ዓይኗን እያየ ተማጸናት "በቻልተኝነቴ እስከዛሬ ውስጥሽን ላደማሁት በሙሉ ከልብሽ ይቅርታ አድርጊልኝ።"

"ተው ለይክ... እንደዚህ የስንብት የሚመስል ነገር አታውራ... እኔ አንተን አጥቼ መኖር በፍፁም አልችልም።" ሜሮን ተነፋረቀች።

"እንደዛ አትበይ፤ አንቺ ቢያንስ ለልጃችን... ለማርቲ ኑሪላት። ደግሞም መርዕድንም ቢሆን እንደልጅሽ አይተሽ እንድትከታተይው አደራ።" ከዚህ በኋላ ለይኩን ብዙም የቀረው የህይወት እንጥፍጣፊ አቅም አልነበረም። እንደሚሞት ታወቀው፤ እርሟን እንድታወጣ ሜሮንን እንዲህ አላት።

*"ሜሪዬ ሰ... ሰውነቴ በድን ሲሆን እየ..ታወቀኝ ነው። ምን ያኽል እንደምትወጂኝ ስለማውቅ አደራ የምልሽ... ለይኩን ሞተ ብለሽ በፍጹም ራስሽን በሀዘን እንዳትጎጂ፤ የምትወጂኝ ከሆነ ለኔ ስትይ ጠንክር በይልኝ። ደግሞም ካንቺና ከልጄ መለየቴ ትልቅ ሀዘን ቢሆንብኝም በመጨረሻዎቹ ደቂቃዎቼም ቢሆን ስላየኂችሁ ልቤ እርፍ ብሎልኛል። ደግ...ደግሞም ብሞትም ወደ ምወዳት እናቴና ወደ ጅብሪል ዓለም እንደምገዝ አትርሺ።"*

"ለይክ እረፍ በቃ!... ዝም በል!... አትሞትም!" ... መሞትና አለመሞት በእሱ ኃይል ሥር ያለ ይመስል ተቆጣችው፤ ለይኩንም ቀበል አድርጎ... "እ.. እሱ አ...አይቀ...ርም ከህ...ይወ..ትት ጋር አ...አብሮ ሞት አለ...ና እንዳታ..." ... ንግግሩን አልጨረሰም። የከርታታው ለይኩን ትንፋሽ ተቋረጠ። ሜሮንን አጥብቆ አቅፎ፣ የልጁን የማርታን እጅ ጭምቅ አድርጎ እንደያዘ... ለዘላለሙ አሸለበ። ለይኩን ተስፋሁን አረፈ። ያልታደለች ሜሮን ቤቱን በእሪታ አደበላለቀችው። ከክፍሉ አንድ ጥግ ቆመው የሚሆነውን በሀዘኔታ ይከታተሉ የነበሩት አባ በላይ ወደ ልጅ ልጃቸው መጥተው አቀፏት። እስራቸው ገብታ ለግማሽ ሰዓት ገደማ ተንሰቀሰቀች።

...|ትንሽ ስትረጋጋ ወደ ጆሮዋ ተጠግተው እንዲህ አሏት፤

"ልጄ ሆይ! አይዞሽ፡ ይሄ ከኛ አቅምና ምርጫ በላይ ነበር። ሞትኮ መቼና እንዴት እንደሚከፈል የማናውቀው የግዴታ እዳችን ነው። ለለይኩን... እኛም አቀድን፣ ለፋንም፤ ፈጣሪም አቀደ፤ የሱም ፍቃድ ፀና፤ ስለሆነም

እኛ ለሱ ፍቃድ እጅ መስጠት ነው ያለብን።" አሏትና የለይኩንን ወደ ጣሪያ የተገለበጠ ዓይን በመዳፈቸው ከደኑት።

{ጠቢባንም ሆኑ ሊቃውንት፣ ነብያትም ሆኑ መናኞች ስለ ፍጥረትም ይሁን ስለ ህይወት ከሚያውቁት የማያውቁት እጅግ እጅግ እጅግ በጣም ይልቃል:: በተለይ ስለነገ ፈጣሪ ከሚገልጽላቸው ቁንጽል እውቀት በስተቀር አብዛኛውን ምስጢር የሚያውቀው እሱ ሠሪው ብቻ ነው::}

⌘ ⌘ ⌘

*በሰባተኛዋ ቀን፡ ሰባተኛው መጋረጃ ተዘረጋ፤*

ሶፎኒያስ ከስድስተኛዋ የብርሃን ሰበዝ እየራቀ በመጣ ቁጥር ብርሃናማዋ ፈለግ እየቀጠነች መጥታ በመጨረሻም ሙሉ ለሙሉ ጠፋች:: እነሆ ሶፎኒያስ ራሱን ድቅድቅ ባለ ጨለማ ውስጥ አገኘ:: ሰባተኛው የክረምት ጉም የሚመስል ጥቁር ጭስ. . .መሬት ለመሬት እየተሳበ መጥቶ ዋጠው፤... ይኼ ● ቃል፣ ድምጽ፣ ◌ ብርሃንና ነገሮችን በሙሉ የሚውጥ ጨለማ ነው:: ከባድ ዝምታ ያረበበበት፡ ባለ እልፍ እፍጋትና አቅም ያለው ህቡዕ እውነታ ነው:: እነሆ ይህ ዓይኖች የማያዩት፣ እውቀቶች የማይፈጽሙት፣ ኃያላን የማይገዳደሩት፣ የብርሃን፣ እውቀትና ኃይል ምንጭ ነው:: ሁሉንም እንዳመጣጡ እንደሚቀበል፣ የ‹ፊዚክስ› ህግጋትን በሙሉ እንደሚያፋልስ የፍቅር ተምሳሌት በህዋ ውስጥ አለ:: እንጦሮጦስ፣ በርባሮስ፣ ‹ብላክ ሆል› የሚባሉ በሮች አሉት፤ እነዚህም የምስጢራዊው ግዝፈቱ፡ ወሰን አልባው ምንምነት ደጃፎች ናቸው:: በዚህ የጨለማ ጉድጓድ ጊዜና ቦታም ይጨፈለቃሉ:: ብርሃንና ድምጽን ጨምሮ ሁሉም እንቅስቃሴዎችና እርግብግቢቶች በሙሉ እየቀነሱና እየዘገዩ ሄደው... ቀጥ፣ ለጥ፣ ጸጥ፣ ረጭ ይላሉ:: ትናንትና ነገ፣ እዚህና እዚያ የሚባሉት አይኖሩም:: ሁሉም ተድበልብለው አንድ የሚሆኑበት አሀዳዊነት ላይ ይከትማሉ:: ይህ ጨለማ ታዲያ የብርሃን አለመኖር ሳይሆን ራሱን የቻለ ኃይል ነው:: ከብርሃን መፈጠር በፊትም የነበረ ጠሊቅ እውነት ነው:: በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ምዕራፍ 8 ላይ እንደተጻፈው *"12፤ ሰሎሞንም:: እግዚአብሔር:: በጨለማው ውስጥ እኖራለሁ ብሎአል፤ 13፤ እኔም ለዘላለም የምትኖርበት ማደሪያ ቤት በእውነት ሠራሁልህ::"* ብሎ እውነታውን አስረግጦልናል::

*{አይገርምም? ታላቁ ጸለምትና ዝምታ ሁሉንም የፍጥርት ብርሃንና ድምጽ አሸንፎ፣ አፍኖ ይገኛል::}*

ድንገት በሶፎኒያስ ዙሪያ ከባድ አውሎ ንፋስ ጨለማውን ዋጀው፤ እነሆ እንደ ራእይ፣ ወህይ፣ ሰመመን ያለ መልእክት ከሶፎኒያስ ምናብ ይፈስ ጀመር:: "አንተ መንገደኛ! እውነትን ፍለጋ ብዙ ተጉዘኻል፣ ብዙ አንብበኻል፣ ብዙዎችንም ጠይቀኻል:: በስተመጨረሻም ራስህን እንድትጠይቅ አቅጣጫ ጠቁመንኻል:: ይህም ከሆነ በኋላ ከራስህ ጋር ተወያይተህ ጥበብ ተገልጦልኻል:: ህይወት አለኝ ከማለት አልፈኽ ራሱ ህይወትን ሆነኻል:: እነሆ አሁን ደግሞ ይህም ጥበብ የመጨረሻው እውነት እንዳልሆነ የምታውቅበት እርከን ላይ አለኽ:: እኛ የምንነግርኽ| አንተም የተረዳኸው በሙሉ ካልተገለጠው ግዙፍ አንጻር ምንም ነው:: ሁላችንም ፍጥረታት የምንደርስበት የእውቀትና የጥበብ ገደብ አለን::

_________{ይህንን ውስንነታችንን በአርምሟዊ ትዕግሥት እንድንለይ ኢዮብ በመጽሐፉ ምዕራፍ ዘጠኝ ከቁጥር ዘጠኝ ጀምሮ እንደሚከተለው አስቀምጦታል... "9፤ ድብ የሚባለውን ኮከብና ኦሪዮን የሚባለውን ኮከብ፥ ሰባቱንም ከዋክብት፥ በደቡብም በኩል ያሉትን የከዋክብት ማደርያዎች ሠርቶአል::

10፤ የማይመረመረውን ታላላቅ ነገር፥ የማይቈጠረውንም ተአምራት ያደርጋል::

11፤ እነሆ፥ ቢመጣብኝ አላየውም፤ ቢያልፍብኝም አላውቀውም:: 12፤ እነሆ፥ ፈጥኖ ቢነጥቅ የሚከለክለው ማን ነው? እርሱንስ:: ምን ታደርጋለህ? የሚለው ማን ነው?" ብሎ ይጠይቅና በተመሳሳይም በምዕራፍ ሠላሳ ስምንት ከቁጥር ሠላሳ አንድ ጀምሮ...

"31፤ በውኑ የሰባቱን ከዋክብት ዘለላ ታስር ዘንድ፥ ወይስ ኦሪዮን የሚባለውን ኮከብ ትፈታ ዘንድ ትችላለህን?

32፤ ወይስ ማዛሮት የሚባሉትን ከዋክብት በጊዜያቸው ታወጣ ዘንድ፥

ወይስ ድብ የሚባለውን ኮከብ ከልጆቹ ጋር ትመራ ዘንድ ትችላለህን?

33፤ የሰማይን ሥርዓት ታውቃለህን? በምድርስ ላይ እንዲሠለጥን ልታደርግ ትችላለህን?

34፤ የውኆች ብዛት ይሸፍንህ ዘንድ፤ ቃልህን ወደ ደመናት ታነሣ ዘንድ ትችላለህን?

፴፭፤ መብረቆች ሄደው። እነሆ፥ እዚህ አለን ይሉህ ዘንድ ልትልካቸው ትችላለህን?

፴፮፤ በውስጠኛው ጥበብን ያኖረ፥ ለልቡስ ልብ ማስተዋልን የሰጠ ማን ነው?" ብሎ ጥያቄውን ያጠናክራል። በተጨማሪም በትንቢተ አሞጽ ምዕራፍ፡ አምስት ላይ እንደሰፈረው፤

"፰፤ ሰባቱን ከዋክብትና አሪዮን የተባለውን ኮከብ የፈጠረውን፥ የሞትን ጥላ ወደ ንጋት የሚለውጠውን፥ ቀኑንም በሌሊት የሚያጨልመውን፥ የባሕሩንም ውኆች ጠርቶ በምድር ፊት ላይ የሚያፈስሳቸውን፥

፱፤ አምባውም እንዲፈርስ በብርቱ ላይ የድንገት ጥፋት የሚያመጣውን ፈልጉ፤ ስሙ እግዚአብሔር ነው።}

እነሆ ሰባተኛው እርከን በፍቅር የተሞላ፣ በህሊና እውነት የሚገለጥ፣ በምህረት ብቻ የሚደረስ የሁለንተናዊነት አምሳለ አምላክ ነው። በእርግጥም የተገለጠው ካልተገለጠው እጅግ በጣም በብዙ ያንሳል። ይህንም ያወቀ ሰው አቢቃ፤ አለቃ የሚባል ጥበብና እውቀት እንዳሌለ ይረዳል። ከከፈታቸው በሮች ይልቅ ያልከፈታቸው፣ በእልፍ፡ አዕላፍ፡ እንደሚበልጡ አስተውሎ ማንኳኳቱን ይቀጥላል። ያንኳኩም ይከፈትለታል። ተከፍቶለት ከገባበት አዳራሽ እጅግ የሚልቅ ሌላ አዳራሽ እንዳለ ያወቀ ግን ጠቢብ ነው። {እነሆ ጠቢብም ያልነውም ጠባብ እውቀቱን ማስተዋል የቻለውን ብቻ ነው።}

አንተ ሰው፤ እንደ ውቅያኖስ ጥልቅ፡ ጨለማ ወለል፡ ስክነትና አንክሮህ ቃላቶችህን እንዲያዩ አድርግ። አሁን አየር ላይ ቁጭ ብለኽ እየተመሰጥክ ያለኸው በቃላት ሳይሆን በዝምታ ጥበብ እንደሆነ አስተውስ። ሁሌም አየር ምገህ አየር እስኪታስወጣ ድረስ ያለውን ጸጥታ፣ አየሩንም ተንፍሰህ ሌላ አየር እስክትስብ ድረስ ያለውን ጸጥታ አስተውለው፤ ጥልቅ እውነትን በየሰከንዱ ይጠቁምኻል።

ዝምታህ ቅርጽ፣ ቀለም፣ ክብደት የለውም። ወርድና ቁመቱ ሊይመተርም። እንዲሁ ሁሉ በዙሪያችን ያለው መጠን ቁስ ከያዘው ቦታ ባዶው ቦታ ወይም ቫክዩም[126] በእጅጉ ይገዝፋል። በአቶሞች መካከል

126 የኳንተም ሜካኒክስና ዳርክ ማተር አጥኚ ሳይንቲስቶች በዩኒቨርስ ውስጥ የሚገኙ፤ የሚታዩ የሚዳሰሱና የሚመዘኑ ነገሮች በሙሉ ከጠቅላላው ሆኖ 5 በመቶ እንደማይሞሉ ይናገራሉ። ይህም 95 በመቶ የሚሆነው ጠፈር በማናውቀው ጥልቅ፤ ጨለማ፤ ዝምተኛ፤ ረቂቅ፤ ሴፈ፤ ኃይል የተሞላ ነው!

እልፍ እና ክፍተት አለ፤ በንጥረ ነገሮች መካከል ሰፊ እና ክፍተት አለ። እናም ምድር ላይ ከተገለጠ፣ ከሚታይ፣ ከሚጨበጠው ያልተገለጠው በእጅጉ ይገዝፋል።

ይህንንም ስታውቅ "እኔ ነኝ!" ካልከው የውሸት መሰፈርቶችህ በላይ ያለውን እውነት ታያለኸ። ከስሜት ሀዋሳት ታልፋለኸ፣ ራስህንም ትክዳለኸ፤ ለሰፊው እውነት እጅ ትሰጣለህ። ልብ በል፣ አንተ በስምህ፣ በንብረትህ፣ በእውቀትህ፣ በማዕረግኸ ከመሰፈር ትልቃለኸ። በዙሪያክ፣ በቤትህ፣ቤተሰብኸ፣ በማህብረሰብኸ፣ በሀገርህም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚከሰቱ ነገሮች በላይ ነህ። አንተኮ ልጄ፤ ከሞትህም በላይ ነህ፤ በወሰን አልባው ኃይል ውስጥ ካደርክ ዘላለማዊ፣ ህያው እርግብግቢት ነህ።

በሰሎሞን ዙፋን ላይ ስለተቀረጸው ክብ ተምሳሌትነት ደግሞ እነግርኸለሁ። ትልቁ እውነትን ተመልከት - በፍጹም ምንምነት፣ መነጣጠል በሌለው ግዙፍ ውህደት ፍጥረትን በሙሉ በአንድ ክብ ይጠቀልላል። እናም ክቡ ውስጥ ሆነህ ክቡን ማየት አትችልም። ሀሊናዊነት ብቻ የክቡን አካልነትህን እንድትረዳ ያደርግኸል። በአንተ የሆነ በሁሉም እንደሆነ፣ በሌላው የሆነም ባንተ እንደሆነ ትረዳለኸ፤ ሁለንተናዊነት ሲሰርጽህ ቅዱስ መንፈስ ተገልጦልኸል ማለት ነው። ይህን የተረዱ ጻድቃን የእኔ ከማለት የእኛ ማለት ይቀናቸዋል። ከሁሉም አንድ ናቸውና ያላቸውን በሙሉ ለምስኪኑ አካላቸው ይለግሳሉ። ሰጠው ግን አይሉም። ሰጠው የሚል መታበይ አንድነትን ካለመረዳት የሚመነጭ ልዩነት ነው። ለየት ያልኩኝ ነኝ ብሎ ማሰብ ያለመብሰል ምልክት ነው። በምድር ምንም የአንተ ካልሆነ ምንስ ማጣት ትፈራለህ? የሰው ልጆች ግን አለማወቅን ሳይሆን ሰይጣንን ይፈራሉ። የሰይጣን ዋና ዋና ጠላቶች ደግሞ ሁለት ናቸው፤ እነርሱም መርጠን የጸናነው ዝምታ እና ሰውን ወደ መልካም የሚጠሩ የፍቅር ቃላት ናቸው።

በድጋሚ አስታውስ፣ ነው ብለን ከደመደምነው በላይ ጥልቅ ሌላ እውነት እንዳለ ስርክ አትርሳ። ጠይቅ፣ መርምር፣ ተፈላሰፍ፣ ጸልይ፣ እንኳኳ... በዚህ ጉዞኸ የበላይ እርከን ስትነቃ እኔ ከሚለው ማንነት፤ የኔ ከሚለው መገለጫ፣ ስም፣ ንብረት፣ እውቀት፣ ማዕረግና መሰል ቃላት በላይ የገዘፈ የነፍስ ባለቤት እንዳለ ትገነዘባለኸ። ትልቁ ገንዘብም መገንዘብ ነው።

ታዲያ ይህንን እውነት ለማፋለስ ምዕራባውያን አላዋቂዎች በጥሞና የምትቀመጠው ግላዊ ኃያል ማንነትህን ለማንቃት ነው ብለው ጥበቡን ሊያፋልሱት ይጣጣራሉ። በዋናነት በጥሞና የምትቀመጠውና ራስህን የምትክደው ግን ከአንተ በላይ ከቁጥር፣ ኃይላትና ገለጻዎች በላቀ፣ ከጠፈር ሰፊ የሆነውን ፈጣሪ በውስጥህ ታገኘው ዘንድ ነው። ቤተ መቅደሴ አንተ ነኽ እንደሚል ቃሉ ዓላማው ዛሬ ራስህን ከእግሩ ሥር ቀብረኽ ነገ በእልፍኙ መጽደቅ ነው። ይህንንም ምሥጢር እወቅ! የማናችንም ተመስጦና ዝም ማለት በዋነኝነት የሚጠቅመው የእኔነትን ትናጋ ባዶ ለማስቀረት ነው። በተመስጦ ውስጥ ያለ ሰው የእብሪተኛ "እኔኮ" ፡ በራስ የመታበይን ግንብ "ኢድና ኢጎ"፣ አፍርሶ ራሱን ይክዳል። እልሁን ዋጥ አድርጎ ዝም ማለት ይችላል። ንዴቱን ገታ አድርጎ ፈገግ ይላል። ትናንሽዬ ፍትጊያዎችን ትቶ በመተንፈስ ብቻ ወደ ጠፈር ይጎናል፤ በየትየለሌ ፍቅር ይጠፈራል። እናም ልጄ የ "እኔኮ" ስሜትህን በትህትና ሰይፍ ቅላው። ወንድ ማለት የራሱን እልህ ያሸነፈ ሰው ነው ብለን እንዳስተማርንክ ራስህን ታግለህ አሸንፍ። ከሰውነትህ፣ ከሐሳብህና ከስሜቶችህ በላይ ግዘፍ፣ ከራስኽ ድንበሮች ለመውጣት ጣር። ልጄ፣ ትግሉ ግን የቀላል እንዳይመስልህ። አታካች ነው። |ይህንን ራሱ ለመረዳት ጥሞና ያሻል። ምልዓት ያስፈልጋል።

"አሁንም ግን ልብ በል፣ አርምሞ በጨለማም በብርሃንም አይወከልም። በባዶነትም በሁለንተናዊነትም አይጠቃለልም። ለዚህም ነው በጉዞኽ መነሻ ላይ ዝምታም፡ ቃላትም አስፈላጊ እንደሆኑ የነገርንኽ። እነሆ ከጥልቅ ጥሞናና ዝምታ የሚወጡ ቃላት ግን ከምትገምተው በላይ ኃያላን ናቸው። ምድርና ሰማይን ኃያሉ አምላክ የፈጠረባቸውን እንደ ሰይፍ የሰሉ ቃላት፤ የዚሁ ልዕለ ኃያል ፈጣሪ ምስጢራዊ ስሞችና የጥበብ መክፈቻ ቁልፎች ይገኙበታል። የእውቀት ቁልፋችንን የሚሰልበው የሰይጣን ከበርቻቻ በሁካታ ውስጥ ነው። ዝምታ፣ መደማመጥና መስማማት ባለበት መኖር አይችልም። ረብሻ ይወዳል፤ ቱማታ ይናፍቀዋል። ግና ክፉ መናፍስትን የሚያዝለፈልፉ አንዳንድ ህቡእ ቃላት አሉ። እነሆ ዛሬ ከእነዚህ መካከል የተወሰኑትን በምናብህ መስክ ላይ እዘራልኻለሁ። በህይወት ዘመንህ በሙሉ ብታጠናቸው፡ እልፍ ትርጓሜና ጥበብን ያዘሉ ስለሆኑ ከልብህ መዝገብ ላይ በወርቃማ ቀለም አስፍራቸው።" — ነፋሻማው የመዕልት ምገድ የተለያዩ ቃላትን ወደ ሶፎኒያስ ልቦና ያሰርጽ ጀመር።

ኦስ፣ ኤል፣ ኤል-ሻዳይ፣ አልፋ፣ አሌፍ፣ አሊፍ፣ ኢላህ፣ ኤሎሄ፣ አላህ፣ ኦላህ፣ ኦል

ኦዳ፣ አዴ፣ አዳም፣ አዳም-ኤል፣ አድባራ፣ አድባር፣ ኤደን፣ ኢደም፣ ኢደናይ፣ ኢደም

ኦራ፣ አውራ፣ አውታር፣ አቫታር፣ አዋ-ራህ፣ አራራት፣ አራራይ

ላሜት፣ ላም፣ ላምባ፣ ላምራ

ሔር፣ ሔር-ሞን፣ ሔር-ሜላ፣ ሔር፣ እግዚአብ-ሔር፣ ሔት፣ ሔዋን

መም፣ መይ፣ ማማ፣ ማይ፣ ማያ፣ ሞያ፣ ሞኣ፣ ሞሐ፣ አርም-ሞ ፡ ጥ-ሞ-ና፣ ማዋና፣ ሞና፣ሞኡናም

ሰብ፣ ሰብእ፣ ሰባት፣ ሱባ፣ ሳብዕ፣ ሳባ፣ ሰብእና

ራህ፣ ራህ-እይ፣ ራህ-ሥር፣ ራሥ፣ ራህ-ዜል፣ ራራ፣ ራማ፣ ራህ-ማ፣ ከ-ራህማ፣ ብ-ራሀማ፣ አል-ራህማ፣ ራሙ-ኤል፣ ራምሳ፣ ራሂም፣ ራያማ፣ ራያ፣ ራወና[127]፣ ኢስ-ራህ-ኤል፣ ፕ-ራያ-ማ፣ ፕሪያንካ፣ ‹ኪሪያ›[128]፣ ክ-ራይ፣

አመን፣ አሙን፣ አሚን፣ አሜን፣ እምነት፣ አሞን[129]

ወልድ፣ ወል፣ ወሌ፣ ወሎ፣ ወልይ፣ ውል፣ ወሀድ፣ዋሂድ፣ ውህድ፣ዋህ፣ ዋው፣ ዋው -ኤል፣ ዋቃ፣ ዋካ፣ ዋኣ፣ ዋዳ፣ ዋርካ፣ ዋል፣ ዋል-ድባ፣ ዋል-ያ፣ ዋ-ኖስ

ቶ ፡ አቶ፣ ከቶ፣ መቶ፣ ጌቶ፣ ቶሎ፣ እቶን፣ ዮቶር፣ ነቶንያል፣ ገባቶን፣ ፒቶን

ታው፣ ታላመስ፣ ታውረስ[130] ፣ ሰውር፣ሶር፣ ሶርሰር፣ ዛር፣ ሶራ[131]፣ ሠራ[132]

የሐ፣ የሃዩ፣ ያ፣ ያህ፣ ያህዌ፣ ያህዋ፣ ያሆ፣ ያሆዴ፣ የሃ፣ እየሃ፣ የግሃ፣ የድ፣ የጽ የዳሄ፣ ህያው፣ ከያህ፣ ሆ-ያህ፣ ሆ-ዴህ፣ ሀሌ-ሉ-ያህ

መላ፣ መልክ፣ መልካም ፡ መልከ-ሃም፣ ካም፣ አ ፡ ካም ፣ ካም-ላክ[133]፣ መለኮት-አምላክ፣ ሃምላክ – ሄምሎክ፣ ሃምራዊ፣ ሃመር፣

---

127 ፍጹም

128 ሜዲቴሽን አይነት አለው፤

129 Man፣ ዉ-ማን; አማን፣ የ-ማን፣ ጀር-ማን እውነተኛ ቤተሰብ፣ የ-መን ፡ ቅድስና በረከት፣ አርማን)

130 የኢትዮጵያ በሬ ምስለ-ከዋከብት

131 ዎፍ

132 ወርቀ ዘቦ፤

133 Kamlakar: Name Kamlakar in the Indian origin, means Brightness, Brilliance

***ገር! ገሬ! ጕሩ! ጕሩህ! ጕሩች! ጕሩቻ! ጕርታ[134] ! ጕራ-ሞድር! ጕራ-ጌ! ጕራ-ፈርዷ! ገርቤ ጕራ-ቻ***

**ፉ: ፏ! ቆፍ - ቋ! ጣህ - ጧ! ሳህ - ሷ! ራህ - ሯ! ዛህ! ዳሌጥ! ...**

*{አብዛኛዎቹ ስሞች ስሙ-አምሳክ ሲሆኑ በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ መቶ አስራ ዘጠኝና በብዙ የቁርዓን ምዕራፎች መክፈቻ ላይም ተጠቅሰዋል።}*

ብዙ ኃያል ቃላት ወደ ምናቡ ከፈሰሱ በኋላ መዝገቡ ተዘጋ። በሰባተኛው ቀን ማብቂያ| ሁሉም ተፈፃፀሞ፣ ሶፎኒያስ ሰባቱን የነፍስ ዋሻዎች አሳብሮ ሲያበቃ ዓይኑን ገለጠ። ከዘላለም ጥሞና የነቃ ያህል ዙሪያ ገባውን ቃኘ። ድሮ ከሚያይበት ፍፁም በተለየ መልኩ ነበር አካባቢውን ያማተረው። **እንዴ የእውቀት ዓይኑ የበራ በሲራዊና የማያውቅ ሰው እኩል ይመለከታሉ ወይ? ነገሮችን ያወቀና ያላወቀ ዓለምን እኩል ሊረዳስ ይቻለዋል?** ከጥልቅ መኝታው በትንሣኤ የነቃው ሶፎኒያስም በአዳዲስ ዓይኖች ዙሪያውን ተመለከተ። ወዲያውም ሰባት ሰዎች ዙሪያውን ከበውት እንደቆሙ ተረዳ። ማንኛውም አንድ ተረኛ መንገደኛ ሰው ከአጠገቡ ቢያልፍ ምናልባትም ሁለቱን ብቻ ነው ማየት የሚችለው። ሰዎቹ በእያንዳንዱ ሽለቆዎች ውስጥ ያገኛቸው የዝምታ፣ የአርምሞ፣ የህይወት መምህራኖቹ ነበሩ። በአንድነት ቆመው ሲያያቸው ግርማ ሞገሣቸው ማረከው። ለየብቻቸው ካያቸው በበለጠ መልኩ በአንድ ላይ ሲያያቸው ደግሞ ስብጥራቸው፣ ስድራቸው፣ ጉራማይሌ ውበታቸው እጁን በአፉ አስጫነው። እንዲሁ ሁሉ የእያንዳንዱ እርከን ጥበብ በነጠላ የሚመዘዝ ሰበዝ ሳይሆን ከሌሎቹ እርከኖች ጋር በውህደት የሚቀሰም ኔክታር ነው። አይነጣጠልም።[135] ከደቂቃዎች በኋላ ከሰባቱ ሽማግሌዎች አንደኛው ከቡድኑ ተነጥለው ወደ ሶፎኒያስ መጡ። ልብ ብሎ ሲያያቸው ያኔ ደብረ-ዘይት መንገድ ላይ ያሳፈራቸው ሽማግሌ እንደሆኑ ማወቅ ቻለ። ከአጠገቡ ሲደርሱ በፈገግታ ተቀበላቸው፣ ሰላምታም አቀረበላቸው። ... "ለዚህ ስኬትኽ እንኳን ደስ አለኽ ለማለት የመጀመሪያው ሰው በመሆኔ ክብር ይሰማኛል።" አሉና ትከሻውን ቸብ ቸብ አደረጉት፤

**"ይሄ ቀላል ስኬት እንዳይመስልህ! እጅግ በጣም ጥቂቶች ብቻ ሊጎናፀፉት የቻሉት ፀጋ ነው። ብዙ ዓለማዊ ትምህርትን፣ የቁስ ሐብትን፣ ሥልጣንና ማዕረግን ያገኙ ሰዎች ራሳቸውን ግን ሳያገኙ**

134 አንደ ወተት ሰው ልጅም ይናጣል! ቅቤው ይወጣል! በጉርታ ጉሩ ይሆናል።

135 Just like the positive & negative feedback mechanisms of endocrine system.

ባዘነው ያልፋሉ:: የኑሮ ትርጉሟን፡ የመፈጠራቸውን ዓላማ ሳያውቁት እንዲሁ ሲዋከቡ ከርመው ይሞታሉ:: ይሄም ብቻ እንዳይመስልኽ፣ የሰው ልጅ ሊገጥመው የሚችለው ትልቁ ቅጣት ሞት ሳይሆን እያሉ አለመኖር ነው:: ብዙ ሰዎች በእውቀትና ጥሞና እልባ የቁም ሞት ውስጥ ጠፍተዋል:: እናም በእልፍ ፈተናና ስቃይ ውስጥ ያሉ የዘመናችን ሰዎች ያንተን እውቀትና እርዳታ ይሻሉ:: እኛም ይሄንን ሁሉ ጥበብ ጭነንብኽ የሰባቱን ሸለቆዎች ጉዞ ያሳየንኽ ለዚህ ትውልድ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ አስተምህሮውን እንድታዳርስ ካለን የነገ ተስፋ ነው:: እንግዲህ የመጣኽበት ጥያቄ ተመልሶልኽ ብቻ ሳይሆን ትልቅ ኃላፊነትም ተቀብለኽ ነው ወደ ሥራኽ የምንሸኝኽ!" አሉትና በአባታዊ ዓይን ተመለከቱት፤ ..."እነሆ የምንሰናበትኽ የመጀመሪያውን የቤት ሥራኽን ሠጥተንኽ ነው::" አሉና በትራቸውን ተመተሙ፤ በሐሳብ መረብ የሰባቱ ሸለቆዎች፣ ሰባቱም መምህራን ሶፎኒያስን ተሰናበቱት:: ወዲያው በዓይን ጥቅሻ ፍጥነት አንስተው ከአንድ የገበሬ ቤት ደጃፍ አደረሱት:: ሶፎኒያስ ከመስፈንጠሩ ነቅቶ፡ ሙሉ ለሙሉ ወደ ራሱ ሲመለስ ከፊት ለፊቱ ካለው ቤት በራፍ ላይ አባ በላይን ቆመው አያቸው:: በእጃቸው ግባ የሚል ምልክት አሳዩት::

⌘ ⌘ ⌘

ሜሮን ከለይኩን ሞትና ቀብር በኋላ ሰው አልሆነችም። በቃ ራሷን ጣለች። ነገር ዓለሙ አስጠላት። ህይወት አንዳችም ትርጉም አልሰጥሽ አለቻት። ዶ/ር ሶፎኒያስ ለአእምሮ ህመሟ ብሎ ያዘዘላትን ኪኒን ሳትውጥ ከራረመች። አባ በላይ ከጎኗ ሆነው የተወሰነ ቢያጽናኗትም ላለፉት ሁለት ሳምንታት እንደ ወጡ ሳይመለሱ ቀርተዋል። ብቻዋን ከማርታ ጋር ቆዝማለች። የማርታ ነገር እየያዛት እንጂ ብዙ ጊዜ ራሷን ከዚህ ስቃይ ለመገላገልም አቅዳ ነበር። በስተመጨረሻም ህመሟ[136] ከልጇ ፍቅር በልጦ ራሷን ከዚህ ስቃይ ለመገላገል፡ ለይኩንንም ለመከተል ወሰነች።

አንድ ቀን የማርታን ት/ቤት መሄድ ጠብቃ ለህመሟ የታዘዙላትን መድኃኒቶችና ሌሎችም ቤቱ ውስጥ ያገኘቻቸውን ኪኒኖች በሙሉ በአንድ ላይ ለመዋጥ ተዘጋጀች። በብርጭቆ ውኃ ቀድታ፡ በመዳፏ

136 የከፍተኛ ድብርት ወይም ድባቴ ህመም በዓለም ላይ ከ300 ሚሊዮን በላይ ሰዎችን እያጠቃ የሚገኝ፣ ኢትዮጵያም ውስጥ ተንሰራፍቶ ያለ የአእምሮ ህመም ነው:: እንደማንኛውም ህመም ዘርፈ ብዙ አካላዊ፣ ሥነ ልቦናዊና ማኅበረሰባዊ መንስኤና መፍትሔ ያለው ይህ በሽታ በተለይም ወጣት ሴቶች ላይ በብዛት ይከሰታል:: ተገቢ ህክምናዎችን ካገኘ የሚድን ሲሆን በቂ ክትትል ግን ይሻል::

ሙሉ እንክብሎችን አፍሳ ወደ አፏ እያስጠጋች ሳለ በሩ ተበረገደ። እነሆ ዶ/ር ሶፎኒያስ አባ በላይን አስከትሎ ገባ። ልታደርግ የነበረውን ሲረዳ በፍጥነት እንክብሎቹን ከእጇ ላይ አስጣላት። በቸልተኝነት ቀና ብላ አየችው። አንድም ባታወራም ሶፎኒያስ ግን ሐሳቦቿን በሙሉ ማንበብ ችሎ ነበር። በምላሹም ለስለስ ያሉ ሰላማዊ ሞገዶችን ላከላት። ሜሮን ሐኪሟ ሶፎኒያስ እንዴት እንደሆነ ባልገባት መንገድ ውስጧን ሲያረጋጋው እየታወቃት ነበር። ለጉድ በፈለገችው ዝምታ ውስጥ ፈውስን ላከላት። ብዙ አዎንታዊ እርግብግቢቶች በአንጎሏ ህዋሳት ላይ እያረፉ ነበር። በረጅሙ ተነፈሰች። ዶ/ር ሶፎኒያስም አብሯት ትንፍስ አለ። ስትታመም አብሯት ታሞ ስትድን አብሯት ሻረ። |ወዲያው ወደ በሩ ዞሮ ቢመለከት ግን አባ በላይን ከቦታቸው አጣቸው።

⌘ ⌘ ⌘

## ከኤረር ስውር ዋሻዎች ሥር፤

*ሰባት የበቁ ነፍሶች ተልዕኳቸውን በማሳካታቸው እየተደሰቱ ወደ አርምሞ ዓለማቸው ተመለሱ፤ በትውልዱ ተስፋ ሳለመቁረጥም ወሰኑ።*

⌘ ⌘ ⌘

## ከሁለት ሣምንት በኋላ...

ዶ/ር ሶፎኒያስና ጓደኛው ዶ/ር ኪሩቤል አዲስ አበባ ከሚገኘው የሶፎኒያስ ቤት ተቀምጠው እየተጨዋወቱ ነው፤

"ታዲያ እንዴት ነበር ጉዞኽ በናትህ?" አለ ዶ/ር ኪሩቤል፤ "ምን አስቸኮለኽ ኪራ? በቅርቡ አንዳችም ሳላስቀር በዝርዝር ላስነብብኽ አይደል፤" አለና ሶፎኒያስ መለሰለት፤

"አው! ለካ መጽሐፍ እየጻፍኩኝ ነው ብለኸኛል... የኔ ነገር እየረሳሁኮ ነው፤ ... ርዕሱን ምን ነበር ያልከኝ?"

**"አርምሞ"**

"አሪፍ ሥራ የሚሆን ይመስለኛል!" አለና ዶ/ር ኪሩቤል በጓደኝነት መንፈስ አበረታው፤... "እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ ይሆናል፤ እናንተም

እንግዲህ በማስተዋወቁ ታግዙኛላችሁ፤" ..."እንዴታ?"...ሁለቱም ሳቅ አሉ፤ "ባይሆን ኪራ አንድ ትልቅ ፕሮጀክት አስቢያለሁ፣ ማዕከላትንም የመክፈት እቅድ አለኝ። አብረን ብንሠራ ደስ ይለኛል።" አለ ሶፎኒያስ፤

"በማንኛውም መንገድ ከጎንኽ ነኝ።"

________*{የሰው ልጅ ማንነቱን አውቆ ራሱን በሁሉም እርከኖቹ ሲያስለጥን፤ በጥሞና ወደ ታላቁ ስብእናው ሲደርስ፡ ከራሱ አልፎ ለህዝብ ይተርፋል:: በልቦናው አልቦ ሁሉን ያቅፋል፣ በነፍሱ ራእይ ትላልቅ ህልሞችን ያቅዳል፣ በተግባራዊ ልፋቱ ይጥራል፣ እውነት በህሊናው ስለበራች አይዘርፍም፣ አይዋሽም:: የህዝብን ላብ ከመካድና ቅስሙን ከመስበር ይታቀባል:: ይልቁንም ያደግኩበትን፣ የምኖርበትን ማኅበረሰብ እንዴት ላግዘው እችላለሁ? ምንስ ላበርክት? ይሆናል ህልሙ:: ታላቁ ማህተመ ጋንዲ እንዳሉት "ራስን ለማግኘት ምርጡ መንገድ ሌሎችን በማገዝ ውስጥ ራስን ማጣት ነው::"}*

⌘ ⌘ ⌘

ዶ/ር ሶፎኒያስ የወጠነው ማዕከል ከሁለት ዓመታት ልፋት በኋላ ነበር እውን የሆነው። **ተቋሙ የአእምሮ ማበልጸጊያ፣ የስብእና ማጎልበቻ፣ የተመስጦና ዮጋ፣ የእውቀትና ፍልስፍና፣ አቅም የሌላቸው የአእምሮ ታማሚዎችን የማከሚያ፣ የሱስና መሰል ልምዶች ማገገሚያ ወዘተ ያለው በአይነቱ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ማዕከል ነበር።** ማዕከሉ ከተከፈተ ጀምሮ ተጠቃሚ ከነበሩት ሰዎች አንዷ ሜሮን ነበረች። መድኃኒቷን በሥነ-ሥርዓት መዋጥ፣ በሜዲቴሽን በየቀኑ መመሰጥ፣ በአንዳንድ ሥራዎችም መሳተፍ ከጀመረች በኋላ ጤናዋ በእጅጉ ተስተካክሏል።

ከእለታት አንድ ቀን እንዲሁ በማዕከሉ ተቀምጣ ሳለ አንዲት በችግር ጉስቁልቁል ያለች ሴት ወንድ ልጇን አቅፋ ወደ ማዕከሉ መጣች። ብዙ የተቸገሩና በተለይ በመጠጥ ሱስ የተጎዱ ሰዎችን ያስጠጋል የሚለውን ዜና ሰምታ ነበር የመጣችው። ዘበኛው ዋናውን በር ሲከፍቱላት መሰስ ብላ ወደ ውስጥ ዘለቀች፤ ሜሮን የታረዘችውን ሴቲት በስተዋለቻት ቁጥር እርግጠኛ እየሆነች መጣች፤..."ኤ...ልሳ" አለች በለሆሳስ፤ ያንን ሁሉ ዋጋ ያስከፈለቻትን ሴት ስታያት ከንዴት ይልቅ የሀዘኔታ ስሜት ወረራት። ዶ/ር ሶፎኒያስ ሌሎችንም ራስሽንም ካለ ገደብ ይቅር በይ ብሎ በተደጋጋሚ የመከራት ታወሳት። በጥሞና ውስጥ ሆና ባሳለፈቻቸው ጊዚያትም ይቅር ባይነትና ሁለንተናዊነትን ተክናለች። ምንም ሳትናገር ከተቀመጠችበት ተስፈንጥራ ተነሳች፤ ተንደርድራ ሄደችና ኤልሳ ላይ

ተጠመጠመችበት። ከሜሮን በላይ ጸጸት እየረመረማት ኤልሳ በእንባ ተጥለቀለቀች። ...ወንድምና እህት የሆኑት፤ የለይኩን ልጆች መርዕድና ማርታም ለመጀመሪያ ጊዜ ተገናኙ፤

⌘ ⌘ ⌘

ይህ ከሆነ ከሁለት ቀናት በኋላ የዶ/ር ሶፎኒያስ ቢሮ ተንኳኳ።

"ክፍት ነው ይግቡ፤" አለ ሶፎኒያስ፡ ላፕ ቶፑ ላይ እንዳቀረቀረ፤ ሜሮን በሩን ከፍታ ገባች፤ በደረቷ አንድ ደብተር ቢጤ አቅፋ ይዛለች።

"አው! ሜሮን እንዴት ነሽ?" አለና ትኩረቱን ወደሷ አዞረ፤

"አሁን፤ ደህና ነኝ ዶክተር ይመስገነው። ይህ ቦታ ለውስጤ ትልቅ ሰላምን እያገኘሁበት ነው።"

"መልካም ነው። እሺ... ዛሬ ምን ልርዳሽ?"

"ዛሬ እንኳን ላደረግክልኝ ሁሉ ነገር ላመሰግንክና አንድ ነገር ልሰጥህ ነው የመጣሁት፤" አለች ሜሮን፣

"አመሰግናለሁ ሜሮን፤ ግን ሥራዬ የሚያስገድደኝን ነው ያደረግኩት። አንቺ ደህና ሆነሽ ከማየት በላይ የሚያስደስተኝ ነገር ደግሞ የለም። ለኔ ምንም ለመስጠት እንድትቸገሪ አልፈልግም። የሙያ ሥነ-ምግባራችንም ከታካሚ ሥጦታ እንድንቀበል አይፈቅድልንም።"

"አታስብ ሥጦታው ሌላ ነገር አይደለም።" ሳቅ አለች፡ እሱም ሀሳቧን አንብቦ ተረዳት፤ ቀጥላም በደረቷ ጥብቅ አድርጋ ይዛው የነበረውን ማስታወሻ ደብተር ከጠረጴዛው ላይ አኖረች።

"ባለፈው፤ ነርሶቹ ስለ ሄድክበት ጉዞ አንድ መጽሐፍ እየጻፍክ እንደሆነ ሲያወሩ ሰማሁ። እናም ይመጥናሉ ብለኽ ካሰብክ እነዚህን የግል ማስታወሻዎቼን ብታካትታቸው ብዬ አስቤ ነው ያመጣውልኽ። ... እነዚህ ማለት... ያሳለፍኳቸውን የህይወቴን ስንክሳሮች ያሰፈርኩባቸው ጽሑፎች ናቸው። አንተ ጋር ለህክምና ከመምጣቴ በፊት የነበሩኝ የሀዘን፣ የደስታ፣ የማጣትና የማግኘት ዋልታዎቼን ታገኝባቿለኽ። በተለይ የኔና የለይኩንን የፍቅር ታሪክ ተጨንቄ በጻፍኳቸው ማስታወሺያዎቼ ውስጥ ተጽፈው ታገኛለህ።" አለችና ከክፍሉ ወጣች።

⌘ ⌘ ⌘

## ከአስር ዓመታት በኋላ፤

### አርምሞ የሥነ-አእምሮ ማዕከል፤

....በዚህ ማዕከል ዶ/ር ሶፎኒያስ ብዙዎችን ወደ ራሳቸው እንዲሄዱ ረድቷል። ይህ በርካታ ዜጎችን ወደ ተሻለ ህይወት፣ ወደ ንቁ ማንነት፣ ወደ ሰከነ ልቦና፣ ወደ ጤነኛና የበለጸገ አእምሮ፣ የተገራ አንደበት፣ በሥነ-ምግባር የታነጸ ትውልድ ያፈራ ቅጥር ግቢ ነው።

|የቄጤማው ክርክም በሚንዘላፈልበት፡ ዙሪያ ገባው በአበቦች ባጌጠ፡ ሰፊ ቅጥር ግቢ ውስጥ ዛሬም ብዙ ወጣቶች በጥሞናና አመክሮ ተቀምጠዋል። ዙሪያቸው በከበሩ ድንጋያት ተውቧል፤ ጆሯቸው ለስለስ ባሉ የባንቡ ዜማዎች[137]፣ አፍንጫቸው በሚያውዱ እጣኖች እየታጠነ ዓይኖቻቸውን ጨፍነው ይመሰጣሉ። ከእነዚህ ወጣቶች አንዱ መርዕድ ነበር። ወደ ውስጥና ወደ ውጭ እየተነፈሰ በሌላ ዓለም ውስጥ ዘፍቋል። ከልጅነቱ ጀምሮ በአርምሞ ጥበቦች ኮትኩቶ ያሳደገው ዶ/ር ሶፎኒያስ ባስተማረው መሰረት ከፍ ያሉ እርከንና ‹ቻክራዎች› ላይ መድረስ ችሏል። አንደበቱ ባይናገርም በ‹ቴሌፓቲ› ከሰዎች ጋር፣ በተለይም በጥሞና ከሚገኙ ሰዎች ጋር በቀላሉ መግባባት ችሏል። ታዲያ ዛሬ ከየት እንደመጣ ያላወቀው መልዕክት ከምናቡ ነገሠ። በተመሳሳይ ምህዋር ላይ እየተርገበገበች ያለች አንዲት ነፍስ ወደሱ ደረሰች። ሁለት ፊደላትም ጎልተው ወጡ... "ቤ...ራ"

|በአርምሞ ዓለም ብቻ የተጸነሰው የመርዕድና ቤራ ፍቅር የእሱን ከወላጆቹ ያጣውን ፍቅር፣ የእሷንም ራሺያ ካሉ ከቤተሰቦቿ በመራቋ የተፈጠሩ ጉድለቶችን የሚሞላ አብሮነትን ፈጥሯል። ሶፎኒያስ እድሜው እየገፋ ሲሄድ ማዕከሉን በዋናነት በእነሱ አስተዳዳሪነት ሥር እንዲሆን አድርጓል። ይህንም የወሰነው በሌላ በምንም ሳይሆን በደረሱበት ከፍተኛ የአርምሞ እርከን መሠረት ነው። ሁለቱ እነሆ ዛሬም በኮይሻ ምድረ ገነት ተሰይመው ካለ ቃላት ይጨዋወቱ ይዘዋል።

137 እያንዳንዱ የሙዚቃ ‹ቄሽ› በአእምሯችን ሴሎች ላይ የተለያየ ተጽእኖ ያሳድራሉ። የአእምሮን ሀዋሳት የሚያረጋጉ፣ ትኩረት የሚጨምሩ፣ የሚያነቁ ወዘተ የድምጽ ‹ቄሾች› አሁን በህክምው ዘርፍ ሰፊ ጥናት እየተደረገባቸው ይገኛል።

››››መርዕድ ለቬራ ታሪኩን ባጫወታት ምሽት ላይ ከጎጆብ ወንዝ ተንሳፎ ከኮይሻ አረንጓዴ፣ ለንሰለታማ ተራሮች ማዶ ተስፈነጠረ፤ ደንቢ[138] ዛፍ ሥር ተቀመጠ። ትናንትን፣ ዛሬንና ነገን እያሰበ በተመስጦ ዓለም ጭልጥ ብሎ ጠፋ።

* * *

138 መጀመሪያ አፀዋት ሆኖ በቅሎ ከዚያ በላዩ ላይ አቅፎት የሚበቅል ዛፍ ሲሆን ኮይሻ አካባቢ ይገኛል፤

# ምዕራፍ አስራ ሁለት

## መርዕድ

---∞---

*"1፤ ሰባተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ እኵል ሰዓት የሚያህል ዝምታ በሰማይ ሆነ።*

*2፤ በእግዚአብሔርም ፊት የሚቆሙትን ሰባቱን መላእክት አየሁ ሰባትም መለከት ተሰጣቸው።"*[139]

⌘

እነሆ ከዚህ ያመረ ስፍራ ሆኜ ወደ ጥሞና ዓለም ነጎድኩኝ። ከኔዋ ሴት ቬራ ርቄ በውጥን ውስጥ ወደ ራሴ የትውስታ ማህደር ተጓዝኩኝ። ከእድሜዬ ማለዳ ጀምሮ ጥያቄዎች ነበሩኝ። ግን ለምን እናቴ ጠላችኝ? ለምንስ በኔ ላይ ፈርዳ በሐሰት መሰከረች? በእናቴ እዳ ለምንድነው የምቀጣው ብዬ ስባዝን ከረምኩኝ። የኋላ ኋላም ድህነት ክፉ መሆኑን ተረዳሁ። ድሃ ለመኖር ሲል ክብሩና ስሙን አውልቆ ሊጥል ይችላል። በተለይ አግኝቶ ማጣት ደስታን ያመሻል። እናቴ ላይም አልፈርድ ዘንድ ራሴን ገሰጽኩኝ። አብሬ ያልኖርኩትና ፈተናውን ያልተጋራሁት ሰው ላይ እፈርድ ዘንድ እኔ ማን ነኝ?ዛሬ በሁለት እግሬ ስቆም ለኔ ከዳዴ ጀምሮ ቀና ለማለቴ ጎንበስ ያሉ ሰዎች መኖራቸውን አልረሳሁም።

በእድሜዬ ስጎለምስም ከልቤም ሌላ ህመም ተተከለ። እንደበቴ አለመከፈቱ አስጨነቀኝ። ለምን መናገር ተሳነኝ ብዬ ብዙ አማረርኩ። ሽክላዬን ሠሪዬ ግን ደግ ነውና ሶፎኒያስን ጣለልኝ። የዝምታና አርምሞ

139 (የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 8)

ኒሻን አጠለቀልኝ። ያላየሁትን አዲስ ዓለም አሳየኝ።[140] ፈጣሪዬንም እንዳውቀው መራኝ። ፈጣሪ ከስሜት ህዋሳት ይበልጥ ዘንድ አስተዋለኹኝ። ፈጣሪዬንም አብዝቼ ፈለኩት፤ እነሆ ቤተ-መቅደሱን ከውስጤ አገኘሁት። ከውስጥ በፍቅር ሞላኝ፣ ከውጪም በብርቱ ክንፉ ከለለኝ። እነሆ ውድዬን አየሁት። በእሱም ደስ አለኝ። ትናንትን እያነሱ ከመርገም ዛሬን አበጅቶ ለነገ ማሳለፈ የተሻለ ዋጋ እንዳለው ተረዳሁ። ዝምታዬንም ወደድኹት።

ጥሩ ህልም በዝምታ ይታያል፣ መጥፎ ቅዠት ግን ያስጨኸል፣ ያስለፈልፋል። እንዲሁ ሁሉ የቁም ቅዠቴን ትቼ ድክመት፣ ጉድለቶቼን መካድ አቆምኩኝ። ራሴን ከነእውነታዬ ተቀበልኹኝ፣ ከሐቅ መታገል ተውኩኝ፣ ህልም ኖረኝ።

እርግጥ ራሴን ማወቅ ስጀምር ፈርቼ ነበር። በሁላችንም ውስጥ የተቀበሩ ብዙ ጉዶች አሉን። የማንገልጥ፣ የማንጋፈጣቸው አስፈሪ ማንነቶች አሉን። ይሄን የብቸኝነት ጸጥ ያለ ጉዞ መጓዝ የሚችሉም ጥቂቶች ናቸው።

ከራሳቸው ጋር በቆራጥነት ለመነጋገርና ለመተያየብ የሚደፍሩ አማኞች ናቸው። ራሳቸውን ማሸነፍ የሚችሉ ደግሞ ብጹዓን ናቸው። ከራስ የሐሳብና የባህሪ ባርነት መውጣት ትልቅ ስኬት ነው። ይህንን ሲያስረግጡ ራስን ከመግዛት ሀገርን መግዛት እንደሚቀል ነግረውናል።

ግን መሞከር አላቆምኩም። ደጋግሜ ሐሳቦቼን ጠርጠርኳቸው፣ ባህሪዎቼን ፈተሽኳቸው፣ አስተሳሰብና አመለካከቴን አጣራሁት፣ አበጠርኹት፣ አብጠርጥሬም ሳበቃ እነሆ ከህሊናዬ ሸንጎ ፊት አንጓለልኹት። የመፈጠሬን ዓላማ፣ የመተንፈሴን ምሥጢር፣ የሩሄንም አመክንዮ ቀይሼ ተጓዝኩኝ። ብዙም አጠናሁ፤ ብዙም መረመርኹኝ። ብዙ ማንበብ በራሱ ብቻውን እንዳያነቃ፤ የሚያነቡትን መምረጥ፣ በጥልቀት አንብቦ ተረድቶ ከህይወት ጋር ማሰናሰል መቻል ግን ያነቃ ዘንድ አስተዋልኹኝ።

እነሆ ከሰው መለየትንም ወደድኹኝ፣ ጡት እንደተወ ህጻን እኔም በራሴ መቆምን ተለማመድኹ። እንደ ዐበይት ኃጢያቶቹ ሁሉ ንዑሳን ኃጢያቶችንም ራቅሁኝ። የማየው፣ የምሰማው፣ የማነበውና የምበላው ነገር ሁሉ በጥንቃቄ መረጥኩኝ። ክፉ ያስገባ ክፉ ያስወጣል፣ መልካም

140 መስማትና ማየት የተሳናቸው ሰዎች እንኳ ይሄንን እጦት የማካካስ ትልቅ ለውጥ ኪያሂዳ፤

ያስገባም መልካም ይተፋል። ሁሉንም አይቼ የሚበጀኝን ግን አጸናሁ። ሰዎችም መጥተው ሲያፌዙብኝ በጸጥታ ታዘብኳቸው። አንዳች ግን አልመለስኩላቸውም፤ አልተበሳጨሁም።

"ወእምኩሉሰ አርምሞ ይኄይስ ወይሤኒ" ብዬ ከሁሉ ይልቅ ዝም ማለቴን መረጥኩ። ዝምታ የደስታ መባቻ ነው። እነሆ ዝም ያለ ሁሉ ግን ጠቢብ አይደለም። ጠቢብ ሁሉ ግን መለያው ዝምታ ነው። አለማወቃችን ገደብ የለውም፣ እውቀታችን ግን በእጅጉ ውስን ነው።

እነሆ ይህ የኔ ትውልድ በስንፍና ተጠምቆ አየሁ። እውቀትን በማጣቱም ሲባዝን ታዘብኹኝ። ምናምንቴ ከፍ ከፍ ሲል፣ ብልጭልጭ ሲመለክ አየሁ። ተራ ምላስ እልፎችን ስትነዳ ተመልክቼ አዘንኩኝ። ወሬ ሲሸጥ፣ እውነትን ከሐሰት፣ አሉባልታን ከዜና የሚለየው መስመር ቀጥኖ ጠፋ፤ አብዛኛዎቹ ቃላቶቻቸውን አይቆጣጠሩም። ሲናገሩም ከአንደበታቸው ጥሩ ነገር አይወጣም። ዳዊት "አፋቸው መርዝ ነው[141]-" እንዳለው ጥላቻ፣ ሽኩቻ፣ ፋክክር፣ ክርክር፣ ጭቅጭቅ፣ ትንቅንቅ፣ ታይታና ውሸት፣ ማስመሰልና መታበይ ለጉድ ነግሠው አየሁ። ምድር ላይ ያለ ሰው ሁሉ የማያውቀውን ነገር ሲፈራ ይኖራል። ለማወቅ ግን ከመኝታው አይነቃም ነበር።

እንዲሁ ተወልዶ የሚሞት አልፎ ሂያጅ ምድርን አጥለቀለቃት። በቃሉ ታማኝ ነኝ ባይ ብዙ ነው፣ ታማኝነትን የሚኖረው ግን ጥቂቱ ነው። |ትችት አቅራቢ ብዙ ነው፣ የመፍትሔ አካል የሚሆን ግን ጥቂቱ ነው። | እቅድ የሚያወጣ ብዙ ነው፣ ተግባር ላይ የሚያውል ግን ጥቂት ነው።

ቆፍ! እንዲሁ ሁሉ የብዙሃኑ አማኝነትን የሚሻ ሰው በኩራት ይፈተን ዘንድ፣ ብዙሃኑ እውቀት የሚሻ ሰው በብር ይፈተን ዘንድ፣ ብዙሃኑ ብርና እውቀትን አግኝቶ ጥበብን የሚያሳድድ ደግሞ በፍትወት ይፈተን ዘንድ እንዳለው አወቅሁ።

ቶር! የሰው ልጅ የነፃ ምርጫ ባለቤት ነው፤ ካሻው ወደ አውሬነት ደረጃም የመውረድ፣ ሰውም የመሆን፤ ታላቅ መንፈስም የመሸከም በጎ ፍቃድ አለው። አብዛኛው በምድር ገጽ ላይ የሚራመድ የሰው ልጅ ግን ውስጣዊው ማንነቱ ገና የሰውነት ደረጃ ላይ እንዳልደረሰ ተረዳሁ። እነሆ ውስጣችን ብዙ ሰው እርከን ላይ ባልደረሱ እኛነቶች ተጠርቋል። ብዙሃኑ ሰው ተብዬ በደመ-ነፍስ ከጭጋግ ውስጥ የሚባትል ነው።

---

141 መዝ፤ ምዕራፍ 13

ራሱን ቁጭ ብሎ ተመልክቶ ለራሱ ዋጋ ያልሰጠ ሰው ደግሞ ለሌሎችም ዋጋ አይሰጥም። ራሱን ያላዳመጠ ባልንጀራውንም ሆነ ባላንጣዬ ነው ያለውን ሐሳብ ከልቡ አያዳምጥም።

በዚህ ላይ ሳለሁ ግን ሌላ ከባድ መከራ ተጫነብኝ፤ ውድ ሀገሬ በእርስ በርስ ጦርነት ስትደማ በእድሜዬ ማለዳ አየሁ። ሰው ሰውነቱን ረስቶ ሰውን ሲገድል፣ ራሱ ሰውም ሲሞት ታዘብኹኝ። የማይታፈስ ደም በየጥጋ ጥጉ ተዘራ፣ እንዲያው እንደ ዋዛ ክቡር የሰው ልጅ ወዳድቆ ሲቀር፤ ልጆቿ በጦርነት ሲጫረሱ እናት መሐል ላይ ሆና በምሬት ስትጮኽ አይቼ ተጠጋኋት።

እነሆም ያየሁባት ስቃይ መሪር ነበር። አጥንቶቿ እስኪላቀቁ ድረስ አምጣ የወለደች ቀን እንኳን እንዲህ አላመማትም። "ውስጣቸው በተረበሸ ጥቂት ትዕቢተኞች ህዝቤ ነውኮ የሚረበሸው፤ የገዛ ልጆቼኮ ናቸው የተዋደቁት፣ የተራቡ፣ የታረዙት!" እያለች ሙሾ አወረደች። ራሷን ማቅ አልብሳ አምርራ አዘነች። የገደለው ባልሽ የሞተው ወንድምሽ እንዲሉ፣ የገደለው ልጅሽ የሞተውም ልጅሽ ሆኖባት ሀዘኗ ከቤቷ ሳይወጣ፣ አንጀቷን እጥፍ አደረገች።

እኔም አብሬያት ተከዝኩኝ። ወንድም እህቶቼን ፍቅር፣ ጥበብና ጥሞና ማጣት ሲያፋጃቸው፣ እሳት ሲበላቸው በቁጭት ተሞልቼ ተመለከትኹኝ። አንዳንዴ እሷን ለማቆምም ሆነ እሷን ለማፍረስ የሚታገሉትን ልጆቿን እንበ እንዳቆረዘዘች በትዝብት ስትመለከት አየኋት። እናት ናትና ሊያፈርሷት በሚራወጡት ልጆቿ እንኳን አለመጨከኗ ገረመኝ። እነርሱ የሚታገሉላት ጠባብ ክልል ካለ እሷ ሰፊ ህልውና ምንምነት፣ ትንሽነት እንደሆነ አለማወቃቸው ቢያስከፋትም በፍጹም ጨክናባቸው አታውቅም። እያየቻቸው ታዝናለች፣ እየወጓት ታቅፋቸዋለች፤ እየናቋት ትወዳቸዋለች፣ እየነከሷት ታጎርሳቸዋለች። ኢትዮጵያ የፍቅር እናት ነችና።

ደግሞም ልጆቿ አንድ ቀን በዝምታ እንደሚግባቡ ተስፋ እንደምታደርግ እያለቀሰች ነገረችኝ። ከጫጫታ፣ ረብሻ፣ ንትርክና ጸብ ወጥተው በሰፊው ጥበብ/ በእውነተኛ የጥሞና ንቃተ-ህሊና የሚበስሉበትን ጊዜ በጉጉት እንደምትጠብቅ አወጋች። የዝምታ ተቃራኒ ዋልታ ጦርነት እንደሆነ አሳወቀችኝ። ጦርነት የድምጾች ድግስ ነው። የጣዕረ ሞቶች ቃትቻ። የጥይትና ፈንጂዎች አደባባይ ፍንዳታ፣ የአረርና ባሩዶች ነፍስ በላ ሽታ፤ ካለፈም በኋላ የሚጮህ መጥፎ ጠባሳ አለው።

እኔም ምክር የማይሰማውን፣ ልቡ የደነደነውን የዚያና የዚህን ትውልድ ክፍል ወቀስኩኝ። እኛ ድኩማኖቹ ግን እስከመቼ እርስ በርሳችን እንራኮታለን? የስሜትና እልህ ግልቢያው አይበቃንም ወይ? ስል ጠየኩኝ፤... ራሳቸውን ያልገሩ ጠባብ ቡድኖች እስከመች እኛን እንዲነዱ እንፈቅዳለን? መቼ ነው ወደ ውጭ ሳይሆን ወደ ውስጣችን መኖር የምንጀምረው? ...ብናስተውል በማኒፌስቶ፣ በፖለቲካ ፉክክርና ጦርነት ጊዜያዊ እንጂ ዘላቂ ሰላም ሊመጣ አይችልም። እውነተኛ ሰላም ከግለሰቦች ውስጥዊ ስክነት እንጂ ከቡድኖች ሽኩቻ አይወለድም። ዋናው ውጊያና ፍልሚያም የሚደረገው ከራስ ጋር ነው።

አንዳንዴ በሃሳብ መከራከር ካላስማማን ዝምታ ያስማማናል። በዝምታዎች መካከል ጸብና ፉክክር ትናንሽ ሞቶችን ይሞታል። እንዲሁ ሁሉ ትክክለኛው ሰላም ከጥሞና ይወለዳል። ብዙ ሰው አርምሞን ከተለማመደ፤ ህዝብ በአንድ ልብ ተሰባስቦም ከተመሰጠ የዘላቂ ሰላም መንገድ ይዘረጋል። ከአንድ ሁለት፣ ከሁለት ሦስት ይሻላልና የብዙሃኑ የነቃ ማንነት ሀገርን ያነቃል።

ዋው! ዜጎች እግረ-ህሊናቸው ሲዳብር የሀገር ሰላምና ብልጽግና ይረጋገጣል።በዚህች ድንቅ ምድር የሰላም በረከት ይታፈሳል። ከሸገር እስከ ድንበር፣ ከራያ እስከ እዣ፣ ከኮይሻ እስከ መናገሻ፣ ከወል-ቂጤ እስከ ወል-መራ፣ ከወል-ቃይት እስከ ወል-አይታ፣ ከወሎ እስከ ወል-ዋሎ፣ ከጎንደር እስከ ሐረር፣ ከሰ-መራ እስከ አስ-መራ፣ ከአክሱም እስከ ላሊበላ፣ ከጀጉል እሰከ ሾንኬ፣ ከሞያሌ እሰከ ባሌ ሰላም፣ እውቀትና ጥሞና ለጉድ ይዝነብ። ሆዳችን ብቻ ሳይሆን አንጎላችንም ይጥገብ ስል በአርምሞ ጸለይኩኝ። በጥሞና ያለን ሰዎች በሁካታ ካሉት ወገኖቻችን በእጅጉ ስለምናንስ ሰላምን ማሳካት ጊዜ እንደሚፈልግ ግን አልተጠራጠርኩም።

ቢሆንም መሣሪያ አልባ የፍቅር ትግሉም አይቆምም። ገና ብዙ ዝም ያለ ወገን ይመጣል፣ ገና በዝምታና እውቀት የሚነቃ የጥሞና ትውልድ ይፈጠራል። አረፍ አይቸኩልም ብሎ በትዕግስት ጥበብን የሚቀስም። በ‹ሃይኪንግ›ና መንፈሳዊ ጉዞ ተራሮችን እየወጣ የነፍሱን ትንሣኤ የሚያውጅ ትውልድ ይመጣል።

የዘመኔ ዜመኛ ዮሐናም እንዲህ ብሎ አዜመ...

"ያበረታል ያላጠፋ ችግር - መንፈስም ሥጋ

ዝምታን ስማት - ጥበብን - ፈልጋት ንቃ!" - ሰምተንም ነቃን፤

ታው! ቀጥሎ ደግሞ ሌላ መልዕክት ወደኔ መጣልኝ። አለኝም፤ ይህ ትውልድ አብዝቶ ዝም ቢል መልካም ነው። ጥሞናው ቃላቶቹን ቢቀድሙም መልካም ነው። እርባና ቢሡ ወሬ፣ አሉባልታ፣ ሐሜት ወዘተ መቀነስ አለበት፤ ድምጸች ይቀንስ፣ ስልኮቹ ሲጠሩ ሌሎችን እንዳይረብሹ ያድርግ፣ የመጥሪያ ደውሎቹን በውስጡ ይሙላ፣ ጥሩንባዎቹን አያንባርቅ፣ የሚከፍታቸውን ማናቸውም ነገሮች በልኩ ያድርግ።

የበይነ መረብ ተጋላጭነቱ አንጎሉን በሚረብሽና በሚቆጣጠር ደረጃ አይሁን። የዘመኑ ቴሌቭዥን፣ የሳተላይት ፊልሞችና ውድድሮች፣ የማኅብረሰባዊ ድህረ ገጾች ምስሎች፣ አጫጭርና ረጅም ቪዲዮዎች እንዲሁም ጌሞች፣ መቅርጸ-አንጎል ድግምታቸው ቁራኛ እንዳይሆን ይጠንቀቅ።

ያህ! በእርግጥ ጨዋታኮ አይጠላም። ከወዳጅ ጋር ሰብሰብ ብሎ መልካም መልካሙን መወያየት፣ መቀላለድና መሰሳቅ ጭንቀትን ያቀላል። የሥራና የኑሮን ውጥረት ያረግባል። በዚያው ልክ ግን ለዝምታም ቦታ ሊሰጠው ይገባል። አንዳንዴ በዝምታ ውስጥ መግባባት ያሻል። የአፍ ወለምታ በቅቤ አይታሽም ይባላል፤ ዝምታ ግን ወለምታ የለውም። በራስ መንገድ፣ በራስ እይታ፣ ከመንጋው ተገንጥሎ መጓዝ ጥበብ ነው። "በመንፈሱ የሰለጠነ ሰው ሃገር ከሚገዛ ሰው ይሻላል።" ምሳሌ [16-52] ተብሎ እንደተጻፈው መንፈሳዊ ስልጣኔያችንን ከቋንቋና ቁሥ ስልጣኔያችን በላይ ቦታ ልንሰጠው ይገባል። የንቢቱን ተወረድ፣ የሠራተኛ ንቦቹንም የቀፎ ንድፍ፣ የማር ወለላ የሚፈስበትን ሰፈፍ ጥበብ ንብ አናቢዎች ያስተውሉ። በእርሻ፣ አበባ በመንከባብ፣ ፀጉር በመቆረጥ፣ ልብስ በመስፋት፣ ወክ በማድረግ፣ ስዕል በመሳል ወዘተ ያሉንን ጥሞናዎች ልብ እንበል፤

እነሆ ለዚያኛው አመጸኛ የዘመኑ ፈረያንም አንተ ተሳስተኽ ሌሎችንም አታሳስት በሉት። ታይታን ፈላጊ ግብዙንም ተገሰጽ በሉት፣ በሥጋዊ መንገድ ሚሊዮኖች ከሚከተሉህ ወደ መንፈሳዊው መንገድ አንድን ሰው መምራት ይሻልሃልና። ያ የምትመራው አንድ ሰው ደግሞ ቅድሚያ ራስህ ቢሆን ምንኛ ያማረ እንደሆነ አሳውቁት።

ላሜት! የሰው ልጅ ከሚያውቀው የማያውቀው ነገር እንደሚበልጥ እስከሚያምን ድረስ ወደ ቀጥተኛው መንገድ አይመጣም። ብዙ ነገሮች እንደምንገምታቸው አይደሉም። እናውቃለን ብለን የምናስባቸው

በርካታ ነገሮች ላይ ስህተት ነን። ለምሳሌ የግመል ኩላሊት እንጂ ሻኛ ውስጥ ውኃ አይጠራቀምም። የኮብራ ጭራ የሚርደው ለማስፈራራት ሳይሆን ራሱ ስለሚፈራ ነው። ኦክቱፐስ ስምንት እግር የለውም፣ ሁለት እግርና ስድስት እጅ እንጂ። ድመት ወተትን የሚሰብር ‹ኤንዛይም› በሰውነቷ የለም - የምንሰጣት ወተት አይስማማትም። በዓለም ላይ በዓመት ብዙ ሰው የሚገድለው እንስሳ ጉማሬ ነው። ይሄው ጉማሬም በአፉ ይጸዳዳል። በአእምሮው ከስቶ ሥጋና ስሜቱን ያደለበ ሰውም አፉ ሰውን የሚያጋድል ክፋት ይተፋል፣ ይረግማል፣ይሰድባል። እናም ስለኛም ይሁን ስለ ዓለም ከምናውቀው የማናውቀው በእጅጉ ይልቃልና ንግግራችን ቁጥብ ይሁን።

ደግሞ ከድምጹ ይህም ተነገረኝ፤ ቃላቶች ማለት አንተ ማለት አይደለህም አለኝ። ማብራሪያም ዋናውን ነገር ሙሉ በሙሉ አይወክልም። በልቡ እውነታዊ ሰላም መኖር ያቃተው በከንፈሩ ላይ ይኖራል። ንግግርኮ ጊዚያዊ አቅጣጫ ማስቀየሪያ እንጂ ዘላቂ እውነት አይደለም። እነሆ ጆሮዬን የደፈነው ሸክላ፡ ባቦካው ጣት ይበሳል። ብርሃን እንደባረኩት ሁሉ ጨለማንም ባረኩት፣ ቃላትን እንዳወደስኩኝ ሁሉ ጸጥታን አወደስኩት። ቃላትም ትርጉም የሚኖራቸው ዝም ያለ አድማጭ ጆሮና ዝም ያለ ልብ ሲገኝ ብቻ መሆኑን ተገነዘብኹ።

ኦሜጋ! ፍጥረታት በሙሉ የሚፈልጉትን ነገር ለማግኘት በዝምታ ይታገሳሉ። ነብር አደኑን ለመያዝ በጸጥታ ያደባል። የሰው ልጅም እንዲሁ ውስጣዊውን ግዙፍ ኃይል ለማጥመድ ማድባት አለበት። በድካም የተገኘ ዝምታ ነፃ ያወጣል። ውስጥን አጥርቶ የመወሰን ጥንካሬንም ይሰጣል። አዎ ይሄ ውስጣዊ ጉዞ እርግጥም ከባድ ነው። ኤቨረስት ተራራን ከመውጣት የበለጠ ይፈትናል። ብዙ ሰዎች አንድን ተራራ ወጥተው ሲጨርሱ ተራራውን አሸነፍነው ይላሉ፤ ተራራው ግን ከነግዙፍ ግርማ ሞገሱ ቆሞ በትዝብት ሲያያቸው አስተዋልኩት። ጉዞ ወደ ውስጥ ሲሆን ግን አሸናፊም ተሸናፊም ተጓዡ ነው። እናም በውሸት የገነባኸውን፡ በወሬ ብልጭልጭ ያሸበረቅከውን የእኔኮ ማንነት ግንብህን በአርምሞ ስታፈርስ እውነተኛው ቤተ-መቅደስህን ታገኘዋለኽ። ገንቢህንም ታደንቃለህ።

ሔት! ከዘረጉ ሳያጥፉ፣ ከቆሙ ሳይቀመጡ፣ በአርምሞ የጸለዩ ደጋጎች እያሉ ይሄ ሁሉ መገለጥ ለምን ለእኔ ተገባኝ? ብዬም ጠየኩኝ። ሰጪው የማይከራከሩት ደግ ስለሆነ እንጂ ተቀባዩስ አይገባኝም ነበር። እሱ ግን ምህረቱ ለዘላለም ነው። ፍቅሩንም ሳይ ከስስታምነት እግረ-ሙቅ

ተላቀቅኹኝ። የቃላት አመስኳዬ ቆመ፤ እንደ ጦጣ ከወዲያ ወዲህ እየዘለሉ የተመሰቃቀሉ ሐሳቦቼ ተስተካከሉ። ያ አምባዬ አበረታኝ።

በእንዲህ ያለ የመገለጠ ጉዞዬ ላይ ሳለሁም ቬራ ወደ ህይወቴ መጣች። የፍቅር እቅፏ ውስጥ ሆኜ እፎይ አልኹኝ፤ ያነጻትን እጅም አመሰገንኹት። እነሆም የኔ ፍቃድ ይሁን የሱ እቅድ ይሄን የሸለመኝ ብዬ ስጠይቅ አንድ መልስም መጣልኝ። የሰው በጎ ፍቃድና የፈጣሪን ቅድመ-ውሳኔ መረዳት ከባድ እውቀት እንደሆነም ተነገረኝ። የአምላክ ጥበብ ግን በሁሉም ዘመን ላይ መብራራት የሚችል ጊዜ ተሻጋሪ ነውና በዘመናችን ባለው የ‹ጌም› ጨዋታ ተምሳሌትነትም ጥበቡ ተብራራልኝ። የጌሙ ዲዛይነር፣ ሥርዓትና ደንብ፣ የጌሙን ገጸ ባህሪያት ሁሉ ቀድሞ አርቅቋል። ጌሙን የሚጫወተው ግን የሰው ልጅ ነው። የመጫወቻ መቆጣጠሪያ ‹ጆይ ስቲክ› ጥሩ አድርጎ የተጫወተ ጥሩ ውጤት አግኝቶ ወደ ከፍተኛ ደረጃዎች ይሻገራል። ጨዋታው ከብዶት፣ አቅቶት የደከመ ሰነፍ ደግሞ ከመጀመሪያውም እርከን ሳያልፍ ይቀራል። ዋናው ጉዳይ ደግሞ የትኛውም ተጫዋች፣ በጣም በጥሩም ይሁን በጣም በደካማነት ጌሙን የሚጫወተው ጌሙን ዲዛይን ያደረገው ሰው የሰውዬውን መጨረሻ ያውቃል። እንዲሁ ሁሉ ፈጣሪም የሰው ልጅ በየትኛውም የህይወቱ አቅጣጫ ቢሄድ መዳረሻው ምን እንደሚሆን ያውቃል። ያም ብቻ ሳይሆን ሰውዬው ያልመረጣቸውንም አማራጮች ወስዶ ቢሆን ኖሮ የጨወታው ማብቂያ ምን ሊሆን እንደሚችል ያውቃል። ለዚህም ነው ፈጣሪ የሆነውን ያልሆነውንም ያውቃል የሚባለው።

*ታዲያ በሰው ሠራሽ ‹ጌም› ጨዋታ ተጫዋቹ ቢሸነፍና ቢሞትም ሞቱ ግን የእውነት ሞት አይደለም። በገሃዱ ዓለም የህይወት ፈተናውን የወደቀ ሰው ግን የሥጋም የነፍስም ሞት ሊሞት ይችላል። ነገር ግን እኔ ሞትን አልፈራም። እኛኮ በፈጣሪ ጣቶች ተዘራን፣ በምድር ታግዘን በቀልን፣ መኸር ሲደርስ ደግሞ እንታጨዳለን።*

የመሬት ስበት ትንሽም ትልቅም እቃን እኩል ስባ ታወርዳለች። እንዲሁ ትልቅም ይባል ትንሽ ሰው ወደ ምድር ሆድ ከመግባት አይቀርም።

እኔ የምፈራው የቁም ሞትን ነው። ቆመው እየሄዱ ሥጋ፣ አንጎል፣ ልቦናና ነፍስ የሚጣሉበትን አሟሟት ነው የምፈራው። ምክንያቱም በምድር ሥንኖር ፈጣሪ ፈተናዎችን በፀጋዎች ውስጥ አሽጎ ስለሚያቀርብልን ከተዘናጋን እንስታለን። እናም በሰጠን ነገሮች ሁሉ ይጠይቀናል። በጤናችን፣ በእውቀታችን፣ በቤተሰብ፣ በልጅ፣ በሚስት፣ በእናት፣ በባል፣ በአባት፣ በሐብታችን፣ በማዕረግና ዝናችን በሙሉ እንጠየቃለን።

እነዚህ ጸጋዎች ስጦታ መሆናቸውን ረስተን በእነርሱ ስንመካ ደግሞ የሰጠንን አምላክ እናሳዝናለን። እኔም በእናቴ ኤልሳ፣ በፍቅረኛዬ ቬራ፣ በእህቴ ማርታ ልፈተን እንደምችል አልጠፋኝም። እናም በእነሱ አልተማመንኩም።

*እኛ ሰዎች ሌላው ቀርቶ በልፋታች፣ በመልካም ሥራችን በጥበባችን ብሎም በዘረጋነው ሥርዓታችን መመካትና መተማመን የለብንም። ይህም ለነፍስ መልካም ነፃነትን ይሰጣታል። ምክንያቱም ነፍስ የሀገረ ገዢ አምባሳደር ነው። መልካም ሥጋ ነፍስን እንደ ክቡር እንግዳ ተቀብሎ ያስተናግዳል። ለቅዱሱ መንገስ ቤተ መቅደሱ ይሆናል፡ ክቡር እንግዳውም የተሰጠውን የቆይታ ጊዜ ሲጨርስ ይሄዳል። እናም ሥጋ አስተናጋጅ፣ ነፍስ ደግሞ ሀገረ-ገዢ ነው።*

*ሁሉም ሰው የራሱ ጂንና መልዓክ አለው። በነገሮች አልመካም፣ በሁኔታዎች አልተነነብይም። ሁኔታዎቹን በአንክሮ እፈጽማለሁ፣ መመካቴ ግን በአንድዬ ነው። ምህረትህ የዘላለም ህይወት ትሁነኝ እያልኹ ማልጄ እማለደዋለሁ።*

ዳሌጥ! ታዲያ ምድር ይሄ እውነታ ሲሸረሸር ትንቀጠቀጣለች፤ ሰማይ እንደ ወረቀት መጠቅለል ይዳዳል። አምልኮ ለአምላክ እንጂ ለፍጥረት መሆን የለበትም። ብርና ዝናን መሰል ጣዖቶች ሲመለክ ምድር ትሳቀቃለች። የማይሆነው ሲሆን ትርዳለች፣ ትንቀጠቀጣለች። እነሆ እኔ መርዕድ ይሄን ሁሉ አየሁ፤ አንዳችም የኔ አይደለምና ምንም ማጣት አልፈራሁም።

*ኤል! ረቂቁ ፈጣሪ ከክብሩ የማይመጥን ስም ሲሰጠው ሰማይ ትናጣለች። ምላሶች የዝምታን ጥልቅ ጥበብ በአልባሌ ነገር ሲያራክሱ የሀዋ አውታራት ይናጋሉ። የፍጥረትን ንጽህና የሚያቆሽሹ ቃላት ግብራቸው ክፉ ነው።*

እነሆም ይህ እንዲሆን ሲገባው አየሁ :- አህዛብ ኃይማኖትን መጠቃቀሚያ አደረጉ፣ ከጽኑ አለታቸውም ስለራቁ ተነቀሉ። ሌሎች ያልተጠሩ ደካማዎችም ከክብሩ ከአለቱ ላይ ተተከሉ፣ ወደ እልፍኙም ዘለቁ።

አሜን! እነዚህ ደካማ ነን ያሉ ቅዱሳን ማለት ልክ ማዕዛው የማይጠፋ ሽቶ እንደጠገቡ አልባሳት ናቸው። የተከተላቸውን፣ የለበሳቸውን በጥሩ ሽታ ያሳምራሉ።

*ራሀ! ቃላቶቼ ውድ ናቸው፤ በየቦታው አይበተኑም። ከአንደበቴ የሚወጡት እንደ መብረቅ ያርዳሉ። እናም በቁጥር መወሰን አለባቸው። የራሳቸው መገለጫ ጊዜ አላቸው፤ ካለጊዜው የሚሆን ነገር ስህተት ነው። ለጫጩትነት ያልደረሰን እንቁላል ሰብሮ ማውጣት ከመለስተኛ ውርጃ አይመሳሰልም ወይ? ስል ጠየቅሁኝ፤*

ሜም! የአርምሞ ነገር ደግሞ ሐሳብን ከመቆጣጠርም በላይ ይዘላል። ልብኽም ይምታ፣ ኩላሊትኽም ያጣራ፣ አእምሮኽም ያስብ ... አንተ ግን በአርምሞ መዘውተር ትችላለህ አለኝ። አላስፈላጊ እንቅስቃሴዎችን ቀንስ። አንድ ሃባ ዝምታና ቁንጽል እርጋታ እንኳን ኃይል አለው። እናም አርምሞ ሌሎችን ይታገሳል፤ አይታበይም፣ አይፀፀትምም።

ጻዴ! ከየትኛውም መጥፎ ብለን ከፈረጅነው ሰው ጀርባ አንድ ጥሩ ነገር ስላለ እሱን እንኮትኩት። ሁሉም ሰው የራሱ ጂንና መልዓክ አለው። ተፈጥሮ ሙሉ ለሙሉ ጥሩ ወይም ሙሉ ለሙሉ መጥፎ የሚባል ሰው እንደሌለ ታውቃለች። ከሁሉም ፍጥረት ጀርባ የፈጠረው ንጹህ ኃይል እንዳለ ጠንቅቃ ስለምታስተውል ለማንም አታዳላም።

እነሆ ጠየቀኝ አየር ዘር ይመርጣለው ወይ? ውኃ ይሄ ነገድ አይጠጣኝ ብሎ አሻፈረኝ ይላል ወይ? መሬትስ ይሄ ጎሣ አይርገጠኝ ብላ ትሰረጉዳለችን? ፍሬ የዘራባትን ሰው ብሔር መርጣ እህል ታበቅላለች ወይ? ፀሐይ የቆዳ ቀለም ለይታ ብርሃን ሙቀቷን ትከለክላለች ወይ?... ተፈጥሮኮ ልዩነትን አታውቃትም።

እኔም ብዙዎችን በዚህ የአንድነት ጥላ ሥር ሰብስቤ በጥሞና የምመራ ኃይል ሆንኩኝ። የእኛ ስብስብ በትንሣኤ ይነቃል፤ የኔ ትውልዶች በሰላምና ህብር ጥበባዊ ወጀብ፣ የጥላቻና ደም የመፋሰስን መንፈስ በማዕበል እንመታዋለን። መሬትን በፍቅር ጎርፍ እንድትርድ እናደርጋታለን።

አዱ! ይህንም የመገዳዳል፣ መጣላት፣ መጎሳቆል እሳት የአርምሞ ውኃ ቻለስኩበት። የአርምሞ ውኃ ግን ከሁሉም በፊት የአእምሮ ግለ ንጽህናን ይጠብቅ ዘንድ ይገለጣል።

**እነሆ! ሰባት ሽማግሌዎች ግዙፍ ጥበብን ሽክፈው፡ አንድ መደብን ከበው ቆመው አየሁ። የፈጣሪ ቶፋዎች[142] መስለውም ታዩኝ - እነሆም አንድ ጥቅስን አነበቡልኝ፤** */ዳዊትም እንዲህ ሲል ዘምሯልና፤*

142 የሌላን ሰው ሥራ ወክሎ የሚሠራ፤ ተወካይ፤

"1፤ አቤቱ፥ አድነኝ፤ ደግ ሰው አልቆአልና፥ ከሰው ልጆችም መተማመን ጐድሎአልና።

2፤ እርስ በርሳቸው ከንቱ ነገርን ይናገራሉ፤ በሽንገላ ከንፈር ሁለት ልብ ሆነው ይናገራሉ።

3፤ የሽንገላን ከንፈሮች ሁሉ እግዚአብሔር ያጠፋቸዋል፥ ታላቅ ነገርን የምትናገረውን ምላስ፤

4፤ ምላሳችንን እናበረታለን፤ ከንፈራችን የእኛ ነው፥ ጌታችን ማን ነው? የሚሉትን።

5፤ ስለ ድሆች መከራ፥ ስለ ችግረኞች ጩኸት እግዚአብሔር። አሁን እነሣለሁ ይላል፤ መድኃኒትን አደርጋለሁ፥ በላዩም እገልጣለሁ።

6፤ በምድር ላይ እንደ ተፈተነ ሰባት ጊዜ እንደ ተጣራ ብር። የእግዚአብሔር ቃላት የነጹ ቃላት ናቸው።

7፤ አቤቱ፥ አንተ ጠብቀን፥ ከዚህችም ትውልድ ለዘላለም ታደገን።" ምዕራፍ 12

*የጥሞና ጥበብ ዘር፣ ቀለም፣ ኃይማኖት ሳይመርጥ ነፍሶችን ያሳድጋል። አንተ ዝም ስትል የፈጠረኽ ባንተ በኩል ያወራል። ‹ቁደስ› - መንግሥተ ሰማይ ቃሎቻቸውን ለሚቆጣጠሩት ነው።*

*እነሆ! ይሄ ጥበብ ከዛፎች ጋር ለዘላለም ይበቅላል፣ ከአበቦች ጋርም ይፈካል.... ከምድር ጋር ይጸናል። ተራሮች እስከቆሙ ድረስ ቃሉና ዝምታው አይወድቁም። ፀሐይ እስከተንበለበለች ድረስ አብርሆት እየለኮሰ ያበራል። ወንዞች እስከፈሰሱ ድረስ በጥበብ ዥረት ይፈሳል። በስውር አክናፋት በአየሩ ውስጥ ይነፍሳል፤ ወደ አነፍናፊ ነፍሶች ውስጥም ይሰርጻልል።*

**...ይሄ አርምሞ!**

*ነፍስን በማስተዋል ያነቃል፣ ምናብን በጥበብ ያመጥቃል።*

*ፍቅር፣ ሰላምና እምነትን ከድቅድቁ ጸፈጸፍ ውስጥ ይወልዳል፤*

*ክብርና ምስጋና አስጀምሮ ላስጨረሰን ይሁን፤*

**←----- ይኸው ነው----→**

# ዋቢ መጽሐፍት


- መጽሐፍ ቅዱስ
- ቅዱስ ቁርዓን
- የአማርኛ መዝገበ ቃላት ከሣቴ ብርሃን
- መጽሐፈ መነኮሳት
- አንድሮሜዳ
- ብሂለ አበው
- ባህረ ሐሳብ
- ጥንታዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ተክለጻዲቅ መኩሪያ
- መጽሐፈ አብርሄት
- አረጋዊ መንፈሳዊ
- የሀዲስ ኪታባት
- ኢቶዮጵ
- ድርሳነ ዑራኤል
- Holy Vedas
- Upanshads
- Zen Mind
- The Miracle Of Mindfulness
- Stillness Speaks
- The Power of Now
- The Book of Amun Ra
- Words of Amun Ra
- Words of The Desert Fathers
- The Ghost of Akhenaten
- Wonderful Ethiopians of Ancient Kushitic Empire
- Anthropology of a Yogi
- The Alchemist
- The Book of Silence
- How to Meditate Poma chodi



## ዶ/ር ኤልያስ ገብሩ አዕምሮ

እንደ ሩስያዊው ደራሲ አንቷን ቼኾቭ በሙያው ኃኪም ነው። ሆኖም ለስነ-ጽሑፍ ባለው ፍቅር ጊዜውን አጣቦ እየጻፈ ሦስት መጽሐፍትን በእንግሊዝኛ እና በአማርኛ ከዚህ ቀደም አስነብቦናል። አሁን ደግሞ በዚህ አስገራሚ ልበ-ወለድ መጥቷል።

"...ዝምታ ጸጥ ማለት ብቻ አይደለም።"

"...ትልቁ ፍልሚያ ከራስ ጋር ነው።"

"...ራስን ለማግኘት፣ ለጥሞና ግዜ፣ ቀጠሮ መስጠት አያሻም።"

"...አርምሞ ይኖራል እንጂ አይሰበክም።"


"...ብቸኝነት ከባድ ጥንካሬ የሚጠይቅ የብልሆች ትምህርት ቤት ነው።"

"...አንዳንዴ መነጋገር ካላግባባን ዝምታ ያግባባናል።"

"...ተመስጦ የእኔኮ ትዕቢታዊ ትናጋን አክስሞ ወደ ሰፊው ዕርከን ያሻግራል!"

"...ያማረው ውስጣዊ የዝምታ ቸረት ዜማ አለው። ይኼ በውጫዊ ጩኸት የማይደፈርስ ዜማ...ነው።"

"...ውስጣቸው የተረበሹ ሰዎች ህዝብና ሀገርን ይረብሻሉ።





$10


የሽፋን ገጽ ቅንብር 0913450005

0966060708

አንድ መቶ ሰማንያ አምስት ብር

አብርሆት

0946-474647